

እውነተኛ አምልኮ የሚጀምረው የሚያመልኩትን በትክክል ከማወቅ ነው

# የምናመልከው እግዚአብሔር ማን ነው?

## የእግዚአብሔር ባሕርያት

«እንወቅ፥ እናውቀውም ዘንድ እግዚአብሔርን እንከተል፥ እንደ ወገግታም ተዘጋጅቶ እናገኘዋለን»

ትንቢተ ሆሴዕ 6:3

ሀብታሙ ሩፍሰገድ

እውነተኛ አምልኮ የሚጀምረው የሚያመልኩትን በትክክል ከማወቅ ነው

# የምናመልከው እግዚአብሔር ማን ነው?

## የእግዚአብሔር ባህርያት

“እንወቅ፤ እናውቀውም ዘንድ እግዚአብሔርን እንከተል፤ እንደ ወገግታም ተዘጋጅቶ እናገኘዋለን፤”

***ትንቢተ ሆሴዕ*** ፮፡፫

**ሀብታሙ ፉልሰገድ**

የማይሸጥ

**የምናመልከው እግዚአብሔር® ማን ነው?**

- የእግዚአብሔር ባሕርያት -

Adobe® Acrobat® eBook Reader® format

**የቅጅ መብት© 2018 ዓ.ም በሀብታሙ ሉልሰገድ**

***መጽሐፉን በተመለከተ ለሚፈለግ ማንኛውም ተጨማሪ ማብራሪያ እና የአጠቃቀም ፈቃድ በሚቀጥለው ገጽ የሚገኙትን አድራሻዎች መጠቀም ይችላሉ።***

***ያለ የቅጂመብት© /ባለቤቱ ፈቃድ/ መጽሐፉን አሳትሞ ማሰራጨት እና መሸጥ ፈጽሞ የተከለከለ ነው።***

***የመጀመርያው መጽሐፌን ስጽፍ እንዳደረግኩት ዛሬም "…በነጻ የተቀበላችሁትንም በነጻ ስጡ" ተብሎ የተጻፈው ቃል ዘላለማዊና የማይለወጥ እውነት ስለሆነ በዚህም ስጦታ ደግሞ እግዚአብሔርን በማመን እና በማወቅ ወደሚገኝ አንድነት እንደ አካል ሁላችንም እናድግና ራስ ወደ ሆነው ወደ ክርስቶስ መገስገስ እንችል ዘንድ በማሰብ የተጻፈ ጽሁፍ ስለሆነ አሁንም በነጻ የተሰጠ ነው።***

***ማንኛውም ሰው ከመጽሐፉ አንዳች ያልተገባ ጥቅምን ለማግኘት ለሽያጭ ለማቅረብ በህትመት መልክ ከማባዛት እና ከማሰራጨት በስተቀር በማንኛውም መልኩ ወይም በማንኛውም መንገድ መልዕክቱ ለብዙዎች ይደርስ ዘንድ እንዲያጋራ ተፈቅዷል።***

***ሁላችን በአዕምሮ ታድሰን እና ይበልጥ በፍቅር ተያይዘን ጌታችን ኢየሱስ ለራሱ ሊያቀርባት የሚፈልጋትን እድፈት ወይም የፊት መጨማደድ ወይም እንዲህ ያለ ነገር የሌለባት ያለ ነውር የሆነች ቅድስት ክብርት ቤተ ክርስቲያን ትገለጥና ሙሽራዋን እንዲወስዳት ትጠራ ዘንድ በውስጤ ባለው ጸጋ የድርሻዬን ለመወጣት የጻፍኩት በነጻም ለአካሉ ግንባታ የሰጠሁት ነው። ስለሆነም ማንም ሰው የጽሁፉን መርህ በጠበቀ መንገድ ለሚወደው ሰው በኤሌክትሮኒክ፣ ሜካኒካል፣ ፎቶ ኮፒ፣ ቅጅ፣ ወይም ሌላ ማንኛውም መንገድ ማጋራት እንዲችል የተፈቀደ ነው።***

***ከዚህም በተጨማሪ በተለያየ መንገድ ለህትመት በሚበቁ ስራዎች ውስጥ ህጋዊ የሆነ የአጻጻፍ መርህን ተከትሎ ጽሁፉን በማጣቀሻነት መጠቀም የተፈቀደ ነው።***

- ፀሃፊውን እንዲሁም የፀሃፊውን ልዩ ልዩ አገልግሎቶች ለማግኘት የሚከተሉትን የማህበራዊ ሚዲያ አማራጮች መከተል ይችላሉ።
- በሁሉም የማህበራዊ ሚዲያ አማራጮች የሚከተለውን አጭር ልዩ የተጠቃሚ መለያ ስም (**Username**) መፈለጊያቸው ላይ በማስገባት በቀላሉ ያገኙናል።

# @Intruthlife

***በእውነት መንገድ ሕይወት አገልግሎትን በሚከተሉት መንገዶች ይከታተሉ!***

| | |
|---|---|
| YouTube | https://youtube.com/@Intruthlife |
| TikTok | https://tiktok.com/@Life_In_truth |
| Facebook | https://facebook.com/Intruthlife |
| Instagram | https://instagram.com/Intruth.life |
| X | https://x.com/Intruthlife |
| Telegram | https://t.me/Intruthlife |
| WhatsApp Channel | https://whatsapp.com/channel/0029VbD5nrG1NCrcJCGr1L22 |
| Personal WhatsApp | https://wa.me/25190707157858 |
| Email | mailto:intruthlife@gmail.com |

# በፀሀፊው ከዚህ በፊት የተጻፉ መጽሐፍት




## እንደገና በሕይወት መኖር

## /ሪቫይቫል ለኢትዮጵያ/

### የተለቀቀው፡ መስከረም 27 2018 ዓ.ም

- መጽሐፉን በነጻ ለማግኘት ከታች የሚታየውን ማስፈንጠሪያ በመጫን ወይም ከላይ የሚገኘውን ፈጣን ምላሽ/ልዩ መለያ ኮድ በመቃኘት በቀላሉ ማግኘት ይችላሉ።

https://t.me/1ntruthlife/5

# ሥጦታ

ሁላችን የእግዚአብሔርን ልጅ በማመንና በማወቅ ወደሚገኝ አንድነት፥ ሙሉ ሰውም ወደ መሆን፥ የክርስቶስም ሙላቱ ወደሚሆን ወደ ሙላቱ ልክ እስክንደርስ ድረስ፥ ቅዱሳን አገልግሎትን ለመሥራትና ለክርስቶስ አካል ሕንጻ ፍጹማን እንሆን ዘንድ፤ እንደ ስሕተት ሽንገላ ባለ ተንኮል በሰዎችም ማታለል ምክንያት በትምህርት ነፋስ ሁሉ እየተፍገመገምን ወዲያና ወዲህም እየተንሳፈፍን ሕፃናት መሆን ወደ ፊት ስለማይገባን፥ እውነትን በፍቅር እየያዝን በነገር ሁሉ ወደ እርሱ ራስ ወደሚሆን ወደ ክርስቶስ እናድግ ዘንድ፤ በዚህም አሕዛብ ደግሞ በአእምሮአቸው ከንቱነት እንደሚመላለሱ ከእንግዲህ ወዲህ እግዚአብሔርን ባለማወቅ በእውቀትም ማጣት በከንቱ እንዳንመላለስ፤ እነርሱ ባለማወቃቸውና በልባቸውም ደንዳንነት ጠንቅ ልቡናቸው እንደጨለመ፥ ከእግዚአብሔርም ሕይወት እንደራቁ፤ ደንዝዘውም በመመኘት ርኵሰትን ሁሉ ለማድረግ ራሳቸውን ወደ ሴሰኝነት አሳልፈው እንደሰጡ እኛ ክርስቶስን እንደዚህ ያልተማርን ስለሆነ፤ እውነትም በኢየሱስ እንዳለ በእርሱ ተምረናልና፤ የሚጠፋውን አሮጌውን ሰው አስወግደን፤በአእምሮአችንም መንፈስ ታድሰን፥ ለእውነት በሚሆኑ ጽድቅና ቅድስና እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠረውን አዲሱን ሰው ለብሰን እድፈት ወይም የፊት መጨማደድ ወይም እንዲህ ያለ ነገር ሳይሆንባት ቅድስትና ያለ ነውር የሆነች ክብርት ቤተ ክርስቲያንን ለሙሽራው ለማዘጋጀት በማለም **ተቋማዊ ላልሆነችው በክርስቶስ ደም ተዋጅታ በእርሱ ለተመሰረተችው በምድር ላይ ለምትገኝ ብቸኛዋና እውነተኛዋ የክርስቶስ ቤተ-ክርስቲያን** ለአካሉ ግንባታ ይሆን ዘንድ

# በነፃ የተሰጠ

# ምስጋና

**"ሁሉ በእርሱ ሆነ፥ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም።"**

**ዮሐንስ ወንጌል 1:3**

"በዘላለሙ አምላክ ትእዛዝ ሕዝቦች ሁሉ አምነው እንዲታዘዙ፣ በነብያት መጻሕፍት አሁን በተገለጠው፣ ከጥንት ጀምሮ ዘመናት ተሰውሮ በነበረው ምስጢር መገለጥ መሠረት፣ በአስተማርሁት ወንጌልና በኢየሱስ ክርስቶስ መሰበክ ሊያጸናችሁ ለሚችለው፣ እርሱ ብቻ ጥበበኛ ለሆነ አምላክ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ለዘላለም ክብር ይሁን፤ አሜን።"

ሮሜ 16:25-27

/አዲሱ መ.ት/

"<u>እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆንህ አንተን</u> የላክኸውንም ኢየሱስ ክርስቶስን <u>ያውቁ ዘንድ</u> ይህች የዘላለም ሕይወት ናት።"

ዮሐንስ ወንጌል 17:3

# ፧፧ ማውጫ


**በፀሀፊው ከዚህ በፊት የተጻፉ መጽሐፍት ........ i**

**ሥጦታ ........ ii**

**ምሥጋና ........ iii**

**ቀዳሚ ቃል ........ vii**

**የአንባቢያን አስተያየት ........ vii**

**መቅድም ........ x**

**መግቢያ ........ xiii**

**ይህ መጽሐፍ እንዴት ቢነበብ የተሻለ ነው? ........ xvi**

**ምዕራፍ አንድ ........ ፩**

**እግዚአብሔርን ማወቅ ........ ፩**

1.1. እግዚአብሔርን ማወቅ የአምልኮ መጀመሪያ ነው፡፡ . . . . . . . . 2

1.2. እግዚአብሔር ይታወቅ ዘንድ ራሱን ገልጧል፡፡ . . . . . . . . 9

1.3. እግዚአብሔርን አለማወቅ ዋጋ ያስከፍላል፡፡ . . . . . . . . 13

1.4. እግዚአብሔርን እንዴት እንወቅ? . . . . . . . . 18

**ምዕራፍ ሁለት ..................................................................................................24**

**የምናመልከው እግዚአብሔር ማን ነው? .................................................24**

መግቢያ ............................... 25

2.1. እግዚአብሔር ሕያው ነው! ............................... 28

2.2. እግዚአብሔር የምንም ነገር ጥገኛ አይደለም! ................. 36

2.3. እግዚአብሔር ሉዓላዊ ነው! ............................. 45

2.4. እግዚአብሔር ትልቅ ነው! .............................. 53

2.5. እግዚአብሔር ኃያል ነው! ................................ 61

2.6. እግዚአብሔር መንፈስ ነው! ............................. 70

2.7. እግዚአብሔር በሁሉም ስፍራ ይገኛል! ...................... 80

2.8. እግዚአብሔር ሁሉን አዋቂ ነው! ........................... 89

2.9. እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው! ........................... 96

2.10. እግዚአብሔር ቅዱስ ነው! ............................. 105

2.11. እግዚአብሔር ጻድቅ ነው! ............................ 116

2.12. እግዚአብሔር ታማኝ ነው! ............................ 126

2.13. እግዚአብሔር እውነት /እውነተኛ/ ነው! ................... 132

2.14. እግዚአብሔር ጠቢብ ነው! ............................ 138

2.15. እግዚአብሔር ትጉና ታታሪ ሰራተኛ ነው! ................... 147

2.16. እግዚአብሔር ብርሃን ነው! ........................... 153

2.17. እግዚአብሔር ሕይወት ነው! ........................... 159

2.18. እግዚአብሔር መኖሪያ ነው! .......................... 164

2.19. እግዚአብሔር ተስፋ ነው! .............................169

2.20. እግዚአብሔር ባለጠጋ አምላክ ነው። .....................173

2.21. እግዚአብሔር ቸር ነው! ............................. 180

2.22. እግዚአብሔር መልካም ነው! ..........................186

2.23. እግዚአብሔር ፍቅር ነው! ............................193

2.24. እግዚአብሔር መሐሪ ነው! ........................... 200

2.25. እግዚአብሔር ታጋሽ ነው! ........................... 207

2.26. እግዚአብሔር ቀናተኛ አምላክ ነው! .................... 214

2.27. እግዚአብሔር ተበቃይና መዓትን የተሞላ የሚቆጣም አምላክ ነው!.. 227

2.28. እግዚአብሔር አባት ነው! ........................... 237

2.29. እግዚአብሔር ወዳጅ ነው! ........................... 245

2.30. እግዚአብሔር የማይለወጥና ዘላለማዊ ነው! .................251

2.31. እግዚአብሔር አምላክ ነው ከእርሱም ሌላ የለም! ............. 255

ማጠቃለያ ..................................... 265

**ዋቢ መጻሕፍት.................................................275**

# ቀዳሚ ቃል

ወንድሜን ሐብታሙ ሉልሰገድን የተዋወቅሁት "ፓሩሲያ - የኢየሱስ መምጣትና የዓለም መጨረሻ ምልክት (የእግዚአብሔር መንግሥት ገጽታ)" የምትለዋን መጽሐፌን ካነበበ በኋላ እርሱም "እንደገና በሕይወት መኖር (ሪቫይቫል ለኢትዮጵያ)" የሚለውን የመጀመሪያ መጽሐፉ የሆነውን ላከልኝ፤ ከዚያ ብዙ ንግግሮችን ካደረግን በኋላ ይህ ወንድም በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ትልቅ ሥራ እንዲሠራ በእግዚአብሔር የተመረጠ መሆኑን ለማመን የማንም ማረጋገጫ አላስፈለገኝም።

በመድሐኒታችንና በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የድነት ሥራ ከዘላለም ሞት ወደ ዘላለም ሕይወት የመጡ ሁሉ የሚያመልኩትን አምላክ እግዚአብሔርን እንዲያውቁ በተለያዩ ቅዱሳን በልዩ ልዩ ቋንቋዎች የተጻፉ መጻሕፍት እንዳሉ ይታወቃል፤ ሆኖም ለእኛ ለኢትዮጵያውያን የእግዚአብሔርን ልዩ ልዩ ባሕሪያትና አሠራሩን በማወቅ እግዚአብሔርን በመምሰል የምናድግበትን መንገድ ፍንትው አድርጎ የሚያሳየን ወንድማችን ሐብታሙ እንደጻፈው ያለ መጽሐፍ ግን አላየሁም።

ወንድማችን ሐብታሙ አምላካችን እግዚአብሔር በዚህች ውስን የሰው አዕምሮ በሙላት ሊታወቅ እንደማይችል ለመግለጥ በተሞከረ በዚህ ጽሑፉ ውስጥ ለዚህ ውስን የሰው ልጅ እግዚአብሔር በቅዱስ ቃሉና በቅዱስ መንፈሱ፣ እንደዚሁም በአንድያ ልጁ በኩል ራሱን ለመግለጥ የሄደበትን የመጨረሻ እውነት ለመተንተን ትልቅ ጥረት እንዳደረገ እናያለን፤

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም አገልግቱን ጨርሶ ወደ አባቱ ለመሄድ በተዘጋጀበት ጊዜ ለቅዱሳን ሁሉ በጸለየው ጸሎቱ መጀመሪያ ላይ "እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆንህ አንተን የላከኸውንም ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘላለም ሕይወት ናት" (ዮሐ. 17፡3) ብሏል።

ይሄ አምላካችን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ "ከመሥዋዕት ይልቅ ምሕረትን፥ ከሚቃጠልም መሥዋዕት ይልቅ እግዚአብሔርን ማወቅ እወድዳለሁና" (ሆሴዕ 6፡6) ስላለ እግዚአብሔርን ለማወቅ የሚደረግ ጥረት አስፈላጊ ብቻ ሳይሆን አማራጭ የሌለው ምርጫ ይሆናል ማለት ነው።

አንድ ሰው እግዚአብሔርን ማወቅ ትልቅ የእግዚአብሔር ሥጦታ ነው አለ፤ እኔም ከዚህ ሰው አባባል ጋር እስማማለሁ! ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰዎች የሰውን ልጅ ማን እንደሆነ ይሉታል ብሎ ሲጠይቅ ከደቀ መዛሙርቱ የተለያየ መልስ እንደ ተሰጠው እናውቃለን፤ ሐዋሪያው ጴጥሮስ ግን "አንተ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ፤" ብሎ ሲመልስለት "የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፥ በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም ይህንን አልገለጸልህምና ብፁዕ ነህ፤" አለው (ማቴ. 16፡13-17)፤ ይህ የሚያሳየን እርሱን ለሚፈልጉት እግዚአብሔርን ማወቅ መገለጥ እንደሆነ ነው፤ በዚሁ መሠረት እግዚአብሔርን ለማወቅ ፈልጎ እርሱን እየተከተለ እግዚአብሔር ራሱን የማይገልጥለት ማንም እንደማይኖር በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በጥሩ ሁኔታ ተቀምጧል።

እኔም ይህንን መጽሐፍ በማነበበት ጊዜ ብዙ የታነጽኩባቸው ሁኔታዎች እንደነበሩ ሳልደብቅ ወደፊትም ደጋግሜ እንደማነበ ከራሴ ጋር ቃል ኪዳን ገብቼአለሁ። እንግዲህ እግዚአብሔርን ለማወቅ ባለ መነሻ ሃሳብ ይህንን መጽሐፍ የሚያነቡ ሁሉ እግዚአብሔርን ወደ መምሰል እንደሚያድጉና ወደፊትም ጌታ ቤተ ክርስቲያንን በሚያድስበት ጊዜ የሥራው ተባባሪዎች እንደሚሆኑ ጥርጥር የለኝም።

<u>*ኤልያስ ኪቲላ (መጋቢ)*</u>

የፓሩሲያ - የኢየሱስ መምጣትና የዓለም መጨረሻ ምልክት (የእግዚአብሔር መንግሥት ገጽታ) መጽሐፍ ፀሃፊ

ቀድሞ በሰሜን ሙሉ ወንጌል አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን (አዲስ አበባ) አገልጋይ የነበረና ዛሬ ላይ ከዚህ ሃላፊነቱ በክብር ያረፈ

አሁን ደግሞ በኦታዋ (ካናዳ) በኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን እያገለገለ የሚገኝ የተወደደ አባት

# የአንባቢያን አስተያየት

## አስተያየት #1

በአጭር ቃል ይህን መጽሐፍ ግለጠው ብባል፤ *"ወደ እውነተኛው አምልኮ እና ጥልቅ ኅብረት የሚያሸጋግር ድልድይ!"*እለዋለሁ።

በዚህ ዘመን፣ በብዙ የህይወት ውጣ ውረድ ውስጥ ሆነን፣ "እግዚአብሔር የት ነው? በእርግጥስ ይወደኛል? ለምን ዝም አለ?" የሚሉ ጥያቄዎች በልባችን ይመላለሱ ይሆናል። አንዳንዴም የምናመልከው አምላክ ማን እንደሆነ በውል ሳናውቅ፣ በልማድ እና በሐይማኖታዊ ስርዓት ብቻ ተጠምደን እናገኘዋለን። ነገር ግን "የምናመልከው እግዚአብሔር ማን ነው?" የተሰኘው ይህ ድንቅ መጽሐፍ፣ ከልማዳዊ አምልኮ አውጥቶን ከፈጣሪያችን ጋር ፊት ለፊት እንድንገናኝ የሚያደርግ መንፈሳዊ መስታወት ነው።

ይህንን መጽሐፍ ማንበብ፣ ስለ እግዚአብሔር መረጃ ማከማቸት ብቻ አይደለም፤ ይልቁንም የህይወት አቅጣጫን የሚቀይር ጉዞ ነው። ገጾቹን በገለጣችሁ ቁጥር፤ በማይለወጠው ፍቅሩ የሚያቅፋችሁን "አባት"፣ በጭንቀታችሁ ጊዜ የማይተዋችሁን ታማኝ "ወዳጅ"፣ እና ከችግራችሁ ሁሉ የሚበልጠውን "ሁሉን ቻይ" ሉዓላዊ አምላክ በቅርበት ታውቁታላችሁ። የእግዚአብሔርን ማንነት በትክክል ስታውቁ፣ ፍርሃታችሁ በድፍረት፣ ጭንቀታችሁ በሰላም፣ ልማዳዊ ጸሎታችሁም በእውነተኛ አምልኮ ይተካል።

ስለዚህ፣ ይህ መጽሐፍ ለብዙዎች በረከት እንደሚሆን አልጠራጠርም። እግዚአብሔር አገልግሎትህን፣ ጥበብህን እና ብዕርህን አብዝቶ ይባርክ!

***ወንድም ወሰኑ አማረ ወ/ሩፋኤል***

በጌታ የተወደደ ወንድም

# አስተያየት #2

በክርስቶስ የተወደዳችሁ አንባቢዎች፤

በወንድም ሀብታሙ ሉልሰገድ የተጻፈው “*የምናመልከው እግዚአብሔር ማን ነው? - የእግዚአብሔር ባህርያት*” መጽሐፍ፣ በአሁኑ ዘመን በቤተክርስቲያንና በአማኞች ዘንድ የሚታየውን የእውቀትና የማንነት ቀውስ ለመፍታት የሚጥር ድንቅ ስራ ነው። ጸሐፊው በአሁናዊቷ ቤተክርስቲያን ውስጥ ለሚታየው ሥርዓት አልባነትና የአምልኮ መልክ መበላሸት ዋነኛው መንስኤ “እግዚአብሔርን በትክክል አለመረዳት” መሆኑን በግልጽ ያሳያል። “እግዚአብሔርን ከማምለክ በፊት ማወቅ ይቀድማል” በሚለው መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርህ ላይ በመቆም፣ አማኙን ወደ እውነተኛ እውቀትና ንስሐ ይጠራል።

ይህ መጽሐፍ እግዚአብሔርን በባህርያቱ በኩል ጠጋ ብሎ ለማወቅ ለሚፈልግ ክርስቲያን እንደ መዝገበ-ሐይማኖት ሊያገለግል በሚችል መልኩ ፴ የእግዚአብሔርን ባህርያት በዝርዝርና በተደራጀ ሁኔታ አስቀምጧል። እግዚአብሔር ሕያው፣ የምንም ነገር ጥገኛ ያልሆነ፣ ሉዓላዊ እና ታላቅ መሆኑን በቅዱስ ቃሉ መነጽር በጥልቀት ይተነትናል። በተጨማሪም ጸሐፊው “በነጻ የተቀበላችሁትን በነጻ ስጡ” (ማቴ ፲፡፰) የሚለውን መለኮታዊ ፈቃድ በመከተል መጽሐፉን ለአካሉ ግንባታ በነጻ ማቅረቡ ለመጽሐፉ መልእክት ትልቅ መንፈሳዊ ታማኝነትን ይሰጠዋል።

ይህ መጽሐፍ በግል ንባብ ብቻ ሳይሆን፣ በአብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ለቡድን ውይይትና ለደቀ-መዝሙርነት ክፍሎች እንደ ማስተማሪያ ማኑዋል (Study Guide) ሆኖ ቢያገለግል፣ አማኞችን እግዚአብሔርን ወደማወቅ አንድነት ለማምጣት ትልቅ አቅም አለው። እያንዳንዱ አንባቢ ይህንን መጽሐፍ በጥልቀት እንዲያነበውና የተረዳውንም እውነት በሕይወት እየተለማመደ ለሌሎችም እንዲያጋራ በጌታ ፍቅር እያሳሰብኩ፣ መልካም የንባብና የበረከት ጊዜ እንዲሆንላችሁ እመኛለሁ።

እግዚአብሔር ቤተክርስቲያንን "እርሱን" በማወቅ ይባርክ!

***የሴፍ ቁምላቸው ደርበው***

በጌታ የተወደደ ወንድም

## አስተያየት #3

ይህን መፅሀፍ አማኞች በህይወታቸው ምልልስ ውስጥ ለነገሮች የሚኖራቸው እይታ መረዳትና ምላሽ ስለ እግዚአብሔር ባላቸው ትክክለኛ እውቀት ላይ የተመሠረተ እንዲሆን የሚያመልኩትና የሚከተሉት አልፎም የሚያገለግሉት አምላክ ማን እንደሆነ በመረዳት ትክክለኛ የአምልኮ ህይወት እንዲኖራቸውና በዙሪያቸው የሚሆኑትን ነገሮች ሁሉ በብርሀን መረዳት እንዲችሉ የሚረዳ በተመረጡ ቃላቶች በመፅሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት በተሠደሩ ሀሳቦች በተቀነበቡ ምዕራፎች የቀረበ በመካከል ቆም የሚያደርጉ ጥልቅ ማሰላሰልና ማብላላትን የሚሹ ጠንካራ ሀሳቦች የያዘ ከተለመደው የአንድ ጎን እይታ ወይም የአግድሞሽ መረዳት በተለየ የማይገናኙ የማይታረቁ የሚመስሉ የእግዚአብሔር ባህሪያትን ድንቅ በሆነ መሠናሠልና ውበት በአንድነት ያዘለ ከአሁን ያለፈ ለትውልድ የሚሆን የእግዚአብሔር የእጅ ስራ የሆነ በወንድማችን በኩል የተቀበልነው የእግዚአብሔርን ረዳትነትና የፀጋውን ባለጠግነት በግልፅ የሚያሳይ ድንቅ ስጦታ ነው።

***ፂዮን ኢደባባይ ካሴ***

በጌታ የተወደደች እህት

# መቅድም

ይህ መጽሐፍ እግዚአብሔር ረድቶኝ ከዚህ በፊት በጻፍኩት አሁናዊ የሆነውን የአገራችን፣ የቤተክርስቲያን እና የእያንዳንዳችንን መንፈሳዊ ቁመና በሚገመግም እና ለሁለንተናዊ ተሃድሶ የሚቀሰቅስ "እንደገና በሕይወት መኖር" የሚለው መጽሐፍ ውስጥ የዛሬዋን በአገራችን የምትገኝ የክርስቶስ ቤተክርስቲያን በምልከታ ግምገማ ባገኘሁት ውጤት ላይ ተመስርቶ እግዚአብሔር በውስጤ ባከበደው ጉዳይ እና በተሰጠኝ ጸጋ አካሉን ለማነጽ ብሎም ለተሃድሶ ጥሪው የራሴን ድርሻ ለማበርከት በማሰብ የተጻፈ አስተማሪ ጽሁፍ ነው።

በቀደመው መጽሐፍ አራተኛው ምዕራፍ ላይ አሁናዊ የቤተክርስቲያንን ቁመና በዳሰስኩበት ስፍራ የመጀመሪያ እንደ አካል የሚታየው ትልቅ ችግር የማንነት ቀውስ እንደሆነ ከተመለከትኩበት መነሻ ሃሳብ ተነስቶ የተጻፈ ነው። ይህ የማንነት ቀውስ በሁለት አቅጣጫ የሚታይ ጉዳይ ሲሆን እነዚህም የምናመልከውን እግዚአብሔርን በትክክል አለመረዳት እንዲሁም እኛ በክርስቶስ ማን እንደሆንን በቅጡ አለመረዳት ናቸው። ይህም የእውቀት ማጣት መንጋውን ለበላተኞችና ለሀሰተኞች ሰለባ አድርጎት የሚታይ ሲሆን በተጨማሪም ህዝቡ እግዚአብሔርን በእውነትና በመንፈስ ለማምለክ ሊኖረው የሚገባውን እርሱን በትክክል ከማወቅ የሚነሳ አክብሮትና ፍርሃት ያሳጣው ሆኖ የሚታይ ነው። በዚህም ምክንያት ለወንጌል እንቅፋት የሆነ የአምላካችንም ስም በአህዛብ የሚሰደብበትን ቅጥ ያጣ ስርዓት አልባ የሆነ ጉባኤና የአምልኮ መልክ በመካከላችን የገለጠ ሆኖ ይታያል።

ይህም ክፍተት ከዚህ በፊት በጻፍኩት መጽሐፍ በዝርዝር ለማስረዳት እንደሞከርኩት እውነተኛ የሆኑ አምላካቸውን በግል ያወቁ ክርስቶስንም በህይወት መግለጥ የቻሉ እግዚአብሔር ጸጋን የሰጣቸው አካሉን ለማነጽ ሸክም ያለባቸው የአብያተ ክርስቲያናትም ጉዳይ የሚያሳስባቸው ለማስተማርም የበቁ እውነተኛ የጸጋ ባለቤቶችን ወደ ፊት እንዲመጡና ይህንን የእውቀት ክፍተት በመሙላት እግዚአብሔርንም በማመንና በማወቅ ወደሚገኝ አንድነት በማደግ የሚፈታ ነው። ዛሬ

ላይ በተለያዩ ቤተ እምነቶች ውስጥ የተንሰራፋው በተለያዩ ጊዜያት እየተጨማመረ ስር የሰደደው በእግዚአብሔር እውቀት ላይ ከፍ ያለ የሰው ሃሳብ እየፈረሰ አዕምሮ ሁሉ ህይወት በሚገኝበት ትምህርት እየታደሰ ለክርስቶስ ለመታዘዝ ይማረክ ዘንድ ያስፈልገዋል።

ይህም አሮጌውን የማፍረስና አዲሱን የመገንባት ስራ ሁላችን በጋራ ተባብረን በፊታችን ያለውን የድርሻችንን እየሰራን በኅብረት የምናመጣው እንጂ ጥቂት ስማቸው የገነነ ግለሰቦች ብቻቸውን በየቦታው እየዞሩ ሰርተው የሚጨርሱት ስራ አይደለም። እውቀት ማጣቱ በመካከላችን የገለጠው መለያየት የክርስቶስን እውነት በመካከላችን ያለመሸቃቀጥ በመግለጥ በአንድነት ሊተካ እና እግዚአብሔር በመካከላችን ሊገልጣት የሚወዳት የገሃነም ደጆች የማይችሏት ብዙዎችን ወደ እግዚአብሔር መንግስት የምትጠራ እግዚአብሔር በታላቅ ክንዱ አብሯት የሚታይላት ቤተ ክርስቲያንን መግለጥ ያስፈልገናል።

በመጨረሻም ይህ ዘመን እምነታችን በብዙ መልኩ እየተፈተነ የሚገኝበት ከጌታችን ምጽአት ደጅ ላይ የሚገኝ በርካታ የዲያብሎስ ሽንገላና ማታለያ በተለያየ መልኩ እረፍት በማይሰጥ ሁኔታ ያለማቋረጥ ወደ ሁላችን የሚረጭበት ተናጋሪ እና ድምጽ የበዛበት ክፉ የሆነ የዘመን እንጥፍጣፊ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ እንደሚነግረን ቀኖቹ ወደፊት ገና ከዚህም የከፉ እንደሚሆኑ እናውቃለን። ታዲያ በእንደዚህ አይነት ሁኔታ የምንገኝ እኛ በእምነታችን ጸንተን የተዘጋጀልንን ታላቅ ርስት ለመውረስ እንችል ዘንድ በአለም ከሚገኘው ብዙ አታላይ የበላተኛ ድምጽ እየራቅን እንደ በግ እረኛችንን በትክክል በማወቅ ድምጹንም በመስማት ኮቴውን መከተል በእጅጉ ያስፈልገናል።

ይህም ማለት በተለያየ መልኩ በማህበራዊ ሚዲያ ከሚለቀቁ ቁርጥራጭ ያልተሟላ መልዕክት ያዘሉ መንፈሳዊ የሚመስሉ ማዘናጊያዎች እየተላቀቅን ሙሉ መልዕክት ያላቸውን ረጃጅም ተከታታይ ትምህርቶች ወደ መመልከት፣ በአካል በዙሪያችን በምትገኝ አጥቢያ ትክክለኛ ኅብረትን በማድረግ ቤተክርስቲያን ህዝቧን ለመመገብ ባዘጋጀቻቸው ልዩ ልዩ ፕሮግራሞች በመሳተፍ፣ ይህንን አይነት እና መሰል

የእግዚአብሔር መንፈስ ያለባቸው መጽሐፍትን በማንበብ ወዘተ ራሳችንን ወደ ክርስቶስ መልክ ማሳደግ ያስፈልገናል።

ከእነዚህም ከላይ ከዘረዘርኳቸው ነጥቦች ሁሉ በላይ ዋናው እና ትክክለኛው ወደ ክርስቶስ መልክ የማደጊያው መንገድ ደግሞ በሌላ በምንም ሊተካ የማይችለው እኛ በግል በውስጣችን ካለው አስተማሪ የሆነ የእርሱ መንፈስ እና ከህያው ቃሉ ጋር የሚኖረን ቆይታ ነው። ይህንን መጽሐፍ ጨምሮ ከላይ የተጠቀሱት ሁሉ ልዩ ልዩ አገልግሎቶች የዚሁ አንድ ሰው በግሉ እግዚአብሔርን በማወቅና በመምሰል የሚያደርገው የእድገት ጉዞ ደጋፊዎች ብቻ ናቸው። በዚህም መረዳት እና መንፈስ አንዳች የሚጠቅም ነገር እንደምታገኙበት በማመን እና ራስን በመግዛት እንደ እግዚአብሔርም ቃል በመፈተሽ ይህንን መጽሐፍ እንድታነቡት እጋብዛችኋለሁ።

ለአካሉ መታነጽ እና ለጋራ ተሃድሶ ለቤተክርስቲያን በነጻ የተሰጠ የራሱ የጸጋው ባለቤት የእግዚአብሔር ገንዘብ የሆነ መጽሐፍ ስለሆነ በማስተዋል እንድታነቡት እንዲሁም በየትኛውም መንገድ ብዙዎች ያነቡትና ይታነጹበት እግዚአብሔርንም ወደ ማወቅ ይደርሱበት ዘንድ ለዘመድ ወዳጆቻችሁ ሁሉ እንድታጋሩት በዚህም የእግዚአብሔርን መንግስት ስራ እንድታግዙ በጌታ ፍቅር አሳስባችኋለሁ።

መልካም የንባብ ጊዜ እንዲሆንላችሁ እንዲሁም በንባባችሁ ውስጥ እግዚአብሔር ይህች ትንሽ መጽሐፍ በድንግዝግዝ እውቀት እርሱን ልትገልጥ ከሞከረችው በላይ ራሱን እንዲገልጥላችሁ በተጠቀማችሁበትም መጠቀም ሌሎችን መጥቀም የምትችሉበትን ጸጋ እንዲያበዛላችሁ በተረዳችሁበትም መረዳት በሕይወት መኖር እንድትችሉ ጸጋን እንዲለቅላችሁ ጸሎቴ ነው።

**ይባርክ፣ እግዚአብሔር ይባርክ!**

**ሀብታሙ ሉልሰገድ**

# መግቢያ

በአለም ላይ ከ8.2 ቢሊዮን በላይ የሚሆን ህዝብ የሚገኝ ሲሆን (United Nations, 2024) ከዚህ አጠቃላይ ቁጥር ውስጥ ወደ 31.5 በመቶ አካባቢ ወይም ወደ 2.6 ሚሊዮን ገደማ የሚደርስ ቁጥር ያለው ህዝብ በምድር ሁሉ እጅግ በዝቶ እና ለቁጥር የሚያዳግት ሆኖ ቁጥሩ በውል ሳይታወቅ በአስር ሺዎች የሚገመት እንደሆነ ከሚታወቀው የአለም ሀይማኖት መካከል በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ተመስርቶ ክርስትና በሚባለው ቋት ውስጥ የሚገኝ ህዝብ ነው። (Christianity, 2019; Hackett, et al., 2025) ከዚሁ የክርስትና ቋት ውስጥ ታዲያ ምንም እንኳን በተመሳሳይ መልኩ ሁሉም እምነታቸው ከመጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነሳ የሚናገሩ ቢሆንም በእምነት አቋም እና አመለካከት ረገድ ፈጽመው የማይገናኙና በውስጡ የተከፋፈሉ ከ45,000 በላይ ቤተ እምነቶችን እንደ ባለ ብዙ ቅርንጫፍ ትልቅ ዛፍ በውስጡ አካቶ የያዘ ነው። (Christianity, 2019)

ምንም እንኳን እንደዚህ እጅግ ብዙ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ እምነታቸው የተመሰረተ እንደሆነ የሚያስቡ አምላካቸው ስሙ እግዚአብሔር የሆነ ቡድኖች ቢኖሩም “ላይፍ ዌይ” የሚባል የምርምር ማዕከል እንደሚናገረው ከእነዚህ የክርስቶስ ተከታይ የሆንን ክርስቲያኖች ነን የሚሉ ህዝቦች መካከል ከ10 በመቶ በታች የሚሆነው ቁጥር ብቻ እምነቴ ተመስርቶበታል የሚለውን የአምላኩ ማንነት የሚገኝበት ቅዱስ መጽሐፍ ከመጀመርያ እስከ መጨረሻ አንብቦ እንደሚያውቅ ይናገራሉ። (Research, 2026) ከዚሁ 10 በመቶ ውስጥ ደግሞ ምን ያክሉ በጥልቀት አምላካቸውን እንደሚገባ ለማወቅ ዕለት ዕለት ከዚህ መጽሐፍ ጋር እንደሚውሉ መገመት አይከብድም። (Society, 2025)

ከላይ እንደተገለጸው የሁሉም ቡድኖች አምላክ ስሙ እግዚአብሔር ይሁን እንጂ እያንዳንዱ ጋር ቀረብ ብላችሁ የአምላካቸውን ማንነት ለማወቅ ስትሞክሩ በእርግጥ የአንዱ ከአንዱ በብዙ መልኩ የተለያየ በባህርይውም ፈጽሞ የማይመሳሰል እንደሆነ በቀላሉ ትገነዘባላችሁ። ታዲያ ይህ ሁሉ የበዛ ልዩነት በመካከላቸው ይኑር እንጂ ከላይ

እንደተገለጸው እምነታችን ተመስርቶበታል የሚሉት ቅዱስ መጽሐፍ በስፋት የሚተርክለት እውነተኛ የሆነው ግን እርሱ አንድ ብቻ ነው፤ ከእርሱም በቀር ሌላ የለም።

በዚሁ የክርስትና ቋት ውስጥ የግላቸውን የእምነት አቋም በሌሎች ላይ ለመጫን አስተምህሯቸውን በተለያየ መንገድ ወደ ህዝቡ የሚያደርሱት ብሎም በዚሁ እንቅስቃሴ በትምህርት ነፋስ እየተወሰዱ በየቤተ እምነቱ የሚረግጡ በግላቸው አምላካቸውን በማወቅ ያላደጉ የዚህ እንቅስቃሴ ሰለባዎች ቀላል የሚባሉ አይደሉም። በዚህም ምክንያት የዚሁ ሰለባ የሆኑ ሰዎች በሚሰሙት ንግግር በመታለል ባልተቋረጠ እሽክርክሪት ከአንዱ ሐይማኖት ወደ ሌላኛው በየቀኑ ሲፈልሱ ይታያሉ። ይህም ያልተቋረጠ ፍልሰት በእርግጥ የሰሙት ስብከት እውነት እንደሆነ በማሰብ እውነተኛውን አምላክ እግዚአብሔርን ፍለጋ የሚወስኑት ውሳኔ ነው።

ይህም እንደ አንድ አማኝ በእርግጥ የምናመልከው እግዚአብሔር ማን ነው? የእኔ እግዚአብሔር እነዚህ ሁሉ በአለም ላይ የሚገኙ ሌሎች የእምነት ክፍሎች ከሚጠሩት እግዚአብሔር በምን ይለያል? እንደሚገባ በአክብሮትና በፍርሃት በእውነተኛም ፍቅር ከልብ በሆነ በእውነትና በመንፈስ የሆነ አምልኮ እርሱን ለማምለክ ስለ እርሱ ማወቅ የሚገባኝ ምንድን ነው? ወዘተ የሚሉትን ጥያቄዎች መመለስ በእጅጉ ያስፈልገናል።

እግዚአብሔር አምላካችን ራሱን የደበቀ እናውቀውም ዘንድ የማይወድ ድብብቆሽ የሚጫወት አምላክ አይደለም። ነገር ግን ከልብ ሲፈልጉት የሚገኝ፣ መታወቅንም የሚወድ ከእስትንፋሳችን ሁሉ ይልቅ ወደ እኛ ቀርቦ በፍጥረቱ ሁሉ ላይ ራሱን የገለጠ የእውቀት አምላክ ነው። በተቃራኒው እግዚአብሔር አለማወቅን በእጅጉ የሚጠላ የምናደርገውን ሁሉ በእውነት፣ በእውቀትም እንድናደርገው የሚፈልግ አምላክ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ በምሳሌ መጽሐፍ ምዕራፍ ፱፡፲ ላይ እንደሚናገረው የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ሲሆን እርሱን ቅዱሱንም ማወቅ ማስተዋል እንደሆነ ይነግረናል። ፍቅር ከእውቀት የሚመነጭ ነገር ሲሆን እግዚአብሔርን እንደሚገባ በፍጹም ልብ፣ በፍጹም ሃሳብ፣ በፍጹም ኃይልና በፍጹም ነፍስ ለመውደድ

የእርሱን ፍቅር፣ በጎነት፣ ምህረት፣ ርህራሄ፣ ትዕግስት ወዘተ ማወቅ በእጅጉ ጠቃሚ ነው።

ይሄው እምነታችን የተገኘበት ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል በ2ኛ ጴጥሮስ 1:4 ላይ እንደሚናገረው በእውነት በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ባለው እውነተኛ ብርሃን ይኸውም ከእግዚአብሔር አፍ የወጣ ህያው ቃል የሚያምን እና ከዚሁም የተወለደ አንድ አማኝ የመለኮት ባህርይ ተካፋይ ለመሆን እና አምላኩን እግዚአብሔርን ለመምሰል የተጠራ ነው። ይህንኑ የተጠራበትን ግብም ለመምታትና ትርጉም ያለው እውነተኛ ኅብረትን ከአምላኩ ጋር ለማድረግ እርሱንም ለመምሰል አምላኩንም ሊመለክ እንደሚገባው በእውነትና በመንፈስ ለማምለክ የሚያመልከው ይህ ዝነኛ ባለ ታላቅም ስም አምላክ እግዚአብሔር በእርግጥ ማን እንደሆነ ማወቅ የግዴታ ያስፈልገዋል።

ይህንንም በአማኙ ማህበረሰብ መካከል የሚታይ ትልቅ ክፍተት ለመሙላት እና ህዝቡን ከአምላኩ ጋር ለማስተዋወቅ ይህ "የምናመልከው እግዚአብሔር ማን ነው? የሚል መጽሐፍ በእጅጉ የሚረዳ እንደሚሆን አምናለሁ።

*ታዲያ በእርግጥ ይህ የምናመልከው እግዚአብሔር ማን ነው?*

Life TRUTH 14:6

# ይህ መጽሐፍ እንዴት ቢነበብ የተሻለ ነው?

ይህ መጽሐፍ የተጻፈው የሥነ መለኮት እውቀትን ለማስፋት ወይም የአእምሮን ጥማት ለማርካት ብቻ አይደለም። ዋና ዓላማው የምናመልከውን እግዚአብሔርን በእውነት እንድናውቀው፣ እንድንወደው፣ እንድናመልከው እና ከእርሱ ጋር በጥልቅ ኅብረት እንድንመላለስ ለመርዳት ነው።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ስለ እግዚአብሔር ማንነትና ባሕርይ የሚናገሩ ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች፣ ምሳሌዎች እና ማብራሪያዎችን ታገኛላችሁ። እነዚህ የቀረቡት መረጃን ለመስጠት ብቻ ሳይሆን፣ ወደ እግዚአብሔር ጥልቅ እውቀትና ከእርሱ ጋር ወዳለ እውነተኛ ኅብረት ለመጋበዝ በማለም ነው። ስለዚህ የዚህ መጽሐፍ ዓላማ ስለ እግዚአብሔር ብዙ ነገር ማወቅ ብቻ ሳይሆን፣ እርሱን ራሱን በቅርበት ማወቅ ነው።

ስለዚህ ይህንን መጽሐፍ በጸሎት መንፈስ እንድታነቡት አበረታታችኋለሁ። እያንዳንዱን ምዕራፍ ከመጀመራችሁ በፊት፣ ጌታ የውስጥ ልባችሁንና አእምሮአችሁን እንዲከፍትላችሁ ጸልዩ። የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር የሚገልጠው መንፈስ ቅዱስ በእውነት እንዲመራችሁ በእርሱ ታመኑ።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያሉትን እያንዳንዱን ክፍሎች በችኮላ ለማለፍ አትሞክሩ። እያንዳንዱ ክፍል ስለ እግዚአብሔር አንድ እውነት እንድናስተውል፣ እንድናሰላስል፣ እና በሕይወታችን እንድንተገብረው አቅዶ ተዘጋጅቷል። ስለዚህ ከእያንዳንዱ ክፍል በኋላ የቀረቡትን የማስተንተኛ ጥያቄዎች (Reflection Questions) ማሰላሰያ (Meditation)፣ ጸሎት (Prayer) እና የአርምሞ ጥቅስ (Memory Verse) በጥንቃቄ ተጠቀሙባቸው።

የማስተንተኛ ጥያቄዎቹ ከምንባቦቹ የተማራችሁትን እውነት በግል ሕይወታችሁ እንድትመለከቱ እና በጥልቀት እንድታስቡ ያግዟችኋል። የማሰላሰያው

ክፍል ደግሞ ያነበባችሁትን እውነት በልባችሁ እንድትይዙ እና የእግዚአብሔር ባሕርይ ከግል ሕይወታችሁ ጋር ምን ግንኙነት እንዳለው እንድታስቡ ይረዳችኋል። የጸሎት ክፍሉም የተማራችሁትን እውነት በግል ሕይወታችሁ ተግባራዊ ለማድረግ እርዳታን ፍለጋ ወደ እግዚአብሔር እንድትቀርቡ ይጋብዛችኋል። የአርምሞ ጥቅሱ ባነበባችሁት በዚያ ክፍል ዙሪያ ጥቂት ጊዜን እንድትወስዱና በእርግጥ የእግዚአብሔር ቃል በነገሩ ላይ ያለውን ሃሳብ በልባችሁ እንድትይዙ ብሎም ቃሉ ከእናንተ ጋር እንዲቆይ ይረዳችኋል።

ነገር ግን ይህ ማለት በየክፍሉ መጨረሻ በተጻፉት የማስተንተኛ ጥያቄዎች፣ ማሰላሰያ ጽሁፍ፣ ጸሎት፣ እና የአርምሞ ጥቅስ ብቻ የተገደባችሁ ናችሁ ማለት አይደለም። በክፍሉ መጨረሻ እነዚሁ ቆም ብሎ የማሰቢያና የማሰላሰያ ጽሁፎች የገቡት ይልቁንስ በእነርሱ አነሳሽነት ወደሚበልጥ እውነተኛ መንፈሳዊ ንክኪ እንድትገቡ ለማድረግ ነው። ስለዚህ በጸሃፊው የተጻፉትን ብቻ ልማዳዊ በሆነ መንገድ አነብንቦ ብቻ ማለፍ ሳይሆን ነገር ግን በእውነትና በመንፈስ በሆነ ንክኪ ሕያው ከሆነው መንፈስ ጋር ኅብረት ለማድረግ ጊዜ እንድትወስዱ ይጠበቃል።

በመጽሐፉ ውስጥ የተጠቀሱትን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ስታነቡ በመጽሐፉ ከተጠቀሱበት መንገድ ባለፈ እግዚአብሔር በዚያ ቃል ውስጥ ያለውን ጥልቅ ሃሳብ ለመረዳት እንድትችሉ በአውዳቸው እንድታነቧቸው እመክራችኋለሁ። የእግዚአብሔር ቃል ራሱ እንዲናገራችሁ ፍቀዱ። ያነበባችሁትን አሰላስሉ፤ ስለ እግዚአብሔር ማንነት፣ ፈቃድ፣ መንገድ እና ከሕይወታችሁ ጋር ስላለው ተግባራዊ ኑሮ አስቡ።

ይህንን መጽሐፍ በፍጥነት ለመጨረስ አትሞክሩ። አንዳንድ ምዕራፎች ደጋግሞ ማንበብን፣ በጥልቀት ማሰላሰልን እና በጸሎት መመርመርን ሊፈልጉ ይችላሉ። መንፈሳዊ እድገት የሚመጣው በማንበብ ብቻ ሳይሆን፣ በማሰላሰል፣ በመታዘዝ፣ እና ከእግዚአብሔር ጋር በሚደረግ እውነተኛ ኅብረት ነው።

በመጨረሻም፣ አንድ ጸሐፊ እግዚአብሔርን ሙሉ በሙሉ ሊገልጠው እንደማይችል አስታውሱ። ይህ መጽሐፍ ቃሉን በታማኝነት ለማቅረብ በትጋት የተዘጋጀ ቢሆንም፣ ከሁሉ የላቀው አስተማሪ የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር በሙላት

የሚመረምረውና የሚያውቀው ራሱ እግዚአብሔር የሆነው መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው። ስለዚህ በምታነቡበት ጊዜ በእርሱ ታመኑ።

በምንባባችሁ ወቅት እግዚአብሔር ቃሉን እንዲያበራላችሁ፣ ፍቅሩን በልባችሁ ትኩስ እንዲያደርግ፣ እምነታችሁን እንዲያበረታና ስለ እርሱ ያላችሁን እውቀት እንዲያሳድግ ጸሎቴ ነው።

የመጨረሻ ምኞቴ ይህ መጽሐፍ የምታነቡት መጽሐፍ ብቻ ሳይሆን፣ እግዚአብሔርን በማወቅ፣ በመውደድና በማምለክ ለማደግ እንዲረዳችሁ ብሎም ለቃሉና ለቃሉ ባለቤት ለእግዚአብሔር ጥልቅ የሆነ ፍቅር ይኖራችሁ ዘንድ ምክንያት እንዲሆንላችሁ ነው።

*ይህ መጽሐፍ በተከፈተ መጽሐፍ ቅዱስ፣ በትሑት ልብ፣ እና*
*በቃሉና በመንፈሱ ራሱን ለእኛ ለገለጠው እግዚአብሔር*
*እውነተኛ በሆነ የማወቅ ጉጉት ቢነበብ የበለጠ ፍሬያማ*
*ያደርጋል።*

**እግዚአብሔር ቢተክርስቲያኑ "እርሱን" በማወቅ ይባርክ!**

# ምዕራፍ

# 1

# አንድ

# እግዚአብሔርን

# ማወቅ

Life
TRUTH 14:6

## 1.1. እግዚአብሔርን ማወቅ የአምልኮ መጀመሪያ ነው።

እግዚአብሔር በትንሹ የሰው አዕምሮ ታውቆ የሚጨረስ እና የሚደረስበት በዚህም እግዚአብሔር በቃ እንደዚህ ነው ተብሎ መደምደሚያ የሚሰጥበት ማንነት ያለው አምላክ አይደለም። ከዚሁ በተቃራኒው ደግሞ እርሱ ራሱ ማንነቱን ለህዝቡ ብሎም ሊያውቀው ለወደደ የትኛውም ግለሰብ ራሱን የሚገልጥ መታወቅን የሚወድ አምላክ ነው። በተለያየ ጊዜ በዘመናት መካከል ከእግዚአብሔር ጋር አንዳች ግንኙነት የሚጀምሩ ሰዎች ሁሉ የመጀመሪያ እርምጃቸው ከእግዚአብሔር ጋር መተዋወቅ ነው።

> "በተለያየ ጊዜ በዘመናት መካከል ከእግዚአብሔር ጋር አንዳች ግንኙነት የሚጀምሩ ሰዎች ሁሉ የመጀመሪያ እርምጃቸው ከእግዚአብሔር ጋር መተዋወቅ ነው።"

አብርሃም ከከለዳውያን ዑር ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ በተለያየ ወቅት በእያንዳንዷ እርምጃው የጠራውን እግዚአብሔርን በማወቅ ያድግ ነበር። በዚህም ግንኙነት እግዚአብሔር ራሱን የጠራሁህ እግዚአብሔር እኔ ነኝ፣ እኔ ኤልሻዳይ ነኝ ወዘተ በሚሉ ቃላት እና ለአብርሃም አዕምሮ በሚከብዱ አደረራጎቹ ራሱን ለአብርሃም በየጊዜው ይገልጥለት ነበር። ይህም አብርሃም እግዚአብሔርን የበለጠ እንዲያውቅ የእግዚአብሔር ወዳጅ እንዲሆን በዚህም እምነቱ እንዲጨምር እግዚአብሔርን እንደሚገባው እንዲፈራው እና እንዲያከብረው እንዳደረገው በሰዶም እና ገሞራ ፍርድ ወቅት ከእግዚአብሔር ጋር ባደረገው የቃላት ምልልስ በግልጽ ይታያል።

በተመሳሳይ መልኩ ለዚህ እግዚአብሔርን በማወቅ ለማደግ አይነተኛ ምሳሌ የሚሆነን የሙሴ ህይወት ነው። ምንም እንኳን ከዮሴፍ ንግስና ጋር ተያይዞ ያዕቆብ ከነቤተሰቡ ወደ ግብጽ ገብቶ በጌሴም መኖር ከጀመረ በኋላ የእነ ሙሴ ትውልድ እስከመጣበት ጊዜ ድረስ ባለው ወቅት እስራኤላውያን ከአምላካቸው ጋር ስለነበራቸው ግንኙነት በቂ እውቀት የሌለን ቢሆንም አባቶቻቸው የሚያመልኩት ከአህዛብ አማልክት የተለየ አምላክ እንዳላቸው ይህም አምላክ ለአባቶቻቸው ተስፋን እንደሰጠ ሰምተው

እንዳደጉ ከሙሴ አስተዳደግ እንዲሁም ካደገ በኋላ በወሰናቸው ውሳኔዎች ውስጥ መመልከት ይቻላል።

ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ይህን በባርነት ቀንበር ውስጥ ያለ አምላኩን በቅጡ የማያውቅ ህዝብ ለአባቶቹ እና ለዘራቸው ሊሰጣት ወደ ማለላቸው ምድር ከመውሰዱ በፊት እርሱ ራሱ ማን እንደሆነ በተወሰነ መልኩ ማስተዋወቅ ነበረበት። ይህም ትውውቅ የጀመረው መሪ እንዲሆን በተመረጠው በሙሴ ነበር። ምንም እንኳን ሙሴ ስለ እግዚአብሔር ሰምቶ ያደገ ዕብራዊ ቢሆንም በምድያም የአማቱን የዮቶርን በጎች እየጠበቀ ሳለ የተመለከተው ያልተለመደ ነገር ቀልቡን ስቦት ሲጠጋ ከቁጥቋጠው ውስጥ የወጣው የመጀመሪያ የእግዚአብሔር ድምጽ ራሱ እግዚአብሔር ቅዱስ እንደሆነ እና እርሱ የተገኘበት ስፍራም የተቀደሰ መሆኑን በመግለጽ ለዚህ ቅድስናው የሚገባ አክብሮትን ሙሴ እንዲያሳይ ጫማውን እንዲያወልቅ በማዘዝ ራሱን ማስተዋወቅ ነበር።

በዚህ የሙሴ እና የእግዚአብሔር ንግግር ወቅት ታዲያ ስለ ቅድስናው እና ወደ እርሱ ስለሚቀርብበት ሁኔታ መግለጫን ከሰጠ በኋላ መጀመሪያ ያደረገው ነገር እርሱ ማን እንደሆነ ማስተዋወቅ ነበር። ይህም ሙሴ በጭላንጭል የሚያውቀው የአባቶቹ የአብርሃም የይስሃቅ እና የያዕቆብ አምላክ መሆኑን ነው። በዚህ እና መሰል ንግግሮቹ በበቂ ሁኔታ እግዚአብሔርን እንዳላወቀ የተረዳው ሙሴ እንደገና ማን እንደሆነ ሲጠይቀው እና ወደ ተላከበት ህዝብ ሄዶ ማን ላከኝና ስሙስ ማን ነው ልበላቸው ብሎ ይጠይቃል።

ታዲያ ለዚህ ጥያቄ እግዚአብሔር የመለሰው መልስ እግዚአብሔር ታውቆ ሊያልቅ የሚችል እንደዚህ ነው ተብሎ አንድ ምሳሌ የማይሰጥበት ከመታወቅም የሚያልፍ ትልቅ አምላክ እንደሆነ የሚገልጽ ነበር። ይህም *"ያለና የሚኖር እኔ ነኝ አለው"* የሚል ነው። የዚህ ጥቅስ የእንግሊዝኛው ፍች *"I am who I am" / "እኔ እኔ ነኝ"* የሚል ይዘት ያለው ቃል ነው። ይህም እግዚአብሔር በምንም አይነት ቋንቋ ሊገለጽና የመጨረሻ የሚባል መግለጫ እና አገላለጽ ሊኖረው የማይችል እጅግ ድንቅ አምላክ እንደሆነ የሚገልጽ ነው።

የዚሁ ቃል የመጀመሪያው የዕብራይስጥ ይዘት *"የምሆነውን እሆናለሁ"* ፣ *"የሆንኩትን ነኝ"* ፣ *"እኔ እኔ ነኝ"* የሚል ፍች ያለው *የነበረ ያለና የሚኖር* የሚለውን የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ማንነት የሚገልጽ ቃል ነው። ይሄው እኔ እኔ ነኝ የሚለው ቃል

በዕብራውያን ዘንድ በእጅጉ የታወቀ እግዚአብሔር ራሱን የገለጠበት ቋንቋ በዮሐንስ ወንጌል 8፡5 ላይ *"እውነት እላችኋለሁ አብርሃም ከመወለዱ በፊት እኔ ነኝ አላቸው"* በሚለው የኢየሱስ ንግግር ውስጥ የሚታይ ነው። ይህም ንግግሩ እግዚአብሔር ራሱን ለህዝቡ ያስተዋወቀበት ንግግር ነበርና በወቅቱ በስፍራው የነበሩ አይሁድ ራሱን እግዚአብሔር አድርጓል ብለው ኢየሱስን ለመውገር ድንጋይ እንዲያነሱ ያደረጋቸው ነበር።

በዚህ እኔ እኔ ነኝ ፣ የምሆነውን እሆናለሁ ወዘተ በሚለው እግዚአብሔር ራሱን በገለጠበት ቃል ውስጥ እግዚአብሔር እርሱ ብቻውን የተለየ አምላክ እንደሆነ ብሎም ለህዝቡ የሚያስፈልገውን ሁሉ የሚሆን ምንም የማይጎድልበት አምላክ እንደሆነ በጥቂቱም ቢሆን የሚገልጽ በብዙ የታጨቀ የእግዚአብሔር ማንነትን ሁሉ በሚስጢር የያዘ ንግግር ነው። ይህም ማንነቱ ጌታችን ኢየሱስ በመጣበት ወቅት እርሱ ማን እንደሆነ ለመግለጽ በተለያየ ወቅት በተለይም በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ እኔ እያለ በተደጋጋሚ ለህዝቡ ስለ ማንነቱ ሲናገር የተተነተነ እውነት ነው።

በዚህም መሰረት እኔ የሕይወት እንጀራ ነኝ ፣ እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ ፣ እኔ የበጎች በር ነኝ ፣ እኔ መልካም እረኛ ነኝ ፣ እኔ ትንሳኤ እና ህይወት ነኝ ፣ እኔ መንገድ እውነት እና ህይወት ነኝ እንዲሁም እኔ እውነተኛ የወይን ግንድ ነኝ በሚሉ ሰባት ጥልቅ ንግግሮች ስለራሱ ተናግሯል። (Carson, 1991) ይህም በዘፀዓት ምዕራፍ 3 ላይ ራሱን ለሙሴ ካስተዋወቀበት እኔ ነኝ ከሚለው ንግግር ጋር ተመሳሳይ ሲሆን ሰባት እኔዎችን ጌታ ኢየሱስ መጠቀሙ በሰባት ቁጥር ውስጥ ካለው ምሉዕነት ጋር ተያይዞ እርሱ እነዚህን ብቻ ያልሆነና በተወሰነ መልኩ ራሱን የገለጠ ነገር ግን በሰዎች ቋንቋ እና አዕምሮ እንደዚህ ነው ተብሎ የማይገለጽ ከሰው እውቀት በላይ የሆነ አምላክ መሆኑን የሚያሳይ ነው።

ከላይ በተገለፀው የዘፀዓት ክፍል ላይ የአባቶቻቸው አምላክ እንደሆነ እና እርሱ እርሱ እንደሆነ ለሙሴ ከገለፀ በኋላ እስራኤልን ከግብጽ ለማውጣት እና በመንገዱ ሁሉ እግዚአብሔርን ብቻ የሚያመልክ ህዝብ በአህዛብ መካከል ለማውጣት ሙሴ ወደ ግብጽ ሄደ። ይሁን እንጂ ወንድሙን አሮንን ጨምሮ የእስራኤል ሽማግሌዎች እግዚአብሔርን ከስማ በለው ታሪክ ዘለው እርሱ ማን እንደሆነ በቅጡ ያወቁ አልነበሩም። ለዚህም የሙሴ ፍርሃት መልስ እንዲሆን በመካከላቸው የእግዚአብሔርን ማንነት ከንግግር ባለፈ

ለማስረዳት ይጠቅመው ዘንድ ኃይሉና ማንነቱ የሚገለጥበት በትርን ይዞ ነበር። አያምኑኝም ቃሌንም አይሰሙም ብሎ ለእግዚአብሔር ፍርሃቱን የገለፀው ሙሴ የተቀበላት በትር ድንቅና ተዓምራትን ማድረግ የምትችል እግዚአብሔር አብሮት እንደሆነ ለእርሱና በዙሪያው ላሉ ሁሉ የምታስረዳ ልዩ ምልክት ነበረች። እንደተባለውም በዚሁ መንገድ አሮን እና የእስራኤል ሽማግሌዎች በእርግጥ አንድ ከመታወቅ የሚያልፍ አምላክ ሙሴን እንደላከው በመረዳት ይለቃቸው ዘንድ የአምላካቸውን ቃል ለፈርዖን ለመናገር አብረውት እንዲገቡ አደረገ።

በርካታ አማልክትን የሚያመልከው የግብጽ ህዝብ እና በምድሪቱ ሁሉ የተበተኑ አህዛብ እግዚአብሔርን በስም እንኳን የሚያውቁት አልነበሩም። (Van De Mieroop, 2016) የእግዚአብሔርን ያመልከኝ ዘንድ ህዝቤን ልቀቅ የሚል መልዕክት ለመናገር ወደ ፈርዖን ለገቡት ሙሴ ፣ አሮን እና የእስራኤል ሽማግሌዎች ከፈርዖን በኩል የተመለሰው መልስ በቀላሉ ለማስረዳትና አጥጋቢ መልስ ለመስጠት እጅግ አስቸጋሪ ጥያቄ ነበር። ይኸውም *"ቃሉን እሰማ ዘንድ እስራኤልንስ እለቅቅ ዘንድ እግዚአብሔር ማን ነው? እግዚአብሔርን አላውቅም፣ እስራኤልንም ደግሞ አልለቅም"*የሚል ነበር።

ታዲያ ከዚህ በኋላ ለዚህ የፈርዖን የንቀት ንግግር እንዲሁም ለአጠቃላይ የግብጽ ህዝብና በዙሪያው ላሉት እስራኤል ሄዶ ይወርሰው ዘንድ ለአባቶቹ በተስፋ በተሰጠው ምድር ለሚኖሩ አህዛብ ሁሉ እርሱ እግዚአብሔር ማን እንደሆነ ያውቁ እና ይፈሩ ዘንድ የፈርኦኑን ጨምሮ የግብፃውያንን ሁሉ በኩር በሞት እስከሚቀጣ ድረስ በርካታ ድንቅንና ተዓምራትን በፀናች እጁ በመካከላቸው አደረገ። በተዓምራት እና በድንቅ የታጀቡት የእነ ሙሴ እና የፈርዖን ተደጋጋሚ ግንኙነቶች እግዚአብሔር ግብጻውያን እንደሚያመልኳቸው ጣዖቶቻቸው ግዑዝ እንዳልሆነና ይልቁንስ ከመታወቅ የሚያልፍ በአህዝብ መካከል እንዳሉት በርካታ አማልክት ያልሆነ ልዩና ብቸኛ ኃያል አምላክ እንደሆነ ገለጠ።

በዚህም መሰረት ከላይ ቃሉን እሰማ ዘንድ እግዚአብሔር ማን ነው ብሎ ላለው ፈርዖን ግልጽ የሆነ የእግዚአብሔር ታላቅነት ተገለጠ፣ ይህችስ የእግዚአብሔር ጣት ናት ያስባለ የመጀመሪያውን የእግዚአብሔር ትዕዛዝ ይኸውም ህዝቡን መልቀቅን ተገዶ ተግባራዊ እንዲያደርግ አደረገው። ይሄው በግብጽ የተደረገው ድንቅ እና ተዓምራት

ከግብፃውያን አልፎ በዙሪያ ባሉት አህዛብ ሁሉ የተሰማ የእግዚአብሔርን ታላቅነት ያስተዋወቀ እስራኤልን የተፈራ ህዝብ ያደረገ ነበር።

እግዚአብሔር በደነደነው የፈርዖን ልብ ምክንያት በግብጻውያን መካከል የገለጣት ያች የፀናች እጁ ለግብፃዊያን እና ለአህዛብ እርሱ ማን እንደሆነ ከማስተዋወቅ እና እስራኤልን ከባርነት ከማላቀቅ ያለፈ አላማ ነበራት። ይኸውም ያመልክ፣ ያጥን እና ያገለግለው ዘንድ የተጠራው የእስራኤል ህዝብ የሚያገለግለውን፣ የሚያጥንለትን እና የሚያመልከውን አምላኩን እግዚአብሔርን እንደሚገባ እንዲያውቅ ማድረግ ነበር።

ይህ ህዝብ በዙሪያው ካሉ ግብጻውያን እና አህዛብ ተለይቶ ከእግዚአብሔር ጋር ልዩ ለሆነ ኪዳናዊ ግንኙነት የተመረጠ ለእግዚአብሔር ርስት እና ህዝብ ለመሆን የተለየ ቅዱስ ህዝብ ሊሆን በዙሪያው ካሉ ህዝቦች በልዩነት የተመረጠ ነበርና እግዚአብሔርን ከሌላው ህዝብ አለፍ ባለ መልኩ በግሉ ማወቅ እና መረዳት ያስፈልገው ነበር። ይህም ከዚህ ወዲያ ከእግዚአብሔር ጋር በሚጓዙት ጉዞ የደስታ ፣ የሰላም ፣ የአቅርቦት ፣ የደህንነት ወዘተ ምንጫቸው እርሱ ብቻ እንደሆነ በማወቅ በማደግ በእግዚአብሔር ፊት የተገባ ምልልስን ለመመላለስ እጅግ በጣም የሚያስፈልጋቸው ነበር።

በዘፀዓት ምዕራፍ 10፡1-2 ባለው ክፍል እግዚአብሔር ለሙሴ የፈርዖንን ልብ ያደነደነው እንዲሁም በዚያች ምድር በግብፃውያን መካከል እጁን የገለጠው ድንቅና ተዓምራትንም ያደረገው በዋነኛነት ህዝቡ እግዚአብሔር እርሱ ማን እንደሆነ ያወቁ ዘንድ እና ይህንንም ማንነቱን ከእርሱ አልፎ ለልጆቹ እና ለልጆቹ ልጆች ይነግር ዘንድ እንደሆነ ያሳስበዋል። እግዚአብሔር በዚሁ የዘፀዓት መጽሐፍ ምዕራፍ 6፡2-3 ባለው ክፍል ለአባቶቻቸው ሁሉን እንደሚችል አምላክ ብቻ እንደተገለጠ እንጂ ስሙ እንዳልታወቀላቸው በመናገር እርሱ ስሙ እግዚአብሔር እንደሆነ አስተዋውቆ የተጀመረ የአብሮነት ጉዞ ነው።

እግዚአብሔርን ስምህ ማን ነው ብሎ በመተዋወቅ ህይወት የጀመረው ሙሴ እርሱን በማወቅ አድጎ ፍጹም በሆነ የእግዚአብሔር መገኘት ውስጥ ውሎ የሚያድር ከዚህ እጅግ የተፈራ አምላክ ጋር እንደ ባልንጀራ አፍ ለአፍ የሚነጋገር እንደ እርሱ ያለ ነቢይ የተባለለት የአምላኩን የልብ ሃሳብ ፈጽሞ በመረዳት ያደገ ሰው ወደ መሆን ደረሰ።

በተቃራኒው ከግብጽ ባርነት ነጻ ያወጣው እግዚአብሔር ማን እንደሆነ በውል ያልተረዳው በመካከሉ የተደረጉት እልፍ ድንቅ እና ተዓምራት አምላኩን እንዲያውቅ ያላደርጉት የእስራኤል ህዝብ ልቡ የደነደነ፣ ደጋግሞ አምላኩን እግዚአብሔርን የሚፈታተን፣ በአለማመን በሽታ የታመመ፣ በማጉረምረም የተሞላ፣ በመብልና በመጠጥ እግዚአብሔርን የሚጠረጥር ፣ ተስፋውን በእምነት ያልተቀበለ እና ትኩር ብሎ ያልተመለከተ፣ አምላኩን ከአህዛብ አማልክት ጋር ቁመት የሚያለካካ ወዘተ መሆኑ ወደ ተባለለት ምድር እንዳይደርስ ይልቁንስ በተለያየ ቸነፈር፣ ቁጣ፣ መቅሰፍት፣ የጠላት ኃይል ወዘተ እዛው ምድረ በዳ እንዲቀር አደረገው።

> “እግዚአብሔርን ስምህ ማን ነው ብሎ በመተዋወቅ ህይወት የጀመረው ሙሴ እርሱን በማወቅ አድጎ ፍጹም በሆነ የእግዚአብሔር መገኘት ውስጥ ውሎ የሚያድር ከዚህ እጅግ የተፈራ አምላክ ጋር እንደ ባልንጀራ አፍ ለአፍ የሚነጋገር እንደ እርሱ ያለ ነቢይ የተባለለት የአምላኩን የልብ ሃሳብ ፈጽሞ በመረዳት ያደገ ሰው ወደ መሆን ደረሰ።”

- ## የማስተንተኛ ጥያቄዎች

1. ይህ ምዕራፍ እግዚአብሔርን ስለማወቅ ምን አስተማረህ?
2. እግዚአብሔርን ማወቅና እውነተኛ አምልኮ ስላላቸው ዝምድና ምን ተረዳህ?
3. በዚህ ሳምንት እግዚአብሔርን ይበልጥ ለማወቅ ምን እርምጃ ልትወስድ አሰብክ?

- ## አሰላሰል

እግዚአብሔር ራሱን የሚገልጠው እንዲታወቅና በእውነት እንዲመለክ ነው። አብርሃምና ሙሴ እግዚአብሔርን እያወቁት በሄዱ መጠን እምነታቸው፣ መታዘዛቸውና ከእርሱ ጋር ያላቸው ግንኙነት እየጠነከረ ሄደ። እኛም እግዚአብሔርን በግል እያወቅነው በሄድን መጠን አምልኳችን ይበልጥ ጥልቅና እውነተኛ ይሆናል። ይህ ምዕራፍ በክርስቲያን ሕይወት ከሁሉ የሚበልጠው ግብ ስለ እግዚአብሔር መረጃ መሰብሰብ ሳይሆን፣ እርሱን ራሱን ማወቅ መሆኑን የሚያስታውስ ነው።

- ## ጸሎት

በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፣ በቃልህ ራስህን ለእኔ ገለጥልኝ። ስለ አንተ የማውቀውን እውቀት በየቀኑ አሳድግልኝ፣ እምነቴ፣ መታዘዜና አምልኮዬም እያደጉ እንዲሄዱ እርዳኝ።

በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አሜን።

- ## የአርምሞ ጥቅስ

*"እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆንህ አንተን የላክኸውንም ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘላለም ሕይወት ናት።"*

*– የዮሐንስ ወንጌል 17፥3 –*

## 1.2. እግዚአብሔር ይታወቅ ዘንድ ራሱን ገልጧል፡፡

*«ወደ እግዚአብሔር **ቅረቡ፥** እርሱም ወደ እናንተ **ይቀርባል።»***

— የያዕቆብ መልእክት 4፡8 —

*«ትእዛዜ በእርሱ ዘንድ ያለችው የሚጠብቃትም የሚወደኝ እርሱ ነው፤ የሚወደኝንም አባቴ ይወደዋል እኔም እወደዋለሁ **ራሴንም እገልጥለታለሁ።»***

— የዮሐንስ ወንጌል 14:21 —

እግዚአብሔር ሰዎች እርሱን ለማወቅ በወደዱበት መጠን ራሱን የሚገልጥ ድንቅ አምላክ ነው። ኢየሱስ ደረቱ ስር ለሚጠጋው ዮሐንስ እና አሳልፎ ለሰጠው የአስቆሮቱ ይሁዳ የተለያየ ነበር። ከእስራቷ ፈትቶ ነጻ ላወጣት መግደላዊት ማርያም ኢየሱስ እንኳን በህይወት እያለ በስጋ ወራቱ ይቅር እና ከሞተ እንኳን በኋላ አስከሬኑን ጭምር የሚያስፈልግ ግንኙነትን ያመጣ ትውውቅ ነበራት። እኛ እግዚአብሔርን ለማወቅ በወደድንበት መጠን እርሱ ደግሞ ራሱን ለእኛ ለመግለጥ የታመነ ነው፡፡

እግዚአብሔር በእጆቹ ስራዎች ማለትም በሰማይ፣ በምድር፣ ከምድር በታች ባለው በውስጣቸውም በሚገኙ ዙሪያችንን የሞሉ አውቀን የማንጨርሳቸው ፍጥረቱ በኩል እርሱ እግዚአብሔር ማን እንደሆነ ሊናገር የሚሞክር ሲሆን ይህንንም ምናልባት እየመረመሩ ያገኙት እንደሆነ እግዚአብሔርን ይፈልጉ ዘንድ ለሰው ልጆች ራሱን ለመግለጥ የፈጠራቸው ናቸው። ይሁን እንጂ ይህን ሁሉ ፍጥረት ጨምሮ ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር የሚናገሩ የሰማይም ጠፈር የእጁን ስራ ዕለት ዕለት የሚያወሩ ቢሆንም እነርሱን አይቶ እግዚአብሔርን ያውቅ ዘንድ ይህ ሁሉ ፍጥረት የተሰጠው የሰው ልጅ ዛሬም ባለማስተዋል እና እግዚአብሔርን ባለማወቅ ሲመላለስ አልፎም እግዚአብሔር የለም ሲል ይታያል።

> “እኛ እግዚአብሔርን ለማወቅ በወደድንበት መጠን እርሱ ደግሞ ራሱን ለእኛ ለመግለጥ የታመነ ነው፡፡”

ከዚህ ውጭ ሌሎች ደግሞ ጳውሎስ በጉዞው ደርሶ እንዳገኛቸው የአቴና ሰዎች የሚያመልኩትን ሳያውቁ በሐይማኖታዊ ምልልስ እና ስርዓት እየተመላለሱ የማያውቁትን አምላክ በማምለክ ተጠምደው ይታያሉ። ጳውሎስ ለእነዚሁ ሰዎች በዚሁ ስፍራ ይህንን ሳታወቁ የምታመልኩትን አምላክ ልንገራችሁ ብሎ በሐዋ 17፡22-23 ባለው ክፍል ሊመለክ የተገባውን የፍጥረታት ሁሉ ፈጣሪ እና ጌታ እግዚአብሔርን ሲያስተዋውቃቸው ይታያል።

መቼም እግዚአብሔር ከመታወቅ ያለፈ ድንቅ አምላክ እንደሆነ ግልጽ ነው። ለዚህም ነው በዘዳግም 29፡29 ላይ *"ምስጢሩ ለአምላካችን ለእግዚአብሔር ነው የተገለጠው ግን የዚህን ህግ ቃሎች ሁሉ እናደርግ ዘንድ ለእኛ ለዘላለምም ለልጆቻችን ነው"*የሚለው። እግዚአብሔር በዘመናት ሂደት ከትናንት ዛሬ ራሱን ለሰው ልጆች ይበልጥ እየገለጠ የሚገኝ ሲሆን የዕብራውያንም ፀሃፊ በመልዕክቱ መጀመሪያ ላይ እንደተናገረው ከጥንት ጀምሮ በብዙ አይነትና በብዙ ጎዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ሲናገር ኖሮ በዚህ ዘመን መጨረሻ ግን ያለውን የመጨረሻ እውነት ሁሉን ወራሽ ባደረገውና አለማትንም በፈጠረበት በልጁ ራሱን ለእኛ እንደገለጠ ይናገራል። ይህም በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ አንድ ላይ እንደተገለጸው እግዚአብሔርን አይቶት የሚያውቅ አንድም ሰው በሌለበት ሁኔታ ስለ ማንነቱ ሊተርክልንና አምላካችን ማን እንደሆነ የበለጠ ሊገልጥልን አልፎም በስጋ በመካከላችን ሊታይ ወዶ በአቅፉ ባለ የተወደደ ብቸኛ ልጁ በኢየሱስ በኩል እንደተተረከልን የሚያሳይ ነው።

ይህም ትረካ በኢየሱስ በኩል አብን እናይ ዘንድ የመለኮት ሙላት በእርሱ ተገልጦ የክብሩ መንፀባረቅና የባህርዩ ምሳሌ በሆነው ልጁ በኩል ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ሁኔታ ራሱን ለእኛ ገልጧል። ይህም ብቻ አይደለም ነገር ግን ከሰው ልጆች ጋር ባደረገው አዲስ ኪዳን ማንም ማንንም እግዚአብሔርን እወቅ ብሎ እንዳያስተምር ከታናሹ ጀምሮ እስከ ታላቁ ድረስ እርሱን ያውቁ ዘንድ ህጉን በልባቸው ውስጥ አኑሯል። ይህም ህግ ሙሴ እንደተቀበለው እና ለእስራኤላውያን እንዳነበበው ብቻ ሳይሆን በክርስቶስ በኩል የተፈፀመ ከመጀመሪያው ህጉ ሲሰጥ በህጉ ውስጥ ያለውን የእግዚአብሔር የልብ ሃሳብ ሁሉ በመግለጥ የተሟላ ሆኖ የተሰጠ የህይወት መንፈስ ህግ ነው።

በዚሁ አዲስ ኪዳን የህዝቡን ሀጢአት እና በደል ይቅር ብሎ ሰውነታቸውን በመቀደሱ ምክንያት በውስጣችን ማደር የጀመረው ከአብ ዘንድ ለሁላችን ሳይሰፈር በሙላት የተለቀቀው የልጁ መንፈስ ሁላችንን ወደ እውነት ሁሉ ይመራ እና ያስተምረን ዘንድ በውስጣችን መኖር ጀምሯል። የተሰጠን ይህ መንፈስ የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገርስ እንኳን ሳይቀር የሚመረምር ሲሆን አብ በኢየሱስ በኩል የገለጠልንን ብሎም በዚሁ በልጁ ውስጥ የሚገኘውን የተሰወረ የጥበብ እና የእውቀት መዝገብ እየገለጠ የሚያስተምር የእውነት መንፈስ ነው። በዚህም መሰረት ሰው ስለ እግዚአብሔር ከመስማት አልፎ እግዚአብሔርን በመንፈሱ አማካኝነት በልጁ በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል እርሱን ወደ ማወቅ እና መረዳት መድረስ እንዲችል ያስችለዋል።

ይህኛው እኛ የተገኘንበት የዘመን ጭላጭ የሆነ ጊዜ ሰው እግዚአብሔርን ያውቅ ዘንድ መንገድ ሁሉ የተመቻቸበት ዳንኤል በትንቢቱ 12:4 ላይ በመጨረሻው ዘመን እውቀት ይበዛል ብሎ እንደተናገረ እውቀት ሞልቶ የተረፈበት፣ መጽሐፍት በእጅ ስልኮቻችን በአይነት የገቡበት፣ ብርሃን የበራላቸው ሰዎች በየሚዲያው ስላወቁት ነገር የሚናገሩበት፣ ከሩቅ የሚታዩ የሰማይ ሰራዊቶች በተደረሰበት ቴክኖሎጅ ቀረብ ብለን እናያቸው ዘንድ እግዚአብሔር ጥበብን ለሰዎች በመስጠቱ ሰው ከምድር ለቅቆ ጨረቃን የረገጠበት፣ ስለ ከዋክብት እና ሌሎች የሰማይ ሰራዊት በርካታ የጥናትና የምርምር ውጤት በየጊዜው የሚለቀቅበት፣ እግዚአብሔር እናውቀው ዘንድ ከቀድሞ ይልቅ አብልጦ ወደ እኛ የቀረበበት እግዚአብሔርን ላለማወቅ ከልብ ጥንካሬ እና ለማወቅ አለመውደድ በስተቀር አንዳች ምክንያት የማይገኝበት ጊዜ ነው።

“የተሰጠን ይህ መንፈስ የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገርስ እንኳን ሳይቀር የሚመረምር ሲሆን አብ በኢየሱስ በኩል የገለጠልንን ብሎም በዚሁ በልጁ ውስጥ የሚገኘውን የተሰወረ የጥበብ እና የእውቀት መዝገብ እየገለጠ የሚያስተምር የእውነት መንፈስ ነው።”

- **የማስተንተኛ ጥያቄዎች**

1. እግዚአብሔር በሕይወቴ ራሱን በምን በምን መንገዶች ገልጦልኛል?
2. እርሱን በጥልቀት ከማወቅ የሚያደናቅፈኝ ነገር ምንድን ነው?
3. በዚህ ሳምንት ወደ እግዚአብሔር የበለጠ ለመቅረብ ምን ተግባራዊ እርምጃ ልውሰድ?

- **አሰላስል**

እግዚአብሔር እርሱን በቅን ልብ ለሚፈልጉት ራሱን አይሰውርም። በፍጥረት፣ በቃሉ፣ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ፣ እንዲሁም በመንፈስ ቅዱስ ራሱን ለእኛ ገልጧል። ነገር ግን የእርሱ መገለጥ እርሱን እንድናደንቅ ብቻ ሳይሆን ከእርሱ ጋር የቅርብ ኅብረት እንድኖረን ነው። ስለዚህ ጥያቄው እግዚአብሔር ራሱን ለመግለጥ ፈቃደኛ ነውን? የሚለው ሳይሆን፣ እኛ እርሱን በእውነት ለማወቅ እንፈልጋለንን? የሚለው ነው። በትሕትናና በታዛዥነት ወደ እርሱ በቀረብን መጠን፣ እርሱም ራሱን በሚያስደንቅ መንገድ ይበልጥ እየገለጠልን ይሄዳል። ይህንን እውነት በየቀኑ በሕይወታችን ልናስታውሰው ያስፈልገናል።

- **ጸሎት**

በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፣ ራስህን በልጅህ በኢየሱስ ክርስቶስና በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ስለገለጥህልን እናመሰግንሃለን። አንተን በቅንነት የሚፈልግ ልብ ስጠኝ። ከአንተ የሚያርቀኝን ነገር ሁሉ አስወግድ፤ በየቀኑም አንተን የበለጠ ለማወቅ ያለኝን ርሃብና ጥማት አሳድግ። ሕይወቴ በአንተ እውቀት እየጠለቀ እንዲሄድ ጸጋህን አብዛልኝ።
በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አሜን።

- **የእርምጃ ጥቅስ**

*"ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ፥ እርሱም ወደ እናንተ ይቀርባል።"*

*— የያዕቆብ መልእክት 4፥8 —*

## 1.3. እግዚአብሔርን አለማወቅ ዋጋ ያስከፍላል::

እግዚአብሔርን ማወቅ አማራጭ አይደለም ይልቁንስ ግዴታ ነው እንጂ። እግዚአብሔር ገና በፍጥረት መጀመሪያ ሁሉን ከሰራ በኋላ የእጁን ስራ ውጤት ሁሉ ዳግም ከቃኘ በኋላ መልካም እንደሆነ ይናገር ነበር። ከዚህ በኋላ ታዲያ እግዚአብሔር ፍጥረት ሁሉ በየወገኑ በተፈጠረበት መንገድ ይሄድ ዘንድ መስመርን ሰርቶለት በዚያ በአገባብ እንዲመላለስ አዝዞት የመኖር ነጻነትን ሰጠው። በዚያኑ ጊዜ ከፍጥረት መካከል ሰው የሚባለው በእግዚአብሔር ምሳሌ የተሰራው ፍጡር እያወቀ እግዚአብሔር ካሰመረለት መስመር ውጭ በመንቀሳቀሱ ለራሱ ከንቱ ማስተዋል ለማይረባም አዕምሮ እንዲሁም ለተገዛለት የጨለማ አለም ባርያና ተገዥ ይሆን ዘንድ ታልፎ ተሰጠ። የዚህ ሰው መተላለፍ ከራሱ አልፎ በአጠቃላይ ምድርን ጨምሮ ፍጥረታትን በሙሉ ለከንቱነት እና ለርግማን ታልፈው የተሰጡ አደረገ።

ከዚህ የውድቀት ጊዜ ጀምሮ የሰው ልጅ እንዲሁም ሌላው ፍጡር ሁሉ በመዋለድ ምድርን እየሞላ የሚገኝ ሲሆን በዚህ ሁሉ ውስጥ ፈጣሪው እግዚአብሔር ከመጀመሪያው ለፈጠረው ፍጡር ያሰመረውና ይመላለስበት ዘንድ የሰጠው የህይወት መርህ ግን አልተቀየረም። ዛሬም ሰው በህይወት ይኖር ዘንድ እግዚአብሔርን መፈለግ፣ ከሕይወት ዛፍ መብላት፣ በገዛ ማስተዋሉ መደገፍን ማቆም ወዘተ የግድ ያስፈልገዋል። እግዚአብሔር ማንነቱ በዘመናት መካከል የማይለወጥ የነበረ፣ ያለና የሚኖር ህያው አምላክ ነው። በየትኛውም የሰው ልጆች ዘመን ውስጥ ባሉ ልዩ ልዩ ባህልና ስልጣኔዎች ወዘተ ውስጥ በሚለዋወጠው የሰው አኗኗር መካከል የእግዚአብሔር መርህ አይለወጥም።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ሰው ከመጀመሪያ ያበላሸውንና ያጣውን እግዚአብሔር ያዘጋጀለትን ከእርሱ ጋር የመኖር ታላቅ እድል ፈጣሪው እግዚአብሔር ሰውን ከወደደበት ከታላቅ ፍቅሩ የተነሳ በምህረቱ ባለጠጋ ስለሆነ ብቻ በራሱ ስራ እንዲሁ በፀጋ ይድን ዘንድ ዕዳውን ከፍሎለት አሮጌውን አሳልፎ በገዛ ደሙ የሆነ አዲስን ኪዳን በመስጠት ዳግመኛ በህይወት ይኖርና በፊቱ ይመላለስ

> "እግዚአብሔር ማንነቱ በዘመናት መካከል የማይለወጥ የነበረ፣ ያለና የሚኖር ህያው አምላክ ነው።"

ዘንድ አስችሎታል። ይህ ማለት ዳግም ከህይወት ዛፍ እየበላ በገዛ ማስተዋሉ ሳይደገፍ እግዚአብሔርን በማወቅ እርሱንም በመምሰል እያደገ እንዲሄድና የመለኮት ባህርይ ተካፋይ በመሆን ሙሉ በሙሉ ተለውጦ በሀጢአት ምክንያት ከእግዚአብሔር ጋር ከተጣላው አሮጌው የወደቀ ሰው ማንነት ይድን እና በአዲስ ሕይወት ይመላለስ ዘንድ ነው።፡

በአንድ የሀይማኖት ተቋም እና ስርዓት ውስጥ ንቁ ተሳታፊ መሆን እና መመላለስ ብቻውን እግዚአብሔርን የማወቅ ዋስትና አይደለም። እግዚአብሔር ራሱን ከፍጥረት ጅማሬ አንስቶ በልዩ ልዩ መንገድ ሲገልጥ ኖሯል። ታዲያ ይህ እግዚአብሔር እርሱ ራሱ በወደደው መንገድ ይመለክ እና ደስ ይሰኝ ዘንድ ለክብሩ ያደረገው ሲሆን እርሱን ማወቅንም የእውነተኛ አምልኮ ሁሉ መነሻ እንዲሆን የሚያደርግ እውነት ነው። በዘፀዓት መጽሐፍ ምዕራፍ 32፡3-6 ባለው ክፍል ውስጥ ከግብጽ የወጣው ህዝብ ሙሴ 40 ቀን ተራራ ላይ ወጥቶ በቆየ ጊዜ ጥጃን ሰርቶ ነገር ግን *"በዓል ን __**ለእግዚአብሔር**__"* በሚል በሙሴ በኩል የሚያገኘውን እግዚአብሔርን ግብፃውያን ለአማልክቶቻቸው ምስል እና ቅርጽ እንደሚሰሩት ቅርጽ ሰርቶ ሊያመልከው ተዘጋጀ።

ምንም እንኳን በዓሉ ለእግዚአብሔር ይባል እና ይሄው አምላክ ህዝቡን ከግብጽ ምድር እንዳወጣ ይነገር እንጂ ከዚህ ንግግር ጥቂት ምዕራፎች በፊት በምዕራፍ 20 አምላኩ ለህዝቡ በብዙ ክብር ከማስጠንቀቂያ ጋር የሰጠውን ትዕዛዝ ይኸውም *"ከአምላክህ በቀር ለሌላ አትስገድ ደግሞ ምንም ቅርጽ ወይም ምስል ለራስህ አታድርግ አታምልክም"* የተባለውን የተላለፈ ነበርና፤ እንኳን እግዚአብሔርን ደስ ሊያሰኝ ህዝቡን ያጠፋ ዘንድ ተቆጥቶ እንዲነሳ ያደረገው በፊቱ የተጠላ ባለማስተዋል የተደረገ የአምልኮ መልክ ይዞ እግዚአብሔርን ክዶ ለእግዚአብሔር ተብሎ የተደረገ ታላቅ እግዚአብሔር የሌለበት የስንፍና ድግስ ነበር።

እግዚአብሔር ለበጎዎችም ለክፉዎችም ዝናብን ያዘንባል ደግሞ ፀሃይን ያወጣል። በሐዋርያት ስራ 14፡16-17 ባለው ክፍል ውስጥ እግዚአብሔር እስከዚያን ጊዜ አህዛብን በራሳቸው ጎዳና ይሄዱ ዘንድ ትቷቸው የነበረና እርሱን ባለማወቅ ይመላለሱ

እንደነበር ይናገርና በዚህም ወቅት እንኳን ሰዎች እግዚአብሔርን ያስቡ ዘንድ መልካም ስራን እየሰራ ከሰማይ ዝናብን እያዘነበ ደግሞ ፍሬ የሚሆንበትን ወራት ሳያጓድል እየሰጠ የሰው ልጆችን ልብ በመብልና በደስታ እየሞላ በመኖር ራሱን ያለ ምስክር ሳይተው እንደኖረ ጳውሎስ በልስጥራን ወንጌልን ባደረሰበት ጊዜ ይናገራል።

> “በአንድ የሀይማኖት ተቋም እና ስርዓት ውስጥ ንቁ ተሳታፊ መሆን እና መመላለስ ብቻውን እግዚአብሔርን የማወቅ ዋስትና አይደለም።”

ይሁን እንጂ ይሄው ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች በላከው መልእክት ውስጥ በመጀመሪያው ምዕራፍ ቁጥር 20 እና 21 ላይ እንደሚናገረው ምንም እንኳን የሚታየው ባህርይ እርሱም የዘላለም ኃይሉ ደግሞም አምላክነቱ ከአለም ፍጥረት ጀምሮ ከተሰሩት ታውቆ ግልጥ ሆኖ ሲታይ የኖረ ቢሆንም እርሱ ይታወቅ ዘንድ ራሱን በዚህ መጠን ገልጦ ሳለ የሰው ልጆች እግዚአብሔርን እያወቁ እንደ እግዚአብሔርነቱ መጠን ስላለከበሩትና ስላላመሰገኑት ልባቸው እንደ ጨለመ ይናገራል። ይህም ብቻ ደግሞ አይደለም ነገር ግን እግዚአብሔርን ለማወቅ ባለወደዱት መጠን እግዚአብሔር የማይገባውን ያደርጉ ዘንድ ለማይረባ አዕምሮ አሳልፎ እንደሰጣቸውም ይናገራል። ይህም እግዚአብሔርን እንደሚገባ ያለማወቅ፣ ያለ እግዚአብሔር ምህረት ከንቱ የሆነውን እስትንፋሱ በአፍንጫው ያለች ደካማ ሰው እንደ እንስሳ ይመስል ዘንድ፣ ለክፉ ምኞቱም ታልፎ እንዲሰጥ ያደረገውን ሁኔታ ያመጣ ነው።

በተመሳሳይ መልኩ እስራኤል እግዚአብሔርን ባለማክበር ይመላለሱ በነበሩበት ሆሴዕ ይተነብይ የነበረበት የነገስታት ዘመን እውነትና ምህረት እግዚአብሔርንም ማወቅ በምድሪቱ ላይ ባልነበረ ጊዜ እግዚአብሔር ህዝቡን ለክፉ ምኞቱ አሳልፎ ሰጥቶት እርግማንና ሐሰት፣ ግድያና ስርቆት ምንዝርናም ሀገሪቱን ሞልቶ እንደነበር በዚህም ምክንያት ምድሪቱ ለለቅሶ፣ ህዝቡም ለምድር አራዊትና ለሰማይ ወፎች መብልነት ተላልፎ ተሰጥቶ እንደነበር ይታያል።

በዚሁ የሆሴዕ መጽሐፍ ውስጥ በምዕራፍ 4፡6 ላይ የዚሁ የህዝቡ ጥፋት ምክንያት እግዚአብሔርን አለማወቁ እንደሆነ ይናገራል። ይህም ብቻ ደግሞ አይደለም

እውቀት ከማጣቱ በተጨማሪ እውቀትን መጥላቱና ለማወቅ እንኳን አለመውደዱ ህዝቡን በእግዚአብሔር ፊት የሚያገለግል ካህን እንዳይሆን ያስናቀው እና በእግዚአብሔር እንዲጠላ ያደረገው ሲሆን ይህንኑ የአምላኩን ህግ መርሳቱ ከእርሱ አልፎ ለልጆቹ የሚተርፍ ጥፋትን እንዳመጣበት ይታያል።

በእንዲህ አይነት እውቀት ማጣት ምክንያት በብዙ ችግር እና መከራ ውስጥ ህዝቡ ካለፈ በኋላ መከራው ሲበዛበትና መፍትሄ ሲያጣ እግዚአብሔር ረድቶት ወደ ማስተዋሉ ተመልሶ እግዚአብሔርን መበደሉን እስኪያውቅ እና ደግሞ የአምላኩን ፊት በእውቀት እስከሚፈልግ ድረስ እግዚአብሔር ለፈቃዱ አሳልፎ ሰጥቶት ከፊቱ ዞር እንዳለ ይታያል። ከዚህ ሁሉ መከራ እና ችግር በኋላ ታዲያ ያለፉበት መከራ ዳግም የእግዚአብሔርን ፊት ለመፈለግ እንዲነሱ ያደረጋቸው ሲሆን ከዚህም በኋላ ሊያውቁት ባለመውደድ ፊታቸውን ያዞሩበትን እግዚአብሔርን እጅግ አድርገው ፈልገውት በብዙ ፍለጋ በቸርነቱ እንደተገኘላቸው ይታያል።

ከዚህ ሁሉ በኋላ ህዝቡ የተረዳው እና በጋራ የተስማማበት አንድ ነገር መፍትሄው ወደ እግዚአብሔር መመለስ እንደሆነ እና እርሱ ራሱ እንደሰበራቸው እርሱ ራሱም ብቻ እንደሚፈውሳቸው፣ እንደ መታቸው በምህረቱ እንደሚጠግናቸው ማስተዋል ነበር። ይህም እግዚአብሔርን አለማወቃቸው ያመጣባቸውን ጥፋት በዘላቂነት ለመቅረፍ *“እንወቅ እናውቀውም ዘንድ እግዚአብሔርን እንከተል እንደ ወገግታም ተዘጋጅቶ እናገኘዋለን፣ እንደ ዝናብም ምድርንም እንደሚያጠጣ እንደ መጨረሻ ዝናብ ይመጣል”* በሚለው ንግግራቸው እግዚአብሔርን ማወቅ እግዚአብሔርን ለመከተል የግዴታ አስፈላጊ የሆነ ቅድመ ሁኔታ እንደሆነና በፍለጋችን ልክ ተገልጦ የሚገኝ ታማኝ አምላክ መሆኑንም የሚገልጽ እውነት ነው። የናዳብና አብዩድ ሞት፣ ታቦቱ በተመለሰበት ወቅት የአዛ መሞት ወዘተ እግዚአብሔር የመርህ አምላክ መሆኑን እና ከእርሱ ጋር ለሚኖረን ግንኙነት መነሻው እርሱን ማወቅ እንደሆነ የሚያሳይ ነው። በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 12፡47 እና 48 ላይ የጌታን ፈቃድ ማወቅ ብሎም ማድረግ እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ ይልቁንስ በአለማወቅ ወይም በቸልተኝነት ምክንያት በጥፋት ውስጥ መገኘት ተመጣጣኝ ለሆነ ቅጣት የሚዳርግ እንጂ ሳይቀጣ የሚቀር እንዳልሆነ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በግልጽ አስተምሯል።

- **የማስተንተኛ ጥያቄዎች**

1. እግዚአብሔርን እንድሚገባ አለማወቅ ውጤቱ ምን እንደሆነ ተረዳህ?
2. እግዚአብሔርን ማወቅህ ሕይወትህን እንዴት ይጠብቃል? እንዴትስ አምልኮህን ይለውጣል?
3. በዚህ ሳምንት በጌታ እውቀት ለማደግ ምን ተግባራዊ እርምጃ ልትወስድ አሰብክ?

- **አሰላስል**

እግዚአብሔርን ማወቅ ሐይማኖታዊ ግዴታ ብቻ ሳይሆን የእውነተኛ አምልኮ መሠረቱ ነው። ቅዱሳት መጻሕፍት እግዚአብሔርን እንደሚገባ ማወቅ ያልወደዱን ሰዎች ሕይወታቸው ወደ ጨለማ፣ ወደ መደናገርና ወደ ጥፋት እንደሚያመራ ደጋግመው ያሳያሉ። በተቃራኒው ወደ እርሱ የሚመለሱ ምሕረትን፣ መታደስንና ሕይወትን ያገኛሉ። ስለዚህ ስለ እግዚአብሔር መስማት ወይም መረጃ መያዝ ብቻ አይበቃም፤ እርሱን በግል ልምምድና በቀረበ ኅብረት ማወቅን ልንከታተል ይገባናል። እግዚአብሔርን በምናውቀው መጠን እንኖረው ዘንድ ያዘጋጀልንን እውነተኛ ሕይወት እናገኛለን። ይህንን እውነት ሁልጊዜ በልባችን ልንይዝ ይገባናል።

- **ጸሎት**

በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፣ ልቤ ከአንተ እውቀት እንዳይርቅ ጠብቀኝ። በቃልህና በመንፈስህ በየቀኑ አንተን ለመፈለግ የሚናፍቅ ልብ ስጠኝ። በእውነትህ እንድመላለስ እርዳኝ፤ ሕይወቴም ባሕርይህን እንዲያንጸባርቅና ስምህን እንዲያከብር ጸጋህን ስጠኝ።
በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አሜን።

- **የአርምሞ ጥቅስ**

*“ሕዝቤ ዕውቀት ከማጣቱ የተነሣ ጠፍቷል። ዕውቀትን ስለ ናቃችሁ፣ እኔም ካህናት እንዳትሆኑ ናቅኋችሁ፤“*

*— ትንቢተ ሆሴዕ 4፡6 —*

Life TRUTH 14:6

## 1.4. እግዚአብሔርን እንዴት እንወቅ?

እግዚአብሔር የፈለገ እንደሚያገኝ፣ የለመነ እንደሚሰጠው ደግሞ ማንም በር ያንኳኳ እንደሚከፈትለት ቃል የገባ፣ እንደ ቃሉም የሆነ እና ሲፈለግ በሙላት የሚገኝ ታማኝ አምላክ ነው። ይህም ከዚህ በላይ በተጠቀሰው የሆሴዕ ምዕራፍ 6 ሃሳብ በግልጽ የሚታይ እውነት ነው። እስራኤላዊያን ወደ እግዚአብሔር ለመመለስ ወስነው እግዚአብሔርንም ማወቅ ወደው በተከተሉት ወቅት እንደ ወገግታ ተዘጋጅቶ እንዳገኙት ይታያል። በዚህም መሰረት የልብ መዘጋጀት ከሰው ሆኖ በመልሱ ደግሞ እግዚአብሔር በተፈለገው ልክ ራሱን ለፈለገው አካል እንደሚገልጥ የሚያሳይ ነው።

ከላይ ባሉት ምንባቦች ለመግለጽ እንደተሞከረው እግዚአብሔር መታወቅን የሚወድ እርሱን በማወቅ በእውነት ሊመለክ የተገባው ራሱን በዙሪያችን ባሉ ፍጥረታት እንዲሁም እኛን ራሳችንን እንኳን ጠጋ ብለን በጥልቀት ብንመለከት ሰሪያችን በእርግጥ ምን አይነት ድንቅ አምላክ እንደሆነ ይነግሩን ዘንድ ራሱን ያለ ምስክር ሳይተው በዙሪያችን ባሉ ፍጥረታት ሁሉ ላይ መልኩ ደምቆ የሚታይ ራሱንም ከእኛ ያልሰወረ በሙላት ተገልጦ የሚገኝ አምላክ ነው። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚናገረው *"እግዚአብሔር አምላክ ነው ለእኛም በራልን"* ተብሎ እንደተጻፈ እናውቀው እና አጥርተን እናየው ዘንድ የእርሱ መልካም ፈቃድ እና በጨለማው ልባችን ላይ የእርሱ ብርሃን ይበራ ዘንድ ብርሃን ይብራ ማለቱ የግድ አስፈላጊ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በሆሴዕ 6፡6 ላይ እግዚአብሔር ከመስዋዕት ይልቅ ምህረትን ደግሞ ከሚቃጠል መስዋዕት ይልቅ እግዚአብሔርን ማወቅ ይበልጥ ደስ እንደሚያሰኘው ይናገራል።

ምንም እንኳን መስዋዕት ለእግዚአብሔር የተወደደ ህዝቡ ለአምላኩ ፍቅሩን የሚገልጥበት መንገድ ቢሆንም ከመስዋዕት ሁሉ ደግሞ የበለጠ ሁለንተና ለእግዚአብሔር የሚሰጥበት የሚቃጠል መስዋዕት ከሌሎቹ

> "እግዚአብሔር የፈለገ እንደሚያገኝ፣ የለመነ እንደሚሰጠው ደግሞ ማንም በር ያንኳኳ እንደሚከፈትለት ቃል የገባ፣ እንደ ቃሉም የሆነ እና ሲፈለግ በሙላት የሚገኝ ታማኝ አምላክ ነው።"

መስዋዕቶች ሁሉ ይልቅ ይበልጥ የተወደደ እና ለእግዚአብሔር መልካም የመዓዛ ሽታ ያለው መስዋዕት እንደሆነ የዘሌዋዊያን መጽሐፍ ይነግረናል። ይሁን እንጂ ከዚህም በእግዚአብሔር ዘንድ እጅግ የተወደደ የሚቃጠል መስዋዕት እንኳን ጭምር የበለጠ እግዚአብሔርን ማወቅ እርሱን የበለጠ ደስ እንደሚያሰኘው ይናገራል። ከዚህ በተቃራኒው እግዚአብሔርን ባለማወቅ የሚደረግ የመስዋዕት ጋጋታ እግዚአብሔርን ደስ እንደማያሰኘው ይልቁንስ እንደሚፀየፈው በትንቢተ ኢሳይያስ 1፡10-17 እንዲሁም በዚሁ የኢሳይያስ መጽሐፍ ምዕራፍ 66፡1-4 ባለው ክፍል ውስጥ ደግሞም በሌሎች በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በስፋት ተዘርዝሮ ይገኛል። እግዚአብሔርን ከማምለክ በፊት እግዚአብሔርን ማወቅ ይቀድማል።

> “እግዚአብሔርን ከማምለክ በፊት እግዚአብሔርን ማወቅ ይቀድማል።”

በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 1 ላይ መጥምቁ ዮሐንስን ሲከተሉ ከነበሩ ደቀመዛሙርት ውስጥ ስለሚመጣው መሲህ ሲሰሙ ከከረሙት መካከል እንድርያስ የሚባለው ሰው ሁልጊዜ በተስፋ መልክ ይመጣል እየተባለ ሲሰበክለት የኖረውን መሲህ አንድ ቀን በዮሐንስ /መጥምቁ/ ጠቋሚነት ፊት ለፊት አየው። ከዚህ ወድያ ይበልጥ ሊያውቀው ወደደና *“ረቢ ሆይ ወዴት ትኖራለህ?”* የሚል አብሮ የመቆየት ፍላጎትን አሳየ። በዚህም ጥያቄ መሰረት ከኢየሱስ ጋር አብሮ የመዋል እድልን አገኘና ከቆይታው ሲመለስ ወንድሙ የሆነውን ጴጥሮስን ፈልጎ በወቅቱ በእስራኤላዊያን ዘንድ ለመስማት የሚከብድ ንግግርን ተናገረ። *“መሲህን አግኝተናል”* ብሎ ተናገረ። በተመሳሳይ መልኩ ሌሎቹም ደቀ መዛሙርት አብረውት በመቆየታቸው ብዛት በየጊዜው እርሱን የበለጠ ለማወቅ እድል ያገኙ ነበር። ይሁን እንጂ ምንም እንኳን ወደ ሶስት አመት ተኩል ከኢየሱስ ጋር አብረው የቆዩ ቢሆንም እርሱ ራሱን ለእነርሱ ሊገልጥ በወደደው መጠን ሊያወቁት አልተቻላቸውም ነበር። ይህም አንድ ጊዜ *“አብን አሳየንና ይበቃናል”* በሚለው የፊልጶስ ንግግር እንዲሁም *“የምነግራችሁ ገና ብዙ ነበረኝ ነገር ግን ልትሸከሙት አትችሉም”* በሚለው ደግሞም *“እንደዚህ የማታስተውሉ ናችሁ?”* ወዘተ በሚሉት የጌታችን ንግግሮች ውስጥ የሚታይ እውነት ነው።

ኢየሱስ የምድር ላይ የስጋ ወራት ቆይታውን ከጨረሰ በኋላ የነገራቸውን ሁሉ የሚያስታውስ/የሚያስረዳ እና ወደ እውነት ሁሉ የሚመራቸው፣ ሊነግራቸው ፈልጎ መሸከም ስለማይችሉ ያልነገራቸውን ሁሉ የሚገልጥና የሚያስተምር መንፈሱን እንደሚልክላቸው ነገራቸው። ይህም በመጨረሻ መጽሐፍትን ያስተውሉ ዘንድ አዕምሯቸውን በመክፈቱ እና ይህንን መንፈስ በመቀበላቸው ተገልጦ የሚታይ እርሱን በማወቅ የጨመሩበትን መልክ እንመለከታለን።

ይህ መንፈስ ዛሬም እኛን ሊያስተምር በአማኞች ሁሉ ውስጥ የሚገኝ ሲሆን ሊማር እና እግዚአብሔርን ሊያውቅ ወድዶ ከእርሱ ጋር ጊዜ መውሰድን ለወደደ ሁሉ ራሱን በመግለጥ ያስተምረዋል። ይህንን በዮሐንስ ወንጌል 14፡21-24 ባለው ክፍል ውስጥ የእርሱ ትዕዛዝ በውስጡ ያለችው ደግሞ የሚጠብቃትም የሚወደው እርሱ እንደሆነ ተናግሮ እንዲህ አይነቱን ሰው እርሱ ብቻ ሳይሆን አባቱም እንደሚወደው ለዚህ ሰው አለም በማታውቀው መልኩ ራሱን የበለጠ እንደሚገልጥ ይናገራል። ይህንም የሚያደርገው አለም የማታወቀው ነገር ግን በአማኞች ሁሉ ውስጥ በሚኖር መንፈሱ በኩል ወደ እንዲህ አይነቱ የሚወደው ሰው እርሱም አባቱም መጥተው እንደሚኖሩ በመግለጥ ያረጋገጠው እውነት ነው። ታዲያ ይህ መንፈስ የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገርስ እንኳን ሳይቀር የሚመረምር እግዚአብሔርን በሙላት የሚያውቀው ራሱ እግዚአብሔር የሆነ የእውነት መንፈሱ ነው።

ይህ መንፈስ አማኞችን ለማስተማር እና ወደ እውነት ለመምራት በውስጣቸው የሚያድር ሲሆን ሰዎች ሁሉ እግዚአብሔርን በማወቅ ያድጉ እና ባልተቋረጠ ሁኔታ በአዕምሮ መታደስ ውስጥ አልፈው ወደ እግዚአብሔር ፍጹም ሙላት ደርሰው ይሞሉ ዘንድ መዳረሻቸውን ቀድመው ይመስሉት ዘንድ ወደ ተጠሩለት የልጁ መልክ አድርጎ በልዩ ልዩ መንገድ ይሰራል። በዚህም አሰራሩ ሰው በግሉ ቃሉን በማንበብ እንዲሁም ከዚህ አስተማሪ መንፈስ ጋር በልዩ ልዩ መንፈሳዊ ልምምዶች የተገባ ኅብረት በማድረግ የሚያድግበት መንገድ ለአንድ ሰው ትክክለኛ እግዚአብሔርን ጤናማ በሆነ መልኩ በማወቅ የማደግ ሂደት አይነተኛው ምትክ የሌለው አካሄድ ነው።

ይሁን እንጂ ከዚህ በተጨማሪ በግል እንዲሁም በጋራ እንደ አካል ጤነኛ የሆነን እድገት እግዚአብሔርን በማመንና በማወቅ እናድግ ዘንድ ወደ ላይ በወጣ ጊዜ ሁላችን

በስፍራችን በፍቅር ተጋጥመን አካል እንደምንሆነው እንደዛ የተገባን እድገት ለማደግ እርስ በእርስ የግዴታ የሚፈላለጉ የፀጋ ስጦታዎችን ለአካሉ ግንባታ እንዲሆን ብሎ እንደሰጠ መጽሐፍ ቅዱስ በኤፌሶን መልዕክት 4፡7-16 ባለው ክፍል ውስጥ ይናገራል።

በዚሁ ክፍል ውስጥ እንደሚናገረው ሰው በግሉ እግዚአብሔርን ከመፈለጉ በዘለለ የበለጠ እግዚአብሔርን በማመንና በማወቅ ያድግ ዘንድ በዚህም እድገት አምላኩን በሚገባ ያወቀ በጠላት ሽንገላ እና ውሸት በቀላሉ የማይወሰድ ይልቁንስ ከህጻንነት ወጥቶ እውነትን በፍቅር አየያዘ በነገር ሁሉ እግዚአብሔርን በማወቅ ራስ ወደሚሆን ወደ ክርስቶስ ያደገ የእግዚአብሔርንም እቃ ጦር እንደሚገባ የለበሰ ይሆን ዘንድ የሚያግዙ ስጦታዎችን ለቤተክርስቲያን ሰጥቷል።

ወንጌላዊ ወንጌልን በማድረስ እና ነፍሳትን በመናጠቅ፣ ሐዋርያው የቤተክርስቲያንን ተደራሽነት በማስፋት፣ አስተማሪው የዳነውን እውነተኛ ደቀመዝሙር በማድረግ፣ እረኛው በጎቹን በመጠበቅ እና በማሰማራት እንዲሁም ነቢያቱ የእግዚአብሔርን የልብ ሃሳብ በመግለጥና አቅጣጫን በማሳየት ሰው ሁሉ ወደ ክርስቶስ ተገቢ የሆነን እድገት ያድግ ዘንድ ተሰጥተዋል። ይህ ማለት ከላይ የተጠቀሱት ስጦታዎች ብቻ ለቤተክርስቲያን አገልግሎት ይውላሉ ማለት ሳይሆን በ1ኛ ቆሮንቶስ መጽሐፍ ምዕራፍ 12 ላይ እንደተጠቀሰው እያንዳንዱ ብልት በስፍራው በመጋጠም እውነተኛ የሆነች የክርስቶስ አካልን የሚገነባበት መንፈሳዊ መንገድ ነው።

በዚህም መሰረት ሰው እግዚአብሔርን በማወቅ ያድግ ዘንድ በግሉ እግዚአብሔርን ከመፈለግ ባለፈ ጤነኛ በሆነ የቅዱሳን ኅብረት ውስጥ በመሳተፍ ለቤተክርስቲያን በተሰጡ የፀጋ ስጦታዎች በመጠቀም እግዚአብሔርን በማመን እና በማወቅ ራስ ወደሚሆን ወደ ክርስቶስ ማደግ የግዴታ ያስፈልገዋል ማለት ነው። ይህም ሂደት በምድር ላይ እንድንኖርበት እስከተሰጠን እድሜ ዘመን ሁሉ ያለማቋረጥ የሚደረግ እግዚአብሔርን ፍለጋ የምንጓዘው የእድሜ ልክ ጉዞ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በ1ኛ ዮሐንስ መልዕክት 3፡1 እና በዮሐንስ ራዕይ ምዕራፍ 22 ላይ በግልጽ እንደተፃፈው ፍለጋችን የሚጠናቀቀው እና እርሱን በሙላት የምናየው የተባረከው ተስፋችን ክርስቶስ ሲመጣ ወይም ደግሞ እኛ ከዚህ ደካማ ስጋ ተላቀን ወደ እርሱ ስንሄድ እንደሆነ ይታያል።

“ሰው በግሉ ቃሉን በማንበብ እንዲሁም ከዚህ አስተማሪ መንፈስ ጋር በልዩ ልዩ መንፈሳዊ ልምምዶች የተገባ ህብረት በማድረግ የሚያድግበት መንገድ ለአንድ ሰው ትክክለኛ እግዚአብሔርን ጤናማ በሆነ መልኩ በማወቅ የማደግ ሂደት አይነተኛው ምትክ የሌለው አካሄድ ነው።”

- **የማስተንተኛ ጥያቄዎች**

1. እግዚአብሔር ራሱን ለሰው ልጆች በምን መንገዶች ገልጧል?
2. እግዚአብሔርን ማወቅ ከውጫዊ ሐይማኖታዊ ሥርዓቶች በላይ ለምን አስፈላጊ ሆነ?
3. በቃሉና በመንፈሱ አማካኝነት ከእግዚአብሔር ጋር ያለህን ኅብረት የበለጠ ለማሳደግ በዚህ ሳምንት ምን ልታደርግ አሰብክ?

- **አሰላስል**

እግዚአብሔር በቅን ልብ ለሚፈልጉት ራሱን ገልጧል። እግዚአብሔርን በሰው ጥበብና በራሳችን ምርምር ብቻ አናገኘውም፤ እርሱ በፍጥረት፣ በቃሉ፣ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ፣ እንዲሁም በመንፈስ ቅዱስ ሥራ ራሱን ስለገለጠልን እናውቀዋለን። እግዚአብሔርን ማወቅ በአንድ ቀን የሚያበቃ ጉዞ ሳይሆን ዕድሜ ልክ የሚቀጥል መንፈሳዊ ጉዞ ነው። በዚህ ጉዞ ውስጥ እግዚአብሔር በየቀኑ ወደ ራሱ ይበልጥ ያቀርበናል፣ ባሕርያችንንም ወደ ክርስቶስ መልክ ይለውጣል። ስለዚህ የእኛ ፍላጎት ሁልጊዜ እርሱን የበለጠ ማወቅና ከእርሱ ጋር ያለንን ኅብረት ማሳደግ ሊሆን እንደሚገባ ማስታወስ ያስፈልጋል።

- **ጸሎት**

በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፣ ራስህን በልጅህ በኢየሱስ ክርስቶስና በመንፈስህ በኩል ስለገለጥህልኝ አመሰግንሃለሁ። በቅንነት አንተን የሚፈልግ ንጹህ ልብን ስጠኝ፤ በእውቀትህም በየቀኑ እንዳድግ እርዳኝ። በቃልህና በመንፈስህ ወደ ጥልቅ ኅብረት ምራኝ፤ በክርስቶስም መልክ እያደግሁ የአካልህ የቤተ ክርስቲያን ህያው ብልት ሆኜ እንድኖር ጸጋህን አብዛልኝ።
በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አሜን።

- **የአርምሞ ጥቅስ**

*"ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ፥ እርሱም ወደ እናንተ ይቀርባል።"*

*— የያዕቆብ መልእክት 4፥8 —*

# ምዕራፍ ሁለት

# የምናመልከው እግዚአብሔር ማን ነው?

## መግቢያ

ከዚህ በፊት በነበረው ምዕራፍ በሰፊው ለመግለጽ እንደተሞከረው እግዚአብሔር በትንሿ የሰው አዕምሮ ታውቆ የማያልቅ እጅግ ድንቅና ከመታወቅ ያለፈ የሆነ ታላቅ አምላክ ነው። ይሁን እንጂ ከዚሁ በተቃራኒ ምንም እንኳን ሊታወቅ የማይችል አምላክ ቢሆንም መታወቅን የሚፈልግ ይታወቅም ዘንድ ራሱን በልዩ ልዩ ሁኔታ ለፍጥረቱ የገለጠ አምላክ ደግሞ ነው።

ኢሳይያስ በስድስተኛው ምዕራፍ እንዳየ ምድር ሁሉ በክብሩ ተሞልታለች፣ ዳዊት በመዝሙሩ እንደነገረን ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ የሰማይም ጠፈር የእጁን ስራ ያወራል። በዚህም መሰረት እግዚአብሔር በፍጥረቱ ሁሉ ውስጥ ራሱ ማን እንደሆነ ይታወቅ ዘንድ ወድዶ የእጁን አሻራ ብሎም አምላክነቱን ትቶልን ይታያል። በዚህ መልኩ እግዚአብሔር በፈጠረው ሁሉ ላይ ይታይና ይታወቅ ዘንድ ራሱን ያለ ምስክር ሳይተው የገለጠ ይሁን እንጂ ሰው እርሱን ማወቅ በወደደበት ልክ ብቻ የሚገለጥ እና ለመታወቅ ሊያውቀው የተገባውን የሰው ልጅ የተከፈተ ልብ የሚፈልግ ትሁት አምላክ ነው።

በሮሜ መጽሐፍ 1:20-21 ውስጥ ባለው ክፍል ጳውሎስ እንደሚነግረን *“የሚታየው ባህርይ እርሱም የዘላለም ኃይሉ ደግሞም አምላክነቱ ከአለም ፍጥረት ጀምሮ ከተሰሩት ታውቆ ግልጥ ሆኖ ይታያል።”* ታዲያ ምንም እንኳን በዚህ መጠን እግዚአብሔር ራሱን ለሰው ልጆች የገለጠ ቢሆንም ዛሬም ድረስ ቀላል የማይባል ቁጥር ያለው ህዝብ እግዚአብሔር የለም ብሎ በድፍረት ይናገራል; የቀረው ሐይማኖተኛ ህዝብም በሐይማኖት ምልልስ እሽክርክሪት ውስጥ ሆኖ አምላኩን በቅጡ ሳያውቅ ስርአትን ይፈፅማል፣ ጥቂት እጅግ በጣም ጥቂት ደግሞ አምላኩን ለማወቅ እግዚአብሔር ራሱን በገለጠበት ህያው ቃሉ በኩል እርሱን ፍለጋ ከመንፈሱ ጋር በመተባበር ጆሮውን ከልቡ ጋር ከፍቶ እግሩ ስር ይውላል።

እግዚአብሔርን ለመፍራት፣ ለመውደድ፣ ለመታዘዝ በአጠቃላይ ተገቢ የሆነን አምልኮ ለማምለክ፣ የምናመልከው እግዚአብሔር ማን እንደሆነ ማወቅ የመጀመሪያው እርምጃ ነው። ለዚህም ነው እግዚአብሔር ራሱ በትንቢተ ሆሴዕ መጽሐፍ 6:6 ላይ ህዝቡ

ከሚያደርገው ሐይማኖታዊ ስርዓት እና ምልልስ በላይ እግዚአብሔርን ማወቅ አብልጦ የሚወድድ እንደሆነ የነገረን።

እግዚአብሔርን ማወቅ ይህንን ያክል እጅግ አስፈላጊ ከሆነ ታዲያ በእርግጥ እግዚአብሔር ማን ነው? ይህንን ጥያቄ የሚመልስልን እግዚአብሔር ራሱ ማን እንደሆነ በዘመናት መካከል ሊያውቁት ወድደው እግሩ ስር በተገኙ ባርያዎቹ በኩል ራሱን የገለጠበት ህያው ቃሉ ብቻ ነው። ይህም ቃል እግዚአብሔር እርሱ ማን እንደሆነ ሊገልጥ በወደደበት ልክ ይገለጥልን ዘንድ ህያው መንፈሱ ደግሞ ያስፈልገናል። በዚህም መሰረት ከብዙ በጥቂቱ እግዚአብሔር ራሱን በቃሉ በኩል በሚከተሉት ማንነቶቹ ገልጦልን ይታያል።

እነዚሁ የእግዚአብሔርን ማንነት የሚገልጡ ባሕርያት ታዲያ በሁለት ዋና ዋና ምድብ ውስጥ የሚካተቱ ናቸው። ይኸውም የእርሱ ብቻ የሆኑ ለማንም የማይካፈሉ የእግዚአብሔር ባሕርያትና መልኩን ያይበት ዘንድ ወድዶ በምሳሌው የፈጠረው የሰው ልጅ እንዲኖረው የተሰጡ ያመኑ ሁሉ እንዲካፈሏቸው የተጠሩላቸው የመለኮት ባሕርያቱ ናቸው። እንደ በሁሉም ስፍራ የመገኘት፣ ሁሉን የማወቅ፣ ሁሉን መቻል፣ ጥገኛ ሳይሆኑ ራስን በራስ ማኖር፣ ፍጹም ሉዓላዊ ስልጣን፣ የማይለወጥና ዘላለማዊ መሆንና አምላክነቱ ያሉ መሰል ባሕርያቱ የእርሱ ብቻ የሆኑና ለማንም ያላካፈላቸው የብቻ ማንነቶቹ ናቸው።

ለሰው ልጆች ያካፈላቸውም ቢሆኑ በከፊል በተወሰነ ደረጃ ተገልጠው የሚታዩ እንጂ እግዚአብሔር የሆነውን በሚመስል መልኩ የትኛውም አይነት ፍጥረት ተመሳሳይ የሆነ ባሕሪ አይታይበትም። ለምሳሌ እግዚአብሔር ቅዱስ ሲሆን የእርሱ የሆኑም ሁሉ ቅዱሳን እንዲሆኑ የተጠሩ ናቸው። ይሁን እንጂ የትኛውም አይነት በእግዚአብሔር ፀጋ ተረድተን ልንደርስበት የምንችለው ቅድስና በምንም አይነት መልኩ የእግዚአብሔርን አይነት ፍጹም ቅድስና ሊደርስ የሚችል አይደለም። ይህም በዙሪያው የሚገኙ ሀጢአት የማያውቁት መላዕክቱ እንኳን በስንፍና የሚከሰሱ ስለሆነ ፊቱን ማየት እንዳይችሉ ራሳቸውን በክንፋቸው በሚሸፍኑበት ድንቅ የአክብሮት ፍርሃት ትዕይንት ውስጥ የሚታይ እውነት ነው።

ምንም እንኳን እነዚሁ የእግዚአብሔር ብቻ የሆኑ ባሕርያት ለሰው ልጆች ይኖራቸው ዘንድ ካካፈላቸው ባሕርያቱ ጋር ሳይቀላቀሉ ተለይተው ሊታዩ የሚገባቸው ቢሆኑም ይህ መጽሐፍ ለአንባቢያኑ አጠንክሮ ሊያሳስበው ለወደደው የእግዚአብሔርን ማንነት ሚዛኑን በጠበቀ መልኩ የማስተዋወቅና እውነተኛ የሆነን በአክብሮትና በፍርሃት የሆነ የፍቅር አምልኮ በህዝቡ መካከል የመፍጠር አሳብ አጥርቶ ለማሳየት በማለም ሁለቱንም ባሕርያት ጸሃፊው ለማስረዳት ይበጃል ብሎ ባሰበው የዝምድና ቅደም ተከተል ተሰባጥረው እንዲቀርቡ ተደርጓል።

ይህም የአንዱ ባሕሪ ከሌላኛው ጋር ባለው ዝምድና ብሎም ለመግለጥ የተፈለገውን ዋና ነገር ለማስረዳት ካለው ጠቀሜታ ጋር ተያይዞ የተደረገ ነው። ለምሳሌ ያክል በመጨረሻ የተጠቀሱት የእግዚአብሔር አይለወጤነትና ዘላለማዊነቱ ብሎም ብቸኛ አምላክነቱ ከዚያ በፊት በተዘረዘሩት በርካታ ባሕርያት ላይ ተመስርተው የእግዚአብሔርን ፍጹም የተለየ ማንነት አጉልቶ ለማሳየት ማብቂያና የመጽሐፉ ማሰሪያ እንዲሆኑ ተደርገዋል።

> “እግዚአብሔር በፈጠረው ሁሉ ላይ ይታይና ይታወቅ ዘንድ ራሱን ያለ ምስክር ሳይተው የገለጠ ይሁን እንጅ ሰው እርሱን ማወቅ በወደደበት ልክ ብቻ የሚገለጥ እና ለመታወቅ ሊያውቀው የተገባውን የሰው ልጅ የተከፈተ ልብ የሚፈልግ ትሁት አምላክ ነው።”

## 2.1. እግዚአብሔር ሕያው ነው!

መ*ጽሐፍ ቅዱስ በዕብራውያን መልዕክት 11:6 ላይ ሲናገር "ወደ እግዚአብሔር የሚቀርብ ሁሉ እግዚአብሔር መኖሩንና ከልብ ለሚሹትም ዋጋ እንደሚሰጥ ማመን ይኖርበታል"* ብሎ ይናገራል። በዚህም ቃል መሰረት አንድ ሰው ስለ እግዚአብሔር ከማወቁ በፊት በቀና ልብ እግዚአብሔር የሚባል አምላክ በእውነት እንዳለ እና ህያው እንደሆነ ማወቅ ያስፈልገዋል። ይህም ማለት እግዚአብሔር ብለን የምናወራለት ይህ አካል የራሱ ማንነት ያለው በእርግጥ ህያው የሆነ ሊታወቅ የሚችል እንደሆነ እንጂ ምናባዊ የሆነና በምንም አይነት መንገድ መኖሩን ልናውቀው የማንችለው ሊዳሰስ የማይችል እንደሆነ ማሰብ አይኖርበትም ማለት ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ በትንቢተ ኤርምያስ 10:10 ላይ *"እግዚአብሔር ግን እውነተኛ አምላክ ነው እርሱም ህያው አምላክና የዘላለም ንጉስ ነው ከቁጣው የተነሳ ምድር ትንቀጠቀጣለች አህዛብም መዓቱን አይችሉም"* ብሎ ይናገራል። በዚህም መሰረት እግዚአብሔር ብለን የምናወራለት ይህ አካል ምናባዊ ብቻ እና የማይዳሰስ ሳይሆን ህያው እና እውነተኛ የሆነ ደግሞ ይህ ማንነቱም በልዩ ልዩ መልኩ በአህዛብ መካከል መዓቱን በገለጠ ጊዜ የሚታይ እንደሆነ ይናገራል። ልክ እንዲሁ ሙሴ በዘዳግም መጽሐፍ 5:26 ላይ እስራኤላዊያንን ስለ መጡበት መንገድ እና ስለሚያመልኩት አምላክ ባስታወሰበት ስፍራ *"ከስጋ ለባሽ ሁሉ እኛ እንደ ሰማን በእሳት ውስጥ ሆኖ ሲናገር የህያው አምላክን ድምጽ ሰምቶ በህይወት የኖረ ማን ነው"*ብሎ ይህንን የእግዚአብሔርን ህያውነት የሚመሰክር ይህ ድንቅ አምላክ በዚያን ጊዜ ራሱን ለዚህ ህዝብ ሊገልጥ በወደደበት ልክ ቀርቦ የተገለጠበትን በዚህም በእሳት ውስጥ ሆኖ ሲናገር ድምጹን መስማታቸውን ይመሰክራል።

ህያው የሚለው ቃል በአማርኛው መዝገበ ቃላት ፍቺ ህይወት ያለው፣ ያልሞተ፣ ኑሮ፣ ነፋስ፣ ሩህ ያለውና ተንቀሳቃሽ በሚሉ አቻ ገላጭ ቃላት ይተረጎማል። በዚህም መሰረት እግዚአብሔር ህያው ነው ብለን ስንል አሁን በዚህ ሰዓት በህይወት የሚገኝ፣ መስማት ማየት እና መመለስ የሚችል፣ ከሌሎች ህያዋን አካላት ጋር መስተጋብር ያለው፣ የሚንቀሳቀስ ሆኖ የሚኖር የራሱ ማንነት ያለው አካል ነው እንጂ ሙት፣ ግዑዝ ወይም

ምናባዊ ብቻ አይደለም ብለን እያልን ነው ማለት ነው። እንደዚህ አይነት ህያው የሆነ ማንነት ያለው አካል በእርግጥ ህያው እንደሆነ የሚገልጹ ባህርያትን ደግሞ የሚያሳይ ነው።

> "እግዚአብሔር ህያው ነው ብለን ስንል አሁን በዚህ ሰዓት በህይወት የሚገኝ፣ መስማት ማየት እና መመለስ የሚችል፣ ከሌሎች ህያዋን አካላት ጋር መስተጋብር ያለው፣ የሚንቀሳቀስ ሆኖ የሚኖር የራሱ ማንነት ያለው አካል ነው እንጅ ሙት፣ ግዑዝ ወይም ምናባዊ ብቻ አይደለም ብለን እያልን ነው"

በዚህም መሰረት አንድ ህያው የሆነ አካል ለሌሎች ህያዋን ፍጥረታት ሊታወቅ በሚችል መልኩ ራሱን የሚገልጥ እና የሚንቀሳቀስ እንዲሆን ያስፈልገዋል። ነፋስ ከወዴት እንደመጣና ወዴት እንደሚሄድ ደግሞ መልኩ ምን እንደሚመስል ተገልጦ እንደማይታየው ነገር ግን በእኛ በኩል አልፎ ሲሄድ ወይም ደግሞ በዙሪያችን ያሉ እንደ ዛፍ ያሉ ሌሎች አካላትን ከስፍራ ስፍራ ሲያንቀሳቅስ በእርግጥ በዚያ ነፋስ እንዳለ እናውቃለን።

በፍጥረት አለም ውስጥ ሁለት የተለያዩ አለማት እንዳሉ የምናውቅ ሲሆን እነርሱም አካላዊ እና መንፈሳዊ የሚባሉት አለማት ናቸው። ሰውና ምድር ላይ የሚርመሰመሰው በማይክሮስኮፕ የሚታዩ ትናንሽ ፍጥረታትን ጨምሮ የሚገኝ በሰው አይን የሚታይ ፍጡር ሁሉ የአካላዊው አለም ህያዋን ስንሆን ከዚህ ውጭ ደግሞ በማይታየው አለም ውስጥ የሚገኙ በሰው አይን የማይታዩ ነገር ግን መኖራቸውን በውስጠኛ ማንነታችን የምንረዳቸው ህያዋን አካላት ደግሞ በመንፈሱ አለም ውስጥ አሉ። በዚህ ውስጥ በመንፈሱ አለም የሚገኙ መላእክት እንዲሁም ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ መንፈስ እንደሆነ የነገረን እግዚአብሔር ህያዋን ሆነው ይገኛሉ።

ይሄው የእግዚአብሔር ህያውነት ለፍጥረት ሁሉ ይታወቅ ዘንድ በእጁ በሰራቸው ፍጥረታቱ በኩል የተገለጠ እና አሻራው በግልጽ የሚታይ ሲሆን ከዚህ በተለየ መልኩ እርሱ እንዳለ ብሎም የህይወታቸው ምንጭ እና ጌታ እንደሆነ ላመኑ ሁሉ ደግሞ ራሱን በተለየ

ሁኔታ ይበልጥ በህያውነቱ ይገልጥላቸዋል። ይህንንም ጉዳይ በተመለከተ ጌታችን ኢየሱስ ራሱ በዮሐንስ ወንጌል 14፡21-23 ባለው ክፍል ውስጥ በግልጽ የተናገረ ሲሆን ከሌላው የአለም ፍጥረት በተለየ ለእነርሱ /ለሚወዱት/ ራሱን እንዴት ይበልጥ እንደሚገልጥ ሲናገር አለም በማያየውና በማያውቀው ብሎም ሊቀበለው በማይችለው የእውነት መንፈስ በኩል ወደሚወዱት እንደሚመጣና ከአባቱ ጋር በዚያ መኖሪያን እንደሚያደርግ ይናገራል። እነዚህ የእርሱ የሆኑት እና የሚወዱት ታዲያ ይህ መንፈስ በውስጣቸው ስለሚኖር እንደሚያውቁት ይናገራል። ይህም የእውነት መንፈስ በውስጣቸው በመኖሩ ምክንያት እግዚአብሔር ህያው መሆኑን ከማወቅ ባለፈ የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር እንኳን ጭምር ከዚህ መንፈስ ጋር ባላቸው ኅብረት ከአለም በተለየ መልኩ መረዳት እንደሚችሉ ያሳያል።

በዚህም መሰረት እግዚአብሔር ህያው ነው ማለት አሁናዊ ኅብረት ያለው መገኘቱ የሚታወቅ፣ አሁን እኛ ባለንበት በዚህ የሚገኝ፣ እውነት እንጂ ምናባዊ ያልሆነ ከሌሎች ህያዋን ጋር መስተጋብር ያለው የሚሰማ፣ የሚመልስ ደግሞ የሚያይ እና የሚንቀሳቀስ የቅርብ አምላክ ነው እንጂ የማይጨበጥ እና የማይዳሰስ በሀሳብ ብቻ የሚገለጽ የሩቅ አምላክ አይደለም ማለት ነው።

ባለፉት ዘመናት እንደ ዛሬው ዘመን ሁሉ ይህንን የእግዚአብሔርን ህያውነት ያላወቁ በሌሎች ስፍራዎች ሰዎች ቅርጽ ሰርተው እንደሚያመልኳቸው ግዑዛን አማልክት መስሏቸው በተሳለቁ ጊዜ እግዚአብሔር በአስፈሪ ግርማው ለሰው በሚገባ ቋንቋ እየተገለጠ ስሙን ሲቀድስ አይተነዋል። ከዚህም መካከል በ2ኛ ነገስት 18 እና 19 ውስጥ በሚገኘው እውነተኛ ታሪክ ውስጥ ሰናክሬም የሚባል የወቅቱ የዚያን ዘመን ታላቅ ንጉስ የተለያዩ አገራትን ነገስታት አማልክቶቻቸውንም እየሰባበረ ደግሞ ቤተ መቅደሳቸውን እያፈረሰ እና እያቃጠለ ከነህዝባቸው በማረከ እና ባፈለሰ ጊዜ በዚህ የድል ጉዞ መሃል ተረኛ ሆና በተገኘችው ይሁዳ ደርሶ ለህዝቡ ጮክ ባለ ድምጽ ንጉሳችሁ ህዝቅያስ አምላካችን እግዚአብሔር ከጠላቶቻችን ያድነናል እያለ አያስታችሁ በመጣሁበት ጎዳና የአህዛብ አማልክት ሰሜኑን እስራኤልን ጨምሮ /እስራኤል በጣኦት አምልኮ ተወስዳ ነበር/ ህዝባቸውን እንዳላዳኑ ደግሞም አማልክቶቻችውን እንደሰባበርኩ አልሰማችሁም ወይ ብሎ ይላቸዋል። በዚህም ወቅት ይህንኑ የንጉሱን የንቀት ንግግር ህያው ወደ ሆነው

እግዚአብሔር ይዞ የቀረበው የወቅቱ የይሁዳ ንጉስ ህዝቅያስ እና ይህንኑ ህያው አምላክ በህያውነቱ የሚያነጋግረው አገልጋዩ ነቢዩ ኢሳይያስ ከዚሁ ሁሉን የሚሰማ ብሎም የሚያይ አምላክ ለንጉሱ የንቀት ንግግር /እንደ አህዛብ አማልክት ግዑዝ ስላደረገው/ የተገለጠ የህያው አምላክን ምላሽ እንደሚመልስ ይናገራል። በዚህም መሰረት አንድ ብቻ ከማይታየው የመንፈሱ አለም የሆነ ህያው መልዓክ ልኮ የዚህን ታላቅ ንጉስ ሰራዊት በአንድ ሌሊት ብቻ 185,000 የሚያክሉትን ገደለ።

*እግዚአብሔር በእውነት ህያው አምላክ ነው!*

በኦሪት ዘፀዓት ምዕራፍ 3 ላይ ሙሴ በቁጥቋጦው ውስጥ የሚያናግረውን አካል ማን እንደሆነ በጠየቀበት ስፍራ ላይ ይሄው ህያው አምላክ ያለና፣ የነበረ፣ ደግሞ የሚኖር አምላክ እንደሆነ ይናገራል። ይህም ማንነቱ ከሌላው ጅማሬ እና ፍፃሜ ያለው ሁሉ ፍጡር በተለየ ሁኔታ ዘላለማዊና እውነተኛ የሆነ ደግሞም ለሌሎች ህያዋን ሁሉ የህያውነታቸው ምንጭ የሆነ ከላይ እንደተገለፀው ታሪክ ሲጠሩት የሚደርስ፣ የሚሰማና የሚመልስ አሁናዊ ኅብረት ያለው ህያው አምላክ እንደሆነ ይታያል።

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ምንም እንኳን ይሄው ማንነቱ ከአለም ፍጥረት ጀምሮ ግልጥ ቢሆንም እንኳን ራሱን ለአለም ከገለጠበት ለየት ባለ ቅርበት ለሚወዱት እና ሊያውቁት ፈልገው ከልባቸው ለሚሹት በመንፈሱ በኩል ይበልጥ ይገለጣል። ይህም ሙሴ በኦሪት ዘፀዓት ምዕራፍ 33 ላይ እኛን በአለም ካለው ህዝብ የተለየን የሚያደርገን ከሌላው በልዩ ሁኔታ በተገለጠ ህያው የሆነ ምልልስ አንተ ከእኛ ጋር መሆንህ ነው እንዳለው ነው።

ልክ እንዲሁ በዚህኛው በአዲሱ ኪዳን ከበፊቱ የበለጠ ራሱን ገልጦ እርሱ ራሱ በሚወዱት የእርሱ ይሆኑ ዘንድ በመረጣቸው ውስጥ በበለጠ ቅርበት መኖር ጀምሯል። ይህም ያመኑትን የእርሱ ቤተ መቅደሶች ደግሞ ህብረታቸውን የእግዚአብሔር ማደሪያ ህንጻዎችና ህያው የክርስቶስ አካል ይሆኑ ዘንድ የበለጠ በህያውነቱ ተገልጦ ቀርቧል። ይህም ማንነቱ በሚከተሉት ሁለት መንገዶች ዕለት ዕለት ህያው ሆኖ ተገልጦ ይታያል።

## 1. ሕያው ቃሉ፡

ይህ ቃሉ ከመጀመሪያው በእግዚአብሔር ዘንድ የነበረ ራሱ እግዚአብሔር የሆነ ደግሞም የበለጠ እግዚአብሔርን እናውቀው ዘንድ ስጋ ሆኖ በሚታየው አለም ከእኛ እንደ አንዱ ሆኖ የተገለጠ ማንነት ነው። በዚህ ሁኔታ ራሱን ይበልጥ ለፍጥረቱ የገለጠው ይህ አምላክ ህይወትን የሚሰጥ መንፈስ ሆኖ ሙታን ለሆኑት ሁሉ አምነው የተቀበሉትን ህያዋን ይሆኑ ዘንድ ህይወትን አካፈላቸው።

ይህ ህያው ቃል ህያው ሆኖ እየሰራ ሁለት አፍ ካለው ስለታም ሰይፍ ይልቅ የተሳለ ሆኖ ነፍስንና መንፈስን፣ ጅማትንና ቅልጥምን ለይቶ እየወጋ የልብንም ስሜት እና ሃሳብ እየመረመረ ያመኑበትን ሁሉ በህይወት እንዲኖሩ እንጂ እንዳይጠፉ አድርጎ በዘላለም ህይወት መንገድ ይመራቸዋል። ይህም ማለት ሰዎች በሚያልፉበት የህይወት መንገድ ሁሉ ራሳቸውን እየካዱ እግዚአብሔርን በመምሰል ለመኖር ራሳቸውን የሚያዩበትና የሚቀርፁበት ህያው የሚሰራ ቃል ነው ማለት ነው።

## 2. ሕያው መንፈሱ፡

ይህ መንፈስ ከላይ የሰማነው ቃል እውነት እንደሆነ በውስጥ ማንነታችን እንድንረዳ ብሎም በህይወት ምልልሳችን ውስጥ ባነበብነው እና ባወቅነው በዚህ እውቀት መኖር እንድንችል የሚያስተምረን እና የሚያስችለን የሚሰራ ሕያው መንፈስ ነው። ይሄው ቅዱስ መንፈስ በውስጣችን የሚኖር እና ባልተቋረጠ ሁኔታ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት የምናደርግበት አካል ሲሆን በዚሁ ግንኙነት ውስጥ ዋና የሆነውን እግዚአብሔር እኛን የወደደበትን ፍቅር በልባችን እየፈሰሰ የሚያስረዳን ነው።

በዮሐንስ ወንጌል 6፡63 ላይ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚናገረው መንፈስ ህይወትን ይሰጣል ብሎም ይሄው የተናገረን ህያው ቃል መንፈስ እንደሆነና ህይወትም እንደሆነ ይናገራል። ይህ ህያው መንፈስ እግዚአብሔር ራሱን ለእኛ በተለየ ሁኔታ ይገልጥ ዘንድ በውስጣችን እንዲሆን እና ወደ እውነት እንዲመራን እና እንዲያስተምረን ብሎም ይህንኑ የተማርነውን እውነት በህይወት እንድንገልጠው የሰጠን ራሱን ወደ እኛ የጨመረበት ድንቅና እጅግ ውድ ስጦታ ነው።

ይህ የእግዚአብሔር ህያውነት መጀመሪያና መጨረሻ የሌለው ፍጥረት ሁሉ ሳይኖር በፊት የጀመረ ለዘላለም የሚኖር በሞት የማይቋረጥ እውነት ነው። ታዲያ በዚሁ ሕያውነቱ እስከ አለም ፍፃሜ ድረስ ሁልጊዜ የእርሱ ከሆኑት ሁሉ ጋር በመንፈስ ብሎም በቃሉ በኩል አብሮ እንዳለ የተናገረ ሲሆን ሁለት እና ከዚያ በላይ ሆነው ልጆቹ በአንድ ልብ በተሰበሰቡበት ሁሉ ደግሞ በዚያ በተለየ መገኘት ራሱን በመካከላቸው በህያውነቱ እንደሚገልጥ ያስረዳል።

ይህ ህያውነቱ ከእርሱ ማንነት አንጻር ሳይሆን ሰዎች እርሱ ይገኝ ዘንድ ራሳቸውን ለመገኘቱ ባመቻቹበትና መገለጡን በናፈቁበት ሁኔታ ሁሉ በተለያየ መጠን በልዩ ልዩ መንገዶች ይገለጣል። እርሱ ሁልጊዜ በልጆቹ መካከል ህያው ሁኖ የሚገኝ ቢሆንም ሀጢአት፣ መተላለፍ እና አመጽ በህዝቡ መካከል በሆነ ጊዜ ህያው ማንነቱ በልዩ ልዩ አሰራሩ በዚህ በሚታየው የእኛ አለም ተገልጦ እንዳይታይ ሲገድበው ይታያል።

በዚህ ክፍል መጀመሪያ ለመግለጽ እንደተሞከረው እግዚአብሔር እያለ እንደሌለ መቁጠር እና ህያውነቱን መካድ ከባድ የህይወት ዋጋን ያስከፍላል። ምንም እንኳን እግዚአብሔር በፍጥረቱ ሁሉ ራሱን ገልጦ የሚገኝ ቢሆንም ዛሬም በርካቶች መኖሩን ይክዳሉ። ከዚህ በተጨማሪ እንዳለ የሚያውቀውም ህያውነቱን ዛሬ ብሎም አሁን እነርሱ ባሉበት በአይናቸው ሌላን ሰው በሚያዩበትና ያዩትን በእጃቸው ሊዳስሱ በሚችሉበት እውነት ልክ ከዚያም ባለፈ ሁኔታ በዙሪያቸው እና በመካከላቸው ሲያልፍም በውስጣቸው እንደሚገኝ አይረዱም።

ይሄው ህያው እንደሆነ እንዳለም አለማወቅ መጽሐፍ ቅዱስ በመዝሙረ ዳዊት 14 ላይ እንደሚናገረው ስንፍና ሲሆን ይህም ስንፍና ሰውን ወደ ጥፋት እንደሚመራው ይናገራል። ይህ ስንፍና እግዚአብሔር የለም የሚያስብል ሲሆን ከዚህም ሲያልፍ አለ የሚሉትን ጭምር እግዚአብሔር ህያው እንደሆነ ባሉበት ሁልጊዜ ህያው ሆኖ እንዳለ አለማወቃቸው እንደሚያይ እና እንደሚሰማ ብሎም ከፉና ደግ እንደሚያደርግ እንዳያስቡ ያደርጋቸዋል። እግዚአብሔር ህያው እንደሆነ ፍጥረትን አይቶ ማመን ያልፈለገ ልብ መጽሐፍ ቅዱስ በሉቃስ ወንጌል 16፡27-31 ባለው ክፍል እንደሚናገረው አንድ ሰው ከሙታን መካከል ተነስቶ እግዚአብሔር እንዳለ ቢነግረው እንኳን ለማመን እጅግ ይቸገራል።

“እግዚአብሔር ህያው እንደሆነ ፍጥረትን አይቶ ማመን ያልፈለገ ልብ አንድ ሰው ከሙታን መካከል ተነስቶ እግዚአብሔር እንዳለ ቢነግረው እንኳን ለማመን እጅግ ይቸገራል።”

## የማስተንተኛ ጥያቄዎች

1. የእግዚአብሔር ሕያውነት ስለ እርሱ ባለህ የቀደመ እውቀት ላይ ምን ጨመረልህ?
2. ሕያው አምላክ ሰዎች ከሠሯቸው ጣዖታት የሚለየው እንዴት ነው?
3. ከሕያው አምላክ ጋር ያለኝን ዕለታዊ ኅብረት እንዴት ማሳደግ እችላለሁ?

## አሰላስል

የምናመልከው እግዚአብሔር ከእኛ የራቀ ሐሳብ ወይም በሰው ልጆች ምናብ የተፈጠረ ሕይወት የሌለው ነገር አይደለም። እርሱ የሚናገር፣ ራሱን የሚገልጥ፣ የሕዝቡን ጸሎት የሚሰማና በመካከላቸው የሚኖር ሕያው አምላክ ነው። በቃሉ፣ በመንፈሱና በክርስቶስ ሥራ አማካኝነት ከእርሱ ጋር እውነተኛ በሆነ ኅብረት እንድንኖር ይጋብዘናል። እግዚአብሔር ሕያው መሆኑን ማወቃችን በእርሱ እንድንታመን፣ እርሱን እንድንፈልግና በየቀኑ ከእርሱ ጋር እንድንመላለስ ሊያነሳሳን ይገባል።

## ጸሎት

በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፣ ራስህን የምትገልጥና ወደ ሕዝብህ የምትቀርብ ሕያው አምላክ ስለሆንህ አመሰግንሃለሁ። አንተን እንደሚገባ ለማመን በአዕምሮ የምረዳው እውነት ብቻ ሳይሆን፣ በሕይወቴ ውስጥ ያለህና የምትሠራ አምላክ እንደሆንህ እንዳውቅ እርዳኝ። በየቀኑ ከአንተ ጋር በኅብረት እንድመላለስ አስተምረኝ።

በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አሜን።

## የአርምሞ ጥቅስ

*"እግዚአብሔር ግን እውነተኛ አምላክ ነው፤ እርሱ ሕያው አምላክና የዘላለም ንጉሥ ነው።"*

*— ትንቢተ ኤርምያስ ፲፥፲ —*

## 2.2. እግዚአብሔር የምንም ነገር ጥገኛ አይደለም!

ከላይ በነበረው ሃተታ ላይ እንደተመለከትነው እግዚአብሔር ራሱን ለሙሴ ማን እንደሆነ ሲያስተዋውቅ እኔ እኔ ነኝ ብሎ እንዳለው ተገልጿል። የዚሁ ክፍል ቃል አገላለጽ በዕብራይስጥ "ኤሀየሀ አሸር ኤሀየሀ"( אֶֽהְיֶ֖ה אֲשֶׁ֣ר אֶֽהְיֶ֑ה, "Ehyeh Asher Ehyeh") የሚል ሲሆን የቃሉ ትርጓሜ እና ይዘትም የምሆነውን እሆናለሁ፣ የነበረ፣ ያለና የሚኖር፣ የምኖረው ከመጀመሪያውም ስለነበርኩ ነው ወዘተ አይነት ይዘት እንዳለው ይነገራል። (Brown, Driver, & Briggs, 1996) (Koehler, Baumgartner, & Stamm, 1994-2000)

በዚህም መሰረት የነበረ የሚለው ቃል በፍጥረት አለም ውስጥ ያለው ጊዜ የሚባለው ነገር ከመፈጠሩ ሁሉ ቀድሞ ወደ ኋላ የሚሄድ ሲሆን እግዚአብሔር ምንም ነገር ወደ መኖር ሳይመጣ በፊት ገና ከመጀመሪያው ያለ ጊዜ፣ ቦታ እና ሁኔታ ገደብ ዛሬ እንዳለ ቀድሞም የነበረ አምላክ እንደሆነ የሚገልጽ ነው። ይሄው ታላቅ አምላክ እግዚአብሔር የትኛውም አይነት ፍጥረት ወደ መኖር ከመምጣቱ በፊት አስቀድሞ ፍጹም በሆነ ክብሩ እና ግርማው ገና ያን ጊዜ ቀድሞውኑ የነበረ ነው። ይህም ከፍጥረት ወደ መኖር መምጣት በኋላ የተፈጠሩ ፍጥረታት ለእርሱ ባላቸው የተለያየ አመለካከት እና አምልኮ ወዘተ የሚጨምር ወይም ደግሞ የሚቀንስ ሳይሆን ቀድሞውኑ በእርሱ ዘንድ የነበረ በምንም አይነት ነገር እና ሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ ማንነቱ ነው።

የሙሴ ፀሎት እንደሆነ በሚታመነው መዝሙረ ዳዊት 90፡2 ላይ ከብዙ ዘመናት በኋላ ወደ ኋላ ሄዶ የፍጥረትን ጅማሮ ያየው የዘፍጥረት ፀሃፊው ሙሴ እግዚአብሔርን *"ተራሮች ሳይወለዱ ምድርም ዓለምም ሳይሰሩ ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ አንተ ነህ"* ብሎ ይናገራል። ይህንኑ ሃሳብ አምላኩን በቅርበት የተረዳው ንጉስ ዳዊት በመዝሙሩ ምዕራፍ 102፡25-28 ባለው ክፍል ውስጥ ሲናገር ይህ የእግዚአብሔር ማንነት ከፍጥረት መኖር እና አለመኖር ጋር ባልተገናኘ መልኩ እርሱ እግዚአብሔር ሳይለወጥ የሚኖር በማንም ላይ ጥገኛ ያልሆነ አምላክ እንደሆነ ይናገራል። *"አቤቱ አንተ ከጥንት ምድርን መሰረትህ ሰማያትም የእጅህ ስራ ናቸው። እነርሱ ይጠፋሉ አንተ ግን ትኖራለህ፣ ሁላቸው*

*እንደ ልብስ ያረጃሉ እንደ መጎናፀፊያም ትለውጣቸዋለህ ይለወጡማል አንተ ግን ያው አንተ ነህ፣ አመቶችህም ከቶ አያልቁም* ብሎ ይናገራል።

> "እግዚአብሔር የፍጥረት ሁሉ ፈጣሪ ሲሆን የተፈጠሩት ነገሮች ሁሉ ፈጽመው በእርሱ ላይ ጥገኛ ሲሆኑ እርሱ ግን በፍጥረቱ ላይ የተመሰረተ አንዳችም ነገር የለውም።"

እግዚአብሔር የፍጥረት ሁሉ ፈጣሪ ሲሆን የተፈጠሩት ነገሮች ሁሉ ፈጽመው በእርሱ ላይ ጥገኛ ሲሆኑ እርሱ ግን በፍጥረቱ ላይ የተመሰረተ አንዳችም ነገር የለውም። ይህንኑ ሀሳብ ጳውሎስ በሮሜ መጽሐፍ 11፡33-36 ባለው ክፍል ሲያብራራልን ሁሉ ከእርሱ በእርሱ የሆነ ደግሞ ለእርሱ የሆነ እንደሆነ ይናገራል። ከዚህም በተጨማሪ ይህንን የነገር ሁሉ ምንጭ እርሱ እግዚአብሔር መሆኑን ሲያስረግጥልን የእግዚአብሔር ጥበብና እውቀት ባለጠግነትም ጥልቅ እንደሆነ ፍርዱም ሊመረመር እንደማይችል ብሎም የጌታን ልብ የሚያውቅ እንደሌለና እግዚአብሔርን በዚህ የፍጥረት ስራው ብሎም በአስተዳደሩ ውስጥ አማካሪ ሆኖ የተገኘ አንድም ነገር እንደሌለ ይናገርና ይህም እግዚአብሔር ብቻውን ያለ ማንም ድርሻ ለማንም የሚመልሰው ብድር ሳይኖረው ብቻውን ከፍ ያለ ማንነት ያለው እንደሆነ ይገልፃል።

ታዲያ በዚህ ጽሁፍ መሰረት ክብር ለእርሱ ብቻ ለዘላለም የሆነው ሁሉ በእርሱና ከእርሱ ስለሆነ ይህም ክብር የሚገባው ሌላ አካል ስለሌለ እንጂ እግዚአብሔር የክብር እጥረት ኖሮበት እንዳልሆነ ይገልፃል። ይህንኑ ነጥብ ጳውሎስ በሌላ ስፍራ በ2ኛ ጢሞቴዎስ ምዕራፍ 2፡13 ላይ ሲናገር እኛ ሁላችን በእርሱ ላይ ፈፅሞ ጥገኛ የሆንን ሲሆን እርሱ ግን ባናምነው እና ሁላችን በእርሱ ላይ ብንዋሽ እንኳን እርሱ ለራሱ የታመነ ሆኖ የሚኖር ራሱን ይክድ ዘንድ እንዳይችል ታማኝነቱ በማንነቱ ላይ የተመሰረተ ለራሱም የሆነ እንጂ በሌላ ፍጡር ሁኔታ ላይ ያልተንጠለጠለ እንደሆነ ያሳያል።

ፍጥረት ሁሉ በእግዚአብሔር መልካምነት ላይ በተመሰረተ ማንነት የሚኖር ምንጩ ራሱ እግዚአብሔር የሆነ የእግዚአብሔር እጅ ስራ ነው። እነዚህ ሁሉ ልዩ ልዩ ፍጥረታት ታዲያ ከአለመኖር ወደ መኖር በእግዚአብሔር ፈቃድ መምጣታቸው ይሄው

ከላይ የተገለጸው ፍጥረታት ሳይኖሩ በፊት በእርሱ ዘንድ ያለው የፈጣሪያቸው የእግዚአብሔር ክብር በእነርሱ ላይ ይታይ ዘንድ የክብሩ ማሳያዎች ይሆኑ ዘንድ ነው። ይህም በቆላስያስ መጽሐፍ 1፡15-16 ባለው ክፍል ላይ ስለ ክርስቶስ ሲናገር እርሱ የማይታይ አምላክ ምሳሌ እንደሆነ እንዲሁም የሚታዩት እና የማይታዩት በመንፈስ አለም የሚገኙ ዙፋናት፣ ጌትነት፣ አለቅነት እና ስልጣናት እንዲሁም በሚታየው አለም ያሉ በሰማይና በምድር ያሉት ፍጥረታት ሁሉ በእርሱ እንደተፈጠሩ ይናገራል። ይህንንም ሀሳብ ሐዋርያው ዮሐንስ በመልዕክቱ ሲናገር ሁሉ በእርሱ እንደሆነ እና ከሆነውም ሁሉ አንዳችስ እንኳ ያለ እርሱ እንዳልሆነ ይናገራል። በዚሁ የቆላስያስ መልዕክት ክፍል ላይ ታዲያ ሐዋርያው ጳውሎስ ነገሩን ሲጠቀልል ሁሉ በእርሱ መፈጠሩን ብቻ ሳይሆን ሁሉ ደግሞ ለእርሱ የተፈጠረ እንደሆነ ይናገራል።

እግዚአብሔር በማንም ላይ ጥገኛ ሳይሆን በዘላለማዊ የማይለወጥ ማንነቱ ክብርና ግርማን ተሞልቶ ብርሃንን እንደ ልብስ ለብሶ ሰማያትን እንደ መጋረጃ እንደዘረጋ፣ በትንሹ የሰው ልጅ አዕምሮ በቀላሉ ሊገባ የማይችል ድንቅ ማንነቱ፣ ከፍጥረት መኖር አስቀድሞ የነበረ እንደሆነ ወዘተ በመዝሙረ ዳዊት መጽሐፍ ምዕራፍ 104 ላይ በዝርዝር ይናገራል። በዚሁ ታላቅ ማንነቱ ዛሬም ድረስ ለትንሹ የሰው ልጅ ለመረዳት አዳጋች የሆነውን እጅግ ብዙ ስራውን ሁሉ በጥበብ እንዳደረገና ፍጥረትን በስፍራ በስፍራው ፈጥሮ እንዳጋጠመ፣ በዚሁ በተፈጠሩበት ስፍራ ከፍጥረታቸው ጅማሬ አንስተው በእግዚአብሔር መልካምነት ላይ በተመሰረተ መጋቢነት እየኖሩ እንዳሉ ይዘረዝራል።

ይህንን ሁሉ ሲናገር ታዲያ በመዝሙረ ዳዊት 104፡27-30 ባለው ክፍል በተለይ እነዚህን ሁሉ የእጁ ስራ የሆኑ ፍጥረታት ምግባቸውን በጊዜው ይሰጣቸው ዘንድ እርሱን ተስፋ የሚያደርጉ የእርሱ ጥገኞች እንደሆኑ ይናገራል። በዚህም ተስፋ በጊዜው ምግባቸውን ሲሰጣቸው የሚሰበሰቡ እጁን ከፍቶ ከመልካም ነገር የሚያጠግባቸው እንደሆኑና ፊቱን በሰወረባቸው ጊዜ እንደሚደነግጡ ይናገራል። ይህም ደግሞ ብቻ አይደለም ይሄው ሰሪያቸው እግዚአብሔር ነፍሳቸውን እንደሚያወጣ እነርሱም ደግሞ እንደሚሞቱ ወደ ተሰሩበት አፈርም እንደሚመለሱ ይናገራል።

ከዚህም ሁሉ በኋላ ደግሞ ይሄው ሰሪያቸው በወደደ ጊዜ መንፈሱን ዳግም ልኮ እንደሚፈጥራቸው የእነዚህም ፍጥረታት ሁሉ መኖሪያ የሆነችውን ምድርም ፊት እንደሚያድስ ይናገራል። ይህ ሁሉ ትንታኔ በግልጽ የሚያሳየው እግዚአብሔር የነገር ሁሉ ምንጭ እንደሆነና እነዚህ ሁሉ ፍጥረታት በሰሪያቸው በእግዚአብሔር ላይ ጥገኛ እንደሆኑ ብሎም የመፈጠራቸው ምክንያት የእርሱን ክብር ለማንፀባረቅ እንደሆነ ነው። በዚህ ሁሉ ውስጥ ታዲያ ይሄው ሰሪያቸው እግዚአብሔር ከእነርሱ በማናቸውም ላይ የተመሰረተ ማንነት የሌለው ከዘላለም ዘላለም በፊት ብቻውን ዛሬ ያለውን ክብር እንደያዘ የነበረ በማንም ምንም አይነት ሁኔታ ላይ ደግሞ ከፍ ወይም ዝቅ የሚል ማንነት የሌለው በምንም ነገር ላይ ጥገኛ ያልሆነ አምላክ እንደሆነ ይታያል።

ለዚህ ከላይ ለተገለጸው ሃተታ አይነተኛ ማሳያ የሚሆነው ከፍጥረታት መካከል እግዚአብሔር በልዩ ሁኔታ ለእርሱ የቀረበ ይሆንና የፈጠራቸውን ሌሎች ፍጥረታት ሁሉ እንዲያስተዳድርለት በራሱ መልክና ምሳሌ የሰራው ሰው ነው። ገና ከፍጥረት ጅማሬው የሰው ልጅ ከምድር አፈር የተበጀ እንደሆነ ይታወቃል። ነገር ግን ይህ ከምድር አፈር የተበጀ አካሉ ብቻውን ህያው ያልነበረ ሲሆን ህያው ይሆን ዘንድ ገና ከጅማሮ በራሱ ህይወት ካለው ሌላ ህያው ማንነት ህይወትን መካፈል ነበረበት።

መጽሐፍ ቅዱስ በዮሐንስ ወንጌል 1፡4 ላይ ገና ከመጀመሪያው ፍጥረት ሁሉ ወደ መኖር ሳይመጣ በፊት በእርሱ ህይወት ነበረች፣ ህይወትም የሰው ብርሃን ነበረች ብሎ እንደሚናገር ይህንኑ ህይወት ከህይወት ራስ /ምንጭ/ ሁሉ በሁሉ የሆነው እግዚአብሔር በመንፈሱ በኩል እንደሰጠውና ይሄው ሰው ህያው ነፍስ እንደሆነ ይታያል። ከዚህ በኋላ ወደ መኖር የመጡ የሰው ልጆች ሁሉ ታዲያ ህይወትን ከዚህ መጀመሪያ ከተሰራው ሰው እየተካፈሉ በስጋና በደም ኅብረት ያላቸው እየሆኑ መባዛትን ቀጠሉ።

ከመጀመሪያው ሰው አዳም በኋላ የተሰራችው ሔዋን እንደ አዳም እግዚአብሔር ከምድር አፈር አበጅቶ እንደ አዳም እስትንፋሱን እፍ ያለባት አልነበረችም። ነገር ግን አንድ ጊዜ ህያው ይሆን ዘንድ ህይወቱን ካካፈለው አዳም ጎን አጥንትን ወስዶ የሰራት የአዳምን ህይወት የተካፈለች አጥንትን ከአጥንቱ እንዲሁም ስጋን ከስጋው የተካፈለች የህያዋን ሁሉ እናት ትሆን ዘንድ ሴት የተደረገች ናት። ከዚሁ ቀጥሎ በዘፍጥረት 2፡24 ላይ

ሲናገር ከአዳም ህይወትን የተካፈለችው ሔዋን ከአዳም ጋር አንድ ስጋ እንደሆነች ከዚህም ወድያ ከእነርሱ ህይወትን እየተካፈለ ከዘራቸው የሚገኝ ሰው ሁሉ አባቱን እና እናቱን የሚተው፣ ከሚስቱም ጋር የሚጣበቅ በዚሁም ተመሳሳይ መንገድ አንድ ስጋ የመሆን ስርአት ውስጥ የሚያልፍ እንደሆነ ይናገራል። ይህንኑ ሀሳብ ለማጠናከር በዘፍጥረት 5 ላይ የአዳምን የትውልድ መጽሐፍ ሲናገር እግዚአብሔር አዳምን በፈጠረ ቀን በእግዚአብሔር ምሳሌ እንዳደረገው ወንድና ሴትም አድርጎ እንደፈጠራቸው እንደባረካቸውም ተናግሮ ይህንን የብዙ ቁጥር አገላለጽ በአንድ ስም ይኸውም በአዳም ሲሰይመው ይታያል።

ታዲያ ከዚህ ወዲያ ይህ በእግዚአብሔር መልክ እና ምሳሌ የተፈጠረው ሰው ከመጀመሪያው በተሰጠው ዘላለማዊ ማንነት ይቆይ ዘንድ ሁልጊዜ እንዲበላው የህይወት ዛፍ /የህይወት ምንጭ/ ተሰጥቶት የነበረ ቢሆንም በራሱ ማስተዋል ይደገፍና እንደ እግዚአብሔር ጥገኛ ያልሆነ ለመሆን ባደረገው ሙከራ ባጋጠመው ውድቀት ምክንያት ከመጀመሪያው ይኖረው ዘንድ ከተሰጠው የእግዚአብሔር ህይወት ፍሰት የተቋረጠ ዳግም ከህይወት ዛፍ በልቶ ለዘላለም ህያው እንዳይሆን ከህይወት ዛፍ እንዲሁም የህይወቱ ምንጭ ካለበት ስፍራ ደግሞ መመለስ እንዳይችል ሆኖ የተባረረ ሆነ።

ይሄው የወደቀ ማንነቱ የአንድ ዛፍ ህይወት ከተተከለበት መሬት ጋር እንደተጣበቀ አሳ ደግሞ ህይወት ይኖረው ዘንድ በውሃ ውስጥ መቆየት እንዳለበት ዛፉ ወይም አሳ ህይወታቸው ከተመሰረተበት ከዚያ መኖሪያ በተነቀሉ/በወጡ/ ጊዜ ወዲያውኑ የሞትን መንገድ እንደሚጀምሩና ከጥቂት ቆይታም በኋላ ፈጽመው ሞተው እንደሚታዩ እንዲሁ ከመጀመሪያው ህይወትን ከህይወት ምንጩ ከእግዚአብሔር የተቀበለው ሰው በመተላለፉ ምክንያት ከምንጩ ጋር በተለያየ በዚያኑ ቅጽበት ሞትን ሞተ። ከዚህ ወድያ ይህንኑ ሞት በአካሉ ለመግለጽ ቀሪ ዘመኑን በየቀኑ በመጠውለግ በታጀበ ህይወት የሚመስል የስጋ ምልልስ የሚኖር ከህይወት የተቋረጠ ተንቀሳቃሽ ሙት ሆነ።

እግዚአብሔር በምንም ነገር ላይ ጥገኛ ያልሆነ የነገር ሁሉ ምንጭ እና ባለቤት ሲሆን ሰው ግን በህይወት ይኖር ዘንድ የግዴታ እግዚአብሔር የሚያስፈልገው ጥገኛ ፍጡር ነው። ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ 15 መሰረት ሰውን በጠቅላላ በተካፈለው ህይወት ላይ ተመስርቶ በሁለት ቋት ውስጥ የሚያስገባቸው ሲሆን ይኸውም አንደኛው ፊተኛው ህያው

ነፍስ የሆነ ሰው አዳም ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ህይወትን የሚሰጥ መንፈስ የሆነው ኋለኛው አዳም ኢየሱስ ነው። ይህንኑ ሀሳብ ሲያብራራ የፊተኛው ሰው ከመሬት መሬታዊ ሲሆን ሁለተኛው ሰው ደግሞ ከሰማይ የሆነ ሰማያዊ እንደሆነ ይናገራል። ታዲያ በዚህ ገለጻ መሰረት ከሴትና ከወንድ የተወለደ ፍጥረታዊ ሰው ሁሉ የፊተኛውን ከመሬት የሆነ መሬታዊ ሰው በስጋና በደም የተካፈለ ስሙም አዳም የሆነ ሰው እንደሆነ ይታያል። ይህም የተካፈልነው ህይወት በአንድ ሰው /የመጀመሪያው ሰው/ በደል ምክንያት ሞቱን አብረን የተካፈልንበት ማንነትን ያስተላለፈ ነው። ለዚህም ነው መጽሐፍ ቅዱስ ሰውን ሁሉ ሀጢአትን የሰሩና የእግዚአብሔር ክብር የጎደላቸው፣ አንድ እንኳ ጽድቅ በመካከላቸው የሌለ የሙታን ስብስብ አድርጎ የሚገልፃቸው። ይህም ገና ያን ጊዜ በመጀመሪያ አዳም በሳተ ጊዜ ገና ያልተወለዱ በእርሱ ዘር ሐረግ ውስጥ የሚገኙ ከሴትና ከወንድ የሚወለዱ ሁሉን በዚህ የሙታን ቋት ውስጥ ቀድሞ ያስገባ ነበር።

ሉቃስ በወንጌሉ ሲጽፍ በሶስተኛው ምዕራፍ ላይ የኢየሱስን ዘር ሐረግ ሲተነትን እንደመሰላቸው የዮሴፍ ልጅ ሆኖ ብሎ በምድር ላይ የሚርመሰመሰውን ሰው ሁሉ ወስዶ አዳም ከሚባል ሰው መነሻ ጋር ያገናኘውና ይህንን አዳምም መጀመሪያ ህይወትን ከሰጠው እግዚአብሔር ጋር አገናኝቶ የእግዚአብሔር ልጅ አድርጎ ይጨርሳል። በዚህ መሰረት ሰው በህይወት ይኖር ዘንድ የግዴታ የህይወት ምንጭ የሆነው ፈጣሪው እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

> “ሰው በህይወት ይኖር ዘንድ የግዴታ የህይወት ምንጭ የሆነው ፈጣሪው እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።”

በአዳም መተላለፍ ምክንያት አብሮ የሞተው የሰው ዘር ታዲያ ከዚህ የሞት ጉድጓድ የሚያወጣው ሌላ ህይወት ያስፈልገው ነበር። በዚህም መሰረት የሰውን መጥፋት የማይወደው እግዚአብሔር ገና ቀድሞ ከእርሱ በቀር ህይወትን ሊሰጠው የሚችል ሌላ የህይወት ምንጭ የሌለው በእርሱ ላይ ጥገኛ የሆነ እንደሆነ ስለሚያውቅ ራሱ ህይወት የሆነውን ልጁን ህይወትን የሚሰጥ የሚቆረስ መንፈስ አድርጎ ላከልን። ህይወት እንደገና ተገለጠ ከዚህ ወዲያ ይህንን ህይወት ሰው ሁሉ ያገኝ እና ይህንኑ የዘላለም ህይወት ተካፍሎ ለዘላለም በህይወት ይኖር ዘንድ የሚበላ የህይወት እንጀራ ደግሞ የሚጠጣ የህይወት ውሃ

ሆኖ መጣ። ነገር ግን በፍጥረታዊ ማንነቱ ሙት የሆነው ከአዳም ሞትን የተካፈለ ሰው ዳግመኛ ከዚህ የህይወት ዛፍ ይበላና በህይወት ይኖር ዘንድ አዳም ደግሞ ወደ እግዚአብሔር መገኘት እንዳይደርስና በህይወት እንዳይኖር ኪሩቤልንና የምትገለባበጥ ሰይፍን አስቀምጦ በዘጋበት ሊታለፍ የማይችል መንገድ በኩል ማለፍ ይችል ዘንድ በራሱ አቅም አይችልም። ነገር ግን ራሱን መስዋዕት አድርጎ በማቅረብ በመረቀው አዲስና ህያው መንገድ ይኸውም በተቆረሰው ስጋው በኩል መጋረጃው ስለተቀደደ የሰውን ልጆች ሁሉ ወክሎ ቀዳሚ ሆኖ ወደ እግዚአብሔር ዘንድ በደረሰው በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በማመን አዳምን ትቶ ከኢየሱስ በመንፈስ ዳግመኛ መወለድ ያስፈልገዋል።


በዚህም መሰረት በፍጥረቱ ያገኘውን የሚጠፋ አዳማዊ ዘር ትቶ ከህያውና ዘላለም ከሚኖር የእግዚአብሔር ቃል ከማይጠፋም ዘር ዳግመኛ ህይወት ከሚሰጠው መንፈስ መወለድ ያስፈልገዋል። *"አሁን ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው አሮጌው ነገር አልፎአል እነሆ ሁሉም አዲስ ሆኗል"* ተብሎ በ2ኛ ቆሮንቶስ 5፡17 ላይ እንደተጻፈ አዲሱን ሰው ባልተቋረጠ ሁኔታ በአዕምሮ መታደስ በመለወጥ መልበስ ይኖርበታል። በዚህም በመተላለፍ ምክንያት ከእግዚአብሔር የተለየውን የአዳምን ወገን ትቶ በአባቱ እጅግ የተወደደውን ራሱ ህይወት ከሆነው ሁለተኛው ሰው ጋር መዋሃድ ይችላል።

አዳም በራሱ ህይወት የሌለው ህይወትን ከእግዚአብሔር እስትንፋስ ያገኘ ሙሉ በሙሉ ጥገኛ የሆነ ፍጡር ሲሆን ሁለተኛው አዳም ኢየሱስ ግን በራሱ ህይወት እንዳለው እንዲሁ ደግሞ በራሱ ህይወት እንዲኖረው ህይወትን የሰጠው አባቱ ሙታንን እንዲያስነሳ ህይወትም እንዲሰጣቸው ያደረገው ለሚወዳቸው ደግሞም ለተቀበሉት እና በስሙ ለሚያምኑ ሁሉ ህይወትን መስጠት የሚችል መንፈስ ነው። በዚህም ዳግመኛ የመወለድ ሂደት ዘርን በመቀየር የመለኮት ባህርይ ተካፋዮች ሆነን የልጁን ህይወት ተካፍለን ለዘላለም በህይወት መኖር ችለናል። በዚህም መሰረት እርሱ ራሱ በራሱ ህይወት ያለው ጥገኛ ያልሆነ ሁሉ የተፈጠረበት የህይወት ምንጭ ሲሆን እኛ ሁላችን ደግሞ ያለ እርሱ ከነጭራሹ መኖር የማንችል ህልውናችን በእርሱ ላይ የተመሰረተ እርሱን መፈለጋችን ምርጫ ሳይሆን ግዴታ የሆነብን ፍጡራን ነን። እርሱ ደግሞ ሁለተኛ እድልን ሰውን እጅግ

በመውደዱ ምክንያት የሰጠ አላማው ፍቅር የሆነ የተወደደና የከበረ በምንም ነገር ላይ ጥገኛ ያልሆነ ድንቅ አምላክ ነው።

*“ታስበው ዘንድ ሰው ምንድን ነው? ትጎበኘውስ ዘንድ የሰው ልጅ ምንድን ነው?”*

*መዝሙረ ዳዊት 8:4*



## የማስተንተኛ ጥያቄዎች

1. የእግዚአብሔር በራሱ በቂነት ስለ ማንነቱ ምን ያስተምርሃል?
2. ፍጥረት ሁሉ በእግዚአብሔር ላይ የሚመሠረተው ለምንድን ነው?
3. በሕይወትህ ውስጥ ይበልጥ በእግዚአብሔር ላይ መመስረት የሚያስፈልግህ የትኞቹ ዘርፎች ላይ ሆኖ አገኘህ?

## አሰላስል

እግዚአብሔር በራሱ ፍጹም በቂ የሆነ አምላክ ነው። እርሱ በፍጥረት ላይ አይመሠረትም፤ ነገር ግን ፍጥረት ሁሉ በእርሱ ላይ ይመሠረታል። እያንዳንዱ እስትንፋስ፣ እያንዳንዱ ጊዜና የምናገኘው በረከት ሁሉ የሕይወት ምንጭ ከሆነው ከእርሱ የሚመጣ ነው። የእግዚአብሔርን በራሱ በቂነት መረዳታችን ትሕትናን ያስተምረናል፤ እውነተኛ ሕይወትም በእርሱ ላይ ሙሉ በሙሉ በመመስረት ብቻ እንደሚገኝ ያስታውሰናል። ስለዚህ ከራሳችን ጥበብና ኃይል ይልቅ በእግዚአብሔር ላይ መታመን እንደሚገባን ሁልጊዜ ማስታወስ ያስፈልገናል።

## ጸሎት

በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፣ ለሁሉ ሕይወትን የምትሰጥ ዘላለማዊና በራስህ በቂ የሆንህ አምላክ ስለሆንህ አመሰግንሃለሁ። በራሴ ጥበብና ኃይል ሳይሆን በአንተ ላይ እንድመሠረት አስተምረኝ። ከአንተ ተለይቼ ምንም እንደሌለኝ፣ በአንተ ውስጥ ግን የምፈልገው ሁሉ እንዳለኝ ሁልጊዜ እንዳስታውስ እርዳኝ።

በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አሜን።

## የአርምሞ ጥቅስ

*“ሁሉ ከእርሱና በእርሱ ለእርሱም ነውና፤ ለእርሱ ለዘላለም ክብር ይሁን፤ አሜን።”*

*— ወደ ሮሜ ሰዎች 11፥36 —*

## 2.3. እግዚአብሔር ሉዓላዊ ነው!

ሉዓላዊ የሚለው ቃል በመዝገበ ቃላት ፍች የበላይ፣ የማይደፈር እና የማይገረሰስ የሚል አቻ ትርጉም ያለው ቃል ነው። (ግዛው, 1994) (Merriam-Webster, n.d.) ይህም በዚያ አንድ አካል ሉዓላዊ መብት አለኝ ብሎ ባለበት ሁኔታ ላይ ፍጹም የሆነ ስልጣንን ከሶስተኛ ወገን ተጽዕኖ ውጭ የሆነ አስተዳደርን፣ በዚያ አስተዳደር ስር የሚገኙ ማናቸውንም ነገር ለማስተዳደር የሚያስችል አቅም እና ሁኔታ ያለው ማንነትን፣ ሁሉን ለመግዛት እና ለማስተዳደር የሚያስችል ቁመናን የተላበሰ፣ ግዛቱን ለማስተዳደር የተሰየመ የንግስና ስፍራን ያዘጋጀ እንዲሆን የሚያስፈልገው እንደሆነ ያሳያል። በዚህም መሰረት ይሄው ሉአላዊ የሚለው ቃል አንድን ነገር በባለቤትነት ከመያዝ እና ባለ ሙሉ መብት ከመሆን ጋር የተያያዘ እንደሆነ ይታያል።

በምድር ላይ የሚገኙ አገራት በተከለለላቸው የአገራቸው ግዛት ውስጥ ያለውን ማንኛውንም ነገር የግል ሀብታቸው አድርገው የሚቆጥሩ ሲሆን በዚህም ክልል ውስጥ በሚገኝ ማናቸውም ነገር ላይ ፍጹም የሆነ ሉአላዊ ስልጣን እንዳላቸው ይናገራሉ። በዚህ የተከለለ የእነርሱ ክልል ውስጥ በአገሪቱ ከሚገኝ ተገቢ የሆነ ስልጣን ያለው አካል ውጭ የትኛውንም አይነት የውጭ ተጽእኖ እና ጣልቃ ገብነት ለመከላከል ሉአላዊ መብታቸውንም ለማስጠበቅ ራሳቸውን በሚችሉት አቅም ያደራጁ ሆነው ይታያሉ። ነገር ግን ምንም እንኳን በዚህ በተሰመረላቸው ክልል ውስጥ የቱንም ያክል ሉአላዊ መብት እንዳላቸው የሚናገሩ ይሁኑ እንጂ በተለያየ ጊዜ ከእነርሱ የበለጠ ኃይል ያለው ሌላ አካል ይህንን መብታቸውን ጥሶ ገብቶ የእነርሱ የሆነ ነገርን ሲወስድ፣ በዚያው ክልል ውስጥ የሚገኙ በስርዓቱ ላይ የተነሱ ቡድኖች ግዛታቸውን ሲከፋፈሉት፣ ዙፋኖቻቸው በተለያየ መንገድ በሌላ ኃይል ከእነርሱ ሲወሰዱ፣ ስልጣናቸው በሞት ምክንያት ሲያልቅ ወዘተ በዘመናት መካከል ይታያል።

ባለፉት ጊዜያት እጅግ ትልልቅ ሆነው የተነሱ እንደ አሦርና ባቢሎን ያሉ መንግስታትን ጨምሮ ከከፍታቸው ሲወድቁ በሌላ ኃይልም ግዛታቸው ሲወሰድ ተመልክተናል። ዛሬም በእኛ ዘመን በኃይል የፈጠረሙ ሃያላን አገራት የፈለጉትን ሌላ ሉአላዊ አገር ግዛት አልፈው ገብተው ያሻቸውን ሲያደርጉ በየጊዜው ይታያል። ይህም ሁሉ እንኳን ባይሆን የትኛውም አይነት ምድራዊ አስተዳደር ሉአላዊ ግዛቴ ነው ባለው ክልሉ

ውስጥ ያለውን ሁሉንም ነገር ሊያውቅ ብሎም ለዜጎቹ ፍላጎታቸውን ሁሉ ሊያሟላ የሚችልበት ምንም አይነት አቅም ኖሮት አይታይም። ነገር ግን በብዙ መልኩ አቅሙ የተወሰነ እና የሚፈልገውን ሁሉ ለማድረግ የሚያስችል በቂ ቁመና ፈጽሞ የሌለው ሆኖ ግዛቱ ባለው ክልል ውስጥ ፍጹም በሆነ ሁኔታ ግዛቱን ሲያስተዳድር አይታይም።

እግዚአብሔር ግን በምድር ከሚገኙ ሁሉ ነገስታት በተለየ መልኩ ሁሉን በፈቃዱ ምክር የሰራ፣ የሰራውን ሁሉ በሚገባ ጠንቅቆ የሚያውቅ እና የሚያስተዳድር ብሎም በየትኛውም አይነት ሌላ ኃይል ስልጣኑ ሊገረሰስ የማይችል፣ ፈቃዱን ሊቃወም የሚችል አንድም ሌላ አካል የሌለው፣ በሁሉም ላይ የሰለጠነ፣ መንግስቱ ለዘላለም የሆነች፣ የስልጣን ጊዜ ማብቂያ የሌለው፣ ለፍጥረቱ ሁሉ የሚያስፈልጋቸውን በበቂ ሁኔታ ማቅረብ የሚችል ሁሉ በሁሉ የሆነ ፍጹም ሉአላዊ ገዥ ነው።

ከዚህ በፊት ባለው የዚሁ መጽሐፍ ክፍል በዝርዝር በተገለጸው መሰረት እግዚአብሔር የማንም ጥገኛ ያልሆነ እንደሆነ ብሎም በሚታየው እንዲሁም በማይታየው አለም የሚገኙ ፍጥረታት ሁሉ ለዚህ ፈጣሪያቸው ክብር ማሳያ ይሆኑ ዘንድ በገዛ ራሱ ፈቃድ እንደሚወደው አድርጎ አስተሳስሮ የሰራቸው የእጁ ስራዎች እንደሆኑ፣ እነዚህም ሁሉ ህይወታቸው /መኖርና አለመኖራቸው/ ሁሉ በዚህ ጌታቸው መልካም ፈቃድ ላይ የተመሰረተ እንደሆነ ተመልክተናል። ይህም ፈጣሪነቱ በፈጠራቸው ሁሉ ላይ ፍፁም የሆነ የባለቤትነት መብትን የሚሰጠው ሲሆን በዚህም ሁሉ ፍጥረቱ ላይ ፍፁም በሆነ የሉአላዊነት ስልጣን የመግዛትና የማስተዳደር መብትን የሚሰጠው ነው። ይህም መብት ግዛትን በባለቤትነት ከመያዝ ባለፈ ያንን ግዛት በፍጹም የበላይነት ለማስተዳደር የሚያስችል አቅም እና አቅርቦትን የሚጠይቅ ነው። ይህንንም ፍፁም የሆነ በማንም ሊገረሰስ የማይችል አቅም ብሎም የተትረፈረፈ አቅርቦት ከብዙ መልካምነት እና ፍቅር ጋር ይዞ የሚገኝ ብቸኛ መንግስት ያለው ገዥ እግዚአብሔር ብቻ ነው።

እግዚአብሔር በዚህ መልኩ ፍጥረቱን ሁሉ ከፈጠረ በኋላ ይህንኑ ፍጥረቱን በአግባቡ ለማስተዳደር የሚችልበትን ለፍጥረቱ የሚስማማ አስተዳደርን የመሰረተ ሲሆን ይህንንም መጽሐፍ ቅዱስ በመዝሙረ ዳዊት 103፡19 ላይ እንደሚነግረን የበላይ ሆኖ በሉአላዊነት ሁሉን ይገዛ ዘንድ እግዚአብሔር ዙፋኑን በሰማይ አጽንቷል። ከዚህ ማንም ሊደርስበት የማይችል ከፍታ እግዚአብሔር ፍጥረቱን ሁሉ በመንግስቱ ውስጥ በእርሱ

ዘንድ ያለውን የፈቃዱን ምክር ያስፈጽሙለት ዘንድ በተለያየ ደረጃ በሚታየው እና በማይታየው አለም ላይ ሰራተኞችን አድርጓል። ይህንኑም አስተዳደር ራሱ ንጉሱ እግዚአብሔር በፍጹም የበላይነት ሁሉን በስልጣኑ ቃል ደግፎ፣ አለማትን ሁሉ በእጆቹ ይዞ፣ ፍጥረቱን ሁሉ በስም እያወቀ እና እየጠራ፣ የማንም ድጋፍ ሳያስፈልገው በፍጹም የበላይነት ለዘላለም የሚያስተዳድር ነው።

> "ፍፁም የሆነ በማንም ሊገረሰስ የማይችል አቅም ብሎም የተትረፈረፈ አቅርቦት ከብዙ መልካምነት እና ፍቅር ጋር ይዞ የሚገኝ ብቸኛ መንግስት ያለው ገዥ እግዚአብሔር ብቻ ነው።"

ይህም አስተዳደሩ በፍጥረቱ የትኛውም አይነት አዕምሮ እና ማስተዋል ሊታወቅ የማይችልና የማይመረመር ሲሆን በየትኛውም ጊዜ፣ በማንኛውም ሁኔታ፣ በፈለገው አካል በልቡ ያለውን በወደደው ላይ የሚፈልገውን የማድረግ ፍፁም መብትን የያዘ ነው። ይህንንም አደራረጉን ሊገዳደር፣ ሊያስቆም፣ ሊቋቋም እና ሊያስቀር የሚችል ስራውን አትሰራም ብሎ ሊቃወመው የሚችል ማንም ሳይኖር በፍጹም ሉአላዊነት መንግስቱን ያስተዳድራል። ይህም ማንነቱ እርሱን የሚመስል ሌላ አምላክ ያለመኖሩ አይነተኛ ማሳያ ሲሆን ይህም ሉአላዊ መብቱ በሰማይ፣ በምድር እንዲሁም ከምድር በታች በሲኦል ጭምር ያለከልካይ የወደደውን ያደርግ ዘንድ መብትን የሚያጎናጽፈው ብሎም ሁሉ የራሱ የግል ሀብት እንደሆነ ጭምር ማሳያ የሚሆን ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ በዘፍጥረት ፩፥፩ ላይ እንደሚናገረው ገና ማንም ሳይኖር ከዘላለም ዘላለም በፊት ብቻውን እንደነበረ እና በፍጥረት ጅማሬውም እግዚአብሔር ብቻውን በፈቃዱ ምክር ሰማያትንና ምድርን ብሎም በውስጣቸው የሚኖሩትን የሚታዩና የማይታዩ ፍጥረታት ሁሉ እንደፈጠረ ይናገራል። ይህም ከላይ በዝርዝር እንደተገለጸው በፍጥረቱ ሁሉ ላይ ፍጹም የሆነ መብትን የሚሰጠው ሲሆን በእነዚህም ፍጥረታቱ ላይ በዚሁ ስልጣኑ ያለ ማንም ከልካይ እና ጣልቃ ገብነት የወደደውን እንደሚያደርግ ተመልክተናል።

በተመሳሳይ መልኩ መጽሐፍ ቅዱስ በኢሳይያስ 46፡9-11 ባለው ክፍል ውስጥ ሲናገር ይህ የመጨረሻውን ከመጀመሪያው፣ ገና የሚመጣውንም ከጥንቱ የማወቁ ምስጢር እና ማንነት እርሱን የሚመስል ሌላ እንዳይኖር ያደረገ መሆኑን ብሎም እግዚአብሔር እርሱ ብቻውን አምላክ የመሆኑ መነሻ እንደሆነ ይናገራል። ይህንን ማድረግ የሚችል በአላማው የፀናና ደስ የሚያሰኘውን ሁሉ ያለ ማንም ከልካይነት የማድረግ ብቃት እርሱ ብቻ ያለው ማንነቱ ነው። በዚሁ ክፍል ሲናገር በወደደው መንገድ፣ በሚፈልገው አካል፣ በወደደው ስፍራ እና ጊዜ አላማውን የሚፈጽም እንደሆነ የተናገረውን የሚያደርግ እና ያቀደውን የሚፈጽም ከልካይ አልባ ፍፁም ሉአላዊ አምላክ እንደሆነ ይናገራል።

ዳንኤል በሰባተኛው ምዕራፍ ከቁጥር 27 ጀምሮ ባለው ክፍል እንደሚነግረን ይህች የእግዚአብሔር መንግስት የዘላለም መንግስት ስትሆን ግዛቶችም ሁሉ የሚገዙላት እና የሚታዘዙላትት ሁሉን የምትገዛ መንግስት ናት። ይህንንም ግዛቱን ለማስተዳደር እግዚአብሔር ዙፋኑን በሰማይ አጽንቷል። ይህች የዘላለም መንግስት ብዙዎች እንደሚያስቡት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር መምጣት የተጀመረች መንግስት አይደለችም። ከዘላለም ዘላለም በፊት ከፍጥረት ቀድማ የነበረች ፍጥረታትን ሁሉ በግዛቷ ውስጥ ያካተተች ነገር ግን በሚታየው እና በማይታየው አለም በሚገኙ አካላት አለመታዘዝ ምክንያት እንደሚገባ በሙላት ያልተገለጠች በእግዚአብሔር የዘላለም እቅድ ውስጥ ተሰውራ የነበረች ፍጹም የፍቅር መንግስት ናት።

ዳንኤል በተናገረበት ወቅትና በኋላ ምድርን ያስተዳድሩ የነበሩ ታላላቅ ነገስታትን እንደ አሦር፣ ባቢሎን፣ ፋርስ፣ ግሪክ እና ሮም ያሉ መንግስታትን እንዲሁም ከዚያ በፊት የነበሩ በርካታ እየተፈራረቁ በምድር ላይ ያስተዳደሩ ምድራዊ ነገስታትን ሁሉ ፈጭታ እና አድቅቃ እንደ ትቢያ ቅሬታቸው እንዳይገኝ አድርጋ በማጥፋት በፍጹም መደላደል በመንግስቷ ውስጥ በመታዘዝ የሚመላለሱን ሁሉ ይዛ በንጉሷ በኢየሱስ ክርስቶስ ገዥነት በሙላት የምትገለጥ አሁንም በመካከላችን የምትገኝ የፍቅር መንግስት ናት። ታዲያ በእነዚህ ሁሉ የሰማይና የምድር ዘመናት እግዚአብሔር በሀሳቡ ያለችውን መንግስቱን በፍጥረቱ መካከል ለመግለጥ በፍጹም ሉአላዊነት ይህችኑ የዘላለም መንግስቱን ሊገዳደሩ የሚወዱ ሃይላትን ሁሉ እያደቀቀ ባልተቋረጠ የፍጥረት ተሃድሶ ሂደት ውስጥ አለማትን እያሳለፈ ይገኛል። በዚህም ሂደት ውስጥ እግዚአብሔር ያለ ማንም

ከልካይነት ነገስታትን ሲያስነሳ እና ሲያወርድ ህዝቡን ወደሚፈልገው አቅጣጫ ሲያፈልስ መንግስታትን ሲመሰርትና ሲያፈርስ ወዘተ ቆይቷል። በሚቀረውም ዘመን ሁሉ ይህንኑ ያለ ከልካይ በስልጣኑ ያደርጋል።

የእግዚአብሔር መንግስት ገዥው እግዚአብሔር ስልጣኑን ለማንም ሳያጋራ በፍጹም የበላይነት የሚያስተዳድርባት የፍቅር መንግስት ስትሆን በዚህም አስተዳደሩ ውስጥ የፈጠራቸውን በሚታይና በማይታይ አለም የሚገኙ ፍጥረቶቹን በፈቃዱ ምክር እንደወሰነው አሰራሩ ስልጣኑን ይገልጥባቸው እና የልቡን ሃሳብ ያደርግ ዘንድ በተለያየ አደረጃጀት አዋቅሮ አብረውት እንዲሰሩ አድርጓል። ይሁን እንጂ በዚህ መንግስት ውስጥ የሚደረገው ሁሉ አንዳችስ እንኳን ያለ እርሱ የማይሆን ሲሆን በየትኛውም አካል ምንም አይነት ነገር ቢደረግ የተደረገው ሁሉ ምንጩ ከእርሱ በእርሱ የሆነ ክብሩን በሙሉ ለእርሱ እንዲሆን የሚያደርግ መንግስታዊ አሰራር ነው።

ይህም አገዛዝ በሰው ልማድ “ቴዎክራሲ” የሚባለው አይነት አገዛዝ ሲሆን ይህም ግዛቱን ሁሉ በቀጥታ በእግዚአብሔር የሚገዛ የሚያደርግና ይህንኑ የገዥውን ፈቃድ በሙላት በልቡና በነፍሱ እንዳለ የሚረዱ እና የሚታዘዙ ብሎም በፈቃዳቸው የሚያደርጉ አካላትን እንደ መልካም ፈቃዱ ወደ ፊት በማምጣት በፍጥረቱ ሁሉ ላይ የሚገዛበት አስተዳደር ነው። በዚህም የእግዚአብሔር መንግስት አስተዳደር ውስጥ እግዚአብሔር የማያውቀው፣ የሆነ አካል መጥቶ ድንገት የሚነግረው ከእርሱ የተወሰረ ብሎም ከቁጥጥሩ ውጭ የሆነ አንዳችስ እንኳን ነገር የሌለ ሲሆን አገዛዙ ሁሉን ቀድሞውኑ ያለ አማራጭ እቅድ እውን ሊያደርገው ወስኖ የጀመረውን ያንኑ ያሰበውን የዘላለም መንግስቱን ሀሳብ በፍጥረቱ መካከል በሙላት ለመግለጥ በመንገዱ ላይ የቆሙትንና አንገታቸውን ያደነደኑትን ሁሉ ከነ ክፉ አሳባቸው እና አመፃቸው ከመንገድ ዞር በማድረግ እውን ለማድረግ እየሰራ ይገኛል።

እግዚአብሔር በመንግስቱ ውስጥ እውን ሊያደርግ የወደደውን ሁሉ ለመግለጥ ያለ ከልካይ በዘመናት መካከል እየሰራ የሚገኝ ሲሆን ይህንኑ የመጀመሪያ ሀሳቡን እና እቅዱን ተግባራዊ ለማድረግ በተወሰነ ዘመን ውስጥ የሚያልፉ የሰው ልጆችን በተሰጣቸው ዘመን የእርሱን የወቅቱን የዘላለም ሀሳብ እንዲያደርጉ በማድረግ ባልተቋረጠ የትውልድ ቅብብሎሽ ይሰራል። ይህም የእግዚአብሔር ሉአላዊ ማንነት ምንም አይነት የግል የሆነ

ሀሳብ በሰው ውስጥ ቢኖር እንኳን እግዚአብሔር እርሱ እርምጃን እየወሰነለት፣ መፈለግና ማድረግን በሰው ልብ ውስጥ እየጨመረ፣ በእግዚአብሔር እጅ ያለችን የነገስታት ልብ እንደ ቦይ ውሃ ደስ ወደሚያሰኘው እየመራና እያፈሰሰ፣ በስጋ ለባሽ ልብ ውስጥ ያለውን ብዙ ሀሳብ በገዛ ራሱ የዘላለም ሀሳብ እየገራና እንደ ፈቃዱ ምክር እየቃኘ ወደ ግቡ ይኸውም በሀሳቡ ወደ አለች የእርሱ መንግስት ይገሰግሳል። ይህም አለምን ከመፍጠሩ አስቀድሞ የወሰነው የገዛ ሀሳቡ ሲሆን ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ የእጁ ስራዎች የሆኑ ፍጥረቱን ሁሉ ለጋራ አላማ በሚወደው መንገድ ፍጹም በሆነ ሉአላዊ ስልጣን ወደ ፈቃዱ እንዲገሰግስ ያደረርጋል።

> “እግዚአብሔር የእጁ ስራዎች የሆኑ ፍጥረቱን ሁሉ ለጋራ አላማ በሚወደው መንገድ ፍጹም በሆነ ሉአላዊ ስልጣን ወደ ፈቃዱ ያፈሳል።”

ለዚህም ነው የዚህችው መንግስት ንጉስ የሆነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ ፀሎትን ሲያስተምር በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ ስምህ ይቀደስ ብሎ ብሎ መንግስትህ ትምጣ በሉ ያለው። ይህችም መንግስት ፈቃዱ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁ በምድር የሚሆንባት ሆና ቀድምውኑ በእግዚአብሔር ልብ ውስጥ እውን ትሆን ዘንድ እንዳቀደ እንዲሁ ለሰዎች ፍፁም ሰላም እና ደስታ ብሎም ለእግዚአብሔር ክብር የምታመጣ ሆና በሙላት የምትገለጥ ይሆናል። ይህንንም የልቡን ሀሳብ እውን ለማድረግ እግዚአብሔር በዘመናት መካከል እንዳደረገው ዛሬም ደግሞ ወደ ፊትም ማብቂያ በሌለው ፍፁም የበላይነቱ ህጋዊ በሆነ ሉአላዊ ስልጣኑ የሚወደውን እያደረገ ለዘላለም ሳይናወጥ ፀንቶ ይኖራል።

እያንዳንዱ ሰው ገና በእናቱ ሆድ ውስጥ ሲፈጠር አጥንቶቹም ሲዋደዱ ቀድሞ ወደ መኖር ባልመጡ ቀኖቹ ሁሉ ውስጥ ፈጣሪው ይኖረው ዘንድ የሚፈልገውን የዘላለም ሀሳቡን የሚደግፍ መልካም ሀሳቡን የፃፈበት ዋና ቁምነገሩ ሲሆን የሰው ልጅ ግን በተለያየ ጊዜ ከዚህ እግዚአብሔር በዘመኑ ይኖረው ዘንድ ከወሰነለት መልካም መንገዱ በአመጽ በተቃራኒ መንገድ ሲሄድና ከእግዚአብሔር ጋር ተጣልቶ ሲወድቅ ይታያል። እግዚአብሔር በልቡ ያለችውን መንግስቱን እውን ለማድረግ እና በህዝቡ መካከል በክብሩ ለመገኘት የትኛውንም መንገድ የሚከተል ሲሆን መጽሐፍ ቅዱስ በምሳሌ 16፡33 ላይ እንደሚነግረን

በጉያ ውስጥ የተጣለችን ዕጣ ሳይቀር ጣልቃ ገብቶ መደብዋን እየወሰነ ፈቃዱን ይፈጽማል። በዚህም የዘላለም የእግዚአብሔር አጀንዳ መንገድ ላይ በተቃራኒ የተገኘ ማንኛውም አካል እና ኃይል ሉአላዊ ስልጣኑን እየተቃወመ ነውና እግዚአብሔር ከዚህ በፊት ባሉት ዘመናት በታላላቅ ነገስታት እና ፍጥረቱ እንዳደረገ ከፊቱ ላይ እየጠረገ ከመንገዱ ዘወር ያደርግና የልቡን ሃሳብ ያለ ማንም ከልካይ ወደ ፍፃሜ ያመጣል። ዳንኤል 4፡35 እንደሚናገረው እንዲሁ በእውነት ይህንን ታላቅ አምላክ *"በምድርም የሚኖሩ ሁሉ እንደ ምናምን ይቆጠራሉ በሰማይም ሰራዊት በምድርም ላይ በሚኖሩ መካከል እንደ ፈቃዱ ያደርጋል እጁንም የሚከለክላት ወይም ምን ታደርጋለህ የሚለው የለም።"*

*"አምላካችንስ በሰማይ ነው፤ እርሱ ደስ የሚለውን ያደርጋል።"*

*መዝሙረ ዳዊት 115:3*

"የልቡን ሀሳብ እውን ለማድረግ እግዚአብሔር በዘመናት መካከል እንዳደረገው ዛሬም ደግሞ ወደ ፊትም ማብቂያ በሌለው ፍፁም የበላይነቱ ህጋዊ በሆነ ሉዓላዊ ስልጣኑ የሚወደውን እያደረገ ለዘላለም ሳይናወጥ ፀንቶ ይኖራል።"

- **የማስተንተኛ ጥያቄዎች**

1. ስለ እግዚአብሔር ሉዓላዊነት ምን ተረዳህ?
2. ለእግዚአብሔር በፍጥረት ሁሉ ላይ ፍጹም ሥልጣን እንዲኖረው ያደረገው ምንድን ነው?
3. እግዚአብሔር ታሪክን እንደሚቆጣጠር ማወቃችን በአኗኗራችንና በእርሱ ባለን መታመን ላይ ምን አይነት ተጽዕኖ ያሳድራል?

- **አሰላስል**

እግዚአብሔር ከብዙ ኃይሎች መካከል አንዱ ብቻ አይደለም፤ በፍጥረት ሁሉ ላይ የሚገዛ ሉዓላዊ ጌታ ነው። ሁሉ ነገር ከእርሱ የተነሣ፣ በእርሱ የሚጸናና ለእርሱ የሆነ ነው። ከእርሱ እውቀት፣ ሥልጣንና ዓላማ ውጭ የሚሆን ምንም ነገር የለም። የእግዚአብሔር ሉዓላዊነት በእርሱ እንድንታመን፣ ዕቅዶቻችንን ለእርሱ እንድንሰጥና በፈቃዱ ታዛዥ ሆነን እንድንመላለስ ያሳስበል። ስለዚህ የሕይወታችን ሁኔታዎች ሁሉ በሉዓላዊው እግዚአብሔር እጅ እንዳሉና በእርሱ ላይ በመታመን መኖር እንደሚገባን ሁልጊዜ ልናስታውስ ያስፈልገናል።

- **ጸሎት**

በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፣ የሁሉ ነገር ፈጣሪና ገዢ የሆንህ ሉዓላዊ ጌታ አንተ ነህ። በሕይወቴ ውስጥ ባሉ ነገሮች ሁሉ ላይ ያለህን ሥልጣን እንዳውቅ አስተምረኝ። መንገዶችህና አደራረጎችህ ባልገቡኝ ጊዜያት እንኳን በጥበብህ እንድታመን እርዳኝ። በራሴ ማስተዋል ላይ የምመሠረትበትን ፍላጎት አስወግድልኝ፤ ለፍጹም ፈቃድህም ሙሉ በሙሉ እንድገዛ አስተምረኝ። መንግሥትህ ትምጣ፤ ፈቃድህም በሕይወቴ ይሁን። በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አሜን።

- **የአርምሞ ጥቅስ**

*“እግዚአብሔር ዙፋኑን በሰማይ አዘጋጀ፥ መንግሥቱም ሁሉን ትገዛለች።”*

*— መዝሙረ ዳዊት 103፥19 —*

## 2.4. እግዚአብሔር ትልቅ ነው!

በዚሁ መጽሐፍ መግቢያ ላይ በግልጽ ለማሳየት እንደተሞከረው እግዚአብሔርን ማን እንደሆነ ማወቅ ፈጽሞ ሊደረስበት የማይችል የሆነና ሰው ከውቅያኖስ ውስጥ ካለ ውሃ የሆነች ያክል ጠብታ እንደማንሳት ያክል ምናልባትም ደግሞ ከዚያም ያነሰ እውቀትን ብቻ የሚያውቅ እንደሆነ ይታወቃል። መጽሐፍ ቅዱስ በኢዮብ 11:7 ላይ እንደሚናገረው የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር ሊመረምር የሚችል ወይም ሁሉን የሚችል አምላክን ፈጽሞ ሊያውቅ የሚችል እንደሌለ እና ይህም እውቀት ከሰማይ ይልቅ ከፍ የሚል ደግሞም ከሲኦል ይልቅ የሚጠልቅ ሊደረስበት የማይችል ጉዳይ እንደሆነ የኢዮብ ወዳጅ የሆነው ሶፋር ይናገራል። በዚሁ ስፍራ ቀጥሎ እንደሚናገረው እግዚአብሔር እና የእግዚአብሔር ነገር ከምድር ይልቅ የሚረዝም ርዝመት እና ከባህርም ይልቅ የሚሰፋ ሰፊ ጉዳይ ነው።

የእግዚአብሔር ታላቅነት እና ክብር በሰው ቋንቋ ለመግለጽ እጅግ የሚያስቸግር የእርሱ ብቻ የሆነ ማንነት ነው። ለዚህም ይመስላል በዚሁ የኢዮብ መጽሐፍ ላይ ከኢዮብ ወዳጆች በኋላ መናገር የጀመረው አስተዋይ ብላቴና ኤሊሁ ስለ እግዚአብሔር ታላቅነት በርካታ ምዕራፎችን ከተናገረ በኋላ በ37ኛው ምዕራፍ 26ኛው ቁጥር ላይ እንዲህ ያለው *“እነሆ እግዚአብሔር ታላቅ ነው፣ እኛም አናውቀውም፣ የዘመኑም ቁጥር አይመረመርም።”* ዛሬ በመስተዋት በድንግዝግዝ እንደምናይ ነን ነገር ግን እርሱ ራሱ ለእኛ በተገለጠ በዚያን ጊዜ ፊት ለፊት እናየዋለን አሁን የምናውቀው በከፊል ነው በዚያን ጊዜ ግን እኛ ራሳችን ሙሉ በሙሉ የታወቅነውን ያህል የምናውቅ እንሆናለን።

*እግዚአብሔር እጅግ ታላቅ ነው።* ሰማይ ከሰማያት በላይ ያለ ሰማይ ይይዘው ዘንድ አይችልም። እርሱ የማይገኝበት እና የማይደርስበት ወይም ደግሞ እንደዚህ ሆኗል ብሎ ማንም በድንገት የሚነግረው እርሱ ያላወቀው አንዳች ነገር በምድር ወይም ደግሞ በሰማይ ብሎም ከምድር በታች ባለው አለም ውስጥ የለም። ከዚህም በላይ እጅግ በጣም ጥልቅ የሆነውን በሰው ልብ ውስጥ የተደበቀ የሰው ሃሳብን ጭምር የሚያውቅ ማስተዋሉ የማይመረመር ሁሉን ቻይ የሆነ የሚመስለውም አንዳች የሌላ ታላቅ አምላክ ነው። እግዚአብሔር ዘመኑ ይመረመር ዘንድ በዚህ ጊዜ መኖር ጀመረ የሚባልበት፣ በዚህ ጊዜ መግዛት አቁሞ ወይም ደክሞት እረፍት ወስዶ ነበር የሚባልበት ብሎም በዚህ ጊዜ

አስተዳደሩ እና ማስተዋሉ ያበቃል፣ ኃይሉም ይደክማል፣ እድሜውም ያረጃል የሚባልበት የጊዜ እና የቦታ ገደብ የማያውቀው በዘመናት የሸመገለ አምላክ ነው፡፡ እርሱ ጊዜን እና ቦታን የፈጠረ፣ ዘላለምን ወደ መኖር ያመጣ፣ ፍጥረትን ሁሉ በገዛ ማስተዋሉ በስፍራ በስፍራቸው ያስቀመጠ በቃሉም ደግፎ የያዛቸው እጅግ ታላቅ እና የከበረ አምላክ ነው፡፡

> “እርሱ ጊዜን እና ቦታን የፈጠረ፣ ዘላለምን ወደ መኖር ያመጣ፣ ፍጥረትን ሁሉ በገዛ ማስተዋሉ በስፍራ በስፍራቸው ያስቀመጠ በቃሉም ደግፎ የያዛቸው እጅግ ታላቅ እና የከበረ አምላክ ነው፡፡”

ሙሴ በዘዳግም መጽሐፍ የመጨረሻ ንግግሩ ለህዝቡ ለእስራኤል እንዲህ አለ፦ “አንተን ለመርዳት በሰማይ ላይ፣ በደመናትም ላይ በግርማው እንደሚገሰግስ እንደ እስራኤል አምላክ ያለ የለም፡፡” እግዚአብሔር ራሱን ሊገልጥላቸው ወድዶ ሊያዩት የሞከሩ ሁሉ ያዩትን ነገር በሰዎች ቃላት መግለጽ ከብዷቸው ሲቸገሩ እና እንደሞተ ሰው ሆነው ሲወድቁ፣ የተገለጠውንም የእግዚአብሔር ክብር ምሳሌ ፊት ለፊት ለማየት ሲቸገሩ አይተናል፡፡ ኢሳይያስ፣ ህዝቅኤል፣ ዳንኤል እና ሐዋርያው ዮሐንስ ለዚህ ጥሩ ማሳያዎች ናቸው፡፡ ይህ ታላቅ የሆነ አምላክ እግዚአብሔር በምስጋና የተፈራ ደግሞ ለሰው አዕምሮ የማይገቡ ድንቅና ተዓምራትን የሚያደርግ ማንም ሊያየው በማይችለው ብርሃን ውስጥ የሚገኝ አምላክ ነው፡፡

አምላኩን ከታናሽነቱ ጀምሮ በማወቅ ያደገው ብላቴናው ዳዊት በመዝሙረ ዳዊት ምዕራፍ 104 ላይ ሲነግረን ይህ ታላቅ አምላክ እጅግ ታላቅ እንደሆነ በመረዳት ለዚህም ታላቅነቱ ነፍሱ እግዚአብሔርን እንድትባርክ ይጠይቃታል፡፡ ይህንንም ከነፍስ የሆነ አክብሮት ለተገለጠለት አምላኩ ለማምጣት ምክንያት የሆነው አምላኩን ክብርና ግርማ ለብሶ፣ ብርሃንንም እንደ ልብስ ለብሶ፣ ሰማይን እንደ መጋረጃ ዘርግቶ ከላይ ሙሴ ለእስራኤል እንዳለው ሰረገላውን ደመና አድርጎ በነፋስ ክንፍ የሚሄድ በሰው አዕምሮ ለመረዳት የሚያዳግት ታላቅነት ያለው አምላክ መሆኑን መገንዘቡ ነበር፡፡ ለዚሁ ነው ኤሊሁ እግዚአብሔር ታላቅ ነው ብሎ እኛም እናውቀውም ያለው፡፡

ይህንን የእግዚአብሔርን ታላቅነት እና ግርማ በዙሪያው እንዲሆኑ ለራሱ ክብር ያዘጋጃቸው ዙፋኑን የሚጋርዱ ኪሩቤሎችና ሱራፌሎችም እንኳን በሙላት ሊያዩት የማይችሉት የቅድስናውና የንጽህናው ልክ፣ ስንፍና የሚከሳቸውን እነዚህኑ ፍጥረታቱን እርሱን ማየት እንዳይችሉ አድርጓቸው በክንፉቸው አካላቸውን እየሸፈኑ በፊቱ በታላቅ አክብሮት እንዲያገለግሉት አድርጓቸዋል። ይህ ታላቅ አምላክ ውኖችን በደመናዎች ውስጥ የሚያስር፣ ደመናውም ያለ እርሱ ፈቃድ እንዳያንጠባጥብ ሳይቀደድ የያዘውን ተሸክሞ የሚቆይለት፣ ወደሚወደውም ልኮ እንዲዘንብ የሚያደርገው፣ መብረቅን በመካከሉ በታላቅ ነጎድጓድ የሚያንጎዳጉድ፣ በረዶን ከመዝገቡ አውጥቶ ለምክርና ለፍርድ አብሮ የሚያዘንብ፣ ፍጥረታት ሁሉ የሚታዘዙለት በፍጥረቱ ሁሉ ላይ የሰለጠነ እጅግ ታላቅና የተፈራ አምላክ ነው። ገዥነትና መፈራት በእርሱ ዘንድ ናቸው፣ ለሰራዊቶቹ ቁጥር የላቸውም፣ ጨረቃ በፊቱ ብሩህ አይደለችም፣ ከዋክብቱም በፊቱ ንጹሃን አይደሉም። ከቁጥር እጅግ የሚበዙትን ከዋክብቱን በስም ይጠራቸዋል፣ ከእነርሱም አንድስ እንኳ ያለ እርሱ ፈቃድ አይጠፋም፣ የሰውን ፀጉር ቁጥር ሁሉ ያውቃል፣ በፊቱ ከእርሱ ማስተዋል የበለጠ አንዳችም ነገር የሌለው ታላቅ ነው።

ይህ ታላቅ አምላክ በሰው ቋንቋ እንደዚህ እና እንደዚያ ነው ተብሎ የሚገለጽበት ርዝመት፣ ወርድ እና ስፋት የሌለው በምንም አይነት መለኪያ የማይለካ፣ በየትኛውም አይነት ቋንቋ እና መግለጫ ሊገለጽ የማይችል ትንሽ ከሆነችው የሰው ልጅ አዕምሮ እጅግ የገዘፈ ታላቅ ነው። ይህ ጌታ ውኖችን በእፍኙ የሰፈረ፣ ሰማይንም በስንዝሩ የለካ፣ የምድርንም አፈር በመስፈሪያ ስብስቦ የያዘ፣ ተራሮችንም በሚዛን ኮረብቶችንም በሚዛኖች የመዘነ ያለ ማንም አማካሪነት እና ድጋፍ ብቻውን በፈቃዱ ምክር በገዛ ማስተዋሉ ፍጥረታትን ሁሉ የፈጠረ እና አስተካክሎ በስፍራቸው ያደረገ ሊመረመር የማይችል ታላቅ አምላክ ነው። በዚህ አምላክ ፊት አህዛብ በገንቦ እንዳለች ጠብታ በሚዛንም እንዳለ ትንሽ ትቢያ የሚቆጠሩ ናቸው።

እርሱ ብቻውን ምድርና ሰማያትን የሰራ ከምድርም ክበብ በላይ በዙፋን ላይ የሚቀመጥ የሆነ በምድር የሚኖሩ ሁሉ በፊቱ እንደ አንበጣ የሚሆኑለት ሰማያትን እንደ መጋረጃ የሚዘረጋ እንደ መኖሪያ ድንኳንም የሚተክላቸው ነው። ይህ የእግዚአብሔር ታላቅነት ፍጥረት ሁሉ ወደ መኖር ከመምጣቱ በፊት የጀመረ በፍጥረት ላይ ያልተመሰረተ

እና ያልተደገፈ በምንም አይነት ሁኔታ የማይናወጥ ጽኑ ታላቅነት ነው። በዚሁ የዘላለም ግርማውና ታላቅነቱ በዙፋኑ ላይ ለዘላለም ያለ ድካምና ያለ መታከት ማስተዋሉ ሳይመረመር ይኖራል። ታዲያ ይህ እጅግ ታላቅና የተፈራ አምላክ በማን ሊመሰል ወይም በምን ምሳሌ ሊገለጽ ይችላል? እርሱ ራሱ እንዳለ ይተካከለው ዘንድ በማን ሊመሰል ይችላል? ሙሴ ለእስራኤል እንዳለ በእርግጥ እንደ እግዚአብሔር ያለ ማንም የለም።

ከላይ የጠቀስናቸው ይህንን ታላቅ አምላክ በምሳሌ ለማየት እድል ያገኙ እንደ ኢሳይያስ፣ ዳንኤል፣ ዮሐንስ፣ ህዝቅኤል ወዘተ ያሉ ሁሉ ሰዎች ታዲያ የእግዚአብሔርን ክብር ምሳሌ ብቻ እንጂ ራሱን እግዚአብሔርን በግልጥ ያዩ እንዳልሆኑ እንመለከታለን። ይህም ማንም ሰው እግዚአብሔርን በተመለከተ አንድ የተወሰነ መልክን በአዕምሮው እንዳይመስል ብሎም ያንኑ መልክ በማናቸውም ቅርጽ እና ምሳሌ ለራሱ አዘጋጅቶ እንዳያመልክ ነው። ከላይ በዝርዝር ለመግለጽ እንደተሞከረው እግዚአብሔር በየትኛውም ፍጥረቱ በሙላት ሊታወቅ የማይቻልና እስካሁንም ድረስ በማንም ያልታየ ሲሆን በአባቱ እቅፍ ባለ አንድ ልጁ በኩል ለእኛ የተተረከና በመንፈሱ ለውስጥ ሰውነታችን የሚብራራ በልቦና አይኖቻችን በተገለጠልን መጠን የምንረዳው ታላቅ አምላክ ነው።

ከላይ የጠቀስናቸውም ይህንን የእግዚአብሔር ክብር ምሳሌ ለማየት የታደሉ ሰዎች ሁሉ ታዲያ ያዩትን ነገር ለእኛ ለመግለጽ *“እንደ”* በሚል ገላጭ ቃል ሰው የሚያውቃቸውን የተመለከቱትን ነገር በጥቂቱ ሊገልጹ የሚችሉ ፍጥረታዊ ነገሮች በማስከተል *“ይመስላል”* እያሉ ለመግለጽ ሲሞክሩ ይታያሉ። ይህም ማለት እንደ ሰው መልክ አምሳያ እንደ ነጭ የበግ ጠጉር ራስ፣ እንደ በረዶ ነጭ የራስ ጠጉር፣ እንደ እሳት ነበልባል አይን፣ በእሳት እንደ ነጠረ ናስ ያሉ እግሮች እና እንደ ብዙ ውሃ ያለ ድምጽ ወዘተ የሚሉ አገላለጾችን ተጠቅመው ስለፃፉልን ይህንን አይነት መልክ በአይነ ህሊናችን ስለን እርሱ እግዚአብሔር እንደሆነ መስለን እንድናመልከው እንኳ አይቻልም።

እስራኤላዊያን ከግብፅ ከወጡ በኋላ እግዚአብሔርን ለማወቅ ዳዴ እያሉ ባሉበት በዚያን ወቅት የነበሩበት የግብጽ አገር ህዝብ አማልክቶቻቸውን በሰሩላቸው ጣኦቶቻቸው በኩል ለማግኘት ቅርጽ ይሰሩ ስለነበር ሌሎች አማልክትን ቅርጽ ሰርተው ማምለክ ሳይጀምሩ በፊት በሲና ተራራ ላይ በከባድ ደመና ተገልጦ ምንም አይነት ተመሳሳይ የሌለው ታላቅ አምላክ እንደሆነ በመገለጡ እንዲያዩ ካደረገ በኋላ በዘፀዓት 20 ላይ ለህዝቡ ከግብጽ

ምድር ያወጣሁህ *"እግዚአብሔር አምላክህ እኔ ነኝ ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ በላይ በሰማይ ካለው በታችም በምድር ካለው ከምድርም በታች በውሃ ካለው ነገር የማናቸውንም ምሳሌ የተቀረፀውንም ምስል ለአንተ አታድርግ፣ አትስገድላቸው፣ አታምልካቸውም"* ብሎ ግልጽ በሆነ ቋንቋ ለሰሙት ድምጽ ቅርጽ ሰርተው እንዳያመልኩ በጥብቅ አዘዛቸው። ይሁን እንጂ ብዙ ሳይቆዩ ይሄው ታላቁ አምላካቸው እግዚአብሔር የበለጠ ቀርቦ በመካከላቸው ያድር ዘንድ ማደርያ ድንኳንን ይሰሩለት ዘንድ ዝርዝር ትዕዛዝን ለመስጠት ሙሴን ወደ ተራራው በጠራበት ወቅት ሳይመጣ እንደዘገየ ባዩ ጊዜ በግብጽ እንደለመዱት በሙሴ ቦታ እግዚአብሔርን የሚያገኙበት የአምላክ ምሳሌን በጥጃ ቅርጽ ሰርተው ከግብጽ አውጥቶናል ላሉት እግዚአብሔር በዓል ሊያደርጉ ተነሱ። ይህም ምን ያክል እግዚአብሔርን ያስቆጣው እንደነበር መጽሐፍ ቅዱስ በዘፀዓት 32 ላይ በዝርዝር ያሳያል።

እርሱ የአማልክት አምላክ፣ የጌቶች ጌታ፣ የነገስታት ንጉስ፣ የሃያላን ሁሉ ደግሞ ኃያል የሆነ ምንም አይነት ማስተያያ እና ምሳሌ የሌለው ብቻውን እውነተኛ አምላክ የሆነ ታላቅ ህያው ጌታ ነው። በዚህ ልክ በሰው አዕምሮ በየትኛውም መንገድ ምንም አይነት መልክ እና ቅርጽ ሊሰጠው ብሎም በአይነ ህሊና እንኳን የተሳለ አንድ ቅርጽ በልቡናችን የማይደረግለት ታላቅ አምላክ፣ እናውቀው ዘንድ ወድዶ ለቃሉ ስጋን አዘጋጅቶ በመካከላችን በማደር የመለኮት ሙላት የተገለጠበት፣ የክብሩ መንፀባርቅ እና የባህርይው ምሳሌ በሆነው አለማትንም በፈጠረበት አንድ ልጁ በኩል ራሱን ለእኛ ገለጠ። ይህም ምስጢር እጅግ ታላቅ ነውና ማንም እግዚአብሔርን በራሱ አቅም ማወቅ እንዳይችል በመዝሙረ ዳዊት ምዕራፍ 118፡27 ላይ *"እግዚአብሔር አምላክ ነው ለእኛም በራልን"* ተብሎ እንደተጻፈ ይሄን ከመታወቅ የሚያልፍ ታላቅ እና የተፈራ አምላክ እናውቀው ዘንድ በክርስቶስ ፊት የእግዚአብሔርን የክብሩን እውቀት ብርሃን እንዲሰጥ በልባችን ውስጥ ይበራ ዘንድ እግዚአብሔር ራሱ ብርሃን ይብራ ብሎ አበራልን።

"እርሱ የአማልክት አምላክ፣ የጌቶች ጌታ፣ የነገስታት ንጉስ፣ የሃያላን ሁሉ ደግሞ ኃያል የሆነ ምንም አይነት ማስተያያ እና ምሳሌ የሌለው ብቻውን እውነተኛ አምላክ የሆነ ታላቅ ህያው ጌታ ነው።"

በዚህም የተገለጠ የእግዚአብሔር ፀጋ በጨለማ የኖረ ህዝብ ብርሃንን አየ። እኛም ደግሞ ይህንን እድል ካገኙ ሁሉ ጋር በክርስቶስ በማመን እግዚአብሔርን በማወቅ እናድግ እና እርሱን እየመሰልን በታላቅ ፍርሃት እና አክብሮት በፊቱ እንመላለስ ዘንድ እርሱ አምላካችን ሆኖ እኛ ደግሞ ህዝቡ ሆነን ልንኖር ከድቅድቅ ጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃኑ ተሻገርን። *ክብር ለታላቅነቱ ይሁን!* ታዲያ ከዚህ ወዲያ በሰው ብልሃት የተፈጠረውን ተረት ሳንከተል አህዛብ አማልክት ብለው እንደሚያመልኳቸው ግዑዝ ጣዖታት የሆኑ አጋንንቶች ሳይሆን በነቃው መንፈሳችን ከመንፈሱ ጋር ኅብረትን በማድረግ፣ በቃሉ ውስጥ መልኩን ሳናቋርጥ በመፈለግ፣ የእርሱን ግርማ አይተን፣ የለበሰውን የምስጋናና የክብር መጎናፀፊያ ተመልክተን፣ ለታላቅነቱ በተገባ አክብሮት፣ በብዙም ፍርሃትና መንቀጥቀጥ፣ በተትረፈረፈ ሰላም እና ደስታ እንደ ልጆች ታላቅ ምሕረቱንና ቸርነቱን ታምነን በፀጋው ዙፋን ፊት እየቀረብን እናመልከዋለን።

*ክብሩ እጅግ ታላቅ ሲሆን ሳለ ማንንም ሳይንቅ በልጁ በኩል እኛ ስፈር መጥቶ ጨለማችንን ገፎ ብርሃንን ላበራልን እና ራሱን ለገለጠልን ጌታችንና አምላካችን እግዚአብሔር ምስጋና ይሁን! አሜን!*

"ይህ ታላቅ አምላክ ውኆችን በደመናዎች ውስጥ የሚያስር፣ ደመናውም ያለ እርሱ ፈቃድ እንዳያንጠባጥብ ሳይቀደድ የያዘውን ተሸክሞ የሚቆይለት፣ ወደሚወደውም ልኮ እንዲዘንብ የሚያደርገው፣ መብረቅን በመካከሉ በታላቅ ነጎድጓድ የሚያንጎዳጉድ፣ በረዶን ከመዝገቡ አውጥቶ ለምክርና ለፍርድ አብሮ የሚያዘንብ፣ ፍጥረታት ሁሉ የሚታዘዙለት በፍጥረቱ ሁሉ ላይ የሰለጠነ እጅግ ታላቅና የተፈራ አምላክ ነው። ገዥነትና መፈራት በእርሱ ዘንድ ናቸው፣ ለሰራዊቶቹ ቁጥር የላቸውም፣ ጨረቃ በፊቱ ብሩህ አይደለችም፣ ከዋክብቱም በፊቱ ንጹሃን አይደሉም። ከቁጥር እጅግ የሚበዙትን ከዋክብቱን በስም ይጠራቸዋል፣ ከእነርሱም አንድስ እንኳ ያለ እርሱ ፈቃድ አይጠፉም፣ የሰውን ፀጉር ቁጥር ሁሉ ያውቃል፣ በፊቱ ከእርሱ ማስተዋል የበለጠ አንዳችም ነገር የሌለው ታላቅ ነው።"

## የማስተንተኛ ጥያቄዎች

1. የእግዚአብሔር ታላቅነት ስለ ማንነቱ ምን አስተማረህ?
2. የሰው ልጅ አስተሳሰብ የእግዚአብሔርን ታላቅነት ሙሉ በሙሉ ሊረዳ የማይችለው ለምንድን ነው?
3. የእግዚአብሔር ታላቅነት እርሱን በምናመልክበትና በምንታመንበት መንገድ ላይ ምን ለውጥ ሊያመጣ ይገባል?

## አሰላስል

እግዚአብሔር ከሰው ልጅ አስተሳሰብና ምናብ ወሰን በላይ የሆነ ፍጹም ታላቅ አምላክ ነው። ታላቅነቱም በኃይሉ፣ በጥበቡ፣ በቅድስናውና በክብሩ ይገለጣል። ነገር ግን የእግዚአብሔር ታላቅነት ከእርሱ እንድንርቅ የሚያደርገን አይደለም፤ ይልቁንም ወደ ጥልቅ አምልኮ፣ ትሕትናና ክብር እንድንገባ ይመራናል። ከፍጥረት ሁሉ በላይ የሆነው እርሱ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን ለእኛ በመግለጥ ከእርሱ ጋር በኅብረት እንድንኖር ጠርቶናል። ስለዚህ ታላቅነቱን በመረዳት በፊቱ በትሕትና መመላለስና በክብር ማምለክ እንደሚገባን ሁልጊዜ ልናስታውስ ያስፈልገናል።

## ጸሎት

በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፣ ታላቅነትህ የማይመረመርና ክብርህ ፍጥረትን ሁሉ የሚሞላ ታላቅና የሚያስፈራ አምላክ አንተ ነህ። አንተ እውነት እንደሆንህ እንዳውቅ ብሎም ስለ ማንነትህ ያለኝን የተገደበ አስተሳሰብ አልፌ አንተን በማወቅ ወደ አንተ መገስገስ እንድችል እርዳኝ። በክብር እንዳመልክህ፣ በኃይልህ እንድታመንና በፊትህ በትሕትና እንድመላለስ አግዘኝ። በልጅህ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በመንፈስህ ራስህን ስለገለጥህልኝ አመሰግንሃለሁ።

በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አሜን።

## የአርምሞ ጥቅስ

*“እግዚአብሔር ታላቅ ነው እጅግም የተመሰገነ ነው፤ ለታላቅነቱም ፍጻሜ የለውም።”*

*— መዝሙረ ዳዊት 145፥3 —*

## 2.5. እግዚአብሔር ኃያል ነው!

ኃይል የአንድ አካል የሚፈልገውን ነገር የማድረግ የተገለጠ አቅም ነው። በዚህ ኃይልም በተገለጠ ስልጣን እንዲሁም ለዚሁ በሚመጥን ሁኔታ ኃይሉን የሚገልጥበት በቂ የማድረጊያ መንገዶች ያሉት በኃይሉ ከሌሎች በዙሪያው ከሚገኙ በልጦ የተገኘ ሆኖ እንዲገለጥ ያስፈልገዋል። መቼም የእግዚአብሔር ኃያልነት በየትኛውም አይነት የሰው ቃል በጥቂቱ እንኳን ሊገለጽ የሚችል አይደለም።

እግዚአብሔር በተለይም በብሉይ ኪዳን ለአብርሃም እና ሌሎች የእምነት አባቶች ራሱን የገለጠበት ስሙ *"ኤልሻዳይ"* የሚል ስም ነው። ይህም ስም ሁሉን ቻይ /Almighty/ ማለት ሲሆን በዚህም እግዚአብሔር ማድረግ ፈልጎ እንዳያደርግ የሚከለክለው ሌላ ተመጣጣኝ ኃይል ሳይኖር የሚፈልገውን ሁሉ በሚፈልገው መንገድ ጊዜና ሰዓት ማድረግ የሚችልበት ከሰው እሳቤ ያለፈ ኃይልና ሁለንተናዊ ብቃት ያለው መሆኑን የሚገልጽ ነው። ኢሳይያስ በትንቢቱ የዘጠነኛው ምዕራፍ ላይ አንዳች ከሰው አዕምሮ ያለፈ መገለጥን በዘመኑ ለህዝቡ ይገልጣል። ይህም መገለጥ ስለ አንድ ህጻን መወለድ የሚተርክ ሲሆን ይህም ህጻን ወንድ ልጅ እንደሆነና አለቅነት በጫንቃው ላይ እንደሚሆን ስሙም ኃያል አምላክ እንደሆነ ይናገራል። በዚሁ ትንቢቱ አያይዞ ይህ ህጻን የዘላለም አባት እንደሆነም ጨምሮ ይመሰክራል። ይህ ንግግር በዘመኑ አብረውት ለሚገኙ እስራኤላዊያን ብሎም ዛሬም ጭምር ይህንን ትንቢት ለምናነብ ለእኛ ለሁላችን በቅጡ እንኳን ለመረዳት እጅግ አደጋች የሆነ ታላቅ ምስጢር ነው። ለዚህም ይመስላል ስለዚህ የሚወለድ ህጻን ጨምሮ በምዕራፍ 53 ሲተነትን *"የሰማነውን ማን አምኗል?"* የእግዚአብሔርስ ክንድ ለማን ተገልጧል ብሎ አምላክ ሰው ሊሆን ያለበትን ሁኔታ የሚተርከው።

ይህ ኃያል አምላክ የሚለው ቃል ለአንድ እስራኤላዊ ብሎም እስራኤል ከግብጽ በወጣበት ወቅት ለነበሩ ግብፃዊያን እና በዙሪያው ላሉ ከነዓናዊያን ደግሞም በዘመናት መካከል ይህችን ታላቅ እጅ ስትሰራና ስትንቀሳቀስ ለተመለከቱ የአህዛብ ነገስታት ሁሉ እንዲሁ ተራ ከሆነ ቃል ያለፈ ጥልቅ ትርጉም አለው። ይህ ኃያል አምላክ የሚለው ማንነቱ ህዝቡ ለሆኑት በቅርበት እርሱን ለማወቅ እድል ያገኙ እስራኤላዊያን ትርጉሙ ብዙ ሲሆን በዚህም ኃይሉ ሌላ ማንም በሰማይ ወይም በምድር የሚገኝ አካል ሊያደርገው ቀርቶ

ፈጽሞ ሊያስበው እንኳን የሚያዳግትን ነገር አድርጓል። የኤርትራ ባህር ተከፍሎ እንደ ግድግዳ የቆመው፣ ዮርዳኖስ በህዝቡ ፊት ተከፍሎ ርቆ በአዳም ከተማ የተከመረው፣ ህዝቡ ነገስታትን ፈጽሞ ይመታና ያሸንፍ ዘንድ ፀሃይ የቆመው፣ በበረዶ ድንጋይ ጠላቶቹን የጨረሰው፣ ምድር ተሰንጥቃ የሚቃወሙትን እንድትውጥ ያደረገው፣ መናን ከሰማይ በየቀኑ ያዘነበው፣ የህዝቡ ጫማና ልብስ እንዳያልቅ የከለከለው ወዘተ ተገልጦ ለህዝቡ የታየ ከእውቀት በዘለለ በተገለጠ ሁኔታ ህዝቡ እለት እለት ይህንን ኃይል ይለማመድ ዘንድ ቀን በደመና፣ ሌሊት ደግሞ በእሳት አምድ አብሮት ሆኖ ያለማመደው ኃይሉ ነው። ይሄው ኃያል አምላክ እስራኤልን ከግብጽ ባወጣ ወቅት ለህዝቡ ራሱን ሊገልጥ በሲና ተራራ ላይ በወረደ ጊዜ የሲና ተራራ ምን ያክል እንደ ጨሰና እንደተናወጠ ብሎም እንደተንቀጠቀጠ ይህ ህዝብ በዚያን ወቅት ምንኛ መደንገጥ እንደደነገጠ ለዚህም ኃይል ተገቢ የሆነን ፍርሃት በመፍራት እግዚአብሔር አይናገረን በእርሱ ፋንታ አንተ ተናገረን ብሎ ሙሴን እንደለመነ ይታወቃል።

የእግዚአብሔር ኃያልነት ዋናው ፍጥረቱን የሚያስተዳድርበት እርሱን የሚመስል ሌላ ሳይኖር ብቻውን ሉዓላዊ በሆነ ታላቅነት የተገኘበት ገደብ አልባ አቅሙ ነው። ይህንን ኃይሉን በውል ያልተረዱ በዘመናት መካከል ትዕግስቱን የተፈታተኑ ሁሉ በዚህ በጥቂቱ በተገለጠ አቅሙ ከወደቁበት እንዳይነሱ ሆነው ሲደቁ ተመልክተናል። ለዚህም አይነተኛው ማሳያ መጀመሪያ ከከፍታው ላይ የተወረወረው ዲያብሎስ ሲሆን በዚህም እግዚአብሔር በኃይሉ ላይ ሊበረታ የሚሞክርን ሁሉ ዛሬም እንዴት በፀናች እጁ ከባድ ቅጣትን እንደሚቀጣ ህያው ማስታወሻ ሆኖ የሚታይ እውነት ነው።

በኃይሉ ሊበረታና ዙፋኑን ከእግዚአብሔር ዙፋን በላይ ሊያደርግ ፈልጎ የመንፈቅለ መንግስት ሙከራን ያሰበው ቀድሞ ከፍጥረቱ በእግዚአብሔር ፊት የሚጋርድ ኪሩብ ለመሆን የተሰራው የዝማሬ አገልግሎት አለቃው ሉሲፈር ዳግም ላይነሳ ከነበረበት ከፍታ ወደ ታችኛው ጥልቅ በዚሁ የተገለጠ

“የእግዚአብሔር ኃያልነት ዋናው ፍጥረቱን የሚያስተዳድርበት እርሱን የሚመስል ሌላ ሳይኖር ብቻውን ሉዓላዊ በሆነ ታላቅነት የተገኘበት ገደብ አልባ አቅሙ ነው።”

የእግዚአብሔር አቅም ከተከታዮቹ ሁሉ ጋር ተጣለ። ከዚህም ጊዜ አንስቶ ከሰማይና ምድር መፈጠር በኋላ በምድር ላይ ይኖሩ ዘንድ የተፈጠሩ የሰው ልጆች ይህንን በፍጥረታት ሁሉ ላይ በሉዓላዊ ስልጣኑ የሚገዛውን ታላቅና ኃያል የተፈራም አምላክ በውል ባልተረዱበትና ለዚህ ኃይል ላለመገዛት በሞከሩበት ጊዜ ሁሉ ይህችው የፀናች የእግዚአብሔር እጅ ደጋግማ ተገልጣ ብዙ ድንቅንና ተዓምራትን አሳይታናለች።

የባቢሎን ግንብ መፍረስና የኢያሪኮ ግንብ በጩኸት መውደቅ፣ እግዚአብሔር የሰው ልጅ በምድር ላይ ተሰብስቦ የሚሰራው የትኛውም አይነት ስሙን ለማስጠራት የገነባው አቅሙ በዚህ የእግዚአብሔር ኃይል ፊት ምን ያክል ምናምንቴና ደካማ እንደሆነ የሚገልጥ ማሳያ ነው። እግዚአብሔር በየትኛውም ሁኔታ ይህንን ኃይሉን ሊገዳደር ብሎም ሉዓላዊ የገዥነት ስልጣኑን ሊጋፋ፣ ለዚህም አምላክነቱ ተገቢውን ክብርና መታዘዝ ሊያሳይ ባልወደደ ሁሉ ላይ ከዚህ ትልቅ ኃይሉ እጅግ በጣም ጥቂቷን ብቻ ገልጦ ታላቅ ነገርን ያደርጋል።

የግብፁ ንጉስ ፈርዖን ለዚህ አይነተኛው ማሳያ ሲሆን እስራኤልን እንዲለቅ ተነግሮት ለዚህ የአምላክ ቃል ለመታዘዝ ፈቃደኛ አለመሆኑ ብሎም ልቡን ማደንደኑ በኩሩን እስከማጣት በደረሰ መልኩ ተከታትለው በአገሪቱ ሁሉ ላይ በተከሰቱ ከፍተኛ መቅሰፍቶች እግዚአብሔርን በታላቅ ኃይሉ እንዲገለጥ ያደረጉት ነበሩ። በዚህም የግብፅን አማልክት ፈጽሞ ቀጥቶ እና ከንቱ አድርጎ ህዝቡን በታላቅ ክንዱ በጸናችም እጅ ከግብጽ እንዳወጣ ተከትሎም በመንገዶቻቸው ሁሉ የተገለጠችው ይህች የእግዚአብሔር እጅ ለመታዘዝ እምቢ ያለውን ፈርዖንና የተመረጠውን የግብጽ ፈረስና ፈረሰኛ ሁሉ በኤርትራ ባህር እንዳሰጠመ ይታያል። ይህም የተገለጠ ታላቅ ኃይል ከግብፃዊያን አልፎ በወቅቱ በዚያ ምድር ለሚገኙ ከነዓናዊያን ሁሉ የተገለጠ ፍጥረትን በዚህ ኃያል አምላክ ፊት በአክብሮትና በፍርሃት እንዲንቀጠቀጥ ያደረገ በታናሽ ህዝብ መካከል የታየ የታላቅ አምላክ ታላቅ ኃይል ነበር። ይህም ኃይል ይህንን ህዝብ ማንም ሳይቋቋመው ርስቱን እንዲወርስና ተፈርቶ እንዲኖር አድርጎት ኖሯል።

እግዚአብሔር በዚሁ ታላቅ ኃይሉና የማይመረመር ማስተዋሉ ፍጥረትን ሁሉ የፈጠረና በስፍራቸው ያስቀመጠ ሲሆን ዛሬም ፍጥረቱ የዚህን ታላቅና የተፈራ ኃያል አምላክ ማንነት በውል ሳይረዳ ለከንቱነት ተላልፎ ተሰጥቶ በምልልሱ ከዚህ ብርቱ የሆነ

አምላክ ጋር ሲተላለፍ ይታያል። ይህ ኃያል የሆነ ጌታ የአማልክት ሁሉ አምላክና የነገስታት ሁሉ ንጉስ፣ የሃያላንም ደግሞ ኃያል የሆነ የመጨረሻ ኃይል ነው። በዘመናት መካከል ይህንኑ ማንነቱን ለማስረገጥ የሰው ልጆች አማልክት ሊያደርጓቸው ቀርፀው ሰርተው ሊያመልኳቸው የወደዱ አማልክትን ሁሉ ሲያደቅ ታይቷል።

በእስራኤላዊያን አለመታዘዝ ምክንያት ተማርኮ በመንደራቸው የተገኘው የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታቦት አምላካቸውን ዳጎንን በመቅደሱ ውስጥ አሰግዶ ደግሞም ሰባብሮ ከንቱ ካደረገ በኋላ ይህንኑ ግዑዝ አምላክ አምላካቸው አድርገው የሚያመልኩ ፍልስጤማዊያን ደግመው በዚሁ በአዛጦን በሚገኝ የዳጎን መድረክ እግራቸው እንዳይረግጥ አድርጎ እጁን በዚሁ ህዝብ ላይ በኃይሉ በመግለጥ የሚያጠፋውን አጥፍቶ የቀረውን ደግሞ በእባጭ በመታ ጊዜ አዛጦንና አስቀሎናን ጨምሮ ህዝቡን ሁሉ በፍርሃት ያስደነገጠ፣ በመቅሰፍት የገደለ፣ በእባጭም የመታ የልዑል አምላክ ኃይል ሲሆን በዚህም ምክንያት ይህንን አምላክ እንደፈሩና እንዳከበሩ ብሎም በተገለጠው ታላቅ ኃይልና በደረሰባቸው ታላቅ ችግር ምክንያት የከተማይቱ ዋይታ እስከ ሰማይ የወጣ እንደነበር መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል።

መጽሐፍ ቅዱስ በ1ኛ ሳሙኤል 2፡1□ ላይ እንደሚናገረው በእርግጥ ከእግዚአብሔር ጋር የሚጣሉ ይደቅቃሉ ይህንንም ለማድረግ እግዚአብሔር ኃይሉን ለመግለጥ የእጁ ስራ የሆነውን የትኛውንም ፍጥረት ይጠቀማል። በዚሁ ታላቅ ኃይሉ እጆቹን በብርሃን ይሰውራል በጠላቶቹም ላይ ይወጣ ዘንድ ያዘዋል፣ የነጎድጓድ ድምጽ ስለ እርሱ ይናገራል፣ ከስፍራውም ይንቀሳቀሳል ከአፉም የሚወጣውን ጉርምርምታ ያሰማል፣ በግርማውም ድምጽ ያንጎዳጉዳል እኛም የማናስተውለውን ታላቅ ነገር ያደርጋል። በረዶውንና ውሽንፍሩን ብርቱንም ዝናብ በምድር ላይ ውደቁ ይላል፣ የውሃውንም ሙላት በደመና ላይ ይጭናል፣ የብርሃኑንም ደመና ይበታትናል፣ ለተግሳጽ ወይም ለምድሩ አልያም ለምህረት ቢሆን ሰው በሚኖርበት አለም ላይ ያዘዘውን ሁሉ ያደርግ ዘንድ ፈቃዱ ወደ መራችው በኃይሉ ያዞራቸዋል። ይህ አምላክ በኃይሉ ለማዕበልና ለወጀቡ ገደብን ያደርጋል፣ ባህርን ይከፍላል፣ ሰአትን /ጥላን/ ወደ ኋላ ይመለሳል፣ ሙታንን ያናግራል፣ ማዕበልና ወጀብን ያዛል፣ በማዕበል ላይ ይራመዳል ወዘተ.... ሌላ የሚመስለው ወይም

የሚስተካከለው የሌለ የኃይሉም ታላቅነት ከመታወቅ ያለፈ እጅግ የተፈራ ኃያል አምላክ ነው፡፡

ይህንን የእግዚአብሔር ኃይል በየዘመናቱ ለመገዳደር የሚያስቡት በጊዜያቸው ታላቅነትን እርሱ ራሱ የነገስታቱ ንጉስ የሆነው የስልጣን ሁሉ ባለቤትና ምንጭ ስልጣንን ብሎም ብልጽግናን አትረፍርፎ የሚሰጣቸው ነገስታትና ባለፀጎች ናቸው፡፡ በወቅቱ እጃቸው ላይ የተገኘው ምንጩ እግዚአብሔር የሆነ ሃይላቸውና ብልጽግናቸው ሲያታልላቸው በራሳቸው አቅምና ኃይል የሆኑትን የሆኑ በመሰላቸው ጊዜ ሁሉ አንደበታቸውን በዚህ ኃያል አምላክ ላይ ባላቀቁ ጊዜ እግዚአብሔር እርሱ ማን እንደሆነ ያውቁ ዘንድ ስሙን ሊያከብር በኃይሉ ሲያናንጎዳጉድ አይተናል፡፡

ራሱን አምላክ ያደረገው ስልጣንና ብልጽግናን እግዚአብሔር አትረፍርፎ ያበዛለት በዲያብሎስ የተመሰለው የጢሮስ ንጉስ፣ በታላቅነቱና በብልጽግናው ልቡ የተኩራራው የባቢሎን ገዥ፣ አምላክ ነው እንጂ ሰው አይደለም የተባለው ሔሮድስ፣ ከፈረስና ፈረሰኞቹ ጋር በኤርትራ ባህር የሰጠመው ፈርዖን እና የመሳሰሉት ለዚህ አይነተኛ ማሳያዎች ናቸው፡፡ ታዲያ በእንደዚህ አይነት መልኩ ኃይሉን ሊገዳደሩ በሞከሩ ጊዜ ሁሉ በአንፃሩ የተገለጠችው የእግዚአብሔር እጅ እንደ አንድ "ተራ" ሰው ሁሉንም ለከንቱ ነገር ተላልፈው እንዲሰጡ ሲያደርጋቸው፣ አንዳንዶቹን እንደ እንስሳ ከዙፋናቸው አውርዶ በምድረ በዳ ሳር ሲያስግጣቸውና ማስተዋላቸውን ወስዶ እንዲቅበዘበዙ ሲያደርጋቸው፣ ሲያልፍም በትል ተበልተው እንዲሞቱ ሲያደርግ ተመልክተናል፡፡

የእግዚአብሔር ኃይል እንደ ታላቅነቱ ሁሉ እንደዚህ ነው ተብሎ ቁጥር የሚደረግ ብሎም ገደብ የሚበጅለት ጉዳይ አይደለም፡፡ የተራራ አምላክ ብቻ አይደለም፣ በሸለቆም ድል የእርሱ ነው፡፡ በበትር ባህርን ከከፈለ አለፍ ብሎ የካህናቱን እግር ውሃ አስነክቶ ታላቅን ጎርፍ ከመፍሰስ አቁሞ ርቆ እንዲከመር ያደርጋል፡፡ ሲፈልግ በሰው ጩኸት ታላቅ ግንብን ያፈራርሳል፣ ደስ ሲለው ፀሃይን ከጉዞዋ አስቁሞ በጠላቶቹ ላይ የበረዶ ድንጋይ ያዘንባል፡፡ *እግዚአብሔር ታላቅ ነው እኛም አናውቀውም ደግሞ ኃያል ነው ግን ማንንም አይንቅም፡፡* እርሱም በማስተዋል ብርታት ኃያል ነው፡፡

ነገስታት እንደ ሌሎች አማልክት ግዑዝ በመሰላቸውና የእርሱን ስም በናቁ ጊዜ ሁሉ ከፍተኛ ጉዳትን ሲያስተናግዱ ተመልክተናል። ነገስታትን እና አማልክቶቻቸውን ሁሉ እየሰባበረ ይሁዳ የደረሰው ሰናክሬም በህያው አምላክ ላይ የተናገረው የድፍረት ንግግር ሩጫውን ገትቶ ወደ አገሩ እንዲመለስ ብሎም እርሱ ራሱ በገዛ ልጆቹ እጅ እንዲገደልና 185,000 ወታደሮችን በአንድ ሌሊት እንዲያጣ አድርጎት አይተናል። እግዚአብሔር በዛችው ጠንካራ እጁ ሌዋታንን ይቀጣል፣ የባህሩን ዘንዶ ይገድላል፣ ነገስታትን ያነግሳል ደግሞ ሲያሻው ያወርዳል፣ ብልጽግናና ገናናነትን ለሰዎች ይሰጣል ደግሞም ይቀማል፣ ምድርን በኃይሉ መስርቷል፣ አለምን በጥበቡ ሰርቷል፣ ሰማያትን በማስተዋሉ አጽንቷል እግዚአብሔር ሲነሳ የማይደነግጥ መግቢያ ቀዳዳና መሸሸጊያ ፈልጎ የማያጣ ደግሞ በየትኛውም መንገድ ከእርሱ ሊደበቅና ሊያመልጥ የሚችል ምንም ኃይል የለም።

ወደ ሰማይ ቢወጣ እርሱ በዚያ አለ ደግሞ ወደ ታች ወደ ሲኦል እንኳን ቢወረድ እርሱ በዚያም አለ። የእግዚአብሔር እጅ በኃይሉ የወደደችውን በፈለገው ስፍራ፣ ሰአትና ሁኔታ ያለ ገደብ እና ከልካይ የልቡን ሃሳብ ታደርጋለች። የትኛውም የሰዎች እና የዲያብሎስ ኃይል ከእግዚአብሔር ይልቅ የበረታ በመሰለበት ጊዜ ሁሉ በእርግጥ እግዚአብሔር የሚታገስ ስለሆነ እንጂ የማይደክም እጁም ከማዳን ያላጠረች ለዘላለም የሃያላን ኃያል እርሱ ነው።

> “የእግዚአብሔር እጅ በሃይሉ የወደደችውን በፈለገው ስፍራ፣ ሰአትና ሁኔታ ያለ ገደብ እና ከልካይ የልቡን ሃሳብ ታደርጋለች።”

መጽሐፍ ቅዱስ በመዝሙረ ዳዊት ምዕራፍ 68 ላይ ሲናገር እግዚአብሔር በተነሳ ጊዜ ጠላቶቹ እንዴት እንደሚበተኑ ይነግረናል። የሚጠሉት ሁሉ እርሱ ሲነሳ ከፊቱ እንደሚሸሹ ይኸውም ጢስ እንደሚበንን ወይም ሰም በእሳት ፊት እንደሚቀልጥ እንደዛው በሆነ መንገድ ፈጽመው እንደሚበንኑና እንደሚቀልጡ ይናገራል። በዚሁ ምዕራፍ ሃጢአተኞችና በእግዚአብሔር ላይ ራሳቸውን ያገዘፉ ነገስታትና ህዝብ ሁሉ በአንድነት በፊቱ እንዴት ለዚህ ታላቅነቱና ኃይሉ እንደሚገዙ ብሎም እንደሚሰግዱ ለዚህም የተገባ ለታላቅ ግርማውና ክብሩ የሚሆን ምስጋናን የምድር ነገስታት ሁሉ ለእግዚአብሔር እንደተቀኙ

ለጌታም እንደ ዘመሩ ይታያል። የአለም አቅም ሁሉ ቢሰበሰብና ፍጥረት ሁሉ አንድ ላይ ተስማምቶ ቢያብርና በእግዚአብሔር ላይ በአንድነት ቢነሳ የእግዚአብሔር ኃይል ከዚህም ሁሉ ይልቅ እጅግ ትበረታለች።

ይህንኑ ሁኔታ መጽሐፍ ቅዱስ በዮሐንስ ራዕይ 19 ላይ ሲነግረን ቀድሞ ያመፀውን ከእግዚአብሔር ፊት የተጣለውን ዲያብሎስንና ሀሳቡን የገዙ የምድር ነገስታትና ህዝባቸውን ሁሉ በአንድነት በጉን ሊወጉ በመጡ ጊዜ ከአፉ በሚወጣ ቃል ብቻ ሁሉን እንዳጠፋቸው እንመለከታለን። ይህም ዛሬ በእውነት ያልደረስንበት ነገር ግን በጊዜውና በሰዓቱ በእርግጥ የሚከናወን በመንፈስ አለም የተወሰነ በአሁናዊ ሁናቴ እውነተኛ የሆነ የዘመን ፍፃሜና መደምደሚያ ነው።

የእግዚአብሔር እጅ ዛሬም ከማዳን አላጠረችም፣ ያው የቀድሞው ኃይሉና የማስተዋሉ ብርታት ዛሬም መጀመሪያ ፍጥረትን በፈጠረበት ከዚያም በኋላ በዘመናት መካከል ፍጥረቱን ባስተዳደረበት በዚያው መጠን ዛሬም ኃያል እንደሆነ ሳይለወጥ አለ። የእግዚአብሔር ኃይል ባለተገለጠበት ወይም እኛ ባልተረዳንበት ጊዜ ሁሉ ኃይሉ በእኛ መካከል እንዳይገለጥ የከለከለ ሀጢአትና አመፃ በመካከላችን ስላለ ብሎም እግዚአብሔር ታላቅ ማዳኑን በመከላከላችን እንዳይገልጥ ኃይሉንም እንዳያሳይ ስለከለከልነው እንጂ እርሱ በዘመናት ብዛት እርጅና ይዞትና ደክሞ ወይም ታክቶ እንዳልሆነ ግልጽ ነው።

እግዚአብሔር አህዛብ የእርሱን ኃይል ያውቁና ያከብሩት ዘንድ በታናናሽና ምናምንቴ ነገር የአለምን ጥበብና ታላቅ ነገር ለማዋረድ ይንቀሳቀሳል። በሽታ፣ ቸነፈር፣ አንበጣ፣ ድርቅ፣ ርሃብ ወዘተ በቅርብ ጊዜ አለማችን ያስተናገደችው ኮሮናን ጨምሮ እንኳን በአይን በማይታዩ ቫይረሶች አማካኝነት አለምን ሁሉ ያስደነገጠበትን የተገለጠ ኃይሉን ተመልክተናል። (Organization, 2020)

> “እግዚአብሔር አህዛብ የእርሱን ኃይል ያውቁና ያከብሩት ዘንድ በታናናሽና ምናምንቴ ነገር የአለምን ጥበብና ታላቅ ነገር ለማዋረድ ይንቀሳቀሳል።”

እግዚአብሔር ሃሳቡ ከሃሳባችን ሰማይ ከምድር ከፍ እንደሚል ከፍ ያለ የሆነ የኃይሉ ታላቅነትም ከአዕምሮአችን ፈጽሞ ያለፈ ታላቅ አምላክ ነው። ይህንንም

የኃይሉን ታላቅነትና ብርታት አለቅነትንና ስልጣናትን ሁሉ በመስቀሉ ድል ነስቶ በሞቱ ሁሉን አሸንፎ ስልጣንን በሰማይና በምድር ከምድርም በታች ባለ ሁሉ ላይ ተቀብሎ ከስም ሁሉ በላይ ያለውን ስም በአሁኑና ሊመጣ ባለው አለም ሳይቀር ይዞ በተነሳ ጊዜ የተገለጠ የእግዚአብሔር ሞኝነት እጅግ ከተጠበበ የሰው ጥበብ ይልቅ እንደሚጠበብ ያየንበት ከሰው ውድቀት ጀምሮ በተፈጸመ ሀጢአት በፍጥረት ሁሉ ላይ የተላለፈን ፍርድ በመስቀሉ የደመሰሰበት ልጆችንም ለራሱ ያደረገበት የጨለማን ስልጣን የዲያብሎስንም ስራ ባፈረሰ ጊዜ ገልጦ አሳይቷል።

ኢሳይያስ በትንቢቱ ከምዕራፍ 2፡19 ጀምሮ ባለው ክፍል እንደሚናገረው እግዚአብሔር ምድርን ያናውጥ ዘንድ በተነሳ ጊዜ ሰዎች ከማስደንገጡና ከግርማው ክብር የተነሳ ወደ ድንጋይ ዋሻና ወደ ምድር ንቃቃት ውስጥ ይገባሉ፣ አማልክቶቻቸውንም ይጥላሉ በዚያም ቀን እግዚአብሔር ብቻውን ከፍ ከፍ ይላል ብሎ እስትንፋሱ በአፍንጫው ያለበትን ሰው ተውት እርሱ ስለምን ይቆጠራል ብሎ ሰው በእግዚአብሔር ፊት እንዴት ታናሽ እንደሆነ ይናገራል። እግዚአብሔር እጅግ ኃያል ነው ነገር ግን ማንንም አይንቅም።

> “የአለም አቅም ሁሉ ቢሰበሰብና ፍጥረት ሁሉ አንድ ላይ ተስማምቶ ቢያብርና በእግዚአብሔር ላይ በአንድነት ቢነሳ የእግዚአብሔር ኃይል ከዚህም ሁሉ ይልቅ እጅግ ትበረታለች።”

## የማስተንተኛ ጥያቄዎች

1. ሁሉን የሚችለው የእግዚአብሔር ኃይል ስለ ማንነቱ ምን ያስተምርሃል?
2. ከሁሉን ቻዩ እግዚአብሔር ኃይል በላይ የሆነ የሚያስፈራህ ነገር ምንድን ነው?
3. ዛሬ በሕይወትህ ውስጥ በየትኛው ጉዳይ የእግዚአብሔርን ኃይል ይበልጥ መታመን ያስፈልግሃል?

## አሰላስል

እግዚአብሔር ሁሉን የሚችል አምላክ ነው። ኃይሉን ሊገድብ ወይም ሊቃወም የሚችል ማንም የለም። በሰማይም ሆነ በምድር ያለው ፍጥረት ሁሉ በእርሱ ኃይልና ሥልጣን ይኖራል፤ ለእርሱም የሚያስቸግር እርሱም አቃተኝ የሚለው አንዳች ነገር የለም። ይህን እውነት ስናውቅ በራሳችን ጥንካሬ ሳይሆን በእግዚአብሔር ኃይል መታመንን እንማራለን። ፈተና፣ መከራ፣ ወይም የማይቻል የሚመስል ሁኔታ ቢገጥመንም፣ ለሁሉን ቻዩ አምላክ የማይቻል ነገር እንደሌለ እናስታውሳለን። ስለዚህ ሕይወታችንን በሙሉ ለእርሱ አሳልፈን በመስጠት በእምነት ልንመላለስ እንደሚገባ ሁልጊዜ ልናስታውስ ያስፈልገናል።

## ጸሎት

በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፣ ሁሉን የምትችል አምላክ ስለሆንህ እናመሰግንሃለን። ከኃይልህ የሚበልጥ ኃይል እንደሌለ ልቤ ሁልጊዜ እንዲያምን እርዳኝ። በችግርና በፈተና ጊዜ በራሴ ሳልታመን በአንተ ኃይል እንድታመን አስተምረኝ። ለአንተ የማይቻል ነገር እንደሌለ ሁልጊዜ እንዳስታውስ፣ በእምነት እንድመላለስና ሕይወቴን ሙሉ በሙሉ ለአንተ እንዳስረክብ ጸጋህን አብዛልኝ።

በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አሜን።

## የአርምሞ ጥቅስ

*“አቤቱ ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፥ እነሆ፥ አንተ ሰማይንና ምድርን በታላቅ ኃይልህና በተዘረጋች ክንድህ ፈጥረሃል፥ ከአንተም የሚያቅት ነገር የለም።”*

*— ኤርምያስ 32፥17 —*

## 2.6. እግዚአብሔር መንፈስ ነው!

እግዚአብሔር ራሱን ለእኛ ከገለጠበት መገለጥ መካከል አንዱና ዋነኛው የመለኮቱን ሙላት፣ የክብሩንም መንፀባረቅ ደግሞ የባህርይውን ምሳሌ የተመለከትንበት ስጋ ሆኖ የመጣው "ከመጀመሪያው" ጀምሮ ከእግዚአብሔር የሆነው ደግሞ ራሱ እግዚአብሔር የሆነው ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ታዲያ ይህ ልጁ ከእርሱ በቀር ማንም አይቶት ስለማያውቀው አባቱ ሲተርክልን በዮሐንስ 4፡24 ላይ እንዲህ አለ፦ *"እግዚአብሔር መንፈስ ነው።"*

በእውነት እላችኋለሁ ከእግዚአብሔር በርካታ ማንነቶች መካከል ይህኛው ለመረዳት በእጅጉ የእግዚአብሔርን እርዳታ የሚፈልግ ደግሞ ከተረዳነው በብዙ መልኩ ስለ እግዚአብሔር ያለንን እይታ የሚቀይር ድንቅ ነገር ነው። በዚህ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ንግግር ውስጥ ላስተዋለ ሰው እያለን ያለው እንደ ሰው መንፈስ አለው ሳይሆን እግዚአብሔር እርሱ ራሱ መንፈስ ነው የሚል ነው።

ይህ መንፈስ የሚለው ቃል ከእብራይስጡ *"ሩዋህ"* የሚል ቃል የሚገኝ ሲሆን ትርጓሜውም መንፈስ፣ ነፋስ እና እስትንፋስ የሚሉ ቃላትን ያዘለ ነው። እነዚህን ቃላት በትኩረት ለተመለከታቸው ሰው የሚገለጹበት ምንም አይነት መልክና ምሳሌ የሌላቸው ሲሆን የሚታወቁበትና ሁሉም ሰው ያያቸው ዘንድ የሚገለጹበት መልክ፣ ቁመት፣ ቀለም፣ ቅርጽ ወዘተ የላቸውም። ነገር ግን የየትኛውም አይነት ፍጥረት በህይወት የመኖር ዋና መነሻ ምክንያት እንደሆኑ ይታወቃል። ከዚህም ባለፈ ምንም እንኳን በአይን ታይተው የማያውቁ ይሁኑ እንጂ በዙሪያችን ሁልጊዜ የሚገኙ መሆናቸውን ሁሉም ፍጥረት ከእነርሱ ጋር ባለው ያልተቋረጠ መስተጋብር ጠንቅቆ ያውቀዋል።

ነፋስን አይቶት የሚያውቅ አንድም ሰው የለም ነገር ግን በየቀኑ በሚራመድበት ጊዜ በሚሰማው የነፋሱ እንቅስቃሴ ወይም በዙሪያው የሚገኙ ሌሎች ነገሮችን ሲያንቀሳቅስ እንዲሁም በእንቅስቃሴው ውስጥ በሚያሰማው ድምጽ ወዘተ ነፋስ ስለመኖሩ እርግጠኛ ሆኖ ያውቀዋል። በዚሁ *"ሩዋህ"* የሚለው ቃል ትርጓሜ ይዘት ውስጥ መንፈስ የሚለው ቃል በአካላዊ አይን የማይታየውን የሰው ውስጠኛ ማንነት፣ የእግዚአብሔርን የመፍጠር አቅም እንዲሁም ህይወትን የመስጠት ማንነት በውስጡ

ይናገራል። ይሄው ቃል በግሪክ *“ኒውማ”*የሚል አቻ ቃል ያለው ሲሆን *“ሩዋህ”*ከሚለው የእብራይስጥ ቃል ጋር በተመሳሰለ መልኩ መንፈስ፣ ነፋስ ወይም የሰው ውስጣዊ የመፍጠር አቅም እንደሆነ ተደርጎ ይተረጎማል። (Danker, 2000) (Koehler, Baumgartner, & Stamm, 1994-2000) (Brown, Driver, & Briggs, 1996)

በሰው ልጆች የፍልስፍና አለም ውስጥ በካላም (Kalām) የስነ ፍጥረት አስተሳሰብ እይታ ማንኛውም ወደ መኖር የመጣ ነገር ሁሉ ለመኖር መነሻ የሆነ ምክንያት ያስፈልገዋል የሚል መሪ ሀሳብ አለው። (Craig, 2009) እንዲሁም በሒሳብ እና ፊዚክስ አለሙ ውስጥ የሚገኙ ብዙ የተመራመሩ ተመራማሪዎች እንደደረሱበት ከዚህ ከሚታየው አለም የተስተካከለ መስተጋብር ጀርባ የማይታዩ ነገር ግን የዚህን የሚታየውን አለም መኖርና አለመኖር የሚወስኑ የማይቀየሩና በእጅጉ አስፈላጊ የሆኑ የፍጥረት ሰሪው በውስጣቸው ያስቀመጣቸው እንደ የመሬት ስበት ያሉ የማይታዩና የማይለወጡ የተፈጥሮ ህጎች አሉ ብለው ይላሉ። ከእነዚህ የማይለወጡ ተፈጥሮን የሚዘወሩ ቁጥሮች ጀርባ በእርግጥ አንድ እጅግ በጣም ምጡቅ የሆነ እውቀት ያለው ፍጥረቱን ሁሉ ወደ መኖር ያመጣ ኃይል አለ ብለው ያምናሉ። (Administration, n.d.) ታዲያ ይህ ከእነዚህ ቁጥሮችና ከፍጥረታቱ ጀርባ ያለው ባለ ብዙ እውቀት የሆነ አካል በእነዚህ በእርሱ በተፈጠሩ የተፈጥሮ ህጎች የማይገዛ ከእነርሱም በላይ የሆነ ማንነት ያለው ነው ብለው ይላሉ።

ለምሳሌ አንድ ሰው ርሃብ፣ ደስታ፣ ሀዘን ወዘተ የምንላቸው ሰዋዊ ስሜቶች ሲሰሙት የሚገለጡ በየትኛውም የአካል ክፍሎቹ ውስጥ ያልተቀመጡ፣ የሚዳሰሱና የሚታዩ ነገሮች ያልሆኑ የሰውየው ወቅታዊ ሁኔታዎች ናቸው። ነገር ግን የዚህ ሰው ደስታ፣ ሀዘን፣ርሃብ፣ ወዘተ ሰውየው ከተሰማው ስሜት አንጻር ስሜቱን ሊገልፁለት በሚችሉ በሚታይ አካላዊ ማንነቱ ላይ በሚገኙ አካል ክፍሎቹ ላይ በግልጽ ይታይና በሌላ ሶስተኛ ወገን በእርግጥ ያ ሰው በዚያን ጊዜ ምን አይነት ሁኔታ ውስጥ እንዳለ እንዲታወቅ ያደርጋሉ። በዚሁ መልኩ የአንድ ሰው አዕምሮአዊ ብስለት እና ንቃተ ህሊና በሚታየው አካላዊ ክፍሉ ይኸውም አንጎል በሚባለው ክፍል ላይ ብቻ የተመሰረተው ሳይሆን ከሰውየው ውስጣዊ ስሪት እና ፍጥረታዊ አቅም ጋር የተሳሰረ ጥልቅ ማንነት ነው።

በዚህ መሰረት እግዚአብሔር መንፈስ ነው ብለን ስንል ከላይ በቃላት ፍችዎቹ ውስጥ ለማየት እንደሞከርነው ነፋስ፣ እሳት ወይም ደግሞ ከፍጥረት ጀርባ ያለ የሆነ ነገር ብቻ ሳይሆን የራሱ ማንነት ያለው፣ ህያው የሆነ፣ የሚሰራና የሚንቀሳቀስ፣ ራሱን እኔ ብሎ የሚጠራ ከፍጥረቱ ጋር በግል በተለያየ መንገድ ግንኙነትን የሚያደርግ፣ በሆነ መልክና ቅርጽ ተመስሎ ያልተወሰነ፣ የማይታይ ነገር ግን ሰማይና ምድሩን ሁሉ ሞልቶ የሚገኝ፣ ለህይወቱ ፍፃሜና ማጠናቀቂያ የሌለው ሞትን የማይሞት የሆነ የራሱ ማንነት ያለው አካል ነው እያልን ነው። የቀረው ፍጥረት ሁሉ ትልቅ ወይም ትንሽ ቢሆን፣ የሚታይ ቢሆን ወይም ደግሞ የማይታይ፣ የሰው ልጅ ፈልጎ ያገኘው ደግሞ ከነመኖሩ የማያውቀው በዚህና በሚመጣው አለም ያለ ፍጡር ሁሉ ምንጩ ይህ መንፈስ የሆነ በምንም ነገር የማይወሰን በኃይሉ ብርታት ታላቅ የሆነ አምላክ ነው።

በኤርምያስ መጽሐፍ 23፡23 ላይ የእግዚአብሔር ቃል እኔ የቅርብ አምላክ ነኝ እንጂ የሩቅ አምላክ አይደለሁም ብሎ ሰማይንና ምድርንስ የሞላሁ እኔ አይደለሁምን ይላል። ልክ ከላይ በተገለፀበት አግባብ ይህ መንፈስ የሆነ ጌታ በዚህ ማንነቱ በምንም ነገር ሳይገደብ የሚከለክለው አንድም ነገር ሳይኖር አሁን በዚህ ሰዓት እዚህ እኛ ጋር ከእስትንፋሳችን ቀርቦ የሚገኝ ሲሆን ደግሞ ከእኛ በጣም ርቆ በሚገኘው እኛ ልንደርስበት የማንችለው ገና ያን ጊዜ ሰማይንና ምድርን በፈጠረበት፣ ቀድሞም በነበረበት፣ ባለፉት ዘመናት ወዳጆቹ ከሆኑ ሁሉ ጋር በሰራበት እና በተገለጠበት ደግሞ ዛሬ እኛ ጋር ባለበት በዚያው መገኘት እና ኃይል ባልተለወጠ መልኩ ሁሉም ቦታ በአንድ አይነት ወቅት እንዲገኝ ያስችለዋል። ይህም በየትኛውም ስፍራ የሚገኝ ማንም እራሱን ማግኘት የፈለገና ሊያወራው የሚወድ ሁሉ ባልተወሰነ አቅም ወይም ቆይ አንድ ጊዜ ከእርሱ ጋር ልጨርስ ሳይል በሙሉ መገኘት ከሚፈልጉት ሁሉ ጋር ኅብረት እንዲያደርግ የሚያስችለው የግል ባህርይው ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 24፡39 ላይ ጌታ ኢየሱስ ከሞቱ እና ከትንሳኤው በኋላ ሶስት አመት ተኩል ሁሉን ትተው ሲከተሉት ለቆዩ እና ስለ እርሱ እየተነጋገሩ በኢየሩሳሌም በተዘጋ ቤት ውስጥ ለነበሩት ደቀ መዛሙርቱ ድንገት በመካከላቸው ቆሞ ሰላም ለእናንተ ይሁን ባላቸው ጊዜ መንፈስ ያዩ መስሏቸው ሲደነግጡና ሲፈሩ ለድንጋጤያቸው የሚሆንን መልስ በመለሰ ጊዜ መንፈስ እንዳልሆነ

ለዚህም ማረጋገጫው የሚታዩና የሚዳሰሱ እጆቹና እግሮቹ እንደሆኑ መንፈስ ግን ስጋና አጥንት እንደሌለው ይነግራቸዋል። ይህም ማለት መንፈስ ኢየሱስ በዚያ ስፍራ የሚዳሰስ እጅና እግሮች ያሉት ሆኖ እንደተገለጠው ስጋና አጥንት ያለው አካል እንዳልሆነ ይገልፃል።

የሚዳሰስና በአካላዊው አለም ግንኙነት በሚያገለግል አካል ውስጥ የተገለጠ አይሁን እንጂ ህያው መሆኑ ብሎም በመካከላችን በዚሁ ማንነቱ መገኘቱን ግን የሚያስቀር አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ በ1ኛ ጢሞቴዎስ 6፡16 ላይ በግልጽ እንደሚናገረው *"እርሱ ብቻ የማይሞት ነው፣ ማንም ሊቀርበው በማይችል ብርሃን ይኖራል፣ አንድ ሰው እንኳ አላየውም ሊያይም አይቻለውም"* ብሎ ይናገራል። ይህም ከላይ የተናገርነውን እውነት የሚያስረግጥ በሚታየው አለም ከሚገኙ ሁሉ ፍጥረታት ይልቅ ገዝፎ በሁሉም ስፍራ በሙሉ ማንነት የሚገኝ ከታላቅ ክብሩ የተነሳ በየትኛውም አይነት ፍጡር ሊገለጽ ሊታይ ወይም ደግሞ በበቂ ቃላት ሊብራራ የማይችል ሆኖ በታላቅ ብርሃን ውስጥ የሚኖር መንፈስ የሆነ ህያው አምላክ እንደሆነ ያስረግጣል።

በዚህ ልክ ማንም አይቶት የማያውቅ የሚገለጽበት ወርድ፣ ቁመትና ስፋት አይኑረው እንጂ በፍጥረቱ ሁሉ ተገልጦ ይታወቅ ዘንድ ራሱን በብዙ መልኩ በመካከላችን ባልተቋረጠ ሁኔታ ቀኑን ሙሉ ሲገልጽ የሚውል አምላክ ደግሞ ነው። ባለፉት ዘመናት ይህ መንፈስ የሆነ ጌታ ራሱን በተለያየ መልኩ ለመለኮታዊ ስራው የፈቃዱን ምክር ለማድረግ ሲንቀሳቀስ አብረውት ይሰሩ ዘንድ ለመረጣቸው ሁሉ በልዩ ልዩ መንገድ ሲገለጥላቸው ኖሯል። በእሳት ውስጥ ባለ የማይቃጠል ቁጥቋጦ፣ ይነድ ከነበረው ሰባት እጥፍ በልጦ በነደደ እቶን እሳት ውስጥ፣ በአውሎ ነፋስ፣ በመላእክት መልክ ወዘተ ሊሰራ የወደደውን በፍጥረቱ መካከል ለማድረግ ሲገለጥ ኖሯል። ይህ ማለት ግን በዚያን ወቅት ራሱን የገለጠበት ያ መልክ መንፈስ የሆነውን እግዚአብሔርን ለመግለጥ በቃ እንደዚህ ነው ብለን እንድንጨርስ የሚያደርገን ምስል ነው ማለት አይደለም።

በሚታየው አለም ላለነው ለእኛ እናውቀው እና እንታዘዘው ዘንድ ራሱን ለእኛ በማቅረብ በእኛ ሁኔታ ከእኛ ጋር የሚነጋገርበት ለአዕምሮ በሚመች መልኩ ራሱን የገለጠበት መንገድ ብቻ ነው። በእነዚህ ራሱን ለሰው ልጆች በገለጠባቸው በየትኛውም መንገድ የእግዚአብሔርን ሙሉ ማንነት ልንረዳ እና ፈጽሞ ልናውቅ አንችልም። ለበርካቶች ራሱን የገለጠበት ይሄው መንገድ የእግዚአብሔር ክብር ምሳሌ ብቻ ተብሎ

የሚገለጽ ወቅታዊ መልክ ብቻ ነው፡፡ ለዚህ ነው እግዚአብሔር ደጋግሞ እስራኤላዊያንን የትኛውንም አይነት መልክ እና ቅርጽ ሰርተው እንዳያመልኩ አጥብቆ ያስጠነቀቃቸው፡፡ በመገናኛው ድንኳን ውስጥ በቃል ኪዳኑ ታቦት እንኳን በስርየት መክደኛው ላይ በደመና ክብሩን ይገልጥ ነበር እንጂ በየትኛውም መልክ ራሱን ለህዝቡ አልገለጠም ነበር፡፡ ይህንንም ማስጠንቀቂያ እግዚአብሔር አምላካቸው የማይታይና በሆነ አካል ውስጥ ሊወሰን የማይችል የተለየ መለያ መልክ የሌለው መሆኑን ሁልጊዜ እንዲያስቡ ሙሴ ለህዝቡ በዘዳግም 4፡12 ላይ ቀድሞ በሲና የነበረውን ሁኔታ እያስታወሰ በእሳት ውስጥ ሆኖ ከተናገረው የእርሱ ቃል በቀር አንድም መልክ እንዳላዩ ያስታውሳቸዋል፡፡

> "እግዚአብሔር የማይታይና በሆነ አካል ውስጥ ሊወሰን የማይችል የተለየ መለያ መልክ የሌለው መሆኑን ሁልጊዜ እንዲያስቡ ሙሴ ለህዝቡ ቀድሞ በሲና የነበረውን ሁኔታ እያስታወሰ በእሳት ውስጥ ሆኖ ከተናገረው የእርሱ ቃል በቀር አንድም መልክ እንዳላዩ ያስታውሳቸዋል፡፡"

ምንም እንኳን በተወሰነ ቁመት እና ስፋት የማይለካ ማንነት ያለው መንፈስ የሆነ በሁሉም ስፍራ የሚገኝ ሊይዘው የሚችል መቅደስ ይሰራለት ዘንድ እንዳይቻል ሰማይ ዙፋኑ ምድርም የእግሩ መረገጫ የሆነለት አምላክ ይሁን እንጂ ራሱን በሰው ልክ አሳንሶ በፍጥረቱ መሃል ለመገኘት ወደደ፡፡ ይህም ምናልባት እየመረመሩ ያገኙት እንደሆነ እግዚአብሔርን ይፈልጉ ዘንድ በምድር ሁሉ ላይ እንዲኖሩ የሰውን ወገኖች ሁሉ ከአንድ ፈጥሮ ያውቁትም ዘንድ ራሱን ያለ ምስክር ሳይተው መልካም ስራ እየሰራ ከሰማይ ዝናብን እያዘነበ ፍሬ የሚሆንበትንም ወራት ለአህዛብ ሁሉ እየሰጠ ልባችንንም በመብልና በደስታ ሲሞላው የኖረ ቢሆንም በዚህ ዘመን መጨረሻ በተለየ ሁኔታ ከጥንት ጀምሮ በብዙ አይነትና በብዙ ጎዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናግሮ አሁን ሁሉን ወራሽ ባደረገው ደግሞም አለማትን በፈጠረበት በልጁ ለእኛ ራሱን ገልጦ ተናገረ፡፡

በዚህ አሁን ራሱን በገለጠበት መገለጥ የመለኮትን ሁሉ ሙላት፣ እስካሁን ያልተገለጠ ታላቅ ክብሩን በማንፀባረቅ እንዲሁም እውነተኛውን የእግዚአብሔርን ማንነት ይኸውም የባህርይውን ምሳሌ ቀድሞም በእቅፉ በነበረው ዘላለማዊ ልጁ በኩል ገለጠ። ይህም ማለት ሰው ሁሉ ኢየሱስን አይቶ አብን ይመለከት ዘንድ እግዚአብሔር ስለ እርሱ ሊገለጥ የሚፈልገውን ሁሉ በልጁ በኩል በሰው ልጆች መካከል ገለጠ። ነገር ግን ይሄው ኢየሱስ ምንም እንኳን በሰው ልጆች መካከል የተገኘና በምድር ላይ የሚርመሰመሰውን የሰው ዘር ይምሰል እንጂ የተሰወረ የጥበብና የእውቀት መዝገብ በእርሱ ዘንድ ያለው አብን ልናይ በወደድንበት ልክ ወደ ደረቱ ጠጋ ብለን እርሱን እናውቀው ዘንድ የመንፈስ ቅዱስ ታላቅ እርዳታ እና የልቦና አይን ብርሃን የሚያስፈልገው፣ ምስጢር የሆነ፣ ከፍጥረቱ ሁሉ ደግሞ በኩር፣ አለም ሳይፈጠር በፊት በእግዚአብሔር አብ ዘንድ የነበረ፣ ራሱ እግዚአብሔር የሆነ አንድያ ልጁ ነው።

እግዚአብሔር መንፈስ ነው! የተገለጠ ውስን አካል የሌለው በሚታየው አለም የትኛውም አይነት ልኬታ የማይለካ ታላቅ አምላክ ነው። ነገር ግን በሰው ቋንቋ የእግዚአብሔር አይኖች፣ የእግዚአብሔር ክንድ፣ የእግዚአብሔር እጅ ወዘተ እያልን በመካከላችን የሚንቀሳቀስና የሚሰራ እነዚህ በምሳሌነት የተጠቀሱ የሰው አካላዊ ክፍሎች የሚሰሩትን ስራ በሙላት የሚያከናውን በማይታየው አለም ውስጥ የሚኖር በሚታየው አለም ላይም የሰለጠነና በተለያየ መንገድ በፍጥረቱ በኩል ራሱን የሚገልጥ አምላክ እንደሆነ እናያለን። ለዚህም ይመስላል ጳውሎስ በ1ኛ ጢሞቴዎስ መልዕክቱ 1፡17 ላይ ብቻውን አምላክ ለሚሆን ለማይጠፋው ለማይታየውም ለዘመናት ንጉስ ምስጋናና ክብር እስከ ዘላለም ድረስ ይሁን አሜን ብሎ ይላል።

ይህም መንፈሳዊ ማንነቱን በዚህም አገላለጽ ውስጥ ህያው መሆኑን፣ የሚመስለው ሌላ የሌለ መሆኑን፣ የማይጠፋና የማይሞት ዘላለማዊም የሆነ ክብርና ምስጋና የተገባው መንፈስ የሆነ የማይታይም የዘመናት ንጉስ እንደሆነ በግልጽ ይናገራል። ኢየሱስ ይህንን መንፈስ የሆነ አምላክ በሚታየው አለም በሙላት የገለጠ አብን ለማየት የምናየው አብ ጋር መድረሻ ብቸኛ መንገዳችን ሆኖ ተገልጦልናል። *አማኑኤል እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ሆነ!* ነገር ግን ዛሬም ድረስ መንፈስ የሆነው እግዚአብሔር ራሱን ለፍጥረቱ ለመግለጥ ይህንን ያክል መንገድ ርቀት የመጣ ቢሆንም የሰው ልጆች

እግዚአብሔርን ማወቅ ያልወደዱ መንገዱንም ኢየሱስ ክርስቶስን ያልፈለጉ ሆነው ይታያሉ።

> “ዛሬም ድረስ መንፈስ የሆነው እግዚአብሔር ራሱን ለፍጥረቱ ለመግለጥ ብዙ ርቀት ቀርቦ ወደ እኛ የመጣ ቢሆንም እንኳን ዛሬም ብዙዎች እግዚአብሔርን ማወቅ ያልወደዱ መንገዱንም ኢየሱስ ክርስቶስን ያልፈለጉ ሆነው ይታያሉ።”

ጳውሎስ በሮሜ 1:20 ላይ የሚታየው ባህርይ እርሱም የዘላለም ኃይሉ ደግሞም አምላክነቱ ከአለም ፍጥረት ጀምሮ ከተሰሩት ታውቆ ግልጥ ሆኖ ይታያልና ብሎ ስለዚህም እግዚአብሔርን እያወቁ እንደ እግዚአብሔርነቱ መጠን ስላላከበሩትና ስላላመስገኑት የሚያመካኙት አጡ፤ ነገር ግን በአሰባቸው ከንቱ ሆኑ የማያስተውለውም ልባቸው ጨለመ ብሎ ይናገራል። ይህም ብቻ አይደለም ነገር ግን እግዚአብሔርን ለማወቅ ባልወደዱት መጠን እግዚአብሔር የማይገባውን ያደርጉ ዘንድ ለማይረባ አዕምሮ አሳልፎ ሰጣቸው ብሎ ጨምሮ ይናገራል።

ከላይ በዝርዝር እንደተገለፀው እግዚአብሔር መንፈስ የሆነና የማይታይ አምላክ ይሁን እንጂ የፈጠራቸው ፍጥረቱ ሁሉ እርሱ ማን እንደሆነ የሚናገሩ ክብሩን ሁሉ የሚያወሩ አምላክነቱ የተገለጠባቸው የእጁ አሻራ የሚታይባቸው ስራዎቹ ናቸው። ከዚህም ባለፈ በልጁ በኩል የገለጠው መልኩ ደግሞም በመንፈሱ ያብራራልን ማንነቱ ዛሬም ድረስ ለሁላችን ተዘርግቶ የሚገኝ ታላቅ እርሱን የማወቅ እድል ነው። ይህም እውነተኛ አምላክ ብቻ እንዲሁም መንፈስ የሆነውን እግዚአብሔርን ማንነቱን ይገልጥልን ዘንድ የላከውን አንድያ ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስንም እናውቅ ዘንድ በዚህም የዘላለም ህይወት ይሆንልን ዘንድ ነው።

ሰው በየትኛውም መንገድ በፍጥረታዊ ማንነቱ መንፈስ የሆነውን እግዚአብሔርን ይረዳ ዘንድ አይችልም። መጽሐፍ ቅዱስ በ1ኛ ቆሮንቶስ 2:14 ላይ እንደሚናገረው እንዲሁ “ለፍጥረታዊ ሰው የእግዚአብሔር መንፈስ ነገር ሞኝነት ነውና አይቀበለውም በመንፈስም የሚመረመር ስለሆነ ሊያውቀው አይችልም።” በዚህም

መሰረት ሰው መንፈሳዊ ነገርን ለመመርመር ብሎም ለመረዳት ህይወትን የሚሰጥ መንፈስ ሆኖ በተገለጠው የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ከመንፈስ ቅዱስ ዳግመኛ መወለድ እና ከእግዚአብሔር መንፈስ ጋር ኅብረት ማድረግ የሚችል መንፈስ የሆነውን እግዚአብሔርን የሚያውቅበት የነቃ ህያው መንፈስ እንዲኖረው የግድ ያስፈልጋል። በዚህም መንፈሳችን በኩል ከመንፈሱ ጋር በሚኖረን ኅብረት በቃሉ በኩል የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር ስንኳ ሳይቀር ሁሉን መመርመር እንችላለን። ለዚሁ ነው ጳውሎስ በዚሁ 1ኛ ቆሮንቶስ 2፡12 ላይ ይህ ሁሉን አዋቂ የሆነ የእግዚአብሔርንም ጥልቅ ነገር ሁሉ የሚመረምር መንፈስ ከእግዚአብሔር እንዲያው የተሰጠንን እናውቅ ዘንድ እንደተሰጠን የሚናገረው።

> “ሰው በየትኛውም መንገድ በፍጥረታዊ ማንነቱ መንፈስ የሆነውን እግዚአብሔርን ይረዳ ዘንድ አይችልም።”

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያቱን በተሰናበተበት ወቅት በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 14 ላይ ሲናገር እርሱ እንደሚሄድ ነገር ግን ሌላ አጽናኝ ይኸውም እርሱ የነገራቸውን ሁሉ የሚያሳስባቸው፣ ወደ እውነትም ሁሉ የሚመራቸው አስተማሪ መንፈስ እንደሚልክላቸው ተስፋ ይሰጣቸዋል። ይህም አለም እርሱን ካወቀችበት መንገድ በተለየ ቅርበት ራሱን ላመኑበት ሁሉ ይገልጥ ዘንድ ያደረገው በአካል በአንድ ስፍራ ተወስኖ ካለበት ማንነቱ ወጥቶ በመንፈሱ በኩል ከአባቱ ጋር የእርሱ በሆኑት ሁሉ ውስጥ መኖሪያን ለማድረግ ስለወደደ እንደሆነ ይናገራል። በዚህም ኅብረት ከፍጥረታዊ ማንነታችን ተላቀን ዳግመኛ ተወልደን ባገኘነው መንፈሳዊ ማንነት መንፈስ የሆነውን እግዚአብሔርን ይበልጥ እናውቅ ዘንድ መንፈሳችንን ማንቀሳቀስ እና ማጠንከር ያስፈልገናል።

በእኛ ስጋ ውስጥ ያለው መንፈስ እጅግ ውስን ሲሆን ራሱ መንፈስ የሆነው እግዚአብሔር ግን ከመታወቅ ያለፈ ገደብ አልባ የሆነ ታላቅ አምላክ ነው። በዚሁ በመንፈሱ አማካኝነት ሁልጊዜ በየትኛውም ስፍራ ከሁላችን ጋር ኅብረትን ማድረግ የሚችል ሲሆን ይህም አብሮነቱ ሊጠብቀን በኋላችን፣ ሊያበረታን በጎናችን፣ ሊመራን በፊታችን ብሎም ሊያስተምረንና ለዘላለም አብሮን ሊኖር ከእስትንፋሳችን ይልቅ ቀርቦ በውስጣችን አለ።

ምንም እንኳን ዛሬም ይሄው መንፈሳዊ ነገርና የመስቀሉ ቃል ለፍጥረታዊው ሰውና አለም ሞኝነት ቢሆንም ለእኛ ለምንድን ግን የእግዚአብሔር ኃይል ለማዳን ነው። በመንፈስ ዳግም ከተወለድን በኋላ እግዚአብሔርን በመምሰል ያልተቋረጠ እድገት ፈጽመን እርሱን እስክንመስል ድረስ በአዕምሮ መታደስ እየተለወጥን የልጁን መልክ ለማንፀባረቅ ከክብር ወደ ክብር መለወጥ ያስፈልገናል።

በዚህም ጉዞ ዛሬ ላይ በድንግዝግዝ ያወቅነው አምላካችን እግዚአብሔር፣ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግመኛ በተገለጠ ጊዜ በሙላት የምናውቀው ይሆናል። አሁን በዚህ መንፈሳዊ ዳግም ውልደት በስጋ የተለዩት የፃድቃን መንፈሶች ፍፁማን ሆነው እኛ ደግሞ ህያዋን የሆንነው በስጋ ወራት በዚህ ምድር በመንፈስ በመመላለስ መገለጡን በመጠባበቅ በእምነት በሚኖር ህይወት አንድ ላይ አካል በመሆን የእግዚአብሔር ማደርያ ህንጻ ለመሆን በመንፈስ እየተሰራን እንገኛለን። በዚህም እርሱ ራሱ የተገኘንበት ህያው እንደሆነ ለዘላለም ለመኖር ህያዋን ሆነን እንኖራለን። ጌታችን ኢየሱስ በስጋው በሞተበት በዚያን ጊዜ በመንፈስ ህያው እንደነበር ይሄ ማደርያ ድንኳናችን እንኳን ቢጠፋ በተካፈልነው ይህ መለኮታዊ ህይወት ከእርሱ ጋር ለዘላለም እርሱ ራሱ ባለበት እንኖራለን።

ሀሌሉያ!

"ሰው መንፈሳዊ ነገርን ለመመርመር ብሎም ለመረዳት ህይወትን የሚሰጥ መንፈስ ሆኖ በተገለጠው የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ከመንፈስ ቅዱስ ዳግመኛ መወለድ እና ከእግዚአብሔር መንፈስ ጋር ህብረት ማድረግ የሚችል መንፈስ የሆነውን እግዚአብሔርን የሚያውቅበት የነቃ ህያው መንፈስ እንዲኖረው የግድ ያስፈልጋል።"

## የማስተንተኛ ጥያቄዎች

1. እግዚአብሔር መንፈስ ነው ማለት ምን ማለት ነው?
2. ማንኛውም የተፈጠረ ምስል እግዚአብሔርን ሙሉ በሙሉ ሊወክል የማይችለው ለምንድን ነው?
3. እግዚአብሔር ራሱን ለሰው ልጆች በምን በምን መንገዶች ገልጧል?

## አሰላሰል

እግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ ዘላለማዊ፣ የማይታይ እና ከፍጥረት ሁሉ በላይ የሆነ ነው። ምንም እንኳን በዓይናችን ልናየው ባንችልም፣ በፍጥረቱ፣ በቃሉ፣ ከሁሉም በላይ ግን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን ገልጦልናል። ስለዚህ እግዚአብሔርን ከፍጥረት ጋር ማመሳሰል ወይም በሰው ምናብ መገደብ አይገባም። እርሱ ልናውቀው እንድንችል ወድዶ ራሱን ስለገለጠልን፣ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ከሕያው አምላክ ጋር ኅብረት ልናደርግ እድል አግኝተናል። እውነተኛ አምልኮም በዚሁ ኅብረት የሚደረግ እርሱን በመንፈስና በእውነት ማምለክ እንደሆነ ሁልጊዜ ልናስታውስ ያስፈልገናል።

## ጸሎት

በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፣ በልጅህ በኢየሱስ ክርስቶስና በቅዱሱ መንፈስህ ራስህን ስለገለጥህልን እናመሰግንሃለን። በሰው ሐሳብ ወይም ምናብ ሳይሆን በእውነትህ መሠረት እንዳመልክህ አስተምረኝ። ልቤን ከፈትልኝ፤ ይበልጥ አውቅህ፣ በመንፈስህም ከአንተ ጋር በቅርበት እውነተኛ በሆነ ኅብረት እንድመላለስ ጸጋህን አብዛልኝ።

በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አሜን።

## የአርምሞ ጥቅስ

*“እግዚአብሔር መንፈስ ነው፥ የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል።”*

*— የዮሐንስ ወንጌል 4፥24 —*

## 2.7. እግዚአብሔር በሁሉም ስፍራ ይገኛል!

በአንድ ወቅት ሁሉን ትተው የተከተሉት እስራኤልን ይቤዣል ብለው ተስፋ ያደረጉት የአይናቸው ማረፊያ የሆነው ሶስት አመት ተኩል ውሎና አዳራቸውን ከእርሱ ጋር አድርገው አምነው የተከተሉት የናዝሬቱ ኢየሱስ ድንገት ተነስቶ በቅጡ ያልተረዱትን ነገር ተናገረ። ይኸውም ልሄድ ነው በዚህ ያለኝን ስራ ጨርሻለሁ የሚል ነበር። ከዚሁ ጋር አያይዞ ሁለተኛ ዳግም ተመልሶ እንደሚመጣና እርሱ ባለበት እነርሱ ደግሞ እንዲሆኑ እንደሚወስዳቸው እስከዚያው ግን በዚያ ለእነርሱ ስፍራ እንደሚያዘጋጅ ነገራቸው። ይህም ብቻ አይደለም ደግሞ ወደ ምሄድበትም ታውቃላችሁ መንገዱንም ታውቃላችሁ ብሎ ነገራቸው።

በወቅቱ መንገዱ እርሱ ራሱ እንደሆነና እርሱን ማየት አብን ማየት እንደሆነ ያላወቁት እርሱን በማወቅ እድገት ሂደት ላይ የሚገኙት ሐዋርያት በዚህ ንግግሩ እጅግ ያዝናሉ። በዚህ ጊዜ ኢየሱስ እኔ ግን እውነት እነግራችኋለሁ እኔ እንድሄድ ይሻላችኋል፣ እኔ ባልሄድ አጽናኙ ወደ እናንተ አይመጣምና እኔ ብሄድ ግን እርሱን እልክላችኋለሁ አላቸው። በዚህም መንገድ እርሱ ራሱ በመንፈሱ በኩል ከአባቱ ጋር ወደ እነርሱ መጥቶ እንደሚኖርና ራሱንም ለአለም ከገለጠበት መንገድ በተለየ መልኩ የእርሱ ለሆኑት እንደሚገልጥ በዚህም ህብረቱን ለዘላለም ከእነርሱ ጋር እንደሚያደርግ ይህም ፈጽሞ ላይተዋቸው በምንም ነገር ባልተገደበ እና ባልተቋረጠ ሁኔታ እስከ አለም ፍፃሜ በሆነ አብሮነት አብሯቸው ሊሆን እንደሆነ ይነግራቸዋል።

ከዚህ በፊት በነበረው ክፍል እግዚአብሔር መንፈስ እንደሆነ ይህም ማለት በየትኛውም አይነት ፍጥረታዊ የሆነ በጊዜና በቦታ በተወሰነ ምንም ነገር ተገድቦ ሊገኝ እና ሊገለጽ እንደማይችል ተገልጿል። በተጨማሪም እግዚአብሔርን ማንም አይቶት የሚያውቅ እንደሌለና በሆነ መልክና ቅርጽም የማይገለጽ እንደሆነ አይተናል። ነገር ግን እግዚአብሔር እርሱን እናውቅ ዘንድ ስለ እርሱ ሊታወቅ የሚያስፈልገውን ሁሉ በእቅፉ "ከመጀመሪያው" በነበረው እንድያ ልጁ በኩል የመለኮቱን ሙላት ገልጦ፣ ክብሩን በማንፀባረቅ፣ ባህርይውንም በምሳሌ በዚህ መልክ እንደገለጠልን ይታወቃል። የዚሁ ቃል ስጋ የመሆኑና በመስቀል ሞት የመሞቱ ምስጢር እኛ ሁላችን የእግዚአብሔር ጽድቅ

እንሆን ዘንድ እና በዚህም ከእግዚአብሔር ጋር በተደረገ እርቅ አማካኝነት በመንፈሱ በኩል እርሱ ራሱ ለዘላለም በእኛ ይኖር ዘንድ ለቅድስና ነው።

"ቃል ስጋ የመሆኑና በመስቀል ሞት የመሞቱ ምስጢር እኛ ሁላችን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንሆን ዘንድ እና በዚህም ከእግዚአብሔር ጋር በተደረገ እርቅ አማካኝነት በመንፈሱ በኩል እርሱ ራሱ ለዘላለም በእኛ ይኖር ዘንድ ለቅድስና ነው።"

"ከመጀመሪያው" ማንም ሊያየው በማይችል ብርሃን ውስጥ በሁሉም ስፍራ ይኖር የነበረው እና የሚኖረው ይህ ጌታ በዚያው ማንነት ለእኛ የበለጠ በተገለጠ ሁኔታ ዛሬም እንደዚያው በሁሉም ስፍራ ይገኛል። ይህም መገኘቱ እግዚአብሔር መንፈስ ስለሆነ በመንፈስ ብቻ የሚታወቅ ለፍጥረታዊ ሰው ፈጽሞ ሊገባ የማይችል እንዲያውም ሞኝነት እና እብደት የሚመስል የማይገባ ንግግር ነው። ነገር ግን እግዚአብሔር ዛሬ አሁን ከዘላለም ዘላለም በፊት በነበረው በዚያው ያልተለወጠ ማንነት እና ክብር በሁሉም ስፍራ አለ።

## ይህን ንግግር እንዴት መረዳት ይቻላል?

ሰው አካላዊ ማንነት ያለው በጊዜና በቦታ የተገደበ አሁን ባለበት ስፍራና ጊዜ ብቻ የሚገኝ አሁናዊ ብቻ የሆነ ውስን ፍጡር ነው። እግዚአብሔር ግን ገና "ከመጀመሪያው" ምንም ነገር ሳይቀረው ቀድሞ ሁሉን የሚያውቅ፣ ባልተቀነሰ ሙላቱ እና ማንነቱ በፍጥረቱ ሁሉ መካከል ውስጥ እና ላይ ያለ ገደብ የሚገኝ፣ እርሱ ያላየውን አይቶ ለሰው ድንገተኛ የሆነን እርሱ ቀድሞ የሚያውቀውን ነገር የሚነግረው ሌላ አካልን ሳይፈልግ ሁሉን ያይና ያውቅ ዘንድ በሁሉም ስፍራ የሚገኝ፣ ይይዘው ዘንድ የሚሰራለት ሰው ሰራሽ የሆነ በቁመትና በስፋቱ ልክ የሆነ ቤት የሌለው፣ በላይ በሰማይ በዙፋኑ ላይ ከፍ ብሎ በክብር የሚገኝ ደግሞ በዚህ በእኛ መካከል አሁን ያለ፣ አልፎም በእኛና በፍጥረቱ ሁሉ ውስጥ ያለውን ስፍራ ሁሉ ሽፍኖ የያዘ በሁሉም ስፍራ የሚገኝ አምላክ ነው። ለዚህ ነው ሰለሞን በ፩ኛ ነገስት 8:27 ላይ *"እነሆ ሰማይ ከሰማያትም በላይ ያለው ሰማይ ይይዝህ ዘንድ*

*አይችልም ይልቁንስ እኔ የሰራሁት ቤት እንዴት ያንስ"* ያለው። እርሱ ራሱም እግዚአብሔር በኢሳይያስ 66 ላይ *"ሰማይ ዙፋኔ ነው ምድርም የእግሬ መረገጫ ናት የምትሰሩልኝ ቤት ምን አይነት ነው"* ብሎ ይላል።

ይሄው አገላለጽ ለሰው በሚገባ ቋንቋ እግዚአብሔር ራሱን ለእኛ ለመግለጽ የተጠቀመበት፣ ሁሉ በሁሉ የሆነ፣ ፍጥረቱን ሁሉ የከደነ፣ በሁሉም ስፍራ የሚገኝ፣ ሁሉን የሚያይና የሚያውቅ አምላክ መሆኑን ነው። ይህም ማለት ምድር የእግሩ መረገጫ ስለሆነች እንደ ሰው አይኑ በሰማይ ብቻ ነው ማለት ሳይሆን መንፈስ የሆነው እግዚአብሔር በሙሉ ማንነቱ እውቀቱና ኃይሉ በሙላት በሁሉም ስፍራ ማለትም በሰማይ ደግሞ ከሰማይ በላይ ባለ ሌላ ሰማይ እንዲሁም በምድር ደግሞ ከምድር በታች ባለው ዝቅታ ሁሉ ውስጥ ያለ አንዳች ገደብ የሚገኝ ታላቅ አምላክ ነው ማለት ነው።

ዳዊት በመዝሙሩ ምዕራፍ 139፡7-10 ባለው ክፍል ላይ እንዲህ አለ፡- ከመንፈስህ ወዴት እሄዳለሁ? ከፊትህስ ወዴት እሸሻለሁ? ወደ ሰማይ ብወጣ አንተ በዚያ ነህ፤ ወደ ሲኦልም ብወርድ በዚያ አለህ፣ እንደ ንስር የንጋትን ክንፍ ብወስድ እስከ ባህር መጨረሻም ብበርር በዚያ እጅህ ትመራኛለች ቀኝህም ትይዘኛለች።

## ይህ ምን አይነት መረዳት ነው?

በየትኛውም የፍጥረት አለም ክፍል ውስጥ ለእግዚአብሔር እንዳይገኝበት የተከለከለ እርሱም የሌለበት ስፍራ ፈጽሞ የለም። በዚህ የዳዊት ንግግር ውስጥ ወደ ሰማይ ብወጣ ብሎ እንደሚል የትኛውም አይነት ከፍታ ከእግዚአብሔር ከፍ ያለና የተሸፈነ እግዚአብሔርም የሌለበት አይደለም። ደግሞ ይህም ብቻ አይደለም ወደ ታች ያለ የዝቅታ መጨረሻ ይኸውም ሲኦል እንኳን በእግዚአብሔር መገኘትና ስልጣን ስር ያለ እንጂ

> "ወደ ምስራቅ በፀሃይ ንጋት በኩል ደግሞ በስተምዕራብ በባህሩ መጨረሻ አቅጣጫ፣ በስተሰሜን በሚገኘው ከፍ ያለ ከፍታና በስተደቡብ ባለ የምድር ዝቅታ ሁሉ እግዚአብሔር በሙላት በስልጣኑ ሳይከለከል ህያው ሆኖ አለ።"

እግዚአብሔር የማይደርስበት ለሌላ አካል የተተወ ከእርሱም መገኘት የራቀ ክልል አይደለም። ወደ ምስራቅ በፀሃይ ንጋት በኩል ደግሞ በስተምዕራብ በባህሩ መጨረሻ አቅጣጫ፣ በስተሰሜን በሚገኘው ከፍ ያለ ከፍታና በስተደቡብ ባለ የምድር ዝቅታ ሁሉ እግዚአብሔር በሙላት በስልጣኑ ሳይከለከል ህያው ሆኖ አለ። በዚህ ሁሉ ታዲያ ሙሴ በዘዳግም 4፡39 ላይ እንዳለ *"እግዚአብሔር በላይ በሰማይ በታችም በምድር አምላክ እንደ ሆነ ሌላም እንደሌለ ዛሬ እወቅ በልብህም ያዝ።"*

እግዚአብሔር በዚህ መልኩ ርቆ በላይ በሰማይ ባለ ከፍታ ወይም በታች ከምድር በታች ባለ ዝቅታ ብቻ ያለ አምላክ አይደለም። ይልቁንስ በሁሉም ስፍራ አለ ካልን በዚህ አሁን እኛ ባለንበትም ደግሞ አለ እያልን ነው እንጂ። መጽሐፍ ቅዱስ በኤርምያስ 23፡28 ላይ እግዚአብሔር ሲናገር *"የቅርብ አምላክ ነኝ እንጂ የሩቅ አምላክ አይደለሁም።" ሰው በስውር ቢሸሽግ እኔ አላየውምን? ሰማይንና ምድርንስ የምሞላ እኔ አይደለሁምን?* ይላል። በዚህም መሰረት እግዚአብሔር በሁሉም ስፍራ ባለው መገኘቱ በፊታችን፣ በኋላችን ደግሞ በዙሪያችን አልፎም በውስጣችን በሙላት በአብሮነቱ አሁን አለ።

በዳንኤል የአንበሳ ጉድጓድ ውስጥ እንዲሁም በንግስና ስፍራው፣ ዮሴፍ በምርኮ ምድር በሄደበት ሁሉ፣ እሳት ውስጥ የተጣሉት ሲድራቅ ሚሳቅና አብድናጎ ጋር በእሳቱ ውስጥ አብሮ በዚያ ሆኖ የሚታይ ነው። በቃሉም ለሚያምንበት ሁሉ በእሳት ውስጥ ባለፈ ጊዜ እንዲሁም በውሃ ውስጥ በሄደ ጊዜ እግዚአብሔር በዚያ አብሮ እንዳለ ይናገራል። ይህም ሰው ወደዚያ ስፍራ ሲሄድ እግዚአብሔር አብሮ ሄዶ የተገኘ ሳይሆን ሰው ወደዚያ ስፍራም ከመሄዱ አስቀድሞ እግዚአብሔር በመላ ማንነትና ስልጣኑ ቀድሞውኑ በዚያ አለ ማለት ነው። ለዚህም ነው ጳውሎስ በሐዋርያት ስራ 17፡28 ላይ እኛ ራሳችን ሁላችን በእርሱ ህያዋን እንደሆንን በእርሱም ውስጥ እንደምንኖርና እንደምንቀሳቀስ ይህም ሙሴ ለእስራኤል እንደተናገረ እርሱ ራሱ እግዚአብሔር መኖሪያችን ሆኖ በእርሱ እንደምንኖር አጠንክሮ የሚናገረው።

እግዚአብሔር በዚህ በሁሉም ስፍራ መገኘቱ ውስጥ አሁናዊ የሆነ ሁሉን የማወቅና የማድረግ ስልጣኑ በተገኘበት ሁሉ ደግሞ አብሮ በሙላት አለ። ሰዎች ግን እግዚአብሔርን ከእነርሱ በጣም የራቀና የሆነ ሰማይ የሚባል አካላዊ ስፍራ ላይ ዙፋን

ሰርቶ የተቀመጠ እዛ ብቻ የሚኖር እኛ ጋርም ለመድረስ እና ያለንበትን ሁኔታ ለመረዳት ጊዜ የሚወስድበት እንደሆነ ያስባሉ። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ በዘዳግም 30፡11-14 ባለው ክፍል ውስጥ እንደሚናገረው እግዚአብሔር እጅግ የቀረበ ቃሉም በአፍና በልባችን ውስጥ የሚገኝ ከእኛም ያልራቀ እርሱን ፍለጋ ወደ ሰማይ መውጣት፣ ባህሩን ተሻግሮ ሩቅ መሄድ ወይም ወደታች ወደ ሲኦል መጓዝ ሳያስፈልገን አሁን እዚህ ከእኛ ጋር ደግሞም በእኛ ውስጥ ዘልቆ በሙላት የሚኖር እኛም ደግሞ በእርሱ የምንኖር ከእስትንፋሳችን ይልቅ እጅግ ቀርቦ ያለ ተፈልጎ የሚገኝ ዙሪያችንን የሞላ አምላክ ነው።

ይሄው የእግዚአብሔር በሁሉም ስፍራ የመገኘቱ ምስጢር እርሱ ራሱ በሚፈቅደው መንገድ ራሱን በገለጠበት ወቅት የሚታወቅና የበለጠ የምንረዳው እውነት ነው። ከአባቱ ከይስሃቅ ቤት ወንድሙ ኤሳው እንዳይገድለው በፍርሃት ሸሽቶ ወደ ካራን ጉዞ የጀመረው ያዕቆብ በመንገዱ መካከል በመሸበትና ለመተኛት ድንጋይ ተንተርሶ ባሸለበ ወቅት እግዚአብሔር መንፈሱን አንቅቶ በዚያ መገኘቱን በገለጠለት ጊዜ *"ይህ ስፍራ እንዴት ያስፈራ"* አለ። እርሱም ደግሞ እንዳለ በእውነት *"እግዚአብሔር በዚህ ስፍራ ነው እኔ አላወቅሁም ነበር"* አለ።

እግዚአብሔር ዛሬ ለዚያውም አሁን በዚህ እኛ ባለንበት ሁኔታና ስፍራ በየትኛውም ጊዜና ሰዓት በሙላት የሚገኝ ሲሆን ከዚህ በፊት ባለው ክፍል መንፈስ የሆነውን እርሱን ለመንካት በውስጣችን ያለውን ከእርሱ ጋር ኅብረት የሚያደርግ ክፍል ይኸውም መንፈሳችንን ማንቀሳቀስ ያስፈልገናል። በተራራው ላይ በሚያስፈራ ግርማው የተገኘው ለህዝቡ ለእስራኤል የተገለጠው እግዚአብሔር ከዚያም መገኘቱን በደመናና በእሳት አምድ ባልተቋረጠ ሁኔታ ይገልጥ የነበረው ይህ ታላቅ አምላክ ዛሬም በዚያው ግርማና ክብሩ ባልተለወጠ ማንነቱ ሁሉን ሞልቶ በሁሉም ስፍራ አለ። ይህንን መገኘቱን ለመረዳትና ለማክበር በዚያም ህልውና ውስጥ ለመኖር የልቦና አይኖቻችን እንዲበሩ ብሎም ፀጋው እንዲበዛልን እግዚአብሔር ይርዳን።

በህዝቡ መካከል በተገለጠ መገኘት አብሮ ይሆን እና ይኖር ዘንድ ወድዶ ሙሴን የማደርያ ድንኳን ህዝቡ ያዘጋጅለት ዘንድ ጥብቅ በሆነ ጥንቃቄ እንዲሰራለት የጠየቀው እግዚአብሔር ሙሴ እንደታዘዘው እንደዚያው እግዚአብሔርን ደስ በሚያሰኝና በሚያከብር መንገድ ሰርቶ ባጠናቀቀ ጊዜ በደመና ተገልጦ በታላቅ ክብር ማደርያውን

በመሙላት በፊቱ እንዲመላለስ የተመረጠው ሙሴ እንኳን ወደ ድንኳኑ መግባት እስከማይችል ድረስ መገኘቱን ለህዝቡ ገልጦ ነበር።

ዛሬም አሁናዊ መገኘቱን ይበልጥ እናውቅ ዘንድ እርሱ ሊገኝበት የሚፈልገውን አይነት ማንነት በፀጋው በመልበስ ተገቢ የሆነ የጽድቅና የቅድስና የኑሮ ምልልስን በመመላለስ በዚህም ሁሉ ላይ ፍቅርን መሰረት በማድረግና በመጨመር መመላለስ ያስፈልገናል። እንደዚህ በሆነበት ሁኔታ እግዚአብሔር እንደ ቃሉ ነውና ሁለት ሰዎች ተስማምተው ባሉበት በዚያ፣ የእርሱን መገኘት በፈለገ በፍጹም ፍቅርና የእግዚአብሔር ስርዓት ላይ በተመሰረተ ቤተሰብ፣ በፍጹም ልቡ እግዚአብሔርን የፈለገ ግለሰብና ማህበረሰብ በሚገኝበት አካባቢ በዚያ ያዘዘውን በረከትና ህይወት ሊገልጥ በመገኘቱም ደስ ሊያሰኝ በግርማውና በክብሩ በራሱ መንገድ ይገለጣል።

የአንድ አማኝ የመጨረሻ በረከት እግዚአብሔር ባለበት በዚያ በተገለጠ እና በሚረዳው ሁኔታ መኖሩ ሲሆን የምንጠብቀው ተስፋም በተገለጠ ጊዜ የምናገኘው የመጨረሻ በረከት እርሱ ራሱ ባለበት በዚያ ለመሆን በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም መገኘት ነው። ይሁን እንጂ ዛሬ በምድር በስጋ ወራታችንም እንኳን ቢሆን ይህንኑ የምንሄድበትን አለም በቅድመ ቅምሻ እናውቀው ዘንድ ምንም እንኳን ደካማ ስጋን የለበስንና ብዙ የሚያደክሙ ነገሮች በሞሉበት ምድር የምንገኝ ቢሆንም በውስጥ ሰውነታችን የምንሄድባትን አለም ሰላም፣ ደስታና ፍቅር ደግሞም የመገኘቱን በረከቶች ሁሉ እየተለማመድን በዚህ እንቆያለን።

እርሱ ራሱ እንዳለ በእርግጥ እስከ አለም ፍፃሜ በመንፈሱ አማካኝነት በሄድንበትና በደረስንበት ሁሉ አብሮን በመሆን ፈጽሞ ሳይለየን እያስተማረንና እያበረታን አብሮን አለ። መዝሙረኛው ዳዊት በ23ኛው ምዕራፍ ላይ እንዳለ በሞት ጥላ መካከል እንኳን ብንሄድ በበትሩና በምርኩዙ ሊያጸናናን እርሱ በዚያ ከእኛ ጋር አብሮ አለና ክፉውን አንፈራም። በእርሱ አብሮነት ውስጥ ያለ የእርሱ ስልጣን፣ አቅምና ኃይል ደግሞም ታላቅ ፍቅር መንገዳችንን ሁሉ በፍጹም ደስታ ከእርሱ ጋር እንድንጓዝ ያስችለናል።

ይህ እግዚአብሔር ያለ ከልካይ በሁሉም ስፍራ አለ የሚለው እውነት ለእኛ ለምናምን ልባችንን እርፍ የሚያደርግ በኩራት ያለ አንዳች ፍርሃት በስልጣን በየትኛውም

ስፍራ እንድንገኝና በህይወት እንድንኖር ዋስትናን የሚሰጠን ብሎም የትኛውም አይነት ችግር ከዚህ አብሮን ካለው ጌታ አቅም በላይ ባለመሆኑ ደስታና ሰላማችን የተጠበቀ እንደሆነ ያስታውሰናል። ይህ በእውነት ምን አይነት ክብር ነው? በዚህ አብሮነቱ ስንደክም እያበረታን፣ ስንወድቅ እያነሳን፣ ስንዝል እየተሸከመ፣ ኃይልን ስናጣ ኃይልን እየሰጠና ፀጋውን እያበዛ ሀጢአታችንን ይቅር እያለ በዚህ በሚያልፈው አለም ማባባያና ማሳቻ ሳንያዝ ሩጫችንን እንጨርስና ቀድሞውኑ እንደነገረን እርሱ ባለበት በዚያ ለዘላለም እንሆን ዘንድ ያስችለናል።

ከዚሁ በተቃራኒ ይህንን አምላክ በሁሉም ስፍራ የተገኘና ሊታወቅ ወድዶ ከፍጥረት ጅማሬ አንስቶ በፍጥረቱ ሁሉ በልዩ ልዩ መንገድ ሲናገር እና ራሱን ሲገልጥ የኖረ ቢሆንም መገኘቱን ሊክዱና ይህንኑ ባወቁበት ልክ እንደ እግዚአብሔርነቱ መጠን ላላከበሩትና ላላመሰገኑት ሁሉ ከፍተኛ ፍርሃትን የሚፈጥር አስደንጋጭ እውነት ነው።

ከመጀመሪያው ጀምሮ እግዚአብሔርን ከፍ ባለው ዙፋኑ አይቶትና አውቆት ሳለ በእርሱ ላይ ያመፀውን ዲያብሎስና ሊከተሉት ወደው ከንቱ ስብከቱን የተቀበሉትን ሁሉ በሲኦል ጭምር በሙሉ ስልጣኑ ተገኝቶ ቁጣውን የሚያፈስው እግዚአብሔር ህያው ሆኖ በሁሉም ስፍራ መገኘቱ እጅግ የሚያስፈራ እውነት ነው። በእግዚአብሔር ፊት የሚጋርድ ኪሩብ ሆኖ በከፍተኛ ውበት የነበረውና በዚሁ አመጽ ምክንያት ወደ ምድር የተጣለው ዲያብሎስ አብረውት የተጣሉት ተከታይ አጋንንቶችና መንፈሳዊ ሰራዊቶቹ ብሎም በሚታየው አለም በምድር ላይ ፈቃዱን ለማድረግ ራሳቸውን የሰጡት ሁሉ በተገለጠ ሁኔታ ከሚንቀሳቀሱት እንቅስቃሴ እና መገኘት የበለጠ በሁሉም ቦታ መሆን የማይችል በጊዜና በሰዓት የተገደበ ፍጡር ነው።

*እግዚአብሔር ግን በተቀደሰ መቅደሱ አለ። ምድርና ምላዋም በክብሩ ተሞልታለች።*

*ስለዚህ ስጋ ለባሽ ሁሉ በፊቱ ዝም ይበል።*

ሀሌሉያ!

> “እግዚአብሔር እጅግ የቀረበ ቃሉም በአፍና በልባችን ውስጥ የሚገኝ ከእኛም ያልራቀ እርሱን ፍለጋ ወደ ሰማይ መውጣት፣ ባህሩን ተሻግሮ ሩቅ መሄድ ወይም ወደታች ወደ ሲኦል መጓዝ ሳያስፈልገን አሁን እዚህ ከእኛ ጋር ደግሞም በእኛ ውስጥ ዘልቆ በሙላት የሚኖር እኛም ደግሞ በእርሱ የምንኖር ከእስትንፋሳችን ይልቅ እጅግ ቀርቦ ያለ ተፈልጎ የሚገኝ ዙሪያችንን የሞላ አምላክ ነው።”

- **የማስተንተኛ ጥያቄዎች**

1. የእግዚአብሔር በሁሉ ቦታ መገኘት ስለ ማንነቱ ባለህ መረዳት ላይ ምን ጨመረልህ?
2. እግዚአብሔር ሁልጊዜ ከእኛ ጋር እንዳለ ማወቃችን ችግሮችን የምንጋፈጥበትን መንገድ እንዴት ይለውጠዋል?
3. የእግዚአብሔር መገኘት እውነታ በየዕለቱ ከእርሱ ጋር በምንመላለስበት መንገድ ላይ ምን ተጽዕኖ ሊያሳድር ይገባል?

- **አሰላስል**

እግዚአብሔር በጊዜ፣ በቦታ ወይም በፍጥረት አይገደብም። በሁሉም ቦታና በሁሉም ሁኔታ ከሕዝቡ ጋር ይገኛል። እግዚአብሔር ሁልጊዜ ቅርባችን እንደሆነ ማወቃችን በእርሱ እንድንተማመን፣ ሰላምና ጽናት እንዲኖረን ያደርገናል፤ ምክንያቱም ከእርሱ ሕልውና ፈጽሞ አንለይም። በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ስናልፍ በእርግጥ እግዚአብሔር በተገኘንበት ስፍራ በዚያ እንዳለ ብቻችንንም እንዳልሆንን ሁልጊዜ ማስታወስ ያስፈልገናል።

- **ጸሎት**

በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፣ ሁልጊዜ ቅርባችን ስለሆንክ እናመሰግንሃለን። በሁሉም ሁኔታ በፊትህ እንዳለን እያወቅን እንድንኖርና በአንተም እንድንታመን እርዳን። በእምነት፣ በፍርሃትና በመተማመን በፊትህ እንድንመላለስ እርዳን።

በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አሜን።

- **የአርምሞ ጥቅስ**

*"ከመንፈስህ ወዴት እሄዳለሁ? ከፊትህስ ወዴት እሸሻለሁ?*

*ወደ ሰማይ ብወጣ፥ አንተ በዚያ ነህ፤ ወደ ሲኦልም ብወርድ፥ በዚያ አለህ።"*

*— መዝሙረ ዳዊት 139፥7-8 —*

## 2.8. እግዚአብሔር ሁሉን አዋቂ ነው!

እግዚአብሔር ታላቅና የተፈራ የሆነ በዙፋኑ ላይ ከነ ሙሉ ክብሩና ስልጣኑ ከዘላለም ዘላለም ጀምሮ የነበረና ያለ ደግሞም የሚኖር መንፈስ የሆነ በሁሉም ስፍራ ደግሞ በሙላት የሚገኝ አምላክ ነው። ታዲያ ይህ መንፈሳዊ ማንነቱና በተወሰነ አካል ውስጥ ሳይገደብ በፍጥረቱ ሁሉ መካከል በሙላት የሚገኝ መሆኑ በየስፍራው ያለውን ሁሉ ያለ አንዳች ጉድለት እንዲያውቅ ደግሞ አድርጎታል።

መጽሐፍ ቅዱስ በኢሳይያስ 46:10 ላይ እንደሚናገረው በመጀመሪያ ሆኖ መጨረሻውን ደግሞ የሚያውቅና የሚናገር ብሎም የሚያደርግ አምላክ ነው። ገና ከጅማሬው ፍጥረት ሁሉ ከአለመኖር ወደ መኖር በመጣ ጊዜ በፊቱ የሚመላለሱ ሁሉ በተፈጠረው ጊዜና ቦታ ገደብ ውስጥ የሚገኙ በሚታየውና በማይታየው አለም ያሉ ሁሉ በየዘመናቸው የሚያደርጉትንና በልባቸው የሚያስቡትን ሁሉ ጭምር ጠንቅቆ ያውቃል። ይህም በመዝሙረ ዳዊት ምዕራፍ 139:16 ላይ እንደሚናገረው ያልተሰራ አካላችንን አይኖቹ ቀድመው ያዩን የተፈጠሩ ቀኖቻችን ሁሉ ገና ወደ መኖር ሳይመጡ አንድ ስንኳ ሳይቀር በእርሱ የታወቁ ብሎም በመጽሐፍ ጭምር የተጻፉ እንደሆነ እናያለን። ይህም ሁሉ እግዚአብሔር በሁሉም ስፍራ ህያው ሆኖ የሚገኝ የትኛውም ፍጥረታዊ ማንነት ሁሉን አልፎ እንዳይገኝ የማይገድበው ስለሆነ እና በየትኛውም ፍጥረታዊ አካል ውስን የሆነ ማስተዋል ያልተገደበውን መጨረሻ የሌለው የበረታ እና የተጠበበ ታላቅ የእግዚአብሔር ማስተዋል ሊደርስበት የማይችል በመሆኑ ነው።

ይህ የእግዚአብሔር ሁሉን አዋቂነት በመንግስቱ አወቃቀር ውስጥ አብረው ሰራተኛ ይሆኑ ዘንድ በፊቱ ይመላለሱና ያገለግሉት ዘንድ በየስፍራው በፍጥረት መካከል የመደባቸው ፍጥረቶቹ መጥተው ድንገተኛ የሆነ እና እግዚአብሔር ያልደረሰበት ምንም አይነት እውቀት የማይጨምሩለት ፍጹም የሆነ ሁሉን አዋቂነት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በኢሳይያስ 40:13 ላይ *"የእግዚአብሔርን መንፈስ ያዘዘ ወይስ አማካሪ ሆኖ ያስተማረው ማን ነው? ወይስ ከማን ጋር ተመካከረ? የማስተዋልንስ መንገድ ማን አሳየው?"* ብሎ እግዚአብሔር ፍጹም በሆነ ማንነት ሁሉን የሚያውቅ እና የሚያስተውል መሆኑን ለዚህም

ብቃቱ ተባባሪ ሆኖ የረዳውና አጠገቡ ሆኖ ያማከረው ማንም አለመኖሩን በግልጽ ያስረዳናል።

በተመሳሳይ ሁኔታ ጳውሎስ በሮሜ መጽሐፍ 11፡33-36 ባለው ክፍል ውስጥ እግዚአብሔር እውቀቱ ጥልቅ እንደሆነ ይደረስበት ዘንድ ለመንገዱ ፍለጋ እንደሌለው ለዚህም አብሮት ሊሰራ እና ሊያማክረው የቀረበ አንዳች ፍጡር እንደሌለ ይልቁንስ ሁሉ ከእርሱ፣ በእርሱና ለእርሱ ብቻ እንደሆነ ይነግረናል። ይህ የእግዚአብሔር እውቀት በዘመናት መካከል የሚለወጥ ወይም አዲስ ነገርን በማወቅ የሚጨምር እውቀት አይደለም። ገና ከመጀመሪያው መጨረሻውን ያወቀበት መካከሉን ሁሉ በዚሁ የማይመረመር ማስተዋሉ የተረዳበት የመጨረሻ እውቀት ነው።

የኤፌሶን መልዕክት ምዕራፍ 1 ላይ እኛ ሁላችን ገና ከሰማይና ምድር መፈጠር በፊት የታወቅን እንደሆነ የሚናገር ሲሆን ዮሐንስ ራዕይ 13፡8 ደግሞ በዚሁ አስደናቂ የእግዚአሔር ሁሉን አዋቂነት ምክንያት ሰው በሀጢአቱ ምክንያት እንደሚወድቅ አስቀድሞ የሚያውቅ በመሆኑ ለዚሁ ውድቀት ያዘጋጀውን ታላቅ የማዳን እርምጃ ይኸውም የአለምን ሁሉ ሀጢአት የሚያስወግደው የእግዚአብሔር በግ መታረድ እንኳን ያን ጊዜ ገና ከመጀመሪያው የሚታወቅ እንደሆነ ይነግረናል። ይህም ብቻ ደግሞ አይደለም በዚሁ የእግዚአብሔር ሁሉን አዋቂነት ምክንያት በፍጥረት አለም ውስን ጊዜና ቦታ የሚደረጉ ክስተቶች ቀድመው የታወቁ በመሆናቸው ከእርሱ ዘንድ ገና ያን ጊዜ ከዘላለም ዘላለም በፊት እርሱ ባወቃቸው ጊዜ ኩነቶቹ እንደተደረጉ የሚቆጠሩ በአሁናዊ አገላለጽ የተገለፁም ናቸው። በዚሁ የዮሐንስ ራዕይ 13፡8 ክፍል ላይ ይሄው የእግዚአብሔር በግ መታረድ ቀድሞ ከአለም ፍጥረት በፊት ሊሆን ያለው በእግዚአብሔር ዘንድ የታወቀ በመሆኑ ያን ጊዜ እንደተደረገ ደግሞ የተቆጠረ ሆኖ ይታያል።

ነገር ግን ዛሬ አሁን በየትኛውም ቦታና ሁኔታ የሚደረጉ ማንኛቸውንም ክስተቶች ቀድሞ የሚያውቅ ብሎም በጊዜና በእውቀት ውስን ከሆኑ ፍጥረቶቹ ጋር አሁናዊ በሆነ ግንኙነት የሚግባባ ሁሉን አስቀድሞ የሚያውቅ አምላክ ነው። ለዚህም ነው እስራኤላዊያን በግብጽ ቀንበር በከበዳቸው በዚያን ጊዜ ወደ አባቶቻቸው አምላክ ወደ እግኢአብሔር ታላቅና መራራ ጩኸትን በጮኹ ጊዜ መከራቸውን ያይና ጩኸታቸውን ይሰማ ዘንድ

በአሁናዊ ነገር ግን ቀድሞውንም በእርሱ ዘንድ በታወቀ እውቀት ከህዝቡ ጋር ይግባባ የነበረው። ታዲያ ይህ በዘመናቸው በተመደቡበት ስፍራ ይመላለሱ ዘንድ ከተገኙ ፍጥረታት ሁሉ ጋር የዘላለም ሃሳቡን ለማከናወን አሁናዊ በሆነ እውቀት ከፍጥረቱ ጋር ግንኙነትን ያደርጋል። ይህም አሁናዊ እውቀት አሁን በዚህ ጊዜና ሰዓት ከእኛ ማስተዋልና እውቀት ፈጽሞ የራቀን የዛሬ ጉዳያችንን ከእርሱ በሚገኝ ጥልቅ እውቀትና ምሪት እርምጃን የሚያራምድ እውቀት ነው።

> "እግዚአብሔር ዛሬ አሁን በየትኛውም ቦታና ሁኔታ የሚደረጉ ማንኛቸውንም ክስተቶች ቀድሞ የሚያውቅ ብሎም በጊዜና በእውቀት ውስን ከሆኑ ፍጥረቶቹ ጋር አሁናዊ በሆነ ግንኙነት የሚግባባ ሁሉን አስቀድሞ የሚያውቅ አምላክ ነው።"

ከላይ ስለ እግዚአብሔር በሁሉም ስፍራ የመገኘት ማንነት ስንመለከት እንደተገለፀው በዚህም ሁሉን አዋቂነቱ በአንድ አይነት ወቅት በተለያየ ስፍራ ከቁጥር የበዙ ፍጥረቶቹ ጋር አሁናዊ በሆነ ግንኙነት ያልተገደበ አሁናዊ እውቀትን ለሁሉም መግለጥ ይችላል።

ይህ ድንቅ አምላክ ታላቁ እግዚአብሔር በሰማያት ላይ ከፈጠራቸው ለቁጥር የሚያዳግቱ በርካታ ቢሊዮን ከዋክብት መካከል በስም የማያውቀው ደግሞ በቀንና በሌሊት በቃሉ የማያሰማራው አንድም ኮከብ የለም።

*"ልቡ በእርሱ ዘንድ ፍጹም የሆነውን ያፀና ዘንድ የእግዚአብሔር አይኖች በምድር ሁሉ ላይ ናቸው።"* ከሰው ልጆች ጋር አብሮ መስራትን የሚወደው ይህ ሁሉን አዋቂ ጌታ ምንም እንኳን ሁሉን የሚያውቅ የወደደውን ለማድረግ ፍጹም የሆነ ሉአላዊ ስልጣን ያለው ቢሆንም ማንንም ሳይንቅ ከሰው ጋር ሲነጋገር ደግሞ ይታያል። ለምሳሌ ያክል ምንም እንኳን የቃየን አቤልን መግደል በእግዚአብሔር ዘንድ ቀድሞውኑ የታወቀ ቢሆንም ቃየን ወድዶ በፈቃዱ ሊያደርገው ያለውን ይህንን በደል እንዳያደርግ ገና በመስዋዕቱ በተናደደና ፊቱ በጠቆረ ጊዜ መልካም ያደርግና ፊቱ ያበራ ዘንድ ብሎም በደጁ እያደባች ያለችው ሞትን የምትወልደው ሀጢአት እንዳታገኘውና ቀድሞ እንዲነግስበት ሲመክረው ይታያል። በዚሁ መንገድ ዛሬም ምንም እንኳን እግዚአብሔር ኃያልና ሁሉን

አዋቂ የሆነ በማስተዋሉ ፍጹም የበረታ ቢሆንም በሁሉ ነገር ውስን ከሆነው የሰው ልጅ ጋር አሁናዊ በሆነ ግንኙነት የዛሬን እውቀት ሲገልጥ ደግሞ ይታያል።

"እግዚአብሔር የሰውን ልጅ እርምጃ፣ መቀመጥና መነሳት፣ መውጣትና መግባት ብሎም የልብ ሃሳብ ሁሉ የሚያውቅ ታላቅ አምላክ ነው።"

እግዚአብሔር የሰውን ልጅ እርምጃ፣ መቀመጥና መነሳት፣ መውጣትና መግባት ብሎም የልብ ሃሳብ ሁሉ የሚያውቅ ታላቅ አምላክ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በ፩ኛ ቆሮንቶስ 2፥፲፩ ላይ *"በእርሱ ውስጥ ካለው ከሰው መንፈስ በቀር ለሰው ያለውን የሚያውቅ ማን ነው?"* ብሎ እንደሚናገር የሰው ልጅ በውጭ ከሚታየው የአፍ ንግግር ብሎም የዕለት ከዕለት እንቅስቃሴው ፈጽሞ የተለየ ማንነትን ሰው ሊደርስበት በማይችለው ውስጠኛ ማንነቱ ይኸውም መንፈሱ ውስጥ ደብቆ ሊይዝ ይችላል። ነገር ግን የእግዚአብሔር ሁሉን አዋቂነት ሰው ራሱ እንኳን አንዳንድ ጊዜ በቅጡ የትኛው እንደሆነ የማይረዳውን ስሜት ወይም ሀሳብ የሆነ በውስጡ ያለ እውቀት ሳይቀር ለይቶ የሚያውቅ የጠለቀ ሁሉን አዋቂነት ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ በዕብራዊያን 4፥፲፫ ላይ እንደሚናገረው *"እኛን በሚቆጣጠር በእርሱ አይኖቹ ፊት ሁሉ ነገር የተራቆተና የተገለጠ ነው እንጂ በእርሱ ፊት የተሰወረ ፍጥረት የለም"* ብሎ ይናገራል። ይህንንም የመጨረሻ መደምደሚያ የሆነ ሀሳብ ከመናገሩ በፊት በቁጥር ፲፪ ላይ ይሄው ሁሉን አዋቂ ጌታ ህያውና የሚሰራ በሆነው ሁለትም አፍ ካለው ሰይፍ ይልቅ በተሳለው ቃሉ አማካኝነት አስቀድሞ ጠንቅቆ የሚያውቀውን ጥልቅ የሆነ የሰው ልጅ ነፍስና መንፈስ፣ ስሜትና ሃሳብ እንዲሁም ጅማትና ቅልጥም ሁሉ አልፎ ለይቶ የሚወጋ እንደሆነ ይናገራል። ይህንኑ ሁሉን አዋቂነቱን ጌታችን ኢየሱስ በማቴዎስ ወንጌል 6፥25-33 ላይ ባለው ክፍል ሰዎች ስለ ነፍስ በሚበሉትና በሚጠጡት እንዲሁም በሚለብሱት ጉዳይ ልባቸው እንዳይያዝ በተናገረበት ስፍራ ይህንን ሁሉ የሚለው የሚያስፈልጋቸውን ስለሚያውቅ እንደሆነ አብሮ ይናገራል።

እግዚአብሔር ያላወቀው ከፍጥረቱ መካከል ማንም ሊነግረው ይዞለት የሚመጣው አዲስ እውቀት በዘላለም ሁሉ ውስጥ የለም። ሁሉ በእግዚአብሔር ዘንድ

ባልተወዛገበ መልኩ ጥርት እና ኩልል ብሎ በጥልቀት የታወቀ ነው። እንዲያውም እግዚአብሔር ሰውን በሚያውቅበት ልክ እና መጠን ብሎም ከዚያ በቀረበ ደረጃ ሰው ራሱን ሊያውቅ እንኳን እንደማይሞክር በእውነት መናገር ይቻላል። *እግዚአብሔር ሁሉን አዋቂ ነው!*

እግዚአብሔር ሰዎች የልብ ሃሳባቸው፣ ንግግራቸውና ኑሯቸው ይመሳሰል ዘንድ በሰዎች ፊት ለታይታ እና ለጊዜያዊ ከበሬታ ያልሆኑትን እየመሰሉ በግብዝነት ለመኖር እንዳይሞክሩ ይፈልጋል። ነገራችን ሁሉ ግልጥ ብሎ ይታወቅ ዘንድ በእግዚአብሔር ፊት ራቁት ነውና ዳዊት እንደፀለየ የአፋችን ቃልና የልባችን ሀሳብ የተመሳሰለ እንዲሆን ያስፈልገናል። እግዚአብሔር ልብን ትቶ የሰውን ፊት ያይና ያደላ ዘንድ ሰው አይደለም። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ በ፩ኛ ሳሙኤል ፲፮፡፯ ላይ እንደሚናገረው እግዚአብሔር እንደ ሳሙኤልና እንደ ቀረው የሰው ልጅ ፊትንና የቁመትን ዘለግታ አይቶ የሚበይን ሳይሆን ውስጠኛውን የሰው ልጅ የድርጊት መነሻ ይኸውም ልብን የሚያይ ነው።

*"በእግዚአብሔር ፊት ግብዝ ከሆንና ለሰው ታይታ ከተለያየ የልብ ሃሳብና የአፍ ቃል እግዚአብሔር ያድነን።"*

በመጨረሻም ይሄው ሁሉን አዋቂ የሆነ ጌታ በፍጥረት እድሜ መጠናቀቅ ሰማይና ምድር ባለፉ ጊዜ ሊፈርድ ወደ ፊቱ የሚመጡን ሁሉ ጭምር በዘላለም መካከል በዘመናት ውስጥ ያለፉ ፍጥረቱን ሁሉ እርምጃ የሚያውቅ አምላክ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በኢሳይያስ ፲፩፡፫ ላይ ስለ ጌታችን ኢየሱስ በተናገረበት ስፍራ ላይ የእውቀት መንፈስ በላዩ ላይ ያረፈበት እንደሆነ ገልጾ ብይንና ፍርድን በጽድቅ እንጂ ያዛባ ዘንድ አይኑ እንደምታይና ጆሮው እንደምትሰማ እንደማይበይን ይናገራል።

ጨለማ በእርሱ ዘንድ አይጨልምም፤ ሌሊትም እንደ ቀን ታበራለች፤ እንደ ጨለማዋም እንደዚሁ ብርሃንዋ ነውና በእናት ሆድ ውስጥ ሰውሮ የሰውን ኩላሊት ጭምር የፈጠረው ሁሉ በፊቱ ራቁት ሆኖ የታወቀ ከሆነው ጌታ ማንም ሊሰወር አይቻለውም። ለዚህም ነው ዳዊት በመዝሙረ ዳዊት ምዕራፍ ፻፴፱ኛ ምዕራፍ ላይ *"አቤቱ መረመርኸኝ አወቅኸኝም፣ አንተ መቀመጤንና መነሳቴን አወቅህ፣ ሃሳቤን ሁሉ ከሩቅ አስተዋልህ፣*

*ፍለጋዬንና እረፍቴን አንተ መረመርህ፣ መንገዶቼን ሁሉ ቀድመህ አወቅህ፣ የአመጽ ቃል በአንደበቴ እንደሌለ፣ አቤቱ አንተ እነሆ የቀድሞውንና የኋላውን አወቅህ"* ብሎ ያለው።

ምንም እንኳን የሰው ልብ ከሁሉ ይልቅ ተንኮለኛ እጅግም ክፉ የሆነ ማንም ደግሞ ሊያውቀው የማይችል ጥልቅ ቢሆንም ለሰው ሁሉ በጽድቅ እንደ መንገዱ፣ እንደ ስራው ፍሬ ይሰጠው ዘንድ እግዚአብሔር ልቡን ይመረምራል ኩላሊቱንም ይፈትናል። ሰዎች በዘመናት መካከል እግዚአብሔር እንደሚያያቸውና እርምጃቸውን ሁሉ እንደሚያውቅ በመርሳት በጥፋት ጎዳና ውስጥ ርቀው ሄደው በእግዚአብሔር ፊት በፍጹም ማንነት ተገልጠው የታወቁ የልባቸውም ሃሳብ ሁሉ ጥርት ብሎ የታዩ በመሆኑ ከባድ ዋጋን ሲከፍሉ ተመልክተናል።

የሚስቱን ቃል ሰምቶ እንዳይበላ ከታዘዘው ዛፍ በልቶ አይኑ በመብራቱ ምክንያት ከእግዚአብሔር ይደበቅ ዘንድ ከሚስቱ ጋር ከተሸሸገው አዳም ጀምሮ፣ በሰገነቱ ላይ ሲንጎራደድ ቤርሳቤህን አይቶ ንግስናውን ተጠቅሞ ማንም ሳያውቅበት ተደጋጋሚ ጥፋትን በባሏ በኦርዩን ላይ ሳይቀር ፈጽሞ ምንም እንዳልተፈጠረ ኑሮውን በአገር ሰላም ሲመራ እስከነበረው ዳዊት እንዲሁም ዕለት ዕለት እኛ ሁላችን ዛሬ ጭምር በዚሁ ሁሉን አዋቂ በሆነው እግዚአብሔር ፊት ፈጽመን ተገልጠን የታወቅን እንደሆነ በግልጥ ይታያል።

*"እግዚአብሔር በተቀደሰ መቅደሱ አለ፣ የእግዚብሔር ዙፋን በሰማይ ነው፣ ዐይኖቹ ሰዎችን ይመለከታሉ ቅንድቦቹም የሰው ልጆችን ይመረምራሉ።"*

መዝሙረ ዳዊት 11:4

"ምንም እንኳን የሰው ልብ ከሁሉ ይልቅ ተንኮለኛ እጅግም ክፉ የሆነ ማንም ደግሞ ሊያውቀው የማይችል ጥልቅ ቢሆንም ለሰው ሁሉ በጽድቅ እንደ መንገዱ፣ እንደ ስራው ፍሬ ይሰጠው ዘንድ እግዚአብሔር ልቡን ይመረምራል ኩላሊቱንም ይፈትናል።"

- **የማስተንተኛ ጥያቄዎች**

1. እግዚአብሔር ሁሉን የሚያውቅ መሆኑ ስለ ማንነቱ ምን አስተማረህ?
2. እግዚአብሔር ልብህን እንደሚያይ ማወቅህ የየዕለት ኑሮህን እንዴት ሊለውጠው ይገባል?
3. የእግዚአብሔርን ሁሉን አዋቂነት መረዳትህ ዛሬ በሕይወትህ ውስጥ በየትኛው ጉዳይ ላይ ሁሉን ትተህ እንድታርፍ አስችሎሃል?

- **አሰላስል**

እግዚአብሔር ሁሉን የሚያውቅ አምላክ ነው። እውቀቱ ፍጹም እና የተሟላ ነው፤ ከፍጥረት ሁሉ ከእርሱ የተሰወረ አንድም ነገር የለም። ያለፈውን፣ ያለውንና የሚመጣውን ሁሉ ያውቃል፤ የልባችንን ሐሳብ፣ የሕይወታችንን ትግል፣ መሻትና ፍላጎቶቻችንን በፍጹም ያውቃል። ይህ እውነት በፊቱ በቅንነትና በግልጽነት እንድንኖር ያስተምረናል፤ እንዲሁም እኛ ማየት የማንችለውን ሁሉ የሚያውቀውን የእግዚአብሔርን ፍጹም ጥበብ እንድንታመን ያስተምረናል። ስለዚህ በራሳችን ማስተዋል ሳይሆን በእርሱ ፍጹም እውቀትና ጥበብ መታመን እንደሚገባን ሁልጊዜ ማስታወስ ያስፈልገናል።

- **ጸሎት**

በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፣ ፈጽመህ ታውቀኛለህ፣ በፍጹምም ፍቅር ትወደኛለህ፤ ስለዚህ አመሰግንሃለሁ። ልቤን መርምር፤ ደስ የማያሰኝህን ሁሉ ከእኔ አርቅ። በፊትህ በቅንነትና በእውነት እንድመላለስ እርዳኝ። በየትኛውም የማልፍበት ጎዳና እና ሁኔታ ከራሴ ማስተዋል ይልቅ በፍጹም ጥበብህ እንድታመን እርዳኝ።

በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አሜን።

- **የእርምጃ ጥቅስ**

*"አቤቱ፥ መረመርኸኝ፥ አወቅኸኝም። አንተ መቀመጤንና መነሣቴን አወቅህ፤ አሳቤን ሁሉ ከሩቅ አስተዋልህ። ፍለጋዬንና ዕረፍቴን አንተ መረመርህ፤ መንገዶቼን ሁሉ ቀድመህ አወቅህ፥።"*

*— መዝሙረ ዳዊት 139፥1-3 —*

## 2.9. እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው!

ባለፉት የመጽሐፉ ክፍሎች እግዚአብሔር የማንም ጥገኛ እንዳልሆነ፣ ታላቅና ኃያል የተፈራ አምላክ እንደሆነ የኃይሉም ብርታት እጅግ ኃያል እንደሆነ ተመልክተናል። አንድ አካል ምንም ያክል ኃይል ቢኖረው ሁሉን ደግሞ የሚችል ማንነት ከሌለው ኃይሉ ብቻውን ምንም ሊያደርግለት አይችልም። ለምሳሌ አንድ ሰው የምድርን ሀብት ሁሉ የግሉ ቢያደርግ እና በገንዘቡ የወደደውን ሁሉ የሚያደርግበት ኃይል ቢኖረውም እንኳን ይሄው ታላቅ ኃይሉና የገንዘብ አቅሙ እድሜውን በምድር ላይ በጨረሰ ጊዜ ከመሞት ሊያስቀሩት ግን አይችሉም። እግዚአብሔር ግን ኃያል ብቻ አይደለም ነገር ግን ሁሉን ቻይ ደግሞ ነው እንጂ።

የእግዚአብሔር ሁሉን ቻይነት ማንነቱ ሲሆን ኃያልነቱ ግን በዚሁ ሁሉን የሚችል ማንነት በተገለጠ ሁኔታ ሲሰራ የታየው የኃይሉ ታላቅነት ነው። ለዚህም ጥሩ ማሳያው ኤርምያስ በትንቢቱ ምዕራፍ 14፡9 ላይ ወደ እግዚአብሔር ሲፀልይ እንደዚህ ይለዋል፣ *"ያድን ዘንድ እንደማይችል ኃያል ስለ ምን ትሆናለህ?"* እዚህ ቦታ ላይ ከተጠቀሰው ቃል በግልጽ መረዳት እንደሚቻለው እግዚአብሔር በቂ ኃይል እንዳለው የተገለጠ ቢሆንም እንኳን ማዳን የሚችል ሆኖ ሳለ በሀጢአታቸው ምክንያት ማዳን እንደማይችልና ኃይልም እንደሌለው ሊያድናቸው እንደማይችል ሆኖ ይታያል።

እግዚአብሔር በኃይሉ ደግሞ በሁሉን ቻይነቱ ከፍ ያለውን እኛም የማናስተውለውን ታላቅና ድንቅ ነገር ያደርጋል። የእግዚአብሔር ሁሉን ቻይነት ከእርሱ ሉአላዊ የሆነ ማንነት ጋር ተስማምቶ የፈቃዱን ምክር በታላቅ ኃይሉ ለማድረግ የሚከለክለው ሳይኖር በፍጥረቱ መካከል ይገለጣል። የዚህ ፍጹም ያልተጋጨ ማንነቱ ማሳያ የፍጥረት አፈጣጠርና ስርዓት ነው። በፈቃዱ ምክር እርሱ እንደወደደ ሉአላዊ በሆነ ማንነቱ በታላቅ ኃይሉም ደስ እንደሚያሰኘው አድርጎ ፍጥረቱን ፈጠረ። እንዲሁም የፈጠራቸው ሁሉ እርሱ ራሱ ባስቀመጠላቸው ስርዓት ይሄዱ ዘንድ በቃሉ ፈጠራቸው በአፉም እስትንፋስ አጸናቸው።

ይህንን ሁሉን ቻይነቱን ፍጥረቱ ያውቅና ይረዳ ዘንድ ብሎም በዚህ የእግዚአብሔር ማንነት ላይ ተመስርቶ በፊቱ በአገባብ ይመላለስ ዘንድ እግዚአብሔር

ከክብሩ ወርዶ በተለይም ራሱን ለሰው ልጆች በቅርበትና በወዳጅነት ሊገልጥ ፈለገ። ነገር ግን ሰው እግዚአብሔር ማን እንደሆነ በጥቂቱ እንኳን የተረዳ አልነበረምና ደጋግሞ በእግዚአብሔር ላይ በማመፁ ምክንያት በተደጋጋሚ ወደቀ። በዚሁ የመውደቅና የመነሳት የሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ ከሰው ጋር ያለውን ጉዳይ ያልጨረሰው እግዚአብሔር ያድነው ዘንድ የራሱን ህዝብ ሊያወጣ ፈልጎ አብርሃም የሚባል ሰው ጋር ደረሰ። ለዚህም ሰው እግዚአብሔር በተለያየ ጊዜ ያውቀውና በፊቱ ተገቢ የሆነን ምልልስ ይመላለስ ዘንድ በልዩ ልዩ ሁኔታ ራሱን የገለጠለት ሲሆን በዘፍጥረት 17፥1 ላይ ራሱን የገለጠበት መንገድ አንዱና ዋነኛው ማንነቱ ነው።

ይኸውም ህዝብ ሊያደርገውና ሊባርከው ቃል ገብቶ ከእናትና ከአባቱ ቤት እንዲወጣ ብሎም ወደማያውቀው ነገር ግን እግዚአብሔር ወደሚያሳየው ምድር እንዲወጣ ታዞ እግዚአብሔርን አምኖ ከካራን የወጣው አብርሃም ሃያ አምስት አመታትን ጠብቆ ልጅን ባልወለደበት ደግሞም በስጋው አርጅቶ የዘጠና ዘጠኝ አመት ሰው በሆነበት ጊዜ የገለጠለት ማንነት ነው። ይህም ሁኔታ በሰው እይታ አብርሃምና ሳራ በእድሜአቸው ሸምግለው ፈጽመውም አርጅተው የነበሩበት በሴቶች የሚሆነውም ልማድ ከሳራ ተቋርጦ የነበረበት የእርጅናቸውም ብዛት ለፍትወት የማይመች በሆነበት ወቅት እግዚአብሔር እርሱ ማን እንደሆነ የገለጠበት ማንነት ነበር። ይህም *"እኔ ኤልሻዳይ ነኝ በፊቴ ተመላለስ ፍጹምም ሁን ቃል ኪዳኔንም በእኔና በአንተ መካከል አደርጋለሁ"* ብሎ በዚህ ለሰው በሚያስቅና ፈጽሞ ያለቀና የደቀቀ የሞተ ሁኔታ ውስጥ ምውት ከሆነው የሳራ ማህፀን ውስጥ በሁሉን ቻይነቱ እግዚአብሔር እንደተናገረ ያደርግ ዘንድ እንደ ቃሉ ለታላቅ ህዝብ የሚሆንበትን ዘር ይኸውም ሳቅ የሆነውን ይስሃቅን ያመጣበት ሁኔታ ነው።

በዚህም የእግዚአብሔር ጉብኝትና የማይመስል ንግግር ወቅት ሳራ የራሷንና የባሏን ሁኔታ ተመልከታ በሰውም አይን ፈጽሞ የማይሆን የሞተ ነገር እንደሆነ አስባ የእግዚአብሔርን ሁሉን ቻይነት ባለማወቋ በሳቀች ጊዜ እግዚአብሔር ስለ ራሱ እንደዚህ አለ፤ *"በውኑ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር አለን?"*። ጥቂት ምዕራፎችን አልፎ በዘፍጥረት 21፥1 ላይ ታዲያ እንደዚህ ይላል *"እግዚአብሔርም እንደተናገረው ሳራን አሰበ፣ እግዚአብሔርም እንደ ተናገረው ለሳራ አደርገላት።"* እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው!

ኢዮብ እግዚአብሔር ሁሉን ያደርግ ዘንድ ቻይ እንደሆነ ሃሳቡም ይከለከል ዘንድ ከቶ እንደማይቻል ለማወቅ ስለ እግዚአብሔር ከመስማት አልፎ እግዚአብሔርን "በአይኑ ማየት" ነበረበት። ይህም በመስማት ብቻ ያወቀውና የተረዳው የእግዚአብሔር ማንነት የእግዚአብሔርን ሁሉን ቻይነት ያልገለጠለት ሆኖ በትንሿ አዕምሮው በተረዳው ልክ እግዚአብሔር እርሱ እንደሆነ ወስኖ አጥሮት ከነበረበት አጥር የወጣ ከብዙ ዋጋ መከፈልና መከራ በኋላ መሐሪ የሆነው ሁሉን ቻይ ጌታ በአውሎ ነፋስ ውስጥ ሆኖ ተገልጦ ያስረዳው የእግዚአብሔር ማንነት ነበር።

ኤርምያስ በ32ኛው ምዕራፍና በ17ኛው ቁጥር ወደ እግዚአብሔር ሲፀልይ እግዚአብሔርን እንደዚህ ይለዋል፣ *"አቤቱ ጌታ እግዚአብሔር ሆይ እነሆ አንተ ሰማይንና ምድርን በታላቅ ኃይልህና በተዘረጋች ክንድህ ፈጥረሃል* ***ከአንተም የሚያቅት ነገር የለም።*** *ስምህ ታላቅና ኃያል አምላክ የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር ነው። በምክር ታላቅ በስራም ብርቱ ነህ ለሁሉም እንደ መንገዱና እንደ ስራው ፍሬ ትሰጥ ዘንድ አይኖችህ በአዳም ልጆች መንገድ ሁሉ ተገልጠዋል።"*

"የእግዚአብሔር ሁሉን ቻይነት በሃይሉ ብርታት ተግባራዊ የሚሆን እውነት ሲሆን ይህም ማንነቱ በዘመናት መካከል ሃይሉ ደክሞ ወይም ከመስራት ታክቶ አይለወጥም።"

ይህ የእግዚአብሔር ሁሉን ቻይነት በኃይሉ ብርታት ተግባራዊ የሚሆን እውነት ሲሆን ይህም ማንነቱ በዘመናት መካከል ኃይሉ ደክሞ ወይም ከመስራት ታክቶ አይለወጥም። ያለምንም ገደብ ሁሉን በታላቅ ኃይሉ እያደረገ ከጥንት ጀምሮ እርሱ ብቻውን የሆነ ከእጁም የሚያመልጥ አንዳች የሌለው እሰራለሁ የሚከለክልስ ማን ነው? ያለ በዘመናት መካከል ያው ሆኖ ሳይለወጥ "ያለና የሚኖር" እንደሆነ ለዘላለም የሚኖር ብቻውን ኤልሻዳይ አምላክ የሆነው እግዚአብሔር ነው።

ይሄው እግዚአብሔር የሚለው ማንነቱ በዘፀዓት ምዕራፍ 3 ላይ እግዚአብሔርና ሙሴ ባደረጉት ንግግር ውስጥ የተጀመረና በዘፀዓት ምዕራፍ 6 ላይ እግዚአብሔር በሚለው ስሙ ለአብርሃም ለይስሃቅና ለያዕቆብ እንዳልተገለጠ ነገር ግን ሁሉን

እንደሚችል አምላክ ለአባቶቻቸው ራሱን እንደገለጠ ነግሮ ያስተዋወቀው ስሙ ነው። ይህ እግዚአብሔር የሚለው ስም ሁሉን ቻይነቱን አካቶ የተገለጠ *"እኔ እኔ ነኝ"* የሚለውን ስሙን ያስተዋወቀበትን ይዘት የተሸከመ ከዚያ በኋላ በዘመናት መካከል "ያህዌህ" /"ጆሆቫ"/ /"አዶናይ"/ ወዘተ እየተባለ የተገለጠና የተተነተነ ታላቅ ስም ነው። በእነዚሁ ስሞች ውስጥ ታዲያ እግዚአብሔር ሁሉ በሁሉ የሆነ ሁሉን ቻይ አምላክ እንደሆነ ስሙን ያወቁ ሁሉ ይረዱ ዘንድ "ያህዌህ ንሲ" /እግዚአብሔር አላማዬ/፣ ያህዌህ ራፋ (አዳኙ እግዚአብሔር)፣ ያህዌህ ጅሪ /መጋቢው እግዚአብሔር/ ወዘተ በሚለው ሁሉን በሁሉ የሚያደርግ በወደድነው ሁኔታ የምንፈልገውን ሁሉ መሙላት የሚችል ሁሉን ቻይ አምላክ እንደሆነ የተገለጠበት ስም ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ በኢሳይያስ 14፡27 ላይ ሲናገር *"የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር ይህንን አስቧል የሚያስጥለውስ ማን ነው? እጁም ተዘርግታለች የሚመልሳትስ ማን ነው?"* ብሎ ይላል። እግዚአብሔር ሁሉን ያደርግ ዘንድ ቻይ የሆነ ሃሳቡም ይከለከል ዘንድ በፊቱ አታደርግም ብሎ የሚቆም ማንም የሌለው ሁሉን ማድረግ የሚችል አምላክ ነው። የትኛውም በትንሿ የሰው አእምሮ ፈጽሞ ሊሆን አይችልም የሚባል ነገር ሁሉ ለእግዚአብሔር ሲበዛ እጅግ ቀላል ነው።

> "እግዚአብሔር ሁሉን ያደርግ ዘንድ ቻይ የሆነ ሃሳቡም ይከለከል ዘንድ በፊቱ አታደርግም ብሎ የሚቆም ማንም የሌለው ሁሉን ማድረግ የሚችል አምላክ ነው።"

እርሱ የደረቁ አጥንቶችን ስጋና ጅማት እስትንፋስም ሰጥቶ ታላቅ ሰራዊት ያደርጋል። ይህ ጉዳይ ለህዝቅኤል በጥያቄ መልክ በቀረበበት ወቅት መልሱ እግዚአብሔር ሆይ እነዚህ አጥንቶች በህይወት ይኖሩና አይኖሩ እንደሆነ አንተ ታውቃለህ የሚል ነበር። የአራት ቀንን ሬሳ መግነዙን ፈትቶ ከመቃብር አውጥቷል፣ ሙታንን ያስነሳል፣ እውራንን ያበራል፣ አጋንንትን ያስወጣል፣ ነገስታትን ያዛል፣ ከዙፋናቸው ያወርዳል ያወጣል፣ ወንዞችን እንደ ወደደ ያፈሳል፣ ውሃን በደመና ያስራል፣ ወደሚፈልገው ስፍራ ወስዶ ዝናብ አድርጎ ያዘንባል፣ ፍጥረትን ሁሉ ይመግባል፣ ከዋክብትን ያሰማራል ወዘተ… ፍጥረቱን ሁሉ

በስልጣኑ ቃል ደግፎ ይዟል። አህዛብ በፊቱ በገንቦ እንዳለች ጠብታ ናቸው በሚዛንም እንዳለ ትንሽ ትቢያ ተቆጥረዋል፤ ደሴቶችን እንደ ቀላል ነገር ያነሳል። ፍጥረት ሁሉ ለዚህ ሁሉን ቻይነቱ ያለ ምንም ማጉረምረም ይታዘዛል።

ሰው በዚህ መካከል አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ዝም ሲል እና እጁ በልዩ ልዩ ምክንያት በተገለጠ ሁኔታ በመካከላችን ባልታየች ጊዜ ወይም ደግሞ እናይ ዘንድ እንዳንችል የልቦና አይኖቻችን በታወሩ ጊዜ እግዚአብሔር ከሁሉን ቻይነቱና ከታላቅ ኃይሉ ድካም ያገኘው አሰራሩ ባለፈው ዘመን የቀረ እጁም ከማዳን ያጠረች ይመስለዋል። ነገር ግን እግዚአብሔር ለዘላለም ባልተለወጠ ሁኔታ ሁሉን ቻይ ሲሆን እርሱ የዘላለም አምላክ የምድር ዳርቻ ፈጣሪ ነውና ፈጽሞ አይደክምም አይታክትም፣ ማስተዋሉም አይመረመርም በኃይሉ ብዛትና በችሎቱ ብርታት አንድስ እንኳን አይታጣውም።

ይህ ሁሉን ቻይ ጌታ እግዚአብሔር ይህንኑ ማንነቱን በፍጥረቱ መካከል ሉአላዊ በሆነ መብቱ ሳይከለከል የሚያደርግ ሲሆን ኃይሉን ይገልጥበትና ታላቅነቱን ያሳየው ዘንድ የሰው ልጅን በልዩ ልዩ ሁኔታ አብሮት እንዲሰራ ያደርጋል። በዚህ ግንኙነት ታድያ ሁሉ ከእርሱ፣ በእርሱና ለእርሱ ሲሆን የሰው ልጅ እግዚአብሔር ማንነቱን በእርሱ ሁኔታ ይገልጥ ዘንድ ፈቃደኛ ከመሆንና አብሮ ለመስራት ከመጨከን ለዚህም የሚከፈለውን የትኛውንም ዋጋ በገዛ ራሱ የእግዚአብሔር ፀጋ ለመክፈል ከመወሰን ሲያልፍም ከመክፈል ሌላ አንዳች የሚያዋጣው ነገር የለም።

የኢየሱስ እናት ማርያም በሉቃስ ወንጌል 1:49 ላይ እንዳለች እኛ የማናውቀውን ታላቅና ሃይለኛ ነገር በገዛ ማስተዋሉና ኃይሉ ብርቱ የሆነ እርሱ በእኛ ታላቅ ስራን ያደርጋል ስሙም ቅዱስ ነው። ነገር ግን በዚህ አብሮ ለመስራት በሚገኝ እድል ከእግዚአብሔር ጋር ስራን የጀመሩ ሁሉ እግዚአብሔር በሁሉን ቻይነቱ የሚያደርገውን ነገር ለመገመት እንኳን ሲቸገሩ ብዙ ጊዜም ይህማ እንዴት ይሆናል ብለው በራሳቸው ውስን ማንነት እግዚአብሔርን ሲገምቱት ይታያሉ።

ሙሴ በኦሪት ዘኁልቍ ምዕራፍ 11 ላይ እንዲመራው የተሰጠው እግዚአብሔርን በማወቅ እድገት ዳዴ ላይ የሚገኝ አስቸጋሪ ህዝብ ስጋን በጠየቁት ጊዜ በምሬት የዚህን ህዝብ ሸክም አሁን ከደረሰበት በላይ ሊሸከም እንደማይችልና እንደተማረረ ገልፆ

በእግዚአብሔር ፊት ሞገስ ቢያገኝ ይገድለው ዘንድ እንደሚፈልግ ጠየቀ። እግዚአብሔር ለዚህ የሙሴ ምሬት መልስ ይሆን ዘንድ ረዳቶችን ከሰጠ በኋላ የህዝቡን የስጋ ጥያቄ ለመመለስ ነገ ስጋ ስለሚበሉ ይቀደሱ ዘንድ ተናገረ። ይህ የእግዚአብሔር መልስ በምድር በዳ መካከል ላለው ከ600,000 በላይ እግረኛ ህዝብ የሚበቃ ወር ሙሉ የሚበላ በቂ የስጋ መጠን ለማግኘት በሰውኛ አስተሳሰብ በቂ የበሬና የበግ መንጋ ከየት እንደሚመጣ ወይ ደግሞ በቂ የባህር አሳ ከየት እንደሚሰበሰብ ሊገባው ስላልቻለ ከየት ይመጣል ብሎ የእግዚአብሔርን ሁሉን ቻይነት ጠየቀ። ነገር ግን እግዚዘብሔር ሁሉን ያደርግ ዘንድ ቻይ የሆነ የተፈጠረውን ሁሉ ካለመኖር ወደ መኖር ያመጣ ጌታ ነበርና *በውኑ የእግዚአብሔር እጅ አጭር ሆነ?* ብሎ ያለውን እንደሚያደርግ አስረግጦ ነገረው ደግሞም አድርጎ አሳየው።

በተመሳሳይ ሁኔታ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱ በተለያየ ጊዜ እርሱን ለማወቅ በሚያደርጉት ጉዞ ውስጥ ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል የሚሉ ጥያቄዎችን ያነሱ ነበር። ነገር ግን ጌታችን ኢየሱስ ማዕበልና ወጀቡን ፀጥ እያደረገ፣ በውሃ ላይ እየተራመደ፣ ሁለት አሳና አምስት እንጀራን ለ5000 ወንድና ቁጥር ለሌለው ሴትና ህፃን እየመገበ እርሱ በእውነት ዛሬም እጁ ከማዳን ያላጠረች የማይደክምና የማይታክት ሁሉን ቻይ ጌታ እንደሆነ ያሳያቸው ነበር። ዛሬም በዚህ ዘመን ያለን ሁላችን በፍጥረት ሁሉ ላይ ተገልጦ ከሚታየው የእግዚአብሔር ሁሉን ቻይነትና ታላቅ ኃይል ይልቅ የገዛ ማስተዋላችንን ስንደገፍ ወይም ደግሞ ደካማውን የጠላት አቅም ስንፈራ በዚህም ከእምነት ደጋግመን ስንጎድል እንታያለን። ነገር ግን እግዚአብሔር ትናንት እንደነበር ዛሬም ኃይሉ ያልደከመ ሁሉን ያደርግ ዘንድ ቻይ የሆነ ኤልሻዳይ አምላክ ነው።

> "እግዚአብሔር ትናንት እንደነበር ዛሬም ሃይሉ ያልደከመ ሁሉን ያደርግ ዘንድ ቻይ የሆነ ኤልሻዳይ አምላክ ነው።"

ከዚሁ በተቃራኒ እግዚአብሔር የእርሱን ሁሉን ቻይነት በደካማው የሰው ማንነት ሊገልጥ በወደደ ጊዜ ሁሉ ምንም እንኳን የሆነው ሁሉ የተደረገው ከእርሱና በእርሱ ቢሆንም ለእርሱ የተገባውን ክብሩን ለእርሱ በመስጠት ፋንታ በርካቶች ለራሳቸው ሊወስዱ ሲሽቀዳደሙ ይታያል። ይህም እግዚአብሔርን የሚያስቆጣውና ክብሩን ለራሱ ይመልስ ዘንድ በቅንዓቱና በቁጣው እንዲንቀሳቀስ ያደርገዋል።

የሰው ልጆች እግዚአብሔር ታላቋን የፀናችውን እጁን ብሎም የተወደደውን ልጁን በእነርሱ ሁኔታ ሊገልጥ በወደደበት ጊዜ ሁሉ በእርሱ ለዚህ ስራ በፀጋ ብቻ የተመረጡ መሆናቸውን በማወቅ በታላቅ ትህትናና አክብሮት በፊቱ እንዲመላለሱ ያስፈልጋቸዋል። በዚህም ተገቢ የሆነን ክብር ክብሩ ለሚገባው እግዚአብሔር ሳያቋርጡ ሊያመጡለት የተገባቸው ብርቱ የሆነው እርሱ በእነርሱ ታላቅ ስራን ሊሰራ እንደወደደ ያውቁ ዘንድ፣ እነርሱ ግን በራሱ በእርሱ ፀጋ ሊያደርጉ የተገባቸውን ያደረጉ ባሪያዎች መሆናቸውን ማወቅ ያስፈልጋቸዋል።

የትኛውንም አይነት ተዓምራትና ድንቅ በማንም ሰው በኩል እግዚአብሔር ቢያደርግ ያ የተደረገ ነገር ሁሉ የተደረገው በእግዚአብሔር እንጂ ነገሩ በተደረገባቸው ሰዎች አለመሆኑን ህዝቡም ሊገነዘብና እይታውን ሊያስተካክል ይገባዋል። እኛ ፈጽመን በደከምንና ያለ እርሱ ባዶ መሆናችንን ይበልጥ ባወቅን ራሳችንንም መካድ በቻልን ቁጥር እግዚአብሔር የበለጠ ኃይሉን በእኛ በኩል ለመግለጥና ክብሩን ለራሱ ለመውሰድ ይመቸዋል።

ይህ ታላቅ የሆነ ገናና ጌታ ሁሉን ቻይነቱ በዘመናት መካከል ተገልጦ የታየ ሲሆን ዛሬም በዚያው ማንነቱ ሊታወቅ በማይችል ብርታቱ እየሰራ አለ። እግዚአብሔር አንድን ስራ ለማከናወን የሚያወጣው ኃይልና የሚደክመው ድካም የሌለ ሲሆን በአፉ ቃልና እስትንፋስ ብቻ የሚወደውን ሁሉ ያለ ማንም ከልካይ ያደርጋል። እንደ ጢሮስ ያሉ በምድር ላይ የሚገኙ ታላላቅ መንግስታትን ከትዕቢታቸው ለማስተንፈስ እግዚአብሔር ሰራዊትን አያሰማራም፤ ቃልን ብቻ ይናገራል የወደደውም ያለ ከልካይ ይሆንለታል። ይህም የኃይሉ ታላቅነት በልጁ ሞት ወቅት በሞቱ ያፈራረሰውን በፍጥረት አለሙ ውስጥ የሚገኝ የተዋቀረ የጨለማ አገዛዝ ከነ ስርዓትና መዋቅሩ ከንቱ ባደረገ ጊዜ የተገለጠ ከየትኛውም ፍጥረታዊ አቅም ኃይል የእግዚአብሔር ድካም በእጅጉ እንደሚበልጥ የታየበት የኃይሉ ታላቅነት ማሳያ ነው።

እግዚአብሔር ሁሉን ያለ ከልካይ ማድረግ የሚችል ሲሆን ከማንነቱ ጋር የሚጣረሱ ፈጽሞ ሊያደርጋቸው የማይችሉ ነገሮችም ደግሞ አሉ። እግዚአብሔር ይዋሽ ዘንድ እንዳይችል እርሱ ራሱ እውነት ነው፣ ሳይታመን እንዳይገኝ ፍጹም ታማኝ ነው፣ ይሞት ዘንድ እንዳይችል የሁሉ ፈጣሪና አስተዳደሪ የሆነ የዘላለም አምላክ ነው። ይሄው

የእግዚአብሔር ሁሉን ቻይነትና የተገለጠ የኃይሉ ታላቅነት በመካከላችን ዛሬም ይገለጥና ይታይ ዘንድ በዚህም በርካቶች ካሉበት የጨለማ አገዛዝ ነጻ ወጥተው በዚህ የፍቅር መንግስት ተካፋይ እንዲሆኑ፣ በጊዜው ከፍ እንዲያደርጋቸው አውቀው በታላቁና ሃይለኛው እግዚአብሔር እጅ ስር በትህትና እና የአክብሮት ፍርሃት ያለ እርሱ ምንም መሆናቸውን በሚገባ ተረድተው ራሳቸውን ያዋረዱ ቅኖችና ትሁታንን ዛሬም ይፈልጋል።

> "እኛ ፈጽመን በደከምንና ያለ እርሱ ባዶ መሆናችንን ይበልጥ ባወቅን ራሳችንንም መካድ በቻልን ቁጥር እግዚአብሔር የበለጠ ሃይሉን በእኛ በኩል ለመግለጥና ክብሩን ለራሱ ለመውሰድ ይመችዋል።"

## የማስተንተኛ ጥያቄዎች

1. እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ መሆኑ ስለ ማንነቱ ምን አስተማረህ?
2. የእግዚአብሔርን ሁሉን ቻይነት ማወቅህ እምነትህን እንዴት ሊያጸናው ይገባል?
3. ዛሬ በየትኛው የሕይወትህ ጉዳይ በእግዚአብሔር ኃይል ላይ ይበልጥ መታመን ያስፈልግሃል?

## አሰላስል

እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ አምላክ ነው። የእርሱ ኃይል ወሰን የለውም፤ ለእርሱ የሚያስቸግር ወይም የማይቻል ነገር የለም። የወሰነውን ፈቃድና ዓላማ ሊያስቆም ወይም ሊቃወም የሚችል ማንም የለም። ይህን እውነት ስናስብ በራሳችን ጥንካሬ ሳይሆን በእርሱ ኃይል ላይ መደገፍን እንማራለን። ድካማችን፣ ፈተናችን ወይም የማይቻል የሚመስል ሁኔታ ቢገጥመንም፣ ሁሉን ቻዩ አምላክ ከሁሉ በላይ እንደሆነ እናውቃለን። ስለዚህ በየዕለቱ በእርሱ ኃይል ተደግፈን በእምነት መኖር እንደሚገባን ሁልጊዜ ማስታወስ ይገባናል።

## ጸሎት

በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፣ ሁሉን ቻይ አምላክ ስለሆንህ እናመሰግንሃለን። በማንኛውም ሁኔታ በአንተ ኃይል እንድታመን እርዳኝ። ስደክም በራሴ ሳልታመን በአንተ እንድደገፍ አስተምረኝ። በእምነትና በትሕትና በፊትህ እንድመላለስ ጸጋህን አብዛልኝ።

በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አሜን።

## የአርምሞ ጥቅስ

*"አቤቱ ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፥ እነሆ፥ አንተ ሰማይንና ምድርን በታላቅ ኃይልህና በተዘረጋች ክንድህ ፈጥረሃል፥ ከአንተም የሚያቅት ነገር የለም።"*

*— ትንቢተ ኤርምያስ 32፥17 —*

## 2.10. እግዚአብሔር ቅዱስ ነው!

*“አቤቱ፥ በአማልክት መካከል እንደ አንተ ያለ ማን ነው? በምስጋና የተፈራህ፥ ድንቅንም የምታደርግ፥ በቅድስና የከበረ እንደ አንተ ያለ ማን ነው?”*

ኦሪት ዘጸአት 15:11

ይህ ቅዱስ የሚለው ቃል በሐይማኖታዊ ልምምዶቻችን እንዲሁም በመንፈሳዊ ምልልሶቻችን ደጋግመን የምንለው በተለያዩ ዝማሬዎች፣ ስብከትና ትምህርቶች የምንሰማው በተለየ ሁኔታ የእግዚአብሔርን ማንነት ለመግለጽ የምንጠቀምበት ልዩ ቃል ነው። ነገር ግን የቃሉ ትርጓሜና ይህንኑ ቃል ተጠቅመን የምንላቸው ነገሮች በእርግጥ በቃሉ ሊተላለፍ የተፈለገው መልዕክት ምን እንደሆነ እንደሚገባ ተረድተን የምንላቸው ግን አይመስልም። ይህ ደግሞ በተለይም የእግዚአብሔርን ልዩ የሆነ ማንነት ይኸውም ቅድስናውን እንደሚገባ እንዳንረዳ ከማድረጉም ባለፈ ይህንኑ ማንነቱን በጥቂቱም ቢሆን በአግባቡ የተረዳና ያወቀ ሰው በዚህ ቅዱስ አምላክ ፊት ሊኖረው የሚገባውን የህይወት ምልልስ ብሎም ለአምልኮ በፊቱ በቀረበ ጊዜ በዚያ እርሱ በሚገኝበት ስፍራ በመገኘቱ ሊኖረው የሚገባውን ለክብሩ የሚገባ ፍርሃትና አክብሮት እንዳይታይበት አድርጎት በልማዳዊ የሐይማኖት ምልልስ ውስጥ ብቻ እንዲወጣና እንዲገባ ሲያደርገው ይታያል።

ቅዱስ ማለት ፍጹም የተለየ፣ እጅግ ከፍ ያለ፣ እንከን አልባ፣ ፍጹም፣ ልዩ፣ የላቀ፣ ለብቻው የሆነ፣ ያልተቀላቀለ፣ ነው፤ እርሱ ራሱ የራሱ “ዓለም” የሆነ፣ ያልተመሳሰለ፣ እኩያ የሌለው፣ ወዘተ የሚሉ ትርጓሜዎች ያሉት ጥልቅ ቃል ነው። (ግዛው, 1994) (Merriam-Webster, n.d.) በዚህም ቃላት ፍች ውስጥ ከላይ እንደሚታየው እንደዚህ አይነት ማንነት ያለው የትኛውም አካል በእርግጥ ግልጽ የሆነ ከሌላ ነገር ጋር ፈጽሞ የማይመሳሰል እጅግ ከፍ ያለ ማንነት ሊኖረው የተገባ ነው። በዚህም መሰረት እግዚአብሔር ቅዱስ ነው ብለን ስንል ቢያንስ ከላይ ባሉት የቃሉ ፍች የሆኑ አቻ ቃላት ልክ እግዚአብሔር የተለየ እና ከፍ ያለ የሆነ ማንነት ያለው ሆኖ የእርሱ ብቻ በሆነ ሌላ ማንም የማይገኝበት የብቻው የሆነ “ዓለም” ኖሮት በልዩ ማንነት ውስጥ እንደሚገኝ ልንረዳ ያስፈልገናል ማለት ነው።

እግዚአብሔር ቅዱስ ነው! ይህንን ልዩ የሆነ የእግዚአብሔር ማንነት በምንም አይነት መንገድና በእንዴትም አይነት የሰው ውስን ቃላት ለመግለጽ አዳጋች ቢሆንም በእግዚአብሔር ጸጋ ሁሉ ይቻላልና እርሱ ራሱ ለእናንተ ይህንን ለምታነቡ እንዲነገርና እንዲብራራ ይወዳልና ጸሃፊው ከፈለገውና እርሱን ለመግለጥ ከሞከረበት ቋንቋ በላይ በሆነ ልዩ መገለጥ ራሱን እንደሚያብራራላችሁ በማመን በብዙ ትህትና የእግዚአብሔርን ቅድስና ለመግለጥ ይሞክራል።

እግዚአብሔር ቅዱስ ነው ብለን ስንል እርሱ ብቻውን የሚገለጽበት በሌላ በምንም አይነት ምሳሌና መልክ ፈጽሞ ሊብራራ የማይችል ከፍ ያለ ማንነት ያለው እጅግ የተለየ ሆኖ ፍጹም በሆነ አንዳች እንከን የሌለበት ሁኔታ ከየትኛውም ፍጥረቱ ጋር በማንነት ሳይቀላቀል ከማንም ጋር ሳይመሳሰል ልቆ የሚገኝበት የራሱ የሆነ የብቻው የሆነ ዓለም ያለው ነው እያልን ነው። ይህም ልዩነቱ በታላቅነቱ፣ በኃይሉ፣ በአሰራሩ፣ በግርማው፣ በጽድቁ፣ በእውነተኛነቱ፣ በማንም ጥገኛ ባለመሆኑ ወዘተ ሊገለጡ በሚችሉ ማንነቶቹ ፍጹምና የተለየ በሆነ ሌላ ማንም ሊቀርበው በማይችል ሁኔታ ከፍ ብሎ የሆነ ጊዜ ላይ ሊጠናቀቅና ሊለወጥ በማይችል ሁኔታ ዘላለማዊ ሆኖ የሚኖር መሆኑ ነው።

> "እግዚአብሔር ቅዱስ ነው ብለን ስንል እርሱ ብቻውን የሚገለጽበት በሌላ በምንም አይነት ምሳሌና መልክ ፈጽሞ ሊብራራ የማይችል ከፍ ያለ ማንነት ያለው እጅግ የተለየ ሆኖ ፍጹም በሆነ አንዳች እንከን የሌለበት ሁኔታ ከየትኛውም ፍጥረቱ ጋር በማንነት ሳይቀላቀል ከማንም ጋር ሳይመሳሰል ልቆ የሚገኝበት የራሱ የሆነ የብቻው የሆነ አለም ያለው ነው እያልን ነው።"

በመዝሙረ ዳዊት ምዕራፍ 86 ቁጥር 8 ላይ *"ጌታ ሆይ ከአማልክት መካከል እንደ አንተ ያለ የለም፣ ከአንተም ስራ ጋር የሚወዳደር ስራ የለም"* ብሎ የእግዚአብሔርን ፍፁም የሆነ ከፍጥረቱ የተለየ ማንነት ይናገራል።

በማንነት እንዲሁም በስራ እግዚአብሔርን የሚመስል አንዳች ሌላ የለም።

ምንም እንኳን ከእግዚአብሔር በቀር ሌላ አምላክ የሌለ ቢሆንም ሰዎች ቅርጽ ሰርተውና የሆነ ስፍራ ሰጥተው አማልክት ይሆኗቸው ዘንድ ስለወደዱ ብቻ አህዛብ አጋንንቶችን አማልክት ብለው ሲያመልኩ ይታያሉ። ይሁን እንጂ ምንም እንኳን በርካታ ህዝብ እግዚአብሔርን ትቶ እነዚህኑ አማልክት ያላቸውን አጋንንቶች የሚያመልክ ቢሆንም አንዳቸውም ከእግዚአብሔር ጋር የሚመሳሰል ወይም ደግሞ የሚጋራ እንኳን መልክና ባህርይ የሌላቸው ፍጥረቶች ናቸው።

በመዝሙረ ዳዊት ምዕራፍ 82 ላይ እግዚአብሔር የተሰጣቸውን ግዛት በታማኝነት እንዲያስተዳድሩ የፈቀደላቸውን በመንፈሱ አለም የሚገኙ የልዑል (የእርሱ) ልጆች የሆኑ መንፈሳዊ አካላትን *"እኔ እናንተ አማልክት ናችሁ አልኩ"* ብሎ ይላቸዋል። ይሁን እንጂ ምንም እንኳን አማልክት (ኤሎሂም) ናችሁ ይበላቸው እንጂ ከእርሱ ባህርይ በተለየ መልኩ ፍትህን የሚያጓድሉ፣ ለክፉዎች የሚያደሉ፣ ለአቅመ ቢሶችና ለድሃ አደጎች የማይፈርዱ፣ የችግረኛና የምስኪኑን መብት የማያስከብሩ፣ የተሰጣቸውን ስልጣን በአግባቡ የማይጠቀሙ፣ በዚህም ምክንያት ምንም እንኳን የልዑል ልጆችና አማልክት ቢሆኑም እንደ ማንኛውም ሰው የሚሞቱ ብሎም እንደማንኛውም ገዥ የሚወድቁ ፍጥረቶች እንደሆኑ ይናገራል።

ይህ "ኤሎሂም" የሚለው ቃል በመንፈሳዊው አለም የሚገኙ ሃይላትን ሁሉ በአንድነት የሚወክል ስያሜ ሲሆን እግዚአብሔርም መንፈስ ነውና በዚሁ ኤሎሂም በሚለው ስያሜ ውስጥ ተካትቶ ይገኛል። ይህንኑም በተለያየ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ውስጥ ስለ እግዚአብሔር ብቻ በሚናገር በርካታ ክፍል ውስጥ አብሮ ተጠቅሶ የሚታይ ነው። ታዲያ በዚሁ የመዝሙረ ዳዊት ምዕራፍ 82 ክፍል ላይ እንደተጠቀሰው እነዚህ ሁሉ በመንፈሳዊው አለም ውስጥ የሚገኙ "ኤሎሂም" በሙሉ እንደ እግዚአብሔር መናፍስት ይሁኑ ብሎም አማልክት ይባሉ እንጂ አንዳቸውም ግን እንደ እግዚአብሔር (ያህዌ) አይደሉም። ለዚህም ነው በዚሁ የመዝሙረ ዳዊት ምዕራፍ 82 ክፍል የመጀመሪያው ቁጥር ላይ እንደተገለፀው እግዚአብሔር በእነዚህ የአማልክት ጉባኤ ተሰይሞ ነገር ግን በእነርሱ በሁላቸው ላይ የሚፈርድ ከእነርሱ ሁሉ ፍጹም የተለየና ከፍ ያለ እንደሆነ የሚናገረው።

ዶ/ር ሚካኤል ሄይዘር የሚባል የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪ እንደሚናገረው እግዚአብሔር ከሌሎች ሁሉም የመንፈሳዊው አለም አካላት ጋር አብሮ መንፈስ የሆነ (ኤሎሂም) ይሁን እንጂ እርሱ ብቻውን ተለይቶ ከእነዚሁ በርካታ አማልክት የተባሉ (ኤሎሂም) መካከል ከፍ ያለ በሁሉ ላይ ደግሞ የሚፈርድ ቅዱስ የሆነ ልዩ ኤሎሂም (ያህዌ) ነው። (Heiser, 2015)

ዳዊት ይህንኑ ቅድስናውን እና ከፍጥረት ሁሉ መካከል ልዩ የሆነ ማንነቱን የተረዳ በሚመስል ሁኔታ በመዝሙረ ዳዊት ምዕራፍ 99 ላይ ይህ እግዚአብሔር በኪሩቤል ላይ በዙፋን የተቀመጠና የነገሰ፣ ከህዝቦች ሁሉ በላይ ከፍ ያለ፣ ታላቅና አስፈሪ የሆነ፣ ሊወደስ የተገባው ስም ያለው፣ ፍትህን የሚወድድ፣ ትክክለኛነትን የመሰረተ፣ ፍትህንና ቅንነትን ለህዝቡ ያደረገ፣ ኃያል የሆነ ንጉስና ከሌላው ሁሉ ፈጽሞ የተለየ ቅዱስ አምላክ እንደሆነ ይናገራል። ለዚህም ቅድስናው ህዝቦች ሁሉ በፊቱ እንዲንቀጠቀጡ፣ ምድርም እንድትናወጥ፣ አህዛብም ሁሉ ቅዱስ በሆነ ተራራው ይህንኑ ቅዱስ አምላክ ከፍ ከፍ እንዲያደርጉት ይናገራል።

የእግዚአብሔርን ክብር ለማየት እድል ካገኙ ሰዎች መካከል የሆነው ጳውሎስ ወደ ሶስተኛው ሰማይ ይኸውም ወደ ገነት ተነጥቆ ስላየው በሰው ቃላት ሊገለጥ የማይችል ክብር በ2ኛ ቆሮንቶስ 12 ላይ ከተረከልን በኋላ ያንኑ ከባቢ የሚገልጽ በሚመስል መልኩ በ1ኛ ጢሞቴዎስ 6፡16 ላይ የነገስታት ንጉስ የጌቶችም ደግሞ ጌታ፣ ብፁዕና ብቻውን የሆነ፣ የሚገዛ ገዥ በራሱ ጊዜ ሊገለጥ እንዳለ ነግሮን ይህም የሚገለጠው ጌታ እርሱ ብቻ የማይሞት እንደሆነና ማንም ሊቀርበው በማይችል ብርሃን የሚኖር እንደሆነ እስከ ዛሬም ድረስ ከዚህ የብቻው የሆነ ታላቅ ክብሩ የተነሳ አንድ ሰው እንኳ እንዳላየውም ደግሞም ሊያየው እንደማይችል ይነግረናል።

ይህንን ገለፃ የበለጠ ለመረዳት ኢሳይያስና ዮሐንስ እድል አግኝተው በእግዚአብሔር ዙፋን ዙሪያ ስላለው ክብር የተረኩልንን ትረካ ማየት በጣም ጠቃሚ ነው። እነዚሁ በኢሳይያስ ምዕራፍ 6 እና በዮሐንስ ራዕይ ምዕራፍ 4 ላይ የተገለጹ ተመሳሳይ ገጽታዎች እግዚአብሔርን በረጅምና ከፍ ባለ ዙፋኑ ላይ ተቀምጦ የልብሱም ዘርፍ መቅደሱን ሞልቶት በዙሪያውም በዚያ ቦታ እንዲገኙ እግዚአብሔር የፈቀደላቸው

መላዕክትና በዙፋን ላይ የተቀመጡ ሽማግሌዎችን ያሳዩናል። በዚህም የእግዚአብሔር ዙፋን ዙርያ የሚገኙ መላዕክትና ሽማግሌዎች ቀንና ሌሊት ሳያርፉ ባልተቋረጠ ሁኔታ በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው ከዘላለም እስከ ዘላለም በህይወት ለሚኖረው /ጳውሎስ እንዳለ ለማይሞተው/ ለእርሱ ክብርና ውዳሴ ምስጋናም እየሰጡ ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ እያሉ ቅድስናውን ሳያቋርጡ ያውጃሉ።

> “እግዚአብሔር ለብቻው ከፍ ያለ፣ የሚመስለው አንዳችስ እንኳን የሌለ፣ በምንም ነገር ደግሞ የማይመሰል፣ ልዩ የሆነ ቅዱስ አምላክ በመሆኑ ፈጽሞ ሀጢአትን አድርገው የማያውቁት በእርሱ መገኘት ዙሪያ በቅርበት የሚኖሩ ፍጥረታቱ እንኳን ቀና ብለው ሊያዩት እንደማይችሉ እናያለን።”

በዚሁ ስፍራ የሚገኙት በህዝቅኤል ምዕራፍ ፤ ላይ የተጠቀሱት የእግዚአብሔርን ዙፋን “የሚሸከሙ” ኪሩቤሎችም ከተሰጣቸው ሁለት ክንፍ በአንደኛው ገላቸውን እንደሚሸፍኑ ይታያል። በዚህና ሌሎችም ተመሳሳይ ምስሎች ውስጥ እንደምናየው እግዚአብሔር ለብቻው ከፍ ያለ፣ የሚመስለው አንዳችስ እንኳን የሌለ፣ በምንም ነገር ደግሞ የማይመሰል፣ ልዩ የሆነ ቅዱስ አምላክ በመሆኑ ፈጽሞ ሀጢአትን አድርገው የማያውቁት በእርሱ መገኘት ዙሪያ በቅርበት የሚኖሩ ፍጥረታቱ እንኳን ቀና ብለው ሊያዩት እንደማይችሉ እናያለን።

መላዕክቱ ምንም እንኳን ሀጢአትን ፈጽመው ባያውቁም እግዚአብሔርን ቀና ብለው እንዳያዩት ስንፍና የሚከስሳቸው እንደሆኑ በዚህም ምክንያት በክንፎቻቸው ገላቸውን እንደሚሸፍኑ ቴማናዊው ኤልፋዝ በኢዮብ መጽሐፍ ምዕራፍ 4፡18 ላይ ይነግረናል። ይህም ፍጹም ልዩ የሆነ የእግዚአብሔር ማንነት ይኸውም ቅድስናው ፍጥረት ብቻ በሆኑ በፊቱ በሚመላለሱ ቅዱሳንና ባሪያዎቹ በአንዳቸውም እንዳይታመን ያደረገው እንደሆነ፣ ሰማያትም እንኳን በፊቱ ንጹሃን እንዳይደሉ የገለጠ አስደናቂ ቅድስና ነው።

እንደዚህ ባለ አስደናቂ ንጽህና እና ቅድስና ሊታይ በማይችል ብርሃን ውስጥ በሚኖረው በታላቁ እግዚአብሔር ፊት ሀጢአትን እንደ ውሃ የሚጠጣ ሰው ምንኛ ያንስ

እና ይቆሽሽ? ንጹህ ይሆን ዘንድ ሰው ምንድን ነው? ፃድቅስ ይሆን ዘንድ ከሴት የተወለደ ምንድን ነው? እግዚአብሔር ሆይ፣ ይህን ያህል በልብህ ስፍራ ትሰጠው ዘንድ ሰው ምንድን ነው? ታስበው፣ ታስታውሰውና ታስብለትስ ዘንድ የሰው ልጅ ምንድን ነው? ከፍ ከፍ ታደርገው ዘንድ፣ ልብህንም ትጥልበት ዘንድ በእርግጥ ሰው ምንድን ነው?

ከላይ በተገለፀው አግባብ መሰረት ፈጽሞ ሀጢአት የማያውቃቸው በፊቱ የተገኙ ፍጥረቱ እንኳን ቀና ብለው ፊቱን ያዩ ዘንድ የሚያስችል ንጽህና የሌላቸው ብሎም ስንፍና የሚከሳቸው የሆኑ እንጂ አንዳቸውም እርሱ እንደሆነው ያልሆኑ ፍጡራን እንደሆኑ ይታያል። በዚህም መሰረት የእግዚአብሔር ቅድስና ይታይ ዘንድ እግዚአብሔር ክብሩን በሚገልጥበት ስፍራ ሁሉ ፍጹም የሆነ ቅድስና በዚያ ደግሞ ይኖር ዘንድ አስፈላጊ እንደሆነ እናያለን።

መጽሐፍ ቅዱስ በዕብራዊያን መጽሐፍ ላይ ምዕራፍ 12 ቁጥር 14 ላይ *“ለመቀደስም ፈልጉ ያለ ቅድስና ማንም ጌታን ማየት አይችልም”* ብሎ ይነግረናል። ይህም እውነት እግዚአብሔር በተለየ መገኘት በተገኘባቸውና ክብሩን በገለጠባቸው ጊዜያት ሁሉ ያየነው ነው። ሙሴ በኮሬብ ተራራ በቁጥቋጦው፣ ኢያሱ የእግዚአብሔር ሰራዊት አለቃን በተገናኘ ወቅት፣ የእግዚአብሔር በሲና ተራራ ላይ በእሳት መውረድ፣ እስራኤላዊያን ዮርዳኖስን በተሻገሩበት ወቅት ወዘተ የእግዚአብሔር ክብር በተገለጠበት ስፍራ ሁሉ ቅድስና አማራጭ የሌለው ቅድመ ሁኔታ ነበር።

እግዚአብሔር ለሙሴ በሰጠው ትዕዛዝ ውስጥ የሊቀ ካህኑን የአሮንን ልብስ በተመለከተ በተናገረው ንግግር ውስጥ በኤፉዱ ቀሚስ የታችኛው ዘርፍ ዙሪያ የወርቅ ሻኩራዎችን እንዲያደርግና ከጥሩ ወርቅም ቅጠል የሚመስል ምልክትን እንዲሰራ በእርሱም ላይ እንደ ማህተም ቅርጽ እንዲያደርግ በዚያም ላይ *“ቅድስና ለእግዚአብሔር”* የሚል ቃልን እንዲቀርጽበት ይነግረዋል። ይህንንም የሰራውን ቅርጽ በሰማያዊ ፈትል በመጠምጠሚያው ፊት ላይ እንዲያንጠለጥለውና በአሮን ግምባር ላይ እንዲሆን ያስጠነቅቀዋል። ይህም ሁሉ በአገልግሎት ጊዜ በአሮን ላይ የሚሆን ሲሆን እርሱም እንዳይሞት ወደ መቅደሱ በቅዱሱ በእግዚአብሔር ፊት ሲገባና ሲወጣ ድምፁ እንዲሰማና

የእስራኤልን ልጆች ሀጢአት ተሸከሞ ወደ እግዚአብሔር ፊት ሲመጣ በፊቱ ሞገስ ያገኝ ዘንድ የሚያደርገው ነበር።

> “አንድ ነጭ ልብስ ከእርሱ ይልቅ በነጻ ሌላ ነጭ ነገር አቅራቢያ በተገኘ ጊዜ እድፉ እንደሚገለጥ እንደዛው በእግዚአብሔር ቅድስና ፊት አንዳች ንጹህ የሆነና በፊቱ ያለ እግዚአብሔር ምህረት መቆም የሚችል ማንም ወይም ምንም የለም።”

አንድ ነጭ ልብስ ከእርሱ ይልቅ በነጻ ሌላ ነጭ ነገር አቅራቢያ በተገኘ ጊዜ እድፉ እንደሚገለጥ እንደዛው በእግዚአብሔር ቅድስና ፊት አንዳች ንጹህ የሆነና በፊቱ ያለ እግዚአብሔር ምህረት መቆም የሚችል ማንም ወይም ምንም የለም።

ከምዕራፍ ስድስት በፊት እስራኤላዊያንን እየተቆጣና እየወቀሰ በርካታ የፍርድ ቃላትን የተናገረው ኢሳይያስ በእግዚአብሔር ፊት በተገኘ ጊዜ እርሱም ደግሞ እንደ ሌላው ቀሪ የአገሩ ህዝብ ከንፈሩ የረከሰ ሰው እንደሆነ አወቀ። ሁሉም ሀጢአትን ሰርተዋል የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሏቸዋል ተብሎ እንደተጻፈ በእግዚአብሔር ፊት ንጹህ የሆነ በቅድስናው ፊት ያለ ፍርሃት ሊቆም የሚችል አንዳች ሰው የለም። በዙሪያው ካሉ ሌሎች ሰዎች የተለየ ጽድቅና ቅድስና እንዳለው የሚቆጥር እንኳን ቢኖር የእርሱ ንጽህና እንደ መርገም ጨርቅ የቆሸሸና የእግዚአብሔር ምህረት የሚያስፈልገው “ጎዶሎ ቅድስና” ነው።

የእግዚአብሔር ቅድስና እግዚአብሔር በተገለጠ ሁኔታ ማንነቱን ሊገልጥ ወድዶ ክብሩን በሚያሳይባቸው ስፍራዎች ሁሉ የሚጋባና ዙሪያውን የሚቀድስ ነው። አንድ ታላቅ ብርሃን በጨለማ ዙሪያ በተገኘና ብርሃኑን በለቀቀ ጊዜ ስፍራ ይዞ የነበረው ጨለማ ድራሹ እንደሚጠፋ ጨለማውም ብርሃኑን ያሸንፈው ዘንድ ፈጽሞ እንደማይችል እንዲሁ እግዚአብሔር ቅድስናውን ሊያሳይ ወድዶ ክብሩን በሚገልጥባቸው በተለየ መገኘቱ በሚመላለስባቸው ስፍራዎች መገኘቱ ታላቅ ዋጋን የሚያስከፍል እጅግም አስፈሪ ሁኔታን የሚፈጥር ነው።

ምንም እንኳን በፊቱ ሊያቆም የሚያስችል ንጽህና ያለው ማንም ባይኖርም ከፊቱ ሁልጊዜ እውነትና ምህረቱ ይሄዳሉና በፍጹም እውነተኛ የተገለጠ ማንነት ምህረቱን

በመፈለግ ራስን አራቁቶ በፊቱ መገኘት ከጥፋት የሚያድን ብቸኛ መንገድ ነው። እግዚአብሔር በልዩ ሁኔታ በተገለጠ ክብር በማደርያ ድንኳኑ በተገኘ ወቅት ያልተገባ ልዩ እሳትን በጥናዎቻቸው ላይ አድርገው በእግዚአብሔር ፊት የቀረቡት የአሮን ልጆች ናታን እና አብዮድ እንዲሁም በሐዋርያቱ መካከል መንፈስ ቅዱስ በሙላት እየሰራ ባለበት በዚያን ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ሊያታልሉ የሞከሩት ባልና ሚስቱ ሃናንያ እና ሰጲራ ለዚህ አይነተኛ ማሳያዎች ናቸው። በዚሁ ስፍራ ሙሴ ለወንድሙ ለአሮን የልጆቹን ሞት ተከትሎ የነገረው የእግዚአብሔር ንግግር ለዚህ ማሰሪያ ነጥብ ነው። *"ወደ እኔ በሚቀርቡት መካከል ቅድስናዬን እገልጣለሁ በህዝቡም ሁሉ ፊት እከበራለሁ ብሎ የተናገረው ይህንን ነው።"*

በዚሁ መሰረት በእግዚአብሔር ፊት ሊገኝ እና የእርሱን ክብር ለማሳየት በአገልግሎት መልክ የሚሳተፍ ሰውም ይሁን እቃ አስቀድሞ በቅድስናው ፊት መቆም የሚያስችል ብቃት ያስፈልገዋል። ይህም ብቃት ሰው በራሱ ሊያመጣው የማይችል እግዚአብሔር ራሱ በወደደው መንገድ ያንን ዕቃ ወይም ፍጡር በፊቱ መቆም ይችል እና ያገለግል ዘንድ የሚቀደስበት የራሱ ልዩ ቅድስና ነው።

እግዚአብሔር በራሱ ትዕዛዝ ሰጭነትና በሙሴ ራዕይ ተቀባይነት ጥበብን በሰጣቸው እስራኤላዊያን ሰሪነት በመካከላቸው ያድር ዘንድ ባሰራው ማደሪያ ድንኳን ውስጥ በሚገኙ መገልገያ እቃዎች እና በዚያው ስፍራ በፊቱ ያጥኑና ያገለግሉ ዘንድ በተመረጡ ህዝቦች ላይ የተረጨው በእግዚአብሔር በራሱ ቅመማ የተዘጋጀው ቅዱስ ቅባት ለዚህ ማሳያ ነው። ከዚህም በተጨማሪ እኛ ሁላችን እግዚአብሔር ባለበት በዚያ እኛ ደግሞ እንሆን ዘንድ የእግዚአብሔር ጽድቅ ሊያደርገን ወድዶ ሀጢአት ያላወቀውን ልጁን ሀጢአት ያደረገበትና ለመስቀል ሞት አሳልፎ የሰጠበት የመስቀሉ ስራ ደግሞ ፍጹም የሆነው የእግዚአብሔር ምህረት ማሳያ እና መልክ ነው።

ይህ ከላይ ያየነው ቅድስና እግዚአብሔር ራሱ ወድዶ እና ፈቅዶ በፊቱ መቆም ይቻለን ዘንድ የሰጠን ሞገስ ሲሆን ይህንንም ለማግኘት ሰው ብቁ ይሆን ዘንድ ያሚላው ቅድመ ሁኔታ የለውም። እስራኤላዊያን በእግዚአብሔር መልካም ፈቃድ ብቻ በአለም ላይ ካለው ህዝብ ተለይተው የክብሩ ማሳያ ይሆኑ ዘንድ የተመረጡና የእግዚአብሔር ርስትና ህዝብ የተባሉ ይሁኑ እንጂ በተባሉት ልክ ሆነው ለመገኘት ደግሞ በዚሁ ቅድስና

በዙሪያው ካሉ ህዝቦች በተለየ የኑሮ ዘይቤና ምልልስ ሊመላለሱ እና ቅድስናውን በህይወት ሊገልጡ ደግሞ ያስፈልጋቸው ነበር። ቅዱስ የተባለው ይህ ህዝብ ከዚህ እግዚአብሔር ለሰው ከሰጠው መመላለሻ መስመር በወጣና ከእግዚአብሔር ቅድስና ርቆ አህዛብን መስሎ በርኩሰት ውስጥ በተገኘበት ጊዜ ሁሉ ለቁጣ የዘገየው አምላኩ ሊምረው ወድዶ ይመለስ እና ራሱን ይቀድስ ዘንድ ደጋግሞ ከጥፋቱ እንዲመለስ ነግሮት ሳይመለስ ቀርቶ ለጠላቶቹ ተላልፎ እየተሰጠ በርካታ ጥፋትን ሲያስተናግድ ኖሯል።

በብሉይና በአዲስ ኪዳን አጽንኦት ሰጥቶ እርሱ ቅዱስ እንደሆነ ህዝቡ ደግሞ ቅዱስ እንዲሆን ግልጽ ትዕዛዝን የሰጠው እግዚአብሔር ህዝቡ በተገለጠው ፀጋ ብርታት ራሱን ከአለም ርኩሰት እየለየ አምላኩን እየመሰለ ይኖር ዘንድ አለማዊነትንና ሀጢአተኝነትን በመካድ በቅድስና መመላለስ ያስፈልገዋል። ቀድሞ ለእስራኤላዊያን በዙሪያችሁ ያሉ አህዛብን አትምሰሏቸው ተብሎ እንደተነገረ ዛሬም እርሱን ለመምሰልና የልጁን መልክ በእኛ ሁኔታ ለማሳየት ብሎም የእርሱን በጎነት በህይወታችን ለመናገር ከጨለማ ወደ ብርሃኑ መጥተናልና፤ በዚህም ባመነው እምነት ብቻ ቅዱስ ህዝብ ተብለን ተጠርተናልና፣ በዚሁ በተጠራንበት ስማችን እንደዛው ሆነን ለመገኘት ባልተቋረጠ ሁኔታ ይህንን አለም ላለመምሰል፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅና ለማድረግ ባልተቋረጠ መልኩ በአእምሮ መታደስ መለወጥ ያስፈልገናል።

በዚህም የዕለት ከዕለት የመታደስ ሂደት በመጋረጃ በማይከደን ፊት የጌታን ክብር እንደ መስተዋት እያብለጨለጭን ያን መልክ እንመስል ዘንድ ሳናቋርጥ ከክብር ወደ ክብር ልንለወጥ ያስፈልገናል። በሙላት የእርሱን መልክ ለመምሰልና ኑሮውን ለመኖር የለበስነው ደካማ ስጋ በእጅጉ የሚገዳደረን ቢሆንም የተገለጠው ፀጋና አብሮን ያለው መንፈሱ ይህንን ቀድሞ የነበረ የእግዚአብሔር ሃሳብ በእኛ ለመፈፀም የሚያስችሉ ከስጋችን፣ ከአለምና ከሰይጣን በላይ የሆኑ የእኛ መቻያ አቅሞች ናቸው። ያን ጊዜ ግን መድሃኒታችን እርሱም ክርስቶስ በተገለጠ ጊዜ እኛ ደግሞ ፈጽመን እርሱን እንድንመስል ድጋሚ ስጋችን፣ ሞት፣ ሰይጣን፣ አለም ወዘተ ላይሰለጥኑብን የትንሳኤውን አካል ለብሰን መዳናችን ፍጹም ይሆናል። የእግዚአብሔር ቅድስና ግን በዚያን ጊዜ እንኳን እርሱን በልጁ በኩል ብቻ እንድናየው የሚያደርግ ፈጽሞ ሊታይ የማይችል ታላቅ ቅድስና ነው። ቅድስና ከዕለት ዕለት ምልልስ የዘለለ በልብ ክርስቶስን በመቀደስ ጭምር ከክፉ ህሊና

ለመንጻት ልባችንን ተረጭተን ሰውነታችንንም በንጹህ ውሃ ታጥበን በእውነተኛ ልቦና በሙሉ እምነት ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ነው።

> “በብሉይና በአዲስ ኪዳን አጽንኦት ሰጥቶ እርሱ ቅዱስ እንደሆነ ህዝቡ ደግሞ ቅዱስ እንዲሆን ግልጽ ትዕዛዝን የሰጠው እግዚአብሔር ህዝቡ በተገለጠው ፀጋ ብርታት ራሱን ከአለም ርኩሰት እየለየ አምላኩን እየመሰለ ይኖር ዘንድ አለማዊነትንና ሀጢአተኝነትን በመካድ በቅድስና መመላለስ ያስፈልገዋል።”

- የማስተንተኛ ጥያቄዎች

1. የእግዚአብሔር ቅድስና ስለ ማንነቱ ባለህ መረዳት ላይ ምን ጨመረልህ?
2. የእግዚአብሔር ቅድስና በፊቱ የምትቀርብበትን መንገድ እንዴት ሊቀርጸው ይገባል?
3. ዛሬ እግዚአብሔር በየትኞቹ የሕይወትህ ክፍሎች ቅድስናን እንድትከተል አሳሰበህ?

- አሰላስል

እግዚአብሔር ቅዱስ ነው። በፍጥረት ሁሉ ላይ ከፍ ያለ፣ ከማንምና ከምንም ጋር የማይመሳሰል ነው። ቅድስናው ፍጹም ንጽሕናውን፣ ጽድቁንና ከኃጢአት ፈጽሞ የተለየ መሆኑን ያሳያል። ስለዚህ በፊቱ በአክብሮት፣ በትሕትናና በፍርሃት ልንቀርብ ይገባናል። ከዚህም በላይ በጸጋው በክርስቶስ ውስጥ ቅዱሳን አድርጎናል፤ በመንፈስ ቅዱስም ሥራ የባሕርዩን ቅድስና በሕይወታችን እንድናንጸባርቅ ጠርቶናል። ስለዚህ ቅዱሱን አምላክ በቅድስና ልናመልክና በዕለት ተዕለት ኑሮአችን ቅድስናን ልንከተል እንደሚገባ ሁልጊዜ እንድናስታውስ ያስፈልገናል።

- ጸሎት

በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፣ ቅድስናህን ስለገለጥህልን እናመሰግንሃለን። ቅዱስ ነህና በአክብሮትና በትሕትና እንዳመልክህ እርዳኝ። ልቤን ከኃጢአት አንጻ፣ በክርስቶስ የሰጠኸኝን ቅድስና በየቀኑ በሕይወቴ እንዳሳይ በመንፈስህ ምራኝ። ባሕርይህን በሐሳቤ፣ በቃሌና በሥራዬ እንዳንጸባርቅ ጸጋህን አብዛልኝ።

በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አሜን።

- የአርምሞ ጥቅስ

*"አቤቱ፥ በአማልክት መካከል እንደ አንተ ያለ ማን ነው? በምስጋና የተፈራህ፥ ድንቅንም የምታደርግ፥ በቅድስና የከበረ እንዳንተ ያለ ማን ነው?"*

*– ኦሪት ዘጸአት 15፥11 –*

## 2.11. እግዚአብሔር ጻድቅ ነው!

ፃድቅ የሚለው ቃል በእንግሊዘኛው "Righteous" ከሚል ቃል ጋር አቻ ሲሆን ይሄው የአማርኛ ቃል ታዲያ ከዕብራይስጥ አቻ ትርጓሜው /Tzadik (צַדִּיק)/ ጋር ተመሳሳይ ቃላት እና አጠራር ያለው ቃል ነው። (Brown, Driver, & Briggs, 1996) ለዚሁ ፃድቅ ለሚለው ቃል የተለያዩ ትርጓሜዎች የሚሰጡት ፍች አንዳች እንከን የለሽ የሆነን፣ ከወቀሳ ነጻ የሆነ፣ በየትኛውም መመዘኛ ሲፈተሽ ዝንፍ የማይል፣ ፅኑ የሆነ፣ የማይለዋወጥ፣ አንድ አይነት ማንነት ያለው፣ ሁልጊዜ ትክክል የሆነን ነገር ብቻ የሚያደርግ አካልን ለመግለጽ ያገለግላል ይላሉ። (ግዛው, 1994) (Merriam-Webster, n.d.)

ይህም በማህበረሰብ ዘንድ ተቀባይነት ባላቸው የትክክለኛነት መመዘኛዎች ተፈትኖ የሚያልፍ አንዳች ጉድፍ የማይገኝበት ህሊናው ሀሳቡና ንግግሩ እንዲሁም የህይወት ምልልስ እርምጃው ተመሳሳይ እና ትክክል የሆነ አካልን ለመግለጽ ይጠቀሙበታል። ይህም ተቀባይነት ሞራላዊ ትክክለኛነትን፣ ከወቀሳ ነጻ የሆነ ህሊናን፣ ወጥ የሆነ መልካም ስነምግባርን እንዲሁም ያልተደበቀ ግልጽ የሆነ ፍጹም ፍትሃዊና ሚዛናዊ ማንነትና አቋምን ይገልፃል። (ግዛው, 1994) (Merriam-Webster, n.d.)

ምንም እንኳን የቃሉ ትርጓሜና አቻ ፍች ከላይ በተዘረዘሩትና ሌሎች ተመሳሳይ ይዘት ያላቸው ቃላት የሚመነዘር ይሁን እንጂ በዚህ አይነት እጅግ ከፍ ያለ ሊደረስበት የማይችል አይነት ፍጹም የሆነ ትክክለኛ ስፍራ ላይ የሚገኝ በሁለንተናው ንፁህ የሆነ ተፈትኖም የሚያልፍ እንከን የለሽ አንዳች አካልን በፍጥረታት መካከል ማግኘት ፈጽሞ የማይቻል ነው። ይህንኑ ቃል ለመመዘን የምንጠቀምባቸው ሰዋዊ መመዘኛዎችና ማህበረሰባዊ የትክክለኛነት ቱምቢዎች በሰው ሚዛን የሚመዘኑ ከሆነ ከስፍራ ስፍራ፣ ከህዝብ ህዝብ፣ ከባህል ባህል ወዘተ ፈጽመው የሚለያዩና አንዳች የሚያስማማ የጋራ ተቀባይነት ያለውን ፍትሃዊ እውነተኛ የጽድቅ ሚዛን ለማግኘት የማይቻል ይሆናል። ለዚህም ይመስላል የእግዚአብሔር ቃል የሰው ልብ ገና ከታናሽነቱ ጀምሮ ክፉና ተንኮለኛ የሆነ ማንም ሊያውቀው የማይችል ሆኖ ርቆ የተደበቀ እንደሆነ በዚህም ምክንያት አንዳች ጻድቅ በሰው ዘር ሁሉ መካከል እንደሌለ ሁሉ ሀጢአትን እንደሰሩ ከላይ በተገለጸው አይነት

መመዘኛ ተፈትሾ በሁለንተናው ትክክል የሆነን ሰው ከየትኛውም ትውልድ፣ ዘር፣ ሐይማኖትና ባህል ወዘተ ልናገኝ እንደማንችል በግልጽ የሚናገረው።

መጽሐፍ ቅዱስ ይህንኑ ጽድቅ በበርካታ ስፍራ ላይ የሚጠቅሰው ሲሆን የዚህም ቃል ትክክለኛ ትርጓሜ በእግዚአብሔር ፊት ያለ እንከን፣ ያለ ነቀፋ ወዘተ ሆኖ ፍጹም በሆነ ትክክለኛና እውነተኛ ማንነት በሁለንተና መገኘት የሚችል ሰውን ለመግለጽ ያገለግላል። ይህም ጽድቅ መመዘኛው የራሱ የእግዚአብሔር ትክክለኛነት እና እውነተኛነት ሲሆን ይህም ማንነቱና መመዘኛው የሰውን ልጅ ከፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ በእርሱ ፊት ተገቢ የሆነን ትክክለኛና እውነተኛ ምልልስ ይመላለስ ዘንድ በተለያየ መልኩ ሲገልጠው የኖረው የራሱ ጽድቅ ነው።

እግዚአብሔርን እንዲመስል ታስቦ በእግዚአብሔር መልክ የተሰራው የሰው ልጅ ፈጣሪውን እየመሰለ በፊቱ ይኖር ዘንድ እግዚአብሔር በየዘመኑ ይህንኑ ጽድቁን በልዩ ልዩ ጎዳና ለሰው ልጆች ገልጧል። የመጀመሪያውን ሰው አዳምን በዚሁ ይኖረው ዘንድ ታስቦ በተፈጠረበት ከፍታ ይኖርና በጽድቅ በእግዚአብሔር ፊት እንዲመላለስ ከህይወት ዛፍ ብቻ እንዲበላ ተነገሮት ነበር። ይህንን ቢያደርግ በተፈጠረበት ጽድቅ በፈጠረው ፈጣሪው ፊት ለዘላለም እንደሚኖር ከተናገረበት ጊዜ ጀምሮ እንደታዘዘው ባለማድረጉ ምክንያት ከጽድቅ የጎደለው የሰው ዘር በየዘመኑ በዚሁ ፈጣሪው ፊት የተገባ ትክክለኛና እውነተኛ የሆነ በእግዚአብሔር መመዘኛ ተመዝኖ የሚያልፍ መልክን እንዲይዝ ደጋግሞ ይህንኑ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ የጽድቅ ህይወት ምልልስን ፈጣሪው ሲገልጥለት ኖሯል። እንዲህ እንዲህ እያለ ለራሱ ይሆን ዘንድ የተለየ በራሱ ጽድቅ የሚኖር ህዝብን ከአለም ህዝብ መካከል ያወጣው እግዚአብሔር የጽድቁ ማሳያዎች እንዲሆኑ ዘርዘር ያለ እርሱን ደስ የሚያሰኘውን በእርሱም ፊት ተመዝኖ ትክክለኛና እውነተኛ የሆነ ህይወትን ህዝቡ ይኖር ዘንድ ህጉን ሰጠ።

ሙሴ በዘዳግም 4፡8 ላይ *"ዛሬ እኔ በፊታችሁ እንዳስቀመጥሁት ህግ ያለ ጽድቅ የሆነ ስርዓትና ህግ ያሉት ሌላ ታላቅ ህዝብ ማን ነው?"* ብሎ ከአምላካቸው የተሰጣቸው ህግ በእርሱ ፊት ተቀባይነትን የሚያስገኝላቸው ጽድቅ እንደሆነ ያሳስባቸዋል። በተመሳሳይ መልኩ በዚሁ የዘዳግም መጽሐፍ ምዕራፍ 6፡25 ላይ *"እንግዲህ ይህን ሁሉ ህግ እርሱ*

*ባዘዘን መሰረት፣ በአምላካችን በእግዚአብሔር (ኤሎሂም ያህዌ) ፊት ተጠንቅቀን ከጠበቅን፣ ያ ለእኛ ጽድቃችን ይሆናል"* ብሎ ይህ የተሰጣቸው የአምላካቸው ህግ ፈጽመው ቢጠብቁት በእርሱ ፊት ጻድቅ የሚያደርጋቸው እንደሆነ ይነግራቸዋል።

ጽድቅ የፍጥረቱ ፈጣሪ እግዚአብሔር ከፍጥረቱ ጋር ኅብረት የሚያደርግበት የእርሱ የራሱ ባህሪ እና የትክክለኛነት መመዘኛ የሆነ ማንነት ነው። እግዚአብሔርን እንዲመስል ታስቦ የተሰራው የሰው ልጅ ደግሞ ከሌላው ፍጥረት ሁሉ ይልቅ ከፈጣሪው ጋር በቅርበትና ጥልቅ በሆነ ግንኙነት ይኖር ዘንድ ታስቦ በመልኩ ተፈጥሯልና ፈጣሪው ራሱ ያለውን ማንነት ይኸውም የእግዚአብሔርን ጽድቅ ማወቅና በዚያው ባወቀው የጽድቅ ህይወት መመላለስ ብቸኛው ወደ ፈጣሪው ሊቀርብ የሚችልበት መንገዱ ነው።

የእግዚአብሔር ጽድቅ እግዚአብሔር ከፍጥረቱ ጋር ባለው ግንኙነት ተገቢ የሆነን እውነተኛ የሆነ ፍትሃዊ ምላሽን ለፍጥረቱ ለመመለስና ሌሎቹን በዚህ መጽሐፍ እንዲሁም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተዘረዘሩትን በርካታ የግሉ የሆኑ ማንነቶቹን በፍጥረቱ መካከል ለመግለጥ መነሻና መካከለኛ የሆነ የተገለጠ ድርጊቱ ምክንያት ነው። ይህም ቀና ብቻ የሆነ የእግዚአብሔር የጽድቅ መንገድ በሰዎች እይታና መመዘኛ ልክ የማይመስል ብሎም እስራኤላዊያን በህዝቅኤል 18 እና 34 ላይ እንዳሉት ሰዎች የእግዚአብሔርን መንገድ ቅን አይደለችም ብለው ጻድቅነቱን የሚጠራጠሩበት ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ሁሉን አዋቂና መልካም የሆነው እግዚአብሔር በብዙ ትዕግስትና በዘገየ ቁጣ ለራሱ በታመነ ማንነት ለሰዎች አዕምሮ በሚመችና በማይመች መንገድ በሉአላዊ ስልጣኑ በየጊዜው ጽድቁን በሰው ልጆች መካከል ይገልጣል።

ከላይ በዝርዝር ለመግለጽ እንደተሞከረው ፍጹም እውነተኛና ትክክለኛ የሆነ በየትኛውም ወቅት የማይለወጥ አንድ አይነት የሆነ ሁለንተናዊ ታማኝነት ያለው ከራሱ ከእግዚአብሔር በስተቀር ሌላ አንዳች ፍጡር

> "ፍጹም እውነተኛና ትክክለኛ የሆነ በየትኛውም ወቅት የማይለወጥ አንድ አይነት የሆነ ሁለንተናዊ ታማኝነት ያለው ከራሱ ከእግዚአብሔር በስተቀር ሌላ አንዳች ፍጡር የለም።"

የለም። እግዚአብሔር ግን ዓላማው ፍቅር የሆነ ዙፋኑን በጽድቅና በፍርድ ላይ የመሰረተ እውነትና ምህረትን ደግሞ ለፍጥረቱ ሁሉ ጥቅም ከፊቱ የሚያስኬድ ብቸኛ ፍጹም ጻድቅ አምላክ ነው። እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ አምላክ ሲሆን ይህንኑ ጽድቁን ሊያጠፉ የሚችሉ ራሱን ይክድ ዘንድ እንዳይችል ፈጽሞ የማያደርጋቸው ነገሮች አሉት። ከእነዚህም መካከል መዋሸትን፣ አለመታመንን፣ ለኪዳን ታማኝ ሆኖ አለመገኘትን ወዘተ የመሳሰሉ ነገሮችን ማድረግ አይችልም። ይህም መጽሐፍ ቅዱስ በ2ኛ ጢሞቴዎስ 2፡13 ላይ *"ባናምነው እርሱ የታመነ ሆኖ ይኖራል፣ ራሱን ሊክድ አይችልምና"* ተብሎ እንደተጻፈው ነው። ይህም የእግዚአብሔር ታማኝነትና ጽድቅ ፈጽሞ የማይለወጥ ምንም አይነት እንከን እና እድፍ የሌለበት ነው። ለወዳጁ ለአብርሃም በእውነት እንደሚባርከው ቃል ኪዳኑንና ተስፋውን በሰጠው በዚያን ጊዜ ሰዎች እንደሚያደርጉት ለማስረዳት የሚሆንን የሙግት ሁሉ ፍጻሜ የሆነ መሃላን ከእነርሱ በሚበልጥ አንዳች ነገር እንደሚምሉት እርሱ ደግሞ እንዲያደርግ ስለ ተስፋ ቃሉ ለዚህም ስላለው ታማኝነትና ስለ ፍጹም ፃድቅነቱ ከእርሱ በሚበልጥ በማንም ሊምል ስላልቻለ በራሱ ማለ።

ይህ የእግዚአብሔር ጽድቅ ፍጥረቱ ሁሉ በፊቱ ይመላለስ ዘንድ ሊጠብቀው የሚገባው የእግዚአብሔር መልክ ነው። ይህም በዝርዝር ለሙሴና ለእስራኤላዊያን በልባቸው ይጠብቁትና ይኖሩበት ዘንድ ከራሱ ከእግዚአብሔር የተሰጠ የህጉ መካከለኛ ይዘት ነው። ከዚህም የህጉ መገለጥና መሰጠት በኋላ ሰው እግዚአብሔር ጋር ለመድረስ በዚህ እግዚአብሔር ማንም ወደ እርሱ ሊቀርብ የሚወድ ያሚላው ዘንድ በሰጠው የራሱ ጽድቅ መመዘኛ ተመዝኖ ሊያልፍ የግዴታ ያስፈልገው ነበር። ጽድቅ የሰውና የእግዚአብሔር ኅብረትና ግንኙነት መነሻ ነጥብ ነው። ነገር ግን በአምላኩ ፊት ፍጹም ይሆንና ይጸድቅ ዘንድ ለህዝቡ የተሰጠው ይሄው ህግ ሰውና እግዚአብሔርን ከማቀራረብ ይልቅ የሰውን ሀጢአት የበለጠ ወደ ብርሃን አምጥቶ እስከ ዛሬ ከህግ መምጣት በፊት በልማድ ሲመላለስ የነበረባቸውን ጊዜያት ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ምን ያክል የተጠሉ እንደሆነ አሳይቶት ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ርቀት ይበልጥ አስፍቶ ዳግም ወደ እግዚአብሔር መገኘት ይህንኑ የጽድቅ መመዘኛ አሟልቶ መቼም ሊደርስ እንደማይችል አውቆ ተስፋ እንዲቆርጥ አደረገው።

በዚህ ተስፋ መቁረጥ ውስጥ ሆኖ ወደ እግዚአብሔር ደግሞ ሊቀርብ እንደማይችል አውቆ በሞት ጎዳና ሲራመድ ለኖረው ህዝብ መፍትሄውንና ችግሩን የሚፈታበትን መንገድ ራሱ ፈጣሪው እግዚአብሔር እንዲቀይስ ከመልካምነቱና ሰውን ከወደደበት ፍቅሩ እንዲያመነጭ አደረገው። ይህም መፍትሄ የእግዚአብሔርን ጽድቅ በሙላት በሰው ልጆች መካከል መግለጥ ነበር። ይህም የእርሱ ፍጹም ትክክለኛነት እና እውነተኛነት መገለጫ የሆነውን የገዛ ጽድቁን ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ስጋ አድርጎ ወደ ምድር ማምጣቱ ነበር።

*ኢየሱስ የእግዚአብሔር ጽድቅ ነው!*

ከላይ በስፋት በተገለጸው መሰረት ህጉ የእግዚአብሔር የጽድቅ መገለጫ ሲሆን ይሄው ስጋ ሆኖ የተገለጠው የእግዚአብሔር ቃል ይኸውም ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ደግሞ በህጉ ውስጥ ያለውን ከአድርግና አታድርግ የዘለለ የእግዚአብሔር የልብ ሀሳብ ሁሉ ፈጽሞ የገለጠ የህግ ሁሉ ፍፃሜ ነበር። ይህ የተገለጠ ስጋ እግዚአብሔር ቀድሞ በህጉ አታመንዝር ብሎ ሲል ገሃዳዊ ከሆነው ነገሩን ባለማድረግ ብቻ ለሰው ከሚሰማው ጽድቅን ያደረገ ስሜት እና ትክክለኛነት በላይ እግዚአብሔር ህጉን በሰጠበት ወቅት በልቡ ያለውን ፍጹም ሃሳብ ይኸውም ነገሩን ባለማድረግ ውስጥ እንኳን ያለን በማየትና በመመኘት ውስጥ የተፈጸመውን የህግ ግድፈትና ከጽድቅ መጉደል የገለጠ ነበር። ይህም ህጉ ሲሰጥ ከመጀመሪያው በተሰጠው ህግ ውስጥ ያለውን የእግዚአብሔርን የልብ ሃሳብ ፈጽሞ የገለጠና ለህጉ ፍፃሜን የሰጠ ነበር።

ከዚህም በተጨማሪ ይህ የእግዚአብሔር ጽደቅ የሆነ አንድ ልጁ ኢየሱስ ህጉን ከመግለጥና ለህጉ ፍፃሜን ከመስጠት በዘለለ በስጋ ወራቱ ተመላልሶ ሀጢአት የሌለበት ጻድቅ ሲሆን እኛ ሁላችን እርሱን አይተን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንሆን ዘንድ ሀጢአት ሆኖ የተቀጣ እንደ አንድ ሀጢአተኛም በምድር ላይ ጽድቅን ሁሉ እያደረገ ይመላለስ ዘንድ የተገባው ሰው ሆነ። ይህም የስጋ ወራት ምልልሱ እግዚአብሔር ገና ከመጀመሪያው ሰው ጀምሮ የሰው ልጅ በፊቱ ይመላለስበት ዘንድ ያሰበውን የልቡን ሃሳብ ፍንትው አድርጎ የገለጠ በህሊናው ሁሉ የፀደቀ ፈጽሞ ነቀፋና ጉድለት እንከንም የሌለበት ያለ ዕድፈት የተኖረ እውነተኛ የሆነ የእግዚአብሔር ጽድቅ ነው። ይህም በሰው ብቻ የተመሰከረ ሳይሆን

> “ኢየሱስ እግዚአብሔር ገና ከመጀመሪያው ሰው ጀምሮ የሰው ልጅ በፊቱ ይመላለስበት ዘንድ ያሰበውን የልቡን ሃሳብ ፍንትው አድርጎ የገለጠ በህሊናው ሁሉ የፀደቀ ፈጽሞ ነቀፋና ጉድለት እንከንም የሌለበት ያለ ዕድፈት የኖረ እውነተኛ የሆነ የእግዚአብሔር ጽድቅ ነው።”

ከሰማይ በመጣ ድምጽ እግዚአብሔር ራሱ *“በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ እርሱ ነው እርሱን ስሙት”* ብሎ ያፀናው ደግሞም ኮቴውን እንከተል ዘንድ የጽድቁን መንገድ ያሳየ እውነተኛ የእግዚአብሔር ጽድቅ ነው። ይህም የእግዚአብሔር መፍትሄ ኢሳይያስ በትንቢቱ ምዕራፍ 59፡16 እንደተናገረ ሰው እንደሌለ አይቶ የገዛ ክንዱ መድሃኒት እንዲያመጣለት አስቦ የገዛ ጽድቁ አግዞት ለሰው ሁሉ መካከለኛና ማላጅ ይኖር ዘንድ በራሱ መንገድ ያደረገው ታላቅ የማዳን ስራው ነው።

በዚህም መንገድ እኛ ሁላችን በእርሱ በማመን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንሆን ዘንድ ያደረገው የኮርማና የፍየል ደም በሰው ልጅ መካከል ያለውን ከእግዚአብሔር ጋር የተራራቀበትንና ከጽድቅ የጎደለበትን ምክንያት ይኸውም ሀጢአትን ፈጽሞ ማስወገድ ስላልቻለ በሙሉ በሚቃጠል መስዋዕትነት ለሀጢአት በሚሰዋ መስዋዕት ደስ ያልተሰኘውና ያልረካው እግዚአብሔር የፊተኛውን ሽሮ ሁለተኛውን ሊያቆም ፈቃዱን ያደርግ ዘንድ የገዛ ጽድቁን ይኸውም ቃሉ የሆነውን ብቸኛ ልጁን ስጋ አዘጋጅቶ በመካከላችን የገለጠበት ለሰው አዕምሮ ለመረዳት አዳጋች የሆነ የእግዚአብሔር ጥበብ ነው። በዚህም መሰረት ስጋ የሆነው ቃሉ እግዚአብሔር ሰው በምድር ላይ እንዲያደርግለት የሚፈልገውን የልቡን ሁሉ ሀሳብ አድርጎለት የሰው ልጆችን ሁሉ ከእግዚአብሔር ፊት ያራቀውን ሀጢአትን በመስቀል ላይ ቀጥቶ ስጋውንም አንድ ጊዜ ፈጽሞ በማቅረብ እኛን ሁላችንን በመቀደስ በልጁ የሚያምን ሁሉ ወደ እግዚአብሔር ሊደርስ የሚችልበትን አዲስና ህያው የሆነ መንገድ መርቆ ከፈተ። በዚህም መሰረት መጽሐፍ ቅዱስ በሮሜ 1፡17 ላይ እንደሚናገረው ለሚያምን ሁሉ ለድነት የሚሆን የእግዚአብሔር ኃይል የሆነ የእግዚአብሔር ጽድቅ በወንጌል ተገለጠ።

ይህም ጽድቅ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ በእምነት የሆነ ሰው በገዛ ኃይሉ ባለፉት ዘመናት ሁሉ ሊያደርገው ፈጽሞ ያልቻለው ነጻ የሆነ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው። ይህም ማለት ኢየሱስ የህግ ፍጻሜ እንደሆነና እግዚአብሔር ከሙታን እንዳስነሳው በልባችን አምነን የምንፀድቀው፣ ይህንኑም እምነታችንን ኢየሱስ ጌታ እንደሆነ በአፋችን በመመስከር የምንድንበት፣ እግዚአብሔር ወደ እርሱ ጽድቅ በየትኛውም መንገድ በራሳችን አቅም መድረስ እንደማንችል ለተረዳን ለእኛ ለሁላችን በምህረቱ ባለጠጋ ስለሆነ ከወደደን ከታላቅ ፍቅሩ የተነሳ ብቻ የገለጠው የአንድም ሰው እጅ የሌለበት ነጻ የሆነ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው። ይህም ነጻ የሆነ ስጦታ እግዚአብሔርን አንድያ ልጁን ጨክኖ ለመስቀል ሞት አሳልፎ እስከ መስጠት የደረሰ ከባድ ዋጋን ያስከፈለው በዚሁ የመስቀል ስራ የእርሱን ጽድቅ ለእኛ ሰጥቶ የእኛን ሀጢአት በልጁ ላይ አድርጎ ሀጢአትን የቀጣበት በጥንቃቄ የሚያዝ የመጨረሻ የመዳን እድልና እንዲሁ በነጻ እጃችን የገባ ዋጋው ታላቅ የሆነ እንቁ ነው።

*"ፃድቅ በእምነት ይኖራል"* ተብሎ እንደተጻፈ፣ ይህ በወንጌል የተገለጠው በነጻ ያገኘነው የእግዚአብሔር ጽድቅ በእምነት በሆነ የጽድቅ ምልልስ የሚታይና የሚረጋገጥ ደግሞ እንዲሆን ያስፈልገዋል። ይህ የእግዚአብሔር ጽድቅ እኛ ሁላችን ከጽድቅ የጎደልንና ሀጢአተኞች እንደሆንን አውቀን በእግዚአብሔር ፊት እርዳታን ፍለጋ በመቅረብ በልጁ በኩል የገለጠውን የእርሱን ጽድቅ (የእግዚአብሔርን ትክክለኛነትና እውነተኛነት) በማመን የምንቀበለው ማንነት ነው።

ታዲያ በዚሁ በህይወታችን የተደረገ የሀጢአትና የጽድቅ ልውውጥ ወቅት ያመነውን የእግዚአብሔር ጽድቅ በእርግጥ እንዳመንነው ለመመስከር በህይወት እንገልጠውና እንኖረው ዘንድ የሚያስችል የጽድቅ ጠላቶች የሆኑትን አለማዊነትንና ሀጢአተኝነትን ማስካድ የሚችል የራሱ ፀጋ አብሮ ለእኛ የተሰጠበት በዚሁ ህይወት ፀንተን እንኖር እና ወደ እውነት ሁሉ በማደግ እርሱ ጋር እንደርስ ዘንድ የሚቀድሰንን መንፈሱን ሳይሰፍር ለእኛ

> "ጽድቅ በእምነት ብቻ የሚገኝ እግዚአብሔርን የመምሰል ስር ሲሆን በህይወት የተገለጠ ቅድስና ደግሞ ከዚሁ ስር የተገኘ የጽድቅ ህይወት ፍሬ ነው።"

የሰጠበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ይህም አጋንንት በእግዚአብሔር መኖር እንደሚያምኑ አልፎም በፊቱ እንደሚንቀጠቀጡት ብቻ ህይወት አልባ የሆነ ሙት እምነት በፊቱ እንዲኖረን ሳይሆን በስራ ማለትም በህይወት ምልልስ ይህንኑ የእግዚአብሔር ጽድቅ በሚያየን ሁሉ ፊት ለመግለጥ የእርሱ እንደራሴዎች ሆነን ከአለም ተለይተን የምንኖርበት ህይወት ነው።

ጽድቅ በእምነት ብቻ የሚገኝ እግዚአብሔርን የመምሰል ስር ሲሆን በህይወት የተገለጠ ቅድስና ደግሞ ከዚሁ ስር የተገኘ የጽድቅ ህይወት ፍሬ ነው። ይህም በሮሜ 3፡31 ላይ እንደተጻፈው ጽድቃችን ከፃፎችና ከፈሪሳዊያን ጽድቅ ይበልጥ ዘንድ በህግ ከተገለጠው የአድርግና አታድርግ ትዕዛዝ በላይ በሆነ በልጁ በኢየሱስ በኩል የተገለጠውን የልቡን ሃሳብ ሁሉ በፀጋው በኩል በማድረግ ከፀጋ በታች ሆነን ከህግ በላይ የሆነ ህሊናችን ሁሉ ነጻ የሆነበት የልጁ አይነት ህይወት ይኖረን ዘንድ ነው። ከእምነት የተነሳ ባገኘነው ጽድቅ ገና ከጅማሬው የእግዚአብሔር ጽድቅ እንደሆነ የተገለጠው ልጁ አንድ እንኳን ሳይቀር የፈፀመውን ህግ ዋጋ የሌለው ሳናደርግ ይልቁንስ በመኖር የምናፀናበት የእርሱ አይነት ህይወት ነው።

መቼም ይህ በእግዚአብሔር ልጅ በማመን ብቻ ያገኘነው የእግዚአብሔር ጽድቅ ከፍጥረት ጅማሬ አንስቶ የሰው ልጅ ባልተቋረጠ መንገድ ሞክሮ ሞክሮ ሊደርስበት ያልቻለው በነጻ የተሰጠን የእግዚአብሔር ፍጹም ትክክለኛነትና እውነተኛነት ነው። ይህም የቅዱሳን ጽድቅ ስራ በገዛ ደሙ የዋጃት እና የገዛት የሆነችው ደግሞም ሊወስዳት የሚመጣላት የእርሱ የሆነች መሽራው ይህችውም ቤተክርስቲያን (የእኛ መንፈሳዊ ቅንብር) የምትለብሰው ነጭ የተልባ እግር ልብስን ከእኛ ውስጥ የሚያወጣ በዚህም እድፈት ወይም የፊት መጨማደድ ወይም እንዲህ ያለ ነገር ሳይሆንባት ቅድስትና ያለ ነውር ትሆን ዘንድ ክብርት የሆነችን ቤተክርስቲያን ለራሱ እንዲያቀርብ ፈልጎ ያደረገው የከበረ የዘላለም እቅዱ ነው። ከዚህ የከበረ ዘላለማዊ ሃሳቡና እቅዱ ውጭ በሆነ መንገድ በአመጽና ባለማመን ብሎም ከእግዚአብሔር ጽድቅ ተቃራኒ በሆነ የርኩሰት አለም የሚኖሩ ሁሉ ከመጀመሪያው በዚሁ አመጽ ከሚታወቀው ሰይጣንና መላዕክቶቹ ጋር አብረው ለእርሱ በተዘጋጀ የእሳት ባህር ከርኩሰታቸው ጋር የሚጣሉበት የእግዚአብሔር ትልቅ ቁም ነገር ነው።

በዚሁ የተገለጠ የእግዚአብሔር ጽድቅ ውስጥ የተገለጡ ለቅዱሳን የተሰጡ ተስፋዎች አዲሱ ሰማይና ምድር ብሎም ቅድስቲቱ ከተማ ኢየሩሳሌም ለውሾችና ለአስማተኞች፣ ለሴሰኞችና ለነፍሰ ገዳዮች፣ ጣኦኦትን ለሚያመልኩና ውሸትን ለሚወድዱ፣ ብሎም በመሰል ከእግዚአብሔር ጽድቅ ተቃራኒ በሆነ የአመጽ ህይወት ለሚሳተፉ ሁሉ ፈጽመው የተከለከሉና የማይሰጡ ናቸው። ነገር ግን ልብሳቸውን በበጉ ደም ላጠቡ፣ ከበጉ ደምና ከምስክራቸውም ቃል የተነሳ በታማኝነት በፊቱ የእግዚአብሔር ጽድቅ ሆነው በመኖር ድል ለነሱ ብቻ የተዘጋጀ ያመኑ ሁሉ እንደ ሰባ እንቦሳ የሚፈነጩባት የጽድቅ ፀሃይ የወጣባት ያወቃትና የልብ አይኑ በርቶ የተመለከታት ሁሉ በስስት አንጋጦ የሚጠብቃት ውድ ተስፋ ናት።

Life
TRUTH 14:6

## የማስተንተኛ ጥያቄዎች

1. የእግዚአብሔር ጽድቅ ስለ ማንነቱ ምን አስተማረህ?
2. ሰው በራሱ ጥረት የእግዚአብሔርን ጽድቅ ማግኘት የማይችለው ለምንድር ነው?
3. የእግዚአብሔርን ጽድቅ በእምነት መቀበልህ የዕለት ተዕለት ኑሮህን እንዴት ሊለውጠው ይገባል?

## አሰላስል

እግዚአብሔር ፍጹም ጻድቅ ነው። ጽድቁ ከሰው ጽድቅ ሁሉ በላይ ነው፤ በሰው ጥረት፣ በመልካም ሥራ ወይም በሕግ መፈጸም ሊደረስበት አይቻልም። እግዚአብሔር ግን ጽድቁን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ገልጧል፤ በእርሱም ለሚያምኑ ሁሉ በጸጋ ሰጥቶአል። ይህን የጽድቅ ስጦታ በእምነት ከተቀበልን በኋላ፣ የእግዚአብሔርን ባሕርይ በሚያንጸባርቅ መንገድ መኖር ይገባናል። ሕይወታችን በእውነት፣ በእምነትና በመታዘዝ የእርሱን ጽድቅ ለዓለም ሊያሳይ ይገባል። ስለዚህ በራሳችን ጽድቅ ሳይሆን በክርስቶስ በተሰጠን የእግዚአብሔር ጽድቅ መመካትና በእርሱ መመላለስ እንደሚገባን ሁልጊዜ ልናስታውስ ያስፈልገናል።

## ጸሎት

በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፣ ጽድቅህን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ስለገለጥህልን እናመሰግንሃለን። በራሴ መልካምነት ወይም ጽድቅ ሳልታመን፣ በልጅህ የሰጠኸኝን ጽድቅ እንድታመን እርዳኝ። በጸጋህ ሕይወቴን ለውጠህ፣ በእውነት፣ በእምነትና በመታዘዝ በፊትህ እንድመላለስ እርዳኝ። ሕይወቴም የአንተን ጽድቅ ለሌሎች እንዲያንጸባርቅ በመንፈስህ አግዘኝ።

በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አሜን።

## የአርምሞ ጥቅስ

*“ጻድቅ በእምነት ይኖራል ተብሎ እንደ ተጻፈ የእግዚአብሔር ጽድቅ ከእምነት ወደ እምነት በእርሱ ይገለጣልና።”*

*— ወደ ሮሜ ሰዎች ፩፥፲፯ —*

## 2.12. እግዚአብሔር ታማኝ ነው!

ታማኝ የሚለው ቃል በዋነኛነት እውነተኛ የሆነ፣ መደገፊያ ሊሆን የሚችል፣ አስተማማኝ፣ ንግግሩ እና ድርጊቱ የተመሳሰለ፣ ቃል ኪዳኑን መጠበቅ የሚችል፣ ልብ የሚጣልበት፣ በእጅ መንሻ ፍትህን የማያዳድል፣ ፍርድን የማያዛባ፣ ሁልጊዜ አንድ አይነትና ወጥ የሆነ አቋም ያለው፣ የማይለወጥ፣ የሚጠበቅበትን ሀላፊነት /ግዴታውን/ መወጣት የሚችል፣ በሌላ ሶስተኛ ወገን ግፊት ያለውን ከማድረግ የማይገታ ወዘተ የሚሉ እጅግ በጣም ከፍተኛ የማንነት ደረጃን የሚፈልጉ ሃሳቦችን ያዘለ ቃል ነው። (ግዛው, 1994) (Merriam-Webster, n.d.)

በዚህም መሰረት ከላይ በተገለጸውና በዝርዝር በተቀመጠው መንገድ የተባለውን አይነት የህይወት ጥራት የሚያሟላ በተለይም ደግሞ ያለውን ለመሆን የሚያስችል ብቃት ያለውና በምንም አይነት ሌላ ሶስተኛ ወገን ተጽዕኖ የማይደርስበት የሚለው ቃል ፍጥረትን በሙሉ ከዚህ ቃል ቋት ውስጥ የሚያስወጣ ሆኖ እናገኘዋለን። ፈጽሞ ባልተቋረጠ ሁኔታ ሁልጊዜ ተመሳሳይ የሆነ ማንነትን ይዞ ሳይለወጥ ያለውን በማድረግ የተገለጠ ህይወት የሚኖር ስጋ ለባሽን ፈልጎ ማግኘት ፍጹም የማይታሰብ ነው። በዚህ አይነት ማንነት የሚታወቅና ቃሉን ሁልጊዜ በመጠበቅ የተመሰከረለት እንከን አልባና ፍጹም ታማኝ የሆነ ሰውን ማንም ሰምቶ ወይም አይቶ የሚያውቅ የለም። ይህም ብቻ ደግሞ አይደለም አንድ አካል በተባለው የህይወት ጥራት ከፍታ ሁልጊዜ ታማኝ ሆኖ ለመገኘት የሚያስችል አቅም እና ቁመና እንዲኖረው ከተጽእኖ ነጻ የሆነ አለም ደግሞ ያስፈልገዋል።

በዚህ ከላይ በተገለጸው የህይወት ጥራት እና የማንነት ከፍታ ልክ ሊገኝ የሚችል ፍጹም ልብ ሊጣልበት የሚችል አካል አምላካችን እግዚአብሔር ብቻ ነው። የእግዚአብሔር ታማኝነት ሌላ ሰውን ባለመታመን ላለማሳዘን በሚል መሰረት ላይ የተገነባ ሳይሆን እግዚአብሔር ከራሱ ማንነት ጋር ይጣላ ዘንድ ስለማይችል ለራሱ የሚታመንበት ጽኑ መሰረቱ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በ2ኛ ጢሞቴዎስ 2፡13 ላይ እንደሚናገረው ሰው ሁሉ ባያምነው እንኳን እርሱ ራሱን ይክድ ዘንድ ስለማይችል ለራሱ የታመነ ሆኖ የሚኖርበት ማንነቱ ነው። ይህም ፍጹም የሆነ የእግዚአብሔር ታማኝነት በዘመናት መካከል የተረጋገጠ በትውልድ ቅብብሎሽ ሁሉ ውስጥ የተመሰከረለት የማይለወጥ ማንነቱ ነው።

> “የእግዚአብሔር ታማኝነት ሌላ ሰውን ባለመታመን ላለማሳዘን በሚል መሰረት ላይ የተገነባ ሳይሆን እግዚአብሔር ከራሱ ማንነት ጋር ይጣላ ዘንድ ስለማይችል ለራሱ የሚታመንበት ጽኑ መሰረቱ ነው።”

እግዚአብሔር ብዙ ህዝብ ሊያደርገው ቃል ኪዳን ገብቶለት ከአባቱ ቤት ወደማያውቀው ምድር የወጣው አብርሃም ምንም እግዚአብሔር ያለውን ሳያደርግለት አመታት ያለፉ እና እድሜውም ልጅን መውለድ የማይችልበት ጊዜ ላይ የደረሰ ቢሆንም ከላይ በቃሉ ፍች እንደተገለፀው በየትኛውም ሁኔታ ያለ ምንም ከልካይ ያለውን ማድረግ የሚችል ቃሉንም መጠበቅ የሚችል ማንነት ያለው እግዚአብሔር በአብርሃምና በሚስቱ እድሜ ማብቂያ ላይ እንደተናገረው የብዙ ህዝብ አባት ሊያደርገው ይስሃቅን ሰጠው። ይህም ይስሃቅ ከሁለት ትውልድ በኋላ ቀድሞ ታማኙ እግዚአብሔር እንደተናገረው እልፍ የሆነ ቁጥር ያለው ህዝብ /እስራኤል/ ሆነ። ታዲያ ይህ ሁሉ ሲሆን ከመጀመሪያው ኪዳኑን የሰጠው እግዚአብሔር ታማኝነቱ ይፈተሽና ጥያቄ ውስጥ ይገባ ዘንድ ሊያረጋግጥ የሚችለው ከመጀመሪያው ኪዳኑ ውስጥ የተሳተፈው ቃል የተገባለት አብርሃም በህይወት በሌለበት ዘመን ለራሱ ታማኝ የሆነው እግዚአብሔር ዘመናትን ተሻግሮ በታማኝነት ቃሉን ጠብቆ እንደተናገረ እንዲሁ አደረገ።

መጽሐፍ ቅዱስ በኢያሱ 21፡45 ላይ እንደሚናገረው ያን የተስፋ ቃል ሊወርስ ለተገባው ትውልድ ኪዳኑ የተሰጣቸው አብርሃም፣ ይስሃቅ እና ያዕቆብ በህይወት በሌሉበት ሁኔታ ከተናገረላቸው መልካም ነገር አንዳችስ እንኳን ሳያጎድል፣ በዘመናት መካከል ቀድሞ የገባውን ቃል በእርጅና ምክንያት ሳይረሳና ሳይዘነጋ ብሎም የማድረግ አቅምን ሳያጣ ለራሱ ታምኖ ሁሉን በታማኝነት ፈፀመ እንጂ ምንም አላስቀረም።

ይህ ፍጹም የሆነ ታማኝ አምላክ ራሱን ይክድ ዘንድ እንዳይችል ታማኝነቱ ለራሱ ነውና ቃሉ ሳይፈፀም ከሚቀር እና ከሚያልፍ ትላልቆቹ ሰማይና ምድር ቢያልፉ እጅግ የሚቀል ነው። በዚህ ክፍል መጀመሪያ ላይ ቃሉን በፈታን ጊዜ እንደተመለከትነው ይህ ታማኝ አምላክ እግዚአብሔር ያለውን በሙሉ ለማድረግ የሚያስችል ማንነት ያለው አምላክ ነው። ይህም ማንነቱ የወደደውን በወደደው ጊዜና ቦታ ብሎም አደራረግ

ለማድረግ የሚያስችል ፍጹም የሆነ ሁሉን ቻይነት፣ ሁሉን አዋቂነት እና በሁሉም ስፍራ የመገኘት ታላቅና ኃያል ማንነት ያለው ነው።

ይህም የተገለጠ ታማኝነቱ እርሱንና ቃሉን አምነው ለጣኦት አንስግድም ብለው ወደ እቶን እሳት ውስጥ በተጣሉት ሶስቱ ብላቴኖች ማለትም ሲድራቅ፣ ሚሳቅና አብድናጎም ህይወት ውስጥ ደምቆ የሚታይ እውነት ነው። በባሪያው ዳዊት ልብ ደስ የተሰኘው እግዚአብሔር ዳዊት ከሞተ በኋላ ሁሉ ይህንኑ ኪዳኑን ለመጠበቅና በታማኝነቱ ለመገኘት በብዙ መልኩ አስቸጋሪ ሆነው የተገኙትን የዳዊት ልጆች ታግሶ *"ስለ ባሪያው ስለ ዳዊትና ስለ ሰጠው የተስፋ ቃል"* በሚል መንግስቱን በፍጹም ጥንቃቄ ቃል እንደገባው ከዘሩ ንግስና ለዘላለም እንዳይጠፋ ዘላለማዊ የሆነውን ንጉስ ይኸውም ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን ከዳዊት ዘር እንዲመጣ አደረገው። በዘመናት መካከል ይህንን ጌታ አምላካቸው አድርገውት ያለፉ ሁሉ ስለ ፍጹም ታማኝነቱ ይመሰክሩለታል።

ለአብርሃም ቀድሞ እንደተናገረ ዘሩን ወደ ግብጽ አስገባ፣ ህዝብ አድርጎ ከግብጽ ባርነት አወጣ፣ ወደ ተስፋይቱ ምድር አደረሰ፣ በመተላለፋቸው ለባርነት አሳልፎ ሰጣቸው፣ በኤርምያስ አስቀድሞ እንደተናገረ ከ7፲ አመት በኋላ ወደ ምድራቸው መለሳቸው፣ መጀመሪያ ለወደቀው ሰው አዳምና ለሚስቱ ከዘሯ የእባቡን ራስ የሚቀጠቅጥ አዳኝ ሊያመጣ ቃል እንደገባው ዘመኑን ጠብቆ ልጁን ላከ፣ እንዳለው በመስቀል ሞት ሀጢአትን ይኸውም የዲያብሎስን ስራ አፍርሶ የጠላቱን ራስ ቀጠቀጠ፣ ከሞት እነሳለሁ እንዳለ ከሞተ ተነሳ፣ እንዲሁ ደግሞ በዚሁ ታማኝነቱ ልወስዳችሁ ዳግመኛ እመጣለሁ እንዳለ በእርግጥ ሊወስደን ተመልሶ በታላቅ ክብር ይመጣል።

እርሱ የተናገረውን ማድረግ እንዳይችል በጊዜ ብዛት የሚያረጅ፣ የሚታክት፣ የሚረሳ፣ የማድረግ አቅም የሚያጣ ወዘተ አይደለም። ይልቁንስ ያለው ሁሉ የሚሆንለት ከአፉ የወጣ ቃል ሁሉ በጊዜው እንዲፈፀም የተናገረው ቃሉ ታማኝነቱን ያፀና ዘንድ ዝናብና በረዶ ከሰማይ እንደሚወርድ

> "እርሱ የተናገረውን ማድረግ እንዳይችል በጊዜ ብዛት የሚያረጅ፣ የሚታክት፣ የሚረሳ፣ የማድረግ አቅምም የሚያጣ ደካማ አይደለም።"

ምድርንም እንደሚያረካት ታበቅልና ታፈራም ዘንድ እንደሚያደርጋት እንጂ ወደ ሰማይ አንዳች ሳያደርግ እንደማይመለስ እንዲሁ የተናገረው ቃሉ የሚሻውን አድርጎ የላከውን ፈቃድ ፈጽሞ ታማኝነቱን ያፀናል እንጂ በከንቱ ተነግሮ ብቻ አይቀርም። ለዚሁ ነው ጳውሎስ በ፩ኛ ተሰሎንቄ መልዕክቱ ምዕራፍ 5 ቁጥር 24 ላይ የእግዚአብሔርን ታማኝነት ሲያፀናልን *"የሚጠራችሁ የታመነ ነው እርሱም ደግሞ ያደርገዋል"* ብሎ ያለን።

ይህ ታማኝነቱ እና በዘመናችን እኛ ራሳችን የተመለከትነው ይሄው ማንነቱ ለዛሬና ወደ ፊት ለሚመጣው ህይወታችን እንድናምነው ሊያደርገን ያስፈልጋል። ነገር ግን አብዛኛውን ጊዜ እግዚአብሔር ለእኛ የሰጣቸው የተስፋ ቃሎች እኛ አሁናዊ በሆነ የህይወት ምልልስ ከምንጓዘው ጉዞ ጋር ፈጽመው የማይመሳሰሉ ስለሚሆኑብን እግዚአብሔር የተናገረውን የረሳ፣ በዙሪያችን ያለው የከበበን ጨለማ፣ ማዕበል እና ችግር ወዘተ ከእግዚአብሔር ያለውን የማድረግ አቅም በላይ የሆነ እየመሰለን ደጋግመን እርሱን ከማመን ስንጎድል እንታያለን። ይህ ደግሞ እግዚአብሔርን ሲያሳዝነው እኛንም ደግሞ ከተስፋ ቃላችን ጋር በፍጥነት እንዳንገናኝ ይልቁንስ አላስፈላጊ ቆይታ ውስጥ እንድንሆን ሲያደርገን ይታያል።

ትናንት ቀይ ባህርን ከፍሎ በደረቅ ምድር ያሻገረን እግዚአብሔር በመንገዳችን ሁሉ የሚበላና የሚጠጣ እንደሚሰጠን፣ ዮርዳኖስን ከፍሎ ጠላቶቻችንን መትቶ አስገባችኋለሁ ያለን የተስፋው ምድር ጋር እንደሚያደርሰን፣ ይህንንም እንዳያደርግ የሚከለክለው አንዳች ምድራዊና ሰማያዊ ኃይል እንደሌለ ልንረዳ ያስፈልገናል። እርሱ ሲያምኑትና ሲደገፉት አልችል ብሎ ተሰብሮ የሚወጋ ሸንበቆ አይደለም። ወይም ደግሞ ከአቅሙ በላይ የሆነ ችግር አጋጥሞት ስላልቻለ ይቅርታ የሚጠይቅ አምላክ አይደለም። ያለውን ሁሉ በታማኝነት አንዳች ሳያስቀር በመሰለን ልክ ሳይሆን እርሱ ባሰበልን ልክ ለማድረግ የሚያስችል ሙሉ ብቃት እና ማንነት ያለው ፍጹም ታማኝ የሆነ ብቸኛ አምላክ ነው።

እንዲህ አይነቱ ሁኔታ እግዚአብሔርን በእኛ እንዲያዝን ከማድረጉም ባለፈ መጽሐፍ ቅዱስ በዕብራዊያን 3፡19 ላይ ባለማመናቸው ጠንቅ ሊገቡ አልቻሉም ተብሎ እንደተጻፈ እግዚአብሔርን ኪዳኑን ለሌላ ትውልድ በታማኝነት እንዲጠብቅና እንዲያደርግ እኛ ግን ከፍፃሜ እንድንጎድል ሊያደርገን ይችላል። ይህም ወተትና ማር

ወደምታፈስስ ምድር ሊያስገባቸው ቃል ገብቶ ከግብጽ ምድር ካስወጣው ህዝብ ውስጥ አለማመኑና አለመታዘዙ በምድረ በዳ ባስቀረው ህዝብ ታሪክ ውስጥ በግልጽ የሚታይ እውነት ነው። በእንዲህ አይነቱ ወቅት ሰው እግዚአብሔር የታማኝነት ችግር እንደሌለበት በማወቅ በትህትና ፊቱ ቀርቦ አለማመኔን እርዳው ማለት ያስፈልገዋል። ከዚህም በተጨማሪ በተስፋው ደስ እያለው በሚያልፍበት መከራ ደግሞ እየታገሰ በፀሎት እየተጋ ፍፃሜውን ሊጠብቅ ያስፈልገዋል።

መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን የተስፋ ፍፃሜ በተመለከተ በዕብራዊያን ፮፡፲፩ እና ዕብራዊያን ፲፡፴፮ ላይ በተመሳሳይ ሁኔታ እንደሚነግረን በእምነት፣ በትዕግስት፣ በትጋትና በፍጹም ጽናት ውስጥ በመሆን የእግዚአብሔርን ፈቃድ እያደረጉ በስፍራ ሆኖ መጠበቅን ይጠይቃል። ዳዊት በመዝሙሩ ምዕራፍ ፲፰ ቁጥር ፴ ላይ እንደሚናገረው *“የእግዚአብሔር ቃል የነጠረ ነው ደግሞ ለሚታመኑት ሁሉ ጋሻ ነው።”*

በዚህ መሰረት እስከ አለም ፍፃሜ ከእናንተ ጋር እሆናለሁ ያለው ጌታ በእርግጥ ዛሬ አሁን ከእኛ ጋር እዚህ አለ። እኔ ባለሁበት እናንተ ደግሞ እንድትሆኑ ልወስዳችሁ ተመልሼ እመጣለሁ እንዳለ በእርግጥ መድሃኒታችን በክብር በደመና ተመልሶ ሊወስደን ይመጣል። እኔ ባለሁበት ለዘላለም ትሆናላችሁ እንደተባለም ለቅሶ፣ ሀዘን፣ እንባ ወዘተ በሌለበት በዚያ አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር በዘላለም እረፍት ውስጥ ከእርሱ ጋር እንሆናለን።

*“የጠራችሁ የታመነ ነው፤ እርሱም ያደርገዋል።” — ፩ኛ ተሰሎንቄ 5፥24*

“እስከ አለም ፍፃሜ ከእናንተ ጋር
እሆናለሁ ያለው ጌታ በእርግጥ ዛሬ አሁን
ከእኛ ጋር እዚህ አለ።”

## የማስተንተኛ ጥያቄዎች

1. የእግዚአብሔር ታማኝነት ስለ ማንነቱ ምን ግንዛቤን ጨመረልህ?
2. የእግዚአብሔር ታማኝነት በአስቸጋሪ ወቅቶች እምነትህን እንዴት ሊያጸናው ይገባል?
3. በበለጠ እምነትና ትዕግሥት እንድትጠብቅ እግዚአብሔር እየጠራህ ያለበት የሕይወትህ ክፍል አለ?

## አሰላስል

እግዚአብሔር ታማኝ ነው፤ ታማኝነትም የእርሱ ባሕርይ አካል ነው። ተስፋዎቹ በሁኔታዎች፣ በሰው ኃይል ወይም በጊዜ መለወጥ ላይ የተመሠረቱ አይደሉም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሰጣቸውን ተስፋዎች ሁሉ የፈጸመው አምላክ ዛሬም ታማኝ ነው፤ የተናገረውንም ሁሉ በእርግጥ ይፈጽማል። ስለዚህ የተስፋዎቹን ፍጻሜ አሁን ባናይም እንኳን፣ በቃሉ ታምነን ልንጸና እንችላለን። የእግዚአብሔር ታማኝነት በሁሉም ዘመን የማይለወጥ ስለሆነ፣ ሕይወታችንን በእርሱ ተስፋ ላይ አድርገን በትዕግሥት መጠበቅ እንደሚገባን ማስታወስ ያስፈልጋል።

## ጸሎት

በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፣ ፈጽሞ የማትለወጥና የማትዝል ታማኝ አምላክ ስለሆንህ እናመሰግንሃለን። ሁኔታዎች አስቸጋሪ በሚሆኑበት ጊዜ እንኳ በተስፋዎችህ እንድታመን እርዳኝ። እምነቴን አጽና፣ ትዕግሥትን አስተምረኝ፣ የቃልህን ፍጻሜ እየጠበቅሁ በፊትህ በታማኝነት እንድመላለስ እርዳኝ። የተናገርኸውን ሁሉ እንደምትፈጽም በልቤ እንድታመን አግዘኝ።

በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አሜን።

## የእርምጃ ጥቅስ

*"የሚጠራችሁ የታመነ ነው፥ እርሱም ደግሞ ያደርገዋል።"*

*— 1ኛ ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 5፥24 —*

## 2.13. እግዚአብሔር እውነት /እውነተኛ/ ነው!

እውነት የሚለው ቃል ሀቅ፣ እርግጥ፣ ሀሰት የሌለበት፣ የነገሮች ትክክለኛ ገጽታ ወዘተ የሚሉ አቻ ትርጓሜዎችን የያዘ ነው። በዚህም መሰረት ይህ እውነት የሚመዘንበትና በሌላ አንፃራዊ የሆነ ተመሳሳይ ሁኔታ የማይለወጥበት መለኪያን የሚፈልግ ሆኖ ይታያል። ይህም እውነትን አንፃራዊ እንዳይሆን እና በርካታ እውነቶች እንዳይኖሩ ነገር ግን ፍጹም የሆነ በእውነት መለኪያ ተመዝኖ ተቀባይነትን ያገኘ አንድና ብቸኛ እርግጥ የሆነ ግልጽ ማንነት ያለው እንዲሆን ያደርገዋል። ለምሳሌ ያክል በዚህ በእኛ ዘመን እንደሚባለው እውነትን እውነት በሚመስል ሽንገላ በርካታ መልክን ሊሰጡት እና ሊያሳምኑን የሚወዱ በርካቶች ከሚያነሷቸው ማስረጃዎች መካከል ዘጠኝ ቁጥር ሆኖ የተጻፈ አሃዛዊ ጽህፈት ለሌላ ሰው ስድስት ሊሆን እንደሚችል በዚህም በሁለተኛ ሰው እይታ መሰረት በእርግጥም ቁጥሩ በእውነት ስድስት እንደሆነ ሊያስረዱ ይሞክራሉ። ነገር ግን ከላይ በእውነት ትርጓሜ ላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ከመጀመሪያው ቁጥሩ በተጻፈበት ወቅት የመጀመሪያው ጸሃፊ በእርሱ አዕምሮ ውስጥ እንዲያስተላልፍለት አስቦ በጻፈበት የመጀመሪያ አውድ ዘጠኝ ወይም ስድስት እንዲሆን አስቦ እንደፃፈው ትክክለኛው እውነታም በዚሁ የእውነት መለኪያ የሆነ የመጀመሪያ አካል የሚወሰን አንፃራዊ ያልሆነ ይልቁንስ ፍጹም የሆነ እውነት ነው።

እግዚአብሔር እርሱ ራሱ እውነት ነው! እውነት የእግዚአብሔር ማንነት ነው። ይህም እግዚአብሔር ሀሰት የሌለበት፣ እንከን አልባ፣ ፍጹም እውነተኛ፣ የየትኛውም ነገር እውነታ መወሰኛ ቁምቢ እንደሆነ የሚገልጽ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በዮሐንስ ወንጌል 14፡6 ላይ በግልጽ እንደሚናገረው የእግዚአብሔር አብ ሙሉ መልክ ማሳያ የሆነው ስጋ ሆኖ የተገለጠው ልጁ ይኸውም ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱ ራሱ እውነት እንደሆነ ተናግሯል። ይህም ቃል በፍጥረት አለሙ ውስጥ ላሉ እውነታዎች ሁሉ የእውነተኛነታቸው ማረጋገጫ፣ ነገሮች በእግዚአብሔር ፊት ያላቸው እይታ መወሰኛ እንደሆነ የሚገልጽ ነው።

ከላይ በመግቢያው ላይ በምሳሌ ለመግለጽ እንደተሞከረው እውነት ፍጹም እንጂ አንፃራዊ ያልሆነ የእውነተኛነቱም መለኪያ እግዚአብሔር በነገሩ ላይ ያለው እይታ እና ትርጉም ብቻ እንደሆነ መገንዘብ ያስፈልገናል። እግዚአብሔር ምንም አይነት ጨለማ በእርሱ ዘንድ የሌለበት ፍጹም ብርሃን፣ ደግሞ ይዋሽና ራሱን ይክድ ዘንድ እንዳይችል

ፈጽሞ ሀሰትን የማይናገር እንደሆነ መገንዘብ ያስፈልገናል። ከዚህ በፊት በዝርዝር የተገለጸው የእግዚአብሔር ታማኝነት እውነት ከመሆኑና ራሱን ይክድ ዘንድ እንዳይችል ሀሰትን የማይናገር ከመሆኑ ጋር የተቆራኘ ፍጹም የሆነ የእርሱ ማንነቱ ነው። በዚህም መሰረት እግዚአብሔር ራሱን ለእኛ የገለጠበት ይህ ቃሉ ፈፅሞ እውነት የሆነ የሚታመን እና ልብ ሊጣልበት የሚችል በየትኛውም መንገድ ተፈልጎ ሀሰትና እርስ በእርስ መጋጨት የማይታይበት ከዘፍጥረት እስከ ራዕይ ድረስ ፈጽሞ ተመጋጋቢ እና ተደጋጋፊ የሆነ አንድና ወጥ ሆኖ የተገለጠ ብቸኛ እውነት ነው። በዚህም እውነት የሆነ ቃል መሰረት ብቻ የተፈጠሩ ነገሮች ሁሉ እውነታ የሚለካ እና የሚረጋገጥ ይሆናል።

ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ፊት ለፊት ለመነጋገር እድልን ያገኘው ጲላጦስ በዮሐንስ ወንጌል 18፡38 ላይ ንጉስ እንደሆነ የተጠየቀው ኢየሱስ ለእውነት ሊመሰክር የመጣና ስለዚህም የተወለደ እንደሆነ ከእውነት የሆነም ሁሉ ድምጹን እንደሚሰማ በነገረው ጊዜ *"እውነት ምንድር ነው?"* ብሎ ከባድ ጥያቄን ጠየቀው። ነገር ግን እውነት ራሱ ይኸውም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በፊቱ ቆሞ ነበርና በርካታ እንከን መፈለጊያ እና ለፍርድ የሚያበቃ ግምገማዎችን ገምግሞ ምንም ባላገኘበት ጊዜ አንዳች ውሸት የሌለበት ፍጹም እውነት እንደሆነ ለመግለጽ በሚመስል ቅኔ *"እኔስ የሚያስከስስ በደል አላገኘሁበትም"* አለ። እንዲሁም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ በዮሐንስ ወንጌል 14፡30 ላይ ሲናገር የውሸት ሁሉ አባት የሆነውና ፈጽሞ እውነትን የማያውቀው የዚህ አለም ገዥ ይኸውም ዲያብሎስ የሚመጣበት ሰዓት እንደደረሰ ነገር ግን እውነት በሆነው በእርሱ ላይ አንዳች የዲያብሎስ የሆነ ነገር እንደሌለ በተናገረበት ሁኔታም የዚህን የእግዚአብሔር እውነት ፍጹም እውነተኛነት ማየት ይቻላል።

መጽሐፍ ቅዱስ በሮሜ 3፡4 ላይ *"ሰው ሁሉ ውሸተኛ ከሆነ እግዚአብሔር እውነተኛ ይሁን"* ብሎ ይናገራል። ይህም በ2ኛ ጢሞቴዎስ 2፡13 ላይ *"ባናምነው እርሱ የታመነ ሆኖ ይኖራል ራሱን ይክድ ዘንድ አይችልምና"* ብሎ ከሚናገረው የእግዚአብሔርን ፍጹም እውነትነትና እውነተኛነት የሚያሳይ ክፍል ጋር ተመሳሳይ ይዘት ያለው ነው። ይህም የየትኛውም እውነት መነሻና መለኪያ እርሱ እግዚአብሔር ራሱ ለነገሮቹ የሰጠው ማብራሪያና በነገሩ ላይ ያለው አቋም እንጂ ሰዎች ተሰብስበው በአንድ ነገር ላይ የደረሱበት ስምምነት እንዳልሆነ የሚያሳይ ነው። ለዚህም አይነተኛ ማሳያ የሚሆን ምሳሌ የተመሳሳይ

ጾታ ጋብቻን እንዲሁም ለሰው ልጅ ነጻነት መስጠት በሚመስል መልኩ ውርጃን ህጋዊ አድርገው የፈቀዱ አገራትና የሰዎች ቡድን የትኛውንም ያክል ጊዜ ይህንን ህግ ያወጡበትንና ለሰው ልጆች መብት የሰጡበትን ምክንያት ደጋግመው ሊያብራሩ ቢሞክሩም በሰው ልጆች አዕምሮም ፍጹም መግባባትና ስምምነት ቢደረስባቸውም የድምጽ ብዛት እውነት አያደርጋቸውም። እግዚአብሔር በእነዚህ ሁለት የተጠቀሱ እና መሰል ጉዳዮች ላይ ያለው ከመጀመሪያው የነበረ ፍጹም እውነት የሆነ የእርሱ አቋምና ማብራሪያ መሰረት በዚህ አይነት ድርጊት ውስጥ የሚሳተፉ ሰዎችን ሁሉ በደለኞችና የተሳሳቱ የሚያደርጋቸው ይሆናል። በዚህም መሰረት በሚታየው አለም የሚገኝ ምንም አይነት እውነት፣ እውነት የሚሆነው እግዚአብሔር በዚያ ጉዳይ ላይ ባለው ግልጽ አቋምና ግምገማ መሰረት ተቀባይነት ሲያገኝ ብቻ ይሆናል።

> "በሚታየው አለም የሚገኝ ምንም አይነት እውነት፣ እውነት የሚሆነው እግዚአብሔር በዚያ ጉዳይ ላይ ባለው ግልጽ አቋምና ግምገማ መሰረት ተቀባይነት ሲያገኝ ብቻ ይሆናል።"

ይህ የእግዚአብሔር እውነት አንፃራዊ ከሆነው የሰው ልጆች ባህል፣ ቋንቋ፣ ወግ፣ ዘር፣ የኑሮ ዘይቤ፣ እሴት ሁሉ በላይ የሆነ በየትኛውም አለም ክፍል ያሉ ህዝቦች ሁሉ የሚስማሙበት ከቦታ ቦታ የማይለያይ ፍጹም የሆነ እውነት ነው። ሰዎች ያላቸው የተለያየ የአስተሳሰብ ደረጃ፣ እውቀት፣ ጥበብና ማስተዋል፣ ስልጣን፣ የኑሮ ደረጃና ስልጣኔ ወዘተ ይህንን እውነት እንዲለያይ ሊያደርገው አይችልም። ይህ የእግዚአብሔር እውነት በየዘመኑ የማይቀየር አሁናዊ የሆነ ፈጽሞ የማይለዋወጥ ይዘት ያለው ዘላለማዊ ትክክለኛነት ነው።

እግዚአብሔር ራሱን በገለጠበት በዚሁ የተገለጠ እውነት በኩል የሚታየውን አለም መገምገምና ከዚህ ፍጹም የሆነ የእግዚአብሔር የማይለወጥ አቋም አንጻር ብቻ የነገሮችን ትክክለኛነት ማየትና መቀበል ብሎም ዘመንን መዋጀት ያስፈልገናል። የሰው ልጆች የደረሱበት የስልጣኔ ደረጃ ከዚህም ጋር ተያይዞ የመጣ የአዲስ ዘመን እሳቤ በዚሁ አዲስ ዘመን የተገኙ ህዝቦች ተስማምተው ያፀደቁትና እውነት ነው ብለው ስፍራ የሰጡት

ማንኛውም በእግዚአብሔር ፍጹም እውነትና እውቀት ላይ ከፍ ያለ የሰው ሃሳብ ሁሉ ከሰዎች አዕምሮ ውስጥ ሊፈርስና በዚሁ የክርስቶስ እውነት ሊተካ የሚገባው እውነት መሳይ ውሸት ነው።

በፍጥረታዊ ማንነት የተገኘ ሰው ሁሉ ከፍጥረቱ አንስቶ ባለው አጠቃላይ የኖረበት የኑሮ ዑደት ውስጥ የተሰራ ማንነት ያለው ሲሆን በአዕምሮ ቅንብሩም ውስጥ ለእውነትና ለውሸት ያለው ስፍራ በዚሁ ፍጥረቱና አስተዳደጉ ላይ ተመስርቶ የተገነባ ነው። በዚህም መሰረት ፍጥረት ሁሉ በዚህ መልኩ ከእግዚአብሔር ክብር የጎደለና ለከንቱነት የተገዛ ሆኖ አዕምሮውን በሞላው የማይደረስበት ፍጹም ውሸት የሆነ እውነት የሚመስል ሄዶ ሄዶ የማይደረስበት አለም ውስጥ እንዲመላለስ አድርጎታል።

በክርስቶስ ኢየሱስ በማመን አሮጌውን ነገር ቀብሮ አዲስ ማንነትን የተላበሰ ሰው ከዚሁ ከፍጥረቱ አንስቶ ከተዋቀረበት የዚህ አለም አንፃራዊ የሆነ እውነት መሰል ውሸት እየተላቀቀ ባልተቋረጠ የአዕምሮ መታደስ ውስጥ በማለፍ በአዕምሮው ውስጥ የተመሸገን ከእግዚአብሔር ፍጹም እውነት ጋር የሚቃረን አሮጌ ነገር ሁሉ በማፍረስ ራሱን ለክርስቶስ (የእግዚአብሔር እውነት) ማስገዛት ይጠበቅበታል። በዚህም የአእምሮ መታደስ ሂደት ውስጥ ያለፈ በየትኛውም የአለም ክፍል የሚገኝ በተለያየ ማህበረሰብ፣ ዘርና አስተዳደግ የተገኙ ሁሉ ውሸትን ከውስጣቸው ያጠፉ የእውነት መመዘኛ ቱምቢያቸው አንድ አይነት የሆነ በክርስቶስ የተጋጠሙና ተመሳሳይ መልክ የተላበሱ ሆነው ይታያሉ።

ይህ የእግዚአብሔር እውነት የነገሮችን እውነተኛነት ከመመዘንና ማረጋገጫ ከመስጠት ባለፈ ፈጽሞ የሚታመን የመትከልና የመንቀል፣ የማፍረስና የመገንባት ስልጣንን አብሮ የተላበሰ ማንነት ያለው እውነት ነው። ገና ከፍጥረት ጅማሬ አንስቶ ይህንን እውነት የሚቃወም ሌላ እውነት የሚመስል ለሰው አዕምሮ የሚመች የዚህ አለም እውቀትና ጥበብ ሁልጊዜ የሰው ልጆችን እስከ ዛሬ ድረስ እያሳተ ከእግዚአብሔርም እያራቃቸው ይገኛል። የዚህም እውነት የሚመስል ውሸት አባት ዲያብሎስ ሲሆን የዚሁ አለማዊ ጥበብና እውቀት ተከታዮች ደግሞ ልጆቹ ናቸው። ታዲያ በዚህ መሰረት ይህ የእውነት ሚዛን የእግዚአብሔርን ልጆች ከዲያብሎስ ልጆች የሚለይ ጥርት ያለ መለያ መልክ ሲሆን በየትኛውም መልኩ ሊቀላቀሉ እንዳይችሉ ሆነው የተጣሉና የማይቀላቀሉ የማንነት መለያዎች ናቸው። የእግዚአብሔር ልጆች በፍጥረታዊ ማንነታቸው

በውስጣቸው የተገነባውን አለማዊ የሆነ የእግዚአብሔር ያልሆነ ስጋዊ ግንባታ እያፈረሱ በማይቋረጥ የአዕምሮ መታደስም እየተለወጡ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ይኸውም የእግዚአብሔርን እውነት በማወቅ ይመላለሱ ዘንድ በዚህም በዙሪያው ሁሉ የተገኘውን ጨለማ ብርሃን ሆነው በመግፈፍ የአሸናፊና የድል ነሺ ኑሮ ይኖሩ ዘንድ ወደ እውነት ሁሉ የሚመራቸው የእውነት መንፈስ በውስጣቸው አላቸው።

የተሰወረ የጥበብና የእውቀት መዝገብ የሆነው ከመታወቅ ያለፈው የእግዚአብሔር አብ መልክ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የመጨረሻው የእውነት መገለጫና ትክክለኛ ትርጓሜ ነው። ይህም በዮሐንስ ራዕይ ፲፱፥፲፩ ላይ ባለው ክፍል ሰማይ ተከፍቶ በተገለጠ ራዕይ ውስጥ በአምባላይ ፈረስ ላይ ተቀምጦ በታየ ወቅት የተረጋገጠ ታማኝነትና ዘላለማዊ እውነትነት ነው። ታዲያ በዚህ መሰረት የሰውን ልጅ ለማዳን እውነቱን በሙላት የገለጠው አምላካችን እግዚአብሔር ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐንስ ፲፯፥፲፯ ላይ እንደተናገረ እውነት በሆነው ቃሉ ሳናቋርጥ እየተቀደስን የዚህ አለም ከሆነ አንጻራዊ የውሸት የሆነ ምልልስ በመላቀቅ በእውነት መንፈስ እየተመራን እውነትን ሁሉ በመልበስ ሽንገላን በእግዚአብሔር እቃ ጦር በመቃወም እውነት ወደ ሆነው ወደ ክርስቶስ እንድናድግ ያስፈልገናል።

ይህም የተለወጠ መልክና ማንነት ገና ከመጀመሪያው እግዚአብሔር ሰውን በፈጠረበት ወቅት ያሰበው የሰው ልጅ ይኖረው ዘንድ የወሰነው የልጁ መልክ ሲሆን በሀጢአት ምክንያት ሰው ከክብሩ ወርዶ ከእውነትም ተለይቶ በሽንገላ አለም እንደኖረ ይታወቃል። ይሁን እንጂ የእንደገና አምላክ የሆነው እግዚአብሔር ዳግመኛ በዚሁ እውነት እንመላለስና ለእውነት በሚሆኑ ጽድቅና ቅድስና እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠረውን አዲሱን ሰው እንለብስ ዘንድ እውነት ከሆነው ልጁ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ዳግመኛ ህይወትን ሰጠን።

> “የተሰወረ የጥበብና የእውቀት መዝገብ የሆነው ከመታወቅ ያለፈው የእግዚአብሔር አብ መልክ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የመጨረሻው የእውነት መገለጫና ትክክለኛ ትርጓሜ ነው።”

## የማስተንተኛ ጥያቄዎች

1. እግዚአብሔር ራሱ እውነት ነው ማለት ምን ማለት ነው?
2. የማይለወጠው የእግዚአብሔር እውነት ውሳኔዎችህንና የዕለት ተዕለት ኑሮህን እንዴት ሊመራው ይገባል?
3. በክርስቶስ እውነት መታደስ የሚያስፈልጋቸው የአስተሳሰብህ ክፍሎች የትኞቹ ናቸው?

## አሰላስል

እግዚአብሔር እውነት ነው። እውነታውን እንዳለ የሚገልጥ፣ ሐሰትንና ሽንገላን የማይቀበል ቅዱስ አምላክ ነው። በሐሳቦች ለውጥ፣ በሰው አመለካከትና በማታለያ የተሞላ ዓለም ውስጥ ቃሉ ግን የማይለወጥና የሚታመን ሆኖ ይኖራል። እውነት ራሱ በሆነው በክርስቶስ አማካኝነት እግዚአብሔርን እንድናውቅ፣ በብርሃኑ እንድንመላለስና በእውነቱ እንድንለወጥ ይገባናል። ስለዚህ የማይለወጠውን የእግዚአብሔርን እውነት በመያዝ መኖርና ሕይወታችንን በእርሱ መምራት እንደሚገባን ልናስታውስ ያስፈልገናል።

## ጸሎት

በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፣ ራስህን እንደ እውነት ስለገለጥህልን እናመሰግንሃለን። ከዲያብሎስ ሐሰትና ሽንገላ አድነኝ፤ በእውነትህም ቀድሰኝ። በአዕምሮ መታደስ በእውነትህ እንድመላለስና የክርስቶስን ባሕርይ በሕይወቴ እንዳንጸባርቅ እርዳኝ። ቃልህ የሕይወቴ መመሪያና መሠረት እንዲሆን አስተምረኝ።

በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አሜን።

## የአርምሞ ጥቅስ

*"በእውነትህ ቀድሳቸው፤ ቃልህ እውነት ነው።"*

*— የዮሐንስ ወንጌል 17፥17 —*

## 2.14. እግዚአብሔር ጠቢብ ነው!

ከዚህ በፊት ባለው ክፍል እግዚአብሔር ታላቅ፣ ሃይለኛ፣ ሁሉን ቻይ፣ ሉአላዊ ወዘተ እንደሆነ በስፋት ተገልጿል። እነዚህ ሁሉ የእግዚአብሔር ማንነቶች ጥበብ ከሌለባቸው ያለ አግባብ ጥቅም ላይ የሚውሉ እና ለጥፋት የሚሆኑ ይሆናሉ። ነገር ግን እግዚአብሔር ፍጹም እንከን አልባ የሆነ ሁሉ በሁሉ አምላክ ነውና ኃይሉና ታላቅነቱ፣ ሁሉን ቻይነቱ፣ ሉአላዊነቱ ወዘተ ፍጹም ድንቅ በሆነ ማስተዋልና ሊመረመር የማይችል ጥበብ የታጀቡ ሆነው ለሰው ልጆች ጥቅም እና ለእግዚአብሔር ክብር በፍጥረቱ መካከል ማንነቱን ሲገልጡ ይታያሉ።

ኃይል ያለ ጥበብ እጅግ አደገኛ ነው። ይህም እውነት በእውቀቱና በኃይሉ በብዙ መጠፋፋት ውስጥ ካለው የሰው ልጅ በላይ ማሳያን እንዳንፈልግ የሚያደርገን ነው። ጥበብ ብልሃትን፣ ዘዴኛ የሆነ ማንነትን፣ አስተዋይ የሆነ ልቦናን፣ አዋቂነትን፣ አደራረግ ማወቅን፣ በእውር ድንበር ያለ ማስተዋል አለመራመድን፣ ጠንቃቃነትንና ልዩ የሆነ አስተውሎትን የሚገልጥ ድንቅ ቃል ነው። (ግዛው, 1994) (Merriam-Webster, n.d.) በእጁ ላይ ያለውን የከበረ ነገር በምን አይነት ጥንቃቄና ማስተዋል ለጥቅም ማዋል እንዳለበት የማያውቅ ሰው ለጥፋት ቅርብ የሆነ እጅግ አሳዛኝ ፍጡር ነው። ያን ሁሉ ጥበብ እና ማስተዋል እንኳን ተቀብሎ እጁ ላይ ያለውን ገንዘብ፣ ዝና እና አቅርቦት ሁሉ በተገቢው መንገድ ማስተናገድ ሳይችል ቀርቶ እርጅናው የተበላሸበት ለቀጣይ ትውልድም ዘላቂን ጥፋት ያወረሰው ንጉስ ሰለሞን የዚህ እውነት አይነተኛ ማሳያ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ደጋግሞ የጥበብን አስፈላጊነት ሲያሳስበን ፀጋውን ከጥበብና ከአዕምሮ ጋር አበዛልን፣ ተገቢ የሆነ የአማኝ ህይወትን ለመኖር የልቦና አይኖች መብራት እንዲሁም የጥበብና የመገለጥ መንፈስ አስፈላጊነትን፣ የጥበብ ዋጋ ከቀይ እንቁ እንኳን የበለጠ መሆኑን ወዘተ ገልጾ ይህንኑ ጥበብ እንድንይዝ ቢጎድለንና ባይኖረን ደግሞ ይኖረን ዘንድ ሳይነቅፍ በልግስና የሚሰጠውን የጥበብ ሁሉ ባለቤት እግዚአብሔርን ጠይቀን እንድንቀበል እንጂ ያለ ጥበብ እንዳንኖር ደጋግሞ ይነግረናል።

እግዚአብሔር እጅግ ኃያልና ብርቱ ማስተዋሉም የማይመረመር ታላቅ አምላክ ነው። ታዲያ ይሄው ታላቅነቱ ውብ በሆነ አደራረጉ ሊደረስበት የማይችል እንከን አልባ

ጥበብን በመግለጥ የተከሸነ ማንነት ነው። ከላይ ጥበብን ለማብራራት በተገለጡት አቻ ትርጓሜዎች ውስጥ ለማየት እንደተሞከረው እግዚአብሔር የሚያደርገውን ሁሉ ድንቅ በሆነ ጥበብ በብዙም ማስተዋል በተለየ ዘዴና የአደራረግ ጥበብ የሚያደርግ ስራዎቹም ሁሉ ይህንኑ የሚመሰክሩለት ታላቅ አምላክ ነው።

እግዚአብሔር የትኛውም አይነት የሰው ልጅ እንዲሁም የፍጥረቱ ሁሉ አዕምሮ እንዲሁ በቀላሉ ሊረዳው በማይችል መንገድ ያለ ማስተዋል ያደረገው የመሰለን ነገር ሁሉ ከሰው ልጆች ሁሉ ጥበብ የበለጠ እጅን በአፍ ላይ የሚያስጭን በእግዚአብሔር "ሞኝነት" ብቻ ተመዝኖ የተደረገ ታላቅ ብልሃት የሚታይበት ሆኖ ይታያል። በዚሁ የእግዚአብሔር አደራረግ ውስጥ የሚገለጡ ለሰው አዕምሮ የማይመቹ የእግዚአብሔር ውሳኔዎችና ስራዎች ሁሉ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ካለው ታላቅ ፍቅር የመነጩ፣ መነሻቸው መልካምነቱ የሆነ፣ ለሰው ልጆች ጥቅም የሚደረጉ በጥበብ የሆኑ የእግዚአብሔር ምርጫዎች ናቸው። ለዚህም ጥሩ መግለጫ የሚሆነን በኤርምያስ 29 ላይ ያለው ለእናንተ የማስባትን ሃሳብ እኔ አውቃለሁ ያለበት በኢሳይያስም ሃሳቤ ከሃሳባችሁ ሰማይ ከምድር ከፍ እንደሚል ከፍ ያለ ነው ብሎ ያለባቸው ዘላለማዊ ቃሎቹ ናቸው። የእግዚአብሔር ጥበብ በፍጥረቱ መጀመሪያ፣ በፍጥረት አለም አወቃቀርና አስተዳደሩ ብሎም ድንቅ በሆነ አደራረጉ እንዲሁም በክርስቶስ ኢየሱስ የመስቀል ስራ ይኸውም በማዳኑ እጅግ ጎልቶ የታየ ነው።


ሰማያት፣ ከሰማያት በላይ ያሉ ሰማያት እንዲሁም ጠፈር እና ከዋክብቱ ሁሉ የእግዚአብሔርን ድንቅ ጥበብ ጩኸው የሚናገሩ ምስክሮች ናቸው። ምድርን በውሃ ላይ የመሰረተበት፣ ያለ ምንም ድጋፍ ታላላቅ ፍጥረቱን በስፍራቸው ያቆመበት፣ በእግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠረው ጠቢብ ሰው፣ እስከ ዛሬ ድረስ ስለ ምንነታቸው ብሎም ስለ መኖራቸው ገና ሊደረስባቸው ያልቻለ ከቁጥር እጅግ የበዙ የዚህ ጠቢብ አምላክ እጅ ስራዎች አስደናቂዎች ናቸው።

የሚታየውና የሚሰማው ሁሉ የእግዚአብሔርን ጢቢብነት አድምቆ የሚያሳይ ሲሆን ከምድር በታች በእናቱ ማህፀን የተበጀው አጥንትና አጥንቱ ከጅማቱ ጋር የተዋደደለት ስጋ ለባሹ ሰውም የዚሁ የእግዚአብሔር ጥበብ ዋና ማሳያ ነው። የእግዚአብሔርን ጥበብ የማይናገር በሚታየውና በማይታየው አለም ውስጥ ያለ አንዳች

ፍጡር የለም። ይሄው አስደናቂ የሆነው የእግዚአብሔር ጥበብ ከመደነቅና ከመገረም በቀር ሰው ስለ እግዚአብሔር አደራረግ ፍንጭና አስተያየት እስከማይኖረው ድረስ እጅን በአፍ ላይ የሚያስጭን ብቻ ነው። ከብዙ የሙግት ጥያቄ በኋላ እግዚአብሔር የተገለጠለት ፃድቅ ሰው ኢዮብ በአውሎ ነፋስ ውስጥ ሆኖ ስለ ፍጥረቱ የጠየቀውን እግዚአብሔርን ምንም ሊመልስለት እንዳይችል ያደረገው በፍጥረቱ ውስጥ የተገለጠለት የእግዚአብሔር ጥበብ ነበር።

የሰው ልጅን ከአፈር ልዩ በሆነና ውስብስብ የሰውነት ስርዓት አዋቅሮ ከሌላው የሚለይበትን የግሉ የሆነ የእጅና የአይን አሻራ፣ ዲኤንኤ /DNA/ ወዘተ የሰጠበት ጥበብ፣ ይህንን የሚያከል ሰውን ትናንሽ በሆኑ ህዋሳት ማዋቀሩ፣ በዚህ መልክ የተፈጠረው ሰው የሚራባና ዘሩን የሚተካበት ሂደት፣ በልቶ ምግቡን ወደ አቅምነት የሚለወጥበት የእንሽርሽሪት ስርዓት፣ በግንኙነት መሰሉን የሚወልድበትና የሚባዛበት መንገድ፣ በማህጸን ውስጥ መተንፈስ የሚችል ህጻን በእንግዴ ልጅ እየተመገበ እየተነፈሰ የሚቆይበት ምስጢር፣ በዚህ ቆይታ የተለያዩ የእድገት ደረጃዎችን ማለፍ መቻሉ፣ የሚወለድበት ጊዜ ሲደርስ ለመውጣት መሞከሩ፣ እንደተወለደ የእናቱን ጡት መፈለጉ፣ በዚህ ሁሉ ጊዜ ውስጥ የእናቱ ጡት የተዘጋጀበት መንገድ፣ የእናቱ ጡት ከምትበላው ምግብ የተዘጋጀበት ጥበብ፣ ያገኘው መልክ፣ በተለያዩ የዝግጅትና መተላለፊያ መንገዶች አልፎ ለህጻኑ አፍ በሚመች መልኩ ይጠባ ዘንድ በርካታ አይኖች ያሉት ጫፍ መዘጋጀቱ፣ ይሄው ልጅ የራሱን እድገት አድጎ አጥንቶቹ ጠንክረው የሚጎለምስ ደግሞ አርጅቶ የሚሞት መሆኑ ይህም ሁሉ አስቀድሞ በፈጣሪው በእግዚአብሔር የተወሰነበት መንገድና የተዋቀረበት ጥበብ ከአዕምሮ በላይ ነው።

የተፈጠሩ ፍጥረታት ሁሉ እርስ በእርስ የተጋመዱበት የተፈጥሮ ስርዓት ሌላኛው አስገራሚ የሆነ የእግዚአብሔር ጥበብ ማሳያ ነው። የሰው ልጅ የሚተነፍሰውን አየር ከእጽዋት ማግኘቱ፣ እጽዋት ደግሞ ከሰው ልጆች የሚቀበሉ መሆናቸው፣ በምድር ላይ ያለውን እርጥበት በፀሃይ ብርሃን አማካኝነት በትነት መልኩ ወደ ሰማይ ወስዶ ባልተቀደደ የደመና አቁማዳ ውስጥ አስሮ በወደደ ጊዜ መልሶ በዝናብ መልክ ወደ ምድር የሚያወርድበት መንገድ ይኸውም ለእጽዋት ሁሉ ያለው ጠቀሜታ ፍጥረትም ሁሉ ከዚህ ሂደት ተመጋቢ መሆኑ አስደናቂ የሆነ የእግዚአብሔር ጥበብ ነው።




የመሬት ስበት፣ የፕላኔቶች በራሳቸው ዛቢያና በፀሃያቸው ዙሪያ የመሽከርከር ሂደት፣ ለቁጥር የሚያዳግቱት እነዚህ የሰማይ ሰራዊቶች ከተፈጠሩበት ጊዜ ጀምረው ባልተቋረጠ ይህንን መሰል እንቅስቃሴ ውስጥ ያለ እንከን መቆየታቸው፣ መሬት ከፀሀይ ያላት ርቀት ይህም በመሬት ላይ ለምንገኝ ሁሉ ያለው የጸሃይ ጨረር ምጣኔ ወዘተ በአጠቃላይ የፍጥረት ስርአት ውስጥ አስደናቂ የሆነ የእግዚአብሔር ጥበብ ተገልጦ ይታያል።

በምርምሩ ዘርፍ የሚገኙ ሳይንቲስቶች /የሂሳብና የፊዚክስ ሊቃውንት/ በብዙ ምርምር ውስጥ አልፈው ከአመታት በኋላ በፍጥረት አለም ውስጥ የሚገኙ የፍጥረታቱን ዑደትና ደህንነት የሚቆጣጠሩ እንደ የመሬት ስበት /ግራቪቲ/ ያሉ የማይለዋወጡ ትናንሽ ቁጥሮችን /Constants/ ባገኙ ጊዜ ብሎም የቀረውን የዚህን ትልቅ አለም ምስጢር ለመረዳት ገና ብዙ ትውልድን የሚፈልግና ሊደረስበትም የማይችል እንደሆነ ባወቁ ጊዜ ከዚህ ሁሉ ፍጥረት ጀርባ ያለው ኃይል እጅግ ሊቅና ጠቢብ /Genius/ ነው ብለው ይናገራሉ።

እግዚአብሔር ይህንን ሁሉ ፍጥረቱን የሚመግብበትና አቅርቦቱን የሚያደርስበት መንገድ ሌላኛው አስደናቂ ጥበብ ነው። ይህም አቅርቦት በመዝሙረ ዳዊት ምዕራፍ 104፡24 ላይ እንደተገለፀው *“አቤቱ ስራህ እጅግ ብዙ ነው ሁሉን በጥበብ አደረግህ”* የሚያስብል አስናቂ የእግዚአብሔር ጥበብ የሚታይበት ነው። ምድርን በመሰረቷ ላይ

መስርቶ እንደ ልብስ በጥልቅ መከደኑ፣ ውሆችንም ሁሉ በተራሮች ላይ ከፍ አድርጎ በደመና ውስጥ አስሮ ማቆሙ፣ በዘለፋው ብቻ እንዲሸሹ አድርጎ በነጎድጓዱ በማስደንገጥ በተራሮች መካከል እንዲፈሱ በማድረግ እንዲሄዱ ወዳዘጋጀላቸው ስፍራ ይኸውም ወደ ቆላው በዚያ ያሉ አራዊቱንና እጽዋቱን ሁሉ ለማጠጣት ማውረዱ፣ በዚህም ሂደታቸው ከልካቸው አልፈው እንዳይሄዱ ለወንዞቹ ድንበርን ማበጀቱ እጅግ አስገራሚ ጥበብ ነው።

ለሚናወጠው የባህር ሞገድ ለሚመለከተው ሁሉ በጩኸቱና በብርታቱ ያገኘውን ሁሉ የሚያጠፋ ለሚመስለው ማጓራቱ ከልኩ እንዳያልፍና ጥፋትን እንዳያስከትል ለባህር ዳርቻን አድርጎ በዘላለም ትዕዛዝ አሸዋን ልኩ አድርጎ ያስቆመው ዘንድ በዙሪያው ማጠሩ እግዚአብሔር እንዴት አይነት ጥበበኛ አምላክ እንደሆነ የሚያሳይ ነው። ውሆችን በተራሮች መካከል አሳልፎ ምንጮችን ወደ ቆላዎች በመላክ የዱር አራዊትን ሁሉ ማጠጣቱ የበረሃ አህያዎችም ሁሉ ጥማት ከዚህ ፍሰት መርካቱ እግዚአብሔር መሳይ የሌለው ጠቢብ እንደሆነ ይመሰክራሉ። እንጀራን ከምድር አውጥቶ ለምለሙን ለሰው ልጆች ጥቅም ሳሩን ደግሞ ለእንስሶች ምግብ ይሆን ዘንድ ያበቅላል። እርሱ ራሱ የተከላቸው የሊባኖስ ዝግባዎች ከተራራው ጫፍ በወረደላቸው ውሃ ይጠግባሉ፣ በእነርሱም ላይ ወፎች ማደርያቸውን አድርገው ይዋለዳሉ፣ ረጅም ተራራዎችን ለዋላዎች አድርጓል እሽኮኮዎችም በድንጋዮች መካከል ይሸሻሉ።

ጨረቃን ለጊዜዎች አድርጓል፣ ፀሃይም መግቢያውን ያውቃል በዚህም ዑደት ጨለማን ያደርጋል ሌሊት ይሆናል በእርሱም የዱር አራዊት ሁሉ ይወጡበታል ወደ ማደሪያቸው ይሰበሰባሉ በየዋሻቸውም ይተኛሉ የቀኑ ተረኛም የሰው ልጅ እስኪመሽ ድረስ ስራውን ለመስራት ወደ ተግባሩ ይወጣል። ታላቅና ሰፊ በሆነው ባህር ውስጥ ስፍር ቁጥር የሌላቸው በአይነትና በዝርያ የሚለያዩ ታላላቆችና ታናናሾች እንስሶች ይኖራሉ። በዚያም ላይ እጅግ ግዙፍ የሆኑ መርከቦች ያለ ስጋት ይሄዱበታል። እነዚህ ሁሉ ምግባቸውን በየጊዜው ይሰጣቸው ዘንድ እግዚአብሔርን ተስፋ ያደርጋሉ፣ በሰጣቸውም ጊዜ ይሰበሰባሉ፣ እጁንም ከፍቶ ከመልካም ነገር ያጠግባቸዋል፤ ፊቱን በሰወረ ጊዜ ይደነግጣሉ፣ ነፍሳቸውን ያወጣል ይሞታሉም ወደ ስፍራቸውም ይመለሳሉ፣ መንፈሱንም ልኮ እንደገና እንዲፈጠሩ ያደርግና የምድርን ፊት ያድሳል። እግዚአብሔር እንዴት ጠቢብ የሆነ ማስተዋሉም የበዛ ድንቅ አምላክ ነው።

"አቤቱ ስራህ እጅግ ብዙ ነው፤ ሁሉን በጥበብ አደረግህ።" -- መዝሙረ ዳዊት 104፡24

ከዚህ ሁሉ በላይ የሆነ ድንቅ ጥበብን እግዚአብሔር የሰውን ልጆች ሁሉ ባዳነበት ታላቅ ማዳኑ ወቅት ገልጧል። ይህም ጥበብ በዚህ አለም ገዦች በአንዱም እንኳን ያልታወቀ ድንቅ የእግዚአብሔር አደራረግ ሲሆን መጽሐፍ ቅዱስ በ2ኛ ቆሮንቶስ 2፡8 ላይ እንደሚናገረው ይሄው አለማወቃቸው የክብርን ጌታ እንዲሰቅሉት እንዳደረጋቸው ያሳያል። ይህም አለማወቅ በምድር ላይ የሚገኙ የሰው ልጆች ብቻ ሳይሆን ከጀርባ ሆኖ ፈቃዱን የሚፈጽምባቸው አለቃ መንፈስ ይኸውም ሰይጣን ጭምር ያልተረዳውና ያላወቀው እግዚአብሔር አለምን ሁሉ ያዳነበት ድንቅ ጥበብ ነው። ይህ የእግዚአብሔር ጥበብ ዛሬም ድረስ ለበርካቶች ያልተገለጠ የዘላለም ምስጢር ሲሆን ከሰው ልጆች ሁሉ የተጠራቀመ ጥበብ በሚበልጥ የእግዚአብሔር ሞኝነት የተከናወነ ታላቅ የማዳን ስራ ነው።

እግዚአብሔር ከሰጠው ከፍታ በሀጢአቱ ምክንያት የወደቀውን የሰው ልጅ ለማዳን ሁሉን አዋቂ የሆነው ጌታ ሰው እንደሚወድቅ ቀድሞውኑ ያወቅ ነበርና ማዳኑንም ደግሞ ቀድሞ አዘጋጅቶ ነበር። በዚህም ውድቀት ወቅት የማይታረቅ ጠላትነትን በሴቲቱና በዘሯ እንዲሁም በእባቡና በዘሩ መካከል ያደረገው እግዚአብሔር ከዚችው ሴት በራሱ አደራረግ በነገር ሁሉ ወንድሞቹን የመሰለ የእባቡን ራስ የሚቀጠቅጥ ልዩ ዘርን በጊዜው ወደ ምድር አመጣ። ከሰው ስርዓት ውጭ የራሱን ዘር በድንግሊቱ ውስጥ አድርጎ ፈጽሞ ሀጢአት የማያውቀውን የራሱን ቃል ስጋ አድርጎ ለዚሁ ታላቅ የማዳን ስራ ወደ ምድር አመጣው።

ተታልሎ ስልጣኑን ለዲያብሎስ የሰጠው ፊተኛው አዳም የጣለውን ስልጣኑን መልሶ ይወስድ ዘንድ በነገር ሁሉ ተፈትኖ ያለፈ እንከን አልባ የሆነ ሁለተኛ አዳምን ከዘሩ ውስጥ አገኘ። በዚህ መልክ ጽድቅን ሁሉ ፈጽሞ ያለ አንዳች እንከን የስጋ ወራቱን ጨርሶ በተጓደለ ፍትህ ወደ መስቀል ተወሰደ። ወደ ምድር የመጣበትን ዋናውን ጉዳዩን ይኸውም የዲያብሎስን ስራ ማፍረስን ሀጢአትን በመስቀል

> "ለተጠሩት ግን አይሁድ ወይም አህዛብም ቢሆኑ የእግዚአብሔር ኃይልና የእግዚአብሔር ጥበብ የሆነው ክርስቶስ ነው። ከሰው ጥበብ ይልቅ የእግዚአብሔር

ላይ በመግደል ስልጣንን ካልተገባው አካል በመቀማት ከእርሱ ጋር የሰው ልጆች ሁሉ ህይወትን ያገኙ ዘንድ በደላቸውን ሁሉ ይቅር ብሎ ይቃወማቸው የነበረውንም በትዕዛዛት የተጻፈውን የዕዳ ጽህፈት ደምስሶ ስራውን ፈጸመ። ይህ ታላቅ የእግዚአብሔር ጥበብ ከሰው ልጅ ፍጥረት ጀምሮ እስከ ምድር ፍፃሜ ድረስ የሚገኙ የሰው ልጆች ሁሉ ሊፈጽሙት የሚችሉትን ሁሉ ሀጢአት የደመሰሰ ታላቅ የማዳን ስራ ነው። በዚህ መንገድ ያመኑና የዳኑትን ሁሉ ከራሱ ጋር ህይወት ሰጥቶ ከእርሱ ጋር ማንም ሊደርስበት በማይችል ሰማያዊ ስፍራ የሰወረበት ጥበብ ከአዕምሮ በላይ የሆነ አስደናቂ የእግዚአብሔር አደራረግ ነው።

ይሄው የመስቀሉ ቃል ታዲያ ዛሬም ድረስ ለሚጠፉት ሞኝነት ሲሆን ለእኛ ለምንድን ደግሞ በአስደናቂ ጥበብ እግዚአብሔር አለምን ሁሉ ያዳነበት የእግዚአብሔር ኃይል ነው። በዚሁ መንገድ እግዚአብሔር የአለምን ሁሉ ጥበብ ሞኝነት ያደረገ ሲሆን አለም ዛሬም ድረስ በራስዋ ጥበብ እግዚአብሔርን ማወቅ ስላልቻለች በስብከት ሞኝነት የሚያምኑትን ሊያድን የእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ ሆኗል።

የተሰቀለው ክርስቶስ ዛሬም ድረስ ለአይሁድ ማሰናከያ ሲሆን ለግሪክ ሰውና ለቀረው አህዛብም ሞኝነት ነው። ለተጠሩት ግን አይሁድ ወይም አህዛብም ቢሆኑ የእግዚአብሔር ኃይልና የእግዚአብሔር ጥበብ የሆነው ክርስቶስ ነው። ከሰው ጥበብ ይልቅ የእግዚአብሔር ሞኝነት ይጠበባልና።

“ውሆችን በተራሮች መካከል አሳልፎ ምንጮችን ወደ ቆላዎች በመላክ የዱር አራዊትን ሁሉ ማጠጣቱ የበረሃ አህያዎችም ሁሉ ጥማት ከዚህ ፍሰት መርካቱ እግዚአብሔር መሳይ የሌለው ጠቢብ እንደሆነ ይመሰክራሉ። እንጀራን ከምድር አውጥቶ ለምለሙን ለሰው ልጆች ጥቅም ሳሩን ደግሞ ለእንሶሶች ምግብ ይሆን ዘንድ ያበቅላል። እርሱ ራሱ የተከላቸው የሊባኖስ ዝግባዎች ከተራራው ጫፍ በወረደላቸው ውሃ ይጠግባሉ፣ በእነርሱም ላይ ወፎች ማደርያቸውን አድርገው ይዋለዳሉ፣ ረጅም ተራራዎችን ለዋላዎች አድርጓል እሽኮኮዎችም በድንጋዮች መካከል ይሸሻሉ። ጨረቃን ለጊዜዎች አድርጓል፣ ፀሃይም መግቢያውን ያውቃል በዚህም ዑደት ጨለማን ያደርጋል ሌሊት ይሆናል በእርሱም የዱር አራዊት ሁሉ ይወጡበታል ወደ ማደሪያቸው ይሰበሰባሉ በየዋሻቸውም ይተኛሉ የቀኑ ተረኛም የሰው ልጅ እስኪመሽ ድረስ ስራውን ለመስራት ወደ ተግባሩ ይወጣል። ታላቅና ሰፊ በሆነው ባህር ውስጥ ስፍር ቁጥር የሌላቸው በአይነትና በዝርያ የሚለያዩ ታላላቆችና ታናናሾች እንስሶች ይኖራሉ። በዚያም ላይ እጅግ ግዙፍ የሆኑ መርከቦች ያለ ስጋት ይሄዱበታል።

## የማስተንተኛ ጥያቄዎች

1. ፍጥረት ስለ እግዚአብሔር ጥበብ ምን ያሳያል?
2. የእግዚአብሔርን ጥበብ ማወቅህ በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ላይ ያለህን ምላሽ እንዴት ሊለውጠው ይገባል?
3. በየትኛው የሕይወትህ ክፍል ከራስህ ማስተዋል ይልቅ በእግዚአብሔር ጥበብ መታመን ያስፈልግሃል?

## አሰላስል

እግዚአብሔር እጅግ ጥበበኛ ነው። የእጁ ሥራ ሁሉ ፍጹም ማስተዋልና የተሟላ ዓላማ እንዳለው ይገልጣል። ምንም እንኳን መንገዶቹ ከሰው አስተሳሰብ በላይ ሊሆኑ ቢችሉም፣ ሁሉን ነገር በበጎነቱና በዘላለማዊ ዕቅዱ መሠረት እየመራ እንደሆነ ልንታመን እንችላለን። የእግዚአብሔር ጥበብ ከሰው ግንዛቤ የሚያልፍ ስለሆነ፣ ሕይወታችንን በራሳችን ማስተዋል ላይ ሳይሆን በእርሱ ፍጹም ጥበብ ላይ ማስቀመጥ ይገባናል። ስለዚህ የማንረዳቸው ሁኔታዎች ቢኖሩም፣ የጥበበኛው አምላክ መንገድ ሁልጊዜ መልካምና ትክክል እንደሆነ በመታመን መመላለስ እንደሚገባን ሁልጊዜ ልናስታውስ ይገባናል።

## ጸሎት

በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፣ ከሰው ግንዛቤ በላይ የሆነውን ፍጹም ጥበብህን ስለገለጥህልን እናመሰግንሃለን። መንገዶችህን በማልረዳበት ጊዜ እንኳን በአንተ ጥበብ እንድታመን እርዳኝ። ሐሳቦቼንና ውሳኔዎቼን በጥበብህ ምራ፤ ወደ ክርስቶስም ይበልጥ እንድቀርብ እርዳኝ። ከራሴ ማስተዋል ይልቅ በቃልህና በፈቃድህ እንድመላለስ ጸጋህን አብዛልኝ።

በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አሜን።

## የአርምሞ ጥቅስ

*"ከሰው ይልቅ የእግዚአብሔር ሞኝነት ይጠበባልና፥ የእግዚአብሔርም ድካም ከሰው ይልቅ ይበረታልና።"*

*– 1ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 1፥25 –*

## 2.15. እግዚአብሔር ትጉና ታታሪ ሰራተኛ ነው!

ሁሉን የምትገዛ መንግስት ባለቤት የሆነው ዙፋኑንና አዳራሹን በሰማይ የሰራና ያዘጋጀ መሰረቱንም በምድር ላይ የመሰረተ የባህርንም ውሃ ጠርቶ በምድር ፊት ላይ የሚያፈስሰው ያለ መታከት ሁልጊዜ በስራ የሚተጋው እርሱ እግዚአብሔር ነው። የዚህ ጌታ ትጋትና ሰራተኛነት በፍጥረት አፈጣጠር ውስጥ ቁልጭ ብሎ የሚታይ ሲሆን ይህንንም ለመረዳት ከዘፍጥረት መጽሐፍ ባለፈ የኢዮብን መጽሐፍ ከምዕራፍ 38 ጀምሮ ማንበብ የበለጠ የእግዚአብሔርን ትጋት ያሳያል። በዚሁ የስድስት ቀናት ያልተቋረጠ የፍጥረት ሂደት ውስጥ እግዚአብሔር ብቻውን ሁሉን እንደ ፈቃዱ ምክር በትጋት ውብ አድርጎ ሰራ። ይህንን ሁሉ ሲያደርግ ታዲያ የሚያግዘው አንዳች በሌለበት ሁኔታ ብቻውን ያደረገው ነበር። በዚህ መሰረት ይህንኑ በልቡ ውስጥ ያለውን ያለ እረፍት ሊያደርገው የጀመረውን መልካም ስራ ለመስራት እስከ ዛሬ ድረስ ቀጥሎ ሳያርፍ እየከናወነ ይገኛል። ከፍጥረት በኋላ በተከሰቱ የውድቀት ሂደቶች ምክንያት ቀድሞውኑ በልቡ ያለችውን ዘላለማዊ የሆነች እንከን አልባ ሁሉን ገዥ መንግስቱን በሰው ልጆች መካከል ለመስራት ያለ መታከት ዛሬም በትጋት እየሰራ ይገኛል።

ይህችን ሁሉን ገዥ መንግስቱን ለመመስረት አዳራሹን ሰርቶ ዙፋኑም ላይ ነግሶ ከሚገኝበት ከፍታው ሆኖ በሁሉን አዋቂነቱ፣ ሁሉን ቻይነቱ ብሎም በሉአላዊ ስልጣኑና በታላቅነቱ ወዘተ የፈቃዱን ምክር ለመስራት ዛሬም እየተጋ አለ። ለመንግስቱ ተቃራኒ የሆነውን የሰውን ልጆች ሁሉ ያሳተውን የዚህ አለም ገዥ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ደግሞ እንቅፋት ወደማይሆንበት፣ ፍትህ ፍጹም ወደሚሆንበት፣ ፍርድም ወደሚከናወንበት የተዘጋጀለት የእሳት ባህር እስኪገባ በዚህም ምክንያት ጽድቅና ቅድስና ለዘላለም ገዥ እስኪሆኑ ድረስ እግዚአብሔር አያርፍም።

የዚህ ጥፋት ተባባሪ የሆነው የሰው ልጅ የተዘረጋውን የእግዚአብሔር የምህረት እጅ ተቀብሎ ከዚህ የዘላለም ጥፋት ያመልጥ ዘንድ እግዚአብሔር ይህንን አለም ከማጥፋት ታግሶ ይገኛል። እርሱ የሀጢአተኛውን ሞት አይወድምና ሁሉ ወደ ንስሃ ይደርሱና ከሀጢአታቸው ተመልሰው በህይወት ይኖሩለት ዘንድ እግዚአብሔር ባልተቋረጠ ትጋት ዛሬም የእርሱ በሆኑ ልጆቹ በኩል ሰውን ሁሉ ወደ እርሱ ሊመልስ እየተጋ ይገኛል። ሁሉ እንዲድን እንጂ አንዱም እንኳን እንዳትጠፋበት ወዶ ዛሬም

በዮሐንስ 10፡16 ላይ ከዚህ በረት ያልሆኑ ሌሎች በጎች አሉኝ እነርሱም ደግሞ ድምጼን ሰምተው ይመጡና የመንጋው አካል ይሆኑ ዘንድ ላመጣ ይገባኛል ብሏል። ስለ እነርሱ አመጽ ለጥፋቱ የሚሆን እልባትን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ሰጥቶ ፍትህን ለማስፈንና የጽድቅ መንግስቱን በሙላት ለመግለጥ እስከዛሬ ይተጋል። እግዚአብሔር ይህንን ስራውን ባልተቋረጠ ትጋት እለት እለት በየሰከንዱ በየስፍራው በሚታይና በማይታይ መልኩ እየሰራ ይገኛል። የዚህም መጨረሻው የልጁ ዳግም ምፃትና ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚከናወነው የጽድቅ ፍርድ ነው።

ወንጌልን ሳይሰማ 70,000 ገደማ ሰው በአለም ዙሪያ በየቀኑ እንደሚሞት የተለያዩ መረጃዎች ያሳያሉ። (Baxter, 2007) የሰው ልጆች ሁሉ መዳን እግዚአብሔር አብ አንድያ ልጁን የላከበት ዋነኛ ጉዳዩ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በማቴዎስ 24 ላይ እንደሚነግረን ይህ የመንግስቱ ወንጌል ለአለም ሁሉ እስኪሰበክና የምድር ጥፋት ጽዋ እስኪሞላ ድረስ ፍፃሜው እንደሚዘገይ ይታያል። በዚህ የእግዚአብሔር ዋና ጉዳይ የሆነ ስራ ውስጥ በልባቸው ብርሃን በርቶ የእግዚአብሔር ልጆች የሆኑ ሁሉ ከእርሱ ጋር አብረው እንዲተጉ የተጠሩ ሰራተኞች ሲሆኑ ይህም በግልጽ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ዕርገት ወቅት በቀጥታ ትዕዛዝ የተላለፈ አደራ ነው።

የስራው ሁሉ ባለቤት ራሱ እግዚአብሔር ሲሆን በምድር ላይ በስጋ የሚገኙ የእርሱ ህዝብ የሆኑ ሁሉ ግን ይህን ሸክም እግዚአብሔር ነገሩን ዋና ጉዳይ አድርጎ በያዘበት ልክ ጉዳያቸው አድርገው ሲኖሩበት አይታዩም። እግዚአብሔር የሰው ልጆችን ሁሉ ለማዳን እና አለምን ወደ ፍፃሜው ለመውሰድ በዚህም አሮጌውን አሳልፎ ሁሉን አዲስ ለማድረግ ብዙና ሰፊ በሆነው መከር ውስጥ ሰራተኛና ገንዘብ የሚሆኑ አብረውት የሚተጉ፣ ሰውን መላክ ፈልጎ ከሰማይ አይኖቹ ወደ ምድር ሲመለከቱ አይኑ የሚያርፍባቸው እኔን ላከኝ የሚሉ ነፍሳቸውን ያፈሰሱ ትጉ ሰራተኞችን ይፈልጋል።

*“አባቴ እስከ ዛሬ ይሰራል እኔም ደግሞ እሰራለሁ”* ብሎ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐንስ ወንጌል 5፡17 ላይ እንደተናገረ እርሱ ደግሞ አባቱ በሚሰራበት ትጋትና ሸክም ልክ እየተጋ የሚገኝበትን ጉዳይ ገልጦልናል። ለሰው ልጆች ሁሉ ህይወታቸው የጀመረበት ቀን

*“የሰው ልጆች ሁሉ መዳን እግዚአብሔር አብ አንድያ ልጁን የላከበት ዋነኛ ጉዳዩ ነው።”*

እንዳላቸው ሁሉ በእግዚአብሔር ዘንድ የታወቀ ፍፃሜን የሚያገኙበት የተቆረጠ ቀን ደግሞ አላቸው። በዚህ መካከል ባላቸው የምድር ላይ ቆይታ ታዲያ ፈጽሞ ነጻ የሆነ ያለ ስራ ሊያልፍ የተገባው ትርፍ የሚባል ጊዜ የሌላቸው ሲሆን እግዚአብሔር እነርሱን በፈጠረበት ወቅት በምድር ላይ እንዲያከናወኑት የሰጣቸውን የእርሱን ፈቃድ በማወቅ ያለ አንዳች ስንፍና በዘመናቸው ተግተው የተሰጣቸውን ስራ እንዲሰሩ ይጠበቅባቸዋል። ይህም ዳዊት በገዛ ዘመኑ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ፈጽሞ እንቀላፋ እንደተባለው ሲሆን ይህም ያለ እረፍት የሰው ልጆችን ሁሉ ለማዳን እና አመጽን ፈጽሞ ለማጥፋት ተግቶ እየሰራ ከሚገኘው እግዚአብሔር ጋር በመስማማት የሚሰራ የዘላለም መንግስታዊ አጀንዳ ነው።

*“ቀን ሳለ የላከኝን ፈቃድ ላደርግ ይገባኛል”* ብሎ ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐንስ ወንጌል 9፡4 ላይ እንደተናገረ ለሁላችንም ዛሬም እንዲሁ ነው። ማንም ሊሰራ የማይችልባት ሰዓት ለሰው ሁሉ ያለው ሲሆን ይህም የበዛ ክፋትን ይዞ በየነገው ከሚመጣው ቀን ጋር የተገናኘ ነው። ይሁን እንጂ በዚህ ሁሉ ውስጥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐንስ ወንጌል 17 ላይ ላደርገው የሰጠኸኝን ስራ ፈጽሜ አከበርሁህ ብሎ እንዳለ ለእኛ ለሁላችንም በእግዚአብሔር ትጋት ልክ ልናደርገው የተፈጠርንበትን የእግዚአብሔር ፈቃድ በማወቅና በመረዳት በትጋት ልንሮጥ ያስፈልገናል።

ይህ የእግዚአብሔር ስራ ለሰው ሁሉ እንደየ ስጦታው መጠን የተሰጠ ሲሆን ተደምሮ ፈቃዱን በሙላት የሚገልጥ እርስ በእርሱ የተጋጠመ የአካል ስራ ነው። በዚህ ስራ የሚገኙና የሚሳተፉ ሁሉ ታዲያ በእግዚአብሔር ልብ ነገሩ በከበደበት ልክ አክብደው ሊይዙትና ሊረዱት እርሱንም ለመፈጸም ሊተጉለት የሚገባ የእግዚአብሔር የዕለት ከዕለት ዋና አጀንዳ ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐንስ ወንጌል 4፡34 ላይ *“የእኔስ መብል የላከኝን ፈቃድ አደርግ ዘንድ ስራውንም እፈጽም ዘንድ ነው”* ብሎ እንዳለ ስራውን በትጋት ማድረግ ያስፈልገናል።

አብረነው ሰራተኞች እንድንሆን እድልን የሰጠን እግዚአብሔር ለነገር ሁሉ ፍፃሜውን ሰጥቶ ሁሉን የእግሩ መረገጫ ያደርግ ዘንድ ራዕዩ የሚቸኩል ሲሆን ይህንንም መጽሐፍ ቅዱስ በኢሳይያስ 43፡13 ላይ እንደሚናገረው ከጥንት ጀምሮ እርሱ የሆነው ኤልሻዳይ አምላክ ያለ ማንም ከልካይ በሉአላዊ ስልጣኑ በልቡ ያለውን የሚያከናውንበት እውነት ነው። እንደ ፈቃዱ ምክር ሁሉን የሚሰራው ይህ ትጉ ሰራተኛ የሆነ አምላክ ቀድሞውኑ በክርስቶስ ለማድረግ እንደወሰነ ይህንንም ዘላለማዊ ፈቃዱን አብረነው እንተጋና ሰራተኞች እንሆን ዘንድ እንዳስታወቀን በሰማይና በምድር ያለውን ሁሉ በልጁ ለመጠቅለል ዛሬም ይተጋል።

ለዚህ ስራ እኛን ሁላችንን የጠራው ይህ ጌታ ለዚሁ ስራው መከናወን እና ለእኛ ደህንነት እስከ አለም ፍፃሜ ድረስ ከእኛ ጋር እንደሚሆን በማይለወጥ ቃሉ ያስታወቀን ሲሆን ይሄንንም የርስቱ መያዣ በሆነ መንፈሱ ማህተም ከዚህም ጋር ለእያንዳንዳችን ለስራው ይሆን ዘንድ ከጥበብና ከአዕምሮ ጋር በተሰጡን የፀጋ ስጦታዎች ያስረገጠልን ቁምነገሩ ነው። በዚህ መሰረት እግዚአብሔር ትጉና ሰራተኛ የሆነ ብቻውን ሁሉን ማድረግ የሚችል የወደደውን ለማድረግ የማንንም እርዳታ የማይፈልግ ታላቅ አምላክ እንደሆነ አውቀን አብረን ሰራተኞች እንድንሆን፣ በሰጠን እድል በተሰጠንም ጊዜ በታማኝነትና በትጋት ከእርሱ ጋር አብረን ልንሮጥ ያስፈልገናል። ይህም በስተመጨረሻ ሽልማትን የሚያሰጠን ሲሆን ከዚህ በፊት ያለፉ በመንግስቱ ስራ የተጉ እንደ ጳውሎስ ያሉ ሰራተኞች በብዙ መከራ ውስጥ ሲያልፉ የሚያሳስባቸው ነገር የአብያተ ክርስቲያናት ጉዳይ እንደነበር እንዲሁ የእግዚአብሔር የልብ ሃሳብ ዋና ጉዳያችን የሆነልን አብረን የምንተጋ ልንሆን ያስፈልገናል።

ከትናንት ይልቅ ዛሬ ላይ መዳናችን ወደ እኛ የቀረበ ሲሆን ጌታችን በተገለጠ ጊዜ አንተ በጎ ታማኝ ባሪያ ወደ ጌታህ ደስታ ግባ እንባል ዘንድ ዛሬ ለእግዚአብሔር መንግስት ስራ በተሰጠን ፀጋ ልክ ልንተጋና አብረን ልንሰራ ያስፈልገናል። ይህም ጳውሎስ እንዳለ “ህይወት ክርስቶስ፣ ሞት ደግሞ ጥቅም” የሆነበት አይነት ብድራትን ትኩር ብሎ ያየ ሰው ጨክኖ የሚሰራው አይነት ስራ ይሆንልን ዘንድ ይገባዋል።

“እግዚአብሔር ትጉና ሰራተኛ የሆነ ብቻውን ሁሉን ማድረግ የሚችል የወደደውን ለማድረግ የማንንም እርዳታ የማይፈልግ ታላቅ አምላክ እንደሆነ አውቀን አብረን ሰራተኞች እንድንሆን፣ በሰጠን እድል በተሰጠንም ጊዜ በታማኝነትና በትጋት ከእርሱ ጋር አብረን ልንሮጥ ያስፈልገናል።”

## የማስተንተኛ ጥያቄዎች

1. እግዚአብሔር በፍጥረትና በድነት ሥራው ያሳየው ያልተቋረጠ ትጋት ስለ ታታሪነቱ ምን ያስተምርሃል?
2. የእግዚአብሔር ትጋት ለአንተ በአደራ የተሰጠውን ሥራ ለመፈጸም ያለህን አመለካከት እንዴት ይፈትነዋል?
3. ዛሬ እግዚአብሔር በመንግሥቱ ውስጥ በየትኛው የአገልግሎት ዘርፍ ይበልጥ በታማኝነት እንድታገለግል እየጠራህ ነው?

## አሰላስል

እግዚአብሔር በሥራው የማይታክት አምላክ ነው። ከፍጥረት ጀምሮ እስከ የድነት ሥራ ድረስ የጀመረውን ሁሉ በፍጹም ጥበቡና በፈቃዱ ይፈጽማል። እርሱ አይደክምም፣ አይታክትምም። እኛም እንደ ልጆቹ ለሰጠን አገልግሎት በትጋት፣ በታማኝነትና በሙሉ ልብ እንድንሰጥ ተጠርተናል። ለጌታ የምናደርገው ሥራ ከንቱ እንዳልሆነ እያወቅን፣ እርሱ እስኪጠራን ድረስ በታማኝነት ልንሠራ ይገባናል። ስለዚህ የማይታክተውን አምላክ በመከተል በሰጠን ሥራ ሳንሰለች በታማኝነት መጽናት እንደሚገባን ሁልጊዜ ማስታወስ ያስፈልገናል።

## ጸሎት

በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፣ ፍጹም ፈቃድህን ለመፈጸም ፈጽሞ የማትታክት አምላክ ስለሆንህ እናመሰግንሃለን። ለእኔ በአደራ የሰጠኸኝን ሥራ እንዳውቅና በትጋት፣ በታማኝነትና በጽናት እንዳገለግልህ እርዳኝ። በመንፈስህ አበርታኝ፤ ሩጫዬን እስክጨርስ ድረስ ለመንግሥትህ በታማኝነት እንድሠራና በሕይወቴ ሁሉ ክርስቶስን እንዳከብር ጸጋህን ስጠኝ።

በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አሜን።

## የአርምሞ ጥቅስ

*"ቀን ሳለ የላከኝን ሥራ ላደርግ ይገባኛል፤ ማንም ሊሠራ የማይችልባት ሌሊት ትመጣለች።"*

*– የዮሐንስ ወንጌል 9፥4 –*

## 2.16. እግዚአብሔር ብርሃን ነው!

ብርሃን በዙሪያችን የሚገኙ በእውነታው አለም ያሉ ነገሮችን ሁሉ ማየት እንችል ዘንድ የሚያደርገን ወሳኝ ነገር ነው። የሰው ልጅ አይን ብርሃን በሌለበት ሁኔታ ምንም እንኳን ፍጹም ጤነኛና ማየት የሚችል ቢሆንም እንኳን ዙሪያውን ማየትና መረዳት አይችልም። አንድን በዙሪያችን ያለ ነገር ማየትና ምንነቱን መረዳት የምንችለው በቂ ብርሃን በዚያ በምናየው ነገር ላይ አርፎ ያ ነገር ያረፈበትን ብርሃን ወደ እኛ አይን በሚያንፀባርቅበት ጊዜ ነው። በዚህ መልኩ ያ የምናየው ነገር በእውነት ምን እንደሆነ አጥርተን ማወቅ እንችል ዘንድ በቂ የሆነ ብርሃንን ማግኘት አለበት። (OpenStax, 2016)

አንድ ሰው ፍጹም ድቅድቅ በሆነ ጨለማ ውስጥ መሆኑ እና በዙሪያው ምንም አይነት ነገር ማየት አለመቻሉ በአካባቢው ምንም እቃ በእርግጥ ስለሌለ ሳይሆን ዙሪያውን በበቂ ሁኔታ ማየትና መረዳት በዚህም እውነታውን መገንዘብ ይችል ዘንድ የሚያስችል በቂ ብርሃን ማግኘት ባለመቻሉ ብቻ ነው። ልክ እንዲሁ አንድን ምንም አይነት ብርሃን የማያንፀባርቅና በላዩ ላይ ያረፈን ብርሃን ሁሉ የሚውጥ ጥቁረት ያለው ምንም አይነት እቃ በሌላ ተመሳሳይ ፍጹም ጥቁር የተቀባ አካባቢ ውስጥ ብናስቀምጠው እቃውን ከተቀመጠበት ከባቢ ለይተን ማየት የማንችል ሲሆን ከዚህ በተለየ ሁኔታ ይሄው ፍጹም ጥቁር የተቀባ እቃ በሌላ እቃው ይታይ ዘንድ የሚያስችል ከባቢ ውስጥ እንኳን ቢቀመጥ የእቃውን ከቅርጽ ያለፈ ትክክለኛ ምንነት ለይተን ማየት አንችልም። ስለዚህ ብርሃን እውነታ ነው፣ ዙሪያን ማወቂያና መመልከቻ መስኮት ነው፣ ልዩ የሆነ እይታ ነው፣ እውቀት ነው፣ መለኮታዊ መገለጥ ነው ማለት ነው። (OpenStax, 2016)

> “ብርሃን እውነታ ነው፣ ዙሪያን ማወቂያና መመልከቻ መስኮት ነው፣ ልዩ የሆነ እይታ፣ እውቀትና መለኮታዊ መገለጥ ነው።”

የቀኑ ክፍል መሽቶ ጨለማ በሆነበት ወቅት በዝተውና ደምቀው የሚታዩን እልፍ ቁጥር ያላቸው ከዋክብት ከእነርሱ ነፀብራቅ የበለጠ ብርሃን በቀኑ የብርሃን ጊዜ ስለሚውጣቸው ምንም እንኳን ስፍራቸውን ያልለቀቁ እና በዚያው የሚገኙ ቢሆንም ከእኛ እይታ ግን ለጊዜው

ይሰወራሉ። ስለዚህ ብርሃን የእይታና የአንድ ነገር እውነታ መግለጫ መሳሪያ ነው ማለት ነው።

እግዚአብሔር በስጋ አይን የማይታይ መንፈስ የሆነ አምላክ ሲሆን በተፈጥሮአዊው የስጋ አይኖች እናየው ዘንድ ፈጽሞ አንችልም። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ በመዝሙረ ዳዊት 118፡27 ላይ እንደሚናገረው *“እግዚአብሔር አምላክ ነው ለእኛም በራልን”* ይላል። ይህም ብርሃን በፍጥረት መጀመሪያ እግዚአብሔር በጨለማው ላይ እንዲበራ ያዘዘው ያለ ፀሃይና ጨረቃ የበራ የራሱ ብርሃን ሲሆን ይህም በሰው ልብ ውስጥ የሚበራና በእውነት እግዚአብሔር እንዳለ የሚገልጥ የውስጥ እይታን የሚሰጥ እውነተኛ ብርሃን ነው።

ይህም ብርሃን አንድ ሰው በእርግጥ እግዚአብሔር በዙሪያው እንዳለ ያይና ይረዳ ዘንድ የሚያስችል እውቀትን የሚሰጠው እይታ ሲሆን ይህም ከውስጠኛ ማንነቱ አልፎ በዙሪያው ባሉ አካላዊ ነገሮች ሁሉ ላይ ጭምር የሚገለጥ የራሱ የእግዚአብሔር ነፀብራቅ ነው። ለዚህም ነው እግዚብሔርን አይተን መኖሩን ያወቅንበትን ይህንን በልባችን የበራ ብርሃን መጽሐፍ ቅዱስ በ2ኛ ቆሮንቶስ 4፡6 ላይ ሲገልጥ *“በክርስቶስ ፊት የእግዚአብሔርን የክብሩን እውቀት ብርሃን እንዲሰጥ በልባችን ውስጥ የበራ ነው”* ብሎ የሚገልፀው። ይህም ብርሃን እርሱ ራሱ ሊታይ በማይቻል ብርሃን ውስጥ የሚኖረው እግዚአብሔር በመልካም ፈቃዱ ሊገለጥልን ወድዶ ጨለማ በሆነው ፍጥረታዊ ልባችን ውስጥ “ብርሃን ይብራ” ብሎ የበራልንና የተገለጠልን ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ አሁንም በ1ኛ ዮሐንስ 5፡20 ላይ *“የእግዚአብሔር ልጅ እንደመጣ እውነተኛም የሆነውን እናውቅ ዘንድ ልቡናን እንደሰጠን እናውቃለን”* ይላል። ይህም ምንም እንኳን ክብሩና የእጁ አሻራ በሚታየው አለም ሁሉ ላይ ፍጥጥ ብሎ በሙላት የሚታይ ሊከደን የማይችል በመሆኑ እግዚአብሔር በዙሪያችን የሞላ ቢሆንም ፍጥረታዊ ሰው ሰምቶ ይረዳው ዘንድ እንዳይቻል በሰው ጥበብ፣ እውቀትና ማስተዋል ይታይ ዘንድ አይችልም። ነገር ግን ከላይ በተገለጸው መሰረት እነዚሁ በዙሪያችን የሞሉ ድንቅ ፍጥረታት በላያቸው ላይ የሰሪያቸውን ክብር ያንፀባርቁና እርሱ በእውነት እንዳለ ይነግሩን ዘንድ እርሱን የምናውቅበት ልቡናና በጨለማችን ላይ የሚበራ እርሱን የሚገልጥ ብርሃን

ያስፈልገናል። ይህም ብርሃን ራሱ እግዚአብሔር የሆነው እርሱን በሙላት ይገልጥ ዘንድ የክብሩ መንፀባረቅና የባህርይው ምሳሌ ሆኖ በስጋ የተገለጠው የእግዚብሔር ጥበብና እውቀት የሆነው በውስጠኛ ማንነታችን ተዘርቶ የሚበቅለው የእርሱ ህያው ቃል ነው። ይህ አዲስ ብርሃን እንደ ጠዋት ፀሃይ ወገግታ ሲሆን መንፈሱ ደግሞ ብርሃኑ የበለጠ ይበራና ግልጥ ብሎ እግዚአብሔር ይታየን ዘንድ የሚያደርግ የብርሃን ድምቀት ነው።

በዚህ መልኩ ተገልጦልን ያወቅነው ብርሃን የሆነው እግዚአብሔር እርሱን ራሱን ብቻ ሳይሆን ዙሪያችንን ጭምር በተለየ መልኩ የምናይበት መነጸር ነው። በፍጥረታዊ ማንነት በዙሪያችን ለሚገኙ ነገሮች የነበረን እይታና መረዳት በዚህ ብርሃን ሲታይ ፈጽሞ ሌላ መልክና እውነታን የሚገልጡ ይሆናሉ። ይህም በእግዚአብሔር ብርሃን የሚታይ ነገር፣ እይታችን በመለወጡ ምክንያት ቀድሞ ትልቅ የሆነብን እጅግ በጣም ትንሽ፣ ከባዱ ቀላል፣ብርሃኑ ጨለማ፣ ዋናው ረብ የለሽ ወዘተ እንዲሆን ይሆናል። ሰው በዚህ ብርሃን እይታውን ከቃኘና መረዳቱን ከለወጠ በኋላ አኗኗሩ፣ አስተሳሰቡ፣ እርምጃው፣ ትኩረቱና እይታው ወዘተ ሁሉ ፈጽሞ ቀድሞ ከነበረው ይለወጣል።

“እግዚአብሔር ብርሃን ነው” ብለን ስንል ከላይ ለሌሎች ነገሮች ያለንን እይታ ይቀይራል ብሎም የዙሪያችንን እውነተኛና ትክክለኛ ገጽታ ፍንትው አድርጎ ያሳያል ብለን ካልነው በተጨማሪ እግዘኢአብሔር ራሱ ብርሃን ማንነቱ የሆነ አካል ነው። ይህም ማለት ማንም ሊደርስበትና ሊያየው በማይቻለው የራሱ ታላቅ ብርሃን ውስጥ የሚኖር እርሱ ራሱ ብርሃን የሆነ አምላክ ነው። በዚህ ገለጻ ውስጥ የእግዚአብሔርን ማንም ሊደርስበት የማይችል ፍጹም ንጹህ የሆነ ጽድቅ፣ ቅድስና፣ እውነተኛነት፣ እንከን አልባ የሆነ ማንነቱን ለመግለጥ የምንጠቀምበት ገለጻ ነው። ብርሃን በሌለበት ጨለማ ውስጥ ሰው ዙሪያውን ማየት እንደማይችለው እንዲሁ ጽድቅ የአመፃን፣ ቅድስና የሀጢአትን፣ እውነት የውሸትን፣ ፍቅር የጥላቻን ወዘተ ገመና ፈጽመው ይገልጡ ዘንድ የሚበሩ እነርሱ በተገኙና በበሩበት አካባቢ ጨለማ ፈጽሞ ድራሹ እንዲጠፋ የሚያደርጉ የእግዚብሔር ብርሃን ፍንጣቂዎች ናቸው።

በዮሐንስ ወንጌል ፤ ላይ እንደሚናገረው የእግዚአብሔር ቃል የሆነው ኢየሱስ ብርሃን እንደሆነ ይገልጥና ይሄው ብርሃንም በጨለማ እንደሚበራና ጨለማም ሊያሸንፈው እንደማይችል ይናገራል። ይህም ፀጋንና እውነትን ተሞልቶ በመካከላችን

የተገኘው የእግዚአብሔር ብርሃን የሆነው ዘላለማዊ ቃሉ በዚህ አለም ጨለማ ላይ እውነተኛ ማንነቱን ይገልጥ ዘንድ መምጣቱን በዚህም የአለምን ገመና ያለ ከልካይ አሸንፎ መግለጡን ለማሳየት የተነገረ እውነት ነው። ይህንንም የበለጠ ለማብራራት ጌታችን ኢየሱስ በዮሐንስ ወንጌል 3፡19 ላይ ብርሃን ወደ አለም እንደመጣና ይህም ብርሃን ስራቸው ክፉ የሆነ ሰዎችን እንደሚያጋልጣቸው ገልጦ በዚሁ ምክንያት ክፋታቸው እንዳይገለጥባቸው ከብርሃን ይልቅ ጨለማን እንደሚወዱ ይናገራል።

ይህም በብርሃንና በጨለማ መካከል ያለ ጠላትነት ፈጽሞ ሊታረቅ የማይችል ዘላለማዊ ጠላትነት ነው። ይህንኑ ለማሳየት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐንስ ወንጌል 7፡7 ላይ በመገኘቱ ብርሃን ስራዋ ክፉ እንደሆነ ስለሚመሰክርባት ጨለማ የሆነችው አለም እርሱን እንደምትጠላው ይናገራል። በዚህም ስራው የእግዚአብሔር ቃልና ብርሃን የሆነው የመለኮት ሙላት በእርሱ የተገለጠበት የአብ ባህርይ ምሳሌና የክብሩ መንፀባረቅ የሆነው በእርሱ ላይ በሙላት የተንፀባረቀውን አብን አይተን እናውቀው ዘንድ ትኩር ብለን የምናየው እውነተኛው ብርሃን እርሱም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ እንደተናገረ እርሱ የአለም ብርሃን ነው። መጽሐፍ በ1ኛ ዮሐንስ 1፡5 ላይ እንደሚል *"እግዚአብሔር ብርሃን ነው ጨለማም በእርሱ ዘንድ ከቶ የለም።"* ይህም ማለት አንዳች ሀጢአት፣ ውሸት፣ አመጽ፣ አለመታመን ወዘተ የማያውቀው በዘመናት መካከል ከፍና ዝቅ ሳይል በቀድሞ ማንነቱ እንደነበረ እንደዛው የሚኖር ጻድቅና እውነተኛ የሆነ ነው ማለት ነው።

በዚህም መሰረት ዙሪያችን በዚህ ብርሃን ሲታይ አለም ያላት እውነተኛ መልክና ትርጉም እንዲሁም ሌሎች በዙሪያችን ያሉ አካላት እውነታና አጠቃላይ የህይወት ትርጓሜ በትክክል ይታወቃል ማለት ነው። ይህም ማለት የየትኛውም ነገር እውነተኛና ትክክለኛ ማንነት ፍጹም በሆነው የእግዚአብሔር ብርሃን የሚታይና እርሱ እግዚአብሔር ለዚያ ነገር ባለው ትርጓሜ የሚወሰንና የሚታወቅ እንዲሆን ያደርገዋል ማለት ነው።

በፍጥረታዊ ማንነት ሲመላለሱ ቆይተው በእግዚአብሔር ምህረት በልባቸው ብርሃን ይብራ ተብሎ እግዚአብሔርን ለማወቅ እድል ያገኙና በዚሁ መሰረት እይታቸውን ለውጠው በዚህ ብርሃን የቀረውን ዘመናቸውን ሊኖሩ ወስነውና መርጠው አዲስ ፍጥረት ለመሆን ከአሮጌው ማንነታቸው ጋር ተፋትተው ወደ ብርሃኑ የመጡ ሁሉ እርሱ ብርሃን

እንደሆነ እነርሱ ደግሞ ብርሃን እንደሆኑ ብሎም በዚሁ ማንነታቸው ምክንያት ፈፅመው ከጨለማ ጋር ኅብረትን እንዳያደርጉና በብርሃን ብቻ የሚመላለሱ የብርሃን ልጆች መሆናቸውም በምልልሳቸው ይታወቅ ዘንድ ያስፈልጋቸዋል፡፡

"ዙሪያችን በዚህ ብርሃን ሲታይ አለም ያላት እውነተኛ መልክና ትርጉም እንዲሁም ሌሎች በዙሪያችን ያሉ አካላት እውነታና አጠቃላይ የህይወት ትርጓሜ በትክክል ይታወቃል ማለት ነው፡፡"

እነዚህን ከድቅድቅ ጨለማ አምልጠው ወደሚደነቀው ብርሃን የመጡትን ሁሉ እነርሱ ራሳቸው ከብርሃን ተወልደዋልና ብርሃን ሆነው ለጨለማው አለም ያበሩ ዘንድ በዚህም የተገኙበትን የብርሃን ምንጭ ይኸውም የጠራቸውን በጎነት ይገልጡ ዘንድ የተጠሩ ያደርጋቸዋል፡፡ እነዚህም የእግዚአብሔርን ህግ ለእግራቸው መብራት ለመንገዳቸውም ብርሃን በማድረግ እውነተኛው ብርሃን ይኸውም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በጨለማው አለም ደምቆ በርቶ አለምንም አሸንፎ የስጋ ወራቱን ጨርሶ ወደተገኘበት ወደ አባቱ እንደ ሄደ እንዲሁ በምሳሌው ይመላለሱ ዘንድ ፈለጉን ተከታዮች እንዲሆኑ ያስፈልጋቸዋል፡፡

ነገር ግን በብርሃን አለሁ የሚልና የብርሃን ባህርይ ሳይኖረው የሚመላለስ ወንድሙንም የሚጠላ እስከ አሁን በጨለማ አለ፡፡ እርሱ የአለም ብርሃን እንደሆነ አለምም በመገኘቱ ክፉ ስራዋንና ጨለማዋን ስለሚገልጥባት እንደጠላችው፣ እነርሱም የአለምን ጨለማ የሚገልጡ በአለምም የተጠሉ የአለም ብርሃኖች ይሆኑ ዘንድ ይገባቸዋል፡፡ ይህም መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚናገረው አስቀድሞ ሳይጠራን በፊት ጠሪው የልጁን መልክ እንድንመስል ወስኖ የጠራን ከተጠራንበትና ብርሃኑ በልባችን ከበራበት ጊዜ ጀምረን ባልተቋረጠ የአዕምሮ መታደስ ውስጥ በማለፍ ከአሮጌው የጨለማ ማንነት እየተፋታን ከክብር ወደ ክብር በመለወጥ የልጁን መልክ እስክንመስል ድረስ ወደ ፍጹም ብርሃንነት የምንለወጥበት ረጅም የብርሃን መንገድ ነው፡፡

- ## የማስተንተኛ ጥያቄዎች

1. የእግዚአብሔር ብርሃን ስለ ማንነቱና ከኃጢአት ጋር ስላለው ግንኙነት ምን ያስተምርሃል?
2. የእግዚአብሔር ብርሃን ራስህን፣ ዓለሙንና ለሕይወትህ ያለውን ዓላማ የምታይበትን መንገድ እንዴት ለውጦታል?
3. ዛሬ እግዚአብሔር በየትኛው የሕይወትህ ክፍል ይበልጥ በብርሃኑ እንድትመላለስ እየጠራህ ነው?

- ## አሰላስል

እግዚአብሔር ብርሃን ነው፤ በእርሱም ጨለማ ፈጽሞ የለም። በመለኮታዊ ብርሃኑ ራሱን ይገልጣል፣ እውነትን ያሳያል፣ ሁሉንም ነገር በጥበቡና በዓላማው መሠረት እንድናይ ያበራልናል። በክርስቶስ አማካኝነት ብርሃኑ ወደ ልባችን በገባ ጊዜ፣ ከኃጢአት፣ ከሐሰትና ከመንፈሳዊ ጨለማ ወጥተን እንደ ብርሃን ልጆች እንድንመላለስ ተጠርተናል። በብርሃኑ ስንመላለስ እርሱን ይበልጥ እናውቃለን፣ ቅድስናውንም በሕይወታችን እናንጸባርቃለን። ስለዚህ የዓለምን ጨለማ ትተን ሁልጊዜ በእግዚአብሔር ብርሃን መመላለስ እንደሚገባን ማስታወስ ያስፈልገናል።

- ## ጸሎት

በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፣ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት ብርሃንህን በልባችን ስላበራህ እናመሰግንሃለን። ይበልጥ እንዳውቅህ ዓይኖቼን ክፈት፤ በእውነትህም በየቀኑ እንድመላለስ እርዳኝ። በሕይወቴ ውስጥ ያለውን የጨለማ ሥራ ሁሉ ግለጥና አስወግድ፤ ወደ ክርስቶስ መልክ ለውጠኝ። ሕይወቴም ቅድስናህንና ፍቅርህን ለሌሎች እንዲያበራ በመንፈስህ ምራኝ።

በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አሜን።

- ## የአርምሞ ጥቅስ

*"እግዚአብሔር ብርሃን ነው ጨለማም በእርሱ ዘንድ ከቶ የለም"*

*– 1ኛ የዮሐንስ መልእክት 1፥5 –*

## 2.17. እግዚአብሔር ሕይወት ነው!

ይህ የእግዚአብሔር ማንነት በዚሁ መጽሐፍ መጀመሪያ ላይ እግዚአብሔር የምንም ነገር ጥገኛ ሳይሆን በራሱ የሚኖር ህያው አምላክ ነው ብለን ካልነው ሃሳብ ጋር በእጅጉ የተገናኘ ነው። ይህም ህይወት የሚባለው ነገር የአንድን ነገር ግዑዝ አለመሆን ብሎም ያለ ማንም ጥገኝነት በራሱ ባልተቋረጠ ሂደት መኖርን የሚቀጥልና በዙሪያው ካለ ሌላ አካል ጋር መስተጋብር ያለው እንዲሆን የሚያደርገው ነው። በዚህም መሰረት በእርግጥ በትክክል ህይወት የሆነ እና ይህንኑ ህይወትም ሊያካፍልና ሊሰጥ የሚችል ከእግዚአብሔር በቀር አንዳች ሌላ የለም።

ፍጥረት ሁሉ ወደ መኖር ሳይመጣ በፊት እግዚብሔር ነበረ። ከዚህም በተጨማሪ መጽሐፍ ቅዱስ በዮሐንስ ወንጌል 1፡3 ላይ እንደሚናገረው በእርሱ ህይወት ራሷ ነበረች። ይህም ብቻ ደግሞ አይደለም በዚሁ በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 14፡6 ላይ እና 11፡25 ላይ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚናገረው እርሱ ራሱ ህይወት እንደሆነ ይታያል። ይህም ህይወት እኛ የወንጌል አማኞች የመለኮትን በሶስትነት የተገለጠ አንድነት እንደምናምን መጽሐፍ ቅዱስም በዮሐንስ ወንጌል 5፡26 ላይ እንደሚናገረው አብ በራሱ ህይወት ያለው ሲሆን ይህንኑም ህይወት ገና ከመጀመሪያው አብ *"ካለበት ጊዜ"* አንስቶ በእቅፉ ለሚገኘው ልጁ ለወልድ ደግሞ እንዲሁ በራሱ ህይወት እንዲኖረው ሰጥቶታል። ይህም ገና ከመጀመሪያው በእርሱ ዘንድ የተገኘ፣ ህይወት ራሱ ለፍጥረቱ ሁሉ እንዲደርስ በወደደበት መንገድ የፈጠራቸውን ሁሉ በህይወት እንዲኖሩና ህያዋን እንዲሆኑ የሚያስችል የሚካፈል ማንነት ነው።

ከራሱ ከእግዚአብሔር በቀር ህይወት የሆነና ለወደዳቸው ሁሉ በህይወት ይኖሩ ዘንድ ህይወትን መስጠት የሚችል ሌላ ማንም የለም። እግዚአብሔር እርሱ ራሱ ህይወት የሆነ ብሎም ህይወትን ደግሞ ሊሰጥ የሚችል የህይወት ሁሉ ምንጭ ነው። ገና ከመጀመሪያው ፍጥረቱን እንደ ፈቃዱ ምክር ወደ

> "ከራሱ ከእግዚአብሔር በቀር ህይወት የሆነና ለወደዳቸው ሁሉ በህይወት ይኖሩ ዘንድ ህይወትን መስጠት የሚችል ሌላ ማንም የለም።"

መኖር ካመጣ ወዲያ የእርሱ ህይወት በሙላት ይገለጥና ይታይ ዘንድ የራሱን መልክና ምሳሌ ከፍጥረቱ መሃል እጅግ ልዩ በሆነው የሰው ልጅ በኩል ይገልጥ ዘንድ ህይወቱን አካፍሎታል። በዚህም መሰረት መጽሐፍ ቅዱስ በዘፍጥረት 2፡7 ላይ እንደሚናገረው የሰውን ልጅ ከምድር አፈር ካበጀው ወዲያ የራሱን የህይወት እስትንፋስ ሰው ደግሞ ህያው ነፍስ ይሆንና በህይወት ይኖር ዘንድ እንዳካፈለው እንመለከታለን። በዚህም ቦታ የሰው ልጅ ህይወቱን ካካፈለው የህይወት ምንጩ ከሆነው እግዚአብሔር ውጭ አንድ ጥበበኛ ሸክላ ሰሪ የሰራው ግዑዝ፣ ህይወት አልባ፣ ባለ ብዙ ቅርጽ ትቢያና አፈር ብቻ እንደሆነ መመልከት ይቻላል።

ህይወትን ከእግዚአብሔር የተካፈለው ሰው በተፈጠረበት ሁኔታ በህይወት ይኖርና ለዘላለም ይቆይ ዘንድ ህይወት ከመጀመሪያው ከተገኘበት ራሱ ህይወት የሆነ ፈጣሪው እግዚብሔር ጋር ያለው ኅብረት የግድ ያስፈልገዋል። ያለዚህ ኅብረት የሰው ልጅ ከህይወት የተቋረጠ በጊዜ ሂደት ወደመጣበት አፈርነት የሚለወጥ ለጥቂት ጊዜ ብቻ የሚንቀሳቀስ ሙት ፍጡር ነው።

የሰው ልጅ ለዘላለም በህይወት እንዲኖር እግዚአብሔር የእርሱን ህይወት በራሱ ላይ ይጨምርና ይኖርበት ዘንድ ባዘጋጀለት ገነት ውስጥ የህይወት ዛፍን ሰጥቶት ነበር። በዚህም መንገድ ከህይወት ዛፍ እየበላ ከመጀመሪያ ህይወቱ የተገኘችበትን ህይወት ይበልጥ እየገለጠ ይኖር ዘንድ የተሰራ ነበር። ከዚህ የህይወት ዛፍ ደግሞ እንዳይበላ በሰራው ሀጢአት ምክንያት ከተባረረ በኋላ ግን ከህይወቱ ምንጭ ጋር ግንኙነቱ የተቋረጠ፣ በሞት መንገድ ላይ የሚገኝ ጊዜያዊ አፈር ብቻ ሆኖ ሞቶ ይኖር ነበር።

ኢዮብ በመጽሐፉ ምዕራፍ 10 ከቁጥር 8-12 ባለው ክፍል እርሱ ፈጣሪው በቸርነቱ ከሰጠው የራሱ ህይወት ውጭ ፈጣሪው እንደ ወደደ አድርጎ በእጁ ለውሶ የሰራው ጭቃ ብቻ እንደሆነ ይናገራል። ነገር ግን ከመጀመሪያው እንዳየን የሰውን ልጅ ህያው ነፍስ ያደረገው የእግዚአብሔር እስትንፋስ ይኸውም የራሱ የእግዚአብሔር ህይወት ሰው ህያው ሆኖ ይኖር ዘንድ የግድ ያስፈልገዋል። ይህም የእግዚአብሔር እስትንፋስ ለሰው ልጆች ብቻ አይደለም፤ ነገር ግን ለህያዋን ሁሉ የግድ የሚያስፈልግ እንደሆነ ዳዊት በመዝሙሩ ምዕራፍ 104፡29-30 ላይ በግልጽ ይናገራል። በዚህም ስፍራ ላይ መዝሙረኛው

እንደሚናገረው ህይወት የሆነው እግዚአብሔር ፊቱን ሲሰውር ፍጥረቱ ሁሉ እንደሚደነግጡ ነፍሳቸውንም እንደሚያወጣና እንደሚሞቱ ወደተገኙበት አፈርም እንደሚመለሱ ይናገርና ደግሞ እንደወደደ መንፈሱን ልኮ እንደሚፈጥራቸው ዳግም በህይወትም እንዲኖሩ እንደሚያደርጋቸው ይናገራል።

ሰው ከእግዚአብሔር ያገኘውን ውድ ህይወት ለዘላለም ጠብቆ ይኖር ዘንድ ከህይወት ዛፍ መብላት ያስፈልገው ነበር። ነገር ግን በመተላለፉና ባለመታዘዙ ምክንያት ደግሞ ከህይወት ዛፍ እንዳይበላ ከገነት ከተባረረ በኋላ የሰው ዘር ሁሉ በሞት ጎዳና እንዲኖር ተገዷል። ከዚህም በኋላ ዳግም ህይወትን ወደ ሰው ልጆች ያመጣና ገና ከመጀመሪያው በሰው ልጆች ላይ እንዲገለጥ የፈለገውን የራሱን ህይወት በሰው ልጆች ያይ ዘንድ ወድዶ በታላቅ ምህረቱና በአስገራሚ ፀጋው እንዲሁ በነጻ የህይወትን ራስ፣ በሰው ልጆች መካከል ስጋ አድርጎ አመጣው።

በዚህም መሰረት የሰው ልጆች ሁሉ ከዚህ የህይወት ውሃ ጠጥተው ከዚህም የህይወት እንጀራ በልተው ለዘላለም ሳይጠፉ በህይወት ይኖሩ ዘንድ ቀድሞውኑ የራሱን ህይወት በእርሱ ያደረገበትን ቃሉን ስጋ አድርጎ ለሁላችን ቆረሰልን። ሁላችን ተካፍለነው የማያልቀው ይህ የተትረፈረፈ ህይወት በእግዚአብሔር ምህረት ዳግመኛ ከህይወት ለጎደለውና በሞት ጥላ ስር ለሚገኘው የሰው ልጅ ተገለጠለት። ይህም ሰው ሁሉ ከዚህ የህይወት ምንጭ ጋር ተገናኝቶ ሰው ሁሉ በህይወት እንዲኖር እንጂ እንዳይጠፋ ወድዶ እግዚአብሔር እንዲሁ በጸጋው ያደረገው ነው። በዚህ መንገድ የተገለጠው ይህ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ህይወት ታዲያ እንዲሁ ምናባዊ ያልሆነ ህይወት ይሆንላቸው ዘንድ ይህንን የህይወት እንጀራ ለመብላት እድል ባገኙ ሁሉ ላይ ስጋ ለብሶ የሚታይና የሚዳሰስ የተገለጠ የራሱ የእግዚአብሔር መልክ ነው።

እግዚአብሔር ተጠንቶ የሚታወቅና ተተርኮ የሚያልቅ እውነት፣ ብሎም በዚህ እውቀት ላይ በተመሰረተ መውጣት መግባት እንዲሁ የምንመላለስበት መንገድ ብቻ ሳይሆን በእኛ ሁኔታ ራሱን ገልጦ የሚያሳይበት ተኑሮ የሚገለጥ ህይወትም ጭምር ነው። ገና ከመጀመሪያው እግዚአብሔር በሰው ልጆች ሊያየው ወድዶ የነበረውን የራሱን መልክ /ህይወት/ ዳግም በሰው ልጆች ያየው ዘንድ ቅዱስ የሆነውን የእርሱን ህይወት ማስተናገድ የሚያስችል የተቀደሰ የሸክላ እቃን በልጁ የመስቀል ስራ ቀድሶ አዘጋጀ። ከዚህም ወድያ

ህይወት የሆነው እግዚአብሔር ራሱን በእነዚህ የክብር እቃዎቹ በኩል ያሳይና የልቡን ሃሳብ ይፈጽም ዘንድ በመንፈሱ በኩል ወደ ሰው ልጆች ሁሉ መጥቶ ይኖር ዘንድ ገባ።

“ህይወትን የሚሰጥ መንፈስ ሆኖ የመጣውና የሰውን ልጆች ሁሉ በትንሳኤ ይዞ የተነሳው ልጁ የሰው ዘር ሁሉ ያየውና ይመስለው ዘንድ ግልጽ ሆኖ በአላማ የተሰቀለለት የህይወት ምልክቱ ነው።”

ከዚህ ወዲያ የመጀመሪያው አዳም በተፈጠረበት የእግዚአብሔር መልክ የእግዚአብሔርን ህይወት ይኖር ዘንድ ከህይወት ዛፍ እንዲበላ እንደተነገረው ያንኑ መልክ ደግሞ በሰው ልጆች ሁሉ መካከል እንዲገልጥ አስቀድሞ ወስኗልና ሁላችን ባልተቋረጠ የአእምሮ መታደስ በመለወጥ አሮጌውን የወደቀ ማንነት በማራገፍ አዲሱን ሰው በመልበስ ወደ እርሱ መልክ /ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ/ እናድግ ዘንድ የሚረዳንን ፀጋና የሚመራንን መንፈስ በሙላት ሰጠን።

ህይወትን የሚሰጥ መንፈስ ሆኖ የመጣውና የሰውን ልጆች ሁሉ በትንሳኤ ይዞ የተነሳው ልጁ የሰው ዘር ሁሉ ያየውና ይመስለው ዘንድ ግልጽ ሆኖ በአላማ የተሰቀለለት የህይወት ምልክቱ ነው። በዚህ ከአሮጌው ሰው እየተላቀቁ ወደ አዲሱ ሰው የሚደረግ የለውጥ ጉዞ እኛ ሁላችን እርሱ ቅዱስ እንደሆነ ቅዱሳን ለመሆን፣ ፍጹም እንደሆነም ፍጹም ለመሆን በተገለጠው ፀጋ ክቡር ወደ ሆነው ህያው ድንጋይ እየቀረብን መንፈሳዊ ቤት በመሆን ለመሰራት ህያዋን ድንጋዮች እንሆናለን። ይህም እኛ እየቀነስንና ፈጽመን እየጠፋን እርሱ በእኛ ህያው ሆኖ በሙላት የሚገለጥበት እኛ በእርሱ ህያዋን ሆነን የምንኖርበት እርሱ በእኛ የሚኖረው የእርሱ ህይወት ነው። እግዚአብሔር እርሱ ራሱ ህይወት ሲሆን የሌላው ፍጡር ሁሉም የህይወት መገኛ ምንጭ ነው። በዚህም መሰረት እኛ በእርሱ እርሱም በእኛ በሆነበት ጊዜ ሁሉ ከእርሱ የተነሳ በእርግጥ ለዘላለም በህይወት የምንኖር ፈጽመን ልንጠፋ የማንችል ህያዋን ነን።

“እግዚአብሔር እርሱ ራሱ ህይወት ሲሆን የሌላው ፍጡር ሁሉም የህይወት መገኛ ምንጭ ነው።”

## የማስተንተኛ ጥያቄዎች

1. እግዚአብሔር የሕይወት ምንጭ ነው ማለት ምን ያስረዳሃል?
2. በክርስቶስ መጽናት በየቀኑ የምትኖረውን ሕይወት እንዴት ይቀርጸዋል?
3. ዛሬ በየትኛው የሕይወትህ ክፍል በእግዚአብሔር ላይ ይበልጥ መደገፍ ያስፈልግሃል?

## አሰላሰል

እግዚአብሔር የሕይወት ምንጭ ነው። ሕይወት ሁሉ ከእርሱ ይመነጫል፤ ከእርሱም ውጭ እውነተኛ ሕይወት የለም። በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት ለሚያምኑት ሁሉ የዘላለም ሕይወትን ሰጥቶአል፤ በእርሱም እንድንኖርና ሕይወቱ በእኛ እንዲገለጥ ይጠራናል። በክርስቶስ መኖር ማለት በቃሉ መጽናት፣ በፈቃዱ መመላለስና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ፍሬያማ ሕይወት መኖር ማለት ነው። ከእርሱ ተለይተን ምንም ልናደርግ እንደማንችል በማወቅ፣ በሁሉም ነገር በእርሱ መደገፍና በእርሱ መኖር እንደሚገባን ጠንቅቀን ልንረዳ ያስፈልገናል።

## ጸሎት

በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፣ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት ሕይወትን ስለሰጠኸን እናመሰግንሃለን። በየቀኑ በአንተ እንድጸና፣ ሕይወቴም የአንተን ሕይወትና እውነት እንዲያንጸባርቅ እርዳኝ። በመንፈስህ አበርታኝ፤ በማደርገው ሁሉ አንተን እንዳከብርና ፈቃድህን እንድፈጽም እርዳኝ።

በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አሜን።

## የአርምሞ ጥቅስ

*"ኢየሱስም፦ እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም።"*

*— የዮሐንስ ወንጌል 14፥6 —*

## 2.18. እግዚአብሔር መኖሪያ ነው!

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር የእርሱ ለሆነ በስሙም ለተጠራ ርስቱና ገንዘቤ ነው ላለው ህዝብ መኖሪያ፣ አምባ እና አለት እንደሆነ ደጋግሞ ይናገራል። ይህ የእግዚአብሔር ማንነት እግዚአብሔር ለህዝቡ ፍጹም የሆነ ደህንነትን፣ ጥበቃን፣ አቅርቦትን፣ ሰላምና ደስታን ወዘተ አስተማማኝ በሆነ ሁኔታ ማቅረብ የሚችል መታመኛ እንደሆነ ለማሳየት የተናገረ ነው። ስለ እግዚአብሔር መኖሪያነት ከተጠቀሱት ብዙ ሰው የሚያውቃቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች መካከል ዘዳግም 33፡26-27 ዋነኛው ነው። ይህም እግዚአብሔር ከግብጽ ምድር በፀናች እጅ ያወጣውን ህዝቡን ከጠላቶቹ ሁሉ የሚጠብቅ በየትኛውም አስቸጋሪ ሁኔታ እንኳን ቢሆን ያለ አንዳች ችግር ህዝቡን በደመናት ላይ በታላቅነት እየሄደ በሰማያትም ላይ ያለ ከልካይ እየሄደ ለህዝቡ ረድኤት ለመሆን የሚተጋ አስተማማኝ መኖሪያ እንደሆነ የሚገልጽ ነው። ሙሴ በስንብቱ ለህዝቡ ለእራኤል ይህንን ደጋግሞ ሲያሳስብ ይህ መኖሪያ የሆነ አምላክ ክንዶቹን ከህዝቡ በታች አድርጎ የሚጠብቅ ጠላቶቹም ህዝቡን እንዲፈሩትና እንዲገዙለት የሚያደርግ ዋስትናው እንደሆነ ይገልፃል።

እግዚአብሔር መኖሪያ ነው ብለን ስንል አስተማማኝ ዋስትና ነው፤ ከየትኛውም አደጋ የሚያስጥል መጠለያ ነው፤ ካልገመትነው አሁናዊ የሆነ ድንገተኛ ችግር የሚታደግ ወዳጅ ነው፤ በፍጹም ሰላምና እረፍት የሚያኖር፣ እውነተኛ ጥበቃን ለሚኖሩበት ህዝቡ የሚያቀርብ አለት የሆነ አምባ ነው ብለን እያልን ነው። (ግዛው, 1994) (Merriam-Webster, n.d.) ይህም በተለይ በመዝሙረ ዳዊት

“እግዚአብሔር መኖሪያ ነው ብለን ስንል አስተማማኝ ዋስትና ነው፤ ከየትኛውም አደጋ የሚያስጥል መጠለያ ነው፤ ካልገመትነው አሁናዊ የሆነ ድንገተኛ ችግር የሚታደግ ወዳጅ ነው፤ በፍጹም ሰላምና እረፍት የሚያኖር፣ እውነተኛ ጥበቃን ለሚኖሩበት ህዝቡ የሚያቀርብ አለት የሆነ አምባ ነው ብለን እያልን ነው።”

ምዕራፍ 46 ላይ በዝርዝር የተገለፀ እውነት ሲሆን የእግዚአብሔር መኖሪያነት ከጥፋት ለመዳንና ደህና ለመሆን ብቻ ሳይሆን ጠላትን ሁሉ ለማጥቃት የሚያስችል ድንቅ መጠጊያ እንደሆነ ይናገራል። ይህም ህዝቡ ባገኘው ታላቅ መከራ ወቅት ደህንነትን መስጠት የሚችል ረዳትነት ሲሆን በሰው አእምሮ እንኳን ከባባድ ከሆኑ እንደ ምድር መነዋወጥና የተራሮች ወደ ባህር ልብ መወሰድ ጭምር ያሉ ለደህንነት ምንም አይነት ቀዳዳ የሌላቸው ሁኔታዎች ጭምር ፈጽሞ ሰላምንና ደህንነት መስጠት የሚችል መኖሪያ እንደሆነ ያሳያል። በእንደዚህ አይነት ወቅትም እንኳን ቢሆን ፍጥረት ሁሉ ስፍራውን በለቀቀበት ሁኔታ እግዚአብሔርን መኖሪያቸው ያደረጉ ሁሉ እርሱ ራሱ ከእነርሱ ጋር በመሆኑ ምክንያት አንዳች ክፉ ሊያገኛቸው አይችልም።

መኖሪያቸው እግዚአብሔር የሆነላቸው ሲድራቅ፣ ሚሳቅና አብድናጎም በአምላካቸው ተወራርደው ቀድሞውኑ አስፈሪ ሆኖ ይነድ ከነበረው በላይ በልጦ ሰባት እጥፍ እንዲነድ ከተደረገ እቶን እሳት ውስጥ አንዳች እንኳን የእሳት ወላፈን ሳያገኛቸው እንዲሁም የገቡበት እሳት ሽታን እንኳን ሳያስቀሩ በሰላም ወጥተው አይተናል። ይህም ሁሉ የሆነው በእሳቱ መካከል የነበረው መኖሪያቸው ከፊታቸው ከተከሰተው የጥፋት አቅም በላይ ስለነበር ነው። በተመሳሳይ መልኩ ይህ መኖሪያ ዳንኤልን ከተራቡ አንበሶች አፍ ያዳነ ሲሆን ይሄው መኖሪያ እስራኤልን በፀናች እጅ ከታላቁ ፈርዖን እጅ አስመልጦና ታድጎ በጠላቶቻቸው መካከል ርስትን ለህዝቡ የሰጠ የተመሰከረለት አስተማማኝ አምባ ነው።

እግዚአብሔር መኖሪያው የሆነለት ሰው እግዚአብሔር በሚገኝበት በዚያ የሚገኝ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በመዝሙረ ዳዊት ምዕራፍ 91 ላይ በእግዚአብሔር ዘንድ ስለመኖር ሲናገር አንድ ሰው እግዚአብሔር መኖሪያው ይሆንለት ዘንድ እርሱ ራሱ እግዚአብሔር ባለበት ይኖር ዘንድ እንደሚገባው ይገልፃል። በልዑል መጠጊያ የሚኖር ሰው ሁሉን በሚችለው በዚህ አምላክ ጥላ ውስጥ የሚያድር እንደሆነ ይናገራል። ይህም ሰውየው እግዚአብሔር ባለበት ለመኖር ወደ እርሱ መጠጋቱ እግዚአብሔርን መኖሪያው እንዳደረገለት ያሳያል። በዚህም ምክንያት ከመኖሪያው ማንነት የተነሳ በዚያ ፍጹም ደህንነትን እንደሚያገኝ የትኛውም አይነት መንፈሳዊና ስጋዊ አደጋ ከሚኖርበት አምላኩ እውቅናና ቁጥጥር ብሎም አቅም በላይ ባለመሆኑ ጉዳት ያገኘው ዘንድ ጠላቱ የቱንም

ያክል ጊዜ ቢሞክር ብዙም መሳሪያ ቢጠቀም አንዱም ሳይደርስበት በሰላም እንደሚኖር ያሳያል።

በዚሁ ክፍል እንዲህ አይነት ወደ እግዚአብሔር የተጠጋ መኖሪያውንም እዚያ ያደረገ ሰው በእግዚአብሔር ጥላ ውስጥ የሚያድር በመኖሪያውም ላባ የተጋረደ በመሆኑ የአዳኝ ወጥመድ፣ የሌሊት ግርማ፣ በቀን የሚበርር ፍላጸ፣ በጨለማም የሚሄድ ክፉ ነገር፣ አደጋ፣ የቀትር ጋኔን ወዘተ እንዳያገኘው የተጠበቀ ይልቁንስ ጠላቶቹ በአጠገቡ ሺህ በቀኙም አስር ሺህ እየሆኑ የሚወድቁለት በእግዚአብሔር ክንፎች በታች ተማምኖ የሚኖር፣ የእግዚአብሔር እውነት እንደ ጋሻ የከበበው ደህንነቱ ፈጽሞ የተጠበቀ ሰው እንደሆነ ይታያል። ይህም ጥበቃ በእግዚአብሔር ሁሉን አዋቂነትና ሁሉን ቻይነት ላይ የተመሰረተ ሲሆን መኖሪያውን በእርሱ ያደረገ ሰው እግሮቹ እንኳን በድንጋይ እንዳይሰናከሉ የሚጠበቅ በመንገዱ ሁሉ ይጠብቁት ዘንድ አምላኩ መላእክቱን ያዘዘለት በዚሁም መሰረት ከፊቱ ያለ እንቅፋት እንዳይመታው በእጆቻቸው የሚያነሱት ምስጉን ሰው ነው። ለዚህም ይመስላል ዳዊት በመዝሙሩ 23ኛ ምዕራፍ ላይ ይህ መኖሪያ የሆነ አምላክ እግዚአብሔር እረኛው እንደሆነ እና በእርሱ በመኖሩም ምክንያት መንገዱ በሞት ጥላ መካከል እንኳን ቢሆን እርሱ ከእርሱ ጋር ነውና ደህንነቱ የተጠበቀ እንደሆነ ፍርሃት እንኳን አጠገቡ እንደማይደርስ ልቡን ሞልቶ ይናገራል።

ይህ እግዚአብሔር መኖሪያ ነው የሚለው አገላለጽ ዘይቤያዊ በሆነ አነጋገር የተገለፀ ገለጻ ሲሆን በዋናነትም ከእግዚአብሔር ጋር የተስማማ ማንነትንና በእርሱ ላይም የተጣለን እምነት የሚያሳይ አገላለጽ ነው። ይህንንም ለማስረዳት በሚመስል መንገድ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱ በእኛ እንደሚኖርና እኛም በእርሱ መኖር እንደሚያስፈልገን ደጋግሞ ተናግሮናል። ይህም ሁኔታ እርሱ ራሱ በፍጹም ውህደትና አንድነት ገና “ከመጀመሪያው” ከአባቱ ጋር ከነበረው ኅብረት ጋር በማነፃፀር የገለጸልን ነው።

> “እግዚአብሔርን መኖሪያ ማድረግ ማለት በእርሱ ላይ በተመሰረተ እምነት እርሱን በማወቅ በማደግ እንደ ልቡ ሃሳብ መኖር ማለት ነው።”

እግዚአብሔርን መኖሪያ ማድረግ ማለት በእርሱ ላይ በተመሰረተ እምነት እርሱን በማወቅ በማደግ እንደ ልቡ ሃሳብ መኖር

ማለት ነው። እግዚአብሔር መንፈስ ነው በዚህም ማንነቱ በየትኛውም ቁስ ሳይገደብ ያለ ልክ በሁሉም ስፍራ የሚገኝ ሁሉም ነገር መኖሪያው የሆነ አምላክ ነው ብለን ከዚህ በፊት የተነጋገርን ሲሆን በተለየ መልኩ ግን እርሱን ለተቀበሉትና በስሙም ሊያምኑ ለወደዱ እርሱ ራሱ በእነርሱ ከመኖሩ ባለፈ እነርሱ በእርሱ ይኖሩ ዘንድ መኖሪያቸው ይሆንላቸዋል። ይህም የእርሱ መኖሪያነት ህጉን ለእግር መብራት ለመንገድ ደግሞ ብርሃን አድርጎ መመላለስን የሚፈልግ ሲሆን ይህም በቃሉ ላይ የተመሰረተ መተማመን እግዚአብሔርን ለታመነበት ሰው መኖሪያና ረዳት መጠጊያም እንዲሆነው ያደርገዋል።

መጽሐፍ ቅዱስ በ1ኛ ዮሐንስ መልዕክት 2፡6፣ 2፡27-28፣ 3፡6-9፣ 3፡15-17፣ 3፡24፣ 4፡13-16 ወዘተ በእርሱ መኖርን ሲያብራራልን በአጭር ቃል እርሱ እንደተመላለሰ መመላለስ እንደሆነ ይናገራሉ። *“ትዕዛዙንም የሚጠብቅ በእርሱ ይኖራል እርሱም ይኖርበታል”* የሚለው ቃል በአንደበት ብቻ ሰዎች እግዚአብሔር መኖሪያቸው እንደሆነ ከሚናገሩት አለፍ ያለ በህይወት ምልልስ የተገለጠ አንዳች ጭካኔንና ከእግዚአብሔር ጋር ወገን መሆንን የሚፈልግ እውነት እንደሆነ ያሳያል። ነገር ግን በእንዲህ አይነት ፍጹም ኅብረት በእርሱ የሚኖር /እግዚአብሔር መኖሪያው የሆነ/ ሰው ከላይ በተገለጸው መልኩ ደህንነቱ ፈጽሞ የተጠበቀ ለዘላለምም እርሱ ባለበት የሚኖር ይሆን ዘንድ የተጠበቀ ነው። ይህም ሰው ከሞት ለማምለጥ ደምን ለመመለስ ከሚፈልገው ገዳዩ በደለኛ ሰው ሸሽቶ ይሄድባቸውና ይኖርባቸው እንደነበሩት የመማፀኛ ከተሞች ወይም ኖህ ከጥፋት ውሃ እንዳመለጠበት በእምነትና በስራ እንደተገለጠው መርከብ አይነት ከዚያም ያለፈ ፍጹም የሆነ ደህንነቱ የተጠበቀ አስተማማኝ የዘላለም መኖሪያ ነው።

ሰው በገዛ አቅሙ ይህንን ማድረግና መኖሪያውን እግዚአብሔር ማድረግ ስለማይችል ጉድለቱን ይሞላለትና ከመጀመሪያው በእግዚአብሔር ልብ እንደነበረ ሰው መኖሪያውን እግዚአብሔርን ያደርግ ዘንድ እግዚአብሔርም በእርሱ ውስጥ ይኖርና ራሱን ይገልጥለት ዘንድ የተገባንም ኅብረት ማድረግ ይችል ዘንድ ከመንፈሱ ሊወለድ እና ሊጠጣ በእርሱም ሊጠመቅ ያስፈልገዋል። በዚህም ከመንፈሱ ጋር ባለን ኅብረትና በተቀበልነው ፀጋ እኛ በእርሱ እንድንኖር እርሱም በእኛ እንዲኖር በዚህ እናውቃለን። እግዚአብሔር አስተማማኝ የሆነ አምባ፣ አለትም የሆነ የማይነቃነቅ የዘላለም መኖሪያ ነው።

> “እግዚአብሔር አስተማማኝ የሆነ አምባ፣ አለትም የሆነ የማይነቃነቅ የዘላለም መኖሪያ ነው።”

## የማስተንተኛ ጥያቄዎች

1. እግዚአብሔር ማደሪያህ ነው ማለት ለአንተ ምን ማለት ነው?
2. በእግዚአብሔር መገኘት መኖር በአስቸጋሪ ጊዜያት እንዴት ሰላም ይሰጥሃል?
3. በየቀኑ ከእግዚአብሔር ጋር ያለህን ኅብረት ለማሳደግ ምን ማድረግ አለብህ?

## አሰላስል

እግዚአብሔር የዘላለም ማደሪያችን፣ መጠጊያችንና ዓለታችን ነው። በእርሱ የሚኖሩ በማንኛውም ሁኔታ ሰላምን፣ ደኅንነትንና ብርታትን ያገኛሉ። የዚህ ዓለም መጠጊያዎች ጊዜያዊና የሚለወጡ ቢሆኑም፣ እግዚአብሔር ግን የማይለወጥና ለዘላለም የሚጸና መጠጊያ ነው። በቃሉ ስንጸናና በፊቱ ስንመላለስ፣ በማይወድቀው መገኘቱ ውስጥ እረፍትን እናገኛለን። ስለዚህ በፍርሃት ወይም በችግር ጊዜ ሁሉ ወደ እግዚአብሔር መሸሸና በእርሱ መታመን እንደሚገባን እናስታውስ።

## ጸሎት

በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፣ የዘላለም መጠጊያዬና ማደሪያዬ ስለሆንህ
አመሰግንሃለሁ። በየቀኑ በአንተ እንድጸና፣ ከፍርሃትና ከችግር ይልቅ በመገኘትህ
እንድታመን እርዳኝ። በመንገድህ እንድመላለስ እርዳኝ፤ እውነተኛ ሰላሜንና ደኅንነቴን
በአንተ ብቻ እንዳገኝ ልቤን አጽና። በሕይወቴ ሁሉ በማይለወጠው ፍቅርህና መገኘትህ
እንድኖር ጸጋህን አብዛልኝ።

በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አሜን።

## የአርምሞ ጥቅስ

*"መኖሪያህ የዘላለም አምላክ ነው፥ የዘላለምም ክንዶች ከአንተ በታች ናቸው፤"*

*— ኦሪት ዘዳግም 33፥27 —*

## 2.19. እግዚአብሔር ተስፋ ነው!

ተስፋ አንዳች በእጅ ያልተያዘ፣ ነገር ግን እንደተያዘ የሚቆጠር በእርግጠኝነት ይሆንልኛል ተብሎ የሚጠበቅ የወደፊት መልካም ነገር ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በሮሜ 8፡24-25 ላይ አንዳች የሚታይ ነገር ተስፋ እንዳልሆነ ነገር ግን ገና ያላየነውን ነገር ተስፋ ማድረጋችን ለዚያ ለምንጠብቀው ነገር ተገቢ የሆነ ትዕግስት እንዲኖረን የሚያደርግ ኃይል ጭምር አብሮ ያለው እንደሆነ ይናገራል። (ግዛው, 1994) (Merriam-Webster, n.d.) (ማኅበር, 1954) ተስፋ እንዲሁ አንድ ሰው በበሬ ወለደ አስተሳሰብ ይሆንልኛል ብሎ ብቻ ከቸች የሚልበት ጉዳይ ሳይሆን ተስፋ የሚያደርገው ነገር ይሆን ዘንድ የሚያስችል ታሪክ እና አሁናዊ ሁኔታ ያለው ሆኖ ተስፋ ይደረግ ዘንድ ከውስጥ ማንነት ጋር የተመሳከረ በእውነት ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ያስፈልገዋል።

ይሄው ተስፋ በዋነኛነት የወደፊት ጥበቃ ይሁን እንጂ የተመሰረተው ግን በትናንትና ታሪካችንና በዛሬ አሁናዊ አቋማችን ላይ ነው። በዚህ መልኩ እርግጠኛ በሆነና ምናባዊ ብቻ ባልሆነ እውነታ ላይ የተመሰረተ ተስፋ አንድን ሰው ነገን በጉጉት እንዲጠበቅና በዚህም የመጠበቅ ሂደት ተስፋውን እያሰበ በብዙ ትዕግስት በመንገዱ ላይ የሚገጥሙትን ችግሮች ሁሉ ማለፍ የሚችልበት አቅም እንዲኖረው የሚያደርገው ነው። ይህም ተስፋ ይሆናል ብለን የምንጠብቀው ነገር እንደሚፈፀም እርግጠኛ የምንሆንበትን እና የማናየውንም ነገር እውን እንደሆነ የምንረዳበትን እምነት በእኛ ውስጥ የሚፈጥር ነው።

እግዚአብሔር እርሱ ራሱ የፍጥረት ሁሉ የየዕለት አሁናዊ ተስፋ ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ ፀሎት ባስተማረ ጊዜ የእለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን በሉ ብሎ እንዳለ እንዲሁም መጽሐፍ ቅዱስ በመዝሙረ ዳዊት 104፡27 ላይ ፍጥረትን ሁሉ የሚመግብ እርሱ እግዚአብሔር እንደሆነ በመግለጽ እነዚህ ሁሉ ምግባቸውን በወቅቱ ይሰጣቸው ዘንድ እርሱን ተስፋ እንደሚያደርጉ ይናገራል። በዚህም መልኩ ለሰው ልጆችና ለእንስሳት እጽዋትን ያበቅል ዘንድ ምግብንም ከምድር እንዲያወጣ ከላይ ከእልፍኙ ተራሮችን እንዲያጠጣና ምድርም በስራው ፍሬ እንድትረካ ዝናብን በወቅቱ ያዘንብ ዘንድ ተስፋ ይደረጋል። ፀሃይን በየቀኑ በስርአቱና የብርሃን ምጣኔው ደግሞም የአየሩን ሁኔታ

አጠቃላይ የፍጥረትን ውቅርና መስተጋብር ይጠብቅ ዘንድ እግዚአብሔር የየዕለት ተስፋ ነው።

ከአቅርቦቱ ባለፈ ህያው በሆነ ከእኛ ጋር ያለው ህብረቱና ግንኙነቱ በእያንዳንዱ እርምጃችን እግሮቻችን እንዳይሰናከሉ እንዲጠብቀን፣ ከፉም ወደ እኛ እንዳይቀርብ፣ በእኛ ላይም የተሰራ መሳሪያ እንዳይከናወን፣ ከክፉ ሁሉ እንዲጠብቀን መቅስፍትም ከቶ እንዳያገኘን ተስፋ እናደርገዋለን። በዚህም አሁናዊ የሆነ ህያው ተስፋ ከመንፈሱ ጋር ባለን ኅብረት ምንም እውቀት በሌለን ግራና ቀኛችንን፣ መነሳትና መቀመጣችንን ብሎም መውጣትና መግባታችንን የማናውቅ እንደሆንን ገብቶን በእያንዳንዱ የህይወት አቅጣጫችን አሁናዊ መሪ እና አስተማሪ ይሆነን ዘንድ ተስፋ እናደርገዋለን።

እርሱን ማወቃችን በእርሱ በራሱ በጎ ፈቃድ ላይ፣ ባበራልን ብርሃንና ባበዛልንም ፀጋ ላይ ተመስርቶ እንደሆነ በማወቅ ደግሞ በቀረልን የህይወት መንገድ ሁሉ ላይ ከእምነት ሳንጠፋ መዳረሻችን ጋር እንደርስ ዘንድ እርሱ ራሱ ሊያደርሰን እንደሚችል በማወቅ ተስፋ እናደርገዋለን። በህይወት ጎዳናችን በምንራመድበት ያልተቋረጠ ከአሮጌው ሰው በመላቀቅ አዲሱን ሰው የመልበስ የአዕምሮ መታደስ ሂደት ፍጹም ደህንነትን ይሰጠንና ልጁን በእኛ ሁኔታ ይገልጥ ዘንድ ተስፋ እናደርገዋለን። በየእለቱ በምናልፍባቸው አስቸጋሪ የስጋ ወራት ቆይታ በሚገጥሙን የህይወት ፈተናዎችና ስለ ስሙም በሚደርሱብን መገፋቶች ሁሉ ተገቢውን በቀልና ፍርድ ይበቀልልንና ይፈርድልን ዘንድ በየእለቱ ተስፋ እናደርገዋለን።

ከዚህም ሁሉ በላይ መጽሐፍ ቅዱስ በ1ኛ ቆሮንቶስ 15፡19 ላይ *“ክርስቶስን ተስፋ ያደረግነው ለዚች ህይወት ብቻ ከሆነ ከሰው ሁሉ ይልቅ የምናሳዝን ነን”* ብሎ እንደሚል በዚህ ሁሉ አሁናዊ እግዚአብሔርን ተስፋ የማድረግ አስቸጋሪ መንገድ ውስጥ በዋናነት እንዲሆንልን በጉጉት የምንጠብቀው የተባረከ ታላቅ ተስፋ ደግሞ አለን። ይኸውም እርሱ ራሱ የተቤዠንና በገዛ ደሙ የዋጀን የመንግስቱም ካህናት እንሆን ዘንድ የጠራንና የቀደሰን ዳግመኛ መጥቶም ሊወስደን ጽኑ ተስፋን የሰጠን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት ነው። ይህም ተስፋ አሮጌውን ሁሉ አሳልፎ ሁሉን አዲስ የሚያደርግ እንባን ሁሉ ከአይናችን አብሶ፣ በቀላችንንም ተበቅሎ፣ በጠላታችን በዲያብሎስም ላይ ተገቢውን የጽድቅ ፍርድ ፈርዶ፣ የማትናወጥ የዘላለም መንግስትን ለእኛ ለልጆቹ የሚያወርስበት

እርሱም አምላካችን ራሱ በመካከላችን ሆኖ በጎቹን በእረኝነት የሚያሰማራበት የዘላለም እረፍትና ደስታ ነው።

በዚህም ተስፋ ላይ አይናችንን የጣልን ስለሆነ አሁን በዚህ የመጠበቅ ሂደት ውስጥ ከጌታ ርቀን በስጋ ወራት ስንሆን ለጊዜው የሚደርሱብንና የምናልፍባቸው መከራዎች ለጊዜው የሆኑና እንደ ምንም የሚቆጠሩ ሊመጣ ካለው ክብርና ደስታ ጋር የማይወዳደሩ እንደሆኑ አወቀን ይልቁንስ ብድራትን እንዲጨምሩልን በማመን በመከራችን ደስ ይለናል። ይህ እግዚአብሔርን ተስፋ ያደረግንበት ባርኮት የመጨረሻው የተባረከ ተስፋችን ሲሆን ይህንኑም በብዙ ናፍቆት በመጠበቅ ከሰማዩ አገራችን የሚመጣውን ይህንኑ አዳኝ ይኸውም ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን አንጋጠን እያየን በናፍቆት እንጠባበቃን። እግዚአብሔር የአሁን ሁሉ በሁሉ የሆነ ተስፋችን ሲሆን ለዘላለም ደግሞ መኖሪያችን ይሆን ዘንድ ያመንነው ታላቅና ብቸኛ ህያው የሆነ ተስፋችን ነው።

> “እግዚአብሔር የአሁን ሁሉ በሁሉ የሆነ ተስፋችን ሲሆን ለዘላለም ደግሞ መኖሪያችን ይሆን ዘንድ ያመንነው ታላቅና ብቸኛ ህያው የሆነ ተስፋችን ነው።”

## የማስተንተኛ ጥያቄዎች

1. እግዚአብሔር ለተስፋህ ብቸኛው የማይናወጥ መሠረት የሆነው ለምንድር ነው?
2. የክርስቶስ ዳግም ምጽአት ተስፋ በአስቸጋሪ ጊዜያት እንዴት ያበረታሃል?
3. ዛሬ ይበልጥ ልትታመንበት የሚገባው የትኛው የእግዚአብሔር ተስፋ ነው?

## አሰላስል

እግዚአብሔር የማይናወጥ ሕያው ተስፋችን ነው። በየዕለቱ በታማኝነት ይጠብቀናል፤ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስም አማካኝነት ከእርሱ ጋር የሚሆን የዘላለም ሕይወት ተስፋ ሰጥቶናል። የዚህ ዓለም ተስፋ ሊቀየር ወይም ሊጠፋ ይችላል፤ በእግዚአብሔር ያለው ተስፋ ግን ፈጽሞ አያሳፍርም። ተስፋዎቹን ስንታመን በመከራ ውስጥ እንኳን በትዕግሥት መጽናትና ዓይኖቻችንን በሚመጣው ክብር ላይ ማድረግ እንችላለን። ስለዚህ በሚታዩ ነገሮች ሳይሆን በማይለወጠው የእግዚአብሔር ተስፋ ላይ በመታመን መኖር ይገባናል።

## ጸሎት

በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፣ ሕያው ተስፋዬ ስለሆንህ አመሰግንሃለሁ። በተስፋዎችህ እንድታመን፣ በመከራ ሁሉ በታማኝነት እንድጸና፣ ዓይኖቼንም በተባረከው ተስፋዬ ይኸውም የክርስቶስ ዳግም ምጽአት ላይ እንዳኖር እርዳኝ። እየጠበቅሁህ ባለሁበት ጊዜ ልቤን በሰላምህ ሙላው፤ በማይለወጠው ቃልህ እንድጸና አጽናኝ። በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አሜን።

## የአርምሞ ጥቅስ

*"በተስፋ ድነናልና፤ ነገር ግን ተስፋ የሚደረግበቱ ነገር ቢታይ ተስፋ አይደለም፤ የሚያየውንማ ማን ተስፋ ያደርገዋል? የማናየውን ግን ተስፋ ብናደርገው በትዕግሥት እንጠባበቃለን።"*

*— ወደ ሮሜ ሰዎች 8፥24-25 —*

## 2.20. እግዚአብሔር ባለጠጋ አምላክ ነው።

ባለፀጋነት የአንድ አካል የተሟላ ሁሉንተናዊ ባለቤትነትና ጉድለት አልባ የሆነ የሀብት ቁመና ነው። የዚሁ ባለጠጋ የሚለው የአማርኛ ቃል አቻ ትርጓሜ ብዙ ሀብት፣ ንብረት ወይም ገንዘብ ያለው፣ የበለፀገ፣ ከበርቴ ወይም ሀብታም የሚል ነው። ይህ ቃል የአንድን አካል በሁለንተና የበለፀገ ማንነት እና ሙላት የሚገልጽ ሲሆን በአጠቃላይ የበዛ የሚታይ ንብረት ያለውንና የበለፀገ ኑሮ የሚኖር አካልን የሚያመላክት ነው። (ግዛው, 1994) (Merriam-Webster, n.d.) ይሄው ባለጠጋ የሚለው ቃል በገንዘብና ቁሳቁስ ላይ ብቻ የታጠረ ቃል ግን አይደለም። ነገር ግን ከገንዘብና ቁሳቁስ ባለፈ አንድ አካል ከሌላው በተለየ መልኩ በተገለጠ ሁኔታ እርሱ ጋር በዝቶ የሚታይ ነገርን ለመግለጽ የሚያገለግል ነው። በዚህም መሰረት የእድሜ ባለጠጋ፣ የእውቀት ባለጠጋ፣ የጥበብ ባለጠጋ፣ የባህርይ ባለጠጋ ወዘተ ብለን የእነዚህን ነገሮች በዚያ ስፍራ ከሌላው በተለየ መልኩ በዝተው መገኘትን ለመግለጽ ልንጠቀምበት እንችላለን።

የእግዚአብሔር ባለጠግነት በምን አይነት ምድራዊ ቋንቋ ሊገለጽና ሊብራራ እንደሚችል ማሰብ እንኳን እጅግ የሚከብድ ነው። የእግዚአብሔር ባለጠግነት በየትኛውም እጅግ የበለፀገ ሌላ ምድራዊና ፍጥረታዊ ማንነት ውስጥ ፈጽመን ልናገኘውና ልንረዳው የማንችለው ሁሉ በሁሉ የሆነ ባለጠግነት ነው። ይህ የእግዚአብሔር ባለጠግነት ፍጥረት ሁሉ የእርሱ እጅ ስራ ከመሆኑ የሚነሳ ሁሉን ጥቅልል አድርጎ ለሰሪው የሚሰጥ ባለጠግነት ነው። ይህም ብቻ አይለም፤ ሰው በትንሿ አዕምሮው እስከአሁን እግዚአብሔር ረድቶት በደረሰበት ጥበብና ምርምር ባገኘው የመላው ፍጥረት እጅግ በጣም ጥቂት ምናልባትም ምንም የሆነ እውቀት ላይ ተመስርቶ ይቅርና እግዚአብሔር ፈቅዶለት ፍጥረቱን ሁሉ እንኳን ማወቅ ቢችል እግዚአብሔር በዚህም ልክ እንኳን የማይለካ ከዚያ በብዙ ያለፈ ባለጠግነት ያለው ነው።

> “የእግዚአብሔር ባለጠግነት በየትኛውም እጅግ የበለፀገ ሌላ ምድራዊና ፍጥረታዊ ማንነት ውስጥ ፈጽመን ልናገኘውና ልንረዳው የማንችለው ሁሉ በሁሉ የሆነ ባለጠግነት ነው።”

መጽሐፍ ቅዱስ በዘፍጥረት 1፡1 ላይ *"በመጀመሪያው እግዚአብሔር ሰማያትንና ምድርን ፈጠረ"* የሚለው ቃል ሁሉን ጠቅልሎ የሰሪው የእግዚአብሔር ንብረት የሚያደርግ ቃል ነው። ይህንንም እግዚአብሔር ከአፉ ብቻ በሚወጣ ቃል ካለመኖር ወደ መኖር ያመጣውን የእርሱ ብቻ የሆነ ፍጥረቱን ሁሉ ጳውሎስ በቆላስያስ 1፡15-16 ባለው ክፍል ሲያስረዳን ይህ ባለጠጋ የሆነ አብን ያየንበት ልጁ የማይታየው አምላክ ምሳሌ እንደሆነ በዚህም ስጋ የሆነ ቃል የሚታዩትና የማይታዩት ሁሉ፣ በሰማይና በምድር ያሉት ሁሉ በእርሱ የተፈጠሩ እንደሆነ ነግሮን ሁሉ በእርሱና ለእርሱ የተፈጠረ እንደሆነ ያስረዳናል። ይህንንም በሚገባ የተረዳው ዳዊት በ1ኛ ዜና 29፡11-14 ባለው ክፍል ውስጥ የእግዚአብሔርን ባለጠግነት ሲነግረን *"በሰማይና በምድር ያለው ሁሉ የአንተ ነው"* ብሎ እርሱ ባለቤት ነውና ሁሉን ደግሞ የሚገዛ እንደሆነ ይነግረናል። ይህም በባለቤትነቱ ምክንያት የተገለጠው ገዥነቱ ሁሉን በእጁ ያደረገና የእርሱ የሆኑትም ሁሉ ለብልጥግናው የተገዙ ብሎም ክብርን የሚያመጡለት እንዲሆኑ ያደረገ ነው።

ታዲያ በእንዲህ አይነት ብልጥግና ውስጥ የሚገኝ አምላክ ከፈጠረው ፍጥረቱ በተለይም ወደ እርሱ ይቀርብ ዘንድ እድል ካገኘው የሰው ልጅ ምን ሊፈልግ ይችላል? ለዚህም መልስ በሚመስል መልኩ መጽሐፍ ቅዱስ በዘዳግም 10፡14፣ በሮሜ 11፡35 ሚክያስ 6፡8 ወዘተ ላይ ባሉ ክፍሎች ሰውን እግዚአብሔር አምላክ ከአንተ የሚፈልገው ምንድር ነው? ወዘተ እያለ ሁሉ ከእርሱ፣ በእርሱና ለእርሱ የተፈጠረ እንደሆነ ደጋግሞ ያስታውሰናል ይጠይቀናልም።

"እነሆ ሰማይ ሰማየ ሰማያትም ምድርም በእርስዋም ያለው ሁሉ የአምላክህ የእግዚአብሔር ነው፣ ሁሉ ከአንተ ዘንድ ነውና ከእጅህም የተቀበልነውን ሰጥተንሃልና መልሰን ለአንተ እናቀርባለን" ወዘተ የሚሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ቃላት ይሄው ባለጠጋ አምላክ እግዚአብሔር ከሰው ልጅ እጅ የሚፈልገው ምንም ነገር እንደሌለ የሚያስታውሱ ናቸው። *"ምድርና ሞላዋ ለእግዚአብሔር ናት ዓለምም በእርስዋም የሚኖሩ ሁሉ"* ተብሎ እንደተፃፈው እንዲሁ ከላይም በስፋት በተገለጠው የእግዚአብሔር ባለጠግነት ውስጥ በፍጥረት አለሙ ውስጥ ያለውን ሁሉ የእግዚአብሔር ንብረት የሚያደርግ እውነት ሲሆን

ይህም በሰው ልጆች እጅ ካለው በተጨማሪ የሰውን የራሱን ነፍስ ጭምር የእግዚአብሔር እንደሆነ የሚያስታውሰን ነው።

እግዚአብሔር አንዳች እጥረትና ጉድለት የሌለበት ሁሉ በሁሉ የሆነ አምላክ ሲሆን በሰው ልጆች እጅ ያለው ሁሉ ብርና ወርቅ ጭምር እንዲሁም ሰው ራሱ በሁለንተናው የእግዚአብሔር ንብረት ነው። ማርቲን ሉተር ደጋግሞ እንደሚለው "አሳቹ ዲያብሎስ እንኳን ሳይቀር ከመጀመሪያው የእግዚአብሔር ፍጡር ነውና እርሱ ራሱ የእግዚአብሔር ንብረት ነው።" በዚህም መሰረት የእግዚአብሔር ብልጥግና ከላይ በመግቢያው ለመግለጽ እንደተሞከረው በሰው አዕምሮ ሊታሰብ ከሚችለው ጭምር ያለፈ ፍጹም የሆነ ብልጥግና ነው።

> "እግዚአብሔር አንዳች እጥረትና ጉድለት የሌለበት ሁሉ በሁሉ የሆነ አምላክ ሲሆን በሰው ልጆች እጅ ያለው ሁሉ ብርና ወርቅ ጭምር እንዲሁም ሰው ራሱ በሁለንተናው የእግዚአብሔር ንብረት ነው።"

ባለጠጋ የሚለውን ቃል ስንፈታ በተናገርነው መሰረት ብልጥግና የአንድ አካል የቁሳቁስ ብዛትና ባለቤትነት ብሎም የተትረፈረፈ ህይወትና እጥረት አልባ ቁመና ነው ያልን ሲሆን፣ ብልጥግና ግን ከቁሳቁስ ያለፈ በእውቀት፣ በዕድሜ፣ በጥበብ ወዘተ ጭምር ሊገለጥ የሚችል እንደሆነ ተገልጿል።

በእግዚአብሔር ብልጥግና ውስጥ ከተፈጠረውና በፊቱ ወደ መኖር ከመጣው የሚታይና የማይታይ ፍጡር በላይ ትልቅ ብልጥግናው የእርሱ የራሱ ማንነት ውስጥ የተሰወረው የጥበብና የእውቀት ብልጥግናው ነው። መጽሐፍ ቅዱስ፣ ተፈጥሮ ወደ መኖር ካመጣው ቁስ ባለፈ ዋና የሆነውን የራሱ የእግዚአብሔር ማንነት ላይ ያተኮረውን ብልጽግናውን ሲነግረን በሮሜ 11፡33 ላይ *"የእግዚአብሔር ባለጠግነትና ጥበብ እውቀቱም እንዴት ጥልቅ ነው"* ብሎ ይናገርና ፍርዱ የማይመረመር እንደሆነ ለመንገዱም ፍለጋ እንደሌለው ይነግረናል። ይህም በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የእግዚአብሔር ባህርያት ብለን የዘረዘርናቸው የእርሱ ብቻ የሆኑ ባህርያትን ጨምሮ እነዚህ በዚህ ክፍል የተጠቀሱ የእውቀት፣ የጥበብ ፣ የማስተዋል፣ የፍርድ፣ የምህረት፣ የትዕግስት፣ የቸርነት ወዘተ

ብልጥግናዎች ከእግዚአብሔር ጋር ከመጀመሪያው አብረውት የኖሩ አለማት ሁሉ የተፈጠሩባቸው የራሱ የእግዚአብሔር እውነተኛ ብልጥግናዎቹ ናቸው።

መጽሐፍ ቅዱስ በ1ኛ ዜና 29፡11-14 ባለው ክፍል መሰረትም እግዚአብሔር በታላቅነት፣ በኃይል፣ በክብር፣ በድልና በግርማ፣ በብርታት፣ ሁሉን በማድረግ ችሎታ፣ በምስጋና፣ በከፍታና በባለጠግነት ሁሉ ፍጹም የበለጠገና ሁሉ ተጠቅልሎ የግሉ ብቻ እንደሆነ ይናገራል። በዚህም መሰረት ሁለንተናዊ የሆነውን የእግዚአብሔርን ብልጥግና በማስረዳት ለዚሁ ብልጥግናው የሚገባን ክብርና ምስጋና ለእርሱ ማቅረብ እንደሚያስፈልግ ያስታውሰናል።

*"ቸር ነውና ምህረቱም ለዘላለም ነውና"* በሚለው ቃል ውስጥ እግዚአብሔር ለሚወዱት ምህረቱንና በረከቱን ትዕግስቱንም እስከ ሺህ ትውልድ ድረስ ሊሰጠው የሚችል በምህረቱ ባለጠጋ የሆነ አምላክ እንደሆነ ያሳየናል። ይኸውም የምህረቱ ባለጠግነት በኤፌሶን 2 ላይ እንደተገለፀው እኛ ሁላችን በነጻ ደህንነትን ያገኘንበት ዋና የእግዚአብሔር ብልጥግና እንደሆነ ይታያል። ታዲያ በዚህ ሁኔታ እንደተመለከትነው ምንም እንኳን ሁሉ የእግዚአብሔር እንደሆነ ከላይ ባለው ዳሰሳ በዝርዝር የተገለፀ ቢሆንም ደካማው ሰው ከእግዚአብሔር የተቀበለውን ያን የእርሱ እንደሆነ፣ እግዚአብሔርም ከእጁ እንደሚሻውና በሰጠውም ጊዜ ለእግዚአብሔር ውለታን እንደዋለለት አይነት ባለማስተዋል ሲያስብ ይታያል።

የእግዚአብሔር ርስትና ህዝብ ሊሆን የተመረጠው የእስራኤል ህዝብ በዚህ እሳቤ ደጋግሞ በእግዚአብሔር ሲወቀስ የሚታይ ሲሆን ይህም በእግዚአብሔር ፈጽሞ የተጠላ እንደሆነ ይታያል። የእግዚአብሔር ብልጥግና ከማንም አንዳችን የማይቀበል፣ የተትረፈረፈ፣ መለኪያ የሌለው ብልጥግና ሲሆን ከእግዚአብሔር ሌላም አንዳች የራሱ ነገር ያለው ሌላ ባለጠጋ የለም። እግዚአብሔር ለዚሁ በሀጢአት ምልልስ ውስጥ ለሚገኝና በልማድ ለእግዚአብሔር መስዋዕትን ሊያቀርብ በግና ፍየል፣ ኮርማና ዋኖስ ይዞ ለሚመጣው ህዝቡ በመዝሙረ ዳዊት ምዕራፍ 50፡9-18 ባለው ክፍል ውስጥ ከእጁ አንዳችን እንደማይወስድ፣ ርሃብ ፈጽሞ የማያውቀው እግዚአብሔር ብራብ እንኳን ብሎ

“የእግዚአብሔር ብልጥግና ከማንም አንዳችን የማይቀበል፣ የተትረፈረፈ፣ መለኪያ የሌለው ብልጥግና ሲሆን ከእግዚአብሔር ሌላም አንዳች የራሱ ነገር ያለው ሌላ ባለጠጋ የለም።”

በልቶ ይጠግብ ዘንድ የምድረ በዳው አራዊት፣ የሰማዩ ወፍ፣ በሺህ ተራራዎች ያሉ እንስሶች ብሎም አለምና ሞላዋ ሁሉ የእርሱ እንደሆነች ይናገራል።

በዚህም መሰረት እግዚአብሔር ከማንም እጅ ምንም እንደማይሻ ስጦታዎቻቸውም ከልብ ሳይሆን ከእጅ የተሰጡ እንደሆኑ በዚህ መልኩ ወደ እርሱ ፊት የሚያመጡት የመስዋዕት ብዛት ለእርሱ ምንም ጥቅምና ደስታ እንደሌለው ጨምሮ ይናገራል። በዚህ መልኩ የሚሰውለት መስዋዕት በፊቱ በሬን የሚያርድለት ሰውን እንደሚገድል፣ ጠቦትንም የሚሰዋ የውሻውን አንገት እንደሚሰብር፣ የእህልንም ቁርባን የሚያቀርብ የእርያን ደም እንደሚያቀርብ፣ ዕጣንንም የሚያጥን ጣኦትን እንደሚባርክ የሆነ በፊቱም እጅግ የተጠላ እንደሆነ ይናገራል።

በዚህ ሁሉ መካከል እግዚአብሔር የእርሱ ያልሆነ የሰው ልጅ ሊሰጠው የሚችል ጎደሎ እንደሌለው እና ከተቀበለው ለፍቅሩ መግለጫ ወደ እግዚአብሔር ፊት በተሰበረ መንፈስ መስዋዕትንና ስጦታን ይዞም የሚመጣ ሰው ከመስዋዕቱ በላይ መታዘዙ በእግዚአብሔር ፊት የበለጠ የተወደደ እንደሆነ ያወቅ ዘንድ ያስፈልገዋል። ለዚህም ነው እግዚአብሔር በሆሴዕ ፮፥፮ ላይ በእግዚአብሔር ዘንድ እጅግ የተወደደ መልካም መዓዛም ካለው የሚቃጠል መስዋዕት እንኳን ይልቅ እርሱን ማወቅ ይበልጥ የተወደደ እንደሆነ የሚናገረው።

*“ምን ይዤ ወደ እግዚአብሔር ፊት ልምጣና በልዑል አምላክ ፊት ልስገድ?”* ብሎ ለዚህ መልስ በሚመስል መልኩ የሚቃጠል መስዋዕትና የአንዱን አመት ጥጃ ይዞ በመምጣት፣ በሺህ አውራ በጎች ወይ በእልፍ የዘይት ፈሳሾች እግዚአብሔርን ደስ ሊያሰኝ ወዶ ለተጨነቀው አልፎም የበኩር ልጁን ስለ በደሉ የሆዱንም ፍሬ ስለ ነፍሱ ሀጢአት ሊሰጥ ጭምር እያሰበ ለነበረው ሰው እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘው ይህ ሁሉ እንዳልሆነ ነገር ግን እግዚአብሔር ደስ ይሰኝ ዘንድ ከእርሱ የሚሻው ፍርድን ያደርግ ዘንድ፣

ምህረትንም ይወድድ ዘንድ፣ ከአምላኩም ጋር በትህትና ይሄድ ዘንድ እንደሆነ እንጂ ከላይ በተዘረዘሩት መንገዶች እንዳልሆነ ይገልፅለታል።

በዚህም መሰረት እግዚአብሔር ከማንም እጅ ምንም ነገር የሚሻ ጉድለት ያለበት አምላክ እንዳልሆነ ነገር ግን ከሰው ልጆች ጋር ያለው አላማ ፍቅር ብቻ እንደሆነ ይታያል። በዚህ ሁሉ ውስጥ ታዲያ የሰው ልጅ ትልቁ ብልጥግናው ራሱ አምላኩ እግዚአብሔር ሲሆን አምላኩ ከእርሱ ጋር መሆኑ ደግሞ የመጨረሻው በረከቱ ነው። ከዚህ ውጭ ግን ከእጁ የተፈጠረውን ቁስ ተቀብሎ ከፊቱ የራቀ ሰው አለሙን ሁሉ እንኳን ቢያተርፍ እጅግ የከሰረ ባዶ የሆነ ደሃ ነው። ይህንንም በሎዶቂያ ቤተክርስቲያን ውስጥ በግልጽ የምናየው ሲሆን በእርሷ ቋንቋ ብልጥግና የተባለው በእግዚአብሔር ፊት ባዶነት እንደነበር እውነተኛ ብልጥግናም ራሱ እግዚአብሔር እንደሆነ ይታያል።

እግዚአብሔርን ገንዘቡ ያደረገ በእውነተኛ ትህትናም በፊቱ የሚመላለስ አብሮነቱም የበዛለት ሰው እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር በመሆኑ ማንም የማይቃወመው እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ከመሆኑ የተነሳ ፍጥረቱ ሁሉ የሚገዛለት የእግዚአብሔር የሆነው ሁሉ የእርሱ የሆነለት ባለጠጋ ሰው ነው። ከዚህ ውጭ የሆነ እግዚአብሔር አልባ ቁሳዊ ብልጥግና ግን ፍጹም የሆነ ባዶነት ነው። ለዚህም አይነተኛው ማሳያ የአለም ክብር ብልጥግናውም ሁሉ ለእኔ ተሰጠኝ ለምወደውና ለሚሰግድልኝም እሰጠዋለሁ ያለው የዘላለም ፍርደኛው የእሳት ባህር የተጠበቀለት የከሰረው የዚህ አለም ገዥ የተባለው ዲያብሎስ ነው። እግዚአብሔርን ተከትሎና ገንዘቡ አድርጎ በቁሳቁስ የደኸየ ለዚህ አለም ገዥ ሰግዶ የአለምን ሀብት ካግበሰበሰ ሰው ይልቅ እጅግ ባለጠጋ ነው።

*ሰው አለሙን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱን ግን ቢያጎድል ምን ይጠቅመዋል?*

> "እግዚአብሔርን ተከትሎና ገንዘቡ አድርጎ በቁሳቁስ የደኸየ፣ ለዚህ አለም ገዥ ሰግዶ የአለምን ሀብት ካግበሰበሰ ሰው ይልቅ እጅግ ባለጠጋ ነው።"

## የማስተንተኛ ጥያቄዎች

1. የእግዚአብሔር ወሰን የሌለው ባለጠግነት ስለ ማንነቱ ምን አስተምሮሃል?
2. እግዚአብሔርን ማወቅ ከዓለም ሀብት ሁሉ የሚበልጥ ሀብት የሆነው ለምንድር ነው?
3. እግዚአብሔር ታላቅ ሀብትህ መሆኑን በየቀኑ ሕይወትህ እንዴት ልታሳይ ትችላለህ?

## አሰላስል

እግዚአብሔር ከልክ በላይ ባለጠጋ ነው። በሰማይና በምድር ያለው ሁሉ የእርሱ ነው፤ ሁሉንም የፈጠረና የሚያስተዳድር እርሱ ነው። ነገር ግን የእርሱ ታላቅ ባለጠግነት በሚታዩ ነገሮች ብቻ አይገለጥም፤ በፍጹም ባሕርዩ፣ በጥበቡ፣ በምሕረቱ፣ በፍቅሩና በጸጋው ውስጥ ይገለጣል። እውነተኛ ባለጠግነት የምድር ሀብትን በማከማቸት ሳይሆን፣ እግዚአብሔርን በማወቅና እርሱን ከሁሉ የሚበልጥ ሀብታችን በማድረግ ይገኛል። ስለዚህ ልባችንን በሚያልፉ የዓለም ሀብቶች ላይ ሳይሆን፣ በማይጠፋው በእግዚአብሔር ላይ ማኖር እንደሚገባን እናስታውስ።

## ጸሎት

በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፣ ልክ የሌለው ባለጠግነትህንና የበዛውን ጸጋህን ስለገለጥህልን እናመሰግንሃለን። በምድራዊ ሀብት እንዳልታመን፣ ከሁሉ በላይ አንተን ሀብቴ አድርጌ እንድኖር አስተምረኝ። በትሕትና፣ በምስጋናና በታማኝነት በመታዘዝ በየቀኑ እንድመላለስ ጸጋህን አብዛልኝ። ልቤም ሁልጊዜ የማይጠፋ ሀብት በሆንከው በአንተ እንዲያርፍ እርዳኝ።

በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አሜን።

## የአርምሞ ጥቅስ

*"የእግዚአብሔር ባለ ጠግነትና ጥበብ እውቀቱም እንዴት ጥልቅ ነው፤"*

*— ወደ ሮሜ ሰዎች ፲፩፥33 —*

## 2.21. እግዚአብሔር ቸር ነው!

አንድ አካል የበለጠገና ሞልቶ የተረፈው እንኳን ሆኖ ቸርነት የሌለው ሊሆን ይችላል። ይህም ቸርነት ማጣት ለሌላ ሰው ከማድረግ በፊት ለራስ እንኳን የተገባን መሰረታዊ ነገር ለማድረግ የማይፈልግ ንፉግነትን ጭምር ያዘለ ስግብግብ ማንነት ያለው ሊሆን ይችላል። ቸር የሚለው ቃል የአንድን አካል በጎነት፣ ርህራሄ፣ ለጋስነት፣ ትህትና፣ መስጠት፣ ታይታን የማይወድ የመስጠትና የማካፈል ፍላጎትና አቅም የሚያሳይ ነው። (ግዛው, 1994) (Merriam-Webster, n.d.) ይህም ቸርነት የአንድን አካል ብልጥግና የሚቀድም ማካፈል ይችል ዘንድ የሚያስፈልገው ማንነት ነው። ከዚህም በተጨማሪ ይሄው ቸርነት ሙሉ ይሆን ዘንድ ሰጭው የሚሰጥበትና ራሱን የሚቆርስበት ልብ በልግስናና በደስታ ይሆን ዘንድ ደግሞ ይገባል።

ከዚህ በፊት ባሉት የዚህ መጽሐፍ ክፍሎች በዝርዝር እንደተገለፀው ፍጥረቱና አለሙ ሁሉ ንብረትነቱ የእግዚአብሔር እንደሆነ ከሆነውም ሁሉ አንዳች እንኳ ያለ እርሱ እንዳልሆነ ተገልጿል። ምንም እንኳን እግዚአብሔር አንዳችን ነገር ከማንም የማይፈልግ በማንም ላይ ጥገኛ ያልሆነ ሁሉ በሁሉ የሆነ አምላክ ቢሆንም እንኳን ያለውን ሁሉ የፈጠረውንም ሁሉ ይጠቀምበት ያስተዳድረውና ይገዛው ዘንድ ለፈጠረው ፍጡር ለሰው ልጅ የሰጠ ቸር አምላክ ነው። ይህም ቸርነቱ የፈጠረውን የእጅ ስራውን ከመስጠት አልፎ መንግስቱን እንኳን ጭምር ሳይቀር ለሰው ልጆች ከመስጠት ያልተቆጠበ እውነተኛ ቸርነት ነው። በየቀኑ፣ በየደቂቃውና ሴኮንዱ እስትንፋስን ለሰው ልጆች፣ የሚበሉትን ምግብ ለምድር ፍጥረታት ሁሉ ሳይጓድል ያቀርባል።

“ምንም እንኳን እግዚአብሔር አንዳችን ነገር ከማንም የማይፈልግ በማንም ላይ ጥገኛ ያልሆነ ሁሉ በሁሉ የሆነ አምላክ ቢሆንም እንኳን ያለውን ሁሉ የፈጠረውንም ሁሉ ይጠቀምበት ያስተዳድረውና ይገዛው ዘንድ ለፈጠረው ፍጡር ለሰው ልጅ የሰጠ ቸር አምላክ ነው።”

ይህ ሁሉ ታዲያ የእግዚአብሔር ንብረት ሆኖ ሳለ በአግባቡ ይጠቀምበት ዘንድ የተሰጠው የሰው ልጅ እንዲሁ በነጻ ከአምላኩ የተሰጠው እንደሆነ ሲዘነጋና ከሰጭው ባህርይ በተቃራኒው በንፉግነት ሲመላለስ ይታያል። እግዚአብሔር በቸርነቱ ለሰው ልጆች ሁሉ የሰጠው ሀብት በምድር ላይ ለነበሩ፣ ላሉና ደግሞ ገና ለሚኖሩ ሁሉ የሚበቃ ሀብት ቢሆንም ይሄው ሁሉን ለራስ የማድረግ ራስን የመውደድ አባዜውና ንፉግነቱ በተመሳሳይ ምድር እየኖሩ ፈጽሞ ባልተቀራረበ የኑሮ ሁኔታ የጠገቡና የተራቡ ህዝቦችን በየቦታው ፈጥሮ ይታያል።

እግዚአብሔር ከመጀመሪያው ሰውን ሲፈጥረው በመልኩና በምሳሌው ያደረገው ይሄው ቸርነቱ ደግሞ በፈጠረው ሰው ውስጥ ይኖርና በፍቅር የተሰጣቸውን ተካፍለው ይኖሩ ዘንድ የነበረ ቢሆንም ሰው ግን ከዚህ ከተፈጠረበት መልክ በእጅጉ ርቆ ሲኖር ይታያል። በዚህም ምክንያት የተፈጠረው የኑሮ ልዩነት ያለውን የበለጠ እንዲኖረው ያጣውን ደግሞ የበለጠ እንዲያጣ እያደረገ አለሙንም በሀብት የበላይ የሆኑ እና የፈረጠሙ እንዲያስተዳድሯት እያደረገ ቀጥሏል። እግዚአብሔር የእርሱ የሆነውን ሁሉ በቸርነቱ ለጥቅማችን የሰጠን ቢሆንም የአለመታዘዝ አመጸኛ ምልልሳችን ከዚህ በተቃራኒው ሆኖ አለሙ ሁሉ የኃይልና ሀብት የበላይነትን ለማግኘት የሚጋደልባት ምድርን አበጀ። ይሄው የሰው *ያለኝ ይበቃኛል* የማይል ማንነትና ሁሉን የማግበስበስ አባዜ ለጎደለውና ላጣ ሰው ማካፈልን ካለመውደድ አልፎ ይኖረው ዘንድ የሰጠውን እግዚአብሔርን እንኳን ለቤቱ ስራ በፈቃዱ በልቡ ተነሳሽነት ይሰጠው ዘንድ ያዘዘውን ትዕዛዝ ተላልፎ ከእግዚአብሔር ጭምር በድፍረት እየሰረቀ እንዲኖር ሲያደርገው ይታያል።

የእግዚአብሔር ቸርነት ከላይ በብልጥግናው በተገለፀው መሰረት የፈጠረውን ለሰው ከመስጠት እልፍ ያለ ራሱን በሙላት በሰው ልጆች ውስጥ ለመግለጥ ሁለንተናውን ጭምር የሰጠበት ያልተቆጠበ ቸርነት ነው። ይህም እኛ ሁላችን ደግሞ የመለኮት ባህርይ ተካፋዮች እንሆንና በነገር ሁሉ እርሱን በመምሰል እንኖር ዘንድ የሰጠን በሸክላ እቃችን ውስጥ የተቀመጠ የከበረ መዝገብ ነው። ገና ከመጀመሪያው ሰው ጋር በዚህ መልኩ የተቀራረበው ቸሩ አግዚአብሔር ለአዳም ያልሰጠው ነገር አልነበረም። በዚህ ልክ ያከብረው ዘንድ ወድዶ ቸርነቱን ያበዛለት ሰው ከዚህ ከፍታው ባለመታዘዝ ምክንያት በወደቀ ጊዜ እንኳን ይህ የእግዚአብሔር ቸርነት ከሰው የተነፈገ አልነበረም። በገዛ ሀጢአቱ

ምክንያት ለውድቀት የተዳረገውን ሰው መልሶ ሊያድነውና ህይወትን ሊሰጠው ወድዶ ራቁትነቱን ይሸፍንለት ዘንድ ቁርበትን አለበሰው።

> “የእግዚአብሔር ቸርነት ከላይ በብልጥግናው በተገለፀው መሰረት የፈጠረውን ለሰው ከመስጠት እልፍ ያለ ራሱን በሙላት በሰው ልጆች ውስጥ ለመግለጥ ሁለንተናውን ጭምር የሰጠበት ያልተቆጠበ ቸርነት ነው።”

*“ቸር ነውና ምህረቱም ለዘለዓለም ነውና”* ተብሎ እንደተጻፈ እንዲሁም እንደሆነ ይህ ባለጠጋ የሆነው ጌታ እግዚአብሔር ብልጥግናውን ሁሉ ለወደደው የሰው ልጅ አንዳች ሳያስቀር ያካፈለ ቸር ነው። ከፈጠረው ፍጥረቱ ሁሉ በላይ ለይቶ የራሱን መልክ ለሰው የሰጠበት የራስ ተነሳሽነት፣ በሳተ ጊዜ የሚደግፍ ርህራሄው፣ ምህረት፣ ቸርነት፣ ይቅርታ፣ ፍቅር፣ በጎነትን ወዘተ አለቀብኝ ሳይል ለሰው ልጆች በየቀኑ ያበዛል። የዚህም ቸርነቱ የመጨረሻው ማሳያ አለሙን ሊያድን ወድዶ ራሱን ይኸውም አንድያ ልጁን ለሀጢአተኛው ሰው አሳልፎ የሰጠበት በዚህም መንገድ የዘላለም ህይወትንና የመንግስቱ ወራሽነትን ለዚሁ በሀጢአት የተጨማለቀ ሞት የሚገባው ሰው የሰጠበት ስጦታ ነው።

ከዚህ የሚበልጥ ቸርነት ለማንም የለውም። በዚህም ብቻ ሳይበቃው ሰው ደግሞ እንዳይወድቅና ከህይወት እንዳይጎድል እለት እለት የሚመራውን፣ ወደ እውነት ሁሉም የሚያደርሰውን የሚቀድሰውንም፣ አለምን የሚያሸንፍበትን አብሮነቱን ይኸውም መንፈስ ቅዱስን ሳይሰፍር ሰጠው፤ በፀጋ ላይ ፀጋን አትረፈረፈለት። በየጊዜው የሚስተውን ሰው ይቅር የሚልበትና የሚታገስበት ልቡ በዚህም የተገለጠው እለት እለት በመንፈሱ በልባችን የሚያፈሰው ፍቅሩ፣ የበዛውም ምህረቱ የእግዚአብሔር የቸርነቱ የመጨረሻ ማሳያ ነው። ለዚህ ነው ጳውሎስ በሮሜ 8፥32 ላይ ይህንኑ የእግዚአብሔር ቸርነት ሲያስረዳ *“ለገዛ ልጁ ያልራራለት ነገር ግን ስለ ሁላችን አሳልፎ የሰጠው ያው ከእርሱ ጋር ደግሞ ሁሉን ነገር እንዲያው እንዴት አይሰጠንም”* ብሎ ያለው።

የእግዚአብሔር ቸርነት ጠላቶች የነበርነውን እኛን ሁላችንን በልጁ ሞት በኩል ከራሱ ጋር በማስታረቅ በሞት ፋንታ ህይወትን በጨለማ ፋንታ ደግሞ ብርሃንን የሰጠ

ነው። ይህም ቸርነት ከተደረገልን ከእኛ የሰው ልጆች በኩል ለዚህ ውለታው ምላሽ የሚሆን ነገርን ለሰጭው ምንም ልንመልስ በማንችልበት መልኩ እንዲሁ በነጻ ስጦታነት የተሰጠን የእግዚአብሔር ታላቅ ቸርነት ማሳያ ነው። ይህንኑ የእግዚአብሔር ቸርነት ያዕቆብ በመልዕክቱ ሲነግረን አጥቶ ለጠየቀው ሁሉ ያለ ነቀፋ በልግስና የሚሰጥ እንደሆነ ይነግረናል።

ለዚህ የእግዚአብሔር ታላቅ ስጦታ የሰው ልጅ ለእግዚአብሔር ሊመልሰው የሚችለው አንዳች ነገር የለም። ሰጭው እግዚአብሔርም ስጦታውን ከተቀበለው ሰው ደግሞ በባርነት ቀንበር እንዳይያዝና ከህይወት እንዳይጎድል ደግሞም የጠላቱ ሽንገላ ሰለባ እንዳይሆን ይልቁንስ ከእርሱ ጋር መሰረቱ ፍቅር በሆነ ግንኙነት በዘላለም ደስታ ውስጥ አለመታዘዝን በመታዘዝ አሸንፎ መዳኑን እለት እለት እየፈጸመ ይኖር ዘንድ ብቻ እንጂ ከእርሱ ሌላ አንዳች ነገርን አይፈልግም። በዚህ ሁሉ የእግዚአብሔር በጎነት ውስጥ የሚታየው አላማው ፍቅር ብቻ ሲሆን ይህም ሰው የተደረገለትን አውቆ ህይወትም በእርሱ ዘንድ ብቻ እንዳለ ተረድቶ መኖሪያውን በአምላኩ በእግዚአብሔር ዘንድ እንዲያደርግ ነው።

የመለኮት ባህርይ ተካፋይ ልንሆን የተጠራን እኛም ከማይጠፋው ዘር ተወልደናልና በእርሱ ስንሆን ፍሬን ልናፈራ ተጠርተናል። ይህም ፍሬ እርሱ ራሱ እንደተመላለሰ መመላለስ ብሎም በልጁ በክርስቶስ ኢየሱስ ዘንድ በነበረ በዚያ ሃሳብ መውጣትና መግባት ነው። ለዚህም የእግዚአብሔር ቸርነት በእኛ ሁኔታ መገለጥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሉቃስ ወንጌል 14፡13-14 ላይ በጎነትን ከሰው ምላሽ ሳንጠብቅ መልሰው ሊያደርጉልን ለማይችሉ ሰዎች በማድረግ እርሱን እንመስል ዘንድ ያዘናል። ጳውሎስም በኤፌሶን 5፡1 ላይ ሲነግረን ከእግዚአብሔር እንደተለወለዱ ልጆች እግዚአብሔርን በመምሰል መኖር እንደሚገባን ያስታውሰናል። ይህም እግዚአብሔርን የመምሰል ምልልስ ራሱን የቻለ ሰፊ ሃሳብ ሲሆን፣ የመንፈስ ፍሬ ከሆነው ፍቅር የሚወጣው ቸርነት ግን አንዱ በእኛ ሊታይ የሚገባው ከእርሱ የተገኘን የመሆናችን ማሳያ የሆነ የእርሱ መልክ እንደሆነ እናውቃለን። ለዚህም ማሰሪያ ይሆን ዘንድ ጳውሎስ በሮሜ 12፡6 ላይ የእርሱ አካል የሆንን እኛ ብዙዎች ብልቶች እንደተሰጠን ስጦታ መጠን አንዳችን ሌላውን በፍጹም ፍቅር በመስጠትም እንድናገለግል ተናግሮ የሚሰጥም በልግስና ሊሰጥ እንደሚገባ ያስታውሳል።

## እግዚአብሔር ቸር ነው!

### ከእግዚአብሔር የተወለደም እርሱ ቸር እንደሆነ ቸር ሊሆን ያስፈልገዋል።

> “የቸርነቱ የመጨረሻው ማሳያ አለሙን ሊያድን ወድዶ ራሱን ይሄውም አንድያ ልጁን ለሀጢአተኛው ሰው አሳልፎ የሰጠበት በዚህም መንገድ የዘላለም ህይወትንና የመንግስቱ ወራሽነትን ለዚሁ በሀጢአት የተጨማለቀ ሞት የሚገባው ሰው የሰጠበት ስጦታ ነው።”

## ▪ የማስተንተኛ ጥያቄዎች

1. የእግዚአብሔር ቸርነት በሕይወትህ እንዴት ተገልጧል?
2. የእግዚአብሔር ልግስና ከሰዎች ጋር ስለምትኖርበት መንገድ ምን ያስተምርሃል?
3. በዚህ ሳምንት ለማን በተለይ ቸርነትና ልግስና ለማሳየት አስብሃል?

## ▪ አሰላስል

እግዚአብሔር ቸርና በጎ አድራጊ ነው። ምንም ሳይጠብቅ በብዛት የሚሰጥ፣ ፍቅሩንና በጎነቱን በጸጋ የሚያሳይ አምላክ ነው። ከሁሉ የሚበልጠው የእርሱ ስጦታ ግን ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ለእኛ መስጠቱ ነው፤ በእርሱም ሕይወትን፣ ጸጋንና የዘላለም ተስፋን ተቀብለናል። እኛም እንደ እርሱ ልጆች የእግዚአብሔርን ቸርነት በሌሎች ላይ በፍቅር፣ በአገልግሎትና በልግስና እንድናንጸባርቅ ተጠርተናል። ስለዚህ የተቀበልነውን በጎነት ለሌሎች በማካፈል የአባታችንን ባሕርይ ማሳየት እንደሚገባን ማስታወስ ያስፈልገናል።

## ▪ ጸሎት

*በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፣ ያለመታከት ስለምታደርግልኝ ቸርነትና ልግስናህ አመሰግንሃለሁ። ልቤን በርኅራኄ ሙላው፤ አንተ እንደወደድከኝ ሌሎችን እንዳፈቅር፣ እንዳገለግልና በልግስና እንድሰጥ እርዳኝ። ሕይወቴ በየቀኑ በጎነትህንና ፍቅርህን ለሌሎች የሚያሳይ ይሁን።*

*በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አሜን።*

## ▪ የአርምሞ ጥቅስ

*"ለገዛ ልጁ ያልራራለት ነገር ግን ስለ ሁላችን አሳልፎ የሰጠው ያው ከእርሱ ጋር ደግሞ ሁሉን ነገር እንዲያው እንዴት አይሰጠንም?*

*– ወደ ሮሜ ሰዎች 8፥32 –*

## 2.22. እግዚአብሔር መልካም ነው!

መልካም የሚለው ቃል አንዳች አወንታዊ ሁኔታን ለማየት የሚያገለግል ቃል ሲሆን ትርጓሜውም በጎ፣ ተቀባይነት ያለው ባህሪ፣ ለሰው ጥቅም የሚሆን፣ ተንኮልና ክፋት የሌለበት፣ የሚወደድ፣ ተስማሚ፣ ውሃ ልክ /መለኪያ/፣ ጥራት ያለው ወዘተ የሚል የአንድን ነገር ወይም ሁኔታ ተቀባይነት ማግኘት ብሎም ጉዳት አልባነት የሚገልጽ ቃል ነው። (ግዛው, 1994) (Merriam-Webster, n.d.) በእነዚህ ሁሉ ቃላት የተተነተነው ይህ መልካም የሚል ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ የመጀመሪያ ምዕራፍ ጀምሮ የተጠቀሰ ቃል ነው። ይህም በዋነኛነት የፍጥረቱ ሁሉ ፈጣሪ የሆነው እግዚአብሔር የፈጠረውን ሁሉ ተመልሶ ካየና ከገመገመ በኋላ የሚሰጠው የስራው መለኪያ ነበር።

የተፈጠረው ሁሉ በልቡና በሀሳቡ ካለው እንዲሆንለት ከወደደው ነገር ጋር የተስማማ በመሆኑ የሚናገረው ማስተካከያ የማያስፈልገው ስራውን ለመግለጽ የተጠቀመበት ጉድለት አልባ ቃል ነበር። በዚሁ የፍጥረት ስራው ግምገማ ወቅት የፈጠረውን ሁሉ መልካምነት የተመለከተ ሲሆን የሰው ብቻውን ሆኖ መታየት ብቻ ግን መልካም አልነበረም። ይህም እግዚአብሔርን ለሰው መልካም ይሆንለት ዘንድ የሚመቸውን ረዳት እንዲፈጥርለትና ጉድለቱን እንዲሞላለት በዚህም ማስተካከያ መልካም እንዲሆንለት አድርጎለታል።

በዚህ መሰረት የመልካም ነገር ሁሉ ምንጭ ራሱ ፈጣሪው እግዚአብሔር እንደሆነ ይታያል። ከዚህም በተጨማሪ የአንድ ነገር መልካም መሆን ወይም ደግሞ አለመሆን የሚወሰነው በራሱ በእግዚአብሔር እንደሆነም ደግሞ ይታያል። ይህም ብቻ አይደለም ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ በናሆም 1:7 ላይ እንደሚነግረን መልካም ራሱ እግዚአብሔር እንደሆነ ይታያል። ይህም የእግዚአብሔር መልካምነት ፍጹም የሆነ፣ ተንኮል አልባ፣ ከክፋትም የራቀ እንደሆነ የሚገልጥ ልዩ የእግዚአብሔር ባህሪ ነው። ከዚህም የተነሳ የየትኛውም አይነት በጎና መልካም ነገር ሁሉ ምንጩ ያዕቆብ በመጽሐፉ 1፡7 ላይ እንደሚነግረን ራሱ እግዚአብሔር ነው። ከዚህም በተጨማሪ በፍጥረት አለም

መካከል ያለን አንድ ነገር መልካም ነው ብሎ ለመወሰን ትክክለኛ መለኪያና ማስተያያው ይሄው መልካም የሆነው እግዚአብሔር በነገሩ ላይ ያለው ምልከታ ብቻ ነው።

እግዚአብሔር መልካም ነው ብለን ስንል በሁለንተና ልክ የሆነ ለሌሎችም በጎ እይታና እሳቤ ያለው፣ ተንኮል አልባ የሆነ በተግባርም የተገለጠ የሚታይ እውነት የሆነ ባህሪ አለው ማለታችን ነው። በዚህም መሰረት ምንጩ ከእግዚአብሔር ያልሆነ ማንኛውም በሰው ልጆች እይታ መልካም መስሎ የሚታይ ነገር ሁሉ ይልቁንስ ክፉ ነው ማለት ነው። ይህም እውነት በዋነኛነት በአዳምና ሔዋን ውድቀት ውስጥ ተገልጦ የሚታይ ነው። ይኸውም እንዳይበሉ የተነገራቸውን ፍሬ መብላታቸው መልካምና ክፉን መለየት እንዳስቻላቸው መገለፁ ነው። ይሁን እንጂ ከዚያ ወድያ የሰው ልጅ በአንድነት ከእግዚአብሔር ክብር የጎደለ፣ የልቡ ሃሳብ ክፉ የሆነ፣ ከመወለዱም ጀምሮ በሀጢአት የተወለደ፣ የልቡ ክፋት ከራሱ ከእግዚአብሔር በቀር ማንም ሊደርስበት የማይችል ጥልቅ፣ ብርሃንም የሌለው ድቅድቅ ጨለማ ሆነ።

ምንም እንኳን ሰው በራሱ ሚዛን መልካምና ክፉን መለያ የሰጣቸው ቢሆንም ልኬታቸው ግን ከአንድ ስፍራ ሌላ ስፍራ በሄድን ጊዜ የሚለያይ ሲሆን፣ እንዲሁ ከአንድ ሰው ሌላ ሰው ጋር መልካቸው የተለያየ ሲሆን ይታያል። ይህም ጌታችን ኢየሱስ ለዚያ መልካሙን ሁሉ ጠብቄያለሁ ብሎ በጽድቁ ለተኩራራው ባለጠጋ ሰውዬ እስከአሁን ያደረገው ነገር በመልካሙ እግዚአብሔር መለኪያ ሲታይ ብዙ የሚቀረው ከመልካምነት የራቀ ጎደሎ እንደሆነ በገለፀበት ስፍራ ላይ እንደተናገረው በእርግጥ ከአንዱ ከእግዚአብሔር በቀር ቸርና መልካም የሚባል ነገር የለም። ሁሉ ሀጢአትን ሰርቷል የእግዚአብሔር ክብርም ጎድሎታል በዚህም ከመልካም ነገር ሁሉ ጎድሏል።

የእግዚአብሔር መልካምነት በሰው ሚዛን የሚለካ ያልሆነ እርሱ ራሱ እግዚአብሔር በማይመረመር ማስተዋሉ ለሰው ልጆች እንዲሁም ለፍጥረቱ ሁሉ ከመጀመሪያው ጀምሮ ያለው ዘላለማዊ የሆነ በጎ ሃሳብ ነው። ነገር ግን ይህ ማለት ሰው አንድን ነገር መልካም ብሎ እንደሚለው ሁልጊዜ ለሰው የሚመች ላይሆን ይችላል። የእግዚአብሔር ፈቃድ በጎ፣ ፍጹምና ደስ የሚያሰኝ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። ይህ ማለት ግን የነገሩ በጎነትና መልካምነት ሰው ለዚያ ነገር ባለው እይታ የሚወሰን ነው ማለት አይደለም። ለምሳሌ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል መሞት የእግዚአብሔር

መልካም ሃሳብ ሲሆን ይህም በተቃራኒው በስጋው መከራን ለሚቀበለው ለኢየሱስ በሰው መመዘኛ መልካም የሚባል ነገር አልነበረም። የእስጢፋኖስ መወገር፣ የጳውሎስ መታሰርና በብዙ መከራ ወደ ቄሳር መወሰድ፣ በወህኒም መቆየት ወዘተ በሰው እይታ ምንም አይነት መልካም ነገር የማይታይባቸው ነገሮች ሲሆኑ በእግዚአብሔር ዘንድ ግን ለሰው ልጆች ጥቅም እንዲሆኑ በጥልቅ ማስተዋሉና መልካምነቱ ይሆኑ ዘንድ አስቀድሞ የወሰናቸው በጎና መልካም ሃሳቦች ነበሩ። ከሰው ጥበብ ይልቅ የእግዚአብሔር ሞኝነት እንዲጠበብ እናውቃለንና የዚህም የመልካምና ክፉ ነገር ልኬታና ስፍር ልዩነት እንዲሁ በእግዚአብሔር እይታ የሚወሰን ነው።

> "የእግዚአብሔር መልካምነት በሰው ሚዛን የሚለካ ያልሆነ እርሱ ራሱ እግዚአብሔር በማይመረመር ማስተዋሉ ለሰው ልጆች እንዲሁም ለፍጥረቱ ሁሉ ከመጀመሪያው ጀምሮ ያለው ዘላለማዊ የሆነ በጎ ሃሳብ ነው።"

እግዚአብሔር ለሚያመሰግኑትም ለማያመሰግኑትም ዝናብና ፀሃይን የምድርንም ፍሬ በየጊዜው ሳያጓድል ይሰጣል። ለሰው ልጆች በሚገባቸውም በማይገባቸውም ሁኔታ እግዚአብሔር በፍጥረቱ መካከል የሚገልጣቸው ነገሮች ሁሉ ለሰው ልጆች ጥቅም የሚያደርጋቸው የእግዚአብሔር መልካምነት ማሳያዎች ናቸው። ክፉ በሚመስል የጽኑ ክንዱ መገለጥ ውስጥ እንኳን የእግዚአብሔር የልብ ሃሳብ የሰው ልጆች ከጥፋት መመለስና እርሱን በማወቅ በህይወት ጎዳና መራመድ እንጂ የሰው ልጆችን ማጥፋት አይደለም። ማንም ሳያስገድደው ለአዳምና ለዘሩ ሁሉ ያደረገው ርህራሄ፣ ለዚህም መልካምነቱ የመጨረሻ ማሳያ የሆነው የአንድያ ልጁ ለጠላቶቹ በመስቀል ላይ መሞት ሌላ አባሪን የማይፈልግ ፍጹም የሆነ የእግዚአብሔር መልካምነት ማስረጃ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በመዝሙረ ዳዊት ምዕራፍ ፻፲፱፡፷፰ ላይ እንደሚናገረው *"እግዚአብሔር መልካም ነው ስራውም ሁሉ መልካም ነው።"*

ምህረቱ፣ ርህራሄው፣ አቅርቦቱ፣ ቸርነቱ፣ ስጦታው፣ ትዕግስቱ ወዘተ በየቀኑ እግዚአብሔር ምን ያክል መልካም እንደሆነ ይነግሩናል። ሁሉ አንዲድን እንጂ አንድ

እንኳን እንዳይጠፋ ያለው ሃሳብ ለዚህም ማሳያ ይሆን ዘንድ ዘጠና ዘጠኙን በሜዳ ትቶ አንዷን የጠፋችውን ፍለጋ የሚሄደው ርቀት የእግዚአብሔር የመልካምነት ማስረጃ ነው። እስከዛሬ ድረስ በአለም ላይ ያለውን ጥፋትና ርኩሰት ሁሉ የታገሰው፣ ሁሉ ወደ ንስሃ እንዲደርሱ መሆኑ፣ የሰው ልጅ ዋና የመምጣቱ ጉዳይም የጠፋውን ሊፈልግና ሊያድን መሆኑ የመጨረሻው ፍጹም የሆነ የእግዚአብሔር መልካምነት ማሳያ ነው።

ለማያመሰግኑት ጭምር በዚህ ልክ የተገለጠው የእግዚአብሔር መልካምነት ለሚወዱት አንደ አሳቡም ለተጠሩት ደግሞም ለሚፈሩት ምርጦቹማ ምን ያክል ይልቅ የበዛ እንደሆነ መገመት ይቻላል። ለዚህም ጥሩ ማሳያ የሚሆነው የእግዚአብሔርን ተደጋጋሚ ተግሳጽ ባለመስማት በልብ ድንዳኔ ለጠላቶቹ ታልፎ ተሰጥቶ በምርኮ ሃገር ለሚገኘው ህዝቡ በኤርሚያስ 29:1 ላይ *"ለእናንተ የማስባትን ሃሳብ እኔ አውቃለሁ፣ ፍፃሜና ተስፋን እሰጣችሁ ዘንድ የሰላም ሃሳብ ናት እንጂ የክፉ ነገር አይደለችም"* ብሎ የገለጠው የፍቅር ቃሉ ነው። በምርኮ አገር ላለው ቃሉን ጠብቆ ሊኖር በተዘጋጀ ህዝብ መካከል በማይመስል ሁኔታ ውስጥ እንኳን እግዚአብሔር ፈጽሞ ክፉ ነገር የማያውቀው በመልካም ሃሳብ የተሞላ የሰላም አምላክ እንደሆነ ታያላችሁ።

የትኛውንም ያክል ጊዜ በሰው ልጆች እይታ እግዚአብሔር ፍጹም ጨካኝና ክፉ እስኪመስል ድረስ በእርሱ ዝምታ ውስጥ የሚወዱት ልጆቹ እንኳን ሲያልፉ ይታዩ እንጂ መጽሐፍ ቅዱስ በሮሜ 8:28 እንዲሁም በመዝሙረ ዳዊት ምዕራፍ 54:11 እንዲሁም ሌሎች እልፍ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ውስጥ እነዚህ ልጆቹ እንዲያልፉባቸው ፈቅዶ የሚያልፉባቸው መንገዶች ሁሉ በእርሱ ዘንድ የታወቁ ተደምረውም ለበጎ እንዲሆኑ የተደረጉ እንደሆኑ መመልከት ይቻላል። ይሁን እንጂ በዚህ ሁሉ ውስጥ መልካም የሚለው ቃል የሚተረጎመው አንድ ሰው እያለፈ ካለበት ሁኔታ አንጻር ሳይሆን እግዚአብሔር በማይመረመር ማስተዋሉ ውስጥ ያንን ሰው በበጎ

> "መልካም የሚለው ቃል የሚተረጎመው አንድ ሰው እያለፈ ካለበት ሁኔታ አንጻር ሳይሆን እግዚአብሔር በማይመረመር ማስተዋሉ ውስጥ ያንን ሰው በበጎ ሃሳቡ በዚያ እንዲያልፍ ከፈቀደበት መልካምነት አንጻር ብቻ ነው።"

ሃሳቡ በዚያ እንዲያልፍ ከፈቀደበት መልካምነት አንጻር ብቻ ነው።

አንድ ሰው ከእግዚአብሔር መልካምነት እና አምላኩ ለሰውየው ካለው በጎ ሀሳብ መነሻ ምክንያት በሰውኛ እጅግ ከባድ በሆነ ከመልካም የራቀ የሚመስል እግዚአብሔርን ክፉ አምላክ እንደሆነ የሚያስመስል ከባድ የህይወት መንገድ ሊሄድ ይችላል። ነገር ግን በዚህ ሁሉ ውስጥ እግዚአብሔር ማንነቱ ነውና ያው መልካም ነው። የእግዚአብሔር መልካምነት ክፉ የሚመስሉ ጊዜያት ካለፉ ወዲያ በግልጥ የሚታይ በዚያ ያለፈውን ሰው እንኳን ሆነ የሚያስብል ለአምላኩ ያለውንም ፍቅር የበለጠ እንዲጨምርና ወደ እርሱ ይበልጥ እንዲጠጋና እምነቱ እንዲያድግ የሚያደርግ ነው።

ይህ የእግዚአብሔር መልካምነት ፍጹም በሆነ ትብብር ከሌሎች ባህርይዎቹ ጋር ተስማምቶ የሚገለጥ ነው እንጂ እግዚአብሔርን ሞኝ እንደሆነና ማንም ተነስቶ ሊዘብትበት እንዲችል የሚፈቅድ ማንነት ግን አይደለም። እግዚአብሔር ከመልካምነቱ ሳይጎድል ቀናተኛና ተበቃይ አምላክም ነው። የእግዚአብሔር ጽድቅ፣ ቅድስና፣ ሉአላዊ ስልጣኑ ወዘተ ከታላቅነቱ፣ ከኃይሉና ከመልካምነቱ ጋር አብረው ከመልካምነቱ ጋር ተስማምተው የሚገለጡ ናቸው። የእግዚአብሔር መልካምነት ሀጢአተኛውን ስለ ሀጢአቱ ተጠያቂ ከመሆን የሚያስቀርና ከሌሎቹ ባሕሪያቱ ጋር የሚጻረር አይደለም፤ ነገር ግን ጽድቅና ፍርድን ተግባራዊ እንዲያደርግም ጭምር የሚያስገድዱት ናቸው። እግዚአብሔር በፃድቅ ፈራጅነቱ የሚፈርደው ፍርድ ፍጹምነቱን ይበልጥ የሚገልጥ እንጂ መልካምነቱን የሚያስቀር አይደለም።

> "እግዚአብሔር በፃድቅ ፈራጅነቱ የሚፈርደው ፍርድ ፍጹምነቱን ይበልጥ የሚገልጥ እንጂ መልካምነቱን የሚያስቀር አይደለም።"

*"እግዚብሔር መልካም ነው"* የሚለው ንግግር በስፋት የሚታወቅበት የናሆም የትንቢት መጽሐፍ እግዚአብሔር አንዳች ፍርድን ከዚህ በፊት መልካምነቱን በገለጠላት የአህዛብ ከተማ ላይ ሊገልጥ ባለበት በቅናቱ ምክንያት በቀልን ሊበቀል ለሀጢአትም የተገባን ምላሽ ሊሰጥ በተጻፈበት ምንባብ ውስጥ በዚህ መካከል ለሚገኙና የእርሱ ለሆኑት ምርጦቹ በመከራ ጊዜ ጭምር የሚሸሽጋቸው፣ በሚያልፉበት አስቸጋሪ ሁኔታ ሁሉ ውስጥ በመልካምነቱ የሚጠብቃቸው እንደሆነ የተገለጠበት ስፍራ ነው። *"እግዚአብሔርን*

> “በየትኛውም አይነት ሁኔታ ውስጥ ሰው በሚያልፍበት ጊዜ የእግዚአብሔር መልካምነት የማይለወጥ የእርሱ ባህሪ እንደሆነ ያውቅ ዘንድ ያስፈልገዋል።”

*ለሚወዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን።”* በየትኛውም አይነት ሁኔታ ውስጥ ሰው በሚያልፍበት ጊዜ የእግዚአብሔር መልካምነት የማይለወጥ የእርሱ ባህሪ እንደሆነ ያውቅ ዘንድ ያስፈልገዋል። ይሁን እንጂ ይህ መልካምነቱ እርሱን የበለጠ እንወደው፣ እናከብረውና እንፈራው ዘንድ እንጂ ፍርድና በቀሉን ረስተን እንድንታበይበት ሊያደርገን አይገባም።

> “የእግዚአብሔር መልካምነት ፍጹም በሆነ ትብብር ከሌሎች ባህርይዎቹ ጋር ተስማምቶ የሚገለጥ ነው እንጅ እግዚአብሔርን ሞኝ እንደሆነና ማንም ተነስቶ ሊዘብትበት እንዲችል የሚፈቅድ ማንነት ግን አይደለም።”

## የማስተንተኛ ጥያቄዎች

1. የእግዚአብሔር መልካምነት ስለ ማንነቱ ባለህ ግንዛቤ ላይ ምን ጨምሮልሃል?
2. ሁኔታዎችን መረዳት በሚያስቸግርበት ጊዜ በእግዚአብሔር በጎነት እንዴት መታመን ትችላለህ?
3. ዛሬ የእግዚአብሔርን መልካምነት ለሌሎች ለማሳየት ምን ልታደርግ አስበሃል?

## አሰላስል

እግዚአብሔር መልካም ነው፤ የሚያደርገው ሁሉ ከፍጹም በጎነቱ የሚፈልቅ ነው። ይሄው መልካምነቱ በፍጥረቱ፣ በምሕረቱ፣ በትዕግሥቱና ከሁሉ በላይ በኢየሱስ ክርስቶስ ውስጥ በግልጽ ተገልጧል። የእርሱ መንገዶች አንዳንድ ጊዜ ከእኛ ግንዛቤ በላይ ሊሆኑ ቢችሉም፣ ዓላማዎቹ ሁልጊዜ መልካምና በጎ እንደሆኑ ልንታመን እንችላለን። እግዚአብሔር ደግ ስለሆነ በሁሉም ሁኔታ ውስጥ እጁን ለመመልከትና በእርሱ ላይ ለመታመን እንችላለን። ስለዚህ ይህን መልካም አምላክ በመታመን የእርሱን በጎነት በሕይወታችን ለሌሎች ማሳየት እንደሚገባን ልናስታውስ ያስፈልገናል።

## ጸሎት

በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፣ በማይለወጥ ሁኔታ ፍጹም መልካም ስለሆነህ እናመሰግንሃለን። በአስቸጋሪ ወቅቶች እንኳን ዓላማህን እንድታመንና በሁሉም ሁኔታ ውስጥ የፍቅርህን እጅ እንዳስተውል እርዳኝ። በጎነትህን ለሌሎች እንዳንጸባርቅ አስተምረኝ፤ ቃሌ፣ ሥራዬና አመለካከቴ የአንተን ባሕርይ እንዲያሳይ አግዘኝ።

በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አሜን።

## የአርምሞ ጥቅስ

*“እግዚአብሔር መልካም ነው፥ በመከራ ቀንም መሸሸጊያ ነው፤ በእርሱ የሚታመኑትንም ያውቃል።”*

*– ትንቢተ ናሆም 1፥7 –*

## 2.23. እግዚአብሔር ፍቅር ነው!

ከዚህ በፊት በተገለፁት የእግዚአብሔር ባህርያት ሁሉ ውስጥ በስፋት እንዳየነው ለእያንዳንዱ ባህርይ አለም ያዘጋጀቻቸው ለዚያ ቃል የሚሆኑ ፍቺዎች ያሉ ሲሆን በእያንዳንዱ ሁኔታ ውስጥ ግን የእግዚአብሔር እይታና ለዚያ ቃል ያለው ፍች ፈጽሞ የተለየ እንደሆነ ይታያል። በዚህም መሰረት የነገር ሁሉ ባለቤትና ፈጣሪ እርሱ እግዚአብሔር ነውና ለየትኛውም ነገር ማሰሪያው የነገሩ ባለቤት የሆነው እግዚአብሔር በዚያ ጉዳይ ላይ ያለው አቋም ነው። ፍቅር፣ አለም አንፃራዊ ነው እንዳለችው እውነት እንዲሁ በሰው ልጆች መካከል በርካታ ትርጉም የተሰጠው ቃል ነው። በተለይም በግሪካዊያን ዘንድ ሶስት በተለየ መልኩ ለቃሉ አቻ ትርጓሜ ያላቸው በዋናነት የሚጠቀሱ ቃላት ያሏቸው ሲሆን እነዚህም "ኤሮስ"፣ "ፊሊያ" እና "አጋፔ" የሚሉ ናቸው። (Danker, 2000)

"ኤሮስ" የሚለው በጾታዊ ግንኙነት ላይ የተመሰረተ ስሜታዊ ፍቅርን ለመግለጽ የሚያገለግል ሲሆን ሁለተኛውና "ፊሊያ" የሚለው ደግሞ ጥልቅ በሆነ መተማመን ላይ የተመሰረተና ለጋራ በሚሆን ጥቅም ላይ የተገነባ አንዱ ሌላውን እንዲጠቅም ታስቦ እርስ በእርስ መጠቃቀምን ለማሳየት ታቅዶ የተገነባን ፍቅር ለመግለጽ የሚያገለግል ነው። ሌላኛውና ሶስተኛውም "አጋፔ" የሚለው ፍቅር ሲሆን ይህም የራስን ጥቅም በመተውና ሌላን ሰው በመጥቀም ላይ የተመሰረተ ለመውደድ ቅድመ ሁኔታን የማይፈልግ ለፍቅሩ ምላሽ እንኳን ባይኖረው አንዱ ሌላውን ራሱን እስከ መስጠት ድረስ በደረሰ መስዋዕትነት ጭምር የሚወድበት ታላቅ ፍቅር ነው። በዚህም መሰረት የመጀመሪያዎቹን ሁለቱን በየሰው ቤት በቀላሉ የምናገኛቸው ሲሆን ሶስተኛው ግን ከፍጥረቱ ክፉና ራስ ወዳድ በሆነው የሰው ልጅ መካከል ፈጽሞ ሊገኝ የማይችል አስደናቂ ፍቅር ነው። (Danker, 2000)

መጽሐፍ ቅዱስ የፍቅር ትክክለኛ ፍች ራሱ እግዚአብሔር እንደሆነ በ1ኛ ዮሐንስ 4፡16 ላይ በግልጽ ይነግረናል። ከዚህም በተጨማሪ እውነተኛ የሆነ ፍቅር እግዚአብሔር እኛን የወደደበት ይሄው "አጋፔ" ፍቅር እንደሆነ ይታያል። ይህም በመጽሐፍ ቅዱስ በ1ኛ ዮሐንስ 4፡10 ላይ በግልጽ እንደተጻፈው፣ ፍቅር እግዚአብሔር እርሱ ራሱ እንደ ወደደን ስለ

ሀጢአታችንም ማስተሰረያ ይሆን ዘንድ ልጁን እንደላከ እንጂ እኛ በምላሹ ስለተደረገልን ውለታ እግዚአብሔርን እንደ ወደድነው አይደለም።

ይህም አይነት ፍቅር ከላይ በቃላት ፍችው ውስጥ በሶስተኛነት የተገለጸው አይነት "አጋፔ" ፍቅር ሲሆን ይኸውም ሊወደድ የማይገባውን አካል ሌላኛው ወዳጅ ዋጋ ጭምር ከፍሎ በመስዋትነት ውስጥ አልፎ ሌላን ሰው መውደድ ነው። ለዚህም ማረጋገጫ መጽሐፍ ቅዱስ በሮሜ 5፡8 ላይ እንደሚናገረው ገና ሀጢአተኞች እና ጠላቶች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ በመሞቱ እግዚአብሔር ስለ እኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል የሚለው ቃል ነው። ታዲያ በዚህ ልክ የተገለጠ "አጋፔ" የሆነ ነፍሱን ስለ ወዳጆቹ ከመስጠት ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ታላቅ ፍቅር ከእግዚአብሔር በቀር ለሌላ ለማንም የለውም። *"በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ህይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ አለሙን እንዲሁ ወዶአልና።"*

ይህ እግዚአብሔር የሰውን ልጅ የወደደበት ፍቅር በሌላ በማንም ዘንድ የሌለ እግዚአብሔር ያለውን አንድ ልጁን ለመስቀል ሞት አሳልፎ በመስጠቱ የተገለጠ ታላቅ ፍቅር ነው። በዚህም መልኩ ሰውን የወደደው እግዚአብሔር ይህንኑ አንድያ ልጁን በወደደበት በዚያው መጠን እኛን ደግሞ የወደደበት ድንቅ ፍቅር ነው። ይህንኑ እግዚአብሔር አብ ልጁን ወልድን የወደደበትን ፍቅር መረዳት እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ያለውን ጥልቅ ፍቅር በሚገባ ለመረዳት በእጅጉ ያግዛል።

"እግዚአብሔር የሰውን ልጅ የወደደበት ፍቅር በሌላ በማንም ዘንድ የሌለ እግዚአብሔር ያለውን አንድ ልጁን ለመስቀል ሞት አሳልፎ በመስጠቱ የተገለጠ ታላቅ ፍቅር ነው።"

ይህም በአባትና በልጁ መካከል ያለ ፍቅር ጊዜና ቦታ የሚባለው ነገር ሳይኖር በፊት ልጁ በአባቱ እቅፍ በነበረበት ዘመን ሁሉ የነበረ ያለና የሚኖር ያልተለወጠ ድንቅ ፍቅር ነው። ይሄው የአባትና የልጅ ፍቅር ፍጹም የሆነ ታላቅ ፍቅር ሲሆን መጽሐፍ ቅዱስ በዮሐንስ 3፡35 ላይ እንደሚናገረው አባት ልጁን በመወደዱ ያለውን ሁሉ ደግሞ ለልጁ የሰጠበት ታላቅ ፍቅር ነው። ከዚህም በተጨማሪ በፍጹም ግልጽነት ላይ የተመሰረተ

አንዱን ከሌላው ነጥሎ ማየትና ማወቅ እስከማይቻል ድረስ የተገለጠ አንዳቸውን በማየት ውስጥ ሌላኛውን የምናይበት እርስ በእርስ ፈጽሞ የተዋሃደ ፍቅር ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በዮሐንስ ወንጌል 5፥20 ላይ እንደሚናገረው *"አብ ወልድን ይወዳል የሚያደርገውንም ሁሉ ያሳየዋል"* ብሎ ይናገራል። ከዚህም ወዲያ እኛ የሰው ልጆች ደግሞ የተወደድንበትን ፍቅር በመካከላችን የተገኘው ልጁ ሲያስረዳን ከአባቱ የሰማውን ሁሉ ለእኛ የገለጠበት የተሰጠውንም ክብር ሁሉ ለእኛ ደግሞ የሰጠበት አባቱ እርሱን በወደደበት በዚያው ፍቅር የተወደድን ወዳጆች አልፎም አባቱ ለልጁ ሁሉን እንደሰጠውና ወራሽ እንዳደረገው አብረን ወራሾች እንድንሆን ያደረገን እንደሆነ ይናገራል።

*ሶ ምን አይነት ታላቅ ፍቅር ነው?*

በዚህ መልኩም የወደዳቸውን በዚህ አለም ያሉትን ወገኖቹን እስከ መጨረሻ ወደዳቸው ብሎ የፍቅሩን ጥግ ያስረዳል።

ይሄው በዚህ ልክ የተገለጠው ገና ፈጽሞ እንደሚገባ ያልተረዳነው እግዚአብሔር እኛን የወደደበት ታላቅ ፍቅር ከተወደድነው ከእኛ ለመወደድ የሚሆን ምንም መነሻ ምክንያት በሌለበትና ይልቁንስ ጠላቶቹ በነበርንበት ጊዜ እርሱ ራሱ ፍቅር ስለሆነ ከወደደን ከታላቅ ፍቅሩ የተነሳ በምህረቱ ባለጠጋም ስለሆነ የተገለጠ እኛም ጋር የደረሰ ፍቅር ነው። ይህ ፍቅር እጅግ ጥልቅ እና ሰፊ ከመሆኑ የተነሳ ስፋቱና ርዝመቱ፣ ከፍታውም ጥልቅቱም ምን ያህል መሆኑን ለማስተዋል ያለ እግዚአብሔር እርዳታ ፈጽሞ የማይቻል ነው። አሁንም እንኳን ያወቅነውን በውስጥ ሰውነታችን በቋንቋ መግለጽ በማንችለው ሁኔታ በልባችን በመንፈሱ በኩል የፈሰሰው ፍቅሩ ከመረዳትና ከማስረዳት እጅግ የሚያልፍ ታላቅ ነው።

እግዚአብሔር ይህንን ሁሉ ታላቅ ፍቅር ለማይገባው፣ ባለመታዘዙ ለወደቀ ሰው ለመግለጥ የሚያስገድደው የእርሱ የራሱ አፍቃሪነት ብቻ ካልሆነ በስተቀር ሌላ አንዳች መነሻ ምክንያት የለውም። እግዚአብሔር ለእስራኤል በዘዳግም 7:6-8 ላይ እንደተናገራት በዙሪያዋ ካሉ አህዛብ መካከል የተለየ ቅድመ ሁኔታን አሟልታ በእርሱ እንዳልተመረጠች ነገር ግን በገዛ ራሱ ተነሳሽነት እንደተወደደች እንደነገራት እኛም ዛሬ እርሱ የመረጠን እንጂ እኛ የመረጥነው እንዳልሆንን መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ የእኛም ልብ አስረግጦ ይነግረናል።

ይህ የእግዚአብሔር ታላቅ ፍቅር ዘላለማዊ የሆነ ፍቅር ሲሆን ይኸውም ገና “ከመጀመሪያው” ፈጽሞ በተዋደደ አንድነት ውስጥ በሚገኙት የግጻዌ መለኮት አባላት መካከል የነበረ ፍቅር ነው። አብ ወልድን ይወዳል ሁሉን በእጁ ሰጥቶታል፣ ወልድ አባቱን ይወዳል በሁለንተና ለእርሱ የሚገዛና ፈቃዱን የሚያደርግ የታዘዘም ነው፣ ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ወልድን ይወዳል ያከብረዋል ስለ እርሱ ደጋግሞ ያስረዳል ሁሉንም ወደ እርሱ ይመራል። ታዲያ በዚሁ ልክ አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ እንደሚዋደዱ እንዲሁ ያመንንና የእግዚአብሔር ቤተሰብ ለመሆን እድል ያገኘን ሁላችን በዚሁ ታላቅ ፍቅር እንድንመላለስ ይፈለግብናል።

> “አብ ወልድን ይወዳል ሁሉን በእጁ ሰጥቶታል፣ ወልድ አባቱን ይወዳል በሁለንተና ለእርሱ የሚገዛና ፈቃዱን የሚያደርግ የታዘዘም ነው፣ ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ወልድን ይወዳል ያከብረዋል ስለ እርሱ ደጋግሞ ያስረዳል ሁሉንም ወደ እርሱ ይመራል።”

በዚህ ቤተሰብ ውስጥ ከፍቅርና ከብርሃን በስተቀር ጥላቻና ጨለማ ፈጽሞ ስፍራ የሌላቸው ሲሆን በዚህ መንግስት ውስጥ ነዋሪ ለመሆን እድል ያገኙ የእግዚአብሔር ቤተሰቦች ሁሉ በዚሁ ብርሃንና ፍቅር የመመላለስ ግዴታም ደግሞ አለባቸው። ነገር ግን በብርሃን አለሁ የሚል ወንድሙንም የሚጠላ እስከ አሁን በጨለማ እንዳለ መጽሐፍ ቅዱስ በ፩ኛ ዮሐንስ 2፡9 ላይ በግልጽ ይነግረናል። ደግሞም በ፩ኛ ዮሐንስ 4፡20 ላይ ጨምሮ እንደሚነግረን ማንም እግዚአብሔርን እወዳለሁ እያለ ወንድሙን ቢጠላ ሐሰተኛ ነው፣ ያየውን ወንድሙን የማይወድ ያላየውን እግዚአብሔር ሊወደው እንዴት ይችላል ብሎ በዚህ ፍቅር የመመላለስ ግዴታችንን ያስተውቀናል።

አብ ልጁን እንደሚወድ ወልድ ደግሞ እኛን እንደወደደን በዚህም አብ ደግሞ አንድ ልጁን በወደደበት ዘላለማዊ ፍቅር እንዲሁ እኛን ሁላችንን እንደወደደን እርስ በእርሳችን ፍጹም በሆነ ግብዝነት የሌለበት ፍቅር እንድንዋደድ ያስፈልገናል።

*“የእግዚአብሔር ልጆች ተብለን ልንጠራ አብ እንዴት ያለውን ፍቅር እንደ ሰጠን እዩ እንዲሁም ነን፤ በዚህም እርሱን እንድንመስል እናውቃለን”* ብሎ በ፩ኛ ዮሐንስ 3፡1 ላይ

መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል። በዚህም ልጁ በብዙ ወንድሞች መካከል በኩር ይሆን ዘንድ አብ አስቀድሞ ያወቃቸውን እነርሱ ደግሞ ደስ የሚሰኝበትንና የሚወደውን ልጁን እንዲመስሉ አስቀድሞ ወስኗል። በዚህም መሰረት በዚህ ታላቅ የፍቅር ግንኙነት የእግዚአብሔር ልጆች ለመሆን እድል ያገኙ ሁሉ እርሱ እንደተመላለሰ፣ እንደወደደና እንዳሰበ እነርሱ ደግሞ እንዲመላለሱ፣ እንዲወዱና በዚያው በእርሱ ዘንድ በነበረ ሃሳብ እንዲገኙ ይጠበቅባቸዋል።

ከዚህ በተቃራኒው የእግዚአብሔር ልጆች ነን ብለው በጨለማ፣ በጥላቻ በአመጽም የሚመላለሱ እነርሱ መጽሐፍ ቅዱስ በዮሐንስ ወንጌል 8፡44 ላይ እንደሚናገረው የአባታቸውን ምኞት ሊያደርጉ ይወዳሉና እነርሱ የአባታቸው የዲያብሎስ ልጆች ናቸው እንጂ ፍቅር የሆነው የእግዚአብሔር አይደሉም። መጽሐፍ ቅዱስ በ1ኛ ዮሐንስ መልዕክት 3፡10 ላይ በግልጽ እንደሚናገረው የእግዚአብሔር ልጆችና የዲያብሎስ ልጆች በዚህ የተገለጡ ናቸው፣ ጽድቅን የማያደርግና ወንድሙን የማይወድ ሁሉ ከእግዚአብሔር አይደለም። ጌታችንም ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴዎስ ወንጌል 7 ላይ እንደነገረን ከእግዚአብሔር የሆኑቱ በፍሬያቸው የሚታወቁ ናቸው።

ከዚህ ሁሉ የእግዚአብሔር ፍቅር መገለጥ በኋላ አንድ እግዚአብሔር ስለወደደው እግዚአብሔርን የሚወድ ሰው ትዕዛዙ በእርሱ ዘንድ ይኖረውና ይጠብቃት ዘንድ ህጉ ሁሉ በፍቅር ተጠቅልሎ ተሰጥቶታል። ይህም ህግንና ነብያትን ሁሉ አንድ ላይ በመሰብሰብ የተገለጠ ታላቅ ትዕዛዝ ሲሆን እነዚሁም እግዚአብሔር አምላክን በፍጹም ነፍስ፣ በፍጹም ልብ፣ በፍጹም ሃሳብና፣ በፍጹም ኃይል መውደድ ብሎም ወንድምን እንደ ራስ የመውደድ የእርስ በእርስ ፍቅር ትዕዛዛት ናቸው። በዚህም መሰረት መጽሐፍ ቅዱስ በ1ኛ ዮሐንስ መልዕክት 3፡16 ላይ እንደሚነግረን ወንድምን መውደድ ከስሜት ያለፈ በተግባር የተገለጠ ይሆን ዘንድ እርሱ ስለ እኛ ነፍሱን አሳልፎ እንደሰጠ በዚህም ፍቅርን እንዳወቅን እኛም በዚሁ ፈለግ ተከትለን ስለ ወንድሞቻችን ነፍሳችንን አሳልፈን እንድንሰጥ ይገባናል። እምነት፣ ተስፋና ፍቅር እነዚህ ሶስቱ ፀንተው የሚኖሩ ሲሆኑ የሚበልጥ መንገድ የሆነው ፍቅር ግን ከሁሉ የበላይ ነው። በዚህ ፍቅር የተነካ ሰው በየትኛውም አይነት የመንፈሳዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ቢገኝ ብዙ የጸጋ ስጦታም በእርሱ ቢገለጥ ፍቅር ግን ከሌለው እርሱ ሰው እንዲሁ በከንቱ የደከመ የከሰረም ምስኪን ብቻ ነው።

“በዚህ ፍቅር የተነካ ሰው በየትኛውም አይነት የመንፈሳዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ቢገኝ ብዙ የጸጋ ስጦታም በእርሱ ቢገለጥ ፍቅር ግን ከሌለው እርሱ ሰው እንዲሁ በከንቱ የደከመ የከሰረም ምስኪን ብቻ ነው።”

”

- **የማስተንተኛ ጥያቄዎች**

1. በክርስቶስ የተገለጠው የእግዚአብሔር ፍቅር ስለ እውነተኛ ፍቅር ያለህን ግንዛቤ እንዴት ይለውጠዋል?
2. እግዚአብሔር እንደወደደህ ሌሎችን መውደድ ምን ማለት ነው?
3. ዛሬ የክርስቶስን ዓይነት ፍቅር ሊታሳየው የሚያስፈልግህ አንድ ሰው አለ?

- **አሰላስል**

እግዚአብሔር ፍቅር ነው፤ ፍቅሩም ፍጹምና የማይለወጥ ነው። ይህ ፍቅር ከሁሉ በላይ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ተገልጧል። እኛ ልንወደድ የማይገባን ሆነን ሳለ ወደደን፤ የእርሱንም ፍቅርና ጸጋ ከፍተኛ መግለጫ የሆነውን አንድ ልጁን ሰጠን። እንዲህ ያለውን ታላቅ ፍቅር ከተቀበልን በኋላ፣ እኛም እግዚአብሔርንና ሰዎችን ራስ ወዳድ ባልሆነ ፍቅር እንድንወድ ተጠርተናል። እውነተኛ ፍቅር በቃል ብቻ ሳይሆን በመስጠት፣ በይቅርታና ራስን መስዋዕት በማድረግ እንደሚገለጥ እናስታውስ።

- **ጸሎት**

በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፣ በዘላለም ፍቅርህ ስለወደድኸኝ አመሰግንሃለሁ። የፍቅርህን ጥልቀት እንዳስተውልና በሌሎች ላይ እንዳንጸባርቀው እርዳኝ። በመስዋዕታዊ ፍቅር እንድወድ፣ በነጻ ይቅር እንድልና በክርስቶስ የፍቅር መንገድ እንድመላለስ እርዳኝ። ሕይወቴ የተቀበልኩትን ፍቅርህን ለሌሎች የሚያሳይ ይሁን።

በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አሜን።

- **የአርምሞ ጥቅስ**

*እግዚአብሔር ፍቅር ነው፥ በፍቅርም የሚኖር በእግዚአብሔር ይኖራል እግዚአብሔርም በእርሱ ይኖራል።*

*— 1ኛ የዮሐንስ መልእክት 4፥16 —*

## 2.24. እግዚአብሔር መሐሪ ነው!

ምህረት አንድ በደል የደረሰበት አካል የበደለውን በዳይ ያለ ተገቢ ተመጣጣኝ የእርምት እርምጃና ቅጣት የሚተውበት ሁኔታ ነው። ይህም በዋናነት በተበደለው አካል የራስ ተነሳሽነት የሚከናወን የተደረገበትንና የደረሰበትን በደል አልፎ ለጥፋቱ የሚገባውን ቅጣት ትቶ በነጻ ወይም ተመጣጣኝ ባልሆነ ከሚገባው ባነሰ ቅጣት ነገሩን የሚቋጭበት ሁኔታ ነው።

ይህ ምህረት ትክክል ይሆን ዘንድ ተበዳይ በዳይን ለጥፋቱ ተገቢ የሆነ ቅጣትን መቅጣት የሚችልበት ወይም ደግሞ በሌላ አካል እንዲቀጣ ማድረግ የሚቻልበት አቅም እና ብቃት እንዲኖረው ያስፈልገዋል። ይህም ምንም እንኳን የተበደለው አካል የበደለውን በተገቢው ሁኔታ ለጥፋቱ የሚመጥን አፀፋዊ ምላሽን መስጠት የሚችልበት ማንነትና ቁመና ያለው ቢሆንም ያንን ኃይሉን ለክፋት በመጠቀም ፋንታ ክፉውን በመልካም ለማሸነፍ በዳይን ያለ ተገቢ ቅጣት የሚተውበትን ሁኔታ የሚፈጥር ነው። (ግዛው, 1994) (Merriam-Webster, n.d.) ታዲያ እንዲህ አይነቱን የበደለውን አስፈላጊውን ተመጣጣኝ የሆነ ቅጣት መቅጣት ከሚችል አካል ለተበዳይ የሚደረግ ርህራሄና ይቅርታ ከበደልም ነጻ የማድረግ ሂደት እርሱ ምህረት ይባላል።

ይህ ምህረት እውነተኛና ሙሉ ለመሆን በዳይን ይቅር ከማለት የሚያልፍ ተበዳይ አብሮ ሊያሳየው የሚገባ ከልብ የሆነ ፍጹም ርህራሄ፣ ቅንነት፣ ፍቅር ብሎም መልካም ፊት (ማቅረብ) እና እንክብካቤ አብሮ ደግሞ እንዲኖረው ያስፈልገዋል። ተበዳይ በደሉን ደግሞ ላያስበው ላያነሳው ለነገሩ የመጨረሻ ፍፃሜ የሚሰጥበት ሁኔታውንም እንደ አለፈ ውሃ ደግሞም ሊገኝ እንደማይችል ከውስጡ ፈጽሞ የሚረሳበትን ልብ አብሮ ሊገልጥ ያስፈልገዋል። ለእንዲህ አይነቱም እውነተኛ ምህረት ይቅር የሚለው አካል ንጹህ ልብ፣ በጎ ህሊናና እውነተኛ የሆነ ፍቅር ያለው ካልሆነ በቀር ፈጽሞ የሚቻል አይደለም። በዚህ አይነት መልኩና ቁመና እውነተኛ የሆነን ምህረት ማድረግ የሚችል መሐሪ ከእግዚአብሔር በቀር ሌላ ሊሆን አይችልም።

እግዚአብሔር ከዚህ በፊትና በኋላ በተገለፁት የእርሱ ባህሪዎች መሰረት ቃሉና ተግባሩ ብሎም የልቡ ሃሳብ ተመሳሳይ፣ ቅን የሆኑለት የፍቅር አምላክ ነው። ይህም

አፍቃሪነቱ የመሐሪነቱና የርህራሄው ዋና መገኛና ምንጭ ነው፡፡ ምንም እንኳን የተፈጠረው ሁሉ የእጁ ስራ የሆነና በዚህም ፍጥረቱ ላይ የወደደውን ለማድረግ ሙሉ ስልጣንና ኃይል ያለው አምላክ ቢሆንም ከእነዚህ፣ በፊቱ በብዙ ጥፋትና በደል ለሚመላለሱ ፍጥረቶቹ ግን እውነተኛ የሆነን ምህረት ከፊታቸው እያስቀደመ በህይወት ይኖሩ ዘንድ ያደርጋቸዋል፡፡

“አፍቃሪነቱ የመሐሪነቱና የርህራሄው ዋና መገኛና ምንጭ ነው፡፡”

ለዚህም አይነተኛው ማሳያ በዮሐንስ ወንጌል 8 ላይ የምትገኘዋ አመንዝራ ሴት ስትሆን፣ በዚህ ሁኔታ ውስጥ ፃድቅና እውነተኛ ከሆነው ፍርድንም ሊፈርድ ደግሞ ይቅርታንም ሊያደርግ የሚችል ሆኖ በዚያ ሊወግራት በተሰበሰበው ህዝብ መካከል የተገኘ ብቸኛው ሰው የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ቢሆንም እንኳን ለበደሏና ለጥፋቷ በህጉ መሰረት የሚገባውን በድንጋይ የመወገርና የመሞት ቅጣት ከመቅጣት ይልቅ ደግማ ሀጢአትን እንዳትሰራ በመንገር በፍጹም ይቅርታ ማሰናበትን ወድዷል፡፡ ይህም ሁኔታ የእግዚአብሔር ማንነት መካከለኛ የሆነውን ለምህረትና ለይቅርታ የፈጠነ ለቁጣና ለበቀል ደግሞ የዘገየ ማንነቱን የሚያሳይ ነው፡፡ እግዚአብሔር ምህረቱን እስከ ሺህ ትውልድ ለልጅ ልጆች የሚጠብቅ በቁጣው ግን የአባቶችን ሀጢአት እስከ ሶስትና አራት ትውልድ ብቻ የሚያመጣ እጅግ መሐሪ ደግ አምላክ ነው፡፡

ይህ የእግዚአብሔር ማንነት ፍጥረት ከተፈጠረ በኋላ የጀመረ አይደለም፡፡ ነገር ግን ገና ከመጀመሪያው በእርሱ ዘንድ ቀድሞም የነበረ የፍቅርና የርህራሄው መገለጫ የሆነ ዘላለማዊ ማንነቱ ነው፡፡ ሁሉን ቀድሞ አዋቂ የሆነው እግዚአብሔር ምንም እንኳን ሊፈጥረው ያለው የሰው ልጅ ከፊቱ ያለውን ፈጣሪውን የሚበድልና የሚያሳዝን እንደሆነ መንገዱን ቀድሞውኑ ያወቀ ቢሆንም ቸርነቱና ለዘላለም የሆነው ምህረቱ ግን ከሰው ጥፋት በላይ ሆኖ በልቡ ያለውን መልካም ሃሳብ ሊፈጽም እንዲችል ያደርገው ነበር፡፡

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በዮሐንስ ራዕይ 13፡10 ላይ እንደተጠቀሰው አንድያ ልጁን ይኸውም የእግዚአብሔርን በግ ከአለም ፍጥረት በፊት እንዲታረድ ያደረገው ይሄው መሐሪነቱ ነው፡፡ ይህም ማለት ገና ከመጀመሪያው እግዚአብሔር ሊፈጥረው ያለው ሰው፣ እግዚአብሔር ሰውን በመፍጠሩ ምክንያት እስኪፀፀት ድረስ እንደሚያሳዝነው

ምህረቱንም እንደሚፈታተንና በብዙ ቁጣው ውስጥ እንደሚያልፍ እያወቀ ቀድሞውኑ ልጁን መስዋዕት አድርጎ ሁሉን የሚያስተካክልበትን ዋና የምህረት ማሳያውን ከሰው በደል በላይ ተማምኖ ሰውን ለክብሩ ይሆን ዘንድ እንደፈጠረው ይታያል። ይህም ምህረቱ ገና ከማለዳው የመጀመሪያው ሰው አዳም እግዚአብሔርን በበደለ ጊዜ መገለጥ የጀመረ እንደነበር ይታያል።

እግዚአብሔር ከሰው ልጆች ሁሉ ጋር ባለው ግንኙነት ውስጥ ዋና አላማው ፍቅር ሲሆን፣ ለዚህም ጤናማ የሆነ እግዚአብሔር እና ሰው እንዲኖራቸው ላሰበው የዘላለም ግቡ መሳካት ለሰው ልጆች የማያልቅ ምህረትን እለት እለት ያደርጋል። መጽሐፍ ቅዱስ በ2ኛ ሳሙኤል 14፡1 ላይ እንደሚናገረው በእግዚአብሔር ልብ ውስጥ ያለው ሃሳብ የተጣለ ሰው እንኳን ፈጽሞ እንዳይጠፋ የሆነ የነፍስን ጥፋት የማይወድ መሐሪ ማንነት ነው። ይህም ማለት በደለኛ የሆነ ሰው በደሉን አውቆ ወደ መሐሪው እግዚአብሔር ፊት በመቅረብ ሀጢአቱንም በመናዘዝና ከጥፋቱ ለመመለስ በመወሰን በህይወት ይኖር ዘንድ ነው እንጂ በሀጢአቱ ይጠፋ ዘንድ የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም ማለት ነው። ለዚህም

> “በደለኛ የሆነ ሰው በደሉን አውቆ ወደ መሐሪው እግዚአብሔር ፊት በመቅረብ ሀጢአቱንም በመናዘዝና ከጥፋቱ ለመመለስ በመወሰን በህይወት ይኖር ዘንድ ነው እንጅ በሀጢአቱ ይጠፋ ዘንድ የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም።”

አቅም ይሆንለት ዘንድ መጽሐፍ ቅዱስ በዕብራዊያን 4፡16 ላይ እንደሚናገረው ለዘላለም የሚሆን የፍጥረትን ሁሉ ሀጢአት በይቅርታ ማለፍ የሚችል ምህረትና የሰውን ድካም ማገዝ የሚችል የሚረዳ ፀጋ ወዳለበት ወደ ፀጋው ዙፋን ሰው በእምነት እንዲቀርብ ይናገራል።

ከላይ እንደተገለፀው እግዚአብሔር አላማው ፍቅር ሲሆን ማንም አንገቱን በማደንደን እንዲሰበርና እንዲጠፋ አይፈልግም። የዚህም ለምህረት የፈጠነ ለቁጣ ደግሞ የዘገየ ማንነቱ ዋና ማሳያዎች እግዚአብሔርን በብዙ የበደሉት የእስራኤል ነገስታት የሆኑት አክአብና ምናሴ ናቸው። ምንም እንኳን ከሌሎቹ ነገስታት የበለጠ በብዙ በደል ውስጥ ያለፉ፣ እግዚአብሔርንና ህዝቡንም ያራራቁ፣ ምድሪቱንም ለጥፋት አሳልፈው የሰጡ

ቢሆንም እንኳን ምህረትን ፈልገው ፊቱ በቀረቡበት ጊዜ ፈጥኖ ይቅር ለማለት የተቸገረ የደነደነ ጨካኝ ልብ ግን እግዚአብሔር አልነበረውም።

ይህ ለሰው ልጆች እጅግ የበዛ የእግዚአብሔር ምህረት በትውልድ መካከል ቀጥሎ የእግዚአብሔር እውነተኛ ምሕረት ማሳያ የሆነውን የልጁን የመስቀል ሞት ገለጠ። ይህ የእግዚአብሔር ምህረት ከሌሎቹ የእርሱ ማንነቶች ጋር ተስማምቶ ባህርያቶቹም ሳይጋጩ ይልቁንስ ተቀባብለው የሚገለጡና እርሱን የሚያሳዩ እንደሆኑ ለእኛ ያስታወቀ ነበር። በተለይም እውነተኛነቱንና ፃድቅ ፈራጅነቱን በምህረቱ የሚሸፍን እንዳልሆነ ይልቁንስ ለእያንዳንዱ በደልና ሀጢአት ተገቢውን ፍርድ በጽድቅ የሚፈርድ እውነተኛ አምላክ እንደሆነ በዚህ እውነትና ምህረት ተስማምተው በጽድቅ በተፈረደ ፍርድ ንጹህ የሆነውን ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን በአለም ሀጢአት ምክንያት መስቀል ባዋለው ጊዜ ታይቷል።

ይህም ሁኔታ የበለጠ የእግዚአብሔርን ፍቅር የገለጠ ደግሞ እውነተኛነቱንና ፃድቅ ፈራጅነቱን ማንም ደግሞ የዘራውን ሊያጭድ የተገባው መሆኑን የሀጢአትም ደመወዝ በእርግጥ ሞት እንደሆነ የበለጠ አጠንክሮ ለፍጥረቱ ደግሞ ያሳሰበ ነው። *"ያልጠፋነው ከእግዚአብሔር ምህረት የተነሳ ነው ርህራሄው ኢያልቅምና"* ብሎ ኤርምያስ በሰቆቃው እንደተናገረ እንዲሁ ለፍጥረቱ ሁሉ ዛሬ ላይ በህይወት የመገኘቱና ያለመጥፋቱ ምስጢር ይሄው የእግዚአብሔር ታላቅ ዘላለማዊ ቸርነትና ምህረት ነው።

መጀመሪያ የሳተው አዳም በመተላለፉ ምክንያት ፍርድ ለኩነኔ ወደ ሰው ሁሉ እንደመጣ እንዲሁ በእግዚአብሔር በጎነትና ቸርነት ምክንያት በአንድ ጻድቅ የጽድቅ ስራ ስጦታው ህይወትን ለማጽደቅ ወደ ሰው ሁሉ መጣ። ይህም ከሰው አዕምሮ በላይ የሆነ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ያለውን ፍቅርና ምህረት ያሳየ በተግባር የተገለጠ የእግዚአብሔር ቸርነት ነው።

እኛ ሁላችን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንሆን ዘንድ ሀጢአት ያላወቀውን ቅዱስ ልጁን ሀጢአት አድርጎ ስለ እኛ ስለ ሁላችን መስቀል ላይ አዋለው። ገና ሀጢአተኞችና በደለኞች ጠላቶችም ሳለን በዚህ ልክ እግዚአብሔር ፍቅርና ምህረቱን ለእኛ ከገለጠ ከዚህ ወዲያ ሀጢአት በመስቀል ላይ ከተቀጣና ጠላትነታችን ቀርቶ ወዳጅ ከሆንን በኋላ እንዴት

ይልቁንስ ምሕረቱ ይበዛልን። እንግዲህ አሁን በፈሰሰው ደም ከፀደቅን በዚሁ ደም በአብ ፊት መቅረብ ከቻልን የጥል ግድግዳውም በመፍረሱ ምክንያት ምህረት ይበልጥ እንዲበዛልንና ሊመጣ ካለው ቁጣና ፍርድ እንድንድን እናውቃለን። የተገለጠው የእግዚአብሔር ፀጋና በአንድ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ ፀጋ የሆነው የህይወት ስጦታ በአለም ካለው ሰውን እንዲፈረድበት ከሚጠይቅ ብዙ በደል ይልቅ የበዛ ሆነ። በዚህም የተገለጠው የበዛ የእግዚአብሔር ምህረት ጴጥሮስ ጌታ ኢየሱስን እንደጠየቀው ወንድሜንም ቢበድለኝ ስንት ጊዜ ይቅር ልበለው እንዳለ በጌታችን መልስም ውስጥ ምህረት ገደብ አልባ እንደሆነ ይታያል። እግዚአብሔር በምህረት ባለጠጋ የሆነ ለዘላለም የሚሆን ምህረት ያለው የሳተን ለመመለስና የወደቀን ለማንሳት የሚቸኩል መማር የማይደክመው የፍቅር አምላክ ነው።

> “እግዚአብሔር በምህረት ባለጠጋ የሆነ ለዘላለም የሚሆን ምህረት ያለው የሳተን ለመመለስና የወደቀን ለማንሳት የሚቸኩል መማር የማይደክመው የፍቅር አምላክ ነው።”

በዚህ መልኩ በበደሉ ልክ ያልተፈረደበትና ከአምላኩ ብዙ ይቅርታን የተቀበለ ሰው ታዲያ በተደረገለት በዚያው ምህረት ልክ እርሱ ደግሞ ለሌላው እንዲያደርግ የታዘዘ ደግሞ ነው። ይህም እግዚአብሔር በደላችንን እንዳለፈ ውሃ እንደሚረሳ ደግሞም እንደማያስበው እንደዛው ከልባችን በሆነ ይቅር መባባል በደልን ሁሉ የምናልፍበት በተደረገልን ምህረት ሌሎችን እየማርን የምንኖርበት አዲስና ህያው የሆነ የአዲስ ኪዳን መንገድ ነው።

ጌታችን ኢየሱስ በተራራው ስብከት እንዲሁም ደግሞ ለተከታዮቹ ይፀልዩት ዘንድ ባስተማራቸው ፀሎት ውስጥ “እኛም የበደሉንን ይቅር እንደምንል በደላችንን ይቅር በለን” በሉ ብሎ ከሰማዩ አባት ይቅርታን ለማግኘት ባልንጀራን ይቅር ማለት በምድር እንደሚያስፈልገን አጠንክሮ ነግሮናል። በተመሳሳይ መልኩ በማቴዎስ ወንጌል 18 ላይ ባሮቹን ሊቆጣጠር በወደደው ጌታ በተብራራው ምሳሌ ውስጥ እንደተነገረን ወንድምን

ይቅር አለማለት ከአብ ይቅርታን እንዳናገኝ የሚያደርገንና ለጥፋት የሚዳርገን እንደሆነ ተገልጿል።

እኛ የምህረቱ ተጠቃሚዎች የሆንን ከማረን ከእግዚአብሔር ጋርም ኅብረት አለን የምንል እርሱ በብርሃን እንዳለ እኛ ደግሞ በብርሃን ልንመላለስ ያስፈልገናል። በዚህም መልኩ እርሱ በብርሃን እንዳለ በብርሃን ብንመላለስ ለእያንዳንዳችን ኅብረት አለን፣ ይህም ኅብረት አንድ አማኝ ከእግዚአብሔር ዘንድ ያገኘውን ትልቅ በህይወት የመኖር እድል ይሰጠዋል። ይኸውም በዚህ ኅብረት የሚገኘው ዕለት ዕለት ትኩስ በሆነውና ከአቤል ደም ይልቅ ምህረትን በሚናገረው ከሀጢአትም ሁሉ በሚያነፃው በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ደም በመታጠብ ከሀጢአት ሁሉ የመንፃት ያለ በደል በእግዚአብሔር ፊትም የመመላለስን ትልቅ እድል የሚያስገኝ ነው።

> “በዚህ ህብረት የሚመላለስ ሰውም እግዚአብሔር ፍቅር እንደሆነ በፍቅር ሊመላለስ ወንድሙንም ሊወድ ጽድቅንም ሁሉ ሊያደርግ ያስፈልገዋል።”

በዚህ ኅብረት የሚመላለስ ሰውም እግዚአብሔር ፍቅር እንደሆነ በፍቅር ሊመላለስ ወንድሙንም ሊወድ ጽድቅንም ሁሉ ሊያደርግ ያስፈልገዋል። መጽሐፍ ቅዱስ በዚሁ በ፩ኛ የዮሐንስ መልዕክት 2፡5 ላይ እንደሚናገረው በእርሱ እንዳለን በዚህ እናውቃለን፣ በእርሱ እኖራለሁ የሚል እርሱ እንደተመላለሰ ራሱ ደግሞ ሊመላለስ ይገባዋል፤ ብሎ በተመሳሳይ ፍቅር፣ መሐሪነትና ይቅርታ፣ ጽድቅና ቅድስና ወዘተ ልንመላለስ እንደሚገባ ያስታውሰናል።

> “እግዚአብሔር ምህረቱን እስከ ሺህ ትውልድ ለልጅ ልጆች የሚጠብቅ በቁጣው ግን የአባቶችን ሀጢአት እስከ ሶስትና አራት ትውልድ ብቻ የሚያመጣ እጅግ መሐሪ ደግ አምላክ ነው።”

- **የማስተንተኛ ጥያቄዎች**

1. የእግዚአብሔር ምሕረት ሕይወትህን እንዴት ለውጦታል?
2. የእግዚአብሔርን ምሕረት መቀበል ለሌሎች ምሕረት እንድናሳይ ሊመራን የሚገባው ለምንድር ነው?
3. ዛሬ ይቅር ልትለው የሚያስፈልግህ ሰው አለ?

- **አሰላሰል**

እግዚአብሔር በምሕረት የበለጸገ ነው። በኃጢአታችን ምክንያት ፍርድ ይገባን ነበር፤ ነገር ግን እርሱ በምሕረቱ ይቅር ሊለን፣ ሊመልሰንና በኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት ሊሰጠን መረጠ። ምሕረቱ ለእኛ ያለውን ታላቅ ፍቅሩንና ርኅራኄውን ያሳያል። እግዚአብሔር ያሳየንን የማይገባንን ምሕረት ተቀብለን እኛም ለሌሎች ምሕረትን፣ ይቅርታንና ፍቅርን እንድናሳይ ተጠርተናል። ስለዚህ እንደ ተቀበልነው ምሕረት ሌሎችን በምሕረት መያዝ እንደሚገባን ማስታወስ ያስፈልገናል።

- **ጸሎት**

በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፣ ስለ ታላቅ ምሕረትህና ይቅርታህ እናመሰግንሃለን። በእኔ ላይ ያደረግኸውን ምሕረት ሁልጊዜ እንዳስታውስ እርዳኝ፤ ያንኑ ምሕረት፣ ፍቅርና ይቅርታ ለሌሎች እንዳሳይ አግዘኝ። ልቤን ከቂምና ከጥላቻ ነጻ አድርገህ፣ እንደ አንተ ርኅሩኅና ይቅር ባይ እንድሆን ቀይረኝ።

በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አሜን።

- **የአርምሞ ጥቅስ**

*"እግዚአብሔር መሓሪና ይቅር ባይ ነው፥ ከቍጣ የራቀ ምሕረቱም የበዛ።*

*— መዝሙረ ዳዊት 103፥8 —*

## 2.25. እግዚአብሔር ታጋሽ ነው!

ትዕግስት አንድን ነገር ሳናይናወጡና ከሁልጊዜ ምልልስ ውጭ ሳይሆኑ በራሱ እስኪሆን ድረስ የመጠበቅ አቅም ነው። የዘገየ ነገርን፣ የገጠሙንን ችግሮች፣ ልዩ ልዩ የህይወት ፈተናዎች ወዘተ በራሳቸው ጊዜ የእኛን የእለት እንቅስቃሴዎች እየጎዱ ካሉበት ሁኔታ እስከሚለቁ እና ሁሉ እንደነበር እና የተሻለ እስከሚሆን ድረስ ያልተገባን ነገር ሳያደርጉ ተረጋግተው የመጠበቅ አቅም ትዕግስት ይባላል።

ሰዎች በየቀኑ በዕለት ከዕለት እንቅስቃሴያቸው ለሚገጥሟቸው ሁኔታዎች፣ በህይወት መስመር ለሚያገኟቸው ሰዎች እንዲሁም በህይወት ለሚኖሩለት አንድ ቀን እደርስበታለሁ ብለው ላስቀመጡት የስኬት መንገድና ግብ ወዘተ በብዙ ሲታገሱ ይታያሉ። ይሁን እንጂ በእነዚሁ ብዙ የሚፈታተኑ የትዕግስት ጎዳናዎች ወቅት ሰዎች በርካታ ጊዜ በመውጣትና በመውረድ ውስጥ ሲያልፉ አንዳንድ ጊዜም ትዕግስታቸው አልቆ አላስፈላጊ ውሳኔዎችን ሲወስኑ ማየት የተለመደ ነው። ነገር ግን እውነተኛ ትዕግስት የሚጠብቁትን ነገር በፍጹም አለመናወጥና እርጋታ ባልተንሸዋረረም እይታና እሳቤ ራስንም በመግዛት በቀናነት መጠበቅ ነው።

የእግዚአብሔር ትዕግስት ከላይ ከተገለጸው የሰው ትዕግስት በብዙ መልኩ የሚለይ ሲሆን ይህም በዋነኛነት ለራስ ጥቅም ሳይሆን ለህዝቡ ጥቅም እግዚአብሔር ራሱን በመግዛት ህዝቡን የሚታገስበት ትዕግስት ነው። ይህም በዋነኛነት እግዚአብሔር ህዝቡን የሚወድ የፍቅር አምላክ ከመሆኑ የሚነሳ ሲሆን ፃድቅነትና ቅድስናውን ከእውነቱና ከምህረቱ ጋር ሚዛናቸውን አስጠብቆ በሉአላዊ ስልጣኑ በኃይሉም ታላቅነትና ሁሉን የማድረግ ችሎታቸው ከፋ ከማድረግ የሚታገስበት ራስን የመግዛት አቅሙ ነው። ይህም የእግዚአብሔር ትዕግስት ሁልጊዜ በእግዚአብሔር ፊት በብዙ ድካምና መተላለፍ ውስጥ ለሚያልፈው የሰው ልጅ ዋነኛው በህይወት የመኖር ዋስትና ነው።

> “የእግዚአብሔር ትዕግስት ሁልጊዜ በእግዚአብሔር ፊት በብዙ ድካምና መተላለፍ ውስጥ ለሚያልፈው የሰው ልጅ ዋነኛው በህይወት የመኖር ዋስትና ነው።”

እግዚአብሔር ከዙፋኑ ሆኖ በእያንዳንዱ ቀንና ሰዓት በየሰው ልብ ውስጥ ጭምር ሳይቀር ያለውን በተግባርም በህዝቡ መካከል የተገለጠውን ከእርሱ ጽድቅና ቅድስና ጋር የተጣላ የሰው ልጅ የአመጽ እንቅስቃሴ ሁሉ አይቶና በቂ እውቀት ይዞ በምላሹ ተገቢ የሆነን ቅጣት ከመቅጣት የሚዘገይበት ቆይታ ይህ የእግዚአብሔር ትዕግስት ነው። ታዲያ በዚህ መካከል የበደለና በዚሁ የአመጽ መንገድ ለጊዜውም ቢሆን ተጠቃሚ የሆነ እግዚአብሔርም ክፉ ወይም ደግ የማያደርግ እንዲያውም ከነጭራሹ የሌለ የሚመስለው ብዙ ሰው ያለ ሲሆን በተቃራኒው ደግሞ ብዙ መከራን በአመጽ ምክንያት እያስተናገደ ያለ እግዚአብሔር አያይም ፍርድንስ አይፈርድም? በዙፋኑስ አለ? ይህንንስ ሁሉ ያያል? የሚሉ ጥያቄዎችን የሚጠይቅ ጉብኝት ጠባቂን ደግሞ በሌላ አቅጣጫ ይፈጥራል። እንዲህ አይነቱም በሰው እይታ እጅግ የበዛ የእግዚአብሔር ትዕግስት በዋናነት እግዚአብሔር አለሙን ሁሉ ስለ ወደደ ለፍጥረቱም ካለው ታላቅ ፍቅር የተነሳ የሳተ ተመልሶ በህይወት ይኖር ዘንድ እንጂ ፈፅሞ እንዳይጠፋ በማሰብ የታገሰው ትዕግስት ነው።

እግዚአብሔር ይታገሳል ማለት ትዕግስቱ "የሚያልቅበት" ወቅት ደግሞ አለው ማለት ሲሆን በዚሁ የእግዚአብሔር የመታገስ ወቅት ሁሉ ታዲያ እግዚአብሔር በምድር ላይ በሰው ልጆች መካከል ያለ አመጽና መተላለፍ፣ በደልና ፍርድ መጓደል ወዘተ እግዚአብሔር ራሱ በዚያ ደስተኛ ሳይሆን እንዲቆይ ያደረገው እንደሆነ ደግሞ ይታያል። ይህም ማለት በዚያን ወቅት እግዚአብሔር በሰው ልጆች መካከል በሚያየው ከእርሱ ማንነት ተቃራኒ የሆነ አመፀኛ እንቅስቃሴ ሁሉ የሚያዝን እንደሆነ የሚናገር ነው። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ይህንን ሁሉ ጥፋትና አመጽ በቀላሉ ሊያስወግድ የሚችልበት ራሱንም በሰው ልጆች ከማዘን የሚጠበቅበት ሙሉ አቅምና ብቃት ያለው ቢሆንም ራሱን በመግዛት በሚያየው ነገር ደስተኛ ሳይሆን ሰው እየሄደ ከሚገኝበት የሞት መንገድ ተመልሶ በህይወት ይኖር ዘንድ መርጦ በብዙ ይታገሳል።

> "የእግዚአብሔር ትዕግስት በዋናነት እግዚአብሔር አለሙን ሁሉ ስለ ወደደ ለፍጥረቱም ካለው ታላቅ ፍቅር የተነሳ የሳተ ተመልሶ በህይወት ይኖር ዘንድ እንጅ ፈፅሞ እንዳይጠፋ በማሰብ የታገሰው ትዕግስት ነው።"

እንዲህ አይነቱ የእግዚአብሔር የበዛ ትዕግስት ፍትህን ያጓደለ የሚመስል ቢሆንም መጽሐፍ ቅዱስ በዘፀዓት 34፡6-7 ክፍል ላይ እንደሚናገረው እግዚአብሔር የሚታገስ ይሁን እንጂ በደለኛውን ከቶ እንደማያነጻ ደግሞ አብሮ ይናገራል። አንድያ ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስንም በመስቀል ላይ ያዋለው ይሄው ታላቅ ፍቅሩ ደግሞ የምህረቱም ብዛት ከዚሁም ጋር አብሮ እውነተኛነቱና ፃድቅ ፈራጅነቱ እንደሆነ ይታወቃል።

የእግዚአብሔር ታጋሽነት እግዚአብሔርን መልካም ያደርግላቸው እና ይፈርድላቸው ዘንድ ለሚጠብቁ ምርጦቹ በጣም ረዥምና ከባድ ሲሆን አንዳንድ ጊዜም ከላይ እንደተገለፀው ትዕግስታቸው አልቆ ከእግዚአብሔር መንገድ የሚሸሹበትን ወይም ደግሞ በብዙ እንባና መከራ በሀጢአተኞች ጭምር እንኳን እስኪቀኑ ድረስ በሚደርስ ሁኔታ እንዲያልፉ የሚያደርግ ከባድ መንገድ ነው። አሳፍ በመዝሙረ ዳዊት ምዕራፍ 73፣ እስራኤላዊያን በሚልኪያስ 3፣ በኢሳይያስ 40 ወዘተ በጽድቅ መንገድ መሄዳችን እግዚአብሔርንም መፍራታችን መታገሳችንም ከንቱ ነው፣ እግዚአብሔር አያይም፣ ፍርዳችን ከአምላካችን አልፋለች ወዘተ በሚሉት ቃላት ይህንኑ የእግዚአብሔር ትዕግስትና ልብ ስፋት ይናገራሉ። እንደዚሁ በህዝቅኤል 18 ና 33 ላይ ያሉ እስራኤላዊያንም እግዚአብሔር ሀጢአተኛውን የሚታገስበትን ሰፊ ትዕግስት አይተው *"የእግዚአብሔር መንገድ ቅን አይደለችም"* ብለው ሲሉ በዚያውም ስፍራ እግዚአብሔር የሀጢአተኛውን ሞት ስለማይወድ ሀጢአተኛ ከሀጢአቱ ተመልሶ በህይወት ይኖር ዘንድ እድልን ሊሰጠው እንደሚታገስ ይናገራል።

መጽሐፍ ቅዱስ በበርካታ ስፍራ እግዚአብሔር ወደ እርሱ የሚጮኹ ምርጦቹን እንደሚሰማ ደግሞ እንደሚመልስላቸው፣ ለሚጠብቁትና ተስፋ ለሚያደርጉትም ጌታ በድንገት ወደ እነርሱ እንደሚመጣ ነገር ግን በዚህ ሁሉ የእግዚአብሔር ትዕግስት መካከል በተስፋ ደስ እያላቸው፣ በመከራ ደግሞ እየታገሱ በፀሎት ፀንተው ሊኖሩ እንደሚያስፈልጋቸው ይናገራል። ይህ የቅዱሳኑ የእግዚአብሔርን ፍርድ ፍለጋ በዚህ አለም ብቻ የተገደበ ሳይሆን ከስጋ ተለይተው ወደ እርሱ የተሰበሰቡ ጭምር በዮሐንስ ራዕይ 6፡ 10 ላይ እንደሚሉት አምላካቸው እንዲፈርድላቸው እንደሚጠይቁት የፃድቃን ነፍሶች በሰማይም ጭምር የቀጠለ ነው።

በዚህ ሁሉ ውስጥ መጽሐፍ ቅዱስ በ2ኛ ጴጥሮስ 3፡9 ላይ እንደሚናገረው ለአንዳንዶች የሚዘገይ እንደሚመስላቸው ትዕግስቱ የበዛው ደግ ጌታ ስለ ተስፋ ቃሉ የማይዘገይ ሲሆን ይህን ሁሉም ትዕግስት የሚታገሰው ሁሉ ወደ ንስሃ እንዲደርሱና ማንም እንዳይጠፋ ወድዶ እንደሆነ ይናገራል።

ይህ ሰፊ የእግዚአብሔር ትዕግስት ከአዳም መተላለፍ የጀመረ፣ በቃየን ወንድሙን መግደል የቀጠለ በሰው ልጆች መካከል ለራሱ የሆነን ሰው በፀጋው እየመረጠ በእርሱ መንገድ በማስኬድ እኛ ሁላችን የምንድንበትና ከጥፋት የምናመልጥበትን መንገድ ለማምጣት በዘመናት መካከል እየጨመረ የታየ የእግዚአብሔር ሰፊ ልብ መገለጥ ነው። በየመንገዱ የተፈታተኑትን በብዙ ፀጋ የእርሱ ህዝብ እንዲሆኑ የመረጣቸውን እስራኤላዊያንን የታገሰበት ትዕግስት፣ በዚህ ልክ ለእነርሱ ከበዛው ፍቅሩና መልካምነቱ በተቃራኒ ሌሎች አማልክትን ጭምር በማምለክ ህፃናቶቻቸውንም ለመስዋዕት በእሳት በማሳለፍ ያስቆጡትን ሁሉ እየታገሰ የሰው ልጆችን ጨርሶ ሳያጠፋ መድሃኒትን ለሁላችን የላከበት የበዛ ትዕግስት አስደናቂ የእግዚአብሔር መልካምነት ማሳያ ነው።

በዚህም የእግዚአብሔርን ለማዳን የሆነ ትዕግስት ያልተረዳው የሰው ልጅ በየዘመኑ በክፋቱ እየቀጠለ ሄዶ ሊያድነው ወድዶ በመካከሉ እርሱን መስሎ የተገኘውን መድሃኒቱን ይኸውም አምላኩን በመስቀል ላይ ገደለ። ይህንንም ሁሉ እግዚአብሔር ታገሰ። በዚህ ሁሉ የሰው ልጅ የጥፋት መንገድ ውስጥ የእርሱ ካልሆኑት አህዛብ በተጨማሪ በስሙ የተጠራው ህዝቡ ጭምር በዙሪያው ያሉ አህዛብን እግዚአብሔር ከህዝቡ ፊት እንዲጠፉ ካደረገበት የአሞራዊያን ሀጢአት ይልቅ የበለጠ መተላለፍን የራሱ የሆነው ህዝብ ሲያደርግ ጭምር እግዚአብሔር በብዙ ታግሷል። ይህንንም በደል መጽሐፍ ቅዱስ በ2ኛ ነገስት 21፡15 ላይ በተነገረበት ዘመን ብቻ የተደረገ ሳይሆን ይልቁንስ ከአባቶቻቸው የጀመረ ከግብጽ እስከዚያን ዘመን ድረስ የቀጠለ እግዚአብሔር በብዙ የታገሰው አንገቱ የደነደነ ህዝብ ክፉ ስራ ነበር።

ይህ ሁሉ እግዚአብሔር ሰውን የሚታገስበት መንገድ እንዲሁ ከመታገስ ባለፈ ህዝቡ ከሀጢአቱ ይመለስና በህይወት ይኖር ዘንድ ደጋግሞ ማሳሰቢያንና ማስጠንቀቂያን በመናገር ጭምር የታጀበ ነው። ይህም ከህዝቡ ባለፈ ለአህዛብ ጭምር የተገለጠ የእግዚአብሔር በጎነት ሲሆን በዚህም መሰረት እግዚአብሔር የላከላቸውን የህይወት ቃል

ሰምተው የአቅጣጫ ለውጥ በማድረግ የትዕግስቱና የምህረቱ ተጠቃሚዎች የሆኑ እንደ ነነዌ ህዝብ ያሉ በርካቶች ናቸው። ከዚሁ በተቃራኒ ምንም እንኳን መጽሐፍ ቅዱስ በተደጋጋሚ በተለይም በኤርምያስ መጽሐፍ ደጋግሞ እንደሚናገረው ገና ከማለዳ ጀምሮ እግዚአብሔር በባሪያዎቹ በኩል ሰዎች እየሄዱ ያሉበትን የጥፋት መንገድ በመግለጥ ተመልሰው በህይወት እንዲኖሩ ሲናገር ቆይቷል።

የሰው ልብ ገና ከታናሽነቱ ጀምሮ ክፉና ማንም የማያውቀው ጥልቅም ስለሆነ ይህም ክፉ ልቡ ያመጣበት አንገተ ደንደናነት ብሎም የእግዚአብሔርን ትዕግስትና ምህረት መለማመድ በርካታ ዋጋን ሲያስከፍለው ታይቷል። ይሄው የሰው ልብ ድንዳኔና የእግዚአብሔርን ትዕግስት ጥቅም አለመረዳት ዛሬ እንዲሁም በሚመጣው እየከፉ በሚሄድ ዘመን ጭምር የሚቀጥል እንደሆነ እኛ ዛሬ በህይወት የምንገኝ በየቀኑ የምናየው ሲሆን በዮሐንስ ራዕይም ይመለሱና በህይወት ይኖሩ ዘንድ እግዚአብሔር ለተግሳጽ በህዝቡ መካከል የሚያደርጋቸው ነገሮች ህዝቡን በምላሹ ንስሃ ከመግባት ይልቅ እግዚአብሔርን እንዲሳደቡ ሲያደርጋቸው ይታያል።

እግዚአብሔር ከመስዋዕት ይልቅ ምህረትን የሚወድ ለሰው ልጆች ምህረትን ማድረግ የማይደክመው ጌታችን ኢየሱስ ለጴጥሮስ እንዳለው ሰባት ጊዜ ሰባ ብቻ ያልሆነ ሰፊ ልብ ያለው ታጋሽና መሐሪ ጌታ ነው። ይህም እጅግ የበዛው ፍቅሩና መልካምነቱ ዘጠና ዘጠኙን በሜዳ ትቶ የጠፋችበትን አንዷን እንዳትበላ ፍለጋ የሚሄድበት ሰው ሁሉ ከጥፋቱ በመመለስ ይቅርታን አግኝቶ ከበደሉ ነፃ በመሆን በህይወት እንዲኖር ያለመ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በትንቢተ ሐጌ 2፡19 ላይ እንደሚናገረው ሰው በዚህ ትዕግስት ተጠቅሞ ከጥፋቱ በተመለሰበት በዚያው ቀን የእግዚአብሔርን በረከት እንደሚያገኝ ይታያል። ይህ ሁሉ ትዕግስት ግን እግዚአብሔር የተጓደለ ፍትህን የሚሰጥ አምላክ ስለሆነ፣ የሚሆነውን ስላልተመለከተ ወይም ብዙዎች እንደሚሉት መንገዳችን በእርግጥ ከእግዚአብሔር ተሰውራና ፍርዳችን ከአምላካችን አልፎ አይደለም። ነገር ግን ዛሬም እግዚአብሔር በተቀደሰ መቅደሱ እንደ ቀድሞው፣ ሁሉ በፊቱ የተራቆተ ሆኖ ሳይደክም፣ ሳይታክት ማስተዋሉም ሳይመረመር ፀጋን አንደተሞላ ለጥቅማችን ብዙ እየታገሰ አለ።

“እግዚአብሔር ከዙፋኑ ሆኖ በእያንዳንዱ ቀንና ሰዓት በየሰው ልብ ውስጥ ጭምር ሳይቀር ያለውን በተግባርም በህዝቡ መካከል የተገለጠውን ከእርሱ ጽድቅና ቅድስና ጋር የተጣላ የሰው ልጅ የአመጽ እንቅስቃሴ ሁሉ አይቶና በቂ እውቀት ይዞ በምላሹ ተገቢ የሆነን ቅጣት ከመቅጣት የሚዘገይበት ቆይታ ይህ የእግዚአብሔር ትዕግስት ነው።”

- **የማስተንተኛ ጥያቄዎች**

1. የእግዚአብሔር ትዕግሥት እንድታድግና እርሱን እንድትመስል በምታደርገው ጉዞ ውስጥ ምን አይነት ዕድል ሰጥቶሃል?
2. የእግዚአብሔር ትዕግሥት ኃጢአትን መደገፍ እንዳልሆነ ማስተዋል ለምን ይጠቅማል?
3. በየትኛው ሁኔታ ላይ ለሌሎች የበለጠ ትዕግሥት ማሳየት ያስፈልግሃል?

- **አሰላስል**

እግዚአብሔር ታጋሽ አምላክ ነው። ትዕግሥቱ ለሰው ልጆች ያለውን ታላቅ ፍቅሩንና ምሕረቱን ያሳያል። ሁሉንም ኃጢአት እያየና ወዲያውኑ ለመፍረድ ሥልጣን እያለው፣ ሰዎች ንስሐ እንዲገቡና ወደ እርሱ እንዲመለሱ ዕድል በመስጠት በትዕግሥት ይጠብቃል። የእግዚአብሔር ትዕግሥት ድካም ወይም ኃጢአትን መፍቀድ አይደለም፤ ነገር ግን ማንም እንዳይጠፋ ሁሉም ወደ ንስሐ እንዲመጣ ያለውን ልባዊ ፍላጎት የሚያሳይ ነው። እኛም ይህን ታላቅ ትዕግሥት ከተቀበልን በኋላ፣ በእርሱ በመታመን በትዕግሥት መመላለስና ለሌሎችም ትዕግሥት ማሳየት ይጠበቅብናል።

- **ጸሎት**

በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፣ ለእኔ ስላሳየኸኝ ታላቅ ትዕግሥትህና ምሕረትህ አመሰግንሃለሁ። ትዕግሥትህን እንደ ቀላል ነገር እንዳልወስድ፣ ነገር ግን በንስሐ፣ በመታዘዝና በምስጋና እንድመልስልህ እርዳኝ። አንተ እንደታገሥኸኝ እኔም ሌሎችን እንድታገስ እርዳኝ። በሁሉም ግንኙነቴ የአንተን ባሕርይ እንዳንጸባርቅ ልቤን ለውጠው።

በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አሜን።

- **የአርምሞ ጥቅስ**

*"ለአንዳንዶች የሚዘገይ እንደሚመስላቸው ጌታ ስለ ተስፋ ቃሉ አይዘገይም፥ ነገር ግን ሁሉ ወደ ንስሐ እንዲደርሱ እንጂ ማንም እንዳይጠፋ ወዶ ስለ እናንተ ይታገሣል።"*

*— 2ኛ የጴጥሮስ መልእክት 3፥9 —*

## 2.26. እግዚአብሔር ቀናተኛ አምላክ ነው!

ቅናት ማለት ሌሎች ያላቸውን መልካም ነገር፣ ስኬት ወይም ዝና ስንመለከት በውስጣችን የሚፈጠር የንዴት፣ የስጋት እና ቅር የመሰኘት ስሜት ነው። (ግዛው, 1994) ይህ ስሜት ብዙውን ጊዜ የሚመነጨው ራስን ከሌሎች ጋር በማነፃፀር፣ የበታችነት ስሜት ሲሰማን ወይም የምንወደውን ሰው የማጣት ፍራቻ ካለን ነው። ይህም ቅናት በተለያዩ መንገዶች ሊገለጽ የሚችል ሲሆን በአወንታዊ መልኩ ሲገለጽ አንድ ሰው በሌሎች ስኬት ተነሳስቶ ራሱን ለማሻሻል፣ ጠንክሮ በመስራት እንደ እነርሱ ስኬታማ ለመሆን፣ እውቀቱን ለማሳደግ ወዘተ የሚጠቀምበት በጎ ስሜት ሆኖ ይታያል። በተቃራኒው ደግሞ በአሉታዊ መልኩ ከላይ እንደተገለፀው ሌሎች ያገኙትን በጎ ነገር እንዲያጡ መመኘት፣ ሰዎችን መጠርጠር፣ አልፎ ተርፎም ከልክ ያለፈ የቁጥጥር ስሜት ውስጥ በመግባት በራስም ሆነ በሌሎች ላይ ጉዳት እስከማድረስ የሚደርስ ክፉ ባህሪ ሊሆን ይቻላል።

ይሄው ቅናት የሚለው ቃል በአጠቃቀሙ ሁለት አይነት ገጽታ ያለው ሲሆን ይህም በተለይ በእንግሊዝኛ Jealousy እና Envy ተብለው በሚገለፁበት መንገድ የሚታይ ነው። ሁለቱም ተመሳሳይ አይነት ይዘት ያላቸው ቃላት ይሁኑ እንጂ ቃላቶቹን በምንጠቀምበት ስፍራ ልንገልጽ የፈለግነው መልዕክት ግን በእጅጉ ይለያያል። (Merriam-Webster, n.d.)

“Envy” የሚለው ቃል ከላይ ቃሉን ስንፈታ ባየነው መሰረት በአሉታዊ መልኩ የሌላን ሰው ስኬት፣ መከናወን፣ ድል፣ ሀብት ወዘተ የግል ለማድረግ መመኘትና ለዚህም በዚሁ ቅናት ተነሳስቶ ኃይልን ጭምር የመጠቀምና አላስፈላጊ ጉዳትን እስከማድረስ የሚደርስ በሁለት አካላት ላይ የተመሰረተ ስሜት ሲሆን በአማርኛም ምቀኝነት እንደሚባለው ነው። (Merriam-Webster, n.d.)

ሌላኛውና ሁለተኛው “Jealousy” የሚባለው ሲሆን ይህም ከፍርሃት፣ ከጥርጣሬ፣ ከባለቤትነት ወዘተ የሚነሳ የእኔ የሆነን ለሌላ አልሰጥም / አላጋራም በሚል ስሜት መብትን ለማስከበር በሚመስል ሁኔታ የሚመነጭ በተለይም በፍቅር ስሜትና

ግንኙነት ውስጥ አንዱ በሌላው ላይ የሚሰማው በሌላ ያልተገባው ሶስተኛ ወገን የእኔ የሆነውን እነጠቃለሁ በሚል ፍርሃት የሚገለጥ በአማርኛው ቅናት የሚለውን ቃል የሚገልጽ አነጋገር ነው። (ግዛው, 1994) (Merriam-Webster, n.d.) በዚህ አይነት ሁኔታ ለምሳሌ ያክል ህጋዊ በሆነ የትዳር ግንኙነት ውስጥ የሚገኙ ሁለት ጥንዶች በገቡት ኪዳን መሰረት አንዳቸው የሌላቸው ሆነው በታማኝነት ሊኖሩ ተስማምተው ሲያበቁ ከኪዳናቸው ውጭ ባልተገባ ሁኔታ አንዳቸው ከሌላ ሶስተኛ ወገን ጋር ግንኙነትን ቢጀምሩ ይህም ሁኔታ ለትዳር አጋራቸው ቢታወቅ ወይም ቢጠረጠር ወዘተ ኪዳኑን ያላፈረሰው አካል የግል ንብረቱ በሆነችው ጥንዱ ከሌላ ጋር ኅብረት መጀመር ምክንያት ይሰማው ዘንድ ተገቢ የሆነው የቅናት ስሜት አይነት ነው። እንዲያውም በተቃራኒው ይህ ትክክለኛ የቅናት ስሜት ባይሰማውና የትዳር አጋሩ በጀመረችው ሌላ ከኪዳን ውጭ የሆነ ግንኙነት ደስተኛ ከሆነ ፍቅሩ የተመሰረተበት መሰረት እንዲሁም እርሱ ራሱ ኪዳኑን የጠበቀበት መንገድ ጥያቄ ውስጥ እንዲገባ ይሆናል።

ይሁን እንጂ በእውነተኛ ፍቅር ላይ የተመሰረተ ኅብረት ያላቸው ጥንዶች አንደኛቸው ለሌላቸው ካላቸው እውነተኛ ጥልቅ የሆነ ፍቅር የተነሳ ምንም አይነት የሶስተኛ ወገን ጣልቃ ገብነትን የማይፈቅዱ ሲሆኑና በዚህም አይነት ሁኔታ መፈጠር ከፍተኛ የቅናት ስሜት የሚሰማቸው ሲሆኑ ይህም ስሜታቸው ነገሩ ተካርሮ ኪዳናቸውን አፍርሰው በፍቺ ሁኔታ እንኳን ሆነው ባሉበት ጊዜ የእነርሱ የነበረን ሰው ከሌላ ጋር ማየት የአለመፈለግና በዚህም የተፈጠረ ከፍተኛ የቅናት ስሜትን ሲያሳዩ ይታያል።

እግዚአብሔር የፍጥረት ሁሉ ፈጣሪ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በቆላስያስ 1፡15-16 ባለው ክፍል ውስጥ እንደሚነግረን የሚታዩትና የማይታዩት በሰማይና በምድር የሚገኙት ሁሉ በእርሱ ተፈጥረዋል። ይህም በዋናነት የተፈጠረውን ሁሉ ከእርሱ የሆነ በእርሱም የሆነ ደግሞም ለእርሱ ክብር የሆነ ይሆን ዘንድ የእግዚአብሔርን ክብር ባለጠግነቱንም ለማሳየት ታላቅነቱን ለማንፀባረቅ ታስበው የተፈጠሩ ያደርጋቸዋል።

*“ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ፣ የሰማይም ጠፈር የእጁን ስራ ያወራል”* ተብሎ በመዝሙረ ዳዊት 19 ላይ እንደተፃፈው የተፈጠሩት ሁሉ የእጁ አሻራ ያለባቸው ለፈጣሪያቸው ክብርን እንዲያመጡ ተደርገው የተሰሩ ፍጥረቶቹ ናቸው።

ይህም የሁሉ ፈጣሪነቱ በፈጠረው ሁሉ ላይ ሙሉ የባለቤትነት ስልጣንን የሚሰጠው ሲሆን የተፈጠሩትንም ሁሉ ለፈጣሪያቸው የመታዘዝ የሚገባውን ክብርም ለእርሱ የማምጣት ግዴታን የሚጥልባቸው ነው።

እግዚአብሔር በፈጠረው ሁሉ ላይ ሉአላዊ መብትና የማስተዳደር ስልጣን ብሎም በቂ ኃይልና ታላቅነት ያለው ከማንም በሚያገኘው ምስጋናና ውዳሴ የሚጨመርለት የጎደለ ክብር የሌለው ቢሆንም የእርሱ የሆነውንና ለእርሱ ብቻ የሚገባውን ማንም ለሌላ ያልተገባው አካል ሲሰጥ ማየት ግን አይፈልግም።

“ምንም እንኳን እግዚአብሔር በፈጠረው ሁሉ ላይ ሉአላዊ መብትና የማስተዳደር ስልጣን ብሎም በቂ ኃይልና ታላቅነት ያለው ከማንም በሚያገኘው ምስጋናና ውዳሴ የሚጨመርለት የጎደለ ክብር የሌለው ቢሆንም የእርሱ የሆነውንና ለእርሱ ብቻ የሚገባውን ማንም ለሌላ ያልተገባው አካል ሲሰጥ ማየት ግን አይፈልግም።”

እግዚአብሔር የሚፈጥረውን ሁሉ ፈጥሮ ከጨረሰ በኋላ አንድ በራሱ መልክ የፈጠረውን ፍጡር ይኸውም ሰውን በፈጠረው ሁሉ ላይ ገዥ እንዲሆን ነግሮት በዘመኑም ሁሉ እርሱን እንዲያከብር ለእርሱም እንዲገዛ አስጠነቀቀው። ነገር ግን ከተፈጠሩት መካከል መታዘዝን ያልወደደ አንድ ኪሩብ ባለመታዘዙ ምክንያት የደረሰበት ታላቅ ውድቀት የዚሁ የእግዚአብሔር ብቻ የሆነ ክብርን እና ስልጣንን በመፈለግ ምክንያት የመጣ ነበር።

መጽሐፍ ቅዱስ በኢሳይያስ 14 እና በህዝቅኤል 28 ላይ በዝርዝር እንደሚነግረን በውበቱ ያማረ ሆኖ የተፈጠረው በፈጣሪውም እጅግ የከበረ ስፍራን ያገኘው በመንገዱም ሁሉ ፍጹም የነበረው ጥበብን የተሞላ ውበቱም የተፈፀመ መደምደሚያ የነበረ ይህ ኪሩብ ልቡ ኮርቶ የእግዚአብሔር ብቻ የሆነውን ክብርና አምላክነት በመፈለጉ በልቡም ወደ ሰማይ አርጋለሁ ዙፋኔንም ከእግዚአብሔር ከዋክብት በላይ ከፍ ከፍ አደርጋለሁ በማለቱ ምክንያት በተገለጠ ታላቅ ኃይሉ የእነዚህ ሁሉ ህጋዊ ባለቤትነት ያለው እግዚአብሔር

ክብሩን፣ አምላክነቱን፣ ስልጣኑን ወዘተ ለማስከበር በቀናው ቅናት ምክንያት ከከፍታው እንዲወድቅ ሆነ።

ይህም የእግዚአብሔር ቅናት ለእርሱ ብቻ የተገባውን አምልኮ፣ ዙፋን፣ ክብር፣ ስልጣን፣ ውዳሴ ወዘተ ለሌላ ያልተገባው አካል ላለማካፈልና ላለመስጠት የነገሮቹ ባለቤት የሆነው እግዚአብሔር የቀናው ህጋዊ የሆነ ቅናት ነው።

በዚህም አለመታዘዙ ምክንያት ከነበረበት ከፍታ ላይ የተጣለው ይህ ኪሩብ ከእርሱ ጋር የተባበሩትን ሁሉ አስከትሎ የዘላለም ፍርደኛ ሆኖ የቅጣት ጊዜውን እየጠበቀ በምድር ላይ መመላለስ ጀመረ። በዚህም ምልልሱ አንድን ፍጹም የሆነ በእግዚአብሔር መልክና ምሳሌ የተሰራ ሊታለል የሚችል ፍጡር ይኸውም ሰውን አግኝቶ የአመጹና የአለመታዘዙ ተባባሪ ይሆን ዘንድ በተንኮሉ በሽንገላ አታለለው። ይህም የሰው ውድቀት ለቃሉ ታማኝ የሆነውን እግዚአብሔር የሰው ልጅ ለተላለፈው መተላለፍ የሚገባውን ቅጣት ይኸውም ሞት እንዲሞት ይፈርድበት ዘንድ አስገደደው።

ጠላት ዲያብሎስ ጌታችን ኢየሱስን በምድረ በዳ በፈተነበት ወቅት እንዳለው በማሳቱና ይህን ተከትሎ በተፈጠረው የሰው ውድቀት ምክንያት ለሰው የተሰጠውን ሁሉ የዚህ አለም መንግስታት፣ ክብርና ብልጥግናቸውን ጭምር በህጋዊነት የተቀበለ የሚገዛ ለሚሰግዱለትም የሚሰጥ ሲፈልግም የሚቀማ የዚህ አለም ገዥ ሆነ። የዚሁ የተጣለ ኪሩብ ሽንገላ ሰለባ የሆነው የሰው ልጅ ጳውሎስ በ1ኛ ጢሞቴዎስ 1፡13 ላይ *“ሳላውቅ ባለማመን ስላደረግሁት ምህረትን አገኘሁ”* ብሎ እንዳለ ምንም እንኳን የእባቡን ምክር ሰምቶ የተታለለ እና ሞት የተገባው ቢሆንም በስህተቱ ምክንያት አሳልፎ የሰጠውን የእግዚአብሔር ግዛት ብሎም ለሰው ልጅ የተሰጠውን ስልጣን ካልተገባ አታልሎ የወሰደ አመፀኛ አካል ላይ ይወስድ ዘንድ ከዚሁ የወደቀ የሰው ዘር ውስጥ የተበላሸውን የሚያስተካክል መድሃኒትን ሊያመጣ በዚህም አለምን ሁሉ ለማዳን ሀጢአትን ሊቀጣ እግዚአብሔር ወሰነ።

ይህንንም ለማድረግ እግዚአብሔር በዘመናት መካከል ከእርሱ ጋር ሊተባበሩ የወደዱ ቤተሰቦችን እየተከተለ ኪዳን እያደረገ ኖረ። በዚህም መልኩ በሄደው ሁሉን የማስመለስ መንገድ ውስጥ ይሄው የተጣለ እባብ እግዚአብሔር እንዳለው ከሴቲቱ ንጹህ

የሆነ ዘር እንዳይመጣ ያልተገባን ግንኙነት ከሰው ልጆች ሴቶች ጋር በማድረግ ሙከራን ያደረገ ሲሆን ከዚያም በኋላ እግዚአብሔር አብሯቸው ሊሰራ የወደዳቸውን ሁሉ ባገኘው መንገድ ሁሉ በመከራ ውስጥ በማሳለፍ ይህንን የማዳን ሂደት ለማስተጓጎልና መንግስቱን፣ ስልጣኑን፣ ክብሩን ወዘተ ለማጽናት ብዙ ሙከራን አድርጓል። የተመረጠቸው ሳራ በአቤሜሌክና በፈርዖን መፈለጓ፣ በየዘመኑ የተሞከረው እግዚአብሔር የመረጠውን የእስራኤል ህዝብ ዘር የማጥፋት መከራ፣ የዳዊትን ዘር ከዙፋኑ ለማጥፋት በተደጋጋሚ የተደረጉ የዘር ማጥፋት መኩራዎች፣ የህዝቡ ተደጋጋሚ ውድቀት ወዘተ የዚሁ ማሳያዎች ናቸው።

ነገር ግን እግዚአብሔር ከመጀመሪያውም የነበረው የፈቃዱ ምክር በሰማይና በምድር ያለውን ሁሉ በክርስቶስ መጠቅለል መንግስቱም ሁሉን ትገዛ ዘንድ ማስቻል ነበርና ይህንን ለእርሱ ብቻ የተገባ ክብርንና ስልጣንን ፈጽሞ የራሱ እስኪያደርግ፣ ጠላቶቹም የእግሩ መረገጫ እስኪሆኑና ለዘላለም ፍርድ ወደ እሳት ባህር እስኪጣሉ ድረስ ለሰው ጥቅም ሲባል በሆነ ትዕግስት ያልተገባን ከባህሪይው ውጭ የሆነ የአመጽ እንቅስቃሴ በየቀኑ በየቦታው ዛሬም በምድር ላይ እያየ ስለ ስሙ መቅናቱ ቀጥሏል።

ጠላት ዲያብሎስ ከሰው አታልሎ ሳይገባው የወሰደውን ስልጣንና የዚህ አለም ገዥነት ተጠቅሞ በሸንገላው የሰው ልጆችን ሁሉ እንዲሰግዱለት አደረገ። በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር ለእርሱ ብቻ የሆነ የተለየን ርስቱ፣ ህዝቡና ወገኑ የሆነ እስራኤል የሚባል ህዝብ በአህዛብ መካከል ለይቶ አወጣ። ታዲያ ይህ ወገን የሆነ ህዝብ በዙሪያው ካሉ በርካታ አማልክት ያሏቸው አህዛብ ጋር በምንም መልኩ እንዳይመሳሰል የተነገረው ይልቁንስ የአምላኩን የእግዚአብሔርን ቅናት የሚቀና የመንግስቱንም መገለጥ የሚናፍቅ እርሱን ለዚሁ ጉዳይ የለየውንና የቀደሰውን አምላኩን ብቻ ወድዶ የቀረበ የሚያመልከውም እንዲሆን የተገባው ነበር። (Van De Mieroop, 2016) (ማኅበር, 1954)

እግዚአብሔር ኪዳኑን ከዚህ ህዝብ ጋር ካፀናበት ጊዜ ጀምሮ በዘፀዓት 20:6፣ በዘፀዓት 34:14፣ በዘዳግም 34:14፣ በዘዳግም 4:24፣ በዘዳግም 5:9፣ በዘዳግም 6:14 እንዲሁም በኢያሱ 24:19 ላይ ደጋግሞ ከተገባው ከአንዱ ከእግዚአብሔር በቀር በላይ በሰማይ ካለው በታችም በምድር ካለው ከምድርም በታች በውሃ ውስጥ ካለው ነገር

የማናቸውንም ምሳሌ የተቀረፀውንም ምስል ለእርሱ እንዳያደርግ፣ እንዳይሰግድላቸው እንዳያመልካቸውም አስጠንቅቆ፣ ይህ ባይሆን ግን በዚህ እግዚአብሔር አምላኩ የሚቀና ቀናተኛ አምላክ እንደሆነ ይናገራል። የዚህም ዋና ምክንያት ዳዊት በመዝሙሩ 96፡5 ላይ እንደሚነግረን ለእግዚአብሔር ከተለየው ይህ ልዩ ወገን የሆነ ህዝብ እስራኤል በቀር አህዛብ ሁሉ የሚያመልኩት አጋንንትን እንደሆነ እና ማንም ከእግዚአብሔር ሌላ ለየትኛውም ምስል፣ ቅርጽ፣ ፍጡር፣ ግዑዝ አካል ወዘተ የሚያቀርበው ስግደት፣ አምልኮ፣ ውዳሴ፣ ክብር ወዘተ ለእግዚአብሔር ብቻ የተገባ ነውና ላልተገባው አካል በመቅረቡ ምክንያት እግዚአብሔርን የእርሱ ብቻ የሆነውን ለእርሱ ብቻ ይሆን ዘንድ መብቱን ለማስከበር በቅናት እንዲገለጥ ያደርገዋል።

ይህንኑ ሃሳብ አጠንክሮ ሙሴ ለእስራኤል ህዝብ በዘዳግም 4፡15-19 ላይ ባለው ክፍል ሲናገር እግዚአብሔር ከዝህቡ ጋር ኪዳን ለማድረግ በኮሬብ በእሳት ውስጥ ሆኖ ተገልጦ ሲናገር ከድምጽ በስተቀር ምንም የሚቀረጽ መልክ እንዳላየ በማስታወስ ከዚህ በተቃራኒው በዙሪያቸው እንዳሉ አህዛብ ያሉትን አምላካቸውን ምስልና ቅርጽ ሰርተው በማናቸውም ነገር ምሳሌ በወንድ፣ በሴት፣ በእንስሳ፣ በወፍ፣ በምድር ላይ በሚሽከረከረው፣ በውሃ ውስጥ በሚኖረው ዓሳ፣ እንዲሁም አይኖቹን ወደ ሰማይ አንስቶ አምላኩ እግዚአብሔር ከሰማይ ሁሉ በታች ላሉት አህዛብ ሁሉ ያለ ልዩነት የሰጣቸውን ፀሀይንና ጨረቃን፣ ከዋከብትንና የሰማይን ሰራዊት ሁሉ አይቶ እንዳይሰግድላቸው እንዳያመልካቸውም በዚህም ምክንያት ስቶ እንዳይረክስና ከእግዚአብሔር ቅድስና እንዳይጎድል ደጋግሞ ያስጠነቅቃቸዋል።

ይህ ሁሉ ባይሆን ግን እግዚአብሔር የእርሱ ብቻ የሆነውን ለእርሱ ብቻ ለማድረግ የሚተጋ የሚባላ እሳት ቀናተኛ አምላክም እንደሆነ በዚሁ በዘዳግም 4፡24 ላይ ይናገራል።

> “እግዚአብሔር የእርሱ ብቻ የሆነውን ለእርሱ ብቻ ለማድረግ የሚተጋ የሚባላ እሳት ቀናተኛ አምላክም እንደሆነ ማወቅ ያስፈልጋል።”

መጽሐፍ ቅዱስ በሮሜ 11፡36 ላይ *“ሁሉ ከእርሱ በእርሱ ለእርሱም ነውና ለእርሱ ለዘላለም ክብር ይሁን”* ይላል። ይህም እንዲሁ ተነብቦ ብቻ የሚታለፍ ቃል ሳይሆን ሁሉን

ለራሱ ክብር የፈጠረ ከፍጥረቱም ሁሉ ክብርን ለዘላለም ሊቀበል የተገባው ሌላ አንዳች የሌለ ፈጣሪው የሆነው ይህ ሁሉ ለብቻው የተገባው ብቸኛ ባለመብት እርሱ ብቻ እንደሆነ ከእርሱም ሌላ እንደሌለ የሚያስታውቅ ቃል ነው። ይህንኑ ሃሳብ ዳዊት በዝርዝር ሲነግረን በ1ኛ ዜና 29፡10-15 ላይ ባለው ክፍል ውስጥ *"በሰማይና በምድር ያለው ሁሉ የአንተ ነው፣ ታላቅነትና ኃይል ክብርም፣ ድልና ግርማም የአንተ ነው፣ መንግስትም፣ በሁሉ ላይ ከፍ ከፍ ማለትና ራስነት፣ ባለጠግነትና ክብር፣ ሁሉን ገዥነት፣ ኃይልና ብርታት"* የእርሱ ብቻ እንደሆነ ይናገራል። ከዚህም የተነሳ ስለሚገባው እንደሚገዙለት ለክቡር ስሙም ምስጋናን እንደሚያቀርቡ ሁሉ ደግሞ ከእርሱ ዘንድ ነውና ከእጁ የተቀበሉትን መልሰው ለፍቅራቸው መግለጫ ይሆንላቸው ዘንድ ለእርሱ እንደሚያቀርቡት ይናገራል።

ይህ ሁሉ ከላይ የተዘረዘረ ነገር ለእግዚአብሔር ብቻ የተገባ የእርሱ የሆነ ሀብቱ ሲሆን ይህንን በየትኛውም መልኩ ያልተገባው ሌላ አካል ሊወስደውና ሊቀበለው ሲሞክር ሲያይ በዚህ እግዚአብሔር ይቀናል። እግዚአብሔር በዚህ ይቀናል ብለን ስንል ይወስድብኛል ወይም ያንስብኛል ብሎ ይፈራል ማለት ግን አይደለም። ነገር ግን እርሱ ብቻውን ቅዱስና ክቡር ለዘላለም ይሆን ዘንድ የተገባው ስለሆነ መንግስቱም ሁሉን ትገዛ ዘንድ ስለሚገባት፣ በስሙ የተጠራ የእርሱ ሊሆንም የተመረጠው ህዝብ የሌላ ይሆን ዘንድ ስለማይገባ፣ ይህም ህዝቡን ከወደደበት ከታላቅ ፍቅሩ የተነሳ ለሰው ልጆች ጥቅም የሚቀናው ቅናት ነው።

> "እግዚአብሔር በዚህ ይቀናል ብለን ስንል ይወስድብኛል ወይም ያንስብኛል ብሎ ይፈራል ማለት ግን አይደለም።"

በዚህም ቅናት ብርሃን በጨለማ ላይ፣ ጽድቅና ቅድስና በአመጽና በሀጢአት ላይ፣ ፍትህና ፍርድም በፍርድ መጓደልና በበደል ላይ እንዲነግሱ ሁሉ በእርሱ ዘንድ ባለው በዚያ ሀሳብ በሰማይ እንዳለው ፈቃዱ እንዲሁ በምድር ይሆን ዘንድ አሮጌውን አጥፍቶ ሁሉን አዲስና ትክክል ለማድረግ በመልካምነቱ ይንቀሳቀሳል።

መጽሐፍ ቅዱስ በኢዮብ መጽሐፍ 35፡6-8 ላይ እንደሚናገረው ሰው ሃጢአትን ቢያደርግና እግዚአብሔርን አላመልክም ቢል እግዚአብሔር የሚጎድልበት አንዳች ነገር

የሌለ ሲሆን በተቃራኒው ደግሞ ጽድቅን ቢያደርግ እግዚአብሔርንም ቢፈራ ለራሱ ጥቅም ካልሆነ በቀር ለእግዚአብሔር የሚሰጠውና የሚጨምርለት እግዚአብሔር የጎደለበት ከሰው እጅ የሚቀበለው ጉድለት እንደሌለ በግልጽ ይናገራል። እግዚአብሔር ክፉውን በመልካም፣ ሀጢአትን በጽድቅና፣ ክፉትን በመልካምነት ወዘተ ይቀይርና ሁሉን ደህና ያደርግ ዘንድ ለስሙ፣ ለቅድስናው፣ ለጽድቁ፣ ለመንግስቱና ለህዝቡ ይቀናል። ለዚህም አይነተኛው ማሳያ እስራኤላዊያን በራሳቸው ሀጢአትና መተላለፍ የእግዚአብሔርን ተግሳጽ አልሰማ ብለው ለጠላቶቻቸው በተሰጡ ጊዜ በሚገዟቸው አህዛብ የደረሰባቸውን ግፍና በደል ተመልክቶ እግዚአብሔር በዘካርያስ 1:14 ላይ በታላቅ ቅናት በኢየሩሳሌምና በጽዮን መቅናቱን ተናግሮ ወደ ኢየሩሳሌም በምህረት መመለሱን ይናገራል።

ከዚህ ውጭ ግን እግዚአብሔር አንዳች ነገርን ፈልጎ ወደ ሰው ልጆች እንደማይመጣ መጽሐፍ ቅዱስ በዘዳግም 10:12-17 ውስጥ ባለው ክፍል በግልጽ ይናገራል። በዚህም ክፍል ውስጥ አምላኩ እግዚአብሔር ከዚህ ህዝብ የሚፈልገው አንዳች ነገር እንደሌለ ነገር ግን አባቶቹን እንደወደደ ኪዳንንም ለእነርሱና ለዘራቸው እንደሰጠ መልካም ይሆንላቸውና ለአባቶቻቸው የገባውን ኪዳን ለእነርሱ ደግሞ ይጠብቅ ዘንድ እንዲፈሩትና እንዲያከብሩት ከእርሱም በቀር ሌላ አምላክን እንዳያመልኩ ይልቁንስ የልባቸውን ክፉት እንዲገርዙና በእርሱ መልክና ምሳሌ እንዲመላለሱ እንጂ አስቀንተውት እንዳይጠፉ፣ የሚላቸውን የሚሰሙ እንጂ አንገተ ደንዳና እንዳይሆኑ ለራሳቸው ጥቅም ነው።

በዚህ መልኩ ከእግዚአብሔር ጋር ኪዳን ውስጥ የገባና በጥላው ስር የሚያድር ህዝቡ የሆነ ሁሉ፣ እርሱ የእርሱ ብቻ የሆነውን እንደሚፈልግና ከዚህ የተለየ ሁኔታን ሲያይ አምላኩ እንደሚቀናው እርሱ ደግሞ የእግዚአብሔርን ቅናት ይቀና ዘንድ ይገባዋል። ይህም መጨረሻው በእውነት እርሱ እግዚአብሔር ብቻ አምላክ እንደሆነ ከእርሱም በቀር ሌላ እንደሌለ ማሳየትና ለእግዚአብሔር ክብርን ማምጣት ነው።

እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን የሚቃወምና ለትሁታን ፀጋን የሚሰጥ እውነተኛ አምላክ ነው። የባቢሎን ግንብ፣ የናቡከደነፆር ትምክህት፣ የብልጣሶር ድፍረት፣ የሄሮድስ ራሱን እንደ አምላክ ማየት፣ እንዲሁም የትዕቢት ሁሉ አባት የሆነው ዲያብሎስ ውድቀት ለዚህ ማሳያዎች ናቸው።

መጽሐፍ ቅዱስ በኢሳይያስ 42፡8 እንደሚናገረው *“እግዚአብሔር እኔ ነኝ ስሜ ይህ ነው ክብሬን ለሌላ ምስጋናዬንም ለተቀረፁ ምስሎች አልሰጥም።”* ብሎ በዚህ ጉዳይ ላይ እግዚአብሔር ያለውን ጽኑ አቋም ይናገራል። በዚህም መሰረት እግዚአብሔር አምላኩ የሆነለት ህዝብ እርሱ እንደሚመላለስ የሚመላለስ፣ የሚጠላውን የሚጠላ፣ የሚወድደውን የሚወድ፣ የስሙን ክብርና ቅድስናውን በህይወት ምልልሱ የሚገልጥ እንዲሆን ይጠበቅበታል። ለዚህም ነው መጽሐፍ ቅዱስ በዘሌዋዊያን 22፡32 ላይ ህዝቡ ይሆን ዘንድ ለተመረጠው እስራኤል *“የተቀደሰውንም ስሜን አታርክሱ እኔ ግን በእስራኤል ልጆች መካከል እቀደሳለሁ”* ብሎ የሚለው።

> “ከእግዚአብሔር ጋር ኪዳን ውስጥ የገባና በጥላው ስር የሚያድር ህዝቡ የሆነ ሁሉ፣ እርሱ የእርሱ ብቻ የሆነውን እንደሚፈልግና ከዚህ የተለየ ሁኔታን ሲያይ አምላኩ እንደሚቀናው እርሱ ደግሞ የእግዚአብሔርን ቅናት ይቀና ዘንድ ይገባዋል።”

ምንም እንኳን የተመረጠው ህዝቡ ሁሉ ያለ ልዩነት በቅድስና ይገኝ ዘንድ ይፈልግ እንጂ ወደ እርሱ ለመቅረብ የበለጠ እድል የሚያገኙ ሁሉ ደግሞ ባገኙት እድል ልክ የበለጠ ቅድስና ይኖራቸው ዘንድ ይጠበቅባቸዋል። ይህንኑ ሲናገር ለማጠን እድል ያገኙት የአሮን ልጆች ናዳብና አብዩድ በእሳት የተበሉበት ምክንያት፣ ሙሴ ወደ ተስፋዋ ምድር ያልገባበት ምክንያት፣ ሀናንያና ሰጲራ የከፈሉት ዋጋ እግዚአብሔር “በሚሰራበት” ጊዜ ወደ ፊቱ መቅረብ እድል ያገኙ ሁሉ የሚጠበቅባቸውን ቅድስና የሚያሳይ ሲሆን ባይሆን ግን ቅናቱ /በእርሱ መገኘት መካከል የተገለጠን አለመታዘዝ ለመቅጣት/ በዚያ እንደሚገለጥ ይታያል።

የእርሱ የሆነ ህዝቡ እርሱ እንደሚመላለስ ከመመላለስ ባለፈ የእርሱን ቅናት የሚቀና እንዲሆን ደግሞ ይጠበቃል። ይህም ማለት ከእግዚአብሔር ባህሪ ውጭ የሆነን ምልልስ የሚጠላ፣ በዚያም ቦታ በዚሁ የእግዚአብሔር ማንነት ላይ የተገለጠውን ከፍ ያለ

የሰውና የዲያብሎስ ሃሳብ የሚያፈርስ በፋንታውም እውነተኛ ሆነውን የእግዚአብሔርን መልክና ሃሳብ የሚገልጥ እንዲሆን ያስፈልገዋል።

ፊንሃስ እስራኤላዊያን እግዚአብሔርን በመበደላቸው ምክንያት በተፈጠረ መቅሰፍት መካከል ወደ አምላካቸው ሲፀልዩ በተቃራኒው ምድያማዊቷን ወደ ድንኳኑ ይዞ የገባውን እስራኤላዊ ከሴቷ ጋር በጦር ወግቶ መግደሉ፣ ኤልያስ በቀርሜሎስ “እግዚአብሔር ወይም በዓል አምላክ ይሁን” ብሎ የተወራረደው ውርርድ፣ እውነተኛው ምሳሌያችን የሰው ልጆች ሁሉ ትኩር ብለው ሊያዩትና ሊከታተሉት የተገባው የሰው ልጅ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ “ቤቴ የፀሎት ቤት ይባላል” ብሎ ለአባቱና ለአምላኩ የቀናው ቅናት ለዚህ ዋና ማሳያ ነው። ዳዊት በመዝሙሩ 69፡9 ላይ “የቤትህ ቅንዓት በልታኛለች” ብሎ “የሚሰድቡህም ስድብ በላዬ ወድቆአልና” የሚለው ጥቅስ እውነተኛ የእግዚአብሔርን ቅናት መቅናት ምን ማለት እንደሆነ ይኸውም በእግዚአብሔር ላይ የሚነገር የትኛውም ስድብ እርሱ ራሱ ዳዊት እንደተሰደበ የሚሰማው ስለዚህም ስድብን ሁሉ የሚታገስበትና ዋጋ የሚከፈልለት ጉዳዩ እንደሆነ ያሳያል።

“እግዚአብሔር ክብሩን ለማንም አያጋራም።”

እግዚአብሔር ክብሩን ለማንም አያጋራም። ሰው በተሰጠው ዘመን እግዚአብሔርን እንደሚገባ በማወቅ በፊቱ በብዙ አክብሮትና ፍርሃት በአገባብም ሊመላለስ ደግሞ ያስፈልገዋል። ከዚህ በተቃራኒው ግን የእግዚአብሔርን ቅናት የሚያስነሳ የትኛውም አይነት እንቅስቃሴ እግዚአብሔርን ለስሙና ለክብሩ ራሱ እንዲንቀሳቀስ ያስገድደዋል።

ይህ የእግዚአብሔር ቅናት ከመልካምነቱ እና ከፍቅሩ ጋር አብሮ ደግሞ ፃድቅና ፈራጅ እንዲሁም ቅዱስ ከመሆኑ ጋር የተስማሙ በራሱ ማስተዋል በፍጥረቱ መካከል የሚገለጥ ባህርይው ነው። እግዚአብሔርን መጀመሪያ ከፈጠረው ሰው አዳም ጀምሮ ትውልድ ሁሉ እየበደለው ጽድቁንም እየገፋ የኖረ

“የእግዚአብሔርን ቅናት የሚያስነሳ የትኛውም አይነት እንቅስቃሴ እግዚአብሔርን ለስሙና ለክብሩ ራሱ እንዲንቀሳቀስ ያስገድደዋል።”

ሲሆን በዚህ መካከል የሚማልድ ጽድቅንም የሚያደርግ በጠፋበት ጊዜ የገዛ ክንዱ መድሃኒትን እያመጣለት ጽድቁም እያገዘው የገዛ ልጁ ጽድቅን እንደ ጥሩር ለብሶ የማዳንን ራስ ቁርም በራሱ ላይ አድርጎ የበቀልንም ልብስ ለብሶ በቅንዓትም መጎናፀፊያው ተጎናጽፎ መጥቶ ከሰው ልጆች መካከል ማንም ሊያደርግለት ያልቻለውን የእግዚአብሔርን በቀል ተበቅሏል።

በዚህም መሰረት በመስቀል ላይ በመሞት ሀጢአትን በመግደል ዲያብሎስን ስልጣን ቀምቶ ሁሉን ትገዛ ዘንድ መንግስቱን ደግሞ በምድር ላይ ገልጦ ይህንንም በሰማይና በምድር ሁሉ ላይ ያገኘውን ስልጣን ለሚያምኑበት ሁሉ የእግዚአብሔርን ቅንዓት ይቀኑና ጽድቅና ቅድስናውን በምድር ይገልጡ ዘንድ በሰማይና በምድር ያለውን ሁሉ በክርስቶስ የመጠቅለል ስራውን እንዲያግዙ ሰጣቸው።

እግዚአብሔር መሐሪ፣ ፍቅርና መልካም ነው ማለት ይዘበትበታል ማለት አይደለም። እርሱ አንዳች ያልጎደለው የሁሉ ባለቤት የሆነ ከማንም አንዳች ነገር የማይፈልግ ሰው ሁሉ ውሸተኛ ቢሆን እርሱ ብቻውን እውነተኛ የሚሆን ሁሉ በሁሉ የሆነ ታላቅና የተፈራ አምላክ ነው። ክብሩንና ቅድስናውን የሚገልጥ ሰው ባይኖር እንኳን እርሱ ራሱ ለስሙ የሚቀና ባልቀደሱትም መካከል በታላቅ ግርማው ተገልጦ ስሙን የሚያከብርና የሚቀድስ እርሱ ብቻውን አምላክ እንደሆነ ከእርሱም በቀር ሌላ እንደሌለ የሚያስታውቅ ቀናተኛ አምላክ ነው።

ከአታላይቱም ይሁዳ ይልቅ ከዳተኛይቱ እስራኤል ፀደቀች ተብሎ እንደተፃፈ የእርሱን ብዙ ሞገስ ያገኘ ምህረትም የበዛለት ሁሉ በፊቱ በዚያው ልክ በብዙ አክብሮትና ፍርሃት በፊቱ ሊመላለስ ደግሞ ያስፈልገዋል። እርሱ የሚያከብሩትን የሚያከብር የናቁትን ደግሞ የሚንቅ በደለኛውንም ከቶ የማያነጻ ፍርድን የማያጓድል ፍፁም ፃድቅ ፈራጅና እውነተኛ የሆነ አምላክ ነው። ከባህሪይው ውጭ ይሆን ዘንድ እንደማይችል ሲገልጽ "ይህ አይሆንልኝም" ብሎ ይላል።

> "እግዚአብሔር መሐሪ፣ ፍቅርና መልካም ነው ማለት ይዘበትበታል ማለት አይደለም።"

እግዚአብሔር ስለ ቅዱስ ስሙ ይቀናልና እግዚአብሔርን እንደ እግዚአብሔርነቱ መጠን አለማክበር ታላቅ ዋጋን ያስከፍላል። ዛሬም በርካቶች እግዚአብሔርን ትተው ገንዘብን፣ ትዳርን፣ አገልግሎትን፣ ስልጣንን፣ ልጅን፣ ወዘተ ሲያመልኩና በልባቸው ከእርሱ የበለጠ ስፍራ ይዘው ሲያይ ይቀናል። ይህም ብቻ አይደለም እንዲህ ያሉ ሰዎች እርሱን በገዛ ደሙ ከገዛውና ከዋጀው ህያው ሰውነታቸው /መቅደሱ/ ያርቁት ዘንድ ሲሞክሩ ሲያይ ስሙን ሊያከብር መቅደሱን ለማጥራት ይንቀሳቀሳል። በገዛ ደሙ በተዋጀችው መንፈሳዊዋ መቅደስ /የሰዎች ቅንብር/ ቤተክርስቲያንም እንዲሁ ይሆናል።

> "መጽሐፍ ቅዱሳችን በኢዮብ መጽሐፍ 35፡6-8 ላይ እንደሚናገረው ሰው ሃጢአትን ቢያደርግና እግዚአብሔርን አላመልክም ቢል እግዚአብሔር የሚጎድልበት አንዳች ነገር የሌለ ሲሆን በተቃራኒው ደግሞ ጽድቅን ቢያደርግ እግዚአብሔርንም ቢፈራ ለራሱ ጥቅም ካልሆነ በቀር ለእግዚአብሔር የሚሰጠውና የሚጨምርለት እግዚአብሔር የጎደለበት ከሰው እጅ የሚቀበለው ጉድለት እንደሌለ በግልጽ ይናገራል። እግዚአብሔር ክፉውን በመልካም፣ ሀጢአትን በጽድቅና፣ ክፋትን በመልካምነት ወዘተ ይቀይርና ሁሉን ደህና ያደርግ ዘንድ ለስሙ፣ ለቅድስናው፣ ለጽድቁ፣ ለመንግስቱና ለህዝቡ ይቀናል።"

- **የማስተንተኛ ጥያቄዎች**

1. የእግዚአብሔር ቅናት ስለ ፍቅሩና ስለ ቅድስናው ምን ያሳያል?
2. በሕይወትህ ውስጥ ከእግዚአብሔር ይልቅ የመጀመሪያ ስፍራን ለመያዝ የሚወዳደር ነገር አለ?
3. ዛሬ የእግዚአብሔርን ስም በበለጠ ታማኝነት እንዴት ማክበር ትችላለህ?

- **አሰላስል**

እግዚአብሔር ቀናተኛ ነው፤ ነገር ግን የእርሱ ቅናት እንደ ሰው ምቀኝነት ያለ አይደለም። እርሱ ብቻ ለአምልኮ፣ ለክብርና ለምስጋና የሚገባ ስለሆነ ቀናተኛ ነው። የእርሱ ቅናት ለሕዝቡ ያለውን ፍቅርና ለእርሱ ብቻ እንዲታመኑና ሁለንተናቸውን እንዲሰጡ ያለውን ፍላጎት ያሳያል። እኛ የእርሱ ስለሆንን፣ በሕይወታችን ከሁሉ በላይ እርሱን ማክበርና ለእርሱ ታማኝ በመሆን ለመኖር ተጠርተናል። ልባችንን ከሚፈልጉ ማናቸውም ነገሮች በመጠበቅ ለእግዚአብሔር ብቻ የተሰጠ ሕይወት መኖር ይጠበቅብናል።

- **ጸሎት**

በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፣ አምልኮና ክብር የሚገባህ አንተ ብቻ ስለሆንህ እናመሰግንሃለን። አንተን ብቻ እንዳመልክና በልቤ ቦታህን ሊወስድ የሚሻን ማንኛውንም ነገር እንዳስወግድ እርዳኝ። ስምህን በክብር እንዳነሳና በፊትህ በታማኝነት እንድመላለስ አግዘኝ። ሕይወቴ ሁሉ ለአንተ ብቻ የተሰጠ እንዲሆን እርዳኝ።

በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አሜን።

- **የአርምሞ ጥቅስ**

*"እኔ እግዚአብሔር ነኝ ስሜ ይህ ነው፤ ክብሬን ለሌላ፥ ምስጋናዬንም ለተቀረጹ ምስሎች አልሰጥም።"*

*– ትንቢተ ኢሳይያስ 42፥8 –*

## 2.27. እግዚአብሔር ተበቃይና መዓትን የተሞላ የሚቆጣም አምላክ ነው!

በ18ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በነበረችው ቤተክርስቲያን የመንፈሳዊ አገልግሎቶች ወይም የስብከቶችና የትምህርቶች ሁሉ አቅጣጫ የእግዚአብሔር ፈራጅነትና ቁጣ ላይ ብቻ ያተኮረ እንደነበር ታሪክ ይናገራል። ከዚህ በኋላ በመጡት ዘመናት ደግሞ ይህንኑ ለማስተካከል በሚመስል መልኩ ከእግዚአብሔር ቁጣና ፍርድ በላይ የአግዚአብሔር ምህረትና ፍቅር የግንኙነታችን መሰረት ነው በሚል በተጓዳኝነት የእግዚአብሔር ፍቅር መሰበክ ጀመረ። (Edwards, 2010)

ይሁን እንጂ ከ18ኛው ክፍለ ዘመን በኋላ የእኛን ዘመን ጀምሮ ከዚያኛው ዘመን በተቃራኒው የእግዚአብሔር ፍቅርና ምህረት ብቻ የሚዘመርበት፣ የሚሰበክበት ወዘተ የእግዚአብሔርን ፃድቅ ፈራጅነት ደግሞም ቁጣውን የዘላለምን ፍርድም የረሳ ሚዛኑን ያልጠበቀ ሆነ። (Tasker, 1951) ይህም ጉዳይ በርካቶችን ፀጋን እንዲያቃልሉ፣ የመዳን ነገር በጣም እንዲቀልባቸው፣ ሀጢአትን ቤተኛ እንዲያደርጉት፣ በስጋቸው እንደወደዱ መሆን የሚችሉ እንዲመስላቸው፣ ብዙዎችን በሰፊው የሞት መንገድ በሀይማኖተኝነት ቤተክርስቲያን ተመመላሾች ብቻ እንዲሆኑ ያደረጋቸውንና የእግዚአብሔርን ትክክለኛ የሆነ ሚዛናዊ መልክና ቁመና ያልገለጠ ሁኔታን አመጣ።

መጽሐፍ ቅዱስ በመዝሙረ ዳዊት ምዕራፍ 89፡14 ላይ ሲናገር የእግዚአብሔር የዙፋኑ መሰረት ጽድቅና ፍርድ እንደሆነ ምህረትና እውነትም ከፊቱ እንደሚሄዱ ይናገራል። ይህም ማለት የእግዚአብሔር እውነትና ምህረት ደግሞም ፃድቅ ፈራጅነቱ በዘመናት መካከል ኪዳን ሲለዋወጥ መሰረቱ ተነካክቶ ዙፋኑ ይነቃነቅ ዘንድ ፈጽሞ የማይለወጥ ጠንካራና ዘላለማዊ እንደሆነ ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ነው። ይህንንም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በስጋ ወራቱ ለደቀ መዛሙርቱ ሲያስተምር በማቴዎስ 7 ላይ ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ የሚለው ሁሉ መንግስተ ሰማያት እንደማይገባ ነገር ግን ፍሬ ማፍራት እንደሚያስፈልግ፣ እርሱ እንደተመላለሰ እንደዛው በተገለጠው ፀጋ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በማድረግ፣ እግዚአብሔርንም በማክበርና በመፍራት መመላለስ እንደሚያስፈልግ በግልጽ ነግሮናል። ይህም ተገቢ የሆነ ሚዛኑን የጠበቀ እውቀትን ስለ እግዚአብሔር

> “እውነቱና ምህረቱ ከፃድቅ ፈራጅነቱ እየቀደሙ በወደቅን ጊዜ ሁሉ በእውነተኛ ንስሃ በመመለስ ደግመን እንድንቆምና ወደ ፍጹምነት እንድንደርስ በዚህም ከፍርድ እንድናመልጥ ያስችሉናል።”

እንድናውቅ ትዕዛዙም በእኛ ዘንድ እንድትሆን እንድንጠብቃትም በዚህም መሰረት እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆነውን እርሱን የላከውንም ኢየሱስ ክርስቶስን በማወቅ የዘላለም ህይወት ይሆንልን ዘንድ ነው። በዚህም መሰረት እውነቱና ምህረቱ ከፃድቅ ፈራጅነቱ እየቀደሙ በወደቅን ጊዜ ሁሉ በእውነተኛ ንስሃ በመመለስ ደግመን እንድንቆምና ወደ ፍጹምነት እንድንደርስ በዚህም ከፍርድ እንድናመልጥ ያስችሉናል።

ከዚህ በፊት ባሉት ክፍሎች እንደተገለፀው እግዚአብሔር አላማው ፍቅር የሆነ ቸርነቱንና ምሕረቱንም እስከ ሺህ ትውልድ ለልጅ ልጅ የሚጠብቅ ታጋሽም አምላክ ነው። ከዚሁ ጋር በተመሳሳይ መልኩ እግዚአብሔር እርሱ ፍጹም ፃድቅና ቅዱስ እውነተኛም የሆነ አመጽንም ፈጽሞ የሚጠላ እንከን አልባ ንጹህ አምላክ ነው።

ጌታችንም ኢየሱስ ክርስቶስ የመምጣቱን ነገር እና የመጣበትን ዋና አላማ ሲነግረን *“እኔ ግን ህይወት እንዲሆንላችሁ እንዲበዛላችሁም መጣሁ”* ብሏል። እግዚአብሔር ቸርና ሩህሩህ መሐሪም ነውና ማንም በሀጢአቱ እንዳይጠፋ ነገር ግን በንስሃ ተመልሶ ከጥፋቱም አምልጦ በህይወት ይኖር ዘንድ፣ የተጣለ ሰው እንኳን ፈጽሞ እንዳይጠፋ በምክሩ ያስባል። እርሱ አንዷን የጠፋች ፍሊጋ ዘጠና ዘጠኙን በሜዳ ትቶ የሚወጣና የሚወርድ ርህራሄንም የተሞላ የፍቅር አምላክ ነው።

ይህ ሁሉ እውነት ሆኖ እያለ እግዚአብሔር ደግሞ ራሱን ይክድ ዘንድ የማይችል ከሀጢአትም ጋር ፈጽሞ የማይተባበር ፃድቅ ፈራጅ የሆነ በደለኛውንም ከቶ የማያነጻ ይልቁንስ ለሁሉ እንደ ስራው ይከፍል ዘንድ በእውነትና በጽድቅ የሚፈርድ አምላክም ነው። እርሱ ያከበሩትን የሚያከብር የናቁትንም ደግሞ የሚንቅ ለትሁታን ፀጋን የሚሰጥ ትዕቢተኞችንም የሚያዋርድና የሚቆጣ አንገቱ የደነደነንና ከጥፋቱ ሊመለስ ያልወደደን ይሰበር ዘንድ ለገዛ ፈቃዱ የሚተው ትክክል የሆነ አምላክ ነው። ከጥፋት ውሃ በኋላ ከኖህና

ከልጆቹ ጋር ሰው በምድር ሊመላለስ የተገባበትን መርህ ያስታወሰው እግዚአብሔር በዘፍጥረት 8፡22 ላይ በምድር ዘመን ሁሉ መዝራትና ማጨድ ብርድና ሙቀት፣ በጋና ክረምት እንዲሁም ቀንና ሌሊት እንደማይቋረጡ ተናግሯል።

ጳውሎስም ይህንኑ የመዝራትና የማጨድ ህግ ሲያስታውሰን በገላትያ 6፡7 ላይ መታለል እንደሌለብን ነግሮን ይኸውም እግዚአብሔር የሚዘበትበት አምላክ እንዳልሆነ ይልቁንስ ሰው ሁሉ የሚዘራውን ያንኑ ደግሞ የሚያጭድ እንደሆነ ይነግረናል። ይህም ማለት ሰው በተሰጠው ዘመን በሚመላለሰው ምልልስ ሞቱን ወይም ህይወቱን የሚወስን እርሱ ራሱ እንደሆነ፣ የእግዚአብሔርም ፍቅርና ምህረት ትዕግስቱም እኛን ወደ እቅፉ መጥሪያ፣ ድካማችንንም ማገዣ እንጂ እንደፈለግን በሀጢአት እንድንጨማለቅና የእግዚአብሔርን ፃድቅ ፈራጅነት እንድንረሳ እንዳልሆነ የዘራነውንም ልናጭድ በእርግጥ ቀን እንዳለ የሚያስታውሰን ነው።

ይህንንም ሁኔታ በሰው ልጆች ዘመን ሁሉ ከአዳም ጀምሮ ያየነው ሲሆን ይህም ዛሬም እንደዛው የቀጠለ ይልቁንስ ሀጢአት በመብዛቱ ምክንያት ገና ከመጀመሪያው የነበረውን በእግዚአብሔር ዘንድ ያለ ጥልቅ ፍቅር፣ ዘላለማዊ ቸርነትና ምህረት ለሰው ልጆች ሁሉ የገለጠ ከበዛውም ሀጢአት ይልቅ የበዛን የእግዚአብሔር ፀጋ ለእኛ ያስተዋወቀ የእግዚአብሔርንም መልካምነት የገለጠ ነው።

የአዳም ከኤደን መባረር፣ የጥፋት ውሃ፣ የቋንቋ መደበላለቅ፣ ሰዶምና ገሞራ፣ የግብጽ መቅሰፍቶች፣ የአሞራዊያንና ከነዓናዊያን ህዝቦች መጥፋት፣ የዳታን እና አቤሮን ቅጣት በብኤልፌጎር ምክንያት በሰጢም የተገለጠው የእግዚአብሔር ቁጣ፣ በ40 ዓመት ምድረ በዳ ላይ ያለቀው የእስራኤል ህዝብ፣ የእስራኤል በጥቂቶቹ የጋይ ሰዎች መመታት፣ የዘመነ መሳፍንት ጥፋቶች፣ በኤሊና በልጆቹ ብሎም በዘመኑ ህዝብ ላይ የደረሰው ሞት፣ የንጉስ ሳኦል ውድቀት፣ ዳዊት በኦርዮ ሞት ምክንያት የከፈለው ዋጋ፣ በሰለሞን ሀጢአት ምክንያት የእስራኤል ለሁለት መከፈል፣ የነገስታቱና የህዝቡ ውድቀት፣ የኢዮርብዓም የባኦስና የአክአብ ቤት ፈጽሞ መጥፋት፣ የእስራኤልና ይሁዳ ለጠላቶቻቸው ለምርኮ ተላልፎ መሰጠት፣ የባቢሎንና የአሦር እንዲሁም ሌሎች ታላላቅ ነገስታት ትዕቢትና ውድቀት፣ ቅጣት፣ የናቡከደነፆር እንደ እንስሳ መሆን፣ የብልጣሰር መንግስት መቀደድና

ሞት፣ የሔሮድስ በትል ተበልቶ መሞት፣ የኢየሩሳሌም የ70ዓ.ም መፍረስና መቃጠል፣ የሐናንያና ሰጲራ ሞት፣ የዮሐንስ ራዕይ መቅሰፍቶችና ቁጣዎች፣ አርማጌዶንና የመጨረሻው ቁጣ እንዲሁም የዘላለም ፍርድ ወንበር እነዚህ ሁሉ የዚሁ የመዝራትና የማጨድ ህጉ ውጤቶች ናቸው።

ከእነዚህ ሁሉ ውስጥ አንዱም እግዚአብሔር ሳይታገስ የምህረት እጁንም ሳይዘረጋ፣ የንስሃ ስብከትንም ሳይሰብክ ቁጣውን መቆጣጠር ከብዶት ራሱንም መግዛት አቅቶት ያደረጋቸው አይደሉም። ነገር ግን ሰዎች የእግዚአብሔርን ምህረትና ፍቅር ረግጠው በጥፋታቸው ለመቀጠል፣ በንስሃም ላለመለስ ወስነው ርቀው በመሄዳቸው ምክንያት ለክፉ ምኞታቸውና ለስጋ አምሮታቸው ለማይረባም አዕምሮ ተላልፈው ተሰጥተው የዘሩት በቅሎ አፍርቶም ያጨዱት ጥፋት ነው።

ከዚህ በፊት ባለው ክፍል በስፋት በተገለፀው መሰረት እግዚአብሔር ባለ ሰፊ ልብ፣ እጅግም ታጋሽ የሆነ የሰውንም ጥፋትና ሞት የማይወድ የፍቅር አምላክ ነው። ነገር ግን ይህ ማለት ፍርድን የሚያጓድል፣ በደለኛውንም ነጻ የሚያደርግ፣ የደሃውንም መገፋት በከንቱ የሚያልፍ፣ የናቁትንም የሚያከብርና እንዲሁ የሚተው አምላክ ነው ማለት አይደለም። ነገር ግን ትዕቢተኞችን ሊያዋርድ፣ የዘበቱበትንም ፍቅሩንም እንደ ከንቱ ነገር ያዩ፣ የምህረት እጁንም ደጋግመው የገፉ፣ የሚንቁትንም የሚንቅ፣ ተገቢንም ቅጣት የሚቀጣ ይህንንም ሳያደርግ እንዳይቀር ይህ አይሆንልኝም ብሎ ለነገሩ ያለውን ቁርጠኝነት እና እርግጠኝነት የተናገረ ፍጹም እውነተኛና ጻድቅ አምላክ ነው።

ይህንን በተገቢው መልኩ የሚገልጽልን ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በትንቢተ ናሆም 1፡2-3 ባለው ክፍል ውስጥ ይገኛል። *"እግዚአብሔር ቀናተኛና ተበቃይ አምላክ ነው፤ እግዚአብሔር ተበቃይና መዓትን የተሞላ ነው፣ እግዚአብሔር ተቃዋሚዎቹን ይበቀላል ለጠላቶቹም ቁጣውን ይጠብቃል፣ እግዚአብሔር ትዕግስተኛ ኃይሉም ታላቅ ነው በደለኛውንም ንጹህ ነህ አይልም።"* ብሎ ይናገራል። በዚህ ክፍል ውስጥ እጅግ በርካታ ሰፊና ጥልቅ ቃላት የሚገኙ ሲሆን የእግዚአብሔር ትዕግስት ፍርድን ለማድረግ የሚያስችለው የኃይል ማነስ ማሳያ እንዳልሆነ ይልቁንስ ኃይሉ ታላቅ እንደሆነ ነገር ግን ትዕግስትን ከቁጣ ይልቅ የሚያስቀድም ምህረትንም የሚወድድ ስለሆነ እንደሆነ ይታያል።

በዚሁ ክፍል በግልጽ እንደሚታየው ለጠላቶቹ ቁጣውን የሚጠብቅ እንደሆነ ለጥፋትም በቂና ተመጣጣኝ የሆነን ቅጣት ሊቀጣ የሚችልበት መዓትን የተሞላ እንደሆነ ይናገራል። እግዚአብሔር በደለኛውንም ከቶ ንጹህ ነህ የማይል ለሁሉ እንደ ስራው የሚከፈል የእርሱ ለሆኑትና ለሚወዱትም አይን ያላየውን ጆሮም ያልሰማውን በሰው እጅም ያልተዳሰሰ ዘላለማዊ በረከትን የጠበቀ እንደሆነ ይታያል። በዚህም እግዚአብሔር ለሚወዱት ያለው በጎነት በሚመጣው ዘመን ብቻ ሳይሆን በዚህኛውም የስጋ ወራት በሉአላዊ ስልጣኑ ከክፋት ሁሉ የእርሱ የሆኑትን የሚጠብቅበት፣ የሚያስፈልጋቸውን የሚሰጥበት፣ ከጠላቶቻቸውና ከሚመጣ ቁጣ የሚያስመልጥበት ኪዳን ያለው ርስቱን ለማላገጫ አሳልፎ የማይሰጥ ታማኝ አምላክ እንደሆነ ይታያል።

አግዚአብሔር ፍቅር እንደሆነው ሁሉ በኃይሉም ታላቅ የሆነ ልትጣሉትና ባለጋራው ልትሆኑ ፈጽማችሁ የማትመርጡት ሲቆጣ ከቁጣው ለማምለጥ መሸሸጊያ የማይገኝለት፣ ከፊቱ ተሰውሮ የሚያመልጥ በደል የሌለ፣ ሁሉ በፊቱ የተራቆተ የሆነለት፣ ሰማይ ምድሩን የሞላ፣ ለቅጣት ፍጥረቱን ሁሉ ሊጠቀምና ሊያዝ የሚችል እጅግም የተፈራ ብርቱና ኃያል የሚባላ እሳት የሆነ አምላክ ነው።

“እግዚአብሔር ፍቅር እንደሆነው ሁሉ በሃይሉም ታላቅ የሆነ ልትጣሉትና ባለጋራው ልትሆኑ ፈጽማችሁ የማትመርጡት ሲቆጣ ከቁጣው ለማምለጥ መሸሸጊያ የማይገኝለት፣ ከፊቱ ተሰውሮ የሚያመልጥ በደል የሌለው፣ ሁሉ በፊቱ የተራቆተ የሆነለት፣ ሰማይ ምድሩን የሞላ፣ ለቅጣት ፍጥረቱን ሁሉ ሊጠቀምና ሊያዝ የሚችል እጅግም የተፈራ ብርቱና ኃያል የሚባላ እሳት የሆነ አምላክ ነው።”

ይህም ቁጣው ለጠላቶቹ በዋነኛነትም ለዲያብሎስ የተዘጋጀ ሲሆን የእግዚአብሔርን የማዳን እጅ ለገፉና የምህረቱ ተጠቃሚ ሊሆኑ ላልወደዱ ሁሉም ዛሬም እንደ ትናንትናው በዚህ የስጋ ወራት እንዲሁም በሚመጣው ዘመን ለጥፋታቸው ተገቢ የሆነ ቅጣትን በጽድቅ በሆነ ፍርድ ሊቀጣ ለራሱ

የታመነ ነው። በዚሁ የትንቢተ ናሆም መጽሐፍ ምዕራፍ 1፡4-7 ባለው ክፍል ውስጥ እንደሚናገረው እግዚአብሔር በተቆጣ ጊዜ በቁጣው ፊት መቆምና ቁጣውን መታገስ የሚችል ማንም እንደሌለ ይናገራል።

ከዚህም የእግዚአብሔር ቁጣ ማምለጥ የሚችል ፍጡር ፈጽሞ እንደሌለ፣ ነገስታት ተራሮችን ውደቁብን ቢሉም እንኳን ተራሮች ራሳቸው ከፊቱ የሚሸሹ፣ ፀሃይና ጨረቃ ለራሳቸው የሚሄዱበትን የሚፈልጉ እንደሆነ በፊቱም ከቶ ሊገኝና ሊቆም የሚችል ማንም እንደሌለ ይታያል። እግዚአብሔር ሲነሳ ጠላቶቹ ይበተናሉ፣ ሰምም በእሳት ፊት እንደሚቀልጥ እንዲሁ ይቀልጣሉ፣ ጭስ እንደሚበንን ይበንናሉ እንጂ አንዳቸውም በፊቱ ይገኙ ዘንድ አይችሉም።

ይሄው የእግዚአብሔር ቁጣ ከበዛ ትዕግስት በኋላ ሲገለጥ ታዲያ የልቡን ሃሳብ ሳይፈጽም ከቶ የማይመለስ ሲሆን ይህም በዋነኛነት ስሙን ባላከበሩና ባልቀደሱ አህዛብ መካከል ስሙን ለመቀደስ በዚህም እርሱ ብቻውን እውነተኛ አምላክ እንደሆነ ከእርሱም ሌላ እንደሌለ ያውቁ ዘንድ ጽድቅና ቅድስናውን ለመግለጥ የሚያደርገው ነው።

ነገር ግን የሚመለስ በጥፋቱም የሚፀፀት በተገኘ ጊዜ ደግሞ ቁጣውን የሚተው እጅግም የሚራራ ሩህሩህ ጌታ ነው። ይህም የእግዚአብሔር ቁጣ ከመልካምነቱ፣ ከፍቅሩና ምህረቱ ብሎም ርህራሄው ጋር ያልተጋጨ ፃድቅና እውነተኛ ዳኛም ይሆን ዘንድ ራሱን ይክድ ዘንድ እንዳይችል ሊያደርገው የሚገባ አንድያ ልጁን ጭምር በመስቀል ላይ እንዲውልና የሰው ልጅን ሁሉ ቅጣት ይቀጣ ዘንድ ያደረገበት የማይለወጥ እውነተኛ የእግዚአብሔር ማንነት ነው።

እግዚአብሔር እንደ አባት የሚገባውን ክብር እንደ ጌታም የሚገባውን መፈራት በህዝቡ ዘንድ ያገኝ ዘንድ የሚፈልግ በብዙ አክብሮትና ፍርሃት ብቻውን ሊመለክ የሚገባው

“እግዚአብሔር እንደ አባት የሚገባውን ክብር እንደ ጌታም የሚገባውን መፈራት በህዝቡ ዘንድ ያገኝ ዘንድ የሚፈልግ በብዙ አክብሮትና ፍርሃት ብቻውን ሊመለክ የሚገባው እውነተኛ አምላክ ነው።”

እውነተኛ አምላክ ነው። ከዚህ በፊት ባለው ክፍል ስለ እግዚአብሔር ቅናት በተገለጸው መሰረት እግዚአብሔር የእርሱ ብቻ የሆነን ክብሩን ለማንም ሊያጋራ የማይወድ የእርሱ የሆነውንም ለማንም የማያስነካ ይህንንም ንብረቱንና ማንነቱን ለማስጠበቅ የሚችል በቂና ከበቂ በላይ የሆነ ኃይል ያለው ምህረትና ፍቅርንም የሚወድ ታጋሽ አምላክ እንደሆነ በስፋት ተገልጿል።

በዚህ መልኩ ፍትህን ለማስከበር በጽድቅና በቅድስናው ከመገለጡ በፊት በትንቢተ ኤርምያስ 7፡13፣ 11፡7፣ 26፡5፣ 29፡19፣ 32፡33፣ 35፡15ና 44፡4 ላይ ለይሁዳ ደጋግሞ ለጠላቶቿ ተላልፋ ከመሰጠቷ በፊት በማለዳ ከጥፋቷ እንድትመለስ እንደተናገረ በዘመናት መካከልም በዚሁ ትዕግስት ከቁጣው እንደዘገየ ዛሬም እንዲሁ ከፍርዱ በፊት እውነቱንና ምህረቱን ያስኬዳል።

ነገር ግን በዚሁ ክፍል ይሁዳ እንዳደረገችው የእግዚአብሔርን ምህረት አለመጠቀም ይልቁንስ የዚህ የእግዚአብሔር እውነት ሰባኪዎችን ማሳደድና መግደል እግዚአብሔርንም መቃወም በትውልድ ሁሉ መካከል ዛሬም ድረስ ይታያል። ከዚህም ወዲያ በይሁዳ ላይ የሰማርያን የጥፋት ገመድና የአክዓብን ቱንቢ በአንቺ ላይ እዘረጋለሁ፣ ብሎ ከእነርሱ በቀደሙ ላይ እንዳደረገው በየዘመናቱ ለትምህርታቸው ከተፃፈው ተምረው አካሄዳቸውን ከእርሱ ጋር ባላስተካከሉ ሁሉ ላይ ዛሬም የእግዚአብሔር ቁጣ እንደ ቀድሞው በልዩ ልዩ መንገድ ይገለጣል።

"ከአታላይቱም ይሁዳ ይልቅ ከዳተኛይቱ እስራኤል ፀደቀች" ተብሎ በትንቢተ ኤርምያስ 3፡11 ላይ እንደተባለ በእግዚአብሔር ፊት ብዙ ምህረትንና ሞገስን ያገኘ እርሱ ብዙ እግዚአብሔርን ማክበር በጽድቅና በቅድስናም መመላለስ ይጠበቅበታል። ይህ ባይሆን ግን ጌታችን ኢየሱስ ስብከቱን ለሰበከላቸው ብዙ ድንቅና ተዓምራትንም ላደረገባቸው የእስራኤል

> ""ከአታላይቱም ይሁዳ ይልቅ ከዳተኛይቱ እስራኤል ፀደቀች" ተብሎ እንደተጻፈ በእግዚአብሔር ፊት ብዙ ምህረትንና ሞገስን ያገኘ እርሱ ብዙ እግዚአብሔርን ማክበር በጽድቅና በቅድስናም መመላለስ ይጠበቅበታል።"

ከተሞች ለኢየሩሳሌምም ጭምር እንዳለ ለእነዚህ አይነት ሰዎች የተዘረጋው የእግዚአብሔር የምሕረት እጅ ይህን እድል ላላገኙ ቢዘረጋ ኖሮ እግዚአብሔርን የተሻለ ሊያከብሩ ይችሉ እንደነበር ተገልጿል። ይህም በእናንተ የተደረገው ድንቅና ተዓምራት በሰዶምና በገሞራ ተደርጎ ቢሆን ፈጥነው አካሄዳቸውን ያስተካክሉ ነበር ብሎ እንዳለ ይህንንም እድል እንደሚገባ ባለመጠቀማቸው ከሰዶምና ከገሞራ የበለጠ ቅጣትና ፍርድ እንደሚጠብቃቸው ገልጦ ያሳየበት ንግግር ነው።

ርስቱና ህዝቡ ለመሆን እድል ያገኘን ሁላችን ከአህዛብ የተለየ የጽድቅና የቅድስና ኑሮ እንዲኖረን በኑሮአችንም እግዚአብሔርን እንድናከብር ይጠበቅብናል። ተመልሶ ሊመጣ የእርሱ የሆኑትን ሊወስድ ቃል የገባው ጌታችን ኢየሱስ መጽሐፍ ቅዱስ በ2ኛ ጴጥሮስ መልዕክት 3፡9 ላይ እንደሚናገረው ለአንዳንዶች የሚዘገይ እንደሚመስላቸው ጌታ ስለ ተስፋ ቃሉ የማይዘገይ ቶሎም እመጣለሁ እንዳለ ቶሎ የሚመጣ ሲሆን ሁሉ ወደ ንስሃ እንዲደርሱ እንጂ ማንም እንዳይጠፋ ወዶ ስለ እነርሱ ዛሬም እንደሚታገስ ይታያል።

ከዚህ ሁሉ በትንንሹ የተገለጡ የእግዚአብሔር ክንዶች በኋላ በአመጿ የቀጠለችው አለም ፈጽሞ የምትቃጠልበት ፍጥረትም ሁሉ ለዘላለም ፍርድ በእግዚአብሔር ፊት የሚቆምበት የመጨረሻው የዘላለም የሆነ ቅጣት ገና ይቀራል። ይህም በዋናነት ለዲያብሎስና ለተከታዮቹ የተጠበቀ ሲሆን ከዚህም በተጨማሪ ዛሬም ድረስ ይህንን የተገለጠ የእግዚአብሔር የምህረት ዕድል ያልተጠቀሙ የአካሄድም ለውጥ ሊያደርጉ ያልወደዱ እውነትንም በዓመፃ የሚከለክሉ ሰዎች በሀጢአተኝነታቸውና በዓመፃቸው ሁሉ ላይ የእግዚአብሔር ቁጣ ከሰማይ ይገለጣል።

“ዛሬም ይህንን የተገለጠ የእግዚአብሔር የምህረት ዕድል ያልተጠቀሙ የአካሄድም ለውጥ ሊያደርጉ ያልወደዱ እውነትንም በዓመፃ የሚከለክሉ ሰዎች በሀጢአተኝነታቸውና በዓመፃቸው ሁሉ ላይ የእግዚአብሔር ቁጣ ከሰማይ ይገለጣል።”

ዛሬም በህይወት ላለንና ይህንን የማዳን ወንጌል በተለያየ መንገድ ለሰማን ሁላችን፣ እያንዳንዳችን እንድንድን እንጂ

አንዳችንም እንዳንጠፋ እግዚአብሔር ይህንን ለእኛ የገለጠ ሲሆን ብናምን የዘላለም ህይወት ባናምን ደግሞ አሁኑኑ የዚሁ የዘላለም ቅጣትና ፍርድ ሰላባዎች የምንሆን ይሆናል። በክርስቶስ በማመን ልብሳቸውን በበጉ ደም በማጠብ ለበጉ በሚሆን የህይወት መጽሐፍ የተመዘገቡ ሁሉ ከዚህ የዘላለም ቁጣ ውጭ ይሆኑ ዘንድ ያመኑትን ክርስቶስ ዳግመኛ በአብ ፊት ይታይላቸዋል።

በተቃራኒው ይህንን የማዳን ስራ የተቃወሙና እርሱን የወጉት፣ ፍቅሩንም ቀምሰው ወደ ኋላ ያፈገፈጉና የተመለሱ፣ ደሙንም የረገጡና ከዚህ ወዲያ ወደው ሀጢአትን የሚያደርጉ፣ የእግዚአብሔርንም ልጅ ለራሳቸው የሚሰቅሉና የሚያውርዱትንም፣ ውሻዎችና አስማተኞች፣ ሴሰኛዎችም፣ ነፍሰ ገዳዮችም፣ ጣኦትንም የሚያመልኩ፣ ውሸትንም የሚወዱ፣ ሁሉ ዕድላቸው ከዲያብሎስ ጋር በዲንና በእሳት በሚቃጠል ባህር ነው።

በዚህም ወቅት እያንዳንዱ እንደ ስራው መጠን ይከፈለዋል፤ ሞትና ሲኦልም በእሳት ባህር ይጣላሉ፣ ይህም የእሳት ባህር ሁለተኛው ሞት ነው። በህይወትም መጽሐፍ ተጽፎ ያልተገኘው ማንኛውም በእሳት ባህር ይጣልና ፍትህና ፍርድ ጽድቅም ሁሉ ተጠብቆ አሮጌው ሁሉ አልፎ ሁሉ አዲስ ይሆናል።

> “እግዚአብሔር ደግሞ ራሱን ይክድ ዘንድ የማይችል ከሀጢአትም ጋር ፈጽሞ የማይተባበር ፃድቅ ፈራጅ የሆነ በደለኛውንም ከቶ የማያነጻ ይልቁንስ ለሁሉ እንደ ስራው ይከፍል ዘንድ በእውነትና በጽድቅ የሚፈርድ አምላክም ነው። እርሱ ያከበሩትን የሚያከብር የናቁትንም ደግሞ የሚንቅ ለትሁታን ፀጋን የሚሰጥ ትዕቢተኞችንም የሚያዋርድና የሚቆጣ አንገቱ የደነደነንና ከጥፋቱ ሊመለስ ያልወደደን ይሰበር ዘንድ ለገዛ ፈቃዱ የሚተው ትክክል የሆነ አምላክ ነው።”

## የማስተንተኛ ጥያቄዎች

1. የእግዚአብሔርን ፍርድ መረዳት ምሕረቱንና ጸጋውን ይበልጥ እንድታደንቅ እንዴት ይረዳሃል?
2. በየትኛው የሕይወትህ ክፍል ለእግዚአብሔር ትዕግሥት በንስሐና በመታዘዝ መመለስ ያስፈልግሃል?
3. የእግዚአብሔርን ቅድስናና ጽድቅ በሚያከብር መንገድ በአገባብ ለመኖር ምን ወሰንክ?

## አሰላስል

እግዚአብሔር ፍጹም ቅዱስና ጻድቅ ነው። ፍቅሩና ምሕረቱ ፍርዱን አያስወግዱም፤ ትዕግሥቱም ኃጢአትን እንደሚያልፍ ወይም እንደማይመለከት አያመለክትም። እግዚአብሔር ሕይወትን ስለሚወድልን ወደ ንስሐ ይጠራናል፤ ነገር ግን ክፋትን ሁሉ እንደ ፍጹም ጽድቁ ይፈርዳል። ቅድስናውንና ጽድቁን ስንረዳ፣ በፊቱ በፍርሃት እና በአክብሮት፣ በምስጋናና በመታዘዝ መመላለስ እንዳለብን እንማራለን። ስለዚህ የእግዚአብሔርን ጸጋ ከንቱ ሳናደርግ፣ በፊቱ በታላቅ ፍርሃትና አክብሮት ልንቀርብ እንደሚገባን ማስታወስ ያስፈልገናል።

## ጸሎት

በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፣ ለእኔ ስለምታሳየኝ ምሕረትህና ትዕግሥትህ ሁልጊዜ አመሰግንሃለሁ። ጸጋህን እንደ ቀላል ነገር እንዳልወስድ፣ ነገር ግን በቅድስና፣ በመታዘዝና በታላቅ አክብሮት በፊትህ እንድመላለስ እርዳኝ። ፍቅርህንና ጻድቅ ፈራጅነትህን በትክክል እንዳስተውል አግዘኝ፤ ሕይወቴም ለስምህ ክብር የሚያመጣ ይሁን። በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አሜን።

## የአርምሞ ጥቅስ

*“እግዚአብሔር ቀናተኛና ተበቃይ አምላክ ነው፤ እግዚአብሔር ተበቃይና መዓትን የተሞላ ነው፤ እግዚአብሔር ተቃዋሚዎቹን ይበቀላል፥ ለጠላቶቹም ቍጣውን ይጠብቃል።”*

*— መዝሙረ ዳዊት 89፥14 —*

## 2.28. እግዚአብሔር አባት ነው!

በመጀመሪያ እግዚአብሔር…ፈጠረ የሚለው የዘፍጥረት 1፥1 ቃል የእግዚአብሔርን አባትነት ለማስረዳት ከሁሉ የተሻለ ምቹ ቃል እንደሆነ አስባለሁ። አባት በዋናነት የህይወት ሁሉ ምንጭና የነገር ሁሉ መገኛ የሆነ ማንነትን የሚገልጽ ቃል (ግዛው, 1994) (Merriam-Webster, n.d.) ሲሆን ይህም በእግዚአብሔር አባትነት ውስጥ ደምቆ የሚታይ እውነት ነው። ሁሉ ከእርሱ የሆነ ከሆነው ሁሉ አንዳች እንኳን ያለ እርሱ ያልሆነ እንደ ፈቃዱ ምክር ነገርን ሁሉ ካለመኖር ወደ መኖር ያመጣ የህይወታቸውም ሁሉ ምንጭና ብቸኛ መገኛ ነው። ይህም ምንጭነቱ ከተፈጠረው ፍጥረት ባለፈ ከእርሱ ጋር ፍጹም እኩልና ከመጀመሪያውም በዘላለማዊ ኅብረት ውስጥ ከእርሱ ጋር የሆኑት ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲሁም ሁሉን የፈጠረበት መንፈሱ እንኳን ጭምር ከእርሱ የወጡ እና እርሱን ለመግለጥ ለእኛ የተገለጡ እንደሆነ ይታያል።

በዮሐንስ ወንጌል 16፡28ና 8፡42 ላይ የተጠቀሰው *"እኔ ከእግዚአብሔር ወጥቼ መጥቻለሁና እርሱ ላከኝ እንጂ ከራሴ አልመጣሁም፤"* እና *"ከአብ ወጥቼ ወደ አለም መጥቻለሁ ደግም አለምን እተወዋለሁ ወደ አብም እሄዳለሁ፤"* የሚሉት ቃላት ልጁ ራሱ ምንም እንኳን ከአብ ጋር ፍጹም ትክክል ቢሆንም አብ ሁሉ በሁሉ ይሆን ዘንድ ልጁ ራሱ ከአብ ወጥቶ የመጣና የተላከ እንደሆነ ያሳያል። በዚህም መሰረት የስጋ ወራቱን ጨርሶ የአባቱን ፈቃድ ይኸውም የተላከበትን ጉዳይ ፈጽሞ ሲጨርስ በዮሐንስ ወንጌል 17፡5 ላይ *"ዓለም ሳይፈጠር በአንተ ዘንድ በነበረኝ ክብር አንተ በራስህ ዘንድ አክብረኝ"* ብሎ ወደ አባቱ የፀለየው ፀሎት ይህንኑ የእግዚአብሔር አባትነትን የሚያስረዳ ነው።

ይህንን የነገር ሁሉ መነሻ የሆነ እውነተኛ የሆነ አባት ይኸውም እግዚአብሔርን ታዲያ ከዚሁ ከመጀመሪያው በእርሱ ዘንድ ከነበረ አንድ ልጁ በስተቀር የሚያውቀው አልነበረም፤ ዛሬም እንኳን እርሱ በሚያውቀው ልክ የሚያውቀው ከራሱ መንፈስ በስተቀር ሌላ አንዳች ፍጥረት የለም። በዚህም መሰረት ምንም እንኳን እኛ ሁላችን ከእርሱ የተገኘን በእርሱም አባትነት ላይ በተመሰረተ ማንነት በየዕለቱ ወጥተን የምንገባ፣ የምንበላና የምንጠጣ የምንተነፍስም ብንሆን ስናመሰግንም ሆነ ሳናመሰግን ጸሀይን የሚያወጣልን

ዝናብንም የሚያዘንብልን ከምድርም ውስጥ የምንበላውን ፍሬ ቢሰጠንም እንኳን እንደ አባት ሳናውቀው በርካታ ዘመናት አልፈዋል፣ ዛሬም እያለፉ ይገኛሉ።

*መጽሐፍ ቅዱስ በዮሐንስ ወንጌል ፲፯፡፫ "እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆንክ አንተን የላክኸውንም ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘላለም ህይወት ናት"* ብሎ እንደሚል አባታችንን ማወቅ እንድንችል እርሱን የምናይበት በመካከላችን ፀጋና እውነትን ተሞልቶ የተገኘው በአባቱ እቅፍ የነበረው አንድና ብቸኛ ልጁ ወደ እኛ ከአባቱ ተልኮ መጣ። በዚህም መሰረት ከአፉ በወጡ የሕይወት ቃላት፣ በተገለጡ ባህርይዎቹ፣ በተራመዳቸው እርምጃዎች፣ በተሰሙት ስሜቶች ወዘተ ውስጥ በውስጡ ያለውን የመለኮት ሙላት፣ የአባታችንንም መልክና ባህርይ ክብሩንም በዚሁ አንድ ልጁ ኢየሱስ በኩል ማወቅ ቻልን።

በዚህም ትረካው የአባታችንን ፍጹም የሚልቅ ፍቅር፣ ርህራሄ፣ ቸርነት፣ ጥበቃ፣ ኅብረት፣ መሪነት፣ ባህርይና ማንነት ክብሩንም ለማየት ቻልን። በዚህም አባትነቱ ምክንያት ያለንን ፍጹም ደህንነት ለእኛ ያለውን ቅርበትም በስራ በተገለጠው አስደናቂ ፍቅሩ ውስጥ ያለውን እኛ እርሱን እንድንወድበት የተገባንን የህብረታችን አላማው የሆነውን የፍቅር መሰረት ገለጠልን። በልዑል መጢጊያ ይኸውም በአባቱ ዘንድ መኖሪያውን ያደረገ በእርሱ የሚወጣ የሚገባም ልጁ ያለውን ፍጹም ጥበቃ ከእርሱ በመገኘቱም ያለውን የከበረ ማንነት፣ ይኖርበት ዘንድ የሚገባውንም ጽድቅና ቅድስና ወዘተ በልጆቹ ጉዳይም ባለጉዳይ ሆኖ የእለት ከእለት እንቅስቃሴያቸው ውስጥ ያገባኛል ብሎ እንደ ባለቤት የሚሳተፍ የእኛ ነገር የሚገደው ቸር አባት መሆኑን ተመለከትን።

በተመሳሳይ መልኩ ልጁ ኢየሱስ አልዓዛርን ከሞት ባስነሳበት ወቅት አባቱን ሁልጊዜ እንድትሰማኝ አወቅሁ ባለበት ንግግሩ ውስጥ በሌላም ስፍራ ብቻውን እንዳልሆነ ነገር ግን አባቱ ከእርሱ ጋር እንዳለ በተናገረበት ስፍራ ሁሉ ውስጥ አብ አባታችን እንደ አባት ሁልጊዜ ከእኛ ጋር ያለውን ቅርበት ብሎም ወዳጅነት አይተናል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ይህ ሁሉ እኛ አብን እናይ ዘንድ ልናየው በእኛ መካከል የተገለጠው መልኩ ይኸውም ልጁ ኢዮሱስ ክርስቶስ አባቱን በሚገባ የተረከልንና በህይወት ምልልሱም አባትና ልጅ ሊኖራቸው ስለሚገባ ህይወት ኖሮ አሳይቶን ወደ አባቱ

የሄደ ቢሆንም ይህ ልጁ ኢየሱስ ከአባቱ ጋር ያለው ፍቅር በእኛ ዘንድ ደግሞ እንዲሆን ከትረካ ባለፈ አብን አባ አባት ብለን የምንጠራበት የልጁ መንፈስ ደግሞ ያስፈልገን ነበር።

አሁን ልጁ ኢየሱስ በመስቀል ላይ በሰራው ስራ የእርሱ የአባታችን መንፈስ ከአብ እንዲሁም አባትነቱን ከገለጠልን በመንፈሱ ሙላት ከተመላለሰ ልጁ ለእኛ ለሁላችን በእርሱ ላመንን እግዚአብሔርንም አባታችን ብለን ለመጥራት ለወደድን ሁሉ ሳይሰፈር ተሰጠን። ይህም መንፈሱ የዚህን የአባታችንን ፍቅር በልባችን ውስጥ አፈሰሰውና፣ ፍቅር እርሱ እኛን እንደወደደን እንጂ እኛ እርሱን እንደወደድነው እንዳልሆነ አስረድቶን አባታችንን ልንወደው በተገባ ፍጹም ፍቅር እንወደው ዘንድ እለት እለት እየመራና እያሳደገን ይገኛል።

> “ይህ የተቀበልነው አባታችን ብለን የምንጠራበት የልጁ መንፈስ በአብ ፊት ያለ ፍርሃት የምንቀርብበትን እንደ ፈቃዱም ማንኛውንም ነገር ለምነን ተቀብለን የምንወጣበትን ድፍረት የሰጠን ሆነ።”

ከዚህ ወዲያ ታዲያ ይህ የተቀበልነው አባታችን ብለን የምንጠራበት የልጁ መንፈስ በአብ ፊት ያለ ፍርሃት የምንቀርብበትን እንደ ፈቃዱም ማንኛውንም ነገር ለምነን ተቀብለን የምንወጣበትን ድፍረት የሰጠን ሆነ። በዚህ ከአብ ጋር ከልጁም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር በመንፈሱ በኩል ባለን ኅብረት የተገለጠው ልጅነት እግዚአብሔር አብ ልጁን ኢየሱስን በወደደበት በዚያ ፍቅር እኩል የተወደድን ያደረገን አንድ ሰው ሊኖረው የሚችለው ሊመካበትም የተገባው የመጨረሻ ሀብቱ ነው።

ይሄው የተቀበልነው ይህ የልጁ መንፈስ ታዲያ እውነተኛ የሆነውን የልጁን የኢየሱስን መልክ ሁልጊዜ እንድንመለከት በዚህም አብ የሚፈልገው አይነት ልጆች እንሆን ዘንድ ፈለጉን እንድንከተል ዕለት ዕለት ከሳትንበት እየመለሰ በምንሄድበትም መንገድ እየመራ ወደ እውነት ሁሉ ይወስደናል። በዚህም ያልተቋረጠ መታደስ ውስጥ አልፈን የአባታችን መልክ ማሳያ የሆነውን ልጁን ይኸውም ኢየሱስ ክርስቶስን እስክንመስል ድረስ በየቀኑ ከክብር ወደ ክብር እንድንለወጥ ያደርገናል።

ይህ ሁሉ በሁሉ የሆነ አባታችን እግዚአብሔር ብቻውን ከቃሉና ከመንፈሱ ጋር ባለው ፍጹም ውህደትና ኅብረት አንዳች ሳይጎድለው ይኖር የነበረና የሚኖር አምላክ ሲሆን እኛ ሁላችን የእርሱ ወራሾች እንሆን ዘንድ ከእርሱም ጋር ዘላለማዊ የሆነ ኅብረት እንዲኖረን ወድዶ ሞተን ከነበርንበት አንስቶ ከልጁ ጋር ህይወትን ሰጠን። በዚህም ስራው ያለውን ሁሉ ሳይሰስት ራሱን ጭምር የሰጠን አባታችን እርሱን አባት ብለንም የምንጠራበትን የልጅነት ስልጣን አብሮ ሰጠን። ከዚህ ወዲያ ታዲያ ቀድሞ ከነበረን እግዚአብሔርን የማያከብር ህይወት እየተላቀቅን እርሱ ራሱ ቅዱስ እንደሆነ ቅዱሳን ለመሆን በተገለጠው ፀጋ በመንፈሱም አመራር እየታገዘን ብልቶቻችን ሁሉ የጽድቅ የጦር እቃ ሆነው እግዚአብሔር አባታችንን ወደሚያከብር ህይወት እንገስግስ ዘንድ ይገባናል።

እግዚአብሔር አባታችን ነው ካልን በኋላ እንደ አባት የሚገባውን ክብር ከልጆቹ ሊያገኝ ደግሞ ያስፈልገዋል። ይህም እግዚአብሔርን እንደ እግዚአብሔርነቱ መጠን የተገባን አክብሮትና ፍርሃት እንደሚወዱት ልጆችም ፍቅርን እንይዝና በዚህም መልክ እንመላለስ ዘንድ ነው። ይህም እግዚአብሔርን መውደዳችን ከተጠመቅንበት በጋራ ከጠጣነውም የእርሱን ፍቅር በልባችን ባፈሰሰው አንድ መንፈስ የተነሳ እርስ በእርሳችን በመዋደድ ደግሞ የምንገልፀው እርሱን የመውደዳችን እውነታ ማሳያ የሆነ ህይወት ነው።

ነገር ግን በዚህ መልኩ እግዚአብሔርን አባታችን ነው ከመንፈሱም ጋር ኅብረት አለን ካልን በኋላ ወንድማችንን በመጥላት የህይወት ምልልስ ውስጥ ብንገኝ መጽሐፍ ቅዱስ በ|ኛ ዮሐንስ መልዕክት |፡9 ላይ እንደሚናገረው በብርሃን አለሁ ብለን የምንዋሽ ነገር ግን እስከ አሁን በጨለማ ያለን ምስኪኖች ያደርገናል።

አባታችንን ሊተርክልን የመጣው የገለጠልንም ሁላችን እንመስለው ዘንድ የተሰጠን ልንደርስበት ዕለት ዕለት የምንተጋለት የልጁ መልክ ካወቅነው ወድያ በእርሱ እንድንኖር ደግሞ አስተምሮናል። ይኸውም በህይወት ምልልሳችን አባታችንን አክብረንና አስከብረን እንድናልፍ ነው። በዚህ ከአብ፣ ከልጁም ከኢየሱስ ጋር በፈጠርነው ኅብረት ዘላለማዊ በሆነ ህይወት አሁን ከእርሱ ጋር በእርሱ ዘንድ ያለን ደግሞ በዚህ በምድር ላይ የመልኩ ማሳያዎች የገዥነቱም መገለጫዎች ሆነን እንደ ልጅ እንወርሳት ዘንድ የተዘጋጀችዋን መንግስት እየሰበክን በርካታ ልጆችን ለአባታችን እንድናመጣ የመንግስቱ ካህናት ሆነን ተቀምጠናል።

በዚህም መልኩ አሁን በምድር ላይ መፃተኞች የሆንን ወደ አባታችን ልንሄድ አባታችን ባለበት በዚያም እርሱ ለሚወዳቸው ያዘጋጀው፣ በአይንም ያልታየ ብዙ ያማረ መኖሪያ አገራችን በሆነችው ሰማይ እንዳለው ሰው ለመሄድ በተዘጋጀ አባቱን ለማየት የሚናፍቅ ልጅነት እንኖራለን። በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ እያልን በሰማይ ያለው ፈቃዱ በምድር የሚሆንበትን ስሙም ተፈርቶና ተቀድሶ በክብር የሚጠራበትን ተስፋ ይኸውም አዲሱን ሰማይና ምድር በብዙ ናፍቆት እንጠባበቃለን።

በዚህ ምድር ላይ ያለ አባትነት ሁሉ ታዲያ እግዚአብሔር ለእኛ ለሁላችን አባት በሆነበት አባትነት የተመሰለና የተሰየመ ነው። ይህም ማለት እውነተኛ አባትነት አብና ወልድ የነበራቸው ያ የተገለጠ ልጁ አባቱን የሚያከብርና የሚወድበት ይህንኑም አክብሮቱንና መውደዱን ፈቃዱን በማድረግ የሚገልጥበት አባት ደግሞ ልጁን ስለሚወድ ያለውን ሁሉ ለልጁ የሚሰጥበት፣ ከክፉ የሚጠብቅበት፣ አቅርቦትን የሚያቀርብበት፣ ስሙ በእርሱ ዘንድ እንዲጠራ የልጅነት ስልጣንን የሚሰጥበት፣ የሚያደርገውን ሁሉ ልጁ ደግሞ ያደርግ ዘንድ የሚያሳይበት፣ ይኖርበት ዘንድ የሚገባውን ህይወት ከፊቱ ቀድሞ ኖሮ በመኳዝ የሚመራ፣ ልብ ለልብ በሆነ እውነተኛ ፍቅር ላይ የተመሰረተ ኅብረት እንደሆነ የተገለጠበት ነው።

“በዚህ ምድር ላይ ያለ አባትነት ሁሉ ታዲያ እግዚአብሔር ለእኛ ለሁላችን አባት በሆነበት አባትነት የተመሰለና የተሰየመ ነው።”

የእግዚአብሔርን የአባትነቱን መልካምነት ብዛት እርሱን የተረከልን የሚያውቀው ልጁ ሲነግረን እኛ ክፉዎች ስንሆን ለልጆቻችን መልካምን ማድረግን ባወቅንበት በዚያ ሚዛን መዝኖ ማንነቱ መልካም የሆነው ክፋትን ፈጽሞ የማያውቀው ይህ አባታችንማ እንዴት ደግ እንደሆነ አሳይቶናል። ይህም ደግነቱ ያለውን ሁሉ ይኸውም ልጁንና መንፈሱን ለእኛ በመስጠት በገለጠው ያልተቆጠበ ፍቅር የተረጋገጠ ነው። ይህም ምንም ሳይቆጥብ ራሱን ጨምሮ ያለውን ሁሉ ለእኛ በመስጠት የተገለጠ አባትነት ዛሬ በምድር ላይ ያሉ አባቶች እንደ አባት እንዲኖራቸው የሚፈልገው ምሳሌው ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ በ1ኛ ቆሮንቶስ መልዕክት 11፡12 ላይ እንደሚናገረው ሁሉ ከእግዚአብሔር ነው። ከላይ በተብራራውም መልኩ ልጁ ኢየሱስ መንፈሱም ጭምር

ከአብ የሚገኙ እንደሆኑ አይተናል። በዚህም መሰረት ይህንኑ ፍቅሩን በእኛ መካከል ደግሞ ለማድረግ በዚህ፣ ሁሉ ከእርሱ በተገኘበት የአባትነት ስልጣኑ መጽሐፍ ቅዱስ በ1ኛ ቆሮንቶስ መልዕክት 3፡23 ላይ እንደሚል የእርሱ የሆነውን ክርስቶስን ለእኛ ሰጥቷል። ይህም እኛን ሁላችንን ደግሞ የእርሱ የክርስቶስ እንሆን ዘንድ እንደ አካል ሙሽራው አድርጎ ሊያቀርብና በዘላለማዊ ኅብረት ውስጥ ከእርሱ ጋር እንድንሆን በፍቃዱ ምክር ቀድሞ የወሰነው ሁሉን በልጁ የሚጠቅልል የዘላለም ሃሳቡ ነው።

*እግዚአብሔር አባታችን ነው!*

የእግዚአብሔር አባትነት የሌሎች ሁሉ ባህርያቱ መነሻ መሰረት እንደሆነ ይታሰባል። እርሱ አባት በመሆኑ ምክንያት ይወዳል፣ ይራራል፣ ለልጆቹ ፍጹም የሆነ ምሳሌ ይሆናል፣ በጽድቅና በቅድስና ይገኛል፣ የሚያስፈልጋቸውን ይሰጣል፣ ይታገሳል፣ ደግሞ ይቆጣል ብሎም የሳቱ ልጆቹን ሊመልስ እና በእቅፉ ውስጥ ሊያቆይ ወድዶ እንዳይጠፉ ይልቁንስ የሰላምን ፍሬ እርሱም ጽድቅን ያፈሩ ዘንድ ይገስጽና ይቀጣቸዋል የበለጠም ፍሬያማ ይሆኑ ዘንድ በየጊዜው ይገርዛቸዋል። መጽሐፍ ቅዱስ በዕብራዊያን መልዕክት 12፡7-11 ባለው ክፍል ውስጥ ይህንኑ አባትነቱን ሲያስረዳ አባት ለልጆቹ እንደሚያደርግ እግዚአብሔር ልጆቹን እንደሚገስጽና እንደሚቀጣ ይናገራል። ይህም ልጆቹ ከእቅፉ ርቀው እንዳይሄዱ ብሎም ለጥፋት እንዳይዳረጉ በአባትነት ፍቅሩ የሚያደርገው አንድ ልጅ ከአባቱ ሊያገኘው የሚገባ የስነ-ምግባር ማስተካከያ ነው። ይህም በዋናነት ከቅድስናው እንድንካፈልና ለዘላለም ከእርሱ ጋር እንድንኖር ለጥቅማችን የሚያደርገው ነው።

የዚሁ ድንቅ የሆነ የእግዚአብሔር የአባትነት ፍቅር ማሳያው በመጽሐፍ ቅዱስ 2ኛ ሳሙኤል 7፡14-15 ላይ ያለው እግዚአብሔር የዳዊትን ልብ አይቶ ለእግዚአብሔርም ቤት ለመስራት መነሳቱን ተመልክቶ ለዘላለም የሚሆንን ኪዳን በሰጠው ጊዜ ስለ ልጁ ስለ ሰለሞን የተናገረው ንግግር ነው። ይህም ከዳዊት ጋር ካለው ኪዳን የተነሳ የአባቶችንም ኪዳን እስከ ሺህ ትውልድ ድረስ የሚጠብቅ ታማኝ አምላክ በመሆኑ ልጁ ሰለሞን ቤቱን እንደሚሰራለት ከእርሱም ጋር በሚኖራቸው ግንኙነት ልጁ ሰለሞን ክፉ ነገርን ቢያደርግ እግዚአብሔርንም ቢበድል እንኳን እንደ አባት ሰው በሚቀጣበት በትርና በሰው ልጆች

መቀጫ ሊገስፀው እና ምህረቱንም ከእርሱ ላያርቅ እንጂ ፈጽሞ እንደተወውና እንደናቀው እንዳራቀውም ፊቱንም እንደሰወረበት አልታዘዝ እንዳለው እንደ ሳኦል ከእርሱ እንደማይርቅ ይናገራል።

## ምን አይነት ድንቅ ፍቅር ነው?

እግዚአብሔር አባት ስለሆነ ልጆቹ በእርሱ መንገድ ይሄዱና የተገባን ፍሬ ያፈሩ ዘንድ ያዘጋጀላቸውንም ርስት ለመውረስ ይበቁ የቅድስናውም ተካፋዮች ይሆኑ ዘንድ ዛሬም ይገስፃል ይቆጣልም። መጽሐፍ እንደሚል ፊቱን የሚያርቅበት በፊቱም የተናቀ ያለ ቅጣትም የሚኖር እንደ ልጅ የአባቱን ፍቅርና ምህረት ትዕግስትና ተግሳጽም የማያገኝ ቢኖር እርሱ ዲቃላ እንጂ ልጅ አይደለም።

“ምን አይነት ድንቅ ፍቅር ነው?

እግዚአብሔር አባት ስለሆነ ልጆቹ በእርሱ መንገድ ይሄዱና የተገባን ፍሬ ያፈሩ ዘንድ ያዘጋጀላቸውንም ርስት ለመውረስ ይበቁ የቅድስናውም ተካፋዮች ይሆኑ ዘንድ ዛሬም ይገስፃል ይቆጣልም። መጽሐፍ እንደሚል ፊቱን የሚያርቅበት በፊቱም የተናቀ ያለ ቅጣትም የሚኖር እንደ ልጅ የአባቱን ፍቅርና ምህረት ትዕግስትና ተግሳጽም የማያገኝ ቢኖር እርሱ ዲቃላ እንጂ ልጅ አይደለም።”

- **የማስተንተኛ ጥያቄዎች**

1. እግዚአብሔርን እንደ አባትህ ማወቅ ከእርሱ ጋር ስላለህ ግንኙነት ያለህን እይታ እንዴት ይለውጠዋል?
2. የሰማያዊ አባትህን ባሕርይ እንድታንጸባርቅ በየትኞቹ የሕይወትህ ክፍሎች ለውጥ ያስፈልግሃል?
3. ዛሬ የእግዚአብሔርን አባታዊ ፍቅር ለሌሎች እንዴት ማሳየት ትችላለህ?

- **አሰላስል**

እግዚአብሔር ፍጹም አባታችን ነው። ሕይወትን የሚሰጠን፣ የሚወደን፣ የሚያስፈልገንን የሚያሟላልንና በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ወደ ኅብረት የጠራን ደግ አባት ነው። እኛ የእርሱ ልጆች ስለሆንን፣ ባሕርዩን በሕይወታችን ለማንጸባረቅ፣ በቅድስና ለመመላለስና በአባታዊ እንክብካቤው ላይ በመታመን ለመኖር ተጠርተናል። የሰማያዊ አባታችን ፍቅር ፍጹም፣ የማይለወጥና ሁልጊዜ ለልጆቹ መልካምን የሚፈልግ ነው። ስለዚህ እንደ ተወደዱ ልጆቹ በእርሱ በመታመን፣ ፈቃዱን በመከተልና ባሕርዩን በማሳየት መኖር እንደሚገባን ሁልጊዜ ማስታወስ ያስፈልገናል።

- **ጸሎት**

በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ልጅህ ስላደረግኸኝ አመሰግንሃለሁ። ፍቅርህን በጥልቀት እንዳውቅ፣ መሪነትህን እንድታመንና ሕይወቴን ለአንተ ክብር እንዳውል እርዳኝ። እንደ ተወደድሁ ልጅህ በፊትህ እንድመላለስና ባሕርይህን ለሌሎች እንዳሳይ አግዘኝ። በእንክብካቤህ ላይ በመታመን በፈቃድህ እንድኖር እርዳኝ።
በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አሜን።

- **የአርምሞ ጥቅስ**

*"የእግዚአብሔር ልጆች ተብለን ልንጠራ አብ እንዴት ያለውን ፍቅር እንደ ሰጠን እዩ፥ እንዲሁም ነን።"*

*— ፩ኛ የዮሐንስ መልእክት ፫፥፩ —*

## 2.29. እግዚአብሔር ወዳጅ ነው!

እግዚአብሔር እጅግ የተፈራ የከበረም እስትንፋሱ በአፍንጫው ካለበት ትንሹ ሰው ጋር ፈጽሞ ንጽጽር ውስጥ የማይገባ እጅግ ትልቅ ከአዕምሮም የሚያልፍ አምላክ ነው። ይሁን እንጂ ምንም እንኳን ሰው ከምድር አፈር በእጁ ካበጀው ሸክላ በሸክላ ሰሪው እጅ እንዳለ እንደወደደም ያደርገው ዘንድ ስልጣን እንዳለው በሰሪው በእግዚአብሔር ፊት እጅግ ትንሽ ፍጡር ሆኖ ያለ ቢሆንም እንኳን ከፈጠረው ፍጥረቱ ሁሉ በበለጠ መልኩ አንዳች ወዳጅነትንና ኅብረትን ወድዶ የራሱን ህይወት ያካፈለው ራሱንም በዚሁ በትንሹ ሰው በኩል ሊገልጥ ወድዶ ወዳጁ ይሆን ዘንድ አስቦ የሰራው ልዩ ፍጥረቱ ነው። (ማኅበር, 1954)

መጽሐፍ ቅዱስ በ2ኛ ቆሮንቶስ 4፡7 ላይ እንደሚናገረው ይሄው እርሱ ራሱን በእኛ ሁኔታ ሊገልጥ ወድዶ መልኩን በውስጣችን የጨመረበት እውነት የኃይሉ ታላቅነት ከእርሱ እንጂ ከእኛ እንዳይሆን ቀድሞውኑ በአላማ ያደረገው ሲሆን በዚህም መልኩ ለዚሁ የሰራን እርሱ የመንፈሱን መያዣ ስለሰጠን ይህን ክቡር መዝገብ በሸክላ እቃ ውስጥ ይዘን የምንገኝ የእርሱ ወዳጆች ሆነናል። በዚህ መልኩ ከመጀመሪያው ሰው አዳም ጋር እግዚአብሔር የጀመረው ወዳጅነት በአንደኛው ወገን አለመታመንና አለመታዘዝ ምክንያት ለረዥም ጊዜ ተቋረጠ። የዚህም ወዳጅነት ዋናና መካከለኛ የሆነው መንፈሱ በዚሁ አለመታዘዝ ምክንያት ከሰው ልጅ ርቆ ሄዶ የነበረ ሲሆን በሁለተኛው አዳም አማካኝነት በምህረቱ ባለጠጋ የሆነው እግዚአብሔር በይቅርታ መንፈሱን መልሶ በመስጠት ወዳጅነቱን ቀጥሏል። ይህም ከእግዚአብሔር ጋር ያለ ወዳጅነት ጥልቅ በሆነ መዋደድ ላይ የተመሰረተና ራስን በመስጠት ጭምር የሚገለጥ ፍጹም ታማኝነትን የሚፈልግ ኅብረት እንደሆነ ያሳያል።

> “ከእግዚአብሔር ጋር ያለ ወዳጅነት ጥልቅ በሆነ መዋደድ ላይ የተመሰረተና ራስን በመስጠት ጭምር የሚገለጥ ፍጹም ታማኝነትን የሚፈልግ ህብረት ነው።”

በራሱ ተነሳሽነት ከሰው ልጆች ጋር ዳግመኛ ወዳጅ ሊሆን ወድዶ ልጁን በሰው ልጆች መካከል የላከው ይህ ትልቅና ትሁት ጌታ ገና ሀጢአተኞችና

ለወዳጅነቱ ያልታመንን ሆነን ሳለን ነፍሱን ስለ ወዳጆቹ በመስጠት ለዚህ ወዳጅነት የሚሰጠውን ታላቅ ዋጋ አሳየን። በዚህም እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ታላቅ ፍቅር እንዲሁም በዚህ ፍቅር ላይ ያደሰውን ወዳጅነት ዋጋ ገለጠ። ይህንኑ ሲያስረዳ የዚህን ወዳጅነት አነሳስ ሲናገር በዮሐንስ ወንጌል 15፡16 ላይ *"እኔ መረጥኋችሁ እንጂ እናንተ አልመረጣችሁኝም"* ብሎ ይናገራል። በዚህም ከእርሱ የተነሳውን የወዳጅነት ጥያቄ በእርሱ በራሱ ፀጋ ተቀብለን ርቀን የነበርነው ቀርበን፣ መፃተኞች የነበርነው ባለገሮችና ቤተሰቦች ሆነን ከእርሱ ጋር ተወዳጀን። ይህም እርሱ ራሱ ገልጦ ያስረዳን ወዳጅነት ታላቅ ዋጋን የሚጠይቅ ብዙ ታማኝነትንም የሚፈልግ ተፈትኖ ሊያልፍ የሚገባው ኅብረት እንደሆነ የሚያሳይ ነው።

ከባርነት እና ከጠላትነት ወደ ወዳጅነት፣ ከመፃተኛነት ወደ ባላገርና ቤተሰብነት የተለወጥንበት ይህ ኅብረት የእርሱ የሆነ ምስጢርን በማወቅና ለዚህም ምስጢር በታማኝነት ለመኖር ተወስነን በእርሱ በራሱ አነሳሽነትና ምርጫ ከባሪያና ከጌታ ባለፈ ግልጽነትና ቅርርብ ከአባቱ የሰማውን ሁሉ ወዳጆቹ እንድንሆን ለመረጠን ለእኛ በማስታወቁ የተረጋገጠ በመስዋዕትነት ጭምር በተግባር የተገለጠ ጥልቅ ወዳጅነት ነው። ይህም ወዳጅነት እርሱ ለእኛ ፍጹም ታማኝ እንደሆነው እኛ ደግሞ ለእርሱ እንድንታመንና በእውነተኛ ህይወት እንድንመላለስ የሚፈልግ ኅብረት ነው። ለዚህም ነው በዚሁ በዮሐንስ ወንጌል 15፡14 ላይ *"እኔ ያዘዝኋችሁን ሁሉ ብታደርጉ እናንተ ወዳጆቼ ናችሁ"* ብሎ ከመጀመሪያው ባለመታዘዝ አሳዝነን ከእኛ ያራቅነውን የወዳጅነታችን መካከለኛ የሆነውን ቅዱሱን መንፈሱን በማክበርና ባለማሳዘን ላይ የተመሰረተ እግረ መንገድ ወይም ዋዛ ያልሆነ በጥንቃቄ የምንይዘው ቁምነገር እንደሆነ ያስታወቀን።

ይህ ወዳጅነት የተመሰረተው የእርሱ ብቻ የሆነውን ምስጢር ለእኛ ወዳጆች እንድንሆን በእርሱ በራሱ ምርጫ ለተመረጥንና ታማኝ ተደርገን ለተቆጠርን በመግለጥ ነው። ይህም ምስጢር እርሱ ራሱ ካልገለጠው በስተቀር በየትኛውም አይነት መልኩ በሰው ጥበብ ሊደረስበት የማይቻለው የራሱ ማንነት ሲሆን በዚህም ማንነቱ ውስጥ እርሱ ለፈጠረው ፍጥረቱ ሁሉ ያለውን እይታ ደግሞ በመረዳት እርሱ እንደሚያስብና እንደሚመላለስ እንመላለስ ዘንድ የገለጠልን ነው። ይህንንም ምስጢር በአባቱ እቅፍ ያለ

አንድ ልጁ አብራርቶ ለሁላችን የገለጠው በተሰጠን መንፈስም የተረጋገጠ በልባችንም የበራ ጽኑ ወዳጃዊ ምስጢር ነው።

እርሱ ራሱ ከዮሐንስ ወንጌል 17፡6 ጀምሮ ባለው ክፍል ውስጥ እንደተናገረው ስሙን በመግለጥ የጀመረ ይገልጥልን ዘንድ የሰጠውን ተሞልቶ የመጣውን ቃል በሙሉ ለእኛ በመስጠት የጠነከረ በዚህም እውነት ተቀድሰን ወዳጆቹ ልንሆን እድል ያገኘን ሁላችን ደግሞ እርሱ እንደ ወደደን እርስ በእርሳችን ተዋደን በመኖር ልንገልጠው አደራ የተሰጠን እንደሆነ በማብራራት የተገለጠ ነው። ይህም እንዋደድበት ዘንድ የታዘዝንበት መዋደድ እርሱ እኛን እንደ ወደደ ነፍሱንም በፈቃዱ ስለ እኛ እንዳኖረ የተተረጎመ ነው እንጂ እኛ እርሱን እንደወደድነው ወረተኛ ያልሆነ እውነተኛ ጥልቅ ፍቅር ነው። እርሱ ደግሞ እኛን የወደደው አንድያ ልጁን በወደደበት በዚያው ፍቅር እንደሆነ በዚሁ በዮሐንስ ወንጌል 17፡26 ላይ አስታውቆናል።

ከዚህ ወድያ በዚሁ ዳግመኛ በራሱ አነሳሽነት በተመሰረተው የኪዳን ወዳጅነት መሰረት በእርሱና በእኛ መካከል የነበረው የጥል ግድግዳ ፈርሶ እርሱ ራሱ እኛን ወንድሞቼ ብሎ እንዲጠራን ያደረገ መቀራረብ ነው። በዚህም መሰረት እርሱ ከፍጥረት በኩር ታላቅም ወንድም ኃያልም አምላክ ታላቅም ጌታ እንከን አልባና ነቀፋ የሌለበት ነውና ፈጽመን ትኩር ብለን ልናየውና ፈለጉን ልንከተል ልናከብረውም የተገባ ወዳጅ ነው።

በዚህ በደም የተደረገ አዲስ ኪዳን የተመሰረተ ጥልቅ ወዳጅነት መሰረት ታዲያ እርሱ በእኛ ውስጥ እኛም ደግሞ በእርሱ የምንመላለስ አንዳች የተደበቀ ነገር ሳይኖረን በፍጹም መተማመን በሚኖር ህይወት የሚገለጥ እንደሆነ በመረዳት ወዳጅነቱን አክብረን በጥንቃቄ ልንኖር ያስፈልገናል።

ይህም ቅርርብ አንድ ልጁን ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን ታላቅ ወንድማችን በማድረጉ በእርሱ የነበረውን የልጁን መንፈስ ይኸውም አባ አባት ብለን የምንጠራበትን መንፈስም በመቀበላችን ያገኘነው የልጅነት ስልጣን የእርሱ የራሱ ደግሞ ወራሾች መሆን ችለናል። በዚህም መሰረት እግዚአብሔር በዘፍጥረት 18፡17 ላይ "የማደርገውን ከወዳጄ ከአብርሃም ደብቄ አደርጋለሁ?" ያለው የአብርሃም ወዳጅ እግዚአብሔር ከዚያ በበለጠ ፍጹም ግልጥነት ማንነቱን ሁሉ በእኛ ውስጥ በማስቀመጥና ወደ እውነት ሁሉ በመምራት

የሚያደርገውንም ሁሉ በእኛ በኩል ጭምር በማድረግ የበለጠ ጥልቅ ወዳጅነትን ሰጥቶናል። ይህም ወዳጅነት እርሱ እኛን በወደደበትና ለእኛ ታምኖ በተገኘበት በዚያ ጥልቀት እርሱን ራሱን ብሎም ከጎናችን የሚገኝ ባልንጀራን በመውደድ የሚገለጥ ያዘዘንንም ሁሉ በታማኝነት በማድረግ የሚረጋገጥ ወዳጅነት እንጂ እንዲሁ በግብዝነት በቃል ብቻ የሚነገር አይደለም። *“ብትወዱኝስ ትዕዛዛቴን ጠብቁ ትዕዛዜ በእርሱ ዘንድ ያለችው የሚጠብቃትም የሚወደኝ እርሱ ነው”* ወዘተ ብሎ ደጋግሞ እንደተናገረ በህይወት የሚገለጥ ወዳጅነት ነው።

> ““የማደርገውን ከወዳጄ ከአብርሃም ደብቄ አደርጋለሁ?” ያለው የአብርሃም ወዳጅ እግዚአብሔር ከዚያ በበለጠ ፍጹም ግልጥነት ማንነቱን ሁሉ በእኛ ውስጥ በማስቀመጥና ወደ እውነት ሁሉ በመምራት የሚያደርገውንም ሁሉ በእኛ በኩል ጭምር በማድረግ የበለጠ ጥልቅ ወዳጅነትን ሰጥቶናል።

እርሱ “የወደዳቸውን እስከ መጨረሻው ወደዳቸው” ተብሎ እንደተፃፈ ለእኛም እርሱን ከመውደድ በተጨማሪ እንጠብቃት ዘንድ የእርሱም ወዳጆች እንደሆንን በዚያ ይታወቅ ዘንድ በዚያው የተገለጠ ፍቅር ልንዋደድ ያስፈልገናል። መጽሐፍ ቅዱስ በሉቃስ ወንጌል ||:5 ላይ ጌታችን ኢየሱስ እውነተኛ የሆነን ወዳጅነት ሊያሳይ ወድዶ በተናገረው ምሳሌ ውስጥ ወዳጅ ለወዳጁ የሚከፍለውን ዋጋ ያሳያል።

ነገር ግን ከፉ የሆነው ሰው በዚህ ልክ ለወዳጁ መልካም ማድረግን ካወቀ ፍጹም የሆነው እርሱ ለእኛ ያለውን መልካምነትና ታማኝነት እኛም ከእርሱ ህይወትን የተካፈልን ሁላችን ደግሞ እርሱን ራሱን ልንወድበት ብሎም እርስ በእርሳችን ልንዋደድበት የሚገባንን ለወዳጅ የሚገባ ፍቅር በጥንቃቄ ማየት ይገባናል።

ይህ ከእርሱ ጋር የጀመርነው ወዳጅነት እርሱ በእያንዳንዱ የቀን ከቀን ውሏችን ውስጥ ባለ የትኛውም አይነት ሃሳብና ድርጊት ሁሉ የነገራችን ባለቤትና አማካሪያችን ሆኖ ባለጉዳይ የሚሆንበት በመካከላችን ምስጢር የሚባል ነገር እንዳይኖር እርሱ ለእኛ

ልንሰማው ወድደን ጆሮ በሰጠነው ልክ የእርሱን ጉዳይ ለእኛ የሚያስታውቅበት እኛም ደግሞ በጉዳያችን ላይ እንዲሳተፍ በወደድንበት በዚያ መጠን በታማኝነት ወዳጅ በመሆን ሸክማችንን የሚያቀል ታማኝ ወዳጅ ሆኖ የሚሳተፍበት ተግባራዊ ወዳጅነት ነው።

በዚህም መሰረት እርሱ አንድ እንኳን ሳይቀር ከጥንት ጀምሮ በእርሱ ዘንድ የነበረው የፈቃዱ ምክር ምን እንደሆነ ያስታወቀን ሲሆን ይኸውም በሰማይና በምድር ያለውን ሁሉ በልጁ መጠቅለል እንደሆነ ነግሮናል። ለዚህም ዋና ጉዳይ እኛ ሁላችን እንደ ወዳጅ በስራው እንሳተፍ ዘንድ ማገዝ የሚያስችለንን ፀጋ ከጥበብና ከአዕምሮ ጋር ለእያንዳንዳችን በመንፈሱ በኩል ሰጥቶናል። ልክ እንዲሁ እርሱ ሁልጊዜ ታማኝ ሆኖ በውስጣችን ከእስትንፋሳችን እንኳን ቀርቦ ተወዳጅቶናልና ራሳችንን በፊቱ ልናራቁት በነገራችንም ሁሉ ላይ ልናሳትፈው ያስፈልገናል።

በዚህም እርሱ ሁሉን የሚያውቅ፣ ሁሉንም የሚችል ነውና ከእርሱ ጋር ያለን ይህ ወዳጅነት ቀንበርን ከላያችን ላይ የሚሰብር ሸክምንም የሚያራግፍ ለጥቅማችን የሆነ የሚበጅም ነው። እርሱ ሁልጊዜ እስከ አለም ፍፃሜ ድረስ ከእኛ ጋር ታማኝ ወዳጅ ሆኖ ሊኖር ቃል ገብቷል። ባለፉት ዘመናት ሁሉ እንዳየነው ማንነቱም እንደሚናገረው እርሱ እንደተናገረው እንደዚያው ታማኝ ሆኖ ሳይለየን ለዘላለም ከእኛ ጋር ነው። እንደ ወዳጅ በምናልፍበት ሁሉ እርሱ ደግሞ ከእኛ ጋር ሆኖ በዚያው መውጫ መንገድን መመላለሻ እውነትንም ሊያስተምረን አብሮን አለ።

*እግዚአብሔር እውነተኛ ወዳጅ ነው።*

> "እርሱ ሁልጊዜ እስከ አለም ፍፃሜ ድረስ ከእኛ ጋር ታማኝ ወዳጅ ሆኖ ሊኖር ቃል ገብቷል። ባለፉት ዘመናት ሁሉ እንዳየነው ማንነቱም እንደሚናገረው እርሱ እንደተናገረው እንደዚያው ታማኝ ሆኖ ሳይለየን ለዘላለም ከእኛ ጋር ነው።"

- **የማስተንተኛ ጥያቄዎች**

1. የሁሉ ፈጣሪ የሆነው እግዚአብሔር ወዳጄ ብሎ አንተን መጥራቱ ምን አይነት ስሜት አለው?
2. እውነተኛ ወዳጅነት እውነተኛ ፍቅርንና መታዘዝን ምን ያክል ይጠይቃል?
3. ወዳጅነታችሁ ለተመሰረተበት የእግዚአብሔር ህግና ኅብረት ይበልጥ ክፍት ማድረግ የሚያስፈልግህ የሕይወትህ ክፍል የትኛው ነው?

- **አሰላስል**

እግዚአብሔር እጅግ ታላቅና ከፍ ያለ ከፍጥረትም ሁሉ በላይ የላቀና የማይደረስበት ቢሆንም፣ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ወደ እኛ ለመቅረብና ወዳጆቼ ብሎ ለመጥራት ወደደ። ይህ ወዳጅነት በእኛ ብቃት ወይም ዋጋ ላይ የተመሠረተ ሳይሆን ከእርሱ ጸጋና ፍቅር የተነሳ የተገኘ ነው። የዓለም ፈጣሪ የሆነው አምላክ ከእኛ ጋር የግል ኅብረት ለመመሥረት መፈለጉ የእርሱን ፍቅርና ለእኛ ያለውን ታላቅ ዓላማ ያሳያል። እንደ ወዳጆቹ እኛም በታማኝነት፣ በመታዘዝና በቅርብ ኅብረት ከእርሱ ጋር ለመመላለስ ተጠርተናል። ስለዚህ ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ወዳጅነት እንደ ታላቅ ጸጋ በመቁጠር በፍቅርና በመታዘዝ መጠበቅ እንደሚገባን ማስታወስ ተገቢ ነው።

- **ጸሎት**

በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ወዳጅህ እንድሆን ስለጠራኸኝ አመሰግንሃለሁ። ይህን የተቀደሰ ግንኙነት እንዳከብር፣ በመንገድህ በታማኝነት እንድመላለስና በሙሉ ልቤ እንዳፈቅርህ እርዳኝ። በመታዘዝና በፍቅር እውነተኛ የአንተ ወዳጅ ሆኜ እንድኖር አስተምረኝ። ልቤን ለመሪነትህና ለኅብረትህ ሁልጊዜ ክፍት አድርግ።

በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አሜን።

- **የአርምሞ ጥቅስ**

*"ከእንግዲህ ወዲህ ባሮች አልላችሁም፤ ባርያ ጌታው የሚያደርገውን አያውቅምና፤ ወዳጆች ግን ብያችኋለሁ፥ ከአባቴ የሰማሁትን ሁሉ ለእናንተ አስታውቄአችኋለሁና።"*

*— የዮሐንስ ወንጌል 15፥15 —*

## 2.30. እግዚአብሔር የማይለወጥና ዘላለማዊ ነው!

እግዚአብሔር ራሱን ለሙሴ ባስተዋወቀበት ጊዜ ራሱን የገለጠበት ስሙ ይኸውም *“ያለና የሚኖር እኔ ነኝ”* ብሎ የሚለው ማንነቱ የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ ማንነት የሚናገር ነው። እግዚአብሔር ፍጥረቱን ሁሉ ከመፍጠሩ በፊት ባለው ፍጹም የሆነ ማንነቱ፣ በተፈጠረ ጊዜ ሂደት የማያድግና የማያንስ ዘላለማዊ ማንነት ቀድሞውኑ ነበረ። በዚያን ጊዜ የነበረው የፈቃዱ ምክር እንዲሁም ማንነቱ ፈጽሞ በጊዜ ሂደት ማስተካከያ ሳይኖረው በዚያው ያልተለወጠ መልኩ እያለፈ በሚሄደው በዘመን የተወሰነ የሰው ልጅ እድሜ መካከል ዛሬም አለ። (ማኅበር, 1954)

ከዚህ በፊት በተዘረዘሩ ባህርያቱ እንዲሁም በዚህ መጽሐፍ ባልተገለጡ የእርሱ ብቻ የሆኑ ማንነቶቹ በአንዳቸውም ሁኔታ ሳይለወጥ ለዘላለም የሚኖር ነው። በዚህም መረዳት ውስጥ ሆኖ መዝሙረኛው ዳዊት በ102ኛው መዝሙረ ዳዊት ምዕራፍ ከቁጥር 25 ጀምሮ ባለው ክፍል የተፈጠሩ ፍጥረቱ ሁሉ የእርሱ እጅ ስራዎች እንደሆኑ እርሱም እነዚህን ሁሉ ያለ አንዳች ደጋፊ እና አማካሪ በገዛ ፈቃዱ ምክር እንደወደደ ለገዛ ራሱ ክብርም እንደፈጠራቸው ተናግሮ እነዚህ ሁሉ ግን በጊዜ ሂደት እንደሚያልፉና እንደሚጠፉ ደግሞ ይናገራል። እነዚህ ሁሉ እንደ ልብስ የሚያረጁና ትናንት በነበራቸው መልክ ዛሬ የማይገኙ ሲሆኑ የሰራቸውም እንደወደደ የሚለዋውጣቸው የሚለወጡለትም ሲሆኑ እርሱ ሰሪያቸው ግን ያው እርሱ ሆኖ አመቶቹም ከቶ ሳያልቁ ለዘላለም ሳይለወጥ የሚኖር ነው።

> “እግዚአብሔር ፍጥረቱን ሁሉ ከመፍጠሩ በፊት ባለው ፍጹም የሆነ ማንነቱ፣ በተፈጠረ ጊዜ ሂደት የማያድግና የማያንስ ዘላለማዊ ማንነት ቀድሞውኑ ነበረ።”

በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማያትንና ምድርን ፈጠረ በሚለው የዘፍጥረት 1፡1 እና በዮሐንስ ራዕይ 21፡1 ላይ ባለው አሮጌው አልፎ ሁሉ አዲስ በሆነበት የሰው ዘመን መካከል እግዚአብሔር በሁኔታ የተለወጠ ማንነት ሳይኖረው ሁሉን እየገዛ የኖረ ነው። ይህም ገና ፍጥረትን ሳይፈጥር በፊት በነበረው በዚያው ማንነቱ ሳይቀየር ዘመናትን የተሻገረ

መልኩ ሲሆን እርሱ ግን ሁሉን በኃይሉ ብርታት እያናወጠ እየለዋወጠም ለዘላለም ሳይለወጥ በዙፋኑ ላይ ፀንቶ ይኖራል። ዳንኤል በትንቢቱ እንዳለው እርሱ "በዘመናት የሸመገለና ሁሉን በስልጣኑ ቃል ደግፎ የያዘ የዘላለም አምላክና ፈጣሪ ነው።

በእነዚህ ሁሉ ጊዜያት ሳይደክምና ሳይታክት ክንዱም ከማዳን ሳታጥር ኃይሉም ሳይዝል ጉልበቱም ሳይላላ በእውቀትም ሳይጨምር ወይም ሳይቀንስ ከዘላለም በፊት እንደነበረ እንደዚያው እርሱ ራሱ የማይደረስበት ከፍታና ጫፍ ሆኖ ለዘላለም ይኖራል። መጽሐፍ ቅዱስ በትንቢተ ሚልክያስ 3፡6 ላይ እንደሚናገረው እርሱ እግዚአብሔር አይለወጥም። ገና ከመጀመሪያው ባለው በዚያው ፈቃዱ ዛሬም በልጁ በክርስቶስ ኢየሱስ በሰማይና በምድር ያለውን ሁሉ ለመጠቅለል በኃይሉ ብርታት እየሰራ ሳይለወጥ አለ።

እርሱ አልፋ ደግሞ ኦሜጋ የሆነ ከእርሱ በፊት ወይም በኋላ ሌላ ማንም የሌለው ዘላለማዊ አምላክ ነው። እርሱ በዘመናት የሸመገለ የነበረ፣ ያለና የሚኖር የዘላለም አምላክ ነው። ለፈጠረው ፍጥረቱ በበዛ ቸርነቱ ከዚህ ዘላለማዊ ማንነቱ አመታትን ያቀዳጃል።

> "እርሱ አልፋ ደግሞ ኦሜጋ የሆነ ከእርሱ በፊት ወይም በኋላ ሌላ ማንም የሌለው ዘላለማዊ አምላክ ነው።"

እርሱ ራሱ ግን ትናንትና፣ ዛሬ ለዘላለምም ያው ነው። ዙፋኑን በሰማይ አድርጎ ሁሉን እየገዛ በፊቱም እያሳለፋቸው እንደ መጎናፀፊያም እየጠቀለላቸው እየተለወጡም ባልተቋረጠ ሂደት "በመጀመሪያ" እንደነበረ እንዲሁም ዛሬም አለ።

ምንም እንኳን "መጀመሪያ" እንደነበረ ዛሬም እንደዚያው የሆነ ከመታወቅም ያለፈ ማለዳ ማለዳም ሁልጊዜ አዲስ የሆነ አምላክ ይሁን እንጂ ለሰው ልጆች ራሱን በየዘመናቱ ይበልጥ እየገለጠ ኖሯል። ይህም ከእርሱ የተለወጠ ማንነት የተነሳ ሳይሆን እርሱ ራሱ ከመጀመሪያው የነበረውን ያልተለወጠ የማይለወጥም መልኩን ለፍጥረቱ ሊገልጥ ሊታወቅላቸውም ወድዶ ያደረገው ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ በዕብራዊያን 1፡1 ላይ እንደሚናገረው ባለፉት ዘመናት በልዩ ልዩ መንገድ በጥላ መልክ ራሱን ለህዝቡ ሊገልጥ ሞክሮ በዚህ የዘመን መጨረሻ ግን

ከመጀመሪያ የነበረውን ዘላለማዊ አስደናቂ ማንነቱን ይበልጥ ለህዝቡ ሊገልጥ አለማትን በፈጠረበት በእቅፉም "ከመጀመሪያው" ጀምሮ አብሮት ባለው በልጁ በኩል ራሱን ተረከልን። በዚህም ምስጢር ሁሉ ለእኛ ተገልጦ ይህንኑ በዘመናት መካከል የማይለዋወጠውን መልኩን በተሻለ መንገድ ማወቅና ተሰውሮ የኖረውን በጥላ ውስጥ የተደበቀ አካላዊ እውነት ሁሉ መረዳት ቻልን።

እርሱ በዚህ የማይለወጥ ዘላለማዊ ማንነቱ የማይናወጥ መንግስትን ለራሱ የገነባ ሲሆን እርሱም ራሱ በዙፋኑ ላይ ሆኖ ያስተዳድረዋል። ለዚህም በሚመስል መልኩ ጌታችን ኢየሱስ ለእኛ ሁላችን በሚሆን መንገድ ለደቀ መዛሙርቱ ፀሎትን ባስተማረ ጊዜ አባታችን ሆይ በሰማያት የምትኖር ብሎ ጀምሮ ክብር ምስጋናም ለዘላለም ለአንተ ነው ብሎ በመጨረስ ይህንኑ በጊዜ የማይለወጥ ክብሩን አስታወቆናል። በዚህ ሁሉ የዘመን መለዋወጥ መካከል ታዲያ ራሱን ለህዝቡ ይበልጥ ይገልጥና ከህዝቡ ጋር ይቀራረብ ዘንድ ኪዳንን ለውጦ የታየ ሲሆን በዚህም የተለወጠ ኪዳን ውስጥ የእርሱ ማንነትና ባህርይ ፈጽሞ ያልተለወጠ ሲሆን ይልቁንስ ከዚህ በፊት ፍጥረቱ እርሱን ባልተረዳበትና ባላወቀበት መልኩ ማንነቱንና ባህርይውን ይበልጥ እናውቅ ዘንድ በልባችን ራሱን አድምቆ የገለጠበት አዲስ መንገድን ያስተዋወቀ ነው።

እርሱ አልፋ ደግሞ ኦሜጋ ነው። በዚህ መካከል የሚያልፉ ሁሉ ፍጥረቶቹ የማይለወጠውን መልኩን በመልካቸው እያንፀባረቁ ክብሩን በመግለጥ በየዘመናቸው ያልፋሉ። ከዚሁ የእርሱ የራሱ ማንነት ባለፈ ከባህርይውም አለመቀየር በዘለለ ቃሉ የዘላለም ሃሳቡ ይኸውም የፈቃዱ ምክር እንዲሁም ሰው ወደ እርሱ ይደርስበት ዘንድ የዘረጋው የደህንነት መንገድ ሁሉ እንዳይለወጡ ደግሞ እናውቃለን።

> "ምስጢር ሁሉ ለእኛ ተገልጦ ይህንኑ በዘመናት መካከል የማይለዋወጠውን መልኩን በተሻለ መንገድ ማወቅና ተሰውሮ የኖረውን በጥላ ውስጥ የተደበቀ አካላዊ እውነት ሁሉ መረዳት ቻልን።"

- **የማስተንተኛ ጥያቄዎች**

1. እግዚአብሔር የማይለወጥ መሆኑን ማወቅ በእርሱ ላይ ያለህን እምነትና መታመን እንዴት ያጠናክረዋል?
2. በየትኞቹ የሕይወትህ ክፍሎች በእግዚአብሔር ዘላለማዊ ተስፋዎች ላይ ይበልጥ መሠረት ማድረግ ያስፈልግሃል?
3. የእግዚአብሔር የማይለወጥ ባሕርይ ዛሬ የአኗኗርህን መንገድ እንዴት ሊመራው ይገባል?

- **አሰላስል**

እግዚአብሔር ዘላለማዊና የማይለወጥ ነው። ፍጥረት ሁሉ ቢለወጥና ቢያልፍም፣ እርሱ ግን ለዘላለም እንደዚያው ይኖራል። ባሕርዩ፣ ተስፋዎቹና ዓላማዎቹ ፍጹምና ዘላለማዊ በሆነው ባሕርዩ ላይ ስለተመሠረቱ ፈጽሞ አይወድቁም። ሰዎችና ሁኔታዎች ሊለዋወጡ ቢችሉም፣ እግዚአብሔር ግን አይለወጥም፤ ስለዚህ በእርሱ ላይ ሙሉ በሙሉ መታመን እንችላለን። የማይለወጠው አምላካችን ሁልጊዜ ታማኝ ስለሆነ፣ በሁሉም ወቅት እርሱን እንደ ጽኑ መሠረታችን ይዘን መመላለስ እንደሚገባን እናስታውስ።

- **ጸሎት**

በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፣ ፈጽሞ የማትለወጥ አምላክ ስለሆንክ አመሰግንሃለሁ። በዘላለማዊ ባሕርይህ፣ በተስፋዎችህና በፍጹም ፈቃድህ ላይ እምነቴን እንዳደርግ እርዳኝ። በዙሪያዬ ያለው ሁሉ ሲለወጥ፣ አንተ ግን ለዘላለም የማትናወጥ መሠረቴ እንደሆንክ አስታውሰኝ። በቃልህ በመታመን በሰላምና በእምነት እንድመላለስ አጽናኝ።

በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አሜን።

- **የአርምሞ ጥቅስ**

*"ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ እስከ ለዘላለምም ያው ነው።"*

*— ወደ ዕብራውያን 13፥8 —*

## 2.31. እግዚአብሔር አምላክ ነው ከእርሱም ሌላ የለም!

አምላክ በምድር ላይ ከሚርመሰመሰው ፍጥረት በላይ የሆነና ለየት ያለ በኃይሉ፣ በአስተሳሰቡና በማስተዋሉ፣ በመፍጠር ችሎታው የተለየ እንዲሁም የፍጥረትን የእለት ከእለት ምልልስና አዕምሮ መቆጣጠር የሚችል ከፍ ያለ ስብዕናን የሚፈልግ ማንነት ነው። በዚህም አገላለጽ መሰረት አንድ ነገር አምላክ ለመሆን አምላክ ይሆንላቸው ዘንድ በላያቸው ላይ ሊሾሙት የወደዱት ሰዎች አምላክ ነው ብለው ያሉት ያ አካል ከእነርሱ ከፍ ያለና ያለ እርሱ አንዳች ነገር ማድረግ እንደማይችሉ በተረዱ ጊዜ ይገባዋል ብለው የሚሰጡት ስፍራ ሲሆን ከእነርሱ የአምላክነት ፍረጃ ባለፈም ይሄው አምላክ ነው የተባለው አካል ነው በተባለውና ከዚያም ባለፈ መጠን እንደተባለለት ሆኖ የሚገኝ እንዲሆን ይጠበቅበታል። አምላክ ለሚያመልከው ህዝቡ አቅርቦትን የሚሰጥ፣ በሚሄዱበት መንገድ የሚመራ፣ ጥፋትን የሚያርም፣ በጠላቶቹ ላይ የሚሰለጥን፣ በሁሉ ላይ ከፍ ሊልና ሊሰለጥን ወዘተ ይገባዋል። (ማኅበር, 1954)

በዚህም መሰረት ሰዎች የሚያመልኳቸው በላያቸውም ላይ እንዲሰለጥኑ ክብር ይገባቸዋል ብለው ስፍራ የሚሰጧቸው በርካታ ነገሮች አሉ። በተለይ በተለይ በቀደሙት ዘመናት እግዚአብሔር አብርሃምን ከዘሩ ለይቶ በመረጠበት በዚያን ወቅት የነበሩት አሞራዊያን ከነዓናዊያን ለበርካታ ነገሮች አማልክቶቻቸው ይሆኑ ዘንድ ስፍራ በመስጠት እነርሱንም በማምለክ ይታወቃሉ። በዚህም መሰረት ፀሃይን፣ ጨረቃን፣ ዝናብን፣ ነፋስን.....ወዘተ ከሰው አቅም በላይ ከፍ ያለ አቅም ያላቸውን ፍጥረታት ሁሉ አማልክት አድርገው ሲያመልኩ ይታያሉ።

እነዚህ ፍጥረታት ካላቸው ከፍ ያለ አቅም የተነሳ ብሎም በሰዎች ቁጥጥር ስር ባለመሆናቸው እንደየሁኔታውም ጥፋትንና ልማትን ለማድረግ አቅም ያላቸው ስለሆኑ ከሰዎችም የዕለት ከዕለት እንቅስቃሴ ጋር በእጅጉ የተቆራኙና የሰዎችንም እርምጃ የሚወስኑ ሆነው ስለሚታዩ የእነዚሁ አካባቢ ሰዎች እንዲሁም በርካታ ሌሎች አህዛብ እነዚህንና ሌሎች መሰል አካላት አማልክቶቻቸው ይሆኑ ዘንድ በላያቸው ላይ ሲሾሙ ሲያመልኳቸውም ይታያሉ። የተለያየ ስያሜን የሚሰጧቸው እነዚህ አማልክቶቻቸው ታዲያ ልዩ በሆነ ሁኔታ ገዥ የሚሆኑበት መስክ ያላቸው በዚያ ጉዳይ ላይም የሚጠየቁና የሚለመኑ በዚያም መስክ ላይ ስኬትን ለማግኘት ከእነዚሁ አማልክት ጋር መግባባትን

የሚጠይቁ አይነት መስለው ይታያሉ። በዚህም መሰረት የፍቅር አምላክ፣ የጦርነት አምላክ፣ የልምላሜ አምላክ፣ የዝናብና የነጎድጓድ አምላክ፣ የነፋስ አምላክ፣ የመዋለድና የመባዛት አምላክ ወዘተ እየተባሉ የሚጠሩ ሰዎች በተቸገሩበት ጉዳይ ላይ መፍትሄ ይፈልጉ ዘንድ የሚሄዱባቸው ይሰሟቸውም ዘንድ የሚጠሯቸው አካላት ናቸው።

አንድ ሰው ከእነዚህ አማልክት ጋር ተገቢ የሆነ ግንኙነት ከሌለው በዚያ መስክ ላይ ብዙ ችግሮችን የሚያስተናግድ እንደሚሆን ይታሰባል ማለት ነው። ይህንንም የአምልኮ ስርዓት ለማድረግና ከአማልክቶቻቸው ጋር ለመገናኘት እነዚህኑ አማልክቶቻቸውን የሚወክሉ ቅርጾችን እነዚሁ የሚያመልኳቸው ሰዎች ይሰሩላቸዋል። ከዚህም ወዲያ የሰሩትን ይህንን ቅርጽ ለእነዚህ አማልክቶቻቸው የሚመለከበት ቤትና መቅደስ ይሆንለት ዘንድ በአዘጋጁት እነርሱም እየመጡ አምላካቸውን በዚያ ለማግኘት ባስተካከሉት በዚህ ስፍራ የተለያዩ ስጦታዎችን እያመጡ በዚህ ቅርጽ ፊትም ለአምላካቸው ይገባል የሚሉትን ስግደት እያቀረቡ ልመናቸውንና አምልኳቸውን ያሳልፋሉ። በዚህ መልኩ የተለያዩ አማልክትን ለተለያዩ ጉዳዮች ያድርጉ እንጂ እነዚህ ፍጥረታት በተፈጥሮ ላይ አላቸው ተብሎ በሚታሰበው አቅም ላይ ተመስርቶ አንዳቸው ከአንዳቸው የሚበላለጡም ሆነው ይታያሉ።

ከእነዚህ የአማልክቶቻቸው ቁጥር እልፍ ከሆነ ያገኙትን ሁሉ አምላክ ለማድረግ የማያርፉ አህዛብ መካከል ታዲያ አንድ እግዚአብሔር የሚባል አምላክ አብርሃም የሚባልን ሰው የእርሱ ይሆንለት ዘንድ ለይቶ መርጦ አወጣ። ይህ እግዚአብሔር የተባለ አምላክ ታዲያ በዚያን ጊዜ በዚያ ስፍራ እንደሚገኙ በርካታ አማልክት በሆኑ የተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ብቻ ልዩ ኃይል ያለው ደግሞ ከሌሎች አማልክት ጋር በኅብረት የሚሰራ እንደዚህ ነው ተብሎም ይታወቅ ዘንድ መልኩም በቅርጽ ይገለጽ ዘንድ የሚታይ የሚዳሰስ ያልሆነ በሁሉም ላይ የሚሰለጥንና የሚገዛ ልዩ አምላክ ነበር። (Van De Mieroop, 2016) (ማኅበር, 1954)

ይህ የአብርሃም አምላክ እግዚአብሔር እንደ አህዛብ አማልክት እርሱን ፍለጋ ረጅም መንገድ አቋርጠህ ሄደህ የሚኖርበት ቦታ ጋር ደርሰህ ታገኘው ዘንድ በአንድ ስፍራ ብቻ የተወሰነም አይደለም። ነገር ግን ባለህበት ሁሉ ያለ፣ የልብህን ስሜትና ሃሳብ ጭምር ሳትነግረው የሚያውቅ፣ በፍጥረቱ ሁሉ ላይ ስልጣን ያለው፣ ሁሉን ደግሞ የፈጠረና ሁሉን

በስልጣኑ ቃል የደገፈ በእውነትና በመንፈስ የሚመለክ እውነተኛ አምላክ ነው። ይይዘው ዘንድ የሚሰራለት የሚበቃው ቤት የለም፣ እንዲህ ነው ተብሎ ይገለጽ ፈጽሞም ይታወቅና ይብራራ ዘንድ እንዳይቻል ቅርጽም እንዳይሰራለት ቁመቱ፣ ወርድና ስፋቱ አይታወቅም። በዚህም መሰረት እርሱን ብቻ የሚያመልክ ለእርሱም የተለየን ቅዱስ ህዝብ ያመጣ ዘንድ እግዚአብሔር አብርሃምን መረጠ። ከዚህ ወዲያም መጽሐፍ ቅዱስ በዘፍጥረት 17 ላይ እንደሚናገረው እግዚአብሔርና አብርሃም ግንኙነታቸውን በተመለከተ በገቡት ቃል ኪዳን ላይ በግልጽ እንደሚታየው እግዚአብሔር እርሱ ለአብርሃም አምላኩ ይሆን ዘንድ አብርሃምና ዘሩ ደግሞ እግዚአብሔርን ብቻ አምላኩ ያደርግና ያመልክ ዘንድ ተስማምተዋል።

ሰዎች የሚያመልኳቸው እስከ ዛሬም ድረስ የሚከተሏቸው በልባቸውም ትልቅ ስፍራ የሚሰጧቸው ብዙ አማልክት ያሉ ቢሆንም አንዳቸውም ግን ከዚህ በፊት ባሉት የዚህ መጽሐፍ ክፍል በተብራራውና በተገለፀው መልኩ የሆነ ማንነት ያላቸው የሆኑ አይደሉም። እነዚህ ሁሉ የተፈጠሩ ፍጥረታት የሆኑ፣ በየጊዜው መልካቸው የሚለዋወጥ፣ ወጥ አቋም የሌላቸው፣ በትውልድ መካከል ፀንተው የማይዘልቁ፣ ይሰሙና ይመልሱ ዘንድ ህያዋን ያልሆኑ፣ የሚያመልኳቸው ሰዎች የሚሰሯቸውና ቅርጽ የሚያበጁላቸው፣ በግልጽ የሚታወቅ የሚያመልኳቸው ሰዎች ስለ እነርሱ የሚናገሩት ያለቀ ታሪክ ያላቸው፣ ለሰዎች ጥያቄ መልስን የማይሰጡ፣ ሲጠሩም የማይሰሙ ግዑዛን ናቸው።

> “ሰዎች የሚያመልኳቸው እስከ ዛሬም ድረስ የሚከተሏቸው በልባቸውም ትልቅ ስፍራ የሚሰጧቸው ብዙ አማልክት ያሉ ቢሆንም አንዳቸውም ግን ከዚህ በፊት ባሉት የዚህ መጽሐፍ ክፍል በተብራራውና በተገለፀው መልኩ የሆነ ማንነት ያላቸው የሆኑ አይደሉም።”

እነዚህ ሁሉ ሰዎች አማልክት ናቸው ያሏቸው ሃይላትና ፍጥረታት እንዲሁም ሰዎች የፈጠሯቸው አማልክት ሁሉ በአንድነት ከእግዚአብሔር ያልሆኑ አጋንንት በሚለው

ቅርጫት ውስጥ የሚከተቱ የጨለማው አለም ሃይላት ህዝቡን በተለያየ መንገድ የሚያስቱባቸው እውነተኛ ከሆነውም አምላክ ከእግዚአብሔር የሚያርቁባቸው ማሳሳቻዎች ናቸው። እነዚሁ አማልክት ራሳቸውን እንኳን ይከላከሉ ዘንድ አቅም የሌላቸው እነርሱ ህዝቡን ሳይሆን ህዝቡ እነርሱን የሚሸከማቸው ግዑዛን ናቸው። ታዲያ እንደዚህ አይነት በምድር ላይ የሚርመሰመሰው ህዝብ የሚያመልካቸው ብዙ አማልክት ዛሬም ድረስ ያሉ ቢሆንም አንዳቸውም ግን እውነት አይደሉም። በዚህም መሰረት የእኛው ዘመን ሂንዱይዝምን ጨምሮ ሌሎች በርካታ ሐይማኖቶች አማልክት ናቸው ብለው የመደቧቸው መቅደስና ካህናትም መድበው የሚያመልኳቸው በርካታ ሺህ አማልክት ዛሬም በህዝቡ መካከል ይገኛሉ።

እግዚአብሔር ግን ቅዱስ እጅግ የተፈራና የተከበረ እውነተኛም አምላክ ነውና ያመልከው ዘንድ ከሌላው በርካታ አማልክት ማዕበል ውስጥ የሚዋኝና ልቡ የረከሰ ህዝብ ጋር እንዳይቀላቀል ለእርሱ ብቻ የተለየ ሁለንተናውን ለእርሱ ይቀድስና ይለይ ዘንድ የተመረጠ በሁለንተናው ቅዱስ ህዝብና ወገንን ከአህዛብ መካከል ለራሱ አወጣ። እግዚአብሔር እርሱ ለእስራኤል ብቻ የሆነ ብሎም የእስራኤል ቅዱስ የተባለ በዙሪያቸው ያሉ አህዛብ ካሏቸው እልፍ አማልክት የተለየ አንድና ብቸኛ የሆነ በሁሉም ላይ ስልጣን ያለው የሁሉም ደግሞ ፈጣሪ የሆነ አምላክ ነው።

ይህ ድንቅ አምላክ እግዚአብሔር ይችለውና ይይዘው ዘንድ ቤት እንዳይሰራለት ሰማይ ዙፋኑ ምድርም የእግሩ መረገጫ ነው። በአንዳች ነገር ተመስሎ ይቀረጽ ዘንድ እንዳይታወቅ በሁሉም ስፍራ ሁሉን አዋቂ ሆኖ የሚገኝ ይጨበጥና ይዳሰስ ዘንድ ምስልም ይሰራለት ዘንድ የማይታይ መንፈስ የሆነ ልዩ አምላክ ነው። እርሱ ውሆችን በእፍኙ ይሰፍራል፣ ሰማይንም በስንዝር ይለካል፣ የምድርንም አፈር በመስፈሪያ ሰብስቦ ይይዛል፣ ተራሮችን በሚዛን ኮረብቶችንም በሚዛኖች የመዘነ ነው። የፈጠረውን ፍጥረት

> “እንግዲህ ይህንን እግዚአብሔርን በማን ትመስሉታላችሁ? ወይስ በምን ምሳሌ ታስተያዩታላችሁ? እርሱ የአማልክት ሁሉ አምላክ፣ የጌቶችም ሁሉ ጌታ፣ የነገስታትም ሁሉ ንጉስ ምሳሌና ማስተያያም የሌለው ልዩ አምላክ ነው።”

ሲፈጥር ያማከረው መንፈሱንም ያስተማረ ማንም የለም። ሁሉ ከእርሱ በእርሱም ነው። እነሆ አህዛብ በፊቱ በገንቦ ላይ እንዳለች ጠብታ ናቸው፣ በሚዛንም እንዳለ ትንሽ ትቢያ ተቆጥረዋል፣ ደሴቶችን እንደ ቀላል ነገር ያነሳል።

እንግዲህ ይህንን እግዚአብሔርን በማን ትመስሉታላችሁ? ወይስ በምን ምሳሌ ታስተያዩታላችሁ? እርሱ የአማልክት ሁሉ አምላክ፣ የጌቶችም ሁሉ ጌታ፣ የነገስታትም ሁሉ ንጉስ ምሳሌና ማስተያያም የሌለው ልዩ አምላክ ነው። እርሱ በኃይሉ ታላቅ፣ በማስተዋሉ ግሩም፣ ሁሉን በእጁ የሰራ በስልጣኑም ቃል ፍጥረትን ሁሉ የሚያኖር፣ በአፉ ቃል ብቻ መኖርና አለመኖራቸውን የሚወስን፣ ለቃል ኪዳኑ ታማኝ፣ ይዋሽ ዘንድ እንዳይችል ሰው ያልሆነ እውነተኛ በሁሉም ስፍራ የሚገኝ፣ ሁሉን አዋቂ ሁሉን ቻይ፣ በሁሉም ላይ ስልጣን ያለው ፍጥረትን ሁሉ የሚመግብ፣ መልካምነቱ ለክፉና ለመልካሙ ሁሉ የሆነ፣ ከሆነው ሁሉ አንዳች እንኳን ያለ እርሱ ያልሆነ፣ ከ እስከ የሚባል ዘመን የሌለው ዘመናትን ሁሉ የፈጠረ የዘላለም አምላክ ነው።

*ታዲያ ይህንን እግዚአብሔርን በማን ትመስሉታላችሁ? በምንስ ምሳሌ ታስታያዩታላችሁ?*

እግዚአብሔር በዚህች ትንሽ መጽሐፍ ተገልጾና ተብራርቶ ያልቅ ዘንድ ውስን አምላክ አይደለም። እርሱን ለመግለጽ ቀርቶ በውስጥ ማንነት እንኳን በጥቂቱ ለመረዳት የእርሱን የራሱን እርዳታ ይፈልጋል። ማንም ሰው በየትኛውም አይነት ልዩ የሆነ ክሽን ቃላት ተጠቅሞ ከፍጥረት ጅማሬ አንስቶ በየዘመኑ በትውልድ ቅብብሎሽ እርሱን ለመግለጽ ቢሞክር ከእርሱ ማንነትና ታላቅነት አንጻር በምድር ሁሉ ላይ ካሉ የውሃ አካላት ላይ አንዳች ትንሽ ጠብታን የማንሳት ያክል እንኳን እንደማይሆን አስባለሁ።

እርሱ እግዚአብሔር እጅግ ታላቅ ክቡርና የተፈራ ልዩ አምላክ ነው። ሙሴ በዘዳግም 33፡26-27 ላይ ከብዙ ማብራሪያ በኋላ በመጨረሻ እንደተናገረው የእርሱ ይሆን ዘንድ ለእግዚአብሔር ቅዱስ ህዝብ ሊሆን ለተመረጠው ከግብጽ ባርነት በአምላኩ ጽኑ እጅ ከወደረኞቹ ቀንበር ተላቆ ነጻ ለወጣው ህዝብ መደምደሚያ እንዲሆነው በሰጠው ቃል እንደሚናገረው *“እንደ እግዚአብሔር ያለ ማንም የለም።”*

እርሱ እግዚአብሔር ብቻውን እውነተኛ የሆነ አምላክ ነው ከእርሱም በቀር ሌላ የለም። ምንም እንኳን ከላይ እንደተገለፀው ሰዎች አማልክቶች ናቸው ብለው የሚያመልኳቸው በልባቸው ስፍራን የሰጧቸው በርካታ አማልክት ቢኖሩም አንዳቸውም ከእግዚአብሔር በቀር እውነት ያልሆኑ የሰው እጅ ስራዎች ብቻ የሆኑ ግዑዛን ናቸው።

> “ማንም ሰው በየትኛውም አይነት ልዩ የሆነ ክሽን ቃላት ተጠቅሞ ከፍጥረት ጅማሬ አንስቶ በየዘመኑ በትውልድ ቅብብሎሽ እርሱን ለመግለጽ ቢሞክር ከእርሱ ማንነትና ታላቅነት አንጻር በምድር ሁሉ ላይ ካሉ የውሃ አካላት ላይ አንዳች ትንሽ ጠብታን የማንሳት ያክል እንኳን እንደማይሆን አስባለሁ።”

እግዚአብሔር ለህዝቡ ደግና መልካም አላማውም ፍቅር የሆነ ህዝቡን ከእርሱ ጋር ይሆንና በፊቱ ይመላለስ ዘንድ የሚመራበት መርህ ያለው ፍትሃዊ፣ ታጋሽና መሐሪ ደግሞ መዓትንም የተሞላና የሚቆጣ ቀናተኛም የሆነ ክብሩን ለማንም አሳልፎ የማይሰጥ ይመለክ ዘንድ ብቻውን የተገባው ታላቅ አምላክ ነው።

ይህ እግዚአብሔር የሰው ልጅን ከሰራበት ጊዜ ጀምሮ በመልኩ ከሰራው ከዚህ ሰው ጋር ተገቢ የሆነን ግንኙነት ይፈልግ የነበረ ቢሆንም ሰው እንደሚገባ እግዚአብሔርን አለማወቁ ሰውን ለተደጋጋሚ ውድቀት ሲዳርገው ኖሯል። ይህም ታላቅ ውድቀት ከዚህ ሁሉን ቻይ የሆነው ደግ ጌታና አምላኩ ተለይቶ መኖሩ ነበር። ከዚህ ወድያ ምንም እንኳን ከማንም ምንም የማይፈልግ ከፍጥረትም በፊት ዛሬ እንዳለ ከብሮ የኖረ ለዘላለምም ክብሩ ከፍና ዝቅ የማይል አምላክ ቢሆንም በዲያብሎስ ተታልሎ ከመገኘቱ ለተባረረው ለፈቃዱም ተላልፎ ተሰጥቶ ለሚባዝነው ረዳት አልባ ተንከራታች ምስኪን የሰው ልጅ ዳግመኛ እግዚአብሔር እርሱ ማን እንደሆነ በሚገባ አውቆ በፊቱ በታላቅ አክብሮትና ፍርሃት ፍቅርና ጥንቃቄም ይመላለስ ዘንድ እንደገና ራሱን ለህዝቡ አብልጦ ሊገልጥ ወደደ።

> “እግዚአብሔር እርሱ ብቻውን በላይ በሰማይ በታችም በምድር አምላክ እንደሆነ ያውቅ ዘንድ ይህንንም በልቡ ይይዝ ዘንድ ከእርሱም በቀር ሌላ እንደሌለ ይረዳ ዘንድ በዚህም እውቀት በእግዚአብሔር ፊት ይመላለስ ዘንድ ይህንን ለህዝቡ እንደገለጠ ይታያል።”

ይህም እውቀት መጨረሻው እግዚአብሔር እርሱ ማን እንደሆነ ጥንቅቅ አድርጎ ማወቅ ሳይሆን መጽሐፍ ቅዱስ በዘዳግም 4፡35 እና 39 ላይ እንደሚናገረው እግዚአብሔር እርሱ ብቻውን በላይ በሰማይ በታችም በምድር አምላክ እንደሆነ ያውቅ ዘንድ ይህንንም በልቡ ይይዝ ዘንድ ከእርሱም በቀር ሌላ እንደሌለ ይረዳ ዘንድ በዚህም እውቀት በእግዚአብሔር ፊት ይመላለስ ዘንድ ይህንን ለህዝቡ እንደገለጠ ይታያል።

ታዲያ እንዲህ አይነቱ በሚጠራው ጊዜ ሁሉ እግዚአብሔር አምላኩ እንደሚቀርበው አምላኩ ወደ እርሱ የሚቀርበውና የሚጠጋው አምላክ ያለው ታላቅ ህዝብ ከዚህ የእግዚአብሔር ለመሆን የተለየ ህዝብ ሌላ ማን ነው? በዚህ እግዚአብሔርን የማወቅ ጎዳና ውስጥ እግዚአብሔር አምላክ እንደሆነ ብቻ ማወቅ በቂ አይደለም ነገር ግን ከእርሱ በቀርም ሌላ እንደሌለ ማወቅ ያስፈልጋል።

ገና በማለዳው እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር በገባው ኪዳን መሰረት እግዚአብሔር ለእስራኤል አምላኩ ሲሆን እስራኤል ደግሞ ከአህዛብ የተለየ ለእግዚአብሔር የተቀደሰ ልዩ ህዝብ ሆኗል። እርሱ ፈጣሪና ሰሪያቸው ደግሞ አምላካቸው ሲሆን እነርሱ ደግሞ የማስማሪያው በጎች መልኩም የሚታይባቸው ቅዱስ ህዝቡ ሆነዋል።

> “እግዚአብሔር አምላክ እንደሆነ ብቻ ማወቅ በቂ አይደለም ነገር ግን ከእርሱ በቀርም ሌላ እንደሌለ ማወቅ ያስፈልጋል።”

በዚህ ሁኔታ እግዚአብሔር በሰማይና በምድር ከምድርም በታች በባህር ውስጥ ባለው ሁሉ ላይ ባለ ሙሉ ስልጣን የሆነ ሁሉን ለእርሱ ክብር ያመጡ ዘንድ ለእርሱ ክብር የሰራቸው ክብርም ሁሉ የተገባው ታላቅ አምላክ ቢሆንም

ፍጥረቱ በተለይም ከእርሱ ጋር ይቀራረብ ዘንድ እድል ያገኘው የሰው ልጅ ደጋግሞ የተለያዩ አማልክትን ለራሱ እያደረገ ከሚወደው አምላኩ ሲኮበልልና ሲጠፋ ይታያል።

ገንዘብ፣ ትዳር፣ ልዩ ልዩ ጣኦት፣ ቅርፃ ቅርጽ፣ ተፈጥሮ፣ እውቀት፣ ስሜት፣ ውበትና ደም ግባት፣ ስልጣን፣ ሀብት ወዘተ በልቡ ላይ ስፍራን የያዙ እግዚአብሔርን ከእርሱ ያራቁ አማልክት ጣኦቶቹ እየሆኑ በዲያብሎስ ማታለያና ማግባቢያ ሳያቋርጥ ወደ ሲኦል እየነጎደ ይታያል።

አምልኮና ስግደት ክብርም የሚገባው የፍጥረታት ሁሉ ጌታ የሆነ፣ ክብርንም ለእርሱ ያመጡለት ዘንድ የሰራቸው፣ እውነተኛ የሆነ፣ ክብርም ሁሉ የተገባው፣ ከእርሱም በቀር ተመሳሳይ ሌላ የሌለው፣ ብቸኛው እውነተኛ አምላክ እግዚአብሔር ብቻ ነው። ገና ከመጀመሪያው ይህንኑ አምልኮ ስግደት ክብርም ከእግዚአብሔር ጋር ሊጋራ እንዲያውም ከእርሱ ሊበልጥ ወድዶ ራሱን በትዕቢት የሞላው የተጣለው ኪሩብ እባቡና አሳቹ ዲያብሎስ ዛሬም ለራሱ ክብርን ሊወስድ ወድዶ የሰው ልጆችን በተለያየ ማባበያ በጊዜያዊም ምድራዊ ማታለያ ከዘላለም ሲያጎድላቸው ይታያል።

> “አምልኮና ስግደት ክብርም የሚገባው የፍጥረታት ሁሉ ጌታ የሆነ፣ ክብርንም ለእርሱ ያመጡለት ዘንድ የሰራቸው፣ እውነተኛ የሆነ፣ ክብርም ሁሉ የተገባው፣ ከእርሱም በቀር ተመሳሳይ ሌላ የሌለው፣ ብቸኛው እውነተኛ አምላክ እግዚአብሔር ብቻ ነው።”

እግዚአብሔርም ይህንኑ ለማስጠንቀቅ በሚመስል መልኩ ደጋግሞ የእርሱ ለመሆን ለተመረጠው ልዩ ወገን የሆነ ህዝቡ በስሙም ለቀደሰው ለዚህ ርስቱ ከእርሱ በቀር በላይ በሰማይ በታችም በምድር ከምድርም በታች ከባህር ውስጥ ካለም የትኛውም ነገር አማልክትን ለእርሱ እንዳያደርግ ምስልና ቅርጽም ሰርቶ እንዳያመልክ ያስጠነቀቀው ሲሆን ይህን ቢያደርግም እግዚአብሔር እርሱ በዚህ የሚቀና እንደሆነ በዚህም ቅናቱ የተቀደሰ ስሙን ያከብርና በአሕዛብ መካከል ይቀድስ ዘንድ በኃይሉ በህዝቡ መካከል እንደሚንቀሳቀስ በቁጣውም እንደሚገለጥ ይናገራል።

ዛሬም የሰው ልጆች ከተለያዩ ለእግዚአብሔር ብቻ ሊሆን ከተገባው የልባቸው ዙፋን ልዩ ልዩ ምድራዊ ጣኦቶቻቸውን ፈጥነው ሊያስወግዱ ክብርን፣ አምልኮና ስግደትን ሁሉ ብቻውን ለሚገባው እውነተኛም አምላክ ለሆነው የፍጥረታት ሁሉ ፈጣሪ ለሆነው ከእርሱም በቀር ሌላ ለሌለው ለእግዚአብሔር ያመጡ ዘንድ ይገባቸዋል።

*እግዚአብሔር እርሱ ብቻውን እውነተኛ ታላቅ አምላክ ነው ከእርሱም በቀር ሌላ አንዳች የለም!*

"ዛሬም የሰው ልጆች ከተለያዩ ለእግዚአብሔር ብቻ ሊሆን ከተገባው የልባቸው ዙፋን ልዩ ልዩ ምድራዊ ጣኦቶቻቸውን ፈጥነው ሊያስወግዱ ክብርን፣ አምልኮና ስግደትን ሁሉ ብቻውን ለሚገባው እውነተኛም አምላክ ለሆነው የፍጥረታት ሁሉ ፈጣሪ ለሆነው ከእርሱም በቀር ሌላ ለሌለው ለእግዚአብሔር ያመጡ ዘንድ ይገባቸዋል።"

TRUTH 14:6

- **የማስተንተኛ ጥያቄዎች**

1. በሕይወትህ ውስጥ ትኩረትህን፣ መታመንህን ወይም መሰጠትህን የሚሹ ከእግዚአብሔር ጋር ሊወዳደሩ የሚችሉ ነገሮች ምንድን ናቸው?
2. እግዚአብሔር ብቻውን አምላክ መሆኑን ማወቅ አምልኮህንና አኗኗርህን እንዴት ይለውጠዋል?
3. ለእግዚአብሔር ብቻ የሚገባውን ቦታ የሚወስድ ማንኛውንም ነገር ለማስወገድ ምን ተግባራዊ እርምጃዎችን ልትወስድ አሰብክ?

- **አሰላስል**

እግዚአብሔር ብቻውን አምላክ ነው፤ ከእርሱ ሌላ እውነተኛ አምላክ የለም። እርሱ ከብዙ አማልክት አንዱ አይደለም፤ ክብሩንም ከማንኛውም ፍጥረት ጋር አይካፈልም። እርሱ ብቻ የፍጥረት ሁሉ ፈጣሪ፣ ጠባቂና ሕጋዊ ንጉሥ ነው። እርሱን በእውነት ስናውቀው፣ ልባችን ከሐሰተኛ የደህንነት ምንጮችና አምልኮአችንን ከሚወዳደሩ ትናንሽ ጣዖታት ነፃ ይወጣል። እግዚአብሔር ብቻ ሙሉ ማንነታችን፣ ፍጹም መታመናችንና ምስጋናችን ይገባዋል። ስለዚህ በሕይወታችን ከእርሱ በላይ ስፍራ የሚይዝ ማንኛውም ነገር እንዳይኖር ልባችንን አጥብቀን ልንይዝ ያስፈልገናል።

- **ጸሎት**

በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፣ አንተን እንደ እውነተኛውና ብቸኛው አምላክ በትክክል እንዳውቅህ ዓይኖቼን ክፈት። በልቤ ውስጥ የአንተን ቦታ የወሰዱ ጣዖታትን እንዳስወግድ እርዳኝ። አንተን ብቻ እንዳመልክ፣ በሁለንተና እንዳምንህና በየዕለቱ ለክብርህ እንድኖር እርዳኝ። ሕይወቴ አንተ ብቻ አምላክ እንደሆንክ የሚመሰክር ይሁን።

በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አሜን።

- **የአርምሞ ጥቅስ**

*“እኔ እግዚአብሔር ነኝ ከእኔም ሌላ ማንም የለም፤ ከእኔም በቀር አምላክ የለም፤”*

*— ትንቢተ ኢሳይያስ 45፥5 —*

## ማጠቃለያ

በእነዚህ ሁሉ ከዚህ በፊት በተገለፁ የእርሱ ባህርያት ምንም እንኳን እርሱን ለመግለጽ ጸሃፊው በብዙ የሞከረ ቢሆንም እርሱ እጅግ ትልቅ ነውና በዚህች ትንሽ መጽሐፍ ብቻ ተተርኮ የሚያልቅ አምላክ ግን አይደለም። እግዚአብሔር ይህ ብቻ አይደለም። በየትኛውም ሰዋዊ ቃላት በተመረጡም ንግግሮች ሁሉ ቢብራራ በውስጥ መንፈሳችን ከምንረዳው እርሱን ተጠጋግተን እንኳን ያወቅነውን ያክል መግለጽ የሚችል አቅም በእነዚህ ፊደላት ውስጥ የለም።

በውስጥ ሰውነታችን የሚሰማንና እርሱን በግል የተረዳነው ስለ እርሱ ልንናገር ከምንችለው ብሎም ከምንሞክረው፣ ስሜታችንና ፍቅራችን ታላቅነቱንም ልናብራራ መርጠን ከምንጠቀምባቸው ቃላት ሁሉ በላይ ነው። አባቱን በህይወት ኖሮ ያሳየን በምልልሱና በትምህርቶቹም የተረከልን አብን ያየነበት ልጁም በመጨረሻ ለደቀ መዛሙርቱ በዚህ ሁሉ ትጋት ለሶስት አመት ተኩል ከተረከው በላይ የሆነ ገና ሊነግራቸው የሚፈልገው ያልነገራቸው በወቅቱ ሊሸከሙት የማይችሉት ብዙ እውነት ገና እንዳለ ይነግራቸዋል። ነገር ግን በእርሱ ዘንድ ያለውን ይህንን እውነትና ምስጢር ሁሉ የሚያውቅ ገና ያልነገራቸውን ሁሉ የሚገልጥና የሚያስተምራቸው ወደ እውነትም ሁሉ የሚያደርሳቸው አስተማሪና አጽናኝ ይኸውም ጌታ መንፈስ ቅዱስ እንደሚመጣ ነገራቸው።

መጽሐፍ ቅዱስ በዘዳግም 29፡29 ላይ እንደሚለው የተገለጠው ለእኛ ለትምህርታችን ደግሞም ለህይወት ሲሆን ያልተገለጠውና ምስጢሩ ደግሞ ለእርሱ ለእግዚአብሔር ነው። ይህንን ሁሉ ለእግዚአብሔር የሆነ ምስጢር ሁሉ ግን ልናውቅ ወድደን በትህትና እግሩ ስር በተገኘንበት ልክ ሊገለጥልንና ሊያስተምረን የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር ሁሉ የሚያውቀው መንፈስ ቅዱስ አሁን ከእኛ ጋር አለ።

ወደ ኢየሱስ ደረት ቀርቦ ብዙ ያወቀውና የተማረው ዮሐንስ ስለ ወዳጁ በተረከው ትረካ መጨረሻ ላይ ይህ የሚተርከው ኢየሱስ ያደረገው ከተተረከው ሌላ ብዙ ነገር ደግሞ እንዳለ ነግሮን ያ ሁሉ በእያንዳንዱ ቢፃፍ ለተፃፉት መጽሐፍት ዓለም ራሱ

ባልበቃቻቸውም ይመስለኛል ብሎ የእርሱን ከመተረክና ከመታወቅ ያለፈ ማንነት ገልጦልናል።

*በዚህች ይልቁንስ ታናሽ የሆነች መጽሐፍ የተነገረውማ ምን ያክል ያነሰ ይሆን?*

በዚህች መጽሐፍ ውስጥ ለመግለጥ ከተሞከረው ባህርያቱ መካከል የሆነው ፍቅሩ ብቻ ጳውሎስ በኤፌሶን መልዕክት 3፡19 ላይ እንደነገረን ስፋቱና ርዝመቱ ከፍታውና ጥልቀቱ ምን ያህል መሆኑን ለማስተዋልና ለመረዳት ለማወቅም ከአዕምሮ የሚያልፍ እንደሆነ፣ በቃላት ሰድሮ ለመግለጽም የሚያዳግት እንደሆነ ነግሮናል።

ኢዮብ እንዳለን *"እግዚአብሔር ታላቅ ነው እኛም አናውቀውም የዘመኑም ቁጥር አይመረመርም።"* ወደ ሰማይ ስንወጣ ሰማዩን እርሱ የሞላ ነው ወደ ሲኦልም ብንወርድ እነርሱ ሁሉ ስለ እርሱ የሚናገሩ ናቸው ሰማያትና ፍጥረት ሁሉ የእግዚአብሔርን ክብር ሳይቋርጡ ይናገራሉ የሰማይም ጠፈር ሁሉ የእጁን ስራ ያወራል።

በዚህ ሁሉ ዘመን ውስጥ ባልተቋረጠ ዑደት በምስራቅ ወጥታ በምዕራብ የምትጠልቀዋ ለጻድቁም ለሀጢአተኛውም እኩል የሚያወጣት በስልጣኑ ቃል ተደግፋ ያለችው ፀሀይና የቀሩት የሰማይ ሰራዊት ሁሉ የእግዚአብሔርን ታላቅነት ሳያቋርጡ ያለ ድካም እስከ ዛሬ ድረስ ያወራሉ። በአንድ ሰው ውስጥ በየእለቱ ያለው የአተነፋፈስ፣ የአመጋገብ የመዋለድ፣ የመረጃ ልውውጥ፣ የሚለዋወጥ ስሜት፣ ከቁጥጥር ውጭ የሆነ ፈቃዱ፣ ባልተቋረጠ መልኩ ከማወቅ የማያርፈው አዕምሮ፣ አልደርስበት ያለው ሰላም፣ በቁሳቁስ ሊያገኘው ያልቻለው እረፍት፣ እርካታ ማጣቱ፣ ሞትና ውልደቱ ወዘተ ሁሉ የእግዚአብሔርን ህያውነትና የነፍሳችን ጉድለት የሚሞላው በእርሱ ብቻ እንደሆነ ሳያቋርጡ ይነግሩናል።

በዚህ ሁሉ መጠን እርሱ ራሱን ያለ ምስክር ሳይተው እናውቀው ዘንድ ወድዶ እንደ ወገግታ ተዘርግቶ የሚገኝ ቢሆንም እናውቀው ዘንድ ባለመፈለግና ልባችንን ለእርሱ በመዝጋታችን ምክንያት በልበ ደንዳናነት ስንመላለስ ለእኛና በዙሪያችን ላለ ህዝብ ለአገርም ቀውስ ምክንያት ስንሆን የራሳችንንም አሉታዊ ድርሻ ስንወጣ እንታያለን። እግዚአብሔርን ሊታወቅ በሚገባው እርሱ ራሱን ለእኛ ሊገልጥ በወደደበት ልክ አለማወቅ ለዚህም የሚገባውን እንደ ተረዳነው እግዚአብሔርነቱ መጠን የሆነ የተገባ በአክብሮትና

በፍርሃት በፍቅርም የሆነ አምልኮ በፊቱ አለማምጣት እርሱንም አለመፍራት ትልቅ ዋጋን የሚያስከፍል ነው።

እውነተኛ በሆነ መንገድ ይህንን ታላቅ አምላክ በእውነትና በመንፈስ ለማምለክም ከስርዓቱ ሁሉ በፊት እርሱን ማወቅ አስፈላጊ ነው። በእሳት ነበልባል በእሾህ ቁጥቋጦ መካከል ያየውን ድንቅ ነገር የበለጠ ለመረዳት ከነጫማው የተጠጋው ሙሴ ወደ እርሱ በቀረበ ጊዜ መጀመሪያ የተገነዘበው ነገር የእርሱን ቅድስናና ወደ እርሱ ለመቅረብም የሚያስፈልገውን የመቀደስ አስፈላጊነት ነበር።

> “የትኛውንም ያክል ጊዜ እርሱን ለማወቅ እየሞከርን ብንኖር እርሱ ልንደርስበትና አውቀን ልንጨርሰው የምንችለው ታውቆ የሚያልቅና የሚደረስበት ውስን አምላክ አይደለም።”

እግዚአብሔር በፊቱ ከምናቀርበው የትኛውም አይነት መስዋዕት በላይ ምህረትና ፍቅርን፣ በእርሱ ዘንድ እጅግ ከተወደደውም የሚቃጠል መስዋዕት በላይ እርሱን ማወቃችንን የበለጠ ይወዳል። የትኛውንም ያክል ጊዜ እርሱን ለማወቅ እየሞከርን ብንኖር እርሱ ልንደርስበትና አውቀን ልንጨርሰው የምንችለው ታውቆ የሚያልቅና የሚደረስበት ውስን አምላክ አይደለም።

ለደረስንበትና ላወቅነው ለዚያ መረዳት እየታመንን በፀጋውና በመንፈሱም እገዛ በህይወታችን እርሱን እየገለጥን የበለጠ እናውቀው ዘንድ ባልተቋረጠ መልኩ የኋላችንን እየረሳን ያላወቅነውን ከፊታችን ያለ ሌላ እውቀት ለመያዝ መዘርጋት ያስፈልገናል።

እነዚህ ሁሉ የእግዚአብሔር ባህርያት ምንም ሳይጣሉና ሳይገፋፉ በመካከላችን እየተገለጡ እስከዛሬ ሳይለወጡ አሉ። እውነቱና ምህረቱ፣ ትዕግስቱና ቁጣው፣ መልካምነቱና መዓቱ፣ ፍቅሩና ቅናቱ፣ ሉአላዊነቱና የፈቃድ አምላክነቱ፣ ታላቅ ኃይሉና ራስን መግዛቱ ወዘተ ተስማምተው በአባትነቱ መሰረት ላይ ለሰው ጥቅም ሁልጊዜ በፊታችን የእርሱን ማንነት ለማሳየት ይገለጣሉ። ይህ አስደናቂ አምላክ እግዚአብሔር የሚመስለው ሌላ ማንም የሌለ ሲሆን በየዘመኑ ራሱን ለህዝቡ የበለጠ እየገለጠ ገና

ከመጀመሪያው በነበረው በዚያው ማንነቱ ሳይለወጥ ዛሬም አለ። የእርሱ የብቻው የሆነ ክብሩን ለማንም አሳልፎ የማይሰጥ ሲሆን ጽድቅንና ፍርድን ፍትህንም ጠብቆ ዛሬም ድረስ ተከብሮ በገናናው ዙፋኑ ሳይናወጥ የማይደረስበት ከፍታ ላይ አለ።

በዚህ ሁሉ ሁኔታ ለሰው ጥቅም በተለያየ መንገድ እርሱን እናውቅ ዘንድ በሰው እይታ "መልካም ወይም ክፉ" በሆነ መንገድ ተገልጦ ያየነው ታላቅነቱ ዋነኛ አላማው እርሱን እናውቅና ወደ እርሱ በትህትና እንቀርብ ዘንድ በዚህም ለዘላለም እርሱ ባለበት እኛ ደግሞ እንሆን ዘንድ ለአመፀኛው ዲያብሎስና ለሰራዊቱ በተዘጋጀ የእሳት ባህር በሁለተኛ ሞትም እንዳንሞት ለማዳን ነው።

ይህ ሁሉ የተገለጠ የእግዚአብሔር የተዘረጋ የምህረት እጅ፣ ከፍጥረቱ የሚመለስበትና ነገር ሁሉ ፍፃሜ የሚያገኝበት፣ ፃድቅ ፈራጅ የሆነው ይህ ነገር ሁሉ በፊቱ የተራቆተ የሆነለት ሁሉን አዋቂው እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ እንደ ስራው ይከፍለው ዘንድ ፍጥረት ሁሉ በፊቱ ለፍርድ የሚቀርብበት ቀን ደግሞ ከፊት አለ። በዚህም ፍትህ ነገር ሁሉ ፍፃሜን የሚያገኝበት፣ በቀልን እግዚአብሔር የሚበቀልበት፣ ፍርድን በጽድቅ የሚፈጽምበት፣ አመፃና ጥፋት ከምንጩ የሚቋረጥበት ሁኔታን ያመጣል። ከዚህም ወዲያ ገና ከመጀመሪያው እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ሊሰጥ ወድዶ የጀመረውን የዘላለም መንግስቱን በምድር ደግሞ ያደርግ ዘንድ አሮጌውን ሁሉ አሳልፎ አዲስ ሰማይና አዲስ ምድርን ያደርጋል።

በመጨረሻም የዚህ መጽሐፍ ዋና አላማ እግዚአብሔርን በማወቅ የበለጠ እናድግ ዘንድ በዚህም እውቀት የተገባን በእውነትና በመንፈስ የሆነ አምልኮና መስዋዕት ለእግዚአብሔር እናቀርብ ዘንድ ነው። ከዚህም በተጨማሪ በሰው ልማድ በተለያየ መልኩ በሐይማኖተኝነት ምልልስ እግዚአብሔርን ሳናውቅ በአምልኮ መልክ ውስጥ ያለን ብንገኝ አካሄዳችንን እናስተካክልና በእግዚአብሔር ፊት የምንቀርብበትን በአክብሮትና በፍርሃት በፍቅርም የሆነ ፀጋ እንድንይዝ በማሰብ የተፃፈ ነው።

እስከ አሁን ድረስ እስትንፋሱ በእርሱ ዘንድ ያለችው ሰው ከዚህ ለነገር ሁሉ ፍፃሜ የሚሰጥ የተፈራና የተከበረ አምላክ ጋር አካሄዱን ለማስተካከል የዘላለም መንግስቱም ወራሽና ተካፋይ ለመሆን እድል ያለው ሲሆን ከዚህ በተቃራኒው ግን በሰው

ልማድና በሐይማኖተኝነት ወግ እንደሚገባ እግዚአብሔርን ባለማወቅና እርሱ ሊከበር በሚገባበት ክብር እግዚአብሔርን በልኩ ሳያከብር ሊኖር የሚወድ እንደ ምርጫው ለማይረባ አእምሮና ለዘላለም ፍርድ ተላልፎ ሊሰጥ እንደሚችል ማስታወስ ያስፈልጋል።

ቸርና ለዘላለም የሚሆን ምህረት ባለቤት የሆነው እግዚአብሔር ግን አላማው ፍቅር ነውና ማንም እንዳይጠፋ ይልቁንስ የማዳኑ ተጠቃሚ ይሆን ዘንድ ወድዶ ስለ ተስፋ ቃሉ ለሚጠብቁት ሁሉ የዘገየ መስሎ ዛሬም አለ። ይህም ሁሉ ሰው ከጥፋቱ በንስሃ ይመለስና በህይወት እንዲኖር የታገሰው ትዕግስት ነው።

*ይህንን መጽሐፍ በልዩ ልዩ መንገድ አግኝታችሁ ለምታነቡ ለእናንተ ወንድምና እህቶቼ ያለኝ መልዕክት የመዳን ቀን ዛሬ ለዚያውን አሁን መሆኑን ነው።*

ከዚህ ወዲያ ባሉት ጥቂት ደቂቃና ሴኮንዶች እንኳን ሊሆን ያለውን ሁሉን አዋቂ ከሆነው ከዚህ ጌታ በቀር የሚያውቅ አንዳች የለምና አካሄዳችሁን በዚህ በተወደደ ቀን ሊሰማችሁ በመድሃኒትም ቀን ሊረዳችሁ ወድዶ ጆሮዎቹን ወደ ሃጢአተኛው ወዳዘነበለ ደግ ጌታ በትህትናና በንስሃ እንድትቀርቡ ዘላለማችሁንም ከዚህ ድንቅ ጌታ ጋር እንድታደርጉ አሳስባችኋለሁ።

በደህንነት መንገድ ውስጥ ላላችሁና እግዚአብሔርን ለምዳችሁት በሐይማኖት ቀንበር ውስጥ ገብታችሁ በተለያየ የአገልግሎት ዘርፍ ሁሉ ውስጥ እየተሳተፋችሁ እግዚአብሔርን በመስዋዕታችሁ ብዛት ደስ ለማሰኘት ከፉኛ ለምትጋጋጡ ለእናንተም እግዚአብሔር ከእኛ የሚፈልገው እኛን እንደሆነ ከመስዋዕታችን እንዲያውም ከሚቃጠለው መስዋዕታችን እንኳን ጭምር በላይ እርሱን ማወቃችንን እንደሚወድ ላስታወሳችሁና ዛሬ በቃሉና በመንፈሱ ራሳችሁን እንድታድሱ ፍፃሜያችሁም ያማረ እንዲሆን ላነቃችሁ እወዳለሁ።

በተለያየ ስያሜ ውስጥ ሆናችሁ ከወንድምነታችሁ በላይ የምትጠሩበት ስም ለሚያስጨንቃችሁ የምድሪቱ ተቋም በሰጠቻችሁ ተሸከርካሪ ወንበር ምክንያት በእግዚአብሔር ፊት ተመሳሳይ ልዩነትና ተቀባይነት ያላችሁ ለሚመስላችሁ ለእናንተ እግዚአብሔር በላያችሁ ላይ ከተሜነው ከህይወታችሁ ለየቅል የሆነ ስያሜያችሁ በላይ ልጅነታችሁን እንደሚፈልግ፣ በዙሪያችሁ እንዳለ ዳግመኛ የተወለደ አንድ ታናሽ ብላቴና

እኩል ልጆች ብቻ እንደሆናችሁ፣ እኛ ሁላችን ደግሞ በፍቅር ተጋጥመን አካል እንሆን ዘንድ ብልቶች ብቻ እንደሆንን ጌታ ኢየሱስም ሳያፍር እንደጠራን እርስ በእርሳችን ወንድሞች ተብለን መጠራራት የሚበቃን እንደሆንን እያስታወስኳችሁ እግዚአብሔርን ለማወቅ ደግሞም በተሰጣችሁ እድል ጳውሎስ እንዳለ ባወቃችሁት ልክ ሌሎችን ለማሳወቅ በቃልና በስራ እንድትበረቱ አሳስባችኋለሁ።

*ይህ ሁሉ ነገር ፍፃሜ የሚያገኝበት ፍጥረትም ሁሉ የሚጠቀለልበት ማንም ሊሰራና በንስሃ ወደ ዚህ ጌታ መድረስ የማይችልበት ጊዜ እጅግ ቅርብ ነው።*

*ዛሬ ግን ይህ የህይወት ቃል የደረሰን ሁላችን በታላቅ ፍርሃት እግዚአብሔርን እንደ እግዚአብሔርነቱ መጠን አክብረን በፊቱ በፀጋው ለመመላለስ ቀን ሳለ ራሳችንን እንድናስተካክል በፍቅሩም እንድኖር ገና እድል አለን።*

> “ወደ ኢየሱስ ደረት ቀርቦ ብዙ ያወቀውና የተማረው ዮሐንስ ስለ ወዳጁ በተረከው ትረካ መጨረሻ ላይ ይህ የሚተርከው ኢየሱስ ያደረገው ከተተረከው ሌላ ብዙ ነገር ደግሞ እንዳለ ነግሮን ያ ሁሉ በእያንዳንዱ ቢፃፍ ለተፃፉት መጽሐፍት ዓለም ራሱ ባልበቃቻቸውም ይመስለኛል ብሎ የእርሱን ከመተረክና ከመታወቅ ያለፈ ማንነት ገልጦልናል። እንዲሁ በዚህች ይልቁንስ ታናሽ የሆነች መጽሐፍ የተነገረውማ ምን ያክል ያነሰ ይሆን?”

## የማስተንተኛ ጥያቄዎች

1. በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የእግዚአብሔርን ባሕርያት ካጠናህ በኋላ ስለ እርሱ ያለህ ግንዛቤ እንዴት ተለወጠ?
2. ከእግዚአብሔር ባሕርያት መካከል ከእርሱ ጋር ያለህን ግንኙነት በጣም የነካው የትኛው ነው? ለምን?
3. የእግዚአብሔር ባሕርያት በፍጹም አንድነት መኖራቸው ባሕርዩን በበለጠ እንድትረዳ እንዴት ይረዳሃል?
4. እግዚአብሔርን ማወቅ እርሱን ከማምለክ በፊት እንደሚመጣ በመማርህ ምክንያት ስለ አምልኮ ያለህ እይታ እንዴት ተለወጠ?
5. አሁን የምታውቀውን የእግዚአብሔርን ባሕርይ በተሻለ ለማንጸባረቅ የትኞቹ የሕይወትህ ክፍሎች መለወጥ ያስፈልጋቸዋል?
6. እግዚአብሔርን እንደ አባት፣ ወዳጅና ጌታ ማወቅህ በየዕለቱ ከእርሱ ጋር ያለህን ግንኙነት እንዴት ሊያሳድገው ይገባል?
7. ሰዎች እግዚአብሔርን በእውነት ሳያውቁ ሐይማኖትን ሲከተሉ ሊያጋጥሚቸው የሚችሉ አደጋዎች ምንድን ናቸው?
8. ይህን መጽሐፍ ከጨረስክ በኋላ በእግዚአብሔር እውቀት ማደግህን እንዴት መቀጠል ትችላለህ?
9. የምታመልከውን አምላክ በጥቂት ነገሮች ብትገልጠው ምን ትላለህ?
10. ከተማርኸው ነገር ምላሽ የሆነ በእግዚአብሔር ፊት ልትገባ የምትፈልገው አንድ ውሳኔ ምንድን ነው?
11. ይህ መጽሐፍ አንተን በእምነትህ እንድታድግና እግዚአብሔርን በማወቅ እውነተኛ የሆነ አምልኮን እንድታመልክ ከረዳህ ሌሎች ወገኖች በተመሳሳይ መልኩ መጽሐፉን አግኝተው እንዲጠቀሙ ለስንት ሰው ጠቆምከውና አጋራሃው?

## አሰላስል

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ እግዚአብሔር ማን እንደሆነ በጥቂቱ በተገለጠልን መሠረት እግዚአብሔርን ለማወቅ የተጓዝነውን የእውቀት ጉዞ ተመልክተናል። እርሱን ዘላለማዊ ፈጣሪ፣ ሁሉን ቻይ አምላክ፣ ቅዱሱ አምላክ፣ ታማኙ አባት፣ አፍቃሪው እረኛ፣ ጻድቁ ፈራጅ፣ መሐሪው አዳኝና ከፍጥረቱ ጋር ኅብረት ለመመሥረት የሚፈልግ እውነተኛ ወዳጅ ሆኖ አይተናል።

ነገር ግን ከዚህ ሁሉ ከተጻፈው በኋላ አንድ እውነት ይቀራል፤ እግዚአብሔር ከእውቀታችን ልክ በላይ እጅግ ታላቅ ነው። የተማርናቸው እያንዳንዱ ባሕርያቱ ከማይመዘነው ታላቅነቱ አንጻር ትንሽ መገለጥ ብቻ ናቸው። ፍቅሩ ቅድስናውን አያሳንስም፤ ምሕረቱ ፍትሐዊነቱን አይሽርም፤ ትዕግሥቱ ጽድቁን አያዳክምም፤ ኃይሉም ሁልጊዜ ከበጎነቱ ጋር ፍጹም ተስማምቶ ይሠራል።

እግዚአብሔርን የማወቅ ዓላማ ስለ እርሱ መረጃ ማከማቸት ብቻ ሳይሆን በእርሱ መለወጥ ነው። ባሕርዩን በጥልቀት ባወቅን መጠን እርሱን እንድንታመን፣ እንድንወድ፣ እንድናመልክ፣ እንድንታዘዝና ምሳሌውን በሕይወታችን እንድናንጸባርቅ ይረዳናል።

ሁሉን የፈጠረው አምላክ በፍጥረቱ ሊታወቅ ይፈልጋል። በከፍተኛው ዙፋን ላይ የሚቀመጠው አምላክ በልጁ በኩል ወደ እኛ ቀርቧል። ክብር ሁሉ የሚገባው አምላክ ከእርሱ ጋር ወደ ኅብረት ጋብዞናል። ታላቅነቱን ብቻ አልገለጠልንም፤ ደግሞም ልጆቹ፣ ወዳጆቹና ርስቱ እንድንሆን መንገድ አዘጋጅቶልናል።

ስለዚህ እግዚአብሔርን የማወቅ ፍላጎታችን በመረጃ ብቻ አይቁም። እርሱን ማወቅ ወደ ጥልቅ አምልኮ፣ ወደ ታላቅ ትሕትና፣ ወደ እውነተኛ ንስሐ፣ ወደ ታማኝነትና በመታዘዝ ሕይወታችንን ሙሉ በሙሉ ለእርሱ የሰጠ ኑሮ ይምራን።

ከዚህ የላቀ ዕድል የለም፤ ይኸውም ብቸኛውን እውነተኛ አምላክ እግዚአብሔርን እንዲሁም መልኩን ሊገልጥበት ወድዶ የላከውን ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ማወቅ ነው።

## ጸሎት

በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፣

ራስህን ለእኛ ስለገለጥክልን እናመሰግንሃለን። ከእኛ የራቀና የማይታወቅ አምላክ ሳትሆን፣ በፍጥረትህ መታወቅ፣ መወደድና መመለክ የምትፈልግ አምላክ ስለሆንክ እናመሰግንሃለን።

ባሕርይህን በተማርንበት ጊዜ፣ ስለ ባሕርያትህ እውቀት ብቻ እንዳንይዝ ነገር ግን ማን እንደሆንክ እውነተኛውን መረዳት እንድናገኝ እርዳን። ቅድስናህን አይተን በአክብሮት እንድንመላለስ፣ ፍቅርህን አይተን ሌሎችን እንድንወድ፣ ምሕረትህን አይተን በትሕትና እንድንኖር፣ ታላቅነትህን አይተን የሕይወታችንን ክፍል ሁሉ ለአንተ እንድንሰጥ አግዘን።

ስለ አንተ ያገኘነው እውቀት አንተን አውቆ እንደጨረሰ ሰው እንዳያስታብየንና የውድቀታችን ምክንያት እንዳይሆንብን ጠብቀን። እውቀታችን አምልኮን፣ አምልኮአችን መታዘዝን፣ መታዘዛችንም ለስምህ ክብርን የሚያመጣ ሕይወትን ያፍራ።

ፊት ለፊት እስከምናይህ ድረስ በፊትህ በአገባብ ለመመላለስ እንችል ዘንድ በመንፈስህ ምራን።

በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አሜን።

---

## የአርምሞ ጥቅስ

*"እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆንህ አንተን የላክኸውንም ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘላለም ሕይወት ናት።"*

*— የዮሐንስ ወንጌል 17፥3 —*

# እግዚአብሔር

# ይባርካችሁ!

# ዋቢ መጻሕፍት


Administration, N. A. (n.d.). *Moon*. Retrieved from https://science.nasa.gov/moon/

Baxter, M. (2007). *The Coming Revolution: Because Status Quo Missions Won't Finish the Job.*

Brown, F., Driver, S. R., & Briggs, C. A. (1996). *The Brown-Driver-Briggs Hebrew and English Lexicon.* Hendrickson Publishers.

Carson, D. A. (1991). *The Gospel According to John* (The Pillar New Testament Commentary ed.). William B. Eerdmans Publishing Company.

Christianity, C. f. (2019). *Quick Facts About Global Christianity*. Retrieved from https://www.gordonconwell.edu/center-for-global-christianity/research/facts-global-christianity/

Craig, W. L. (2009). *The Blackwell Companion to Natural Theology: The Kalam Cosmological Argument.* (W. L. Craig, & J. P. Moreland, Eds.) Wiley-Blackwell.

Danker, F. W. (2000). *A Greek-English Lexicon of the New Testament and Other Early Christian Literature* (3rd ed.). University of Chicago Press.

Edwards, J. (2010). *Jonathan Edwards's "Sinners in the Hands of an Angry God": A Casebook.* (W. H. Kimnach, K. P. Minkema, & C. J. Maskell, Eds.) Yale University Press.

Hackett, C., Stonawski, M., Tong, Y., Kramer, S., Shi, A., & Fahmy, D. (2025, June 9). *How the Global Religious Landscape Changed From 2010 to 2020*. Retrieved from https://www.pewresearch.org/religion/2025/06/09/how-the-global-religious-landscape-changed-from-2010-to-2020/

Heiser, M. S. (2015). *The Unseen Realm: Recovering the Supernatural Worldview of the Bible.* Bellingham, WA: Lexham Press.

Koehler, L., Baumgartner, W., & Stamm, J. J. (1994-2000). *The Hebrew and Aramaic Lexicon of the Old Testament.* Brill.

Merriam-Webster. (n.d.). *Definations of words*. Retrieved June 2026, from Merriam-Webster.com.

OpenStax. (2016). *University Physics Volume 3* (Vol. 3). OpenStax, Rice University.

Organization, W. H. (2020, March 11). *WHO Director-General's opening remarks at the media briefing on COVID-19 – 11 March 2020*. Retrieved from https://www.who.int/director-general/speeches/detail/who-director-general-s-opening-remarks-at-the-media-briefing-on-covid-19---11-march-2020

Research, L. (2026, February 10). *Fewer than 1 in 3 churchgoers read the Bible daily*. Retrieved from https://research.lifeway.com/2026/02/10/fewer-than-1-in-3-churchgoers-read-the-bible-daily/

Society, A. B. (2025). *State of the Bible in the Church*. Retrieved from https://www.americanbible.org/sotb-church-2025/

Tasker, R. V. (1951). *The Biblical Doctrine of the Wrath of God.* The Tyndale Press.

United Nations, D. o. (2024). *World Population Prospects 2024: Summary of Results.* Retrieved from https://desapublications.un.org/publications/world-population-prospects-2024-summary-results

Van De Mieroop, M. (2016). *The Ancient Near East, c. 3000–330 BC* (3rd ed.). Wiley-Blackwell.

ማኅበር, የ. መ. (1954). *መጽሐፍ ቅዱስ - የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት.* ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት.

ግዛው, ባ. ዘ. (1994). *ዘርጋው የአማርኛ መዝገበ ቃላት* (የመጀመሪያ እትም ed.). አዲስ አበባ.

እውነተኛ አምልኮ የሚጀምረው
የሚያመልኩትን በትክክል ከማወቅ ነው

# የምናመልከው እግዚአብሔር ማን ነው?

በጥያቄዎች፣ ግራ መጋባቶች እና በተለዋዋጭ እምነቶች በተሞላች ዓለም ውስጥ፣ "የምናመልከው እግዚአብሔር ማን ነው?" የተሰኘው ይህ መጽሐፍ ስለ እግዚአብሔር ባህርይ፣ ማንነት እና አምላክነቱ የማይለወጡ እውነቶችን እንድታውቅ ይጋብዝሃል።

ይህ መጽሐፍ የእግዚአብሔርን ባህሪያት ለማወቅ ብቻ የተጻፈ አይደለም፤ እርሱን ራሱን በግል ለማወቅ የሚመራ ነው። ወደ ፊቱ ይበልጥ ያቀርብሃል፣ እምነትህን ያጸናል፣ እናም የአምልኮ ሕይወትህን ይለውጣል።

## በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የምታገኙት

- የእግዚአብሔርን ግርማና ታላቅነት በጥልቀት
- ለእኛ ያለውን ፍቅር፣ ጸጋና ታማኝነት
- የእግዚአብሔር ባሕሪያት ሕይወታችንንና አምልኳችንን እንዴት እንደሚቀርጹ
- ከፍጥረታቱ ፈጣሪ እግዚአብሔር ጋር ጥልቅ የሆነ ወዳጅነት

## ስለ ጸሐፊው



*ሀብታሙ ሉልሰገድ ለእግዚአብሔር ቃል ጥልቅ ፍቅር ያለው አማኝ፣ መምህር እና የወንጌል እውነት ሰባኪ ነው። የልቡ ምኞት ሰዎች እግዚአብሔርን በግል እንዲያውቁ፣ ወደ እውነተኛ አምልኮና ዓላማ ያለው ሕይወት በሚመራ ከእርሱ ጋር ያለ ኅብረት እንዲያድጉ መርዳት ነው።*

*በዚህ መጽሐፍ አማካኝነት፣ ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርቡ፣ እምነታችሁን የሚያጸኑ፣ እና በመንፈሳዊ ጉዞአችሁ የሚያበረታቷችሁ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነቶችንና ተግባራዊ መንፈሳዊ ግንዛቤዎችን ታገኛላችሁ። ከዚህም በተጨማሪ ከዚህ በፊት በእግዚአብሔር ጸጋ ጽፎ ለአንባቢያን በነጻ ያበረከተው ሁለንተናዊ የአካል ተሃድሶን የሚናፍቀው "እንጸገና በሕይወት መኖር /ሪቫይቫል ለኢትዮጵያ/" የሚለው መፅሐፉ ይህንኑ የሚያግዝ ተጨማሪ አበርክቶ ነው።*

*ይህ መጽሐፍ ወደ እርሱ ይበልጥ እንዲያቀርባችሁና፣ እውነተኛ በሆነ አምልኮ የተሞላ ሕይወትን እንድትኖሩ እንዲያግዛችሁ እመኛለሁ።*

*ክብር ሁሉ ለእግዚአብሔር ይሁን!*